



ከንቱ ድካም



ጣፋጭ ጠጮች

ከደቡብ ሲኮዮቲያ ምድር

ታገል ሰይፉ

መቼም በፍቅር መሀል የዱላ ነገር ኩሶሳ ቸር ማሉበ ይከብዳል። ዱላ የጠበኞች ቋንቋ ነው። በአንባታምኝ ዘንድ ግን ዱላ የፍቅር መግለጫ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል።

የአንባታ ብሄረሰብ ህዝብ በሶሜን ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በደቡብ በኩል ደሞ ከሸኩቾ ዞን ተሠራበተው ይኖራሉ። በምዕራብ ምስራቅ በኩልም የሃዲያና የሶሚን አሞ ዞኖች ያዋስኑዋቸዋል። የሚያዋስናቸው ነገር ካለ በብዙምቻችን ዘንድ የሚታየው ዱላን አንደጠበ መቀስቀሻ አድርጎ የመቁጠር ልማድ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድ የከንባታ ወጣት ልጅቱን ምን ያክል እንደሚጠ
ለመናገር ምላሱን አያስረዝማም። ይልቁንስ ከምላሱም ሀ
ከቁመቱ በላይ የሆነ ረጅም ብትር ይዞ ከቢትዋ በመግባት
ስሜቱን ይገልጣል።

ከዚያ በፊት ግን ልጅቱን የሚመርጡለት ወላጆቹ ናቸው
እዝርስ ከመረጡ አርሱ ፍቅር አይገደውም። ወላጆቹም ታዲ
ስለልጅትዋ ውበት የሚነግሩት በታላት ጋጋታ አይደለም
ክንክታዎች ከመናገር ይልቅ በማሳየት ያምናሉ። እናም ራሱ
ሂዶ እንዲታዘብ አድራሻዋን ይሰጣሩታል።

እንግዲህ የፍቅር መገለጫ ዘንጉን ይዞ ክቢትዋ ከተዋ
የሚለው ከዚያ በኋላ ነው። ኡድቲት እንደተመለስ ወላጆቹ
ምን ስትሰራ እንዳገኛት ይጠይቁታል።

ምክንያቱም ለፍቅር ጥያቄው ምላሽ የምትሰጠው እርሷ
አይደለችም። ልክ እርሱ ሲደርስ በመስራት ላይ ያለችው
ነገር እንጂ።

ለምሳሌ ልጅቱ ቤት ስትጠርግ ከደረሰ እጅዋ ላይ ያለ
መጥረጊያ ሳይሆን እንቢታ ነው። እናም እንደ ቁሻሻ ዝ
አድርጋው በእቢታዋ ሳትጠርገው በፊት ዘንጉን አወ
ይወጣል። እርሱ ሲደርስ ውሃ ልትቀዳ ባዶ እንስራ ተሸ
ከወጣችም ተመሳሳይ ትርጓሜ አለው። ቡና ተጠጥቶ ሲ
ስታጥብ ከደረሰም ጉዳዩ አብሮ እንዳከተመለት በቂ ምክ
ይሆናል።

የሚያጠግብ ትዳር ከሆነ ግን ቡና ስታፈላ እንደሚደ
ያምናሉ። አስበለዚያ ውሃ ቀድታ ስትመለስ ያኛትዋ። መገ
ላይ ካልተገናኙም አብረት ውስጥ ወተት ስታለ
መተያየታቸው አይቀርም። እነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎ
ወደክንባትኛ ሲተረጎሙ «እኛም ወደናል ይሁን» ማለ
ናቸው።

ከዚያ በኋላ ያን ረጅም ዱላውን አሳይቶ ወደቤቱ ይመለ
እንዲህ ነደረገ ፍቅሩን በዱልኛ ነግሯታል ማለት ነው።

አንደ ከንባታዎች ዱላ የጠበ መግለጫ መሆኑ ቀርቶ የፍቅር
ፈንቴ የሚሆንበት ጊዜ መቼ ይሆን?

* * *

እንደምታውቁት የሩቅ ምስራቅ ሰዎች መጠሪያ ጉንጭ
አይሞላም። «ቾ»፣ «ሆ»፣ «ኪ» ሲባሉ ስምታችኋል። እንደዚህ
እየተባሉ እስከትም አያቶቻቸው ቢጠሩ እንኳ የኛን
ገበረማርያም ርዘመት አይደርሱበትም።

ይሄ ያስገረማቸው የመሐል ሀገር ፌዘኞችም የሩቅ
ምስራቆች እንደዚህ ያለ አጫጭር ስሞች እንዴት
እንደሚያወጡላቸው ሲተነትኑ፣ ለምሳሌ እናትየው ምጥ ላይ
ሆና አንድ ትሪ ሲወድት ከተሰማ የልጅም ስም «ኪ» ወይም
«ዚው» አለያም «ኪም» ይሆናል። የተሰማው ድምፅ ከጥሬና
ከካልቾ ጋር የሚቀራረብ ከሆነ ደግሞ «ቾ» ወይም «ቻ»
አለያም «ቾ» ተብሎ ይጠራል ይሳሉ።

ይሄ የአዲሳበቢዎች ቀልድ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር
የለውም። አሁን የምናጫውታችሁ ግን እውነተኛውን የኤርቦሬ
ብሂረሰብ ስም አወጣጥ ይሆናል።

ብሂረሰቡ በሀገራችን ደቡብ ክልል በሄመርና ቦና ወረዳ
ውስጥ የሚገኝ ነው። ኤርቦሬች ለየት ያለ ስም አወጣጥ
አላቸው። የመሃል አገሩ ሰው «ስምን መልአክ ያወጣዋል»
ነው የሚለው። ኤርቦሬሞች ደግሞ «ስምን የበሬ ቆዳም
ያወጣዋል» የሚሉ ይመስላሉ።

ህፃን ሲወለድ ኤርቦሬዎች በሬ አርደው ይቀበሉታል።
ይህም ከብሂረሰቡ ታላላት በዓሉች አንዱ አንዱ ይቆጠራል።
በተለይም የህፃኑ ስም የሚወጣበት ቀን በጣም ከባድ በዓል
ይከሄዳል። በዓሉም በብሂረሰቡ ዘንድ «ቱስማ» እና «አቡሻል»
በመባል ይታወቃል።

የህፃኑ ስም የሚወጣው አትቡቱ በሚቆረጥበት አሰት
ሰሆን፣ የእትቡቱ ቁራጭ የሚቀመጠውም ሰልደቱ በታረደው
በሬ ቆዳ ላይ ነው። እናም የዚያ ቆዳ ቀለም የልጅን ስያሜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደወስሞል።

የብዛረስዞን ሎም አውሣኖ ወደ አማርኛ ተርጉሞ ለማቅረብ ያህል ለምሳሌ፣ ቆዳው ነጭ ከሆነ ሀሳኑ ነጩ ተብሎ ይጠራል። ቡራቡራም ከሆነ የልጹ ሎም ቡራ ሆኖ መቅረቱ ነው።

* * *

ከዘዘን ይልቅ የሰርግ ደስታ ሞት ሞት የሚሸታቸው አሉ። ሰርግ ላይ በጣም አስቸጋሪው ነገር የድግሱ ጣጣ ብቻ አይደለም። ቡሰይ በከተማው አካባቢ የመሸሪቷ ቪሉ ሻይሽ የማይመለሰው ራዕምታት እየፈጠረ ነው። ለአንድ ቀን የሚ ኪራይ አስከ አምስት ሺህ ብር እንደሚከፈልም ይነገራል።

ከለ ቪሉም ኣሁን ደመቅሽ አበባዬ ብሎ መዝ የሚያሳፍር ይመስላል። በቡሚዎች ሰርግ ግን አሁን ደመ ብሎ ነገር የለም። የቡሚዋ ሙሽራት በሰርጉዋ እስት ከለሳ የተሻለ ለብሳ ስለማትታይ ነው።

ቡሚዎች ደቡብ ኦሞ ዞን ተፈልገው አይታጡም። በ ከደቡብ ኢትዮጵያ ብዛረስዞች አንዱ ነው። የህዘባቸው ቁ ወደ ሃያ ሶስት ሺህ ይጠጋል። ቋንቋቸውም ኖንጋቶ የሚባል ነው።

ታዲያ እነህ ሰዎች በደገሱት ሰርግ ላይ ሙሽራ ከታዳሚው መለየት በጣም ይከብዳችሁዋል። ምክንያቱ በአዲስ ልብስ ደምቃ አለመታየትዋ ነው። በዚህ ታሪክ አንኳ ባለፉት ዓመታት በኖንጋቶምኖ ኢያንትራሪች ልትቀዳ ወደ ወንዝ ስትወርድ የሰበሰችውን አሮጌ አትቀይርም። እናም በቡሚዎች ሰርግ ላይ ኣሁን ደመ አበባዬ ብሎ ማጨብጨብ አስቸጋሪ ነው።

በቡሚዎች ባህል ሙሽራት የምትደምቀው ከባልዋ ስትገባ ነው። ያን ጊዜ ባለቤትዋ ቤት ያፈራውን ፍያል እንዴት ያለ ግልድም ያበጅላታል። ይህን ጊዜ ግን ደመቅሽ የቡሚ ልጅ ማለት ይቻል ይሆናል።

* * *

ሰው በሞተ ዕለት ድንኳን መጣል አስከሬኑን በውሃ ማጠብ፣ እና በጨርቅ መገነዝ ከዚያም አያለቀሱ ወደ መቃብሩ መውሰድና ወደጉን ዘለግ ተደርጎ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ መቅበር የተለመደ ነው። የሟች ቤተሰቦችም ለወራት ያክል ወራቸውን በመላጨት ሀዘናቸውን ይገልጣሉ።

ቦዴዎች በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልላዊ መስተዳድር ዙሪያም በደቡብ አሞ ዞን ሰሜማንጉ ከሚባል ወረዳ ውስጥ ይኖራሉ። ብዱኛ የሚባል ቋንቋ አላቸው። ቡበዛታቸውም ወደ ሶስት ሺህ እንደሚጠጉ ይነገራል። በቦዴዎች ሰፊር ትልቅ ሰው ከሞተ ወዲያውኑ የሚጣለው ድንኳን ሳይሆን በሬ ነው።

በገራችን ላይ በሌላው አካባቢ ሬሳው አፊር ሳይነካ አህል መቅመስ ነውር እንደሆነ ለምታችሁ ይሆናል። ይሄ ነውር ራሱ በቦዴዎች ዘንድ እንደነውር የሚቆጠር ነው።

እነሱ ሰው በሞተ ጊዜ ሬሳውን አስቀምጠው ለሶስት ቀን ያክል ታላችና ታናሽ ማወራረዳቸው አይቀርም። አሁንም አስከሬን አስቀምጦ መበላት ነውር የመሰለው ካለ «ሬሬው ከመታረዱ በፊት ሰውየውን ቢቀብሩት ምን ችግራቸው?» ይል ይሆናል።

ይሄ የዋህነት ነው። በሬው ካልታረደ በቀር ማቹ አይተዘርም። ምክንያቱም አስከሬኑ የሚታጠበው በውሃ ሳይሆን በበሬው ደም ስለሆነ ።

ከዚያም አራፊ ጨርቅ ፍለጋ ጊዜ አያባክኑም። በዚያው የበሬ ቆዳ ጥፍር አርገው ይከፍኑታል። (የከፈን ቆዳው ራሳ ሳጥኑም ጭምር እንደሆነ ልብ ይሏል።)

ሲገነዙት ለለ ተገላቢጦሽ ነገር ታያላችሁ፤ አስከሬኑን ከወገቡ ሰበር አድርገው የተቀመጠ ያስመስሉታል። መደኋላው ጋር ያስሯቸዋል። እንዲህ አንገቱን ደፍቶ የተቀመጠውን አስከሬንም በቆዳ ከጭንቅ ስልቻ ከሚመስሉት በኋላ ወደመቃብሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉድጓድ ይወስዱታል።

ጉድጓዱም እንደተለመደው ዝርግና ሞላላ አይደለም፣ እንዳልተለመደው ክብና ጠባብ እንጂ።

እስከሬኑ ተጣጥፎ ወደዚያ ጉድጓድ ሲወሰዱት በሃሳቡ ጭፈራ ታጅቦ ነው። ሁሉም ሰሚቹ ያዘነውን ያክል መጨፈሩ አይቀርም። ምናልባትም «የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዳ የሚባለው ቀብር ላይ ይሆናል። በሴላ አጣባል አያንጻንሷን ኩቲያቸውን እንደ ዕንባ መቃብሩ ላይ አያንጠባጠቡ ሀዘናቸውን ይገልጣሉ ማለት ነው።

የበዴጆች ተገላቢጦሽ በዚህ አያበቃም። ለምሳሌ በሌላው ባህል ከቀብር መልስ የሚች ቤተሰቦች ጉፋፌያቸውን ተሳጭተው ሀዘን ይቀመጣሉ። ይሂ ለበዴጆች ቅብጠት ነው በነሱ ቀሪለስ የሚች ቤተሰቦች ወጉራቸውን አይለጩም እንዲያውም መሪር ሀዘናቸውን ለመግለፅ ለወራት ያህ ወጉራቸውን አጉፍረው ይቆያሉ።

አናም አንድ ቦዴ ወጉን ማሳደግ ሲጀምር መደንገ ይባል። አንዳች ነገን ጥሞታልና።

* * *

ከሠመር ቀሪለስ ወጮች እንዱን እናጫውታችሁ፣

በዚህ ቀሪለስ ውስጥ ኖ ከመወለዳቸው «ሚንጊ» የሚባ ፀያፍ ስም የሚወጣላቸው ህፃናት አሉ። ሚንጊ የህመር ቃል ሲሆን በአማርኛ ገፅ የሚለው ቃል ይመስላል።

እነኘህ ህፃናት ለአቅመ ሚንጊነት የሚደርሱት ጥር ማብቀል ሲጀምሩ ነው። የህፃኑ የላይኛው ድድ ቀድሞ በጥር ከተሸፈነ ለሀገርም ሆነ ለቤተሰብ የሚበጅ ሰው አይደለም ብለው ያምናሉ። እንዲያውም አባቱን እስከመግደል የሚደርስ ጭካኔ አብሮ እንደሚበቅልበት ያመለክታል ባዙች ናቸው።

የድድ አምላክ ከዚህ ጉድ ሰውሮት ጥርሱን ከታች ማብቀል የጀመረ ህፃን ሊለም ፈተና ይጠብቀዋል። እነኚያኑ ውተት ጥርሶቹን ማራገፍ ያለበት ከታችኛው ድድ ይምሮ ነው።

የላይኛው ጥርስ ቀድሞ ከተነቀለ ሌላ ጥርስ ከማብቀሉ በፊት የሚተክለለት «ሚንጊ» የሚባለው ሲዖሚ ይሆናል። ህፃኑ አገር ጥሉት መንገድ ላይ ሲወድቅ የላይኛው ጥርሱ ከተነቀለም ከማህበረሰቡም ሰመነቀል በቂ ምክንያት ይሆነዋል።

ስለዚህም ህፃን ሲወድት የመጀመሪያው ጥያቄ «የላይኛው ጥርሱ ተርፏል ወይ?» የሚል ነው። የላይኛው ጥርሱ ከወሰቀ ወደታች መውረዱ አይቀርም። ሚንጊ ተብሎ ወደተጠላው ህበረተሰብ...

ህመሮች ደህን ባህል ያመጡት ከብቶቻቸውን አስተውለው እንደሆነ ይነገራል። ሳምና በሬን አይተው፤ ፍየልን በግንም ታዝበው፤ የፈጠሩት ባህል ነው። እነኚህ እንስሶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ «ቅዱሳን» ስለሚቆጠሩ በድንበ ይመገቡዋቸዋል። ቅዱስ ያሰኛቸው ደሞ የሲጋቸው ጣፋጭነት ብቻ አይደለም። ሁሉም ጥርስ ማብቀል የሚጀምሩት ከታችኛው ድድ ስለሆነ እንጂ...


አርከሰ ተብለው ከመበል ተራ የወጡት እንስሶች ጥርስ ደሞ ከላይኛው ድድ መብቀል ይጀምራል። እነኚህ እንስሶች እንደ አሀያና ፈረስ ያሉት ናቸው። ህመሮች ጅብም ጥርስ የሚያበቅለው ከላይኛው ድዱ ጀምሮ እንደሆነ ይናገራሉ።

ስለዚህ ከላይኛው ድድ ማብቀል የጀመረውን ህፃን የጅብ ያክል ይፈሩታል። በዚች ምድርም ከሱ የበለጠ «ሚንጊ» እንደሌለ አርግጠኞች ናቸው።

ከዚህ የተነሳ የወላጅና የአካባቢ ፍቅር ለጥቶ የሚያድገው ህፃን የኋላ ኋላ እውነተኛው «ሚንጊ» መሆኑ ይቀራል?

* በማፋሚ ወጮች ስር የሚገኙት ትረካዎች በታገል ሰይፉ የተዘጋጁ ቢሆኑም የትረካዎቹ ምንጭ አማኑኤል አብርሃም መሆኑን እንገልፃለን - አርታኢው)

t.me/OLDBOOKSPDF



ድሰ ወይስ ሸንፈት



ከበደ ሚካኤል

የገንዘብ ፍቅር

እጅግ አርጎ በጣም ገንዘብ የወደደ
ሁሉን በያይነቱ ዕቃ አየነገደ
ሱቅ ከፍቶ የሚኖር አንድ ሰው ነበረ፤
አንድ ቀን አንድ ሀብታም በጣም የከበረ
ከሱቱ ገባና ጧቱን በማለዳ
አንስቶ አገላብጦ አንድ የነብር ቆዳ
ዋጋው ጠይቆ ካወቀ በኋላ፤
በፍጥነት ተነሳ ዋጋውን ሊያጥላላ
አይነ ግቡ ሳለ መልኩ የተስማማ
የተዋበ ሆኖ ለምን እንዲህ ገማ?
እጣህ ነበረ በጠየቅኸው ዋጋ፤
ግን ሽታው መጥፎ ነው ሰውም አያስጠጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

በደኅና አልተሰራም አለና መለሰው፤
ነጋዴውም አለ ውስጡን አለስልሰው
ደክመው የሰሩት ነው በደኅና እየፋቁ
በዚህ በከተማ ዞረው በየሱቁ
ቢሹም አያገኙ ይህን የመሰለ
ይመኑኝ ጥሩ ነው ይመልከቱ አያለ
ቢናገር ሀብታሙ ቢያምር ምን ይጠቅማል
ጠረኑ መጥፎ ነው ሲቀርቡት ይገማል
አለና ሳይገዛ ቢሄድበት ትቶ
ሳይሸጥ በመቅረቱ በጣም ተቆጭቶ
የመለሰው መስሎት በቶሎ አስረድቶ
ምስኪኑ ነጋዴ ቸኩሎ እንዲህ አለ፤
ለአርስዎ ብቤ ነው ለሌላም አይደለ
ይህን መሳይ ቆዳ በዚህ አገር የለም
እዩት እንዴት ያምራል ይህ የጠጉር ቀለም
ግማቱም ከኔ ነው ከቆዳው አይደለም።



ቁምጩ ትምባው

የዘመነ ደርግ አስቂኝ ገጠመኝ

ደረጀ ደስታ

በአንድ አጋጣሚ ስለ ቁምጩ አምባው ያልሰማ ሰው መቼም አይገኝም። እኒህ የጐሻም ክፍለ ሀገር የአንድ ወረዳ ገዥ የነበሩት ስመ ገናና ሰው አሁን በቀይሽብር ወንጀል ተከሰው በአስር ላይ ይገኛሉ።

እነሆ... ስለ ቁምጩ ጥቂት እናወጋለን።

ቁምጩ አስተዳዳሪ ሳሉ የአንበሳ ስዕል አስርተው ከግርጌው «ጐሻም አንበሳ ነው» የሚል ጽሑፍ አስፈሩበት። ሕዝቡም በዚህ ተደስቶ ሲኖር ሳለ ገበሬው ግብር በጊዜ አላስገባ ብሎ አስቸገራቸው። ይሽኔ ቁምጩ ገበሬውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ስብስበው፤ «አሁን ይህን አንበሳ ላም ላድርገው?» በማለት ግዳጁን እንዲወጣ አደረጉት ይባላል። አምን፤ በቆምጩ ስም የሚነገሩ በርካታ ቀልዶች አሉ። ያለማጋነን ቆምጩ የዘመነ ደርግ አለቃ ገብረሃና ነበሩ። አርሳቸው ግን ይህን ክብር በመቀዳጀታቸው ደስተኛ አይደሉም።

«ብቻ የትም ቦታ በምሄድበት ጊዜ ሰዎች ይጠቋቆሙብኛል። በብዛት ዞረው ያዩኛል። እኔ ሰዎቹን አላውቃቸውም። አሁን በዛ ሰሞን እንኳ (1985) አዲስ አበባ ሄጄ ነበር። ቅድም አንዳልኩህ ልጆን ጠይቄ ነው የመጣሁትኝ። እዚያ አንድ ለቅሶ ነበር። እዚያው ነው ደርሼ የመጣሁትኝ። እና ታዲያ ያው እዚያ፣ ያው እዚያ... ይሉኛል። እንዴ? እኔ አልሰረቅኩ፣ አልቀጠፍኩ። እኔ ከሰው የተለየ ስራ አልሰራሁ... እና ይሄ ሁሉ ኸኒ ሰው ያወጣልኝ ስም ነው» ይላሉ።

ስለ ቆምጩ ሊነሳ አያሌ ቀልዶች ትዝ ይሉናል። እኒያ በቆምጩ አምባው ስም የሚነገሩትን ቀልዶችና የግለሰቡን ህይወት የተመለከተ ታሪክ ምልልስ አዋህደ እንዲህ አቅርቤዋለሁ፤

«ትክክለኛ ስምዎ ማን ይባላል?»

«ቆምጩ አምባው ይልማ። እንደዚያ ነው የምባለው።»

«የሕይወት ታሪክዎን ባጭሩ ቢነግሩኝ»

«በ1933 ገዛምን ወረዳ ውስጥ ማያ አንገታም ቀበሌ ነው የተወለድኩት። ከዚያ ለትምህርት እንደደረስኩኝ አናትና አባቴ ቤተ አየሱስ የተባለ ትምህርት ቤት አስገቡኝ። ከዚያም ዳዊትና ድጓ ጸመድጓ ወጥቼ ደብረኤልያስ ቅኔ ትምህርት ቤት ገባሁኝ። እዚያ እንደገባሁ በሽታ ገባ። አባቴ ከዚያ አውጥቶ አገሬ መልሶ ወሰደኝ። አያይ በሽታው ይበርዳል መልሰህ እዚያው ጨምረኝ ብለው አባቴ አምቢ አለኝ። ከዚያ እዚያው ደብረ ኤልያስ ትምህርት ቤት

ገባሁና የስድስተኛ ክፍል ትምህርቴን አጠናቀቅሁ። ከዚያም በነበረው ባህል መሰረት በልጅነቴ ጋብቻ መሰረትኩ። አሁን የአስር ልጆች አባት ነኝ። ከዚያ የአናት ያባቴን ከብቶች ገንዲ አሚባል በሽታ ገብቶ ስለፈጃቸው በ1958 መህኒ ፖሊስ በወታደርነት ተቀጠርኩኝ። የአስር አለቅነት ማዕረጌን እንደያዝኩ በ1971 የወረዳ አስተዳዳሪ ሆኜ ተሾምኩ።»

«እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ ነው የተማሩት?»

«በወረዳ አስተዳዳሪነት ከቢሁኝ ደብረወርቅ እንደተዛወርኩኝ ከሰባተኛ - ዘጠነኛ ክፍል ትምህርቴን ፈጽሜ በተልእኮ (በኮርስፖንዳንስ) የ12ኛ ክፍል ትምህርቴን አጠናቅቄያለሁ።»

«የት የት ቦታዎች ሰርተዋል?»

«ቢሁን፣ እነሴ፣ እናርጅ እናውጋ፣ አቸፈር፣ ማቻከል ወረዳዎች በወረዳ አስተዳዳሪነት ሰርቻለሁ።»

«የሰሯቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?»

«እንግዲህ እኔ በተዘዋወርኩበት ወረዳ ሁሉ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ማገበራዊ መገልገያዎች፣ መንገዶች፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ያልሰራሁበትና ያልመሰረትኩበት የለም። በተለያዩ ወረዳዎች ከ20 በላይ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች፣ ከ10 ያላነሱ ክሊኒኮች አንድ የጤና ጣቢያ ሰርቻለሁ። የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንም ሰርቻለሁ። በዚህ መስክ ለምሳሌ በሞጣ ዙሪያ አንድ ከፍተኛ የስፖርት ሜዳ አዘጋጅቼ በ1977 የኢትዮጵያ ትቅደም ዋንጫ ውድድር እንዲደረግበት አድርጌያለሁ። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ብሄራዊ ዘመቻዎች ማለትም በመሰረተ ትምህርት ዘመቻ፣ በተለያዩ የጤና ነክ ዘመቻዎች፣ በክትባትና በመሳሰሉት ሕዝቡን በማንቀሳቀስ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሳይቀር ሽልማትና እርዳታ አግኝተናል። በአንዘህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘመቻዎችም ሆነ ግብር በማሰባሰብ ሂደት የተሰተነከለኝ አልነበረም። አንደኛ ነው ሁልጊዜ የምመጣው።»

«እነዚህን ሁሉ ስራዎች ሲያከናውኑ ጎበዶተሰቡን ለማግባባት የሚጠቀሙበት ዘዴ ምን ነበር?»

«እንግዲህ አንደኛ የበለጠ ውጤት ለማግኘት አርሶ አደሩን አለመለያየት ነው። ሁለተኛ ደሞ በየጊዜው ማስተማር መቀስቀስ ነው። አብዛኛውን በማያመርትበት ቀን ስራ በማይሰራበት ቀን ሁሉም ኃላፊ ተቡትጥ አሱ ዘንድ እንዲሂድ ስለምፈልግ ሁላችንም እንሂዳለን። በዚያ በአረፍት ቀን ስምን ቢተክርስቲያን አይሆንም እንዲውም እዚያ ጥሩ ነው። ሰው አዳራሽ ውስጥ ተኮናሰ ንግግሩ የሚጥም አይመስለውም። ደሞ ሰው ሙቡም ከሆነ ባንድ በኩል ለቅሶው አያለ ባንድ በኩል ስልትምህርት ብናስተምረው ገለጻ ብናደርግለት ይሰማል። ሌላው ያው ሽልማት ማበረታቻ መሳይ መስጠት ነው።»

«በሽልማት ማበረታታት ሲሉ እንደኡት ነው? ምን ምንድነው የሚሽልሙት?»

«ለምሳሌ እኔ አንድ ዝግጅት ወይም ስብሰባ እንደዚህ አዘጋጅቼ ከሆነ ወንበሮች አዘጋጅና ደነማ የሆነውን ሊቀመንበር መጨረሻው ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ነው የማደርገው። በጣም ንብዝ ክብ የሆነውን ደሞ ግንባር ላይ ነው አማስቀምጠው። ግብር አሚያስገባ፣ በጸረ ስደስት ትባት ጥሩ ውጤት ያሳየውን «ና ያንተ ወንበር ይህ ነው» ብዬ ከፊት አስቀምጠዋለሁ። እንደሱ ሰመቀመጫ ሲል ሌላው የግድ ይሰራል።

ሌላ ደሞ ለምሳሌ ግብር በደንብ አድርገ ለማስገባት እኔ የማስር የማስገደድ ስልት አልጠቀምም። ይህ ምንድነው ጠብመንጃ አሱን አስመጣና ሶስቱን አንድ ሳይ በማዋቀር አውላላ ሜዳ ላይ አቆመዋለሁ። እና ቆሎ

ሕዝቡን አስተባብሮ ግብር አሚያስገባ ካለ ይህንኑ መሳሪያ ያሟል ብዬ አስንግራለሁ። ታዲያ ሁሉም ባንድ ጊዜ አስገቱቱ ያንን መሳሪያ ለማግኘት ገበሬውን ለምናም በሆን አባዘሀ ቶሎ አምጣ እኔ ልሽለምበት አያለ በማሰተባበር ያንን የዘመኑን ግብር ወዲያው ያስገባል። እና መሳሪያ አንጨት ነው ምን ችግር አለ። ሌላ ነገር የምርምር መሳሪያ አንደዚህ መስጠት ነው አንጂ አማያቅተን ሰው አሚያጠፋ ነገር መስጠት ምን ይቸግረናል። ያንን አያነሳን አንሽልመዋለን።»

«ሬዲዮና ጋዜጣም ይጠቀማሉ የሚባሰውስ?»

«አንዱ አሱማ ዋናው ነው አንጂ። የኔ ዋናው ማበረታቻ አሱ ነው። በቀጥታ የተሰራውን ስራ ወስጀ በሬዲዮና በጋዜጣ አስነገርለታለሁ። ያንን ጋዜጣ ደሞ ባህር-ዳር ወይም ደብረማርቆስ በመውጣት ቶሎ አምጥቼ አየው አንዲህ ያለ ስራ ብትሰሩ ለማችሁ በጋዜጣ ወጣ ብዬ ያንን ጋዜጣ ወስጀ ቢሮአቸው ላይ አለጥፍላቸዋለሁ። ያኒ የአገሌ ሰው በሬዲዮ ተጠርቶ በጋዜጣ ወጥቶ የኔ ተበሰ ሊቀር ነው ወይ? አያለ አሚቆጭ ይበዛል። አንዲያውም የኛ ሰምን አይነገርም ባዶ አየበዛ ስለመጣ የሰራኸውን አይቼ ትክክለኛ ሆኖ ከገኘሁት ይተላሰፍልሀል አምላቸው ብዙ ነበሩ።»

«የአርስምስ ስም ብዙ ጊዜ በሬዲዮ ይተላለፋል?»

«አሥነ አንዲያውም ማስታወቂያ ሚኒስትር የቆምጩ አማው ነው። ሁልጊዜ አሚነገረው የሱ ነው። አሱ ገዝቷቸዋል። ጋዜጠኞች ሲሄዱ ይጋብዛቸዋል። ቢራ ያጠጣቸዋል። መስተንግዶው ከባድ ነው አያሱ ይሰድቧቸዋል። ይህን ግን አሚያስወሩብኝ አንደኔ መስራት የተሳናቸው ሁሉ ናቸው። ታዲያ እነሱም የትአለ ስራ? የሰራችሁትን አሳዩንና እናስተላልፍላችሁ ሲሏቸው ምንም

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰሩት የላቸውም::»

«ሬዲዮ ሲሉ ትዝ አለኝ ይሄስ ምንድነው አንድ ቀን አርስም አውቶቡስ ውስጥ ሆነው ወደክፍለ ሀገር በመጓዝ ላይ ሳሉ አንዳጋጣሚ የዜና ሰዓት ነበርና ዜና ሲወረ የአርስም ስም በመጠራቱ ሹፌሩን አቁም አቁም በማለት ወደ መንገደኞቹ በመዞር ስሙ ስሙ ቆምጩ አምባው ማለት እኔ ነኝ በማለት...?»

«ይህ ሀሰት ነው:: ጨርሶ ካንደበቴ አልወጣም:: ለማኝኸውም ጥያቄው መቅረቡ ደስ ነው ያለኝ:: ይኛ ሊመራብኝ የቻለው እንዴት መሰለህ? ገና የወረዳ አስተዳደ ሆኘ ቢሆን እንደሄድኩኝ አንድም ወፍጮ በወረዳው አልነበረም:: እና ደካሞች፣ አርጉሃች፣ ሴቶች ድንጋይ ከድንጋይ እያፋጩ ፍዳ ያዩ ነበር:: ስለዚህ ሕዝቡን አስተባበርኩና 15 ሺ ብር አንዲያዋጣ አድርጌ ወፍጮ ቤት አስተከልኩ:: እና ያ ወፍጮ ተገዝቶ ስራ ሲጀምር ብሞጣ አውራጃ የሚገኘው ወፍጮ ስራ ጀመረ' ተብሎ በራዲዮ ተነገረ:: እና በስራና በልማት የቀደምኳቸው ወረ አስተዳዳሪዎች ያንን አስወሩብኝ::»

«ምን ብለው ነው ያስወሩብዎት?»

«አንደው ዝም ብለው ስራ ሳይሰሩ እየተንጠራሩ ወደ ጋላ ይቀሩና እኔ በልማት የቀደምኳቸው ምን ይለ «ወፍጮው ስራ ጀመረ» ተብሎ በራዲዮ ሲነገር ቆምጩ አባይ ላይ ነበረ:: ከአዲስ አበባ ወደ ጉጅም ይመጣ ነበ እና እኔ ነኝ ቆምጩ አምባው እወቁኝ ብሎ በአውቶቡስ ላይ ተናገረ ብለው ይህንን አስወሩ:: ያስወሩ:: አሚያሸኝ ተግባርና ስራ ነው:: ሌላ ማንም ቢያወራ አይሰጠብኝም:: አይጸፍብኝም:: የህዝቡን ማህበራዊ ችግር ግን ከሰኞ ጭላንጭል አውቀት ጋር ከዚያ ሕዝብ ጋር በማገናኘ ችግሩን ልፈታለት ሞክሬያለሁ:: እንዴ፤ ወፍጮውን

እንዲያ ሳስተክለው ሕዝቡ ዋታለ ያወፍጮ አሚፈጨው ሰውዮ' እያለ ወፍጮ አይቶ ስለሚያውቅ 'ለመሆኑ ምን ይመስላል ምን አይነት ሰው ነው' አስክ ማለት ሁሉ ደርሶ ነበር እኮ

«ደሞ ሌሎችም አሉ:: በአርስም ስም የሚነገሩ ቀልዶች እንደዚህ:: ስለአነሱ አሚያውቁት ነገር አለ?»

«አንግዲህ ከዚህ ቀደምም ቢሆን ይህ ጥያቄ ቀርቦልኝ እንደው አንድም ቀን ቀልድ አንዳልቀለድኩ ተናግሬያለሁ:: እኔ ስራ እንጂ ቀልድ አልወድም:: ሰቀልድ ጊዜ አልነበረኝም:: እንደውም በየጊዜው አሁን ድረስ አዚህ እየመጡ አሚያበሽግሩኝ አሉ:: ከተለያዩ መጽሐፍቶች እንደዚህ መሳን አያሉ ይጠይቁኛል:: አንዳንዶቹም እንደው ባንተ ስም መጽሐፍ ልንጽፍ ፈልገን ነበረ:: ወዲያው ም ታሪክ ነው አያሉ ይጠይቁኛል:: እኔ ግን ወይዳ እኔ የናንተ መጽሐፍት ማሻሻጫና ማዳመቂያ አይደለሁ-ም ደሞም ያላልኩትን ብትሉ አክሳለሁ አያልኩ ብዙውችን መልሺያለሁ::»

«ታዲያ እነዚህ ሁሉ ቀልዶች ከምን የመነጩ ይመስልሃታል?»

«አንግዲህ በምሳሌ ልንገርህ:: ለምሳሌ አንደዛ እንዲህ ብሎው አስወሩብኝ:: የክፍለ ሀገሩ ጋርቲ ኮሚቴ ተሰብስቦ ከተጥታ ወደ ሶሻሊዝም መግባት ሲቻል የብሔራዊ ዲሞክ ራሲ አብዮት ፓርግራም ሰምን አስፈለገን በማለት ቆምጨን ጠየቀው:: ታዲያ ቆምጨም «እንዴ! ታዲያ ለምን ሶሻሊዝምን በቀጥታ አታደርጉትም? ባሰስልጣኖቹ አናንተ እያደ ላችሁ? ቆምጨ ከለከላችሁ እንዴ ታዲያ?» ብሎ መለሰላቸው በማለት አስወሩብኝ:: እንግዲህ ይህ ምንን ያመለክታል? እኔ ደካማ አላዋቂ መሆኔን በማሳየት ምንም አደነት የልማት ስራ መስራት እንደማልችል

t.me/OLDBOOKSPDF

ስማሰያት ከማስብ የመነጨ ነው።»

«ለምሳሌ ቀድሞ በሞጣ አካባቢ አንድ ትልቅ የስፖርት ሜዳ ማሰራትዎን ገልጸ ውልኛል። እና ያንን ሜዳ መርቀው ሲከፍቱ አንግዲህ ይህን ሜዳ የምንጠቀመው በቋጠባና በአቅድ ነው። በዚ መሰረት በጋ በጋ ትጫወቱበታላችሁ፤ ክረምት ክረምት ደሞ ይታረሳል ብለዋል እሚባልም ነገር አለ። እና..»

«ደሞ እንዲህ አሉ? ይበሉ ምናለ አኔ ግን ካንደበቱ አለመውጣቱን ነው አማውቀው። ደሞ ይሽኛውን አልሰማሁትም። እኔ የሰማሁት ሌላ ነበር።»

«ምንድነበር የሰሙትን?»

«አዎ አንደዚ ቆምው የስፖርት ሜዳ ሲሰራ... አንግዲህ ያኔ ሜዳው ሲሰራ ይሄ ሩሎ መንገድ ይጠቀጥቅ ነበር... እና እኔም ቁታ ለብሼ ያንን መንገድ አጠቀጥቅ ነበር። እና ምናሉ ካሳዩ አራጋው ያኔ ወደሞጣ ይሄዱ ነበርና እግረ መንገዳቸውን ቆምው አንዱ ሳናግረው ብለው ና ብለው ቢጠሩት። ያንን የስፖርት ሜዳ እየሰራ ነአያይ እኔ አልመጣም አብሮት የማያድርጥ አንቅስቃሴ ነው። እና እኔም በአብዮታዊ ሰራ አንቅስቃሴ ላይ ስለሆንኩ አድርጌ አልመጣም ብሏቸው እምቢ ብሎ ቀረ... እያሉ አስወሩብኝ። እና ይሄ ምንን ያሳያል? ማአከላዊነት አሰመጠበቅ ብልግናን የሚያሳይ ነው። ግን አውነቱ አሳቸውም አልመጡም። እኔም አንዲያ አላልኩም።»

«ፖለቲካ ትምህርት ቤት ገብተው ነበር አዚያም ቀልደ ቢጤ...»

«አዎ ገብቼያለሁ። አዎ ደሞም ከዚያም አንድ ቀልደ ነበረች። ያኔ ኢምፔሪያሊዝም እሚባል ነገር ነበረና አገሩ ተነስቶ ክፍል ውስጥ ሲያወራ ብዙ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነጻ በመውጣታቸው ኢምፔሪያሊዝም እርታኑን ሱርቷል

ብሎ አለ። እና ቆምጩም ብድግ ብሎ «ቁጭ በል አንተ ሙቭታም፤ ኢምፔሪያሊዝም እርታኑን ሲሆን ሽንት ቤት ነው ወይ ቆሞ ያየኸው? የትስባትክ ያየኸውን ነው እምታወራው?» ብሎ ተናገረ አያሉ አውርተውብኛል። እኔ ግን አላልኩም።»

«ግን የፖለቲካ ትምህርት ቤት ህይወትም እንዴት ነበር? ይኸው አሁን አንኳ ከቤተክርስቲያን ነው የመጡት። ሃይማኖትና ማሌን እንዴት ያስኬዱት ነበር?»

«አዎ እኔ መንፈሳዊነቱ መቼም ቢሆን አይለየኝም። በዚህ የተነሳም ፖለቲካ ትምህርት ቤት ውስጥ እየጸለየ ጸዊት ተያዘበት ብለው አስወርተዋል። እርግጥ ግን አግዜርን ልቤ መቸም አልካደውም። ደሞም አዚያ ስገባ ማርክሲዝም ሌኒንዝም ያራምዳል ብለው ሳይሆን በትምህርት ቢታገዝ ሕብረተሰቡን አስተባብሮ ልማትን ሊያፋጥን ይችላል ብለው ነው።

በተረፈ በፖለቲካ ትምህርት ቤት ውስጥ ትዝ የሚለኝ አንድ ጊዜ ተከስሼ ነበር። ትምህርት ቤቱ አካባቢ የሆነ ቡድን የልማት አስተባባሪ አድርገውኝ ነበር። እና እኔ ልማትና ሰራ የሰመድኩ ስለሆነ ካድሬምቹ ሲዘራቸውን ወርቃቸውን አድርገው ሲንቡራደዱ እኔ ቁታ ለብሼ አሰራ ነበር። እና ውሃ አጠልቀለሁ ድንጋይ አፈነቅሳለሁ ምን አላለሁ። እና ባንደዜ ሰስት ሜዳ ቆፍሬ ጨረስኩ። ይህንን ያዩ ካድሬምች ኦኦ ብለው ከሰሱኝ። ገበሬውን አምጥታችሁብን በቁፋሮ ፌዩን ብለው አመለከቱብኝ። አንሰራምም ብለው አመጹ። እና እኔም አልሰራም ካሉ ይቅር እንጂ የምን ክስ የምን ጣጣ ነው ብዬ ተከራከርኩ። ኋላ ከሰራችሁ ስሩ ተብለው በአነሱ ተፈረደ። አንግዲህ የማስታውሰው ይሄን ይሄን ነው።»

«ከቀድሞ ባለስልጣናት ጋርስ የነበርዎት ግንኙነት

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ይመስል ነበር። ከፕሬዚዳንት መንግስቱ ጋርስ እንደዚህ ተገናኝተው ያውቃሉ?»

«ከፕሬዚዳንቱ ጋር አሚያገናኘን ነገር የለም። እኔ አግኝቻቸውም አላውቅ። ግን እኔ ያልተናገርኩትን ነገር እየተናገሩ ብዙ ነገር ተወርቷል። እና እኔም አሲጋ ነበር። ግን የደረብሰኝ ነገር የለም። ለምሳሌ እንደዚ ምናሉ ባንድ ወቅት ሊቢያና ቻድ ተጣልተው ነበር። እና ያኔ ደሞ የወጣ፡ የአፍሪካ ሊቀመንበር ፕሬዚዳንት መንግስቱ ነበሩ። እና ካሳዬ አራጋው ቆምጩን ጠርተውት 'ቆምጩ አንተ እኮ ንጉዝ ነህ፣ እና በአንተ አስተያየት የሲቢያና የቻድ ግጭት ምን ይመስልሃል?' ብለው ጠየቁት እና ቆምጩም ዓንዴ እኔን ምን ትጠይቁኛላችሁ ሊቀመንበር መንግስቱ ያልቻሉትን ሂጀ ላስታርቅላችሁ ነው ወይ...' አለ ብለው አስወሩብኝ። እና በሌላ በኩል ደሞ እኔ ከባለስልጣናት ጋር ግንኙነት የለኝም። አንዲያውም ያን ያህል ስደክም ለአውራጃ አስተዳዳሪነት ስሾም ስሜን በፍሉድ አጥፍተው ሌላ ሰው ሾመውበታል።»

«እና እንደው ምንም ቀልድ ወጥቶኝም አያውቅ ነው የሚሉት?»

«እኔ በጭራሽ። እርግጥ ምንድነው እኔ ያልኩትን በሌላ አያዙሩ አሚያወሩት ነገር አለ። እኔን ሰማጣላት። ለምሳሌ አንደዚ ከደብረሊባኖስ ድርሻ ግብርኤል አሚባል አገር ከአንድ ዋና አስተዳዳሪ ጋር አየሄድን ነበር። በመኪና ነበር እምንሄድ። አሳቸው የአህል ኮታ ሲገመግሙ ነው የመጡት። እኔ ደሞ የመሰረተ ትምህርት የምሰጠው ወረቀት ልሰጥ ነው። እና ስንሄድ ከፊታችን ሶስት አህያ አየጋለቡ ይሄዳሉ። ይሽህዜ አስተዳዳሪው ወደኔ ዞር አሉና 'ቆምጩ እነዚህ አህዮች ምንድናቸው? ክትድም ይምጡ ከፊት ከፊታችን ይጋልባሉ?' ብለው ጠየቁኝ። እና አኔም

ኃያውልቃት እንግዲህ አርሰም በደንብ አድርገው የሚገመግሙ ከሆነ እኔ ሀገር አንኳን ሰው ይሽሙ አህያውም ነቅቷል። አናም አቀባበል መሆኑ ነው ብዬ አልኳቸው። እና ይቺን ወስደው አስተዳዳሪውን 'አህያ ስለሞክ አቀባበል አሚያደርግልህ አህያ ነው' አሰው ብለው ዞር አደረጓት።»

«ሌባ አይወዱም ይባላል? ለመሆኑ እንዴት እንደት አድርገው ነበር የሚቀጡት?»

«እም ሌባ አልወድም። አንደዚ ቢሁን ወረዳ እያሸሁ ሌባ በጣም በዛብኝ። ይሰርቃሉ የተባሉትን ሁሉ ጠራሁና ጠመንጃ እያሽከምኩ ሾምኳቸው። በሱ እንግዲህ ጠበቁ አልኩና ሁለት ሁለት ካርታ ጥይት ሰጠኋቸው። አናንተ ታጠፋላችሁ ተብሎ በሚስጥር ተነግሮኛልና አስቲ አሁን አሚያጠፋውን አናያለን። አናንተ ግን ጠበቁ ብዬ አደራ አልኳቸው። ከዚያ ከበት አይሰረቅ፤ ምን አይሰረቅ፤ ሴባ ቀጥ አለ። ታዲያልህ ቆየት ብሎ አንደዚ አንደው ልቤ ጠረጠረና ጋበዝኳቸውና አረቂ እየጠጣን 'አይ' የናንተ ነገር አሁንም ትሰርቃላችሁ አሉ 'ምነ አየለመንኳችሁ? መሳሪያ መግፈፉ ማለሩ አይረባም ያጣላል። ስለዚህ ኧረባችሁ?' አልኳቸው። በዚህ ጊዜ አንዱ ሞቅ ብሎት ነበረና 'አያይ አያ ቆምጩ እኛኮ አንሰርቅም። ብንሰርቅም ከአርሰም አገር አይደለም ከዳሞት ነው' አሰና አረፈው። እና እኔም አለመተዋቸውን አወቅኩ። እና እንዲያ እያደረግሁ ነው ሌባ የምይዘው። ከማባረር ከማሰር እንዲህ ቀርቦ እያጫወቱ እያጫወቱ መያዝና መክሮ መመለሱን እመርጣለሁ።»

«ብዙ ጊዜ እንዲህ ገጠር ውስጥ ተዘዋውረው ሲሰሩ መቸም አስተዳዳሪ ነዎትና የቢሮዎን ስራ ምን ጊዜ ነው የሚሰሩት? ደሞ ስብሰባም ወደላይም ወደታችም ሲኖርዎት

t.me/OLDBOOKSPDF

ይችላል?»

«እኔ ብዙ ጊዜ የቢሮ ስራ አልወድም። 10 ቀን ቢሮ ካለሁ 20 ቀን እዳሪ ነኝ። ስብሰባ እንካ ስጠራ አልመጣም እያልኩ ብዙ ጊዜ እቃወማለሁ። ዛሬ ተሰብስበን ነገ ስብሰባ ይሉኛል። እኔ ስንት የገጠር ስራ አለብኝ። ከተቻለኝ አስፈቅዳለሁ ካልሆነም እምትወያዩበትን አጀንዳ በስልክ ንገሩኝ እያልኩ እጠይቃለሁ። እና ያኔ «ስለ አህል ኮታ ስለትምህርት ስለ ምናምን ድክመት ነው...» ይሉኛል። አያይ እኔጋ ደህና ነው፣ የደክመውን ጠይቁ። ከደከመው ጋር ተሰብሰቡ እያልኩ ወደ ስራዬ እሄዳለሁ።»

* * *

በቆምጩ አምባው ስም የሚነገሩ ቅልዶች

የመፈክር ጋጋታ የበዛበት ሰሞን ነው - ኢሰፓ ከመምጣቱ በፊት በኢሰፓኮ ጊዜ። እና የጊዜው መፈክርም «የኢሰፓኮ ተልእኮ ይሳካል!» የሚል ነበር። ታዲያ ቆምጩ አንድ ቀን ንግግር አድርገው ካበቁ በኋላ ተገቢውን መፈክር በማስማት ሕዝቡ እንዲበተን ያደርጋሉ። ጀሌ በማግስቱ ትዝ ሲላቸው ከመፈክሮች ሁሉ «የኢሰፓኮ ተልእኮ ይሳካል» የምትለዋን ዘንግተዋታል። ስለዚህ ቶሎ ብለው ሕዝብ እንዲሰበሰብ ያደርጉና በሉ ግራ አጀቻሁን ወደላይ ይላሉ። ሕዝቡ ግራ እጁን ይሰቅላል። ታዲያ በመሃል ያቺ መዘንጊ መፈክር አሁንም ትጠፋለች። በያሰቧት ቢያት ቢለሯት ትዝ አልላቸው ትላለች። ይሽኔ ቆመው ተናደዱና እንዲህ የሚል መፈክር አሰሙ ይባላል

«ሰሞኑን ከመጣው ጋር ወደፊት!»

* * *

ቆምጩ የካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ቤት ገብተው ለ6 ወራት የፖለቲካ ትምህርት ቀስመው ነበር። ታዲያ

ጠዲያቸው አውቀት ሊንቀሳቀስ ከርመው ሳለ ሌሎች ከድራጮች ለተጨማሪ የፖለቲካ ትምህርት ወደ ጀርመን መሄዳቸውን ይሰማሉ። አንዲያ ከሆነ ታዲያ አሳቸው እናርጅ እናውጋ ውስጥ የሚቀመጡበት ምክንያት ምንድ ነው? በእስቸኳይ ማመልከቻ ማስገባት ነበረባቸው። ማመልከቻውን ታዲያ አንዲህ ሲሉ ነው የጻፉት ይባላል።

ጓድ ካሳዬ አራጋው የ... ተጠሪ። ከዚህ በፊት የካቲት 66 ጉበቼ ለ6 ወራት የፖለቲካ ትምህርት መቅሰሜ ይታወቃል። ስለሆነም በዚህ ባገኘሁት ትምህርት ጎበረተስቡን ሳስተምር ቆይቼ ትምህርቱ አሁን ያለቀበኝ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪና ብዙ ሊቆይ የሚችል ትምህርት ከወደ ጀርመን እገኝ ዘንድ ወደዚያው አንዲልኩኝ አጠይቃለሁ።

* * *

ጋዜጠኛው፡- ጓድ ቆምጩ አምባው ኢምፒሪያሊዝምን እንዴት ያዩታል?

ቆምጩ፡- እናንተ እንዳሻችሁ አዩት እኔ ግን የገሪጥ ነው እማየው (አሉ ይባላል)

* * *

አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን ቆምጩን ሊጎበኛቸው ብቅ ብሉ ኖሮ «እሺ ጓድ ቆምጩ አምባው አጠቃላይ እንስቃሴም ምን ይመስላል?» በማለት ይጠይቃቸዋል።

ቆምጩም ሲመልሱ «...አንግዲህ በዚህ በአፍ ወረዳ አብዮታዊ እንቅስቃሴው ጣቂል። በኢኮኖሚው በኩል ገበሬው ቆላውን ሰንጐ ይዞታል። በፖለቲካው በኩል ደሞ እኔና ካድሬው ሕዝቡን ሰንገን ይዘነዋል» አሉ ይባላል።

* * *

ካድሬው ትምህርት ሊያስተማረ ነበር። አብዮታዊት እናት አገራችንን የውጩ መንግስታት እየረዷት ነው። ለምሳሌ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከወዳጅ አገሮች ሶቪዬት ኅብረት፣ ኩሪያ፣ ኩባ፣ ቻይና እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። በስዕላዊው ረገድም አንግሊዝ፣ ፈረንሳያና ጣሊያን ይገኙበታል። ደሞም ራሊ አማረካ ረድኦሉች... እያለ ሲያስተምር፤

ቆምጨ፡- የሊሎቹን እንኳ ሰምቻለሁ። ግን ይቺ «ራሊ» የምትባለዋን አገር ግን አላውቃትም። ካድራ ትቀጥሩሰ ልበል?፡- ብለው አፋጠጡት ይባላል።

* * *

ቆምጨ ሕዝቡን ለስራ የሚጠሩባትና አዋጅ የሚያስነገሩባት አንዲት ጥሩንባ ነበረቻቸው ይባላል። ታዲያ አንድ ቀን ይቺ ጥሩንባ ትጠፋለች። ብትፈለግ አልተገኘችም። በዚህን ጊዜ ቆምጨ ሕዝቡን ሰብስበው «የዚህንኛ ሕዝብ ሆዩ ስማ ሰሞኑን አንድ የጎንድ ቆምጨ እምባው እብሎታዊ ጥሩንባ ጠፍቶለች። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ያለችበትን ቦታ እሚያውቅ ካለ እንዲጠቁም እብሎታዊ ጥሪ ተላልፎለታል። ካልሆነ ግን ጎድ ቆምጨ አምባው ለላ አብሎታዊ ጥሩንባ የሚገዙ ሠራተኞቹን አስታውቃለሁ።

* * *

ካድራው ሲያወራ በየንግግሩ ጣልቃ ሲኒን እንዳለው ማርክስ እንዳለው ኢንግልስ እንዳለው... ይላል። ቆምጨም ይቺን ልብ ብለው ኖሯል። እናም በጣም ተገረሙና ወይ ጉድ እኛ እቶ እንዳለው እንደኤት እግዚር የባረካቸው ሰው ቢሆኑ ነው እንዲህ ዓይነት ልጆች የወለዱ። የአባትነ ስም ካስጠሩ ላይቀር እንዲያ ነው ኢያሱ ወደስራቸው ሄዱ ይባላል።

* * *

ቆምጨ መፈክር ይወዳሉ ይባላል። ሆኖም ግን የሳቸው ለየት ያለ ነው። አቀራረባቸው።

«ሁሉም ጠላ ለመጠጣት ገበሰ ያምርት!»

«መሰረተ ትምህርት የማይማር ቡዳ ነው!»

«እንዳንዴም ከጓድ ቆምጨ አምባው አመራር ጋር ወደፊት!» ብለዋል ይባላል።

* * *

የመፈክር ነገር ከተነሳ ጓድ ካሳዬ አራጋው አንድ ጊዜ የቆምጨን አገር ሲጎበኙ ሰንበተው ይመለሳሉ። ቆምጨም ታዲያ አለቃቸውን መሸኘት ነበረባቸው። ደሞ አሸኛኘቱ በመፈክር ቢታጅብ ይመረጣል። አናማ ሕዝቡን እንዲህ እንዲል አዘዙ ይባላል።

«አናቱ ኪዳነምሕረት ጓድ ካሳዬ አራጋውን በሰላም ታግባ»

ሕዝቡም «ታግባ» እያለ ተቀበለ።

* * *

ቆምጨ ኪስ ሚዳ አሰርተው ጥሮ ሚዳው እንዳለቀ የሰፈሩን ሴት ሁሉ አበት ይዞ እንዲወጣ አዘው አስለቀለቱት። ከዚያም ኪስ ጨዋታ ተካሂዶ ሚዳው ሲመረቅ ባደረጉት ንግግር፡-


«እንግዲህ ዛሬ ለ24 ተጫዋቾች አንድ ኪስ አትርበን እንድትጫወቱ ተደርጓል። አቅማችን ሲፈቅድ ደግሞ እያንዳንዳችሁ አንድ ኪስ ይዛችሁ እንድትጫወቱ ይደረጋል» አሉ ይባላል።


* * *

ቆምጨን እንዱ አለቃቸው «መሃይም ነህ» የሚል ዘለፋ የሰፈረበት ደብዳቤ ይጽፍላቸዋል። አርሳቸውም ለዚህ ዘለፋ ባስቸኳይ የጻፉት የአጅ ጽሁፍ ደብዳቤ፡-

«መሀይምስ አንተ ነህ። በአጅ መጻፍ አትዩህ በታይፕ የምትጽፍ» አሉት ይባላል።


t.me/OLDBOOKSPDF







ግልቢያ በዘዴ



ሁለተኛው ስብ-ስጨዲ

ተስፋዬ ገብረአብ

ወሬው መዛመት የጀመረው ሚያዝያ 2ቀን፣ 1991 እኩለ ቀን አካባቢ ቢሆንም አንኳ ከዓረብ ሃገራት ስለመጣው ታላቅ ቱጃር 'ቀደም ሲልም እናውቅ ነበር' የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አልታጡም።

ብዙዎች ግራ በመጋባት የሰውየውን ማንነት ጠየቁ፣ «ለመሆኑ ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ ማነው?» እናውቃለን የሚሉ መልስ ሰጡ፣

«ሙባረክ ቢጠሩት የማይሰማ ቢሊዮኔር ነው። 34 የነዳጅ ጉድጓዶች አሉት። እነዚህ የነዳጅ ጉድጓዶች 150

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓመት ቢቀዱ እንኳ የሚያልቁ አይደሉም። ይህ ሰው ሳዑዲ ዓረቢያ ላይ የጦር መሳሪያ ፋብሪካዎችም አሉት። ስለ ሀብቱ ተናግሮ ማብቃት ከቶ አይቻልም። ባንድ ቃል የጠገበ ቱጃር ነው ማለቱ ይቀላል።»

እናውቃለን የሚሉት እንዲህ ሲሉም አከሉበት፣

«ሙባረክ ማለት ለኢትዮጵያ ከሰማይ የወረደ ሲሳይ ነው። ከሙባረክ ጋር ሲነፃፀር የሚድሮክ ባለጉብረት የሆነው መህመድ አል - አሙዲ አዚህ ግባ አይባልም። ልዩነታቸው የትየለሌ ነው። እንዲያውም ምናለፋችሁ፣ እንጦጦን ከራስ ዳሽን ተራራ ጋር ማወዳደር ማለት ነው።»

የቅዳሜ ተሊያት የአዲሳባ ወሬ ስለ ሙባረክ ብቻ ነበር። በተለይም «ቸር» መሆኑ እንደጉድ ተወሳ። ከሀምሳ ሺህ ብር በታች ቢሞት ቼክ አይቆርጥም። ይህ ደግሞ የተጋነነ ወሬ አለመሆኑን አብነት አየጠቀሱ የሚያወጉ ነበሩ። በተለይም የኒውዮርክ ከፌ ባለቤት ለሆነችው ለቀፀላወርቅ ጌታሁን ለአንድ ሰኒ ቡና አንድ ሺህ ዶላር እንደከፈላት አያሌ ሰምች ያውቃሉ። ቀፀላወርቅ አሜሪካ አስራስድስት ዓመታት የቆየች ጠና ያለች ሴት ናት። ገንዘብ እንዴት እንደሚገኝ በቂ ዕውቀት አላት። ይህን ጹብ ዕዳ ግን እንዲያው በደፈናው የአምላክ ምርቃት ከማለት በቀር ከቶ ስም ልታገኝለት ተቸገረች። ቱጃሩ ሙባረክ ቦሌ መንገድ ላይ ታምሩ ለተባለ ትራፊክ 75ሺ ብር፣ ካዛንቺስ አካባቢ ያሰምገም ምክንያት ለአንድ ሊስትሮ 50 ሺ ብር፣ አስመራ መንገድ የሰርግ ሰአስርዓታቸውን በማክበር ላይ ለነበሩ ሙሽሮች 120 ሺ ብር፣ ለአንድ የከሰሩ ባለሆቴል 200ሺ ብር፣ ግዮን ሆቴል ቡና ላቀረበለት አስተናጋጅ 100ሺ ብር ቼክ እንደቆረጠ እናውቃለን የሚሉ አያደነቁ ተናገሩ። የሙባረክን ዝና መናገር የጀመሩት ሰምች ታሪኩንና

ቸርነቱን ሲያወሩ እንደማንቀጥቀጥ ያደርጋቸው ነበር። ቁና ቁና ሲተነፍሱም ተስተውለዋል።

ወሬው በፍጥነት ከቦታ ቦታ ይሰራጭ ያዘ። ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ በገባበት ሆቴል ሁሉ በአጸቢዎቹ አማካይነት ለተዋወቃቸው ሰምች ቼክ መበጠሱ ተደጋግሞ ተነገረ። አጸቢዎቹ ደግሞ ተራ ፓራ ኮማንዶዎች አንዳይመስሏችሁ። በዘመነ-ደርግ ዴዴሳ በተባለው የማሰልጠኛ ጣቢያ በኩሪያኖች የሰለጠኑ ወጣት መስመራዊ መኮንኖች ናቸው። ሙባረክ የሚጠቀምበት መኪና ሽንጣሙ ሲሙዚን ሲሆን፣ ሲሙዚኑ ደግሞ በሁለት ቶዮታ ላንድ ክሩዘሮች ከፊትና ከኋላ ይታጀባል። ምን ይህ ብቻ! ሙባረክ የግል አይሮፕላን ጭምር አለው። ምናለፋችሁ ጠቅለል ባለ መልኩ 'ሙባረክ ከአሜሪከብዜር ቁጥሮ ሀያልና ሀብታም ቱጃር ነው' በሳል ማጋነን አይሆንም።

ወሬዎች ወሬ ይወልዱ ጀመር...

አንደሚነገረው ከሆነ 'አላሙዲን ደጅ ጠንተው ሳይሳካላቸው የቀሩ አርቲስቶች በሙሉ በአስቸኳይ እኔ ዘንድ አንዲቀርቡ ብሏል' ነው የሚባለው። ይህም ለኢትዮጵያ ስነጥበብ ታላቅ ትንሳኤ መሆኑ ተነገረ። አሜሪአብዜር ኢትዮጵያን አንዳልዘነጋት ጭምር ተወሳ።

ወሬው አዲስ አበባን ሲያምሳት ነበር የሰነበተው...

በዚሁ ዕለት፣ ሂልተን ሆቴል በመጠጥ ባንኩኒ ዙሪያ የተሰባሰቡ አራት ኢንቨስተሮች ስለዚሁ ታላቅ ሰው ነበር የሚነጋገሩት። የኢንቨስተሮቹ ስሜት ሁለት አይነት ነበር። ስጋትና ጉጉት። ስጋቱ የመነጨው «ከአላሙዲ የተረፈውን የስራ መስክ ሁሉ ይህ ቱጃር ጠቅልሎ ከያዘው ባዶ ሜዳ ላይ እንቀራለን?» ከሚል የሚነሳ ሲሆን፣ የተደሰቱት ወገኖች ደግሞ «ምናልባት ሙባረክ ከተባለው ከዚህ ቱጃር ጋር የመቀራረብ እድል

t.me/OLDBOOKSPDF

አናገኝ ይሆናል» ከሚል የተስፋ ሀልም የተመዘዘ ነበር። ግራም ነፈሰ ቀኝ የሙባረክን ስም እያነሱ በመንጫጫት ያወጉ ያዙ፤

ከአራቱ አንዱ ግን ጥርጣሬ ገብቶት ነበር፤ ደጋግሞ አንዲህ ሲል ነበር የሚጠይቀው፤

«ርግጠኛ ናችሁ!? ሙባረክ የሚባል ቢሊዮነር አዲስ ገብቶአል?»

«አብደሀል!?» ሲል ቡዋረቀበት ወሬውን ያመጣው ልጅአግር ኢንቨስተር። «እኔኮ ራሴ ተዋውቄዋለሁ ነው የምልህ። ምን አስዋሸኝ? ለምንስ አዋሽለሁ? ሙባረክ ተዋውቆኝ ሲያበቃ ሌላ ቀን እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ ብሎኛል። ከአማካሪዎቹ አንዱ ጓደኛዬ ነው። አብሮ አደጌ፤ ካምፓስ ጭምር አብረን ነበርን። የፈጠራ ተረት አይደለም ኮ የማወራላችሁ፤ ሙባረክን እኔራሴ ተዋውቄዋለሁ።»

«እድሜው ምን ያህል ይሆናል?»

«ገና ልጅ ነው። ከአርባ አምስት አያልፍም።»

«ነጭ ነው?»

«ስታየው ሀበሻ ነው የሚመስልህ። በርግጥ ቀላ ያለ ነው። ጠጉሩ ግን ቡና ዓይነት ሆኖ ሱጫ ነው። እንዳብዛኞቹ የዓረብ ሀብታሞች ደግሞ ወዛምና የተመቸው ነው። ከጠጉሩና ወዛም ከመሆኑ በቀር ግን የሀበሻ መልክ ነው ያለው።»

«ዜግነቱስ?»

«ዜግነቱንኳ እንጃ! የሳዑዲ ዓረቢያ ቪጋ መሰለኝ። በእናቱ ግን ኢትዮጵያዊ ነው። የሚደንቀው ደሞ ልክ እንደ ሼክ አላሙዲ እርሱም ደሴ ነው የተወለደው። ተአምር ነው መቸም። ደሴ ታሪክ እየሰራች ነው። ገና ሶስተኛውን አላሙዲ ጉትታ ታመጣለች»

ይህን ብሎ በሳቅ አውካካ። ሽበት ጣል ጣል ያደረገው

የአስመጪና ላኪነትን ንግድ የሚሰራው ሰው፤ ድንገት ጣልቃ ገብቶ፤

«ከንግዲህ አል - አሙዲ ያልቅለታል!» ሲል አፌዘ።

ሌላው ግን ተቃወመው፤

«ምን ይሆናል? ዋናዋናዎቹን የንግድ መስኮች ይዘዋቸዋል። ውድድር ውስጥ ይገባል እንጂ ሌላ ምን ይሆናል?»

«ከብሩስ? ከብሩ ሁላ እንደ ጉም ይበናል! ታያለህ ሙባረክ ገናና ለመሆን ጊዜ አይወስድበትም። በዚህ ላይ ይሄኛው ዘዴኛ ቢጤ ነው። ራሱን የድሆች አባት ብሎ ነው የተነሳው። አላሙዲ እኮ ዝነኛ ሰዎችን እየመረጠ ነው የሚረዳው። ላለው ይጨመርለታል እንዲሉ...»

«የሚገርመው» አለ ወጣቱ ነጋዴ፤ «ሙባረክ የመንዝ አማርኛ የመናገሩ ጉዳይ ነው። መደናቀፍ የለ፤ ምን የለ? እንደውላ በሚፈስ አማርኛ ነው ኮ የሚያዋራህ። ይሄ... ጓደኛዬ ያልኳችሁ አማካሪው እንደነገረኝ የፊታችን ሰኞ ጠዋት አራት ከሩብ ላይ ከራሱ ከመሰስ ዜናዊ ጋር ቀጠሮ ተይዞለታል...»

«ለምን?»

«አስር ሺ ቤተሰብ የሚያቅፍ የመኖሪያ አፓርታማዎች በሁለት ዓመት ውስጥ ሰርቶ፤ እያንዳንዱን ቤት በሙቱ ብር ሂሳብ የማከራየት ዕቅድ አለው»

አራቱም በማድነቅ አይናቸውን አፈጠጡ። ሽምገል ያሉት ሰው ግን ራሳቸውን ግራቀኝ በመነቅነቅ፤

«የተጋነነ ወሬ እንዳይሆን» አሉ። ወጣቱ ግን በተቃውሞ ጮኸ።

«ከአማካሪው ነው ኮ የሰማሁት። ራሱ ነው ኮ ስኔ ለራሴ የነገረኝ። የቅድመ ሁኔታ ጥናቱ ጭምር እንዳለቀ ነው ያረጋገጠልኝ። ምንም የተጋነነ ነገር የለውም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጠጡ በጨማመሩ ቁጥር ግን በእንድነት ሙባረክን ሙሉ በሙሉ ማድነቅና አላሙዲን ማጥላላት ጀመሩ። ሙባረክ የኢትዮጵያን ከባድ ችግር በጫንቃው ስመሸከም የተሳከ ቅዱስ ሰው በመሆኑ ላይ ያለ ልዩነት ተሰማሙ። የሚድሮክ ባለንብረት የሆነው አልአሙዲ ምንም እንኳ በግል የበደላቸው አንዳችም ነገር ባይኖርም «በውድቀቱ» ተደሰቱ። እንዲያውም «መቆየት ደግ ነው» ሲሉ ተጨዋወቱ።

* * *

በዚሁ አለት፤ ማለትም ቅዳሜ ሚያዝያ 2ቀን፣1991 የሙባረክን ወሬ የሰሙ ሁለት አርቲስቶች ይህን ገንዘብ የተረፈው የጠገበ ቱጃር ለማጥመድ አሰላ የጀመሩት አኩሉ ቀን ላይ ነበር። ያረፈበትን ቤታና የቅዳሜ ማታ ፕሮግራሞቹን ለማግኘት ወሬ ሲያነፈንፉ ቢውሉም ከቶ ሊሳካላቸው አልቻለም። ፍንጭ እንኳ ሳያገኙ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆነ። ቅዳሜ እንደሞነ ልታመልጣቸው መሆኑን ሲረዱ ግን አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ። ታላላቅ ሆቴሎችንም ሆነ አዝማሪ ቤቶችን እየዞሩ በማለስ የሙባረክን ቱሳ መርገጥና እንደምገ ብለው የዚህን ቱጃር ቀልብ ስበው ደቃ መገሙሩ ለመሆን ያለማወላወል ቀረጡ፤

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስክ አኩለ ሌሊት ድረስ አዲስ አበባን ከራስጠጉሩዋ እስክ እግር ጥፍሯ አሰሱት። ሆኖም ሙባረክ የተባለ ሰው ከቶ ሊያገኙ አልቻሉም።

አኩለ ሌሊት ላይ ኢምፔሪያል ሆቴልን ፈትሸውና አጠያይቀው ሙባረክ የተባለ በአደብ የመጣ ሶው አለመኖሩ ሲነገራቸው ግን ቆም ብለው ለማሰብ ተገደዱ። ደክሟቸዋል። ተስፋ ቆርጠዋል። እና በዚሁ በሞተ ስሜት ጥቂት ቃላት ተሰዋወጡ፤

«ለለሙባረክ የተወራው ሁሉ ውሸት መሆን አለበት

አለ ቀጠን አጠር ያለው ድምጣዊ።

«ውሸት አይደለም!» ሲል ተቃወመው ወፍራም ረጅሙ - እውቅ ተዋናይ።

«እንግዲያው ዛሬ አዲሳባ ላይ አለው የተባለው የጭፈራ ፕሮግራም ተሰርዞ ሊሆን ይችላል።»

«አይመስለኝም። ፕሮግራሙ አለመሰረዙን ዛሬ ጠዋት ጭምር ሰምቼያለሁ።»

«እና ምን ይሻላል ታዲያ?» አለ በመበሳጨት። ተዋናዩ መልስ አልሰጠም። ሁለቱም በአሳብ ተውጠው በመኪናቸው ውስጥ ተክዘው ቀሩ።

ግን ድንገት ከአምቼ አቅጣጫ ወደ ቦሌ የሚከንፉ ሰስት መኪኖች ታዩ። ሁለቱ አርቲስቶች ቀና፤ ነታ አሉ። ከፊትና ከኋላ እንደ ውሃ በሚፈሱ ቱዮታ ላንድክሩዘሮች የታጀበ ጥቁር ሊሙዚን መኪና፣ ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ!!

«ሙባረክ ነው!» ሲል ጮኸ ተዋናዩ። ሁለቱም ባልተጠበቀው ደስታ ተጯጯሁ።

«ርግጠኛ ነህ!»

ድምጣዊው ሲቃ ያዘው።

«ራሱ ነው፤ ራሱ ሙባረክ!! በሁለት ስቴሽን ዋገኖች በታጀበ ሊሙዚን እንደሚሄድ ስምቼያለሁ። ራሱ ነው፣ ይልቅ ተከተላቸው። ፍጠን! እንዳያመልጡን ፍጠን!»

ድምጣዊው መኪናውን አስነሰቶ ተፈተለከ። ተዋናዩ እንደ አብደት አድርጉት የባጥ የቆጡን ይለፈልፍ ጀመር፤

«አሁን ትገ አለኝ እንጂ፤ አኩለ ሌሊት ላይ እንደሚወጣ ሰምቼ ነበር። ዋነዋ፣ ታላቅ ዕድል፣ ፍጠን ይልቅ፣ አየህ እኔንኑ አምፔሪያል እንዲድ ያልኩህ። እዚህ ባንመጣ ኖሮ አናገኛቸውም ነበር... ፍጠን አሁን!» ሙባረክን አርፖርት ሞቴል አጠገብ ደረሱበት። ከዚያ ትንሩሸቸውን ሰብስበው ተጠግተው ይከተሉዋቸው ገቡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ርግጠኛ ነህ፤ እነርሱ ናቸው?»

«ምነካህ? ራሱ ሙባረክ ነው አያልኩህ። ይልቅ ዓይንህን ተከለህ ጉዱ። ድንገት እንዳያመልጡን። መብራት ቢይዝህ እንኳ እንዳትቀም። ጥለህ ተከተላቸው። እንኳን አገኘናቸው ብቻ! ይብላኝ ለአላሙዲ። ይብላኝ ለአላሙዲ ተከታዮች። ፀሀይ ለጨለመባቸው! ታያለህ! ሙባረክ አላሙዲን ተስፋ አስቆርጦ ከዚህ አገር ያባርረዋል። እነአጅሬም የገንዘብ ምንጫቸው ሲነጥፍና መኪናቸውን ለመሸጥ ሲያስማሙ ባይናችን እናያለን...»

በስቴሽን ዋገን የታጀበችው ሊሙዚን አንደ ዘንደ እየተምዘገዘገች አሎምፒያ ስትደርስ ወደ ግራ ታጠፈች። ከመቶ ሜትር ጉዞ በኋላ ደግሞ አስፓልቱን ትተው በቀኝ በኩል ወደ ኮረኮንቹ መንገድ ገቡ።

«የት ነው የሚሄዱት?»

ድምፃዊው ጠየቀ።

«እንጃ! እዚህ አካባቢ ምን አለ?»

ድምፃዊው ድንገት አንድ ነገር በማስታወስ እንደ ማፏጨት ታጣው።

«እዚህ አካባቢ አንድ አዲስ የተከፈተ ቤት አለ። ከካናዳ የመጣች ኢትዮጵያዊት ናት የከፈተችው። ውበትዋን ልነገርህ አልችልም። እዚያ መሆን አለበት የሚሄዱት»

በኮሮኮንቹ መንገድ እየተጠማዘዙ ሰአስር ደቂቃ ያህል እንደተጓዙ ደጃፉ በመኪና ሰራዊት ከተወረረ አንድ ቪላ ቤት ደርሰው ቆሙ። ይህን ጊዜ ድምፃዊው ድንገት ቱግ አለ፤

«የመኪና ብዛት ታያለህ? ተወርቶአል ማለት ነው። አዳሜ አሰፍስፎ እየጠበቀ ነው። ሆዳም ሁላ!»

ሁለቱ አርቲስቶች የመኪና ማቆሚያ ቦታ እየፈለጉ የተገጠገጡትን መኪናዎች ያስተውሉ ገቡ፤

«ታየዋለህ ይሄንን» አለው ተዋናዩ ወደ አንድ መኪና እያመለከተ፤

«ማነው?»

«ያ ነዋ...» ብሎ የአንድ ታዋቂ ድምፃዊ ስም ጠራለት፤

«ምን ሊሆን መጣ ደሞ እሱ!»

«ጆሮዬ ተደፈን፤ ድምፂ ጉረነነ ብሎ ሊለምን ይሆናላ! ሆዳም!»

ሁለቱ አርቲስቶች ጀማል አብዱራህማን መባረክን ተከትለው «ባንክቨር ፕብ» ተብሎ ወደሚጠራው ጭፈራ ቤት ገቡ።

* * *

የ«ባንኩቨር ፕብ» የመስተንግዶ አዳራሽ ሞቋል። ሀምሳ ያህል እንግዶችን በከርሱ የያዘ ቢሆንም ከቶ አልተጨናነቀም። የምዕራባውያን የተመረጡ ዘፈኖች አዳራሹ ውስጥ እንደ ደራሽ ወንዝ እየተገማሸሩ የቅዳሜ ምሽት አዲስ አበቤዎችን ያዝናናሉ።

ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሲል ግን ድንገት መዚታው ቀጥ አለና አዳራሹ በፀጥታ ተሞላ። ፀጥታው ግን አልቀጠለም። አንድ ሰው ሰሬድዮ ዜና ንባብ በሚስማማ ወፍራም ድምፅ እንዲህ ሲል ተናገረ፤

«በአጋጣሚ እዚህ የተገኛችሁ እንግዶቻችን፤ በአጋጣሚ በመካከላችን አንድ እንግዳ አሉ። ከውጭ ሀገር የመጡ ኢንቨስተር ናቸው። ከቡር ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ ይባላሉ። ከታላቅ አክብሮት ጋር እዚህ በአጋጣሚ የተገኛችሁትን ሁሉ ለመጋበዝ ይፈቀድላቸው ዘንድ ጠይቀዋል።»

ድንገተኛ ሩጫትና ሆታ አዳራሹን ሰነጠቀው። አብዛኛው የጠበቀውን የሰማ ነው የሚመስለው። ጩኸቱና ሩጫቱ እንዲሁም ጭብጨባው ለጥቂት ሰኮንዶች ቀጠለ። ሁካታው ጋብ ሳይል ግን ሙዚቃው ተከተለ። ሙዚቃውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ተከትሎ ደግሞ የውስኪ ጠርሙሶች በየተሰተናጋ
ጠረጴዛ ላይ ይሰየሙ ያዙ። በዚያች ቅፅበትም ሙባረክን
የሚያወድሱ ንግግሮች በየጫጫታው መካከል ይሰግ
ጀመር። አልፎ አልፎ ደግሞ አላሙዲን የሚያወግዙ
የሚመስሉ ሽሙጦች ተደመጡ። ሆታው፣ መጠጡ
ቀጠለ፤

ከአንድ ሰዓት በኋላ ግን ሙዚቃው አንደገና ፀጥ
ረጭ በማለቱ የሙባረክ ተጋባዦችም ትንሩሻቸውን
ውጠው የሚነገረውን ለማዳመጥ ጆሯቸውን ተከሉ፣
ሰፊዲዮ ዜና ንባብ የሚሰማማው ድምፅ መጣ፤

«ከቡራን አንግዶቻችን በአጋጣሚ አንድ ባለቅኔ እዚህ
በመካከላችን ይገኛሉ። ብዙዎቻችሁ በስም ሳታውቋቸው
አትቀሩም። ለማንኛውም ክቡር ሙባረክን አስመልክቶ
እዚሁ የጫጫርኪት ግጥም አለቺኝ ብለዋልና
ታዳምጧቸው ዘንድ እንጋብዛችኋለን።»

ባለቅኔው ወደ ማይክራፎኑ አስኪቀርቡ ግን አንዳንድ
ማጉረምረሞች ተሰሙ።

«እኛ ልንገናና እንጂ ግጥም ልንሰማ አልመጣንም።»

«ግብጣው ይቅር እንጂ መብታችንን እንኳ አሳልፈን
አንሰጥም፤»

«እኛ እኮ ኢትዮጵያውያን ነን፤ ኢትዮጵያዊ ለገዝፈ
ሲል ክብሩን አሳልፎ አይሰጥም፤»

ሆኖም የባለቅኔው ድምፅ ፈጥኖ በመከተሉ፣ ይህን
መሰሉ ማጉረምረም ሳይቀጥል ቀረ።

ሽምገል ያሉት ባለቅኔ ለሀሉም ታዩ፤

«አጋጣሚው ይገርማል መቼም» ሲሉ ጀመሩ።
«ድንገት ነው እዚህ የመጣሁት። ልጀ ናት ይዛ
የመጣችው። እና ክቡር ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ
ስለተባሉት ወንድማችን ታላቅነት ሲነገር ስሰማ ግን
ተቀምጠው ከነበሩት ሰዎችም የኢንሽአላህን የሀሣ

ወዳድነት ስሚት ስገነዘብ፤ በተለይም ኢትዮጵያ ላይ
ለመሰራት ያቀዱትን በጐ ተግባር ስሪዳ ድንገት እንድ
አራት መስመር ግጥም ጫር ጫር አድረግሁ። በእውነቱ
ግጥም እንኳ ትቼ ነበር። ዳሩ ግን የክቡር ሙባረክ
ታላቅ ስብዕና እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቁ የታላት
እንከብሶች ከብ ወደሆነው የጭንቅላቱ የፈጠራ ከረጢት
ይጉርፉ ዘንድ አደረገ። እና ክቡር ሙባረክ እነዚህን
አራት መስመር ስንኞች በአክብሮት እንዲቀበሉኝ
በትህትና አጠይቃለሁ።»

ጭብጨባው ጐረፈ፤

ባለቅኔው ጭብጨባው ጋብ ሲል ጠበቀው ቀጠሉ፤

«ሰጊታም ጊታ አለው፣ ይላል ርዕሱ»

በዚህ ጊዜ ታዳሚው በሳቅ አውካካ። ርዕሱን
አስመልክቶም ይንሾካሾክ ያዘ።

የግጥም ንባቡ ቀጠለ፤

«ኢትዮጵያ አልል በይ...
አልል በይ ኢትዮጵያ
ይርከፈክፍ ጀመር
የሙባረክ ካፊያ
ቅዱስ ማህፀንሽ
አፈራ በ-ታያ
ኩሪ እናት አለም
እምዬ ኢትዮጵያ»

ባለቅኔው ወረቀታቸውን ሲያጣጥፉ ጭብጨባው፣
ሩጨቱና ሆታው አዳራሹን አናጋው። አንዳንዶቹ ግን
እንዲህ ሲሉ አጉረመረሙ፤

«ርዕሱና ይዘቱን አሁን ምናገናኛቸው?»

«ይሄ በእውነቱ ልመና ነው። እንዲያውም ስለማርያም
ብሎ መለመን በተሻለ»

ሆኖም ግን ሙዚቃው ስለቀጠለ በተቃውሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚያጉረመርሙት እንግዶች ጆሮውን የሰጠ አልነበረም። ለነገሩ አብዛኛው ሰው «ግጥሙ የተዋጣለት ነው» ብሉ ደምድሞ ነበር።

ከሁለት ሰዓት ጭፈራ፣ ፌንጠዝያና፣ ያለገደ መጠጣት በኋላ እንደገና ሙዚቃው ረጭ ብሉ መረዋ ድምፅ ተከሰተ፤

«እንግዶቻችን ከቡር ሙባረክ የአንድ ደቂቃ ንግግር ለማድረግ ይፈቀድላቸው ዘንድ በአክብሮት ጠይቀዋል።»

ከዚያም ጀማል አብዱራህማን ሙባረክ ከነሙሉ ግርማ ሞገሳቸው ለተስተናጋጁ ሁሉ በግልፅ ታዩ። የባንኩቬር ፕብ አዳራሽ በፀጥታ ተዋጠች።

የአንድ ደቂቃ ንግግር!

ምን ሊሆን ይችላል?

ሙባረክ በጣፈጠ አማርኛ፣ ግርማ ሞገስ ባለው ድምፅ የሚከተለውን ተናገሩ፤

«ውድ እዚህ የተገኛችሁ ወገኖቼ! እኔ አብሬያችሁ ለመኖር፤ አብሬያችሁ ለመስራት የመጣሁ ወገናችሁ ነኝ።»

ጭብጨባው እንደ መብረቅ ድምፅ አዳራሹን ስላናጋው ሙባረክ ንግግራቸውን መቀጠል ሳይቻላቸው ቀረ። በእንድ ስልት፣ ባልተዘበራረቀ ሁኔታ፣ በደማቅ ህብረ ድምፅ የወረደው የጭብጨባ ዶፍ ለሁለት ደቂቃ ያህል ቀጥሎ ቀስበቀስ ጋብ ማለት ጀመረ። ጭብጨባው ጋብ ማለት ሲጀምር ግን አንዳንድ ንግግሮች ተሰሙ፤

«ከባድ ንግግር ነው!»

«ብስለት አለው ሰውየው!»

«ምሁራዊ ናቸው ቃላቶቹ!»

ከቡር ሙባረክ ፈገግ ብለው ሲያበቁ ንግግራቸውን ቀጠሉ፤

«ብዙ ንግግር አላበዛም። ወደፊት እያለ

የምንጨዋወታቸው አብይ ጉዳዮች ይኖሩናል። ለዛሬው ግን እንዲያው እጅ መንሻ ትሆን ዘንድ እዚህ ላላችሁት ለእያንዳንዳችሁ ዛሬውኑ ሃምሳ ሺ ብር ለመስጠት ወስኛለሁ።»

ድንገተኛ አልልታ የቤቱን ጣሪያና ግድግዳ አነቃቀው። ከዚያ በኋላ በተለይ ሙባረክን የሚያሞግሱ ድምፆች በገሀድ መሰማት ጀመሩ። ሙባረክ ለእያንዳንዱ ተጋባዥ ቼክ እየሰጡ፤ እያንዳንዱን ለጥቂት ደቂቃዎች ካነጋገሩ በኋላ የተጋባዡ ስሜት ሙሉ በሙሉ ተመሰሳይ ሆነ።

ተጋባዡ ሙባረክን ሊያደንቅ እግረመንገዱን አላሙዲን ማጥላላቱንና መሸርደዱን ተያያዘው። በዚህ ሁኔታ ያልተደሰቱ ጥቂት ሰዎች ግን ነበሩ። እንዲያውም አንድ ቁጡ የሚመስል ወጣት ሰው ድንገት ግልፍ ብሉት፤ አላሙዲን በሚያወግዙት ሰዎች ላይ ወረደባቸው፤ በቁጣ ድምፅ እንዲህ አለ፤

«አላሙዲን ለምንድነው የምትቦጭቁት? ምናደረጋችሁ? ሰውዬው ቆራጥ ኢንቨስተር ነው። ይሰራል። ሀገርን ጠቅሞ ራሱን ይጠቅማል። ሀቁ ይኸው ብቻ ነው። ሀገራችንን የሚጠቅም ስራ የሚሰራውን ኢንቨስተር ሁሉ ልናከብርና ልንንከባከብ ይገባናል። ከነፈሰው ጋር መንፈስ አሳፋሪ ልማድ ነው። እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ማለትም አህያ መሆንና እንደ አህያ ማሰብ ማለት ነው። ከዚያ ውጭ አላሙዲ እንደግለሰብ እንዳሻው የመኖር መብት አለው። ለአገሌ ሰጠ - እኔ አላገኘሁም ከሚል የቅናት መነሻ ሰውዬውንና አጋሮቹን በሀሜት መቦጨቅ በጣም ያሳፍራል። ኢትዮጵያዊ ባህል አይደለም። በእውነቱ ይህ ከፉ ልማድ አየተዋሃደን እንዳይሆን እሰጋለሁ።»

ይህን ንግግር ግን እያሉ ሰዎች ሳይታገሱት ቀሩ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

በተለይም አምስት ያህል ወጠምሻ ጉረምሶች፣ «የዚህን አወቅሁ ባይ ወጠጤ መንጋጋ ካላፈረስን ሞቱን እንገፍለን!» ሲሉ ለገላጋይ አስቸገሩ። ከአምስቱ አንዲ ጭራሽ እንደ አብደት አደረገው። ሁለት እጁን ራሱ ላይ አድርጎ መጮህ ጀመረ፣

«እባካችሁ ልቀቁኝ! ምን በደልኳችሁ? ይህን የአላሙዲ ሰሌ ልቡ ላይ አቆምበታለሁ!» እያለ አሪታውን አቀለጠው። እንደማይለቁት ሲረዳ ግን በአልህ ስቅስቅ ብሎ አሰቀሰ።

ቡጢ የመሰንዘር አውቀቱና አቅሙ የሌላቸው ታዲያ በዚህ ወቅት ስራ አልፈቱም። ፊዋነው ወደ ሙባረክ ቀርበው የግርግሩን መንስኤ ነገሩት። እነርሱም ታዲያ ፊታቸው ላንባ መስሎ ነበር። በርግጥ ጉንጫቸው እንዲያ የቀላው ሙባረክ በመሰደቡ ይሁን ውስኪ አብዝተው በመውሰዳቸው መለየት አዳጋች ነበር። የግርግሩን መንስኤ እየተቀባበሉ ሲናገሩ ግን ከንፈራቸውን በስሜትና በቁጭት ደጋግመው ይነክሱ ነበር። ጡንቻዎቻቸው ሲባጉ ቢጠ ቢሆንም ሁሉም ቡጢ ጨብጠው ነበር። አወቅሁ ባዩ ተሳዳቢ ሰው አላሙዲ ያሰረገው ወሬ አቀባይ መሆኑን በርግጠኝነት ሰሙባረክ ነገሩት። የበላበትን ወጪት በሰበረው በዚህ ሰው ንግግር ተጋባዡ ሁሉ ክፉኛ እንዳዘነም ጨምረው ነገሩት። በዚያም አላበቁ። አምስት ተጋባዦች አወቅሁ ባዩን ካላደባየነው ብለው ነበር፣ አንዲያውም ላም ያኘከችው ጨርቅ እናስመስለዋለን፣ እያሉ ለገላጋይ ማስጥገራቸውን ሳይቀር ነገሩት። በተሰይ ደግሞ ከአምስቱ በአድሜ አነስተኛ፣ በቁመት ግን ቀዳሚ የሆነው ወጣት ያን ከሀዲ ቡጢ ባለማቅመሱ ምክንያት በአልህ ተንሰቅሰቅ እንዳስቀሰ አወጉት። በዚህ መካከል ታዲያ ከሙባረክ ግራና ቀኝ በተጠንቀቅ የቆሙት ሁለት አማካሪዎቹ

በየደቂቃው ወደ ጆሮው ጠጋ አያሉ ሽከ ይሉት ነበር። አሱም ራሱን ላይ ታች ያወዘውላል።

ሙባረክ የግርግሩን መንስኤ አናምጠ ሲያበቃ፣ «ተንሰቅስቆ ያለቀሰውን ወጣት አምጠልኝ» ሲል አዘዘ።

በሁለት ደቂቃ ውስጥ ወጣቱ ሙባረክ ፊት ቀረበ፣ «ማነው ስምህ?» አለው ሙባረክ በጭቅርና በአክበሮት አያስተዋለው።

ወጣቱ ግን ለተጠየቀው መልስ መስጠቱን ትቶ፣ በቁጭት እየነፈረ እንዲህ አለ፣

«ወይኔ ግርማ! ያን የአላሙዲ አሽከር ትምህርት ሳልሰጠው አመለጠኝ። ድሞ አለቀውም። የገባበት ገብቼ ልከ አገባዋለሁ!»

ሙባረክ ፊገግ አለ፣

«አሃ! ግርማ ነው ስምህ? በጣም ነው የማመሰግንህ ግርማ። እውነተኛ ታማኝ ወዳጅ መሆንህን ተረድቼያለሁ። ለዚህ ውለታህ ደግሞ ለጊዜው...»

ሙባረክ የጀመረውን ንግግር ሳይጨርስ ከደረት ሲኑ ቺክ መገዘ አወጣ። ወዲያው ጫርጫር አደረገ እና ቺኩን ለግርማ አቀበለው።

«አልቀበልም» አለ ግርማ ሁለት እጁን ከፍ አድርጎ። ግን ወዲያው እጁን ወደ ቺኩ መልሶ መስደድ ጀምሮ ነበር። በዚህ ቅዕበት የከበቡት ሁሉ «ተቀበል! ተቀበል!» አያሉ አደፋፈሩት። እንዲያ ባይሉትም ግን መቀበሉ ባልቀረ ነበር። ግርማ ቺኩን ተቀብሎ የተገፈለትን የገንዘብ ልክ እንደዋዛ መልክት አደረገ። ሙቹሽ። በቁሙ ሊወድቅ ምንም አልቀረው።

ሙባረክ እይኑን ወጣቱ ላይ ተክሎ ጥቂት ቆየ፣ ከዚያም፣

«ለመሆኑ የአላሙዲ ወሬ አቀባይ፣ ያላችሁት ሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

የታለ?» ሲል ጠየቀ።

ለዚህ ፈጣን ምላሽ የሰጠችው የባንኩቨር ፐብ ባለቤት ነበረች፣

«ቼኩን ነጥቀን አባረነዋል። ይኸው ቼኩ!»

ይህን ብላ ሃምሳ ሺህ ብር የተፃፈበትን ቼክ ለሙባረክ አቀረበች።

«ስሙ ተዕፎበታል?» ሲል ጠየቀ ሙባረክ።

«አልተፃፈበትም።»

«እንግዲያው በር ላይ ላለው የጥበቃ ሰራተኛ ስጪው»

«ክቡር ሙባረክ፤ የጥበቃ ሰራተኛው ድርሻውን ወስዷል!»

«ይሁን፣ ይህንንም ጨምሪለት!»

ሙባረክን የከበቡት ሁሉ ምንነቱ ያልታወቀ ድምፅ አሰሙ። ክዳር እዳር መቁነጥነጦች ታዩ። የስቃይ ስርቅርቅታዎች። ያልተስተካከለ አተነፋፈስ። ጣር፣ ሀይወት፣ ሞት፣ ሀብት፣ ምኞት፣ ዕድል፣ አጋጣሚ።

ሙባረክን የከበቡት ሁሉ በዚያች ደቂቃ ዘበኛውን መሆን ተመኙ። ቀንበት። የባንኩቨር ፐብ ባለቤት ጭምር በሙባረክ ውሳኔ አልተደሰተችም። ሆኖም ቼኩን ይዛ ወደ በሩ ማዝገምዋ አልቀረም። ልብዋ ብዙ እያበ ነበር። ያን ቼክ ለዘበኛው ያለመስጠት ሀሳብ መጣባት። ግን ደሞ ስጋት ያዛት። ሙባረክ ሲወጣ ድንገት ዘበኛውን ጠርቶ ቼኩ መድረስ አለመድረሱን ሊጠይቀው ይችል ይሆናል። ከጠየቀውና መጭበርበሩን ከተረዳ ደግሞ ያኔም ባንኩቨር ፐብ ላይደርስ ይችላል። ያም ብቻ አይደለም። ቼኩ ለዘበኛው እንዲሰጥ ሙባረክ ሲያዝ ብዙ ሰው ሰምቷል። አንዱ ሄዶ ሊያቃጥር ይችላል። ሰው አንደሁ ለሰው አይተኛ። ምትኛ የሞላበት ሀገር! ምርጫ አልነበራትም። ዘበኛውን ጠርታ እንዲህ

አለችው፣

«ስማኝ ክቤ...» አለች። ክበደ ነው ስሙ። ቀደም ሲል ግን አንኪን አቆሳምጣ ልትጠራው ስሙ እንኪ እየጠፋባት «ማነህ አንተ...» ነበር የምትለው። ክቤ ይህን አሳምሮ አስተውሏል። እና እንዲህ አለችው፣

«ስማኝ ክቤ... በድጋሚ ገንዘብ እንዲሰጥህ አድርጌያለሁ። መጀመሪያ ከተቀበልከው ጋር መቶ ሺህ ብር ማለት ነው። እኔ ባልነግርልህ ሀምሳ ሳንቲምም አታገኝም ነበር። ይህን የማደርገው ግን ሰዕድቅ ብዬ አይምሰልህ። ባንተ ስም እኔም መጠቀም ስለምፈልግ ነው። እኔ ቀጥታ ብቀበል ስሜ ይጠፋል። ገብቶሀል?»

«በጣም ገብቶኛል እሜቴ!» አለ በትህትና «...ደግሞስ ቁራሽ እንጀራ እንኪ ባጣሁበት ጊዜ ርስም አይደሉ ለዚህ ስራስ ያበቁኝ? ይመኑኝ እሜቴ፣ ገንዘብ አገኘሁ ብዬ ግልብጥ የምል ሰው አይደለሁም። ረጅሙን ህይወቴን በክባድ መከራ ያሳለፍኩ ሰው ነኝ። እርስም ይበቃሃል ያሉኝን ከሰጡኝ ይበቃኛል። የቅድሙም ያሁኑም እርስም ዘንድ ይሁን» ብሎ እጁን ወደኪሱ ሰዶ ቀደም ሲል የተሰጠውን የሀምሳ ሺህ ብር ቼክ አውጥቶ እጁን ዘረጋ፣

የባንኩቨር ፐብ ባለቤት ገሃታዋ ሁሉ በፈገግታ ተሞላ፣ የጣዛ ዓይንዋን ተጠራጠረች። እናም፣

«ጥሩ ብለሀል!» ብላ ቼኩን ፈጥና ተቀበለችው። አያይዛም «ክቡር ሙባረክ ሲወጡ ድንገት ጠርተው ከጠየቁህ መቶ ሺህ ብር መቀበልህን ንገራቸው። ገባህ?»

«ገብቶኛል እሜቴ!»

«አምን፣ ጠባይህ ሁልጊዜ አንዲህ መልክም መሆን አለበት። እኔ ለገንዘብ የሚስገበገብ ሰው አልወድም»

ዘበኛው ፈገግ አለ፣

«ልክ ነዎት እሜቴ፣ ገንዘብና ወዳጅ ወደ መቃብር

t.me/OLDBOOKSPDF

ተከትሎ አይወርድም። ሁላችንም ሌጣችንን ነው ወደ ጉድጓድ የምንሄድ»

* * *

ፊንጠዝያው ቀጠለ...

በአጋጣሚ በማብሣው ላይ የተገኙ ድምፃውያን፣ ገጣሚያንና የዜማ ደራሲዎችም ተባብረው «ለጊዜው ጌታ አለው» የሚል ዘፈን በማዘጋጀታቸው መባረክና አሸቢሎቹ በዚያ ምርጥና አዲስ ዘፈን ሴሊቱን መሉ ደነሱ። እስክ ንጋት ድረስም ከቶ ድካም የተሰማው አልነበረም።

* * *

ሚያዝያ 4፣ ሰኞ ማለዳ።

ከንግድ ባንክ ዋናው ቅርንጫፍ ከአቶ ጀማል አብዱራህማን መባረክ የባንክ ሂሳብ በድምሩ 12 ሚሊዮን ብር ለመውሰድ የመጡት ኢትዮጵያውያን ቼኩ ላይ መነዘርላቸው ቀረ። ምክንያቱም «አንገንድ የሚጥሩ ነገሮች ስላሉ» የሚል ነበር።

ሚያዝያ 6፣ ረቡዕ ማለዳ።

የንግድ ባንክ ዋናው ቅርንጫፍ መስራያ ቤት ስራ አስኪያጅ ድንገት ወደ አንግዳ ማስተናገኝው ክፍል በመግባት ሰማለዳው ደንበኞች የሚከተለውን ንግግር አደረጉ፣

«ውድ ደንበኞቻችን፣ ክአቶ ጀማል አብዱራህማን መባረክ የባንክ አካውንት ተከፋይ ሂሳብ ሰመውሰድ የመጣችሁ አባላችሁ ወደ ዋናው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ብትሄዱልን። ለለሰራር ያመቸን ዘንድ በጋራ የምናንጋግራችሁ ጥሪት ጉዳይ አለ።»

የባንኩ የማለዳው ተስተናጋጆች ቀስበቀስ ወደ አዳራሹ ማምራት ጀመሩ። ሽክ ያላለ የለም። ከመባረክ የባንክ ሂሳብ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚጠይቁት

ባለጉዳዮች 3:30 ሰዓት ሲል መሉ በመሉ በአዳራሹ ተሰበሰቡ፣

የባንኩ ስራ አስኪያጅም ወደ መድረኩ ወጥቶ የሚከተለውን ንግግር አደረገ፣

«ውድ ደንበኞቻችን... ካልተሳሳትኩ ክአቶ ጀማል አብዱራህማን መባረክ የባንክ አካውንት ከ12 ሚልዮን ብር በላይ ተከፋይ ገንዘብ ለመጠየቅ ነው የመጣችሁት። በጣም እናዝናለን። ግለሰቡ በአካውንቱ ከአምስት ሺህ ብር በላይ ስለሌለው ልንከፍላችሁ አልቻልንም። በዚህ አጋጣሚ ግን ግለሰቡን በተመለከተ ሰናንተ አንድገልፅላችሁ ከፖሊስ አንድ መረጃ ደርሶዋል። ሰናንተ ቼክ ሲያድል የሰነበትው ግለሰብ ኢንቨስተር አይደለም።


በሽተኛ ነው። በሀሺሽ ሱስ የተለከፈና አይምሮው በትክክል የማይሰራ መሆኑ በህኪም ተረጋግጧል። ቴስትሩ ያለው ከጀርባ ነበር። አምስት የአዲሰባ ወሮበሎች ከዚህ ሰው በስተጀርባ ተሸሽገው ሲቀልዱባችሁና ሲዘርፏችሁ ነው የሰነበቱት። አስካሁን በፖሊስ እንደተረጋገጠው ወሮበሎቹ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ የምልሽ ገንዘብ ተቀብለዋል። አንድ ሳምንት ሙሉ አደሲ ሀብታሞችና አርቲስቶች ከአዲሱ ቱሪር ጋር ለመተዋወቅ አማካሪ ለተባሉት ወሮበሎች ጥሪታቸውን እያሟጠጡ ገንዘባቸውን ሲያስረክቡ ነው የሰነበቱት። አንግዲህ ፖሊስ እነዚህን አጭበርባሪዎች ለመያዝ ጥረት እያደረገ ነው። አሁድ ለት ካገር ወጥተዋል የሚል ነገርም አለ። በርግጥ «መባረክ» ተብሎ ቼክ ሲነሰንስ የነበረው ሰው ተይዟል። ግን ሀሺሽ ካልወሰደ ትንፋሹ ቀጥ የሚል በሽተኛ በመሆኑ ፖሊሶች ወደቤቱ እንዲመለስ አድርገውታል። ያዘዙትን ከማድረግ ባሻገር ምንም የሚያውቀው ነገርም የለም። አንግዲህ የቾሮታ ቼክ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰጣችሁ መቼም ተርፋችኋል። ለሰጣችሁት አገልግሎት
ቼክ ለተቀበላችሁ ግን ክልብ እናዝናለን። በተለይም እ
ባንክኛ እንደመሆኔ ጉዳዩ በጣም ያሳዝነኛል። ሆኖ
አንድ ስህተት ስለተፈጠረ በቼክ ላይ ያላችሁ እም
እንዳይቀዘቅዝ አደራ እላለሁ።»

ከግማሽ ሰዓት በኋላ የባንኩ ደሻፍ ተቦጫጭቀ
በተጣሉ የቼክ ቁርጥራጮች ተሞላ። የእለቱ የመዘጋ
ቤት ጉዳና ጠራጊም እንዲህ ሲል አጉተመተመ፤


«ዛሬ ደሞ ሰው ምነክው? ወረቀት የመጣል ሱ
ይዞታል ልበል? ክፉት ነው! እኔን በማድከም ለሁ
ምን ይጠቀማሉ?»



ዝናብ

መስፍን ሀብተማርያም

አንድ ማክሰኞ ዕለት ከስምንት ሰዓት በኋላ በአዲስ
አበባ ከተማ የዘነበው ኃይለኛ ዝናብ ለዚህ ጽሑፌ
መነሻ ስለሆነኝ፣ በውነቱ ዝናብ በዝናብነቱ አይመሰገንም
እንጂ ባመሰግን ደስ ባለኝ ነበር። ከፒያሳ ወደ ካዛንቺስ
በ«ውይይት» ታክሲ ተንሸቼ የምጓዘው ሰውዬ በከባዱ
ዝናብ ምክንያት ሹፌሩ አቁሞ ውረዱ ስለንና አራት
ኪሎ በጋዜጠኞች አጠራር «ድድ ማስጫ» እሚሉት
ቦታ ሂጀ ከፎቅ ሥር ተጠለልኩ። ዝናቡ ይለዋል።
ያወርደዋል። ጎርፉ ይሮጣል። ዕድሜ ለውይይት ታክሲ



t.me/OLDBOOKSPDF

«ድድ ማስጫ» ቆሜ ድድ ማሰጣቱን ጀመርኩ። አጋጣሚው የዝናብ ተጠላይምችን ሁኔታ በዝርዝር እያሳየኝ ብዙ ነገሮችን ተመለከትኩ። በረንዳው ላይ የቆምኩት ሰውዬ ቁስ በቀስ ስገሩ ቆይቼ ሳላስበው ቡጥ ቢቱ ገር ጋ መድረሴን ልብ ያልኩት በኋላ ነበር።

አካባቢው በጭጋግ እንደታፈነ ነው። ንደሰኛ ንፋስ ውሽንፍሩን በረንዳው ድረስ ይረጨዋል። ልብሳችን አላው በስበሰ። ነገሩ ሰወሬ አይመችም። እንደኔ ሰው ርቅ ሥር ሆኖ የዝናብ ከለላ አያገኝምና፣ አስፋልቱ ላይ የሚታየው ትርምስምስ ሊሳ ነው። አንዱ ከወዲያ ይሮጣል። ሌላው የያዘውን ዕቃ ሽፋፍኖ ለማዳን የማዱን ዝም አያለ በውሃ ይርሳል። አንድ ትልቅ አሞራ ክባሻዉ ርቅ የወደቀ ይመስላል፣ አየሩን በክንፉ እየጠረገ እንደሚንዘባዥ ስካራም ወዲያ ወዲህ አየዋዠቀ ጭጋግ ውስጥ ዝና ለዐይናችን ተሰወረ። ኋላ እንደኛ መጠለያ አያቸግረውም አልኩ በልቤ።

ነባድላዉ በሰማዩ እየተሯሯጠ ማሰቃያቱን ቀጥሏል። አንዲት እናት ከለሳ አንገቷ ላይ እንደታጠረች ወራ ካሳየው የምትሰዋን ልጇን እየሳንቀለች በራሷ አረምኛ ልክ ታስሮጣታች። ጥቂት መኪኖች ያለምንም ከፍያ በውሃ እየታጠቡ ጎርፉን ሠንሥቀው ያልፋሉ። በዚህ መሃል አንድ ብልጥ ውሻ የቆመ ቢታክሲ ሥር ተኝቶ የተጠለልነውን ስምኝ ትክ ብሎ ያየናል። «እንደኔ ሐሳቡ መጣለት?» ... ብዬ ተገረምኩ።

እውነትም ዝናብ ያጽፋል። እናንተስ ሰታስበት ... በበጎ መልኩ ካየነውና ከአስቀኖው ብንነሣ ብን የሚል ካራያ እንኳ ከተፈጥሮ አወራረዱ ማማር ጋር በወበት ሲጋደይ የቆየን ስውነት ቀዝቀዝ አያደርግም? ጥሩ የሠመመን እንቅልፍ የሚያመጣ፣ ሳቅረኛችን በደመነፍስ የሚያስታቅፍና በውድቅት ማገዶት መሃል

ደስ በሚል ስሜት የሚያፍነከንክ። ባለማቋረጥ ሰስስ ብሎ የሚወርድ ዝናብም አለ። ደሞ የዛሬው ዓይነት እንደ ጋዝ ሠልፍ የሚያሰባስብ ነገር ግን ከግርማውና ከድምቀቱ በተጨማሪ በአዕል ውሃ ምንጭነቱ የብሩህ ተስፋ፣ የብልፅግናና የመልካም ሕይወት ተምሳሌት የሚሆን ዝናብ ያጋጥማል።

ዝናብ ሲባል ግን ምን ያህል ስንቶችን ያበሳጫል? ምን ያህል ደግሞ ለስንቶች ደስ ይላል? የሚለውን ጥያቄ ላንሣ እፈልጋለሁ። ሰምሳሴ ሴተኛ አዳሪዎች በቅሙበት ያጅፍ ካላቆያቸው አይወዱትም። ሊስትሮዎች ከማንም የበለጠ ጥላቻ እንደሚኖራቸው አትጠራጠሩ። ታክሲዎችም በሠኑ ተሣፋሪ ለስሚርትባቸው ሰጥቅማቸው አይውልምና «ይሄ ሁሉ ዝናብ ሳልሠራበት አሰተኒ» ሳይሉ አይቀሩም። ከሁሉ በላይ ልብስ አጣቢ እንኪን በርሚሉ ውስጥ የሚይገባለትን ትርፍ ዝናብ ከምንም የሚቆጥረው አይመስለኝም።

በለላ መልኩ ደሞ ካየነው፣ በቀላል ምሳሌ፣ ሰማዩ አጠራትሞ ያረገዘውን ውሃ ያውሳችሁ ብሎ ሲለቀው እንዳንድ ደስ የሚሉ ነገሮችም በዘሁ አጋጣሚ ተክሰተው ሰቁም ነገር ይበቃሉ። ሰምሳሴ ሰዎች በክባድ ዝናብ ተባርረው መጠለያ ይፈልጋሉ። አንዲት በጀ ጠቅለል ያለ ዕቃ ይዛ የቆመች ቆንጅዬ – ግን ኮስታራ – ልጅ ትሮራለች። አንድ ደግሞ ሥራ ሰዓቱ ከቢሮ አስወጥቶ ከራሳቱን አስሮ ብሩህ ፈገግታ ያሰው ወጣት አጠግቧ ከዝናብ ለመጠለል ይቆማል። ንግግር ተለዋወጠው፣ ተዋወቁ፣ አንድ ቁን በጋበ፣ ተጋብተው ሀሰት ሰስት ወልደው የዕድር አባሉች የሠፈር ማኅበርተኞች ቢሆኑ ዝናብ ምን አደረገ ይባላል?

ዝናብ ተጠልሰው ድንገት የሚያገኙት ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ ዘመድ ደግሞ ሌላው የሚወደድ ተዕይንት ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያውም ማጋነን ባይሆንብኝ ብዙ ውሃ ካበሰበሰ ከሌቃ ከአንደኛው ወደ ሌላው የሚሸጋገሩ የውሃ ጠብታዎች በዚያን ወቅት ጥሩ የፍትር መግለጫዎች ይሆናሉ።

ወደ «ውይይት» ታክሲው ልመልሳችሁ – ከአራት ኪሎ ጊዮርጊስ ብዬ፣ ካዛንቺስ ትቼ የተመለከቱበትን።

ጉርሱ አሰፋልቱን ሞልቶታል። ውሃው መሂጃ አጥቶ ዝም ብሎ ይሮጣል። ማዘጋጃ ቤት ምን ያህል በውሃ ማውረጃ ቱቦ እንዳልደከመ የተረዳሁት ያኔ ነበር። ብቻ እንደምንም፣ መሪና ፍሬን ብም ነገር የሚያመሰለው ግዩስኽ ሹፌር መንገደኛው ላይ ውሃውን እየበተነ እሽክረክረና ጊዮርጊስ አደረሰን። እዚያ ወሪድኩና ዝቦ እየመታኝ፣ ውሃ በውሃ ሆኜ ሌላ ታክሲ, ውስጥ ለገባ አንዲት ቆንጆ ወጣት ፊት ሰፈሩ ተተምጣ አየሁ። ምንም በማይመስለኝና፣ ተፈጥሮ ያው በምትለኝ ጣዕ ውስጥ ገባሁና ዝም ብዬ እመሰከታት ጀመር። ታዛቢ በሌለበት ያንን ያህል ሳያት መቆየቱ ግን በጣም ገርሞኛል። ለማንኛውም ... በዚያ ለመሣፈር ሣፈያው፣ ግጭቱ (የመኪና) የከርቡራታር ብልሽት፣ የወያሶች አደንቋሪ ጥሪ መሀል ሁሉ... ያቺን ቆንጆ ልጅ፣ / እሽተና ቆንጆ እንዴሉ...// ዝም ብዬ ሳያት... ኮሚያማምሩ የወንሯ ዘለላዎች ላይ፣ ከግንባርዋም ከጆሮ ግንዷም ጠልጠል ብለው የተበተኑ የወንሯ ዘለላዎች ላይ የውሃ እንክብሎች ጠብ እያሉ ሰጠርዱ በውሀ የራሰው ልብሷ የሚያሸፍልሰውን ድንቅ ቅርጿን ሲያወጣው... ውበቷ አዛው በዛው እየጨመረ እየሳሳ ... አሳ, ሰአድናቂዋ ድንታ በሷ ሆና ትከ ብላ ወለሱን ወደ ታች ሰታይ ... የኔ የወብት አድናቆት ወደላይ እየመጠቀ ልብሴ በዝናብ መዘፈቁን ሰጊዜው አለሰሳኝ እላችኋለሁ።

ዝናብ በተፈጥሮ አወራረዱ በሰው ልጆች

የሚያደርሰው አንዳንድ ችግር እንደሚኖር በርግጥ ጠፍቶኝ አይደለም። ጽንሥላቸው በንፋስ የሚወሰድባቸው ጠና ያሉ ሰዎች ይዚን አባባሌን እንደሚያጸኑት አምናለሁ። የአንድ አገር ጪማው ወልቶበት ከሃርፋ ጋር አየርጠ ያስመሰለ አንድ ሰው አዛው አራት ኪሎ በተመለከቱበት ቦታ ቆሚ አይቻለሁ። በዚያን አጋጣሚ ባርኔጣ የሚወድቅበት ሰው እንዴት ከሃርፋ ጋር ይታገል ይሆን ብዬ አሰብኩ። ነገሩ በርግጥ ማቅ ሲያጭር ይችል ይሆናል። ሆኖም ኩስተር ባለ አመሰካከት ሁኔታዎችን ለንመግም በውድ የተገዛ ባርኔጣ ምን ያህል እንደሚቆጭ ከልብ ማሰብ አለብን። በከባድ ዝናብ ወቅት የመሳጣ ሰው ባርኔጣ ንፋስ ወርውሮት ሳርፍ ውስጥ ከወደቀ ደሞ ያለው አማራጭ ሳርፉን መኩተል ሳይሆን ቶሎ ታክሲ ፈልጎ እቤት መግባት ነው።

በነገራችን ሳይ ... ስለ ዝናብ መጠለልና ዝናብ ከለሚያከወልሉ ሰዎች ለምን ትንሽ እናወጋም? ባልታሰበ ወቅት የሚመጣ ኃይለኛ ዝናብ ከተጠሮ ማለተንገሉ አርግጥ ነው። ለብርድና ለልብስ መበሰበስ ያጋልጣል። ያም ሆነ ይህ መፍትሔው ካሁን አሁን ያባራል እያሉ ዛደ መጠለል ነው። በየርቁ በረንዳ፣ በየቡና ቤቱ፣ በየሱቁ መሰባሰብም አይቀርም። ታዲያ ሁሉም ተጠላይ ከለግዝነ ግሬያና መሳሸሸም አያጣውም። ትንሽ ጠፈጠፍ ሰመሸሽ ሲባል የሌላውን አግር መርገጥና ከግድግዳ ጋር ማጣበቅ ሁሉ ይኖራል። የሚገርመው ሁሉም የራሱን ምቾት ፈላጊ ይሆንና የሌላውን መሳደት አላይ ያላል። አንዳንዱ ከቀርቀሮው ላይ የሚፈናጠሩ የውሃ ጠብታዎችን ለመከላከል ሰሬያ የሚያህል ጽንሥላውን አናንጫቸው ላይ ያዘረጋል። በዚህ አጋጣሚ ጽንሥላቸውን እንደዘረጉ ታክሲ, ውስጥ ካልገባን እያሉ ከበሩ ጋር የሚታገሉ ሰዎችም ተመልክቻለሁ። በዝናብ ግሬያ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳንዱ ሊደግፋችሁ ምንም አይቀረውም። ከሁሉም በላይ የሚያናድዷችሁ ደግሞ ከአውቶብስ ወይም ከታክሲ ገና ሲወርድ በኃይል እየዘሰሱ ስልሥር ሜትር ርቀት ሮጠው ገሥግሠው ሲያበቁ የቆሙትን ሰዎች ያስምርቁ ገፍትረው የሚጠለሉት ናቸው። እንዲህ ያሉትን የተጠላዮችን ሠልፍ የሚያረግዱ ሰዎች ውሃ የሚገላቸው የሚመስላቸው ላይሆኑ አይቀሩም። ሰነሱ የሚታያቸው ቶሎ ደርሰው «አቤት ... አቤት... ተመስገን ጌታዬ» ማለታቸው ብቻ ነው። ሆኖም ግን ሁሉም ግዴለሽ አይደለምና ከተጠላዮች መሀል አንዷን መነዕር የሰነቱ ኮሳሳ ወጣት «ነይ ማሚት... እኔ ካፖርት ይከላከልልሻል ... ወዲህ ሁኚ ... አበሰበሰሽ እኮ » የሚል ምራቁን ዋጥ ያደረገ አሳቢ ሰው አይታጣም።

ከዝናብ አስጠላዮችም መሀል ቤቱ በሰው ሞላ ሲል፣ በሩን መዝጋታቸው የማይቀርም ቢሆን፣ ቅንነት የተሞላቸው ይገኙባቸዋል። ሱት ወይም ሴኔ የንግድ ቢታም ከሆነ «መስታወቱን አትደገፉ» ወይም «እትጋፉ... የግድግዳው ቀለም ይላጣል» የሚል ዓይነት ማስጠንቀቂያ መስማት የተለመደ ነው። አንዳንዱ ሁኔታ ግን ከማሳዘን አልፎ ያሣፍራል። ቦዝናብ በሰበሰ፣ በተጠላዮች ሳይወዱ ተገፍቶ ከበረንዳው ወደ ቡና ቤቱ ሲገፈተሩ «ምን ልታዘዝ?» መባል ምን ያህል እንደማያስደንግጥ የሚያውቀው በኪሱ ሣያ አምስት ሣንቲም ያልያዘ ሰው ብቻ ነው።። ደሞ በእንዲህ ዐይነቱ ጊዜ ኮሴታውን ቀልብሶ ውጭ ውጭውን የሚያይ ዝናብ ተጠላይ በጣቱ ጀርባውን ጎንጥ እያደረገ «ምንድነው ያዘገከው?» ብሎ እሚያፋጥጠውን ቡና ማሺን ላይ የተመደበው ሰው መሆኑ በጣም ያስገርማል። ታዲያ ያኒ የሚኖረው አማራጭ «ተጠልዬ ነው» የሚል ምልክት ለማስተላለፍ የዝናብ ጠፈጠፍ የሌለበትን ግንባር በእጅ ሞዣች

እያደረጉ ዝም ማለት ብቻ ነው። ይሄ ሲገርማችሁ ከታክሲ መሣፈሪያ በስተቀር ምንም ገንዘብ የሌለውን ሰው ‹‹የሩ መጠለያ ላሳይዎት›› እያሉ ጉርሻ የሚጠይቁ በዘንዶች በከተማችን አለመኖራቸው ዝናብ በየአስፋልቱ ለሚያባርረን አንድ ዐጋ ነው አላለሁ።

ለማናቸውም ግን ዝናብ ለመሸሽ የሚታይ ጥድፊያና ሩጫ ከወለምታና ስብራት አንስቶ ብዙ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል መታወቅ አለበት። አንድ ጊዜ አንዲያውም ሁለት ሰዎች ለመጠለል ሲሮጡ ተጋጭተው አንደኛው መሞቱ በጋዜጣ እንደተገለፀ ትዝ ይለኛል። ከአንድ ባለ ለማያልፍ ውሃ ደንብረው ሲሮጡ፣ አይጣል አንጂ፣ በመኪና መገጨትም አለ። ከለማይ በፈለሰ ውሃ ማቢያ ከስ መመሥረት አይቻልም እንጂ አንዳንድ ችኩል ሰው በእግሩ እየዘለለ የሚረጨውም ውሃ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ነጭ በነጭ ለብሰው ለሠርግ የወጡ ሴቶች ይዛን አሳምረው ያውቁታል። ዝናብ፣ አሁንም ቢሆን፣ እንደ ተዋጊ በራ ሲያስደንብር አይገባም። ተገዢው መንገድ ቀልጠፍ ብሎ ግራ ቀኝ አይቶ መጠለያ መፈለግ ነው። መጠለያ ካጡ ደግሞ ያሰው አማራጭ በትዕግስት እየተደበደቡ መሄድ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ዝናብ የማይፈሩ አንዳንድ ደክማ ሰዎች መኖራቸው ሊነሳ የሚችል ጉዳዮች ይመስሰኛል፤ ለምሳሌ ኃይለኛ ዝናብ እየዘነበ፣ ሰው ሁሉ ተጠልሎ ሣለ ዘንበል ቢጪ አንጠልጥላ፣ አጠላዋን ጥብቅ አድርጋ ይዛ፣ ምንም ነገር እንዳልሆነ ሁሉ አንጉትዋን ደፋ አድርጋ በጥምና የምትይዝ ሴት አይታችሁ አታውቁምን? ወዴት ይሆን የጉዞዋ መጪረሻ? ...? የትነሳችውስ ከየት ሰሆን ይችላል?... ማን ያውቃል! ምናልባት አንድ ምስኪን መልዕክተኛ ልትሆን ትችላለች። ከመርካቶ ተነሥታ... በአባኩራን ሠፈር አሳብራ... በአጥንጮ በር

t.me/OLDBOOKSPDF

አቀራርጣ... ሽሮ ሜዳ ለመሄድ የተነሳች። ማን ያውቃል! ቶሎ ካልደረሰች «አመቤቷ» ይቆጧታል። ዐውደ ዓመት ተቃርቦም ከሆነ ብዙ ብዙ የሚሠራ ሥራ አለ። በርበሬው አልተወቀጠም... ቅቤው አልተነጠረም... የገበያው ውድነት፣ ወፍጮ ቤቱ፣ ወረፋው፣ ምኑ ቅጡ! ዐይናፋርነት? ሠርቼ ልብላበት? ማን ያውቃል!

ዝናብ የማይፈሩ ግን የሷ ዓይነቶች ብቻ አይደሉም። ሕፃናት በጎርፉ መሃል ይሮጡበታል። ዕብዶች ያስጮኻቱት ይጫዙበታል። በዚህ መሀል ዘንጉን የያዘ መንገዱ የጠፋበት ዓይነሥውር ለማኝ ማየት ምንም እንደሚያሳዝን መገመት አያስቸግርም።

ከእንስሳትም መሀል ለዝናብ ደንታ የሌላቸው አይጠፉም። ምናልባት እንድ ጌኛ፣ ዝም ብሎ ሜዳ ላይ የቆመ፣ የማይንቃነቅ ጌኛ ታዩ ይሆናል። ባለቤት ይኖረው ይሆን? የሥራ ዘመኑ እንደሆነ ሕብቅቷል፣ ቂላችሁም ታስቡ ይሆናል። «አህያ የማይችለው ዝናብ» ተባለ እንጂ አህያስ በጣም ዝናብ ይችላል።

ታዲያ ከዚህ ለየት ያሉ ሁኔታዎችን ሳቡብ መጠኑን በእጅጉ ያላለፈ ዝናብ ከመልካም ሰዒት ጋር የሚያያዝበት፣ ሰተፈጥሮ አድናቆት የሚውልበት፣ ደስ የሚያሰኝ ገጽታው ይታሰበኛል። ከሰማዩ ማጉረምረምና ከደመናዎች መሯሯጥ ጋር ታጅቦ ሲመጣ፣ ነገን ለምትናፍቅ ነፍስ የለጠው ትፍስሐት፣ በሕካባቢው ላይ ከሚፈነጥቀው ግርማ ጋር አምሮና ደምቆ ይታየኛል። ሰማዩ የሚሸክ ጎብረ ቀለም የፀሐይ ብርሐንና ጥላ ሲፈራረቅበት ... ነፋሱ ዛፎቹን እያስጎነበሰ ትጠሎቹን በተፈጥሮ ዜማ ሲያጫውታቸው... ወፎች በየጎጆአቸው ለመግባት ሲጠራሩ የሚፈጥረው ደማቅ ድባብ ምንኛ ያስደስታል ብዬ አስባለሁ። ገና የመጀመሪያዎቹ ወፋፍራም ጠብታዎች ቆርቆሮው ላይ ሲያርፉ የውስጥ

ሽብር ተኖ የሚጠፋ ይመስላል። የአእምሮ ትኩረት ደስ ወደሚል አቅጣጫ ይለበስባል። የመንፈስ አርጋታ በሠረፀባቸው ዐይኖች የሚስተዋል ጥንታዊ ፀጋ...

በርግጥም በዚህ ወቅት ምናባችን (IMAGINATION) ሣለፊያ ማረፊያ ያገኛል። አታክልቱና ዕፀዋቱ ሲዘናፈሱ... ለበቦች ለሲላያቸው በድምቀት ሲያሸበሽቡ ይታየናል። የከተማው ቆሻሻ፣ ሞቶ የተጣለው ውሻ፣ ድመት ሳይቀር ማኅበራዊ ሕይወታችንን ሲተነፍገን የቆየው እኩይ ነገር ሁሉ... ተጠራርጎ ወደየወገዙ ሲገባም ጥሩ ንጹሕ አየር ለመተንፈስ ያሰን ብሩህ ዕድል ይታሰበናል።

ዝናብ ከሚያስገኝልን የምናብ አርካታ ዋናው የነጠሩ ነው። ልምላሜ፣ ብልፅግና፣ ሰላማዊ ሕይወት... መሠረቱ ከዚያ ነው። አዝርዕቱ ከነፋሱ አቅጣጫ ጋር ጎብረ ነቅናቂያቸውን ሲያዛምዱ፣ በቅሎው ሲንሿሿ፣ ጤፉ፣ ስንዴው፣ አየተኛ ሲነሳ በየሸንተረሩ ድፍርስ ውሃ ሲንደረደር... ውሃ የሕይወት ምንጭ!... ደሞ ጠረኑ የሚያውድ የንፁሕ አፈር ሽታ ጥጆች ያበግ፣ የጥየል ግልገሎች የተፈጥሮ ምንነት አፈታትን ድቅን ይላል።

በዝናብ ጊዜ ለመንፈስ አርጋታ አመቺ ድባብ የሚፈጥሩ፣ አካባቢን በጽሞና ለማስተዋልና የተፈጥሮን ሉዓላዊነት አበክሮ ለማጤን የሚገፋፉ ሁኔታዎች አሉ። የልጅነትን አደረሉ ከፍለዘመን ምጭትና ተስፋን፣ ያደንበትን ቀዬ፣ ውሃ የተራጨንበትን ጅረት መስክና አረብታውን ለማስታወስና፣ መፀዒውን የሕይወት አፎይታ በዓይነ ሕሊና ለመቃኘት መነሻ የሚሆኑ ትዕይንቶችም ይኖራሉ።

ዝናብ የመልካም ሕልምም ተምላሌት ነው - ልብ መጥቆ ርቅ ለሰከነ ሕልውና የሚታተትበት። ዝናብ በተስፋ ሰምናብ አርካታ ለፊ መድረክ ይሰጣል። የኪነጥበብ ሰዎች ቢናፍቁት፣ ፍቅረኞች በዝምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቋንቋቸው ቢነጋገሩበት የማይደንቀንም ለዚህ ነው
ሩቅ ሳትሄዱ ከደራስያን ኮሮጆ ዶልዱሞና ታፍኖ የ
ብሰር ብቅ ይላል። ያኔ ቅኔ ዜማ ይካናል። ዘንቦ ዘን
ሲያባራ ደግሞ የጻመናውን ቁልል ሠንጥቃ ብቅ የምት
ፀሐይ ስትወጣ... ወርቅማ ጨረራ ብሩህ መስመ
ሠርቱ አድማሳቱን ሲቃኝ... በዚያን ደማቅ ትዕይን
መሀል... ሠዓሊው ቡሩሹን ይጨብጣል። ዝናብ!

መጣጥ






መንግስቱ ለማ


ያገር ልሣኪ

«ያገር ልማድ» ቢሉት አንዲያው በደፈና፣
«ያገር ልማድ» ቢሉት አንዲያው በጨፈና፣
ፍሬ አጣ ነገሩ፣ መላው ሆነ መና
«ልማድ» አንዲያው «ልማድ» የሚባል የታለ?
ክፉ ልማድ አለ፣ በጎ ልማድ አለ፣
መጥፎ ልማድ አለ ጠንቱኛ ልማድ።
ባሪያ መሸጥ መግዛት ነበረ ልማድ
ዛሬ ማን ይነቅሩል የዚያን መወገድ
ክቱ ጢምቡስ በቀር ክበጉ ከከብቱ
ካፍንጫው ከማያልፍ አስተዋይነቱ?
ያነዱ እነ ጢምቡስ ሲጮኹ ነበረ፣
«ሃይማኖት ፈረሰ ያገር ልማድ ቀረ!»
ልማድ በሕንድ አገር ባሏ ሲሞት ሚስቱ
ትተበር ይል ነበር፣ ሞቷ ሆኖ ሞቱ፣
ጉንፋን የማያውቃት ያች ጢነኛይቱ፣
አእምሮ ገዛና ሰው ልማዱን ሻረ።
ያነዱ እነ ጢምቡስ ሲጮሁ ነበረ
«ሃይማኖት ፈረሰ! ያገር ልማድ ቀረ!»
ታዲያ እንግዲህ «ልማድ» «ባሕል» እየተባሉ
ጠንቋይ ይኑር ነወይ ሕዝብ እንዳታለለ?
ይቀጥል ነው እንዴ የጉቦ ልማድ
የወገን ያድልዎ ያጋር የዘመድ??

t.me/OLDBOOKSPDF



የቀበጡ ዕለት



ሀውዜንና ጉቴኒካ

ሳምሶን ስውሩ

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ኤፕሪል 26-1937 ዓ.ም አስቱ ማክሰኞ የገበያ ቀን ነበር። የቦስኮች መኖርያ የሆነችው ጉሬኒካ አደባባዮቿ በገበያተኛ ተጥለቅልቀዋል። ገበያው ከደራ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሄንክል 1-11s እና ጃንከር 52-s የተባሉ የጀርመን ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች የጉሬኒካን አየር ሙሉ ለሙሉ ከተቆጣጠሩት በኋላ በገበያተኛው ላይ ቦምብ ያዘንቡ ጀመር። ገበያዋ በታላቅ ፍንዳታዎች ቀውጢ ሆነች። ሬሳ በሬሳ ላይ ተከመረ። ህፃን፣ ሽማግሌ፣ ወንድና ሴት የማይለየው የናዚዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

በምብ እየተደጋገመ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ንፁሀንን ድምጥማጣቸውን አጠፋው።

የዓይን ምስክሮች ሲናገሩ 'አውሮፕላኖቹ ደግመው ደጋግመው አስኪሰለቻቸው ገበያዋን በፈንጂና በቦምብ ቅጥቅጠዋታል' ብለዋል። ከድብደባው ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በቦታው የደረሰ አንድ ሪፖርተር «በመንገዱ ሁለት ገሮች እየቀረብን ስንሄድ የሴቶች፣ የወንዶችና የህፃናት አስከሬኖች ተመልክተናል። አልፎ አልፎም የሚያለቅሱ ህፃናትና የሚያቃስቱ ጎልማሶች ድምፅ ይሰማ ነበር። ወደ ተከመረው አስከሬን ስንጠጋ አንድ አረጋዊ አየሁ። የተቀደደውና የተቃጠለው ልብሳቸው ቁስ አንደሆኑ ያመለክታል። ፊታቸው በአሳትና በጭስ ተሰብልቧል። መኪናዬን አቁሜ ወደ አረጋዊው ቀረብኩ፤ መናገር አይችሉም። ለመናገር ይሞክሩና ሲያቅታቸው ገም ይላሉ።

እሻቸውን ብድግ አድርገው በአራት ማይልስ ርቀት በመቀጣጠል ላይ ያለውን ነበልባል በጣታቸው ሰቀሙኝ፤ ከዚያም 'በምብ' የሚለውን ቃል ብቻ ተናግረው ፀጥ አሉ። በነበልባልና በጭስ እንዲሁም በተከመሩ ፍርስራሾች ውስጥ የተቃጠለ የሰው ልጅ ስጋ የሚዘገንን ጠረን ነበረው። በዚህ መሃል ቃሬዛ የተሸከሙ ወታደሮች አንደ ህፃን ልጅ እያነቡ አስከሬን ይሰበስቡ ነበር።

ብዙዎቹ ህንፃዎች በነበልባል እየጋዩ ስለ ነበር በመንገዶቹ ለመጓዝ አስቸጋሪ ሆኖአል። በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ትንሽ ወታደራዊ ኢላማዎች መኖራቸው ቢታወቅም የናዚዎቹ የቦምብ ዝናም ግን በቀጥታ ገበያተኛው ላይ ነበር ያነጣጠረው። የሚትሰር የጥፋት መላእክተኞች የጫኑትን የቦምብ ከምር ተከሳካይ በሌለት በጉራኒካ ገበያ ላይ አራገፉት።

ከዚህ ሰለባ የተረፉ ሰዎች አንድ ዓይነት ቃላትን ነበር የሚናገሩት። ይህም «አውሮፕላኖች... ፍንዳታዎች... ተኩሶችና... እሳት» የሚል ነበር።

ይህ ከሰው ልጅ ሞራልና ርህራሄ ፈፅሞ የራቀ ኢ-ሰብአዊ ጭፍጨፋ በዚህ ታሳቅ ገበያ ላይ ተፈፀመ። «ይህንን ጥፋት የሚደግም የሰው ልጅ ዳግመኛ በምድር ላይ ይፈጠር ይሆን?»

የሪፖርተሩ ጥያቄ ነበር።

* * *

ከ50 ዓመታት በኋላ ይህ ጥፋት ተደገመ። ዳግመኛም አዶልፍ ሒትለር ስገሰ አስፋው ሲሆን ዳግመኛዋ የጉሬኒካ ገበያ ህውዜን ሆነች።

አንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ሰኔ 10-1980 ዓ.ም በዚህ የገበያ ቀን ከገጠር፣ ከከተማና ከህውዜን አካባቢ ያሉ ሰዎች ገበያዋን አጨናንቀዋታል። ሴቶች፣ ወንዶች፣ ህፃናት እና አረጋውያን አንደተለመደው የገበያዋ አድምተኞች ነበሩ።

ገበያው ደርቷል። ግዢና ሽያጭ ይከናወናል። በድንት ፈጣን የሆኑ ጀቶች የህውዜንን አየር ተረከቡት። ቦምብ ተርከፋከፈ። ሰው በሰው ላይ መውደቅ ጀመረ። ህውዜን ተደበላለቀች። ነፍስ ጡጭ ነፍስ ግቢ ሆነ። አስከሬን በአስከሬን ላይ ተደራረበ። አየተደጋገመ የሚወርደው ቦምብ ድምፁ ጆሮ ይበጠርቃል። አሳቱ የሰውን ልጅ ወደ ትቢያ ይለውጣል። ጩኸት... ትርምስ... መውደቅ... መነሳት... እንደገና መውደቅ።

አውሮፕላኖቹ ለእይታ ይጠፉና እንደገና ተመልሰው ይመጣሉ። አንድም የሰው ልጅ በገበያዋ አንዳይተርፍ የታዘዙ ይመስላሉ። ገበያዋ በአሳት ተለበለበች። ሆኖም አሳቱ ላይ አሳት ከመወርወር አልታቀቡም። ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖቹ በተከታታይ የሚመላለሱ ሲሆን ባጭር ጊዜ ልዩነትም ለሚተኮሰው ዙር ድብደባ እየተተካኩ ነበር ጭፍጨፋውን የሚያካሂዱት። የመከላከያ ምንም

t.me/OLDBOOKSPDF

አማራጭ ያልነበራት ሀውዜን የሚወርደው የቦምብ ውርጅብኝ ከመኖር ወደ አለመኖር ሰወጣት። አሪታቸውን ያሰሙ የነበሩት ገበያተኞቿ ድምፃቸው እየጠፋ ሂደ። ከመጀመርያው ዙር ድብደባ የተረፉ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩም ከሚቀጥለው ዙር ሊያመልጡ አልቻሉም ነበር።

አሳት የሚተፉት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች አሁንም ይመላለሳሉ። በሀውዜን ገበያ ውስጥ የተቆለለው የሰው ልጅ አስከሬን ለአይታ ይዘገንናል። እናታቸውን የሚጣሩ ህፃናት አልፎ አልፎ ይሰማሉ። ሌሎች ደግሞ አይናቸው ጠፍቶ ፊታቸው ተለብልቦ በአጸቸው እየዳሰሱ እናቶቻቸውን ይፈልጋሉ።

ብዙዎቹ እናቶች ግን ሰውነታቸው እየተገሸላለጠ ወድቀዋል። ልጆቻቸውን 'አለሁ' ማለት አይችሉም። አሸልበዋል... ቦምብ... አሳት... ጩኸት... ሁካታ... ቀውጢ... ጀቶች... ዳግመኛ ናዚዎች... ሀውዜን ዳግማዊ ጐሬኒካ...



የሰፍሬቃ ልጆች

ተስፋዬ ገብረአብ

ባለፈው ዓመት የክረምቱ መራት መግቢያ ላይ ወደ ቢሾፍቱ ብቅ ብዬ ነበር። የትውልድ መንደሬ ከሆነችው ከዚች ውብ መንደር ከራቅሁ አስር አመት ቢሆልፈኝም በአመት ሶስት ጊዜ ያህል የምጠይቃቸው ሁለት አርመናውያን ወዳጆች አሉኝ። ቫርቱክስና ሳልፒ ይባላሉ። ከቢሾፍቱ ሀይቅ የራቀዉ ኮረብታ ላይ ትልቅ የቱዳ ፋብሪካ አላቸው።

ፋብሪካው ወደሚገኝበት ኮረብታ ተጉዋዝኩ...

ስትስት እጅግ ከምታምረው ሳልፒ፣ ቀልድና ቁምነገሩ ከማይጠገበው ቫርቱክስ ተገናኝቼ ለማውጋት እጅግ ጉጉቼ ነበር። ዳሩ ሳይሆን ቀረ። ላባደሮቹ እንጂ ቫርቱክስና ሳልፒ

t.me/OLDBOOKSPDF

የለም። ያኔም በፋብሪካው የሚሰሩት ሁሉ የኔው መንደር ልጆች በመሆናቸው ለእነርሱ የሞቀ ሰላምታ አቅርቢ ሳቢኝ፣ ፊቴን ታይቶ መደማይጠገበው ሀይቅ መልሺ ቀዝቃዛውን የቢሾፍቱ ነፋስ ማስተናገዱን ተያያዝከት።

በደቂቃዎች ውስጥ የህንድ ዜግነት ያለው የፋብሪካው ሰ አስኪያጅ ካለሀበት ብቅ ብሎ ተዋወቀኝ። ማን ነበር ያለ ስሙን? ቪጄ ኩማር? እንጃ ብቻ ለማንኛውም ስሙን ነገር ሲያበቃ፣

«ዶቫር ቱክስና የሳልፒ ወዳጅ መሆንህን ሰማሁ» አለኝ።

«ሁላችንም የቢሾፍቱ ልጆች ነን» አልኩት።

በአነጋገሬ ፈገግ አለ። እሱስ የምን ልጅ ይሆን?

ካገሩ ምድር ውጪ እስካለ ድረስ «የህንድ ልጅ» መሆ ግድ ነው። ከህይት ተመልሶ ህንድ የተባለች የህገሩን ምድ ሲረግጥ ግን ስለተወለደበት መንደር ማሰብ ይጀምራል ምናልባትም የቫይቮር - የካፑር - የናግፑር ልጅ ነኝ ይ ይሆናል። የመንደሩን አፈር ሲረግጥ ደግሞ ጌኔ የኋቶ ኮሚ ልጅ ነኝ ማለቱ አይቀርም። ካቡቱ ግቢ ሲከስት፣ ግልፅ ነው ቪጄ ነኝ ማለቱ ግድ ይሆናል። ይህ የአስተሳሰብ ትምህ ተከተለ ለሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ነው።

ህንዳዊው ሌሬ አስኪያጅ እንዲህ አለኝ፣

«ቢሾፍቱ ሀይቅ እጅግ ውብ ነው። ግን ለምን ጥቅም ላይ ሳይውል ቀረ»

ለዚህ ጥያቄ መልስ የለኝም። አፍርበታለሁም። እኔ በበኩሌ በቢሾፍቱ ልጅነቴ የምኮራው ስሜቴ በደመነፍስ ደሜ ውስጥ ጠልቆ ስለገባ እንጂ፣ የቢሾፍቱ ሀብት ለኑራት የሚያበረ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ ሁኔታው እንገት የሚያስደፋ ነው በዚያን ቢሾፍቱ በአሳዛ ጉመራ ከተከሰተ ሳስት ሺህ አመታት አስቆጥሮአል። አርሞዎች ቢሾፍቱ በሚል ስም ከጠሩት ደግ ሳስት መቶ አመት ግሰፉ ይነገራል። እኔ «የቢሾፍቱ ልጅ ከተሰኘሁ ደግሞ ስላሳ አመት ሞላኝ። በነዚህ ሁሉ ዘመናት ቢሾፍቱ ከገበረዎች አንር መለቃለቂያ ያለፉ አገልግሎ አልሰጠም። ምናልባት ግን የገፀዎችን አሀዞች የውሃ ጥ

አርክቶ ለሆን ይችላል። ይሽው ነው።

ከህንዳዊው ጋር በቢሾፍቱ ሀይቅ የራስጌ ኮረብታዎች ላይ ተቃምጠን ስንጨዋወት ሃና አለማየሁ መጣች። ያንተ ያለህ! በልጅነቴ ነው በውኔ? ይህቺን ሴት በአይነ ሲጋ ካየሁዋት ስድስት አመት አልፎኛ ነበር። የመንደራችን ልጅ ናት። የቢሾፍቱኤ ዙሪያመጣዘት ተነስቼ አቀፍኩዋት። እስዋም ሰላታዋኛ ሙሽት። መነቀስ ብቻ ነበር የቀረን። ተያይዘን መጣንብ አታተን። የአምላክ ያለህ! ሃና አሁንም ውብ ናት። በልጅነት ዘመናችን በእኛ የአድሜ ክልል የሚገኝ የቢሾፍቱ ወጣት ሁሉ በዚህች ልጅ ፍቅር ተለክፎ እንደነበር አስታውሳለሁ። ሳልዋሽ ልንገራችሁ? እኔ ራሴ ሁለት አመት ሙሉ አፈርድሜ በልቻለሁ። ይሽው አሁን ግን ከነሙሉ ፀጋዋ አጠገቤ ቁማለች፣

ህንዳዊው ሁኔታችን ገባው መሰለኝ ጥሎን ሄደ። እኛም ታዲያ ከምገወደወና ከሚወደን የቢሾፍቱ ሀይቅ የራስጌ ኮረብታ ላይ ተቀምጠን ተፈጥሮአዊ የሆነውን ጣፋጭ የቢሾፍቱ አየር እየተቋዋደስን ወጋችንን እንጠርቅ ገባን።

«እንደምናለሽ ታዲያ ወብትዋ ሃና?»

«አንተነፍሳለን» ብላ ፈገግ አለች «ኤአንተስ እንዴት ነህ? ጋለጠኛ መሆንህን ሰምቻለሁ። እንደምጭትህ ስለተሳካልህ ደሰ ብሎኛል። ግን ደሞ ከኛ ልጆች ፈፅሞ ርቀህል ይባላል። ይህ ተገቢ ነው?»

«ልክ ነሽ ሃና። ግን ይህ የሆነው በክፋት ሳይሆን ስራ እየበዛ ነው። አንዳንድ መሬዎችን ግን አሰማለሁ። አንቺም ሆስተስ ሆነሻል አሉ።»

ሃና ትክሻዬን ይዛ እንዲህ አለቺኝ፣

«ረጅም ጊዜ ሆነን ሳንገናኘ። በሚገርም ሁኔታ ብዙ ተለውጠሀል። እውነቱን ነው። ፈገግ ባትል ኖሮ አላውቅህም ነበር።»

ቀበሌጠ ውብ ሆነሻል ሃና። በልጅነቱ ባንቺ ፍቅር መውደቁ ስህት አልነበረም ማለት ነው?»

ሃና በስሱ ፈገግ አለች። ፈገግታዋ ትንግርታዊ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

የወብትዋን ደረጃ በቃላት ለመግለፅ መሞከር ከንቱ ድካ
ነው። ‘ወይዘሪት ቢሾፍቱ’ ብትባል ይገባታል።
«ለመሆኑ ትዳር ቢጤ መሰረትሽ?»
«ገና ነኝ» አለች ሃና «_አሎኛ ግን አለኝ። በቅርቡ ማግባ
አይቀርም። አንተስ?»
ቡተኩሱ ስሜት ነበር መልስ የሰጠሁዋት፣
«እኔ እንዱዋ_ ከሦስት አመት በፊት አግብቼ ነበር። አሁ
ግን ተለያየተናል። ምናለፋሽ በጥቅሉ ‘ፈት’ ነኝ ማለት ይቻላል።
ሃና በሳቅ ፈነዳች።
«ምናሳቀሽ?»
«አሁንም በራስህ ላይ መቀለዱን አልተውክም?»
«መቼ ቀለድኩ? እውነቱን ነውኮ የነገርኩሽ።»
«ለውነቱ ካንተ ጋር ባለመገናኘቴ ብዙ ነገር ነው ያጣሁ
የቢሾፍቱ ልጆች ልዩ መለያ ባህርይ የሆኑት የሚያስቁ እውነ
ይናፍቁኛል። ግን እስኪ ልጠይቅህ? እዚህ ምን ልታደ
መጣህ?»
«ሳልኮ ዘንድ።»
«ታመኸቸዋለህ እነሳልኮንን?»
«ቢሆንስ በዓመት ሶስት ጊዜ ብቅ እላለሁ። ሆዴን እስኪያመ
ድረስ የሚያስቅ ነገር ያወሩልኛል። እውነተኞቹ የኛ መገለ
ልጆች ናቸው። የመራራ ቀልድ ልማዶቻችን ተዋህደዋቸዋል
«ልክ ነህ» አለች ሃና ትከዝ ብላ «_ እነቨርቴክስ የኛ ሰዎ
ናቸው። እስክሁን ከቢሾፍቱ አልራቁም።»
ይህን ብላ ስታቅቃ፣
«ለመሆኑ ከኛ ልጆች ማንን ታገኛለህ?» ስትል ጠየቀቸ
«ማንንም» ሰል መለስኩ።
እንዲህ ስላት እኒያ ቀልብ የሚያስቱ አይኖችዋን ቢሾፍ
ሀይቅ ላይ ተክላ ተመለከተች።
« ጉዋደኞችህንም አታገኛቸው?»
«ብፍህም። ከሁለም ተራርቂያለሁ። ላገኛቸው አፈልግ ነበ
ስራ አየበዛ ሳልችል ቀረሁ። አብዛኞቹ ደሞ ወደ ዝልል ናቸው
ሰነገሩ አዲሳባ ካለችም አልገናኝም_»

«ስለ ባህሩ ግርማ ምንም አልሰማህም ማለት ነው?»
«ባህሩ ምን ሆነ?» አልኩ ደንግጬ። ባህሩ የልጅነትና የልብ
ጉዋደኛዬ ነው። ከጅማ የህክምና ሳይንስ ኮሌጅ በክብር ማዕረግ
ከተመረቀ ወዲህ አግኝቼው አላውቅም። ባህሩ ብሩህ አይምሮ
ያለው ልዩ ሰው መሆኑን አሳምሬ አውቃለሁ። እና ምን ሆነ?
«ምንም አልሆነ» አለች ሃና «_ብቻ ኢትዮጵያንና ቢሾፍቱን
ለዘልአለሙ ተሰናብቶ ወደ ታላቋ ብሪታንያ ተሰዶአል -
ለዘልአለሙኮ»
አባባልዋ ልቤን ነዘረው። ትክ ብዬ አጤንሁዋት።
ሃና ቀጠለች፣
«እኔ አስተናጋጅ በነበርኩበት አይሮፕላን ነበር ወደ ለንደን
የበረረው። ጥቂት አወራን። ባህሩን እንግሊዞች ጠለቃት።
የሰላሳኛ ዓመት ተማሪ ሳለ መምህሩ የነበረና ልዩ አቅሙን
የተገነዘበ አንድ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰር ሲመረቅ ጠብቆ መጥቶ
ምን እንዳለው ታውቃለህ?»
«ምናለው?»
ጭንቅላትህ ሰኢትዮጵያ አይመጥንም። ያንተ ጭንቅላት
የአለም ህዝብ ሀብት ነው። ታላቋ ብሪታንያ በጥብቅ
ትፈልገሀለች። አትምህን ሙሉ በሙሉ መጠቀም የምትችለው
ስፉ የትምህርት ዕድልና የመመራመሪያ መስክ ስታገኝ ብቻ
ነው። አለበለዚያ ኢትዮጵያ ብትቆይ ዕድልህ ጠባብ ይሆናል።
በሽተኛ ዝርፊያችን ኮማከም፣ ኮማሪን ባሻገር ምን ትሰራለህ
ይህን ደሞ ተራ ሀኪሞች ሁሉ ሲፈፅሙት ይችላሉ። ያንተ
ጭንቅላት ግን ከዚህ ባሻገር የዓለምን ህዝብ ሁሉ ሊጠቅም
ከሚችል የምርምር ስራ ላይ መዋል ይችላል ሲል አሳመነው።
ፕሮፌሰሩ አልዋሸም ሊባል ይችል ይሆናል። ግን እኛስ? ባህሩ
ግርማን የመሰሉ የኛ ልጆች በዚህ መንገድ ጥለውን ከነጉዱ
ስኛ ማን ይቀራናል? ለዚህ ጥያቄ መልስ አይገኝለትም።
ለማጽናናውም ያክተር ባህሩ እንግሊዛዊውን ተከትሎ ተሰዶአል።
ወደ ሀዘር ቤት ይመለስ እንደሆነ ጠይቁው ነበር። ርግጠኛ
አልነበረም። መመለስ እንደማያሻ ስረዳ ወደ አይሮፕላኑ መቀመጫ
ቤት ገባቸ አሰተኳኩ። ተንሸዋሸዉ አሰተኳኩ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

አያናጂ አሁንም እንባ አቅርረው ነበር። ብዙድ የመኑት ያነበል ስውንትዋ ሽምትዋ ሲል አስተዋልኩ።

«ስምን እንዲያ ተስማሽ ሆነ?»

«አንጀኒ» አሉኝ። «...ለተለዩ ሚንሳሳቶች ክብር አሰኙ። ያለን የመሰለ ሚንሳሳት ያላቸው ስዎችን ለዘልነለሙ ማሳት አሰኙቷ ነው። አበር አደገ ...ያለበቱ ምክንያት ለዘልነለሙ ዋለላ ሲሄድ አያስደንግም በተለይ ለዘልነለሙ ...ለህን። ብቹ ምን መሰለህ...? ሰዎችን አላንዛዘ ማሳት መፈራ ነው። አዲያ በቀለ መሞቱን የሰማው አለትም እንድችው ሳለትስ ነበር ያደረከት...»

«አዳኛ ሞኮ» ስል በድንገቱ አይኔ ፈሰ ጠየትዋቸት። «አልሰማህም?»

«ሠምራለሁ»

«አዳኛ ከሞተ አዙ በጠኝ አመት አስፈለ» አሰኘ።

ባለዘጠኑ ደረቱ ቀደ። አዳኛ የልጅነት ንግናኝትን ነበር። ዘንምዘርቱ ደህግ አልነበረም። ሆኖም ጠላንቹ በልመና የሚተዳደሩ ለዘጠሩ የሰላት ንብሱን ማፕንት ጉምር ያቸዝ ነበር። በዚህ ምክንያት ትምዘርቱን በቅጠ መከታተል ተስኖት አስጀዘር አስተውለበት ግን አዳኛ እንኋትና ስምን ሞቀ ዋ አወጋቸኝ!

«ሞሚወሳ ታሪክ የለውም። ወታደረንት ተተጠረና አረችራ ዘሞቶ አዚናው ሞተ» ለዩቲቱሞች ያነበል ዘዘሙ ተሞሞነ። አያናጂችንን ለጀም ዝዜ ዘሀዱቱ ደረት ላሁ ተነበን ቀረን። አስፈረጠውን ዝምታ የሰዘረችው ዋ ነበረች። በአንናት ስሜት ተጉፋፍኑ መሳናሰሳ ጀመረች፡

«...ነዝያኛቱ ልጆች እንጂ ጨጠ ዘር ተብትንተል። ትጥኑን ታጠ-ታት ናስ የተስማ ልጅ ናዘፈት ላይ ሴተኛ አሩፉ ሆነሽ አለ። ምንኮደረገ ዋ በልጅነትዋ አናትና አብተሞን ሞት ከጠታት። እንዘዘዙው - ታፈሰ ቶላ መነሳን ተዘፉ አነ ዘርአይ አነ ጉድታ - አሠንም ስፈ የላችውም። ዘመንኑ ሲያጠፍልኮ ያጠላለሰ። አነ እንኋያጠምዱ የመከፈቸው ናስም። ግን ዓስ ቢያጠምዱብ ግን ያጋቸትዋል ስለዚህ በሽክሳ ቀን አፈቱ መጠባበቅ

ያጀምሩና ማምሸውን ጉምና ላይ ወየተው ያስተወሳሉ። በቦጵ ሀያቸው በፍቢ ስለሚጠው አንጀታቸው ተጉልዓሉ ሊጠጣ የደሰ አስቢመስል ድረስ ያቀስተሉ። የሰጠቦች ነኛ ልጅች ሀያውት ያሀን ያመስላል።»

ዋ ተጠሰችና እንዳሀ አለች «... ደንቀውን ታስታወሰሀ?»

«ሞሚዝ። የማልረሳው ሰው ቢኖር አሱ ነው።»

አውን አዘሮማሪስት ነው። አሚነባ ዩኒቨርስቲ መምህር ሆኖአል። አመሪካን ሀዘ ማስተርስን ፈጨርስ ሲመለስ ከአንደን ጅሞር አብረን ነዘር የመማረው። ነጥን በተመለከተ ብዙ አዘ,ንን። አዲነባ ላሁ መኮጠዚዮ ቤት ያለው አንነት ማስጸዚዮ የመንግስት የኬራያ ጉጅ ሞፕንት አንደማሀችል አንስቱ ተገመነገጨ። ወቋሞ ሀዘ ስለመጥር ስፖስ ታዲያ ቫወር ያለው ቤት ለማፕንት ዝዜ ሀዘራን መቀው ነዘረብኘ ሲል ጠየቀኙ። ደንቀው አንዲያ ያመሻሪ አንጂ ዘሀዘ ቤት የመኖር መገፈሱ አንደብረት ጠንክራ መሞጉን ተረድቷታለሀ። ያ የመገፈስ ሞንክረው የትድረስ እንደማዘልት ግን ስላወቁም።»

«አብሮተኛ መጥን ያስፈልጋል» አልኩዋት።

ዋ ግን ዘዚህ ሳተስሞጣ ቀረች።

«አንድ እኛ ብቻውን አሃጨሀድብም» ብላኝ ቅጂም አሰች። ከየነቱት የዘምታ ቅጂታ ቢነሳም የምሪት ብስትዋን ትዘረግፍልኝ ቀጠለች፡

«ስለ ቢሾናቱ ልጆች አንድነንድ ልንገርህ አቸላለሀ። ስላማቢችን ታጠ-ታታለ ... ሀያሉት መሄኒ ስርንት- እዘሀን ሀሉ ታጠ-ቀሞሰሀ። አብዘሀን ድረስ ስዘልነት የማያሀቅ የወንድ ንዋያኛ አንኒ ስራ መሃዘ አልቻለም። ዋስሀሀን መሳዙ ደሞ ክሊ ሆኖአል። ስስና ጠና ንኒቱ ከጠለሰች ተጠሰአል። ነገመማት ሀያውት አሃታመትም። ትሩንኑ አማሪካ ከሂደች ቢነሳ ቢጫ መሄና ተድንች የተነሳቸውን ፍቱ ልነ ዝዜ - ለዘሾናቱ ልጅች ከመሳ። ዘዚያ ድምስ ጠፋ። ዝሀስ ባልታጠቀ ምክንያት አብዶ ከተማ ወሰዞ ፈጨርችና ሳሳ ስሊቀችም ያጠላል። ዘያልኑ ዘዚያም ነንጫ ቢሆንም ስንገዘብ ሲል ሰው ከመንደል የማሀመስ ፈጨነትን አረመፈ ዘመሆት የማዘነገው የለም። ተስማ

t.me/OLDBOOKSPDF

የወሬው ባለስልጣን በሆንም ጉረኛ፣ ጉቦኛና ምቀኛ መሆኑን ነው ሁሉም የሚያወራው_»

ሁለት እጀን ራሴ ላይ አትሬ ጮህኩ።

«ሃና በቃሽ»

እስዋ ግን አልበቃትም።

«የሚያሳስበኝ ምን እንደሆነ ልንገርህ? ደህና ጭንቅላት ያላቸውና በለስ የቀናቸው በመንደራችን ውስጥ ቆይተው ለወገኖቻቸው ስራ መፍጠር ካልቻሉ የቢሾፍቱ ልጅነት፡ ከዙ ምን ትርጉም ይኖረዋል? የቢሾፍቱ ልጆች ተመስሰው የሚጠሩ ሰዎች ከአራት ሙቶ አመት በፊትም ነበሩ። አሁንም አሉ። ወደፊትም ይኖራሉ። የቢሾፍቱ ልጆች - በቢሾፍቱ ልጆች ይተካሉ። ያለፉት ለአሁኖቹ ከስንፍናና ከድህነነት ያለፈ የሚያወርሱት አንዳችም ቁም ነገር አለመኖሩ ሲታሰብ ልብ አይደማም? እስኪ ሳልፒና ቫርቴክስን አስብቸው። ቆዳ ሩብረካ ከፍተው ከሰባ በላይ የመንደራችንን ልጆች ከስራ አጥነት ማዳን ችለዋል። ሳልፒና ቫርቴክስ ወላሻቸው ሀገር የመሄድ እድሉ አያላቸው ሰምን እዚህ ሊቆዩ ወሰኑ? እዚህ ሀገር ያልተነካ ድንግል ሀብት መኖሩን ተረድተው ነው። እኛ ታዲያ ያልተነካውን ሀብት ማየት የምንጀምረው መቼ ይሆን?' ብዬ ሳስብ ተስፉ አቆርጣለሁ። ለምን በለኝ? በቂ ማስረጃ ሳቅርብልህ። ለእናታም ቢሆን እስኪ ለቢሾፍቱ ሀይቅ አስብ። የእሳ ስራዊት በሆዱ አቅፎአል። የቢሾፍቱ ሰዎች ግን ባለፉት ኋራት መቶ አመታት አሸቅና ሽር ነው የሚመገቡት። ኩሩ ያመጡና አድሰኛቹ የቢሾፍቱ አሳሞች ልክ እንደሰው ልጅ ሲያረጁ ነው ተፈጥሮአዊ ሞታቸውን የሚሞቱት። እንግዲህ የአመጋገብ ለውጥ ለማምጣት እንኳ ያልቻልን ነን እኛ የቢሾፍቱ ልጆች»

በዚህ መልኩ ለአንድ ሰዓት ያህል አወጋን_

ከቢሾፍቱ ሀይቅ የራስጌ ኮረብታዎች ላይ መቀመጥ መንፈስን ያድሳል። በዚህ ላይ ደግሞ ሃና ከጉኔ አለች። ውበትዋ ብቻ ሳይሆን ጨዋታዋም ይሞታል። መግባባት መቻልም ታላቅ ፀጋ ነው። ሌላው ቀርቶ እንደ ቀልድ ወዳጆችን የሆነውን ሀይቅ በሰውኛ ዘይቤ ያቀለልነው ባንድ ስሜትና ልብ ነበር። የቢሾፍቱ

ልጆች እንደመሆናችን በራስ ላይ ሲሰመቀለድ ከጥንት የወረስነው አውቀት ነበረን። እና ግዑዙን ሀይቅ በመነባንብ መልኩ እየተቀባበልን እንዲህ አልነው፤ እኔ ጀመርኩ፤ እሷ ቀጠለች

- ወዳጆችን ቢሾፍቱ ሆይ! የለየልህ ደጉብ መሆንህን አመን።
- በቦዶ ጉራ የምታቅራራ ደንቆሮ መሆንህን ተገንዘብ።
- የድህነት ማሰሮ መሆንህን ዕወቅ።
- ጉማህን አደጋፈርክ፣ ማዕበልህን እያገማሸርክ በሺህዎች አመት ኖረሀል።
- እና ምን ይጠበስ? ወደፊትም እንደተጉለትህ ትኖራለህ።
- የወርቅ ጭንቅላት ያላቸው ልጆችህ ወዴት አሉ?
- እንደ እንቆቁዚዮን የሚያብሩ ቆነጃጅት በዘሀቸው መንደር ተወልደዋል (ይህን እኔ ነበር

ያልኩት፤ ሃና ፈጠን ብላ ቀጠለች)

- የጣዘብ ሰዎች ከቢሾፍቱ አንበርት ላይ ብቅ ብለው ነበር። ጽሩ አላከበርካቸውም።
- እነዚህ ውዶችህ ታዲያ ዛሬ የት ናቸው?
- ጥለውህ ሲኮበልሉ አለማመስገህ ለምን ይሆን?
- ማመፁ ቢቀር ተንሰቅስቀህ ማልቀስ አይገባህም ነበርን?
- ለመሆኑ በስምህ የሚጠሩትን ብርቆች ትወዳቸዋለህ?
- አይመስለኝም፤ ወዳጅና ጠላትህን የማትለይ ደንቆሮ መሆንህ ሀቅ ነው።
- በድንቁርናህ ላይ የስንፍና ታማኝ ወንድም መሆንህ ሲታሰብ አይምሮ ይቆስላል።
- ለመሆኑ የምዕለት ቀን ሲመጣ ለስንፍናህ የሚከፈልህ ዋጋ ምን እንደሆን ትገነዘባለህ?

እንደ ቢተክርስቲያን ዝማሬ እየተቀባበልን ቢሾፍቱ ላይ የርግማን ዶፍ አዘንመን ስናበቃ ተያየንና ሳቅን። ሃና እንዴት ትጥማለች?

በዚህ መልኩ የአንድ ሰዓት ቆይታችን አበቃ። ውቢትዋ የመንደራችን ልጅ፤ ያቺ እንደ አስክንድር ምስሶ ከተቆሰስ አከርማ መሀል የምትመዘዘው የእንቆቁዚዮን ሰበዝ ተሰናብታኝ ልትሄድ ሆነ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሮችዋ በፊት ግን እንዲህ አለችኝ።

«ዋናውን ነገር ሳልነግርህ ረስቼው። በሚቀጥለው ሳምንት ጠቅልዬ አሜሪካ ወደሚባለው የስደተኞች ሀገር እየሄድኩ ነው።»

የመሰላኮ ያለህ!

«አብደሻል?» ስል ጮህኩ።

ድንገተኛ የብርድ ስሜት የሰራ አካሉቴን አናወጠው።

«የመነደፈ ልጅ ሆደ፣ ፍፁም ጤኛ ነኝ።»

ደህን ብላ በዘገን ንም የተሸፉን ፈጣግታ መገበቺኝ። አይኖቼን እፍጥጬ እንደተከልሀባት ደንዝዤያለሁ።

ሃና ቀጠለች፣

«ወርሃዊ ጥሩ ስራ አለኝ። የቤተሰቤና የኔ ኑሮ ግን መሻሻል አልቻለም። ስለዚህ ከባሌ ጋር ቺካጎ ወደተባለችው ከተማ እየኮድን ነው። እዚያ ሀገር ሀያ አመት ያህል ሰመስራትና ለመኖር ወስነናል።»

«ስለ ቪሻፍቱ ልጅነት ያወጋነው ሁሉ ፋይዳቢስ ነበር?» ስል በሞተ ስሜት ጠየቅሁዋት።

«አንድ እጅ ብቻውን አያጨበጭብም ብዬህ ነበር። በኛ ሀገር የህል ስውጥ ያስፈልጋል። ድንቁርናችንንና ስንፍናችንን የሚያስወግድ ስውጥ ካልመጣ በህገራችን ዕድገት ሀልም ነው።»

«እኛ ታዲያ የዚያ ስውጥ አንቀሳቃሽ ሞተር ስምን አንሆንም?»

ሃና ለስክንዶች ያህል ተደምማ ከቆየች በኋላ እንዲህ ስትል ጠየቀቺኝ፤

«ሮህንስን ታውቀዋለህ?»

«ሮህንስ?»

«መሞምቱ ሮህስ።»

«አዎን።»

«የሰውጥ መንገድ ጠራጊ ነበር። መንገዱን ጠርጉ ሲያበቃ በወጣትነቱ ምቶ። ወጀጅ ሆይኝ እኔ እህትህ መንገድ ጠራጊ ስመሆን የሚያህቃ ችሎታውም ሀን ወነው የለኝም። እውነቱን ልንገርህ? ራስ ወደድ ነኝ። ምቾት ደሞ አወዳለሁ። በርግጥ ድሮ ምቾትን አሳውተውም ነበር። አሁን ቀመስኩት። ስተምሰው ሳፈጠኝ። እውነቴን አይመስልህም?»

«አጠላሻለሁ ሃና» ብዬ ጮህኩባት።

ፈገግ ብላ በአትከሮች አስተዋለቺኝ። ታያየን። ከመቅሰበት አገባዋ በደማት አይኖችዋ ውስጥ ተጠቀጠቀ። ቅንድቦችዋን አርገበገበች። የምር የጥላቻ ቀስቶች ልቤ ላይ ይስነቁሩ ያዙ። ድንገትም ሀሚያቃስት ድምፅ ወረደነባት፣

«አድምጪኝ ሃና፣ ከስደት ውሳኔሽ ማንም ሊያግድሽ እንደማይችል አውቃለሁ። እንኮዋን የኔ ዲስኩር የከርሳሙና ነደደቡ የቢሻፍቱ ህይቅ ፍትር አንኳ አያቆምሽም። ግን አስኪ ለአፍታ ቆም ብለሽ አስቢ። ከዚያ አመት በኋላ አንቺ ማነሽ? የቢሾፍቱ ልጆች ሁሉ ይረሱሻል። አንቺም ቢሾፍቱን ትረሺዋለሽ። ርግዮ ነውና ወጣትና ቁንጅ ሰላሆንሽ በሰው ሳብ የሰለጠነውን የሩቅ ሰዎች ምድር ያለብዙ ችግር ትለምጂዋለሽ። ጥሪት ለመያዝ ደፋ ቀና ማለትሽም አይቀርም። ታዲያ ጉልበትሽ ያለርህራሄ በጭካኔ ተመነምሖም ቢሆን ለአንድ የፈረንጅ ቡሀቃ የሚሆን ያህል መዛዋጠር አያቅትሽም። ከዚያስ? ሰዎች ያልፋሉ፤ ተራሮችና ህይቆች ግን ይናራሉ አንዲሉ ከአመታት በዙዋላ በወርቅ ኮሚሽመተው የምኞት ኮረብታ ወዲያ ማዶ ያለው ከወገኖችና ከልማድ የመራቅ የህይወት መራር እውነታ እንደ ወረቀት የነጣ ልብሽን በስል መርፌ እየጠቀጠቀ ያደማዋል። አመኚኝ ሃና...»

አቋረጠቺኝ።

«... ያልከው ሁሉ ታሪካዊ ተረት ነው። እውነት ቢሆንም ዋጋቢስ እውነት። ባጭሩ ልንገርህ? ድህነትና ስንፍናን ላለመውረስ መሸሸለሁ። ዶክተር ባሁሩ ልክ ነበር።»

«ድሀች ነን ሃና። ሆኖም ግን የቢሾፍቱ ልጆች ነን። ታዲያ ኮሽነታችን ወዴት ማምለጥ ይቻለናል?»

«የምትለው ይገባኛል። ፍልስፍና ሰተርክፈከፈበት እምነት ስል ግን ተጨባጭ ምክቴን መሰጥት ተስኖኛል። ብዙ አስቤበት ነበር። በስራ ምክንያት ካደጉ አገሮች መዲናዎች ደርሼ በመጣሁ ቁጥር ግን በትውልድ መንደሬ ከወገኖቼ ጋር የመኖር ሞራሉ እየመጣኝ ሄደ። በኛ ሀብ ነጥስ ከምትዘራው የካሄር ጭራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ እንኳ መድረስ አንዳልቻልን ታውቃለህ?»

ከሃና ጋር ዘለሁ ተሰየየን።


እኔን ተስፍቢት የቆዳ ፋብሪካው ስራ አስኪያጅ ለሀገሙ ሀንዳዊ ለሳልፒ የሚሰጥ አንድ ማስታወሻ ቢጤ ሰጥታው ስትነጉድ ከጀርባዋ አየሁዋት። እና ሃና ሄደች። በአይኔ ተከተልኩዋት። ከመኪናዋ አጠገብ ደረሰች። አረንጉዋዴ ቱሉታ ሲፍትባ መኪናዋ አጠገብ ስትደርስ ድንገት ወደኔ ዘወር አለች። በርታት ተንጨን – አይን ለአይን። ሰስንዝብት አጅዋን አወዛወዘችልኝ። ምላሽ ሰጠሁዋት። «ለዘልዓለሙ» የሚል ታልም ወደ ልቢ መጣ። በተከፉ ስሜት ፊቴን ወደ ገበሙ-ኖው ሀይቅ መለስኩ። ማየት አልቻልኩም። ብሸር አሰብኝ። እያነባሁ ይሆን? ግን ለማን? ስራሊ? ለሃና? ወይስ ለቢሾፍቱ ልጆች?

ዱሩ የቢሾፍቱ ልጆች ልብ ከጣና ሐይቅ ልጆች ልብ በምን ይለያል? ግን ደሞ ለምን የጣና ልጆች ብቻ? የዳቡስ ልጆች – የተዘሬ – የአዋሽ – የአዳይ ልጆች። የአሸንጌ - የላንጋኖ - የበልበላ - የጨለመበዘት ልጆች። የፊንጫፈ - የጉጅብ - የጣሮ - የሻሾማ ልጆች። የአሞ - የኩልመስክ - የድብዙ ልጆች - የቢሾፍቱ ልጆች። እምን ቢሾፍቱ የጣና ሐይቅ ምሳሌ ነው። ጣና ደግሞ የቫክቶሪያ ሐይቅ። ቪክቶሪያ የታንጋኒካ፣ ታንጋኒካ የዙምበዚ ምሳሌዎች ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ ታዲያ እንዲህ ስል አንጉራጉራለሁ።

የአፍሪቃ ምድር ሰዎች ከጦርነት የሚላቀቁትቡት፣ ከስደት ወደ ስደት መንከባሻቸው የሚያከትምበት፣ በረሃብ መጠበሳቸው የሚያቢቃበት የተስፉ እስት መቼ ይሆን?

ልቦለድ



ዳንኪሪኞቹ ጎፈሬት

ቴዎድሮስ ተፈረደኝ

ዳንኪረኞቹ ነፋሳት አውሪቂስ፣ ቶርኔዶና «የአሿራው ዲያቢሉስ» ይባላሉ። በውትያኖስ በባህርና በትላልቅ ኃይቆች ዳርቻ በሰፈሩ ነዋሪዎችና በመርከበኞች ዘንድ የታወቁና የተፈሩ ናቸው። ገና ውሃው መተራመስ ሲጀምርና ማእበሉም እያየለ ሲመጣ በአካባቢው ያሉ ሁሉ አይኖቻቸውን ወደዚያ በመወርወር ይጠባበቃሉ። የመጀመሪያዋን ቀለበት መሰል ነገር በውሃው ላይ ይፈልጋሉ። ቀለበትዋን ሲያዩ ታዲያ እግሬ አውጭኝ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

እናኒ በውሃ ላይ እየጣዙ የሚጓዙ ቀለበት መሳይ ነገሮች የደረሱበትን ነገር ሁሉ በኃይለኛ ጉልበት የሚውጡ የባሕር አሮች እንደሆኑ ስለሚታወቅ የሚደፍራቸው አንድ ስንኳ የለም። አሽከርክሪት (Whirs pool) በመባል ይታወቃሉ። ልክ እንደተዘቀዘቀ ደወል ከላይ ሰፊ ሆነው ከወደታች ጠባብ የሆኑ የውሃ ላይ ጉድጓዶች ናቸው። በብዙ ዎች ዘንድም ይፈራሉ። በመንገዳቸው የሚያጋጥማቸውን ማንኛውም ነገር በትዕበት ፉት ብለው ይውጡታል።

አሽከርክሪቶች ከውሃ ላይ የሚነሱ ቢሆኑም በውሃ ላይ ተወስነው ግን አይቀሩም። በከፍተኛ ፍጥነት የሚሽከረከሩ በመሆናቸውም ከበላያቸው የሚገኘውን አየር ያጠቡታል። እንግዲህ ይህ የሚጠባ አየር ነው ውሃውን ጥሰው በመውጣት አውሎ ንፋስ ሆኖ በአካባቢው በሚገኙ መሬቶች ላይ የሚከሰተው። በመሬት ላይ የሚያገኛቸውን ቀላል ነገሮች እያንገዋለለ፣ አፈራ እያበነነ የሚጓዘው ይህ ንፋስ በሩቅ ምስራቅ አገሮች «የአቧራው ዲያቢሶ»ስ» በመባል ይታወቃል። በአገራችን አውሎ ንፋስ የምንለው አይነት መሆኑ ነው። በአብዛኛው የሚከሰተውም በረሃማና ሚዳማ በሆኑ አካባቢዎች ነው።

የአቧራው ዲያቢሶስ ምንም ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከጠራ ሰማይ ላይ ድንገት ከተፍ ብሎ አሰልቺውን ሞቃታማ የበረሃ ተሲያት ለማስዋብ የተሳነ ጸንኪረኛ ይመስል እየተውረገረገ ያልፋል። በአብዛኛው መስታውት ከመስበርና ፊቱ የሚያገኛቸውን እንደቆሻሻ ማጠራቀሚያ ያሉ ቀላል ቁሳቁሶች ከመድፋት ያለፈ ጉዳት አያደርሰም።

ግና በአይነቱ ከዚህ ንፋስ ጋር የሚመሳሰል በኃይሉ ግን እጅግ የሚበረታ ሌላ የነፋስ አይነት አለ። ይህ አደገ ከሚፈሩትና ሚስጥራዊ ከሆኑት የአየር ነውጦች አንዱ የሆነው ቶርኔዶ የሚባለው ወጀብ ነው። ቶርኔዶ በከፍተኛ

ኃይል የተሞላ እየተጠመለመለ የሚጓዝ ወጀብ ነው። በሰዓት እስከ 320 ኪ.ሜ በሚደርስ ፍጥነት ይጓዛል።

የቶርኔዶ ወጀብ ከግዙፍ ጥቁር ደመና ስር በመነሳት ወደ መሬት የሚወርድ ቱቦ መሳይ ደመና ነው። ብዙውን ጊዜ እንደስፖሪንግ ወደ ላይና ወደ ታች በመለጠጥ ተመልሶ ወደ ስሜናዊ ምስራቅ አትጣጫ ይጓዛል። ምንም እንኳ የቶርኔዶ ወጀብ በመላው ዓለም የሚከሰት ቢሆንም በአብዛኛው የሚታዩት ግን በሰሜን አሜሪካን በሩት ምስራቅ አካባቢዎች እንደሆነ ተዕፎአል። በየአመቱ በሰሜን አሜሪካ ብቻ እስከ 700 የሚደርሱ ቶርኔዶዎች እንደሚከሰቱም ተመዝግቦአል።

በምድር ላይ ከሚከሰቱ የአየር ነውጦች በኃይለኛነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ሌላው ወጀብ ደግሞ አውሪቁስ (ሽሪኬን) የምንለው ነው። ይህ ወጀብ ስሙን ያገኘው ጥንት በአውስትራሊያ አበርጊንስ ውስጥ ይገኙ ከነበሩ ትሪያኖ ከሚባሉ ገሣዎች ነው።

ምንም እንኳ እነዚህ ገሣዎች ከተማቸውም ሆነ ስልጣኔያቸው ከምድር ገፅ የጠፋ ቢሆንም በዘመኑ ግን በስልጣኔ የሚወዳደራቸው እንዳልነበረ ታሪክ ያስረዳል። ለእመት ለጥቶው የነባቷትን ከተማ በደቲታ በማፈራረስ የብዙዎችን ህይወት የሚቀጥፈውን ይህን ወጀብ የሚከላከሉበት ምንም አይነት ሰብአዊ ኃይል ስላልነበራቸው ወጀቡን እንደአምላክ በመቁጠር የሰውና የእንስሳ መሥዋእት ያቀርቡለት ነበር። ወጀቡ ስሙን ያገኘው ሂዩራኬን (የስይጣናት ሀሳ አለቃ) ብለው ከሚጠሩት አማልእክት ነው።

ሽሪኬን (አውራቁስ) በምድር ላይ ከሚከሰቱ የአየር ነውጦች በኃይለኛነቱ ተወዳዳሪ የለውም። ከቶርኔዶ የሚለየውም በአብዛኛው ውሃ ተሳቅሎ ከገናብ ጋር አብሮ የሚመጣ በመሆኑ ነው። በአማርኛችን አውራቁስ ይባላል።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሳይንቲስቶች መላ ምት ከሆነ የአውራቂስ ወጀብ ኃይል በአንድ ደቂቃ ውስጥ አንድ ሺህ አቶሚክ ቦንቦችን ብናፈነዳ ከምናገኘው ኃይል ጋር ይመጣጠናል። ይህ ወጀብ አልፎ አልፎ በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የሚከሰት ባይሆን ግን በምድር ላይ ህይወት የሚባል ነገር ባልኖረም ነበር።

በእነዚህ ኃይለኛ ወጀቦች ተመትተውና ጉብረታቸው ፈራርሶ በህይወት የተረፉ ጥቂት ሰዎች አሉ። ከነዚህም ሰዎች መሀከል ካፒቴን ሆል አንዱ ነው።

በሚጫጫነው ሞቃታማ የግንቦት ከሰአት አየር ካፒቴን ሆል ከቤቱ በስተጀርባ በሚገኘው ሜዳ ላይ ተንጋሎ ከባለቤቱ ጋር ያወጋል። በደቡባዊ ምስራቅበኩል በተደጋጋሚ የሚበርቀውን መብረቅ ያስተዋለ ቢሆንም እንከ ትኩረት ሊቸረው ግን አልፈቀደም ነበር። በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆዩ ከበስተደቡብ በኩል የኃይለኛ ንፋስ ድምፅ በመስማቸው አንገታቸውን ወደዚያው ሲያቀኑ በአካባቢው የነበሩ ዛፎች ሁሉ ወደ አንድ ጉን አዝምመው ተመለከቱ።

«ኃይለኛ ንፋስ እየመጣ ነው» አሰኝው ባለቤቱ የፍርሀት ቃና ባዘለ ድምፅ። ለምን እንደሆነ ባይገባትም ውስጧ በጣም ፈርቶአል።

ካፒቴኑ ምንም መልስ አልሰጣትም። በልቡ የንፋሱን ፍጥነት ያሰላል።

«እባክህ ወደ ቤት እንግባ» አለች ባለቤቱ።

«እቤት መግባት ከምን ያስጥለናል ብለሽ ነው? ሞት ከመጣ እንደሁ ያው ነው ቤት ሆኑ ውጭ ማምለጥ አይቻልም» ሲል መለሰላት።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ሰጆሮ የሚሰቀጥጥ፣ ሰብሰናን የሚንጥ ነገድንድ አስተጋባ። ባልና ሚስቱ በድንጋጤ ተቃቀፉ።

ካፒቴኑ ከተቀመጠበት በመነሳት ወደ ምዕራብ

ተመለከተ። አድማ ግዙፍና እንደ ጥላሸት የጠቆረ ደመና አድማሱን ሙሉ ለሙሉ ጋርዶታል። ከዚህ ደመና ስር ደግሞ የተጠበሰለ መጋረጃ የሚመስሉ መለስተኛ ጥቁረት ያላቸው ደመናዎች ይታያሉ። ካፒቴን ሆል ሚትሮሎጂስት በመሆኑ የዝናብ ዳመናዎች እንደሆኑ ለመገመት አልተቸገረም፣ መለስ በማለት ወደ ባለቤቱ ተመለከተ። አርሷም ፊዛ ስማይ ሰማዩን ትመለከታለች። አየር ሲለወጥና አየቀዘቀዘ ሲመጣ ታወቀው። ከዚህ በኋላ የተመለከተውን እንዲህ ሲል ይገልፃል።

«በግምት ከአራት ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኘው ጥቀርሻማው ደመና በቀጥታ ወደ እኛ እንደሚገሰግስ አስተዋልሁ። ዳመናው የመድፍ አፈሙዝ የሚመስል ወደ ምድር ዝቅ ብሎ የወረደ አፍ አለው። አንዳች የሚዘውረው ነገር ያለ ይመስል በከፍተኛ ፍጥነት ይሽከረከራል። አስከ አሁን ድረስ ከበስተደቡብ በኩል ሲነፍስ የቆየው ንፋስ ፍጥነቱን እየቀነሰ ሲመጣ ታወቀኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደግሞ አትጣጫውን ቀይሮ ከበስተደቡባዊ ምስራቅ በኩል በቀጥታ ሳያቋርጥ ወደ ጥፋሩ ደመና በከፍተኛ ፍጥነት መጉዋዝ ጀመረ።

እንደ መድፍ አፍ ከሾጠጠው ደመናና ከመሬቱ መካከል እጅግ ግዙፍ የመብረቅ ብልጭታዎች በተደጋጋሚ ይብለጨለጩ ጀመር። አንደኛው መብረቅ አልፎ ሌላኛው እስከሚጀምርበት ባለችው ጥቂት የዐጥታ ቅፅበት ውስጥ በሩቅ ያለ አውሮፕላን የሚያስማውን አይነት ድምፅ ይሰማኝ ነበር።»

ከዚህ በኋላ ነበር አንግዲህ ካፒቴን ሆልና ባለቤቱ በፍርሃት ተውጠው አየተራራጡ ወደ ቢታቸው የገቡት። ብዙም ሳይቆይ አካባቢው ሁሉ በጥቁር ደመና ተሸፈነ። ጠብደል በረዶዎችም በቤቱ ጣራ ላይ ይዘንቡ ጀመር። ቤቱ በአራቱም አትጣጫ መብረቅ ይብለጨለጭ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካፒቴኑ በፍርሃት ተውጦ በየክፍሎቹ እየተዘዋወረ ሲመለከት በምእራብ አቅጣጫ ያለው የቤቱ ግድግዳ እንደ እንዳች ሲነዝር ተመለከተ። ከወደ ኮርኒሱ በኩልም ወደ ውስጥ ማጋደል መጀመሩን በማስተዋሉ እንዳይደረመስ ሰጋ። ካፒቴኑ ከዚህ በኋላ የተመለከተውን ደግሞ እንዲህ በማለት ገልያታል።

«ለምድር ቀርበ የሚበር ጀት በሚያሰማው አይነት ድምፅ ጆሮዎቼ በመደንቆራቸውና ሊደረመስ እንደሚችል በመገመቴ ክፍሱን ጥዬ ለመውጣት ወደበሩ ሳመራ አንድ ሌላ የሚያስገርም ነገር ተፈጠረ። የማላያቸው እጆች ጆሮዬን ደፍነው የያዙት ይመስል እንደዚያ ሲያደነቁረኝ የነበረው ጩኸት በቅፅበት ውስጥ ፀጥ አለ። በጆሮ ግንዴ ስርና በአናቴ ላይ ከምትነዝረው ልቤ በስተቀር ምንም የሚሰማኝ ነገር አልነበረም። ቤቱ እንደ አንዳች ነገር ሲርድ ግን ይታየኝ ነበር። ወዲያውም በክፍሉ መ@ጫ በር በኩል ልዩ ብርሃን አንበባረቀ። ብርሃኑ ሰማያዊ ቀለም ያለው በመሆኑ ክፍሉ በአሳት የጋየ መሰለኝና ተጨነቅሁ። አይኖቼን ወደነ ክልክም የመስኮቱ መጋረጃዎች ሽቅብ ተገልበውና ከኮርኒሱ ጋር ተጣብቀው ተመለከትሁ። መጽሐፎች፣ መፅሄቶችና ወረቀቶች በመውጫው በር ላይ ተከምረዋል፣ በወለሉ ላይም በርካታ ወረቀቶችና መፅሃፎች ተበታትነው ይታዩኝ ነበር። በአየር ላይ የሚሽከረከሩም ነበሩ።

ድንጋጤዬ መለስ ሲልልኝ የቤቴን ጓሮ ለመመልከት በማሰብ ወደነው ተነሳሁ። ገና ሁለት እርምጃ እንኳ ሳልራመድ እንዳች ነገር ቤቴን ሲገፈው ተሰማኝ። መራት ከዳኝና ተንበረከክሁ። ወዲያውም ባርኒጣዬ በኃይለኛ ጉልበት ተመንጥቃ ከሳዬ ላይ ስትወሰድ ተሰማኝ። በአካባቢው የሸሩ ነገሮችም ሁሉ ወደ ላይ መበረር ጀመሩ። በዘህን ጊዜ ነበር የቤቴ ጣራ መወሰዱ የገባኝ።


እንደምንም አየተውተረተርኩ ስነሳ እንደገና ኃይለኛ ጩኸት አስተጋባ። በከፍተኛ ጉልበት ተገፍትሬም በጀርባዬ ምድጃው ውስጥ ተወተፍኩ። በምእራብ በኩል የሚገኘው የቤቱ ዳርቻ በሳዬ ላይ ተደረመሰ። እንደ አድል ሆነና የከፉ ጉዳት ስላልደረሰብኝ ተረፍኩ። የተሰማኝን ስሜት ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል። ለቤቱ ከማዘን ይልቅ ባየሁት ውበት እጅግ ተደንቄ ነበር። በእነዚህ ከአመት በላይ ረኻቦም በሆኑብኝ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የተሰማኝንና ያየሁትን ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል። ማለት የምችለው ዝም ብቻ ነው፣ እንዲያው ዝም።»

የአውራቂስ ወደብ አሩቅ ምስራቅ አካባቢ በሚገኙ አገሮች ዘንድ ታይፋን በመባል ይጠራል።


በአውራቂስ የተነሳ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶአል። በታሪክ ከተመዘገቡት የተፈጥሮ አደጋዎች ሁሉ በመጥፎነቱ የተመዘገበው በጥቅምት 1737 በቤንጋል ሰርጥ በተከሰተው ታይፋን የደረሰው ነው። ንፋሱ ሲያቆም የ300ሺ ሰዎች ህይወት ጠፍቶና አካባቢው መሉ ለመሉ ከሰው ፀድቶ ነበር። በዚያ አደጋ ብቻ ከ20ሺ በላይ መርከቦችና ጀልባዎች ሰምጠዋል።

እ.ኤ.አ በ1991 ፓኪስታንን የመታውና ለ150ሺ ሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው ታይፋንም በከፍተኛነታቸው ከሚጠቀሱ የተፈጥሮ አደጋዎች ይመደባል። ባለንበት ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በሰሜን አሜሪካ ቴክሳስ ውስጥ ተከስቶ የነበረው አውሬቂስ ደግሞ ከፍተኛ ንብረት ካወደመባት መካከል ይጠቀሳል። ይህ አውሬቂስ በጥቂት ሰአታት ውስጥ የ6000 ሰዎችን ህይወት ቀጥፎአል፣ ወደ 20 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ግምት ያለው ንብረት አውድሞአል።

t.me/OLDBOOKSPDF



አባይ! አባይ!
ያገር አባይ!
ያገር ሲሳይ
ያሳገሩ ዘምሮ!
ያንን ጋራ ዞሮ!



የሱ-ተፈው ጦስ

ሻምበል የሰራህይወቅ

በደርግ ጊዜ ከነበሩት የጦር ኃይል አካላት አንዱ «ሶስተኛው አብዮታዊ ሰራዊት» (ሶአሰ) ነበር። በ1981 ይህን ጦር እንዲያጠናክሩ ከተቋቋሙት ክፍሎችም አንደኛው 26ኛው «ወላፈን» ክፍለ ጦር ነበር። ቀጥሎ የምተርክላችሁ ወንጀል የተፈፀመው በዚሁ ክፍለ ጦር ውስጥ ነው።

ከደሴ ወደ ኩታበር በሚወስደው መንገድ 12 ኪሎ ሜትሮች ያህል እንደተጓዝን ለጥ ያለውንና በብዙ ዐሐጥትና የሙዚቃ ባለሙያዎች የሚወደሰውን የአላሻን

t.me/OLDBOOKSPDF

ረግረጋማ ሜዳ እናገኛለን። እዚህ ስፍራ የክፍለጦሩ ጠቅላይ መምሪያ ይገኛል። ከጠቅላይ ሰፈሩ ፊት ለፊት የሚገኙትን ተራሮች መሀል ለመሀል ሰንጥቆ በሚሄደው የበጋ ጥርጊያ መንገድ አምስት ኪሎ ሜትር እንደተጓዙም በአካባቢው መጠሪያ 'ዋሌት' የሚባለውንና የ264ኛ ብርጌድ ማዘዣ ጣቢያን እናገኛለን።

የሐምሌ 1982 ደመወዝ የሚከፈልበት ወቅት ነበር። የጦሩ ክፍሎች ገንዘብ አውጥተው ለአባላቱ በማከፋፈል ላይ ናቸው። የመቶ አለቃ ደሳለኝ ቹሌራም (የ264ኛ ብርጌድ የፋይናንስ መኮንን) ከአንድ መቶ ሺህ ብር ያላነሰ ገንዘብ ወጪ አድርገው አብዛኛውን ከከፈሉ በኋላ ሰነዱንና ቀሪውን ገንዘብ (በግምት ሰላሳ ሺህ ብር) ሳምሶናይታቸው (አነስተኛ የገንዘብ መያዣ ሻንጣቸው) ውስጥ ከተው በአካባቢያቸው የገንዘብ ካዝና ስለሌለ የአካባቢው ጥበቃ እንዲጠናከር አድርገው ቦርሳውን ተንተርሰው ይተኛሉ። ሆኖም ሚት ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ሳምሶናይቱ የለም። እሪ ይላሉ። አገር ይረበሻል። ወዲያውኑም ጉዳዩን የቅርብ አለቆቻቸው ለሆኑት የብርጌድ አመራር አካላት (ለአዛዦ፣ የፖለቲካና የወታደራዊ ደህንነት ጥበቃ ኃላፊዎች) ያመለክታሉ። ኃላፊዎቹም እቦታው ድረስ በመምጣት ጉዳዩን ካጤኑ በኋላ ፍተሻ እንዲካሄድ ያደርጋሉ። ውጤት ባለማግኘታቸው ግን ማንኛውም ሰው ከከለሉ እንዳይወጣ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥተው በደረጃቸው ለየአለቆቻቸው ዘገባ ለማቅረብ ወደ ክፍለጦሩ መምሪያ ይሄዳሉ።

የክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል ክበደ ደበሳ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊውን ሻለቃ ከበደ ነጣምን (በወቅቱ ሻምበል) በማማከር የብርጌዱን የገንዘብ ቤተ መኮንን፣ የአራተኛ ሻለቃ የአስተዳደርና የድርጅት

መኮንኖችን፣ እንደዚሁም ደግሞ የብርጌዱና የሻለቃዎች ሂሳብ ቤት ሰራተኛ ወታደሮችን ወደ ደሴ ማዕከላዊ ምርመራ እንዲላኩ ያደርጋሉ።

ከአስር ቀናት ግርፊያና ድብደባ በኋላም የብርጌዱ የገንዘብ ቤት መኮንንና ሂሳብ ሰራተኛው ሲቀሩ ሌሎቹ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። በክፍለጦሩ ዋና አዛዥ በነባ ለተሰቀቱት ሰዎች የቀረበው የሽንገላ ቃልም «እይዟችሁ፣ የወንጀሉን አቅጣጫ ለማወቅ ሲባል ህይወትም ሊጠፋ ስለሚችል ከዚህ መትረፋችሁ ሊያዕናናችሁ ይገባል» የሚል ነበር። የሞራል ካሳ እንዲሆናቸው ፈቃድ ተሰጣቸው። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ ተረሳ።

በጥቅምት ወር አጋማሽ፣ 1983 ላይ ግን አንድ ወታደር ከባለገሠሉ ከፍተኛ ልዩ ዕጣ መካከል የሁለተኛውን የአራተኛው ዕጣ እንዲሁም አምስት የማስተዛዘኛ ዕጣዎች በድምሩ ብር አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ አስር ብር የደረሰው መሆኑንና የሁለተኛውን የአራተኛው ዕጣ ቲኬቶች ከመታወቂያ ወረቀቱና ሰላሳ ብር ጋር የጠፋበት መሆኑን ለማመልከት ከፍለጦሩ ጠቅላይ ሰፈር ድረስ ይመጣል። እንዴት ሊሆን እንደቻለ እንዳንድ አባላት ለወታደሩ ጥያቄ ያቀርቡለታል። ወታደሩም ቀደም ሲል ህክምና ሲከታተል ቆይቶ በማገገም ላይ እንዳለ ከገለፀ በኋላ በዚያን ወቅት አንድ አስተኛ ቴፕሪኮርደሩን በመሸጥ ከሰላሳ በላይ የባለገሠሀን የሎተሪ ቲኬት በመግዛት እያንዳንዱን ቁጥር በወረቀት ላይ መዝግቦ በዘመዶቹና በጓደኞቹ ስም በዝርዝር ዕጩ እንደነበር ያስረዳል። የሎተሪ ዕጣው አሸናፊ በይፋ እንደተገለበም አንድ የሎተሪ ማውጫ ኩቲኬት አዟሪዎች ተቀብሎ ከራሱ ሎተሪ ጋር ካስተያየ በኋላ የደረሱትን የሎተሪ ዕጣዎች በመለየት ለብቻ አስቀምጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያልደረሱትንም ለብቻ ለይቶ ከገራዶ ወደ ከፍለ ጦሩ ጠቅላይ ሰፈር አላሻ በመምጣት ላይ እያለ 'አሸናፊ' የሆኑት ቲኬቶች ከላይ እንደተገለፀው የጠፉበት መሆኑን ይገልፃል። አብዛኛው ሰው በጥርጣሬ «እንዴት ሊሆን ይችላል?» በማለት ሲጠይቅ፣ የተቀረው በማለሰቡ ንዝህላልነት እየተናደደ የአድሱን አስገራሚነትና ጠማማነት ሲያወሳ ከረመ። ወታደሩም አቤቱታውን በቃል ለክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ አቅርቦ ስለነበር አዛዥ መኮንኑም አስቸኳይ ትእዛዝ ለአስተዳደር መምሪያው አስተላለፉ። ትእዛዙም ደሴ ለሚገኘው የብሄራዊ ሎተሪ ቅርንጫፍ ዕህፈት ቤት የተላከ ሲሆን፣ የ2ኛና ፡ኛ የባለዝሆን ክፍተኛ ልዩ ፅጣ አሸናፊ በከፍለጦሩ ውስጥ እንደሚገኝና ቲኬቱ ለጊዜው የጠፉ ስለሆነ ግን ሌሎች ግለሰቦች በማጭበርበር ገንዘቡን እንዳይቀበሉ እንዲደረግ የሚያዝ ነው።

ከሶስት ቀናት በኋላ የክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ ከአንዳንድ መኮንኖችና የበታች ሹማምንት ጋር ባሉበት ሰዓት አሸናፊው ወታደር የደስታ ስሜት ፊቱ ላይ እየተነበበ መጥቶ የሞቀ ወታደራዊ ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። በመቀጠልም የጠፉበትን የለ-ተሪ ቲኬቶች፣ መታወቂያውንና ሰላሳ ብሩን ሽንት ቤት ውስጥ እንዳገኘ ይናገራል። አዛዥ መኮንኑም አዕሩቂ የደስታ ስሜታቸውን እጁን በመጨበጥ ይገልፀ-ሰታል። ይሽኔ በአካባቢው የነበረው ሰው በሙሉ በጣም ተደነቀ። የወታደራዊ ደህንነት ጥበቃ ኃላፊ የነበሩት መኮንን ግን «ቲኬቱ የት አለ?» በማለት ጠየቁት። ወታደሩም የለወጠው ቅጠልያ ልብስ ውስጥ እንደረሳው ገለፀላቸው። ሰው ወታደሩ ላይ ይጮህበታል። «አሁንም ትጥለዋለህ! ጥንቃቄ አድርግ እንጂ» አሉት። በተለይ ዋና አዛዥ ይህ ይህን ጉዳይ ጫንና ረገጥ አድረገው ተናገሩት።

በዚህ እንዲለ ወታደሩ ትጠልያ ዩኒፎርሙ ላይ ደርቦ በለበሰው የሲቭል ጃኬት የውስጥ ኪስ ውስጥ ገንዘብ ይታይ ነበር። ኮሎኔሉም ዓይናቸውን በቀጥታ ብሩ ላይ በመወርወር «አሱ የያገከው ገንዘብ ምንድነው?» በማለት ጠየቁት። ወታደሩ ጉልድና፣ ባለ አማርኛ «አሄማ አርሶ ሽለ.ማት ናው። አርሶ አኝ አባቲና አዛዥ አዴሉም። ሱገ ሂዝለ። ማቹም እኔ ዴስታ አርሶ ናው» አለ። ወታደሩ ለማለት የፈለገው ግልፅ ነበር። አሱ የሙዩ ሰማንያ ሽህ ብር ባለቤት በመሆኑ ለሚወጣቸውና ውለተኛ አዛዡ ሱፍ ልብስ ሊገዛላቸው ነው። አሁንም የደህንነት መኮንኑ «ገንዘቡን ከየት አመጣኸው?» ሲሉ ጠየቁት። ወታደሩም «ኢሄ! ደሴ ባህራዊ ሎቶሪ ጥፋት ቤት መስተናባራ ቢሉ አንድ ሽ አሚሲቲ ማቱ ብሪ ሳጣ። ዋዳጊት አጋር ቤቲ ሄዶ ጋንዘቡ ሲራካብ ካጊላል አሉ።»

«የምን ማስተናበሪያ? እንደዚህ አይነት ነገር አለ እንዴ?» ወታደሩ አሁንም ፈጠን ብሎ «ኢሄ! አሴ! ማስተናገጃ ተብሎ ሳጣል። ሎቶሪ ኃላፊ ባንክ ቤት ሄዶ ማጣ፣ ሳጣ» አለ።

አዛዥ መኮንኑም «ቆይ! ቆይ! እኔ ይህንን አልፈልግም፣ ስራከህ አድርገው» በማለት ከእንጉት በላይ ሰናገሩ፣ በቦታው የነበሩት በሙሉ «እንዴ! ጓድ ኮሎኔል ይሽማ የልጁ መብት ነው። የደስታዬ ነው ብሎ ሲሰጥዎት ይቀበሉ እንጂ። ሙቀበል አለብዎት፣ ነውር ነው» የሚል ሀሳብ ሰነዘሩ። ኮሎኔል ክበደም ሲጋራቸውን አውጥተው ከለኩሱ በኋላ «ና! ና! አያስፈልግም። በፍፁም አይሆንም!» በማለት ተግደረደሩ። የደህንነት መኮንኑ ሬጋ ብለው «ኧረ ጌታዬ ምን ችግር አለው? ይሄ አኩ የወታደሩ የግል ስጦታ ነው። መቀበል ይኖርብዎታል» ሲሏቸው ግን ቀድሞውንም የመኮንኑን

t.me/OLDBOOKSPDF

ቃል ሲጠባበቁ የቆዩ ይመስል ዓይን ዓይኑን አይተው
«እናንተ ካላችሁ ምን ቸገረኝ፤ ስንት ነው አስሂ
ቁጠረው!» በማለት የደህንነት ኃላፊውን አዘዙት።
ቆጠረው። አንድ ሺህ ብር መሆኑንም አረጋግጠ
አስረከባቸው። ኮሎኔሉ ገንዘቡን ከተቀበሉ በኋላ «ለግሌ
የማውለው አይሆንም። ገንዘቡ በጠቅላላ ለመኪናዬ
ጥገና ይውላል» በማለት ገንዘቡን ቢሮአቸው አስቀምጠው
ተመልሰው መጡ። እንደ ወታደሩ በላቸውም ላይ
የደስታ ስሜት ይነበባል።

ኮሎኔሉ ከሌሎች ወታደራዊ መኮንኖች ጋር ሲተያዩ
ግርማ ሞገስ የማይታይባቸውና ያልሆኑትን ሆነው
ለመገኘት የሚጥሩ ሰው ናቸው። በደረሰባቸው የመቁሰል
አደጋ ይሁን ወይም በሌላ በሚራመዱበት ወቅት የግራ
እግራቸው ይጎተታል። በቶሎ የሚበሳጨውና በትንሽ
ነገር ደግሞ ደስታ የሚያሰክራቸው ናቸው። ሲጋራ
በብዛት ያጨሳሉ። በዚሁ ሳቢያ ሳይሆንም አይቀርም
የምግብ ፍላጉታቸው ደካማ የሆነው። ውሀዋን እንኳን
አይጠሉዋትም። ኮሎኔሉ አሰብ አድርገው «የት ሂደ?»
ሲሉ ጠየቁ። ወታደሩ ቀረበ። አድማቂዎች «ጌታዬ፤
በገንዘቡ ምን እንደሚያደርግበት እስቲ ይጠይቁት»
ሲሉ ተንጫጩ። የእርላቸው ፍላጉት ና ጥያቄም ይኸው
ቢሆንም «ዎች አውት!» አሉ። ይህ ሁልጊዜ ክሰተር
ማለታቸውን የሚገልፁበት ቋንቋ ነው። በጣም ሲናደዱ
ደግሞ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ የሩሲያንኛ ስድብ አላቸው -
«ዩፐቶማይት» የሚሉት።

«አሁን የት ሂደህ ነው ገንዘቡን የምትቀበለው?»
«ጌታዬ! አገር ቤት ናው»
«አገርህ የት ነው?»
«ሲዳሞ ክፐላጋር ና»
«አናትና አባት አለህ?»

«አዎ»
«በገንዘቡ ምን ታደርግበታለህ?»
«ኢንጊዴ በማሻመራ ቤት ኢሰራል። ክዛ ደሞ
እንዳሉኔታ ናው»
«በጣም ጥሩ ነው። ግን ተመልሰህ ትመጣለህ?»
«ኢንዴ? ታዳ ሚን ኢሰራል? በሶስቲ ዋር ተማልስሼ
መጣሉ!»
«አህ! የምትፈልገውም የሶስት ወር ፈቃድ ነው
ማለት ነው? በሱ ለም/መ/አለቃ ጌታቸው ትርፌ ንገሩትና
ይፃፍለት»
ይህ ድርጊት ከተፈፀመ ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን
ለኮሎኔል ከበደ ደበሳ ከደቡብ ወሎ አስተዳደር አካባቢ
ማዕከላዊ ምርመራ አንድ አስደንጋጭ መልዕክት
ደረሳቸው። ለመጥፎ ድርጊቶቻቸው ሁሉ ተባባሪ
ሁነዋቸው የቆዩት የክፍለ ጦሩ ፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ
በህክምና ሰበብ ከግንባር ፊርጥጠው አዲስ አበባ ከሄዱ
ወራት በመቆጠራቸው አዛዦቹ የሚሄዱበት ጠፍቷቸው
ተጨንቀዋል። የልባቸውን ለማን ይተንፍሱት?
ለማንኛውም የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊውን ተወካይ
ምክር ለማግኘት ሄዱ። እንደደረሱም «አባከህ ይኸ
ልጅ እኮ ጉድ አድርጐን ሄደ!» አሉት። ሁኔታውን
ያልተረዱት ተወካይ «የትኛው ልጅ?» ሲሉ ይጠይቃሉ።
«ይኸ ስሞኑን ሱተሪ ጠጣልኝ ያሰው ወታደር!»
የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊው ተወካይ ጉዳዩ ግልፅ
ስላልሆነላቸው በደንብ እንዲያስረዷቸው ጠየቁ።
«በጣም እኮ የሚገርም ነገር ነው። ልጁ ደሴ
ማዕከላዊ ምርመራ ስለሚፈለግ በኤስቮኒይ እንድናቀርበው
ተጠይቀናል። ስለዚሁ ጉዳይ የክፍለ ጦሩን ጥብቅ
የአስተዳደር መኮንን ብጠይቅ ከሁለት ቀናት በፊት
የደሰፍ ወረቀት ተሰጥቶት እንደሄደ ገለፀልኝ። ትልቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

እዳ እኮ ነው። ከመሄዱ በፊት ሰምን እንዳልነገሩኝ አላውቅም» በማለትም ሸመጠጡ። (ለነገሩ ሳወታደሩ ወረቀት ተፅፎለት እንዲሄድ ያዘዙት አሳቸው ራሳቸው ነበሩ) ይገርምሃል፣ ይህ ልጅ ምናልባት ከ264ኛ ብርጌድ የጠፋውን ገንዘብ ሳይሰርቅ አልቀረም። አሰበሰዚያም አንዱን ገበሬ ወይም ነጋዴ ዘርፎ ሊሆን ይችላል። እንደምሰማው እኮ ወታደሩ ሰተሪም አልወጣለትም።»

የፖሊቲካ ኃላፊው ተወካይም «ጓድ ኩሉኔል፣ እውነትም የሚገርም ድርጊት ነው። በዚህ አይነት እኩ እርስወገም 'ማኖ' አስነክቶት - የሄደ ስለሆነ ጉዳዩ ሳይወላሰብ አይቀርም» በማለት ይበልጥ አሸበሯቸው። ኩሉኒሉ ትክሻቸው ላይ እንጠልጥለውት የነበረውን ወታደራዊ ማዕረግ ያለበት ፊልድ ጃኬት «በጣም አዝናለሁ» በማለት አሽቀነጠሩት። ተወካይ መኩንኑ «ይህ ወታደር እውነት የብርጌዱን ገንዘብ ሰርቆ ከሆነ ብቻውን ያልፈፀመውና ሴላ አባሪ፣ ተባባሪ ያለው መሆኑን መረዳት አያዳግትም። ታዲያ ጓድ ኩሉኔል መፍትሄው ምን ይመስልዎታል?» ሲሉ ጠየቋቸው።

«እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል ጓድ ...? አለመኖሩን ገልፀን የሚወስዱትን አርምጃ መጠበቅና ወደእኛም ከመጣ ማሰረዳት እንጂ ምን አደርጋለሁ። ደግሞ እኔ ገንዘቡን አልፈልግም ብዬ ነበር። ይህ ደህንነት የሚባል ሰውዬኮ ነው ያሳሳተኝ ... እባክህን ይህ የደህንነት መኮንን በጣም ችኩልና ፈጣን ነው። የከፍለ ጦራችን ወታደሮች ሰውን በመቼ አጥንተው ትክክለኛ ስም እንደሚሰጡት ይገርመኛል። ምን ያሉት መሰለህ? 'ካፒቴን ስፒዲ'። እውነታቸውን ነው። እኔ ብዙ ጊዜ አይቼዋለሁ። በጣም ይቸኩላል፤ ይፈጥናል። እኔ እንኳን ትኩረት አድርጌበት ስለተከታተልኩት አውቂዋለሁ። ፊትም አልሰጠውም። ስለዚህ አንተን

እንሳያሳስትህ ተጠንቀቅ» ብሰው ኩሉኔሉ ከሰው ጋር ቀጠሮ አለኝ ብለው የወጡት የተንኮል መረባቸውን እንዴት መዘርጋት እንዳለባቸው ለማውጠንጠን ነበር። በእርግጥም ድንቅ ሀሳብ አገኙ - ወታደሩን አሳደ በምስጢር አርምጃ የመውሰድ።

የክፍለ ጦሩ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ ተወካይም ሆኑ የደህንነት ኃላፊው ሳያውቁ ም/መ/አለቃ ጌታቸው ትርፌ የውሎ አበል ተክፍሏቸው በሚቀጥለው ቀን ለአዲስ አበባ ጉዞ እንዲዘጋጁ ተደረገ። ጉዳዩ ጥብቅ የነበረ ምስጢር ቢሆንም ከደህንነት ጆሮ የሚያመልጥ ነገር ባለመኖሩ የክፍለ ጦሩ ደህንነት ኃላፊ ደረሱበት። የፖለቲካ ኃላፊ ተወካዩንም ሰምተው እንደሆነ ቢጠይቋቸው አለመስማታቸውን ስለገለፁላቸው ከሙያ አንፃር የፖለቲካ ኃላፊ ተወካይ ባሉበት መመሪያ ሰመስጠት እንደሚፈልጉ የደህንነት ኃላፊው ተናገሩ። በዚህም መሰረት «መንገደኛው መኩንን» ተጠርተው ጉዟቸው እስከየት ድረስ እንደሆነ ይጠይቃሉ።

«እኔ ራሴ የሲዳሞ ሰው ስሰሆንኩ አካባቢውን አውቀዋለሁ። የልጁን የትውልድ ቦታም ከህይወት ታሪክ መዝገቡ ላይ አግኝቻለሁ። የምሄደውም ወደዚያው ነው። ያለምንም ችግር እንደምይዘውም እርግጠኛ ነኝ» አሉ። የደህንነት መኮንኑም በበኩላቸው መጀመሪያ አዲስ አበባ መፈሰግ እንዳለባቸውና በተሰይም «ሲዳሞ ተራ» በመባል የሚታወቀው ቦታ ላይ እንዲያተኩሩ ሲመክሩ፣ ወደ ሲዳሞ ከመሄዳቸውም በፊት ክፍለ ሀገር አውቶቡስ መናኸሪያ የመንገደኞች ስም ዝርዝር ስለሚኖር እዚያ እንዲመለከቱ እንደዚሁም በአጋጣሚ መንገድ ላይ ቢያያቸው ሊሸሽ ስለሚችል መነፅርና መለዮ በመጠቀም ራሳቸውን ደብቀው ጉዳዩን እንዲከታተሉ ጠበቅ ያለ መመሪያ ሰጧቸው። «አዳኙ

t.me/OLDBOOKSPDF

መኮንን» ግን ያለምንም ሳንካ ተልዕኮአቸውን እንደሚወጡት በልበ ሙሉነት አረጋገጡ።

ኮየቂት ቀናት በኒላም ኩሉኑል ከዘኗ ደበሳ ከመሳ ፈገግታ ጋር ወታኒሩ የመያዙ ዜና ከሲኖም በሰልክ እንደተገለፀላቸው ለከፍለ ጦሩ ፖለቲካ ኃላፊ ተወካይ አዘሰሩ። ተወካዩም ብዛም ደስ የሚል ዜና ነው ብሎ ሞገ አሳየ። በዚህ የልብነት ተግባር ውስጥ ሰንቱ ተሳትፎ ያሰገ መቼም ያለገን ማወት አርክ ከማሆኑም በላይ እንዴት አደገኛ ውስብስብና ሪቂት ምስጠር ያለበ ይሆን? እንግዲያው ጊዜዉ ወታኒሩ በገመኗ ታስሮ የአከባቢው የህዝባዊ ፖለስ ኃይል ችግር ተምርና ተመኗከው ይዘው ማምጣት አለባቸው። ስለዚህ ይህንን ትኩረት ያደረገበትና በሞንቃቂ ተሃዘ እንዲመጣ ከሚመለከተው አካል ጋር ያነጋገሩበት» የሚል አስተያየት ሰጡ።

«ለይዳለም! የእኔ አመጣጥ እንዲያውም ያጠኛ እንድትወቀው ልገልፅልህ ነበር። አሁን አንድ ተሽከርካሪ ለጀነራል ሆሱም ገዝሬለሉ ነግሬ አልነበሩ። ከዚያም ጋር አንድ መኮንንና ሁለት አሻሺ ወታኒሮች አብሬ አልክስኩ። በተጨማሪም ቅንጅ ግላስቲክ ገመድ አልኩና ታስሮ እንዲመጣ ጥብቅ ትእዛዝ አስጣለሁ። አሁን አንተ ተሽከርካሪውን እንደምልክ አወቀው» ብሎለት ደረተቸውን ነቅተው ተናገሩ። የፖለቲክ ኃላፊ ተወካዩም በመሳኔያቸው ተስማሙበት። ሆኖም የደህንነት መኮንኑ እንዲያውቁት ቢያደርጉ ዋና መሆኑን ሲገልፁ ዋና አዛዙ «አሱን ተወው እባክህ፣ የሚፈያደው አንተኛም ንዝር የለም። እኩ በእሁኑ ወቅት እኛን ለማስወንጀል እየተጋጋጠ ስለሆነ አፉን አስይዘዋለሁ። ይልቅስ እሁን የትኛውን መኮንን አዘረን እንላክ» አሉ። የፖለቲክ ኃላፊው ተወካይም የክፍለ ጦሩ ወታኒር ፖለስ ሻምበል አሳዥ ከሁለት ጠንካራ ወታኒሮች ጋር በሄሉ እንደሚሸል ጥቆማ አቀረበ። ዋና አዛዙ ግን «አይደ ... ደደ ... አንተ አታውቀውም ለካ? እሱ እኩ ለክራም ነው። አሪቂውን ሲጠጣ ደጠፋብኮል። ቀደ እኔ ራሱ ከብርጌዶችም በሆን ጠንካራ መኮንን አፈልጋለሁ። እኔ እኩ ለሞኑን እንቅልፍ አልነበረኝም። አሁን ትገሽ እርደታ አግኝቶለሁ፣ አረፍ ልበል» በማለት መደዜታቸው ገቡ።

ወራው ከተሰማ ጀምር በደሴ አካባቢም ጉጭ በስፋት ደጠራ ጀመረ። የክፍለጦሩ ዋና አዛዥ ማታ ማታ ውስኪያቸውን ከተለመደው በላይ አየጠጡ ደብረቀርቁ ጀመረ። አንጋራቸው ሁሉ የአጉራ ዘለልነት ባህርይ ደታደበት ገዛ። ጉራቸውም የሚቻል አልሆነም። በተለደ የደህንነት መኮንኑን በአሽሙር ይቀጠቀጧቸው ነበር። የደህንነት መኮንኑም አንተል መሆን ጀመሩ። ደለምንም ስራ በአገራቸው ረዥም መንገድ መሄድ፣ ብቻቸውን ማውራት ‹እኔ ምን አባኝ› ማለት ጀመሩ። ኩሉኑስ ደኸኔ ደበልኮ ተደስቱ።

አንድ ቀን እሁድ «አሞቢዘባራ» የተባለውን ወታደር በማሞ የፈጦኝ አስረው እንዲመጡ የተላኩት ሰዎች በድን ራሳ ደዘው ደሴ የመድረሳቸው ዜና በክፍለጦሩ ጠቅላይ ስፈር ሲናፈስ ዋና አዛዡም ባስማሩት ኃይል አማካኝነት የሚደውቋት ዜና ከጅሮአቸው ጥልቅ አለ። ደኸኔ ስሁኔታው አዳስ በመምስል ለክፍለ ጦሩ ፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ ተወካይ ወራውን ለማድረስ «እሳት ለብስውና እሳት ጉርስው» ገለገሉ። እንደ ደረሱም «ፃድ ... በጣም የሚያሳዝን ነው። ሰውየው እኩ ራሱን ገደለ ነው የሚሉኝ» አሉት። የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊው ተወካይ ደግሞ በክፍለ ጦሩ ውስጥ ራስን በራስ የማጥፋት ሁኔታ ከረዥም ጊዜ በኋላ እንዴት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊያገለሽ ቻለ? በማለት «የትኛው ሰውዬ?» ሲሉ ግሬ
ተጋበተው ወየቋቸው።

«ያንኔ እነ ጊታቸው ሲያዙት የሊዲት ሰበበኛ ሰውዬ»
ለፖሊስ መምሪያ ኃላፊው ተመካሂ አሁን ቁልጭ ያለ
ስዕል ታያቸው። ድርጊቱ አደገኛ ሴራ ስለመሆኑም
ግርማሌያቸው ሰፋ ያለ መልክ ያዘ። ሆኖም እሱቂ
ምን ምላሽ አኘ ይሆን? በማለ «እንዴት ደህና
ወታደሩ በደንብ ታስሮ እንዲመጣ አልተባለም እንዴ
ምን ሲደረግ ይኼ ለፅሕት ያችላል? ይኼ እኮ ሊታመን
የሚቻል አያደለም። ያለ የወንጀለኞች ሁሉ ወንጀል፣
የግፍ ሁሉ ግፍ ነው። ደህን ህሊናዬ አደተበሰውም።
ዕዳያ አሁን ሰምቸ የት አሉ? ድርጊቱስ እንዴት
ታወቀን» የሚል ሀሳብና ጥያቄ ሰንዘሩ።

ኮሎኔል ከበደም «በሣም ደንግጦሳል፣ እኔ ራሴ
ጥበት ትእዛዝ ሰጥቼ፣ ገመና ላደተር ገዘቼ ልክ፣
እንዴት ለሆን እንደቻለ አልገባኝም። ጊታቸው እንኳን
በሣም ጥንቁት ነው፣ አምነዋለሁ። ከሱቱሙ በላይ
የሆነ ነገር ካልገጠመው በስተቀር። አሁን እኮ ደሴ
ሆስፒታል ናቸው አሉኝ። መልዕክቱ ስለደረሰኝ ልንገርህ
ብዬ ነው። እስቲ እኔም መጣሁ» ብለው ሄዱ።

ከዮቱት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ሲኖም የሚደውን
ዘፍሞደል - 60 የሚያሽከረክረው የቢሮት ሹም አሳሻ
ከፍለ ሠር ጠቅላይ ሰፈር ደረሰ። በሚገው የገበሩት
መኮንኖች ስለሁኔታው ለማወቅ እጅግ ጎተራው ስለነበር
ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ጀመረ።

«ወታደሩ እንዴት ሊሞት ቻለ?»

«በትሩንትኖው ዕለት ነው ከሲኖም አዲስ አበባ
የገነው። ከምሽቱ ሰዓት ሰጎት ገደማ ላይ እንደደረሰም
የጌድነው መኖ አለቃ ዐጋቤ ቤት ነበር። መኖ አለቃ
ጌቶቹና መኖ አለቃ ዐጋቤ አመናሪያ ቤት፣ እኔ

ሁለቱ አጀቢ ወታደሮችና ሚቹ ወታደር ደግሞ ሰርቪስ
ቤት እንደገቡ ተደረገ። አንቅልፍ ላይ እንዳሰን
ከሴሊቱ በጠኝ ሰዓት የተኩስ ድምፅ ተሰምቶ ለንባንን
ወታደሩ ራሱን በራሱ ገድሎ ተገኘ።»

«ቦንቻቸው ከገበረ ወታደሩ ራሱን ለመግደሉ እንዴት
ሚረጋገጥ ቻልከ?»

«ወታደሩ ከእኛ ትንሽ ራቅ ብሎ ከሰተኛ አወዳደቁም
ሰቢቸው ሲሠን፣ አንድ ከላሽንኮቭ ጠመንጃም ጉኑ
መድቶ ታያቢል።»

«ወታደሩ እጁን ተደም ሲል አልታሰረም ነበር?»

«አስከተኛበት ጊዜ ድረስ አጁ የኋሊያሽ በደንብ
መታሰሩን አውቃለሁ። ሁኔታው ከተፈጠረ በኋላ ግን
እጁ የተፈታ ነበር።»

«ማን ፈታው?»

«ምናልባት ወታደሮቹ አሳልተውሰት እንደሠን?
የፈታውን አሳውቅም።»

«አሁን ወታደሮቹ የት አሉ?»

«እነሱማ መሳሪያቸውን መከና ላይ ጥለው የት
እንደገ አልታወቀም።»

«ወታደሩን ፖሊስ ማዚያ ለማሳደር ምን ችግር
ገጦሚችሁ ነበር?»

«አንደኛ አዲስ አበባ አምሽተን ስለገባን፣ ሁለተኛ
ዕደሴ ጉዞ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ለመነሳት ስለፈለግን
ዛቹ እንጂ ሌላ ችግር አልነበረም።»

«ወታደሩ በሌሎቻችሁ ላይ እንዴት አደጋ ለማድረስ
አልሞከረም?»

«ወታደሩ ተደም ሲል ከአንዱም ሁለቱ ራሱን
ለመግደል ሙከራ አድርጉ ነበር። እንዲያውም አንድ
ጊዜ በገመድ ራሱን የማነቅ ሙከራ አድርጉ ሐኪም
ቤት ድረስ ወስደን ነው ነፍሱ ልትተርፍ የቻለችው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ የወታደሩ ፍላጐት ራሱን ብቻ ማጥፋት ስለነበር
ነው።»

«ስለጠፉት ወታደሮች ጉዳይ አዲስ አበባ
ያመለከታችሁት ጉዳይ አለ?»

«አላመለከትንም። እዚህ ከደረስን በኋላ
እናመለክታለን ተብሎ ነው።»

«ማታ እስከ ስንት ሰዓት ድረስ ሳትተኙ አመሻችሁ?»

«እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት ድረስ ሁላችንም
አልተኛንም። መኮንኖቹም እየተመላለሱ ሲያዙን
አምሽተዋል።»

«ወታደሩ ራሱን መግደሉንስ ለፖሊስ ወይም
ለደህንነት አላመለከታችሁም?»

«በጭራሽ። እኛ ሌሊት ተነስተን የመጣነው ወደዚህ
ነው።»

በማግሥቱ የደሴ ማዕከላዊ ምርመራ ሰዎቹ እንዲላኩለት
ጥያቄ አቀረበ። ተላኩለት። ሁለቱ መኮንኖችና ሾፌሩ
ታስረው ምርመራው ተጧጧፈ። ለህዝብ ጆሮ የሚደርስ
ነገር ግን የለም። ባንዛሩ ሌላ ከስተት ተፈጠረ።
ከትግራይና ከሰሜን ወሎ በተጨማሪ ሰሜንና ደቡብ
ጐንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጐጃም፣ መተከል፣ ወለጋ፣
ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ወዘተ በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር
መዋል ጀመሩ። እነ ም/መ/አለቃ ጌታቸው ትርፈኛ
ከደሴ ወህኒ ቤት በኢህአዴግ አማካኝነት ነፃ ወጡ።

ኢህአዴግ መላ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ የቀድሞ የጦር
አባላት ወደ ተሀድሶ ማዕከል እንዲገቡ ጥሪ በተደረገ
ጊዜም ነፃ ወረቀት ተሰጥቷቸው የተሰቀቁት ሁለቱ
መኮንኖች፣ ማለትም መ/አ ጌታቸውና መ/አ በጋሹ
ቡላይ ተሀድሶ ማዕከል ገቡ። በተሀድሶ ማዕከሉ የሚሰጥ
ግለሂስ ውይይት ላይም ይህ የግድያ ሴራ ተነሳ።
በዚያን ጊዜ በሀቀኛ መኮንኖች ጥንካሬና በኢህአዴግ

ታጋዮች ትብብር ሁለቱ መኮንኖች ዳግም ዘብጢያ
እንዲወርዱ ተደረገ።

በታጠቅ ተሀድሶ ማዕከል ትምህርት ላይ የነበሩት
ኮሎኔል ክበደ ደበላም በዚሁ ጉዳይ እንደሚፈለጉ
ቡላይ ከሚገኙት ወንድማቸው መልዕክት የደረሳቸው
በመሆኑ ለህክምና በሚል ሰበብ ከታጠቅ ወደ አዲስ
አበባ ሄዱ። ከዚያም በእውነት ለድርጅቱ ዓላማ ተገገር
ሆነው አሊያም ለዚያ ህዝብ ነፃነት ለመታገል ቆርጠውና
አስበውበት ሳይሆን ከዚህ ጉድ ለማምለጥ ሲሉ ብቻ
የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ሙጢኝ በማለት ጫካ ገቡ።


ውድ አንባቢ፣ ይህን ምስኪን ወታደር መግደል
ስለምን አስፈለገ? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። የወንጀሉ
ጭብጥ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል። የ264ኛ
ብርጌድ ገንዘብ የተሰረቀው ፍፁም በተቀነባበረ ሴራ
ነው። የሎተሪው ዕጣ እንደወጣ ተደርጐ የተቀናጀውም
ወታደሩን በሰበብ ከከልሉ ለማራቅ ተፈልጐ ሲሆን
ወታደሩን ቀድሞ አሳዶ መያዝ ያስፈለገበትም ምክንያት
በደሴ ማዕከላዊ ምርመራ በኩል ወታደሩ በከትትል
መያዙ ሰለማይቀር ከውርደት ለመዳን ነው።
በመጨረሻም ወታደሩ እንዲገደል ያስፈለገውም የሴሎችን
ድርጊት አጻፍኖ ለማስቀረት ሲሆን፣ በተሰዬ የዋና
አዛዥ በመጨረሻ መጥፋት ወንጀሉ በማን ይውጠነጠን
እንደነበረ በግልፅ እንድንገነዘብ ይረዳናል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈተና

አሸቱ ተፈራ

ባለም የታወቀው ኮሚኩ ተሞናይ
ሳት በሳት የሚያደርግ ገና ከራት ሲታይ
ምትክ ሳያገኝ እንዳረጀ ሲያውቁ
አድናቂዎች ሁሉ በጣም ተጨነቁ።
ቻርሊ ቻፕሊንን የሚተካ ይምጣ በማለት
ጧት ማታ ሕዝብ ቢያስቸግር
ቻርሊን ለመተካት ተያዘ ምክር።
ኮሚቴ አቆሙና ይህን የሚሰራ
እችላለሁ የሚል አንድ ባንድ ተጠራ።
አንደኛ ለወጣ መቶ ሺ ዶላር
ለለጣቂው ኮራጅ ሶፋና ወንበር
ሶስተኛ ለወጣው ማለፊያ ብዕር
ሽልማት ለመስጠት ኮሚቴው ወሰኖ
ብዙ ሰው አወቀው ይሄው ተበትኖ።
ይህንን ሲሰማ ቻርሊ አሰቦ በጣም
«ቁና ዶላር ሲገኝ መናቅ አያዋጣም»
አለና ጠንክሮ በውል ተሰማምዶ
መልኩን ለዋወጠው ቁንጅና ቤት ሄዶ።
በውድድሩ ዕለት በደንብ ተዘጋጅቶ
ላቡ ጠብ አስከሚል ኩምከና ጀመረ አመድረክ ላይ ወጥቶ
አልቆ ውድድሩ ውጤቱ ሲነገር
«ቻርሊ ቻፕሊንን ደህና አርጎ በመቅዳት ልቆ ታይቷል ሲሸ
በማለት በዳኞች ስለተፈረደ
አብዩን ሽልማት ኮራጁ ወሰደ
ቻርሊ በመከራ፣ ሶስተኛ ወጣና ብዕር ይዞ ሄደ።
ይህን የመሰለ፣ የሚያስደንቅ ነገር፣ በየትም ይገኛል
የሰውን ችሎታ፣ ፈተና ይለካል፣
የሚባለው ነገር ያጠራጥረኛል።



የባለቴቶቹ ልጆች

ሰአዳ መሀመድ

ከመንገዱ ማዶ በግርማ ሞገስ ከተገሸረው ሆስፒታል ቅፅር ግቢ አምስቱ ባልቴቶች እየተንጫጩ ሲወጡ አየኋቸው። ካሰችን ሆስፒታል አስገብተው መመለሳቸው ነው። እኔም እነርሱን ተከትዬ ነበር የመጣሁት። የእድሜ አኩያዬና ጓደኛዬ የሆነችው ካሰች የገጠማትን ችግር ከራሴ የብሶት ድራዎ ጋር አብሬ ላኝክ ቆይቼ ባልቴቶቹ ሲመጡ ከአሳቢ ተላቀቅሁና ወደኔ የሚመጡትን እኒያን በድህነት የታሹ የመከራ ቋሚ አባላት አመለከት ጀመር። ከአምስቱ አንዷ እናቴ ናት። ሌላዋ የካሰች እናት። ሌሎቹም

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመሳሳይ ጐረቤቶች ናቸው። አምስቱም ባልቴቶች የጋራ መልክና ባህሪያት አሏቸው። ልብሶቻቸው፤ ከሳታቸው፤ ድህነታቸው፤ ቋንቋቸው፤ ሁለመናቸው።

ባልቴቶቹ እየተንጫጩ አጠገቢ ደርሰው ቆሙ። እናቲ እትዬ አልታዬን እየገሰፀቻቸው ነበር፤

«እርሶ ድሞ ሁልጊዜ እኔ ያልኩት ታልሆነ ይላሉ። እሁን በርስም ቤት ደግ ማለትም ነው? ሁላችንም እኩ ወልደናል። ነግ ይዞብን የሚመጣውን መከሬ እናውቀውም። ነግ በኔ እንበል እንጂ። ምን ደርሶ የርግማን ድር መትቦተብ ነው።» እናቲ እኒ የሰበሰኩትን ነጠላ ግማሽ ቅዳጅ ትከሻዋ ላይ ጣል አርጋለች።

«እትዬ አልታዬ የሚሉትኮ ትክክል ነው። አሁን ካቡ በእናቷ ላይ የፈፀመችው በደል፤ በራሷ ላይ የጣለችው መከራ ሆድ የሚያሰልስ ነው? እንደዚህች አይነቷን ዋልዶ ድራሿን ማጥፋት ነው እንጂ!» እትዬ ዘርፌ እናቲ በቁጣ ሳሽም አደረጓትና ከቀሚሳቸው ስር የለበሱትን ቦታዛፊ ውስጥልብስ አሻቸውን በደረታቸው በኩል አሰባብተው ወደ ላይ እየሳቱቱ ያስተካክሉ ጀመር።

«ዘርፌ ደግሞ ደርሰሽ በሞቀበት ጣዱኝ ትያለሽ። አዘነ እትዬ አልታዬ የሚሉት ደግ ነገር ሆኖ ነው? የእግዜሩ አይን ልትጠነቁሉ ፈለጋችሁ እንዴ? ሽሮ ያመጣውን በወጋ ተቀብሎ ተመስገን ማለት እያለ እንሰበር እንሰንጠር፣ ማለት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው?» እትዬ ተዋቡም በመግቱ ተሳተፉ።

የንትርኩ ርዕስ ካሰች ናት። ካሰች ገና በለጋ እድሜዋ አርግዛ ልታስወርድ ባደረገችው መከራ ክፉኛ አደጋ ስለደረሰባት ነበር ገና በማለዳው ሠፒታል ያስገባናት ባልቴቶቹ ካሰችን በማውገዝና ባለማውገዝ መከሰል ሲነታረኩ እያዳመጡ ተደምመው የቆዩት ሃኒሰች እናት ጣልቃ ገብተው በቆሰለ መንፈስ ጥቂት ተናገሩ፤

«አሁን የናንተ ጭቅጭቅ ምን የሚሉት ነው? ችግሩ የኔም አይደል? መዓቱ የወደቀው በኔ አይደል?» ይህን ብለው የሞጨሞጩ አይኖቻቸውን በነጠላቸው ጫፍ ጨማምቀው ንግግራቸውን አራዘሙ፤

«አንድ ጊዜ አግዜር ያመጣብኝን እኔው አችለዋለሁ። ከሰባት ልጆቼ ጋር በችግር ስማትቅ ቀርቦ ያገዘኝ የለ። አሁንም ቢሆን ያለ አባት ያሳደግኋቸው ልጆቼ ነገ ደርሰው ይጦሩኛል ብዬ ከሰው አንዳያንሱ ስንከላወስላቸው አንዳልኖርኩ ልፋቴን ከንቱ ቢያደርጉትም፤ ተስፋ የጣልኩባት ካሰች አደባባይ ብታወጣኝም፤ የማንንም ምፅዋት አልጠይቅም። ኪዳነ ምህረት እንደምታደርግ ታደርገኛለች። የአስከዛሬ ልመናዬን እንደሁ አልሰማችኝም። አኔም.. ሀሌ.. አኔማ»

እንባቸው በዓይናቸው ግጥም አሰና በሳግ ተደነቃቅፈው ዝም አሉ። ሴቶቹ ከንፈራቸውን ይመጡ ጀመር።

«አፈር መስለን አሳድገናቸው መልሰው እኛኑ አፈር የሚከቱን እዙይ ፍራሞች» እትዬ አልታዬ ርግማናቸውን ያዘንቡ ጀመር።

«እትዬ አልታዬ ምነው በሰው ቁስል እንጨት ባይሰዱ» እናቲ ነበረች።

«ሆድ ሰባሰው ማጭድ አታውሰው አሉ የሀገሬ ሰዎች...» እትዬ ተዋበች አያቃሰቱ ተናገሩ።

«እሬ ወዲያ! የምን ቅብ እንጋችነት ነው አሉ? ከመሀላችን ያልወሰደ አሰ እንዴ? ሰልጆቻችን ስንል በችግር አስንጋ ተጠብሰን የለም እንዴ? ስለነሱ ብዙ መከራ አልቀጠርንም? ታዲያ አሁን ደርሰው በዓይናችን አመድ ሲነሰንሱ አሰየው አበጃችሁ ፣ ማለት አለብን? እነዚህን ወፈሰላ ገልብጦ በርበሬ ማጠን ነበር!» እትዬ ዘርፌ ይህን ብለው ሲያበቁ በዓይናቸው ጥግ ግሽልጥ አድርገው ሳመጡኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጉድፈላ» አልኩና ወደ ኋላዬ ሸሸት ብዬ ቆምኩ። እኔንም ከካሰች ጋር ሊደምሩኝ ጸርጸር ማለታቸው ገብቶኛል።

ባልቴቶቹ እርስ በርስ ጎራ ለይተው በነገር ይሸነቆጣሉ። እናቲና እትዬ ተዋበች በአንድ ጎን፣ እትዬ አልታዬና እትዬ ዘርፌ በሌላ ጎን ሆነው በካሰች ላይ ርግማን እያዘነቡ እሽሙር እየተወራወሩ ይቆራቆሳሉ። የካሰች እናት ግን የሴቶቹን እገቦ በገዘፉ ከማዳመጥ አላለፉም።

...ካሰች የእትዬ አበቡ ሶስተኛ ልጅ ናት። ጓደኞቼና የእድሜ እኩያዬ። አብረን ማደጋችንና ጉርብትናችን ብዙ ነገሮችን አወራርሶናል። በተለይም ድህነታችንን ለማሸነፍ በጨቅላነታችን ወደ አደባባይ በመውጣታችንና በትምህርታችን ባለመግፋታችን ይበልጥ እንመሳሰላለን። ወላጆቻችንም ተመሳሳይ ናቸው። ከጉሮ ደረጃቸው ጋር የማይመጣጠን ልጆች አፍርተዋል። እትዬ አበቡ ሰባት ልጆች አሏቸው። እትዬ ተዋቡና እትዬ ዘርፌ ስምንት ስምንት ልጆች አፍርተዋል። እትዬ አልታዬ ስድስት ልጆች አናቴ ደግሞ እኔን ጨምሮ ዘጠኝ ወልዳለች።

የሁሉም እናቶች ጓዳ በአጠት የቀዘቀዘና ቡቱራቡ ህፃናት እረታ የተመሰቃቀለ ነው። የደሪቁ ሌማቶቻቸውን አተክሮ ለማየት ጥንካሬ የሌላቸው ሆደ ቡቡዎች ናቸው። ባዶ ማጀታቸውን ባሰቡ ቁጥር በቅጠልና በዝቡቡት ጭስ የተጨናበሱ አይኖቻቸው የሚያንጠባጠቡትን ዘለላ እንባ ለመጥረግ የሰለቹ ናቸው። ስዘመናት የፈሰሰ እንባቸው ምንጩ ደርቆ ፍንጣቂ እንባ ለማውረድ የሚደፈርሱ ዓይኖቻቸውን ቃጠሎ ለማስታመም አቅም ያነሳቸው...

አምስቱም ባልቴቶች የሚኖሩት በአንድ ግቢ ውስጥ እርስ በርስ በተደጋገፈ አምስት ደሳሳ ጎጆዎች ውስጥ ነው። ሁሉም ጎጆዎች ደግሞ ባለሁለት ክፍልና ጠባብ

ናቸው። በየቦታው የተበሳሳ ጣሪያቸው የዐይን ጨረር አመልቶ አያስገባ የሚገለፍጥባቸው፤ ከሚፈረፈር ግድግዳቸው አጥንት የመሳሰሉ ማገሮቻቸው ያገጠጡባቸው ጉስቁል ጎጆዎች...

በጎጆዎቹ ውስጥ ደግሞ ላይ በላይ የተወለዱ በርካታ ህፃናት ሞልተው ብታል። አብዛኞቹ አባቶቻቸውን የማያውቁና በሞትና በፍች የተነጠቁ፤ የእናቶቻቸው እዳዎች ናቸው። እኔም በውስጣቸው አለሁ – እዳዋኬ።

የግቢያችን የቆርቆሮ አጥር ለአመታት ተገትሮ፤ በዘመናት ፍርርቆሽ አርጅቶና በዝገት ተውጦ ተሸረሸረብኝ። ከልሱ ያኖራቸውን ማስጠሉ ገጆችን ለውጭው ትዕይንት ከፉፍቶ የሰጠ አልባሌ ክፍት አፍ ነው። በግቢው ውስጥ ተወልደን እትብታችን በሰፈሩ የተቀበረው ልጆች ነፍስ አያወቅን ስንመጣ የእናቶቻችን ሩጫ ጠኒያችንን እንደማይገድሰው ተረድተን በየፊናችን እንጀራ ፍለጋ ማሰንን። ለጉሪ አዝዋሪዎች፤ ሊስትሮዎች፤ ቆሎ ሻጮች፤ የታክሲ ላይ ወያላዎች፤ በሰፈሩ በሞሉት ቡና ቤቶችና ጠጅ ቤቶች በተላላኪነት ተቀጥረው የሚሰሩ ትናንሽ ጭሎዎች ሁሉም ምሽቱን ጠብቀው ወደ ጎጇቸው ይመለሳሉ።

ሁሉ ታላላቅ ወንድሞቼ መንገድ ዳር እየቆሙ ለባለታክሲዎች ዝርዝር ሳንቲም መሸጣቸውን ትተው ወደ ታክሲ ረዳትነት ሲሸጋገሩ እኔ ደግሞ ቆሎ እያዞርኩ መሸጤን ትቼ በእናርሱ እግር ተተካሁ። በታክሲ መሳፈሪያ ቦታ ሳንቲም መሸጥ ጀመርኩ።

ከእናቶቻችን እንሰቶ ሁላችንም ኑሮን ለማሸነፍ እንውተረተራለን። ከካሰች ጋርም የተለያየነው እኔ የሰራ ስውር እንዳደረገው ነበር። እሷ እሁንም ቆሎ መሸጧን ቀጥላበታለች። ኑሯችን እንደወትሮው መልኩን ላይቀይር ይችላል። እንደባቡር ፉርሽ እየተምዘገዘገ በዘቀጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

ድህነታችን ስር ይሃዳል። በውስጡ መሀይምነትን ርሀብንና ጉስቁልናን ተሸክሞ...

ለአንድ ዓመት ያህል የቆየሁበት የሳንቲም ሽያጭ ስራዬ ረብ አላመጣልኝም። ይልቁንም እየታከተኝና ከእቅሜ በላይ እየሆነ መጣ። ከመንገድ ዳር ቆሜ እየከነፈ ካሚመጣው ታክሲ ውስጥ አንቱን በመስኮት ብቅ ላደረገ ወያላ በእፍኜ የሞላኋቸውን ሳንቲሞች እያሳየሁ «ሳንቲም! ሳንቲም!» እያልኩ መሮጥ በአንድ ብር አምስት ሳንቲም ለማትረፍ ለሚገዛኝ ወያላ፣ ዘጠና አምስት ሳንቲም አተብዬ እንዲን ብር ሰመውስድ ከሚነዳደው ታክሲ ኋላ ኋላ መንደሁዬ አለያም የተወረወረችልኝን አምስት ሳንቲም ትርፍ ይዛ የምትመጣ እንዲት ብር ንፋስ ይሏት ሲነጉድ፤ ስነተላት መኪና መንገዱ መሀል ንብታ ስትውለበለብ! ስትወድት አብሬያት ስወድቅ፣ መኪና እንዳይገጨኝ ስሳሰብ። ጥጋበኛ ወያላ ያጋጠመኝ እለት ደግሞ ዘጠና አምስቱን ይዘብኝ ይጨደና ስለኪሳራዎና ስለ ደካማነቱ የማፈስሰው እንባ ቀማሽውን ወያላ አደብቼ ለመያዝ በየታክሲው መሰበቅ ከጠራራ የሚያመልጠኝ ገበያ... ሁሉም ስሊችት ስላሳኝ እንደ ቀድሞዬ ከክሎች ጋር በየምሽቱ መለጎጥ ቤቶቸንና ጠፎ ቤቶችን እያካልኩ የታቀፍኩትን የሰረዷ ቸሎ መሸጥ ልቻልና አሁን። ሀሰቤን ለናዝር አልናገር እያፈላሁ ሳመሽታ በዘረበት ሳምንት የገቢያቸን እየር በመጥፎ ዜና ተበከለ።

«ካሰች አረገቸ» እያሉ እናቶቻችን ሲንሹካሹኩ ሁላችንም የገዢው ልጆች ስሆኑ። እንደ..ት አንለማ... መፈናፈኛ በሌለው ቀያችን ወደያት ቦር ተብለው ያለፈራለ?

የካሰች እናት ንቅዬ እለዙ በፈጨንቃቸው፤ በጠዋቸው ሚሰጥራቸውን ለጎረቤቶቻቸው ተንፈሱ። እናቶቻችን ደግሞ ሸኽለካላቸው ምስጢር ተረበሹ። ስለ ገዛ ልጅነቸው አንቅልፍ አጡ። ሁሉም ሴት ልጆች አሏቸውና...

«ኖኔስ ልጅ ምን ታደርግ ይሆንን» እያሉ አትላቸውን ሊያባትቱ ተሰሙና ወራው ሁላችንም ውስጥ ውስጣችንን ሲያረቡሪን ከረመ። ዛሬ ጠዋት ግን የታፈነ ጭንቀታችንን የሚያፈነዳ ጨኸት ከአትዬ አበቡ ጎጆ ተሰማ። ወደየስራችን ልንበታተን ከደረቅ ቂጣችን ጋር ስንታገል የነበርነው የምናምንቱው ቁርስ ታዳሚዎች፣ የግቢው ልጆችና እናቶች ተሯሩጠን ከተሙነበት ጎጆ ደረስን።

ካሰች ከተንጋለለችበት ቁርበት ላይ ሆና በህመም ትጥራለች። መኝታዋ በትውከት ተበላሽቷል። አንድ ፍሬ ልጅ የምትሰኘው ካሰች በሚያንፈራግጣት ህመም ደክማ አርጅና ያደተቃት ባልቴት መሰላለች።

«መርዝ ጠጥታ ልትሞትብኝ ነው። እባካችሁ ከጉድ አውጡኝ!... ኪዳነ ምህረት ትታደጋችሁ» ይላሉ አትዬ አበቡ – ደረታቸውን እየደለቁ። በጉራቸውን እየነፈጉ ወደ ሞት የምትንደረደር ልጃቸውን ከሚሀጠቡጣት የሞት መለኩት አንድናስነሳት ተማፀኑ።

ካሰች ረጅሙን ዘለአለማዊ እንቅልፍ ጠርታዋለች። እሱ ግን ወደሷ ከመድረሱ በፊት እያወራጨ አትሚን ሲሰልባት ይሳቸርባታል።

አፋፍሰን ወደ ሠፈር ታል መለድነት። የጠጣቸው መድሀኒት እምብዛም አልጎዳትም። ከመንደር ስራስር በማሾት ጎዳ ተወሽቃ በድህረ ላይ፣ በፈጨቅላነቷ ላይ ቆንጥር ሲያስቅልባት እንደ ቁልቋሱ ሲያስለቅሳት በማህፀኗ የተቋጠረውን እድሰ ቢስ ናሬ ልታፈሪግ የተጋተችው... ልንሱን ዘጣሆሰ ሊያመነጓት ሀያል አልነበረውም። ያልትሆው ሩቃ የሰሽ የሆድ ስራያ ስተተባት እንሽ...

ሀኪሞቹ ያለ ዕድሚዋ አናት ላለመሆን ልጇን ለታፈናንግፍ ስራስር በጠጣችው ህዋን አዘጉባት። ዳሩ ሁለስ የሚያችን ቢተርበ አዝናባት የለ... ግን ያህ ችግር እንዴት እንደገጠማት ለማወቅ ቢንቱ መልነም ነበር። ብቻ ከሞት አፍጀት። ትንሽ ተን ሙተኛት ስላለባትም አልጋ አስኪቸነላት

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንገተኛ ክፍል እንድትቆይ አደረጓት።

እትዬ አበቡ የልጃቸውን ከሞት መትረፍ እንደተረዱ አምላክን አላመሰገኑም። ሁሌም ከአፋቸው የማትጠፋውን ኪዳን ምህረትን እምርረው ወቀሱ። በሰባቱ ልጆቻቸው ላይ ካስች አዲስ ጨቅላ፣ የሚርበው- ማሙሽ ልታመጣባቸው ነው። ሴት ልጃቸው በባህሉትን የሚወገዘውን ከጋብቻ ውጪ የሚወለድ ዲቃላ ልታስታቅፋቸው መሆኑ ያንገሸግሻቸዋል። ጎረቤቶቻቸውም ጎራ ለይተው በሳቸውና በልጃቸው ጉዳይ ይናጫሉ።

...አስራ ዘጠኝ ቁጥር አውቶብስ በተሳፋሪ ተሞልታ አጠገባችን መጥታ ቆመች። ተንጋግተን ገባን። ባልቴቶቹ አሁንም ይናቆራሉ። ይንጫጫሉ። በአሽሙር ይሽቃሸቃሉ። እትዬ አበቡ ደግሞ ከድንገተኛ ክፍል ሳስተኟት ልጃቸው ምግብ ሰርተው ሲያመጡላት ሂሳብ ያሰሉ ገብተዋል...

«አጥሚት ብገዛ... ድንች ብቀቅል...» እያሉ ያቱተመትማሉ።

የናቴንና የሴቶቹን ንትርክ የአውቶብሱ ተሳፋሪዎች በጥሞና ያዳምጡታል። ንትርካቸው ፈር ሲቀና ወደየራሳቸው ልጆች ጉዳይ ዞረ።

«የኔ ልጅስ ብትሆን?»

«እረ የኔዋስ...»

ይባባሉ ጀመር። እናቴን አየኋት። ታየኛለች። የፈራችኝ መሰለኝ። እንደ እትዬ አበቡ ልጅ እንደ ካሰች የመነጋገሪያ ርዕስ የማደርጋት መስሏት ይሆን?

እትዬ ዘርፌ ድንገት አይናቸው እኔ ላይ ሲያርፍ አብረያቸው መሆኔን አስታወሱና ነው መሰል፣

«አንቺ?!... አለሽ እንዴ?... አኔክ ቀድመሽን የሐዲሯ መስሎኝ። የናንተ ጉድ መቼም አያልትም። ነግ ከነግ ወዲያ ምን እንደምታመጡ አይታወቅም። እግዜር ከመጥቴ

ይሰውረን እንጂ እንዲህ አፈር መስለን የቀይ ጥቁር ሆንን አሳድገናቸው ልፋታችንን ውሀ ታስበሉታላችሁ። መረኖች!... እንገታችሁን ደፍታችሁ የምትሰሩት ስራ!.. እም» ራሳቸውን በዛቻ ነቀነቁብኝ።

«ጆሮ ለባለቤቱ ባዳኮ ነው እትዬ ዘርፌ» አለች እናቴ በሽሙጥ።

አየኋት። አሁንም ታየኛለች። አይናቿን ሸሸኋቸው። በጠረጠረችኝ መንገድ ላይ ባልሆንም ሰቆይታ ሳያት አልደፈርኩም። አይናቿ የሚለማመጡ፣ የሚያዝኑ፣ የሚቆጡ፣ የሚሳቀቁ ይመስላሉ። ቀሪዎቹ ሴቶች እየተቀባበሉ ይወርዱብኝ ጀመር።

«ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ...» አልኩ።

ዙሪያዬን ሳማትር ተሳፋሪዎቹ ሁሉ እኔኑ ነው በትዝብት የሚመለከቱኝ። ሰው ስለምን ነገሮችን ሳይረዳ ለትዝብት ይጣደፋል?... የእናቴን ሽሙጥ እየተቀባበሉ የሚያዳምቁትን የግቢያችንን ሴቶች ጠላኋቸው። የጭቃ ጅራፋቸውን የሚያጮሁ ለከት የለሾች!... ከተጣለችው አሳት ዙሪያ ከበው የነገር ነበልባል የሚያቀጣጥሉ አራጋቢዎች መሰሉኝ። የሚንቀለቀለውን አሳት በሆይሆይታ የሚሞቁ...

ስፈራችን ደርሰን ከአውቶብሱ ስንወርድ እንኳንም ሁላችንም በአንድ ቤት የማናድር ሆንን ስል አሰብኩ። እንጂ እንዴት ይኮን ነበር?...

* * *

ካሰች ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ ግቢያችንን ሲያምሰው የነበረው ሀሜትና ጫጫታ ጋብ አለ። የእናቶቻችን ስጋት ግን ካለበትም ፈቀቅ አላለ። ከካሰች በስተቀር ሁሉም ወደየፊናው መክነፉን ቀጥሏል። ህይወት እንደጥንቷ ለሰከት ወራት ያህል ተጠለች። በአራተኛው ወር አጋማሽ የላንቲም ችርቻሮዬን ገቢ እየቆጠርኩ ወደ ቤቴ እየገሰኩ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ግቢ ስገባ አዲስ አይነት እንቅስቃሴ ይታያል። ደንገጥ ብሏል። ግቢዎችን ግን በደንብ ተጫውቷል። አናቱና እትዬ ዘርፌ ከወላለቀው ማዕድቤት ውስጥ በሮስ ይጨናነቃሉ። ምን እንደሚሰሩ ለማወቅ አልገባኝም። የጋራ ማድቤታችን እንደሁ ሰለሽቅም በሮስ ትታፈናለች። ወደ አናቴ ጎጆ ስጠጋ እትዬ አብቡ ከኛ ቤት ጎድጓዳ ሳህን ይዘው ሲወጡ ደፋ ላይ ተገናኘን።

«ውይ ስንዬ መጣሽ?... ካሰኞ ኮ ወንድ ልጅ ተገላገለች። ግቢና እንኳን ማርያም ማረችሽ በያትኩ» አሉኝ።

ገፅታቸውን የሞላው ፈገግታ በቅሬታና በአሮይታ መሀል ተወጥሮ የሚያሸነክል አይነት ነው። አየተፋጠኑ አልፈውኝ ወደ ጎጇቸው ገቡ። ከወዲያ የግቢዮችን ሀፍናትና እናቶች ጫጫታ አየተነሳ ይወድቃል። ሁሉም ከነካሰች ቤት መሰብሰባቸውን ተረዳሁ። በኮርጀዬ ውስጥ የታሰሩትን ሳይሸሙ ያደሩ ሳንቲሞቼን እያንጋጋሁ ወደ ቤቴ ገባሁ።

ካሰኞ ወንድ ልጅ ተገላገለች! የእትዬ አበቡ ድምፅ በጆሮዬ አቃጨለብኝ። ካሰኞ ከወር በፊት ሰኔ ብቻ የነበረችኝ ታሪክ እንባዬን ሊያፈስሰው ተፈታተነኝ።

...አንድ ምሽት ሁለት ቀን ተሸጠ ባይባል ያደረባትን የለዘዘ ቆሰ በምጣድ ላይ ሞቅ ሞት አርጋ ወደ ጎጃና ይዘ ወጣች። ለነስተኛ ቀን ማደር የለበትም። ካለበለዚያ መክሰሯነው። ሁሌም ከምታዘወትረው ጠጅ ቤት ገባች። ብዙም አልቀናት። የተሸጠላት የሀምሳ ሳንቲም ብቻ ነበር።

እየመሸ ነው። ጠጅ ቀጅው ገበናሩ ጠራት። ሁለም አራት ሲበላ እሷ በስፍራው ካሰኞ ጠርቶ አራቱን ያጋራታል። ዛራም አብራው አራት እንድትበላ ወደ ጎዳ ይሏት ገባ። የሚንጫጫ ርሀቧን ልታስታግስ ማዕዱን አጣጣመችው። በልተው ሲጨርሱ ልትወጣ ተነሳች። ገበናሩ ግን ጎትቶ አስቀራት። ታገሱ። እንዳትሙህ አሉ

አፈናት። ከቆሻሻው የጣውላ መለል ላይ አጋደማት። በመጨረሻም ደፈራት። ጉዷን አምታ ከረመች። በኋላም ማርሚን አወቃች። ገበናሩን ፈሰገችው። ክስተቱን እንደሰማ ስራውን ለቀቀ። በገበናሩ ቦታ ሌላ ጠጅ ቀጅ ተቀጠረ...

ይህን ስትነግረኝ እላለቀሰችም ነበር። ልቤ አስኪፈርስ ያነባሁት እኔ ነበርኩ። አሷ ግን ከእናቷ ጀምሮ ማንም አምኖ ላልተቀበላት እጣ ፈንታዋ፣ ተጋሪ ላጣችለት ህዘንዋ፣ በብልግና ለተተረጎመው በደሏ፣ እዬዬዋን የምታስነካው ወደ ውስጧ በምታንጠባጥበው እንባዋ ነው። ወደ ውስጥ ማልቀስ ምንኛ ልብን ይሰረቡር ይሆን?...

«እንኳን ማሪያም ማረችሽ በያትኩ» የእናቴ ድምፅ አሁንም አቃጨለብኝ። ፈገግ አልኩ። ፈገግታዬ ግን የምሬት ነበር። እኛም እንደ እናቶቻችን እንኳን ማሪያም ማረችሽ ሰመባባል መቧታታችን ወግ ማዕረግ አልነበረም። አርግማን ቢሆን እንኳ... ያላዋቂነት፣ የድህነት፣ የህይወት ዘፋ ገፅታዎች አርግማን... በምሬት አሰብኩ። በግድ ስለተበነሰው ልጅ፣ ልታጨናግፈው ራሷን ከአደጋ ጋር ስላላተመችው ካሰኝ፣ እምቢኝ አሻፈረኝ ብሎ ስለተወለደው ጨቅላ፣ ስለ እናቴና ስለ አሱ የወደፊት እጣ... ደግሞም በምሬት ፈገግሁ። በህዘን ጊዘ ቅጭም የሚል ስሜት ጫና ሲበዛበት ለተቃራኒው ስሜት ዕዳውን ያሸክማል መሰል እንባዬ ሲሆኖፍ ፈገታዬ ገደብ አጣ... ግን ከማልቀስ አይሸልም – ውስጥን ያነዳል።

አፈን ደምደም አለኝ። ሀሳቤ ይመርራልና ተንሸገሸኩ። እየፈገግሁ እንኳን ማርያም ማረችሽ ልላት ይገባኛል ወይስ አይገባኝም? መወሰን አቃተኝ።

በደመነፍስ ወደነካሰች ጎጆ እየተጉተተኩ ሐዲኩ። የግቢያችን ቤተሰቦች በፍራሻ ዙሪያ ተክልኩለው ይንጫጫሉ። አይ የነሱ ነገር! ድህነታቸውን በጫጫታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይረሱት ይመስል የመጫሚህን ባህል አዳብረዋል።

ወደ ውስጥ ገባሁ። ካሰች ጨቅላዋን ታቅፋ ከተኛችበት ፍራሽ ቀና አለች። አየችኝ። አየኋት። አንደበቴን ከማላወሌ በፊት አይኖቿ ወደ ውጭ ሲያነቡ አየኋቸው። ጉንጮቿ በቅፅበት በትኩስ አንባዋ ራሱ። በአንባዋ የምትነግረኝን ስማሁት። እኔም በአንባዬ ላፅናናት ላዋራት... የተንቆረዘዘ አንባዬን ለቀቅሁት። ተግባባን! ወደሷ ተንደረደርኩ። ተቃቀፍን። ተላቀስን።


ለለነገ አጣዋ በለቅሶዋ አወጋችኝ። በለቅሶዬ አዳመጥኳት። አዲሱ ጨቅላ ሽቅብ እግሮቹን እያንፈራገጠ ማለቃቀስ ጀመረ። ደግሞም አሪ አለ።

'ምንድን ይሆን የሚጠይቀን?'

'እንግዲህ ምን ልታደርጉኝ ነው?' እንደሚለን ተሰማኝ።

ለስታችንም ማልቀስ ቀጠልን። እናቱ ህፃኑን አቅፋ! እኔ ደግሞ እሷን አቅፌ... የባልቴቶቹ ጉስቁል ልጆች።

ልቦለድ



ሰልኝ - ተባልኝ - ጀባሳል!!

አብረሃም ረታ ዓለሙ

(ከ1848 - 1983)

በ1800ዎቹ ሩብ ዘመን ታሪክ ...

መሳፍንቱን «ከሪንገ» በመዘረር፣ እነራስ አሊን ወጪ በማድረግ፣ በቦታቸው ቋረኛ ካሳን አስነስቶ፣ ከማዕዘን ማዕዘን እየተወነጨፈ «በፅኑ» የድሆች ድጋፍ ንጉሰ ነገስት ቴዎድሮስ አልተሰኘምን? በዚያን ዘመን ዋድሣና የአገር ቤዛ ተገኝ ተብሎ ጉንደርና ዙሪያ ገባው ጮቤ አልረገጡምን? ፀሐይ ንጉስ ነገሰ ተብሎ ነዋ! በኋላም ንጉሳዊው እንቅስቃሴ ሲጀመር «አረመኔ» እና «አብድ» ተብሎ አልተዘበተበትምን? አልተዶሰተበትም? በአራቱም

t.me/OLDBOOKSPDF

ማዕዘን አልተዋከበምን? ድንኳን ለድንኳን በባዶ እግር መንከራተት ነውር ሆኖ ለምን ጉንደር ቤተመንግስት «አልተሞላቀቀም» ተብሎ የንጉስ ላህይ የለውም ተብሎ አልተሸረደደምን? ዛሬም ምንም የታሪክ ምልክት በሌለባት መቅደላ እንደ ብዙ ለምች ናሮ የብዙ ሚሊዮን ወገኖቹን እኩይና ሰናይ ምግባር በአንድ ጫንቃው አልተሸከመምን? ሞተ። ያዘነለት ሁሉ ...

«መቅደላ አፋፉ ላይ ጨሽት በረከተ፣
የሌቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ምተ።
የየጀውን ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ
የወለውን ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለራስም ገደሰውም አያውቁ።» ብሎ አለቀሰ ይባላል።

በቴዎድሮስ እንጀታቸው የተቃጠለ ሁሉ መጪምቹን አጼ ተክለ ጊዮርጊስና አጼ ዮሐንስን ባድቅ፣ ቸር፣ ደግ አላሏቸውምን ከቶውንም በቴዎድሮስ ላይ ጦር መርተው አምጥተው ስለስበገደሏቸው ተቃውሞ ግጥሟቸዋልን? ፍፁም! በፍፁም! እንዲያውም ከአረመኔ አና እብድ «ባላገሱን» ተባለ እንጂ። «ዶሮ በየፍጉ ከምር ቆሞ ይሮሀል» ሆነና ነባሩ እንዲያውም ከንጋሴ ዘር ተገኘው ንጉስ ተገኘ ተብሎ «ፍደሳ» አልተደረገምን? አፄ ዮሐንስ ቢነግሱ ንግስና ወደ ባለቤቷ ተመለሰች ተብሎ 'ተፈደሰ' ይባላል!! ስርወ መንግስት ወደ ጥንት ቤቷ 'አክሱም ዕዮን' ገባች ተባለ!! «ለዕለ አሐዱ በከመ ምግባሩ» ሆነና፣ የቴዎድሮስ እጣ ደርሶአቸው፣ ሙተማ ላይ 'ለአንድነቷ' ቢወድቁ 'ይበላቸው! አሳቸውን ብሎ ንጉስ! ቋስ ናቸው! ድሮም ቢሆን ንጉስ ያዋጋል እንጂ እንደ ተራ ወታደር ጦርነት መሀል ገብቶ አንገቱን ማስቆረጥ አይገባውም። አበደ ማህዲ! ይበላቸው! ደግ!! አሰይ!!! ተባለ ይባላል!!' እንዲያውም

«... አፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው፣
እኛም ሁላችን ናቅናቸው።
ንጉስ ቢሏቸው በመሀሉ፣
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ።» ተባለ ይባላል!!

ምኒልክ ነገሰ። የሳህለ ስላሴ አጥንት፣ የንገደ ሰሎሞን (ይሁዳ) ዝርያ፣ ዛውዱ ተገቢውን ቦታ አገኘ ተባለ! ሽዋ ጨፈረ! ዓመት ሙሉ ደገሰ! አዲስ አበባ ተብሎ ተከተመ! 'የቴዎድሮስና የዮሐንስ ግፍ በምኒልክ በአባ ዳኘው ተፈጠመ' ተባለ! ይባላል። ከፍጥረት አዳም ወይም ከጥንታዊ ጋርዮሽ ስርዓት ጀምሮ ሲባል!! ይኸው እዚህ ላይ ደርሰናል። በአድዋ ጦርነት ወራሪውን ጦር አስክመረብ ወንዝ አባረረው በድል አዲስ አበባ ሲገቡም ...

«ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ አንቁላል ነበር ይሸን ጊዜ አበሻ።
መካናቹ ብዙ በሮም በሶሪያ፣
ወላድ አፎጋየሁ በሲትዮጵያ። (ዮምኒልክ አናት)
ምኒልክ ተጉዘ የምትጠይቀኝ፣
ፊትም አሳሰፈ ኋላም አይገኝ።» ተባሰላቸው ይባላል!!

ሰንበት ሲባልም ወቃሽ ተነሳባቸው። ዋኤርትራን ህዝብ አሳልፎ የሰጠ፣ ጸቡቱን ለባቡር ሀዲድ የሸጠ፣ ዛሬ ለእርስ በርስ ጦርነት የዳረገን፣ ሌሎች በድንኳን አየተንከራተቱ አገር ሲያቀኑ፣ አጅሬ አንዱ እንኮበር፣ አንዱ ደብረ ብርሃን፣ አዲስ ዓለም፣ አንዱ እንጦጦ፣ አንዱ አዲሳባ፣ ቤተመንግስቱን እያስገነባ አዝማሪ አቁሞ ጠጅ እያስጣሰ ... ህዝቡን በሆዱ ደለለው፣ በተለይ ሸዋን' ይባላል!! ከምኒልክ እስክ ተፈሪ ባለው የጊዜ ድንበር ላይ መጠነኛ ሁከት ቢፈጠር፣

«ወይ ጠቡን አልተው ወይ ራሱን አልቻለም፣
ለንክሱ ሂደ ያንንም ያንንም።...» ተባለ - ይባላል!!

t.me/OLDBOOKSPDF

ምኒልክ በአልጋ - ዋሉ ሞቱም። ንግስት ዘውዲቱን ለማንገስ ተሞከረ። ባልሰየው ራስ ወሌ ብጡል ሰሚኦ ስለነበራ ንግስና ሾልካ ወደ ስሜን ልታዘግም ሆኖ ስጋት ተፈጠረ ይባላል!! መላ ተመታና ልጅ ኢያሱ ነገሱ። የአምዱ ምኒልክ የልጅ ልጅ አሰይ!! አሰይ!! ተባለ። በወዲህ ልጅ አግር፣ በወዲህ በምኒልክ አጠገብ፣ የምኒልክ ወዝ እየሸተታቸው ያደጉ በመሆናቸው፣ ዘመናዊነት ይፀንገባቸዋል ተብሎ ነዋ!! መንፈቅ እንደቆዩ ነባር መጣ። «ሽርጥ ታጠቁ! ሰላት ሰገዱ!! የእስላም ቅምጥ አኖሩ!!! ከቱርክ ተዋዋሉ! አደን እያሉ ዝሆኖችን ፈጁ!! የአሰተዳደር ስራ ትተው አመንዝራ ሆኑ!!! ንግስ እንጫወት እያሉ ስንቱን መኳንንት መርዝ በተቀባ ሹል ብረት ወግተው ፈጁ ...» ተባለ!! ይባላል!! በኋላም ፍቼ ታስረው ከዚያም አምልጠው አፍቀራ በረሃ ሲገቡ ሆድ ባሳቸውና፣

«... ሱሪዬን አውልቄ አገልድሚያታለሁ፣

ቀን የሞላልኝ እንደሁ፣ እታጠቃታለሁ።» ብለው አገራጉሩ ይባላል!

ኋላም እነሁ የአምዱ ምኒልክ የልጅ ልጅ እንደ 'ዱርዬ' ታድነው ከተያዙ በኋላ በጋራ ሙሰቃ ታስረው ቆዩ። ከዚያም ሞቱ ተባለ!! ህዝቡም፣

«ሲሆን ተከናነብ፣ ያለዚያ ልበሰው፣

ምን ያንፈራግጣል፣ ከወደቀ ወዲያ ሰው» አላቸው ይባላል!

ከልጅ ኢያሱና ከንግስት ዘውዲቱ ሞት በኋላ በ1923 በኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ ተባለ! ብልሁ የምኒልክ የእህት ልጅ የራስ መኮንን ወ/ሚካኤል ሁለተኛ ልጅ፣ ተፈሪ መኮንን ስመ - መንግስታቸውን 'ኃይለ - ስላሴ' አሰኝተው ነገሱ። ቀኃስ ተባሉ። የመጀመሪያውን ፓርላማና ህገ - መንግስት አደራጁ! አረቀቁ!! አፍሩዙ

አውቀት! አዩዙ ዘዴ!! አይዙዙ ብልሃት ... ኢትዮጵያንም ከዓለም ማህበር አስገቧት ተባለ!!

«ኃይለ ስላሴ ሐዋርያ፣

የሰራ መሪ ባለሞያ።

ባገዲራውን ይዘ የሚገለግለው፣

አንድም ለውም የለ አሱን የሚደርስለው።

... ሴላውማ አውሬ በጣሙን ጪካኝ ነው

ነገር ግን አንበሳ በዓለም ተፈሪ ነው።» ተባለላቸው ይባላል!!

ወዲያው ማይጨው ዘመቻ ሆነ። በመርዝ ጋዝ፣ በእቶን እሳት ተሸነፍን ይባላል!! ንጉሱም ብይን እና ዳኝነት ከዓለም ማህበር አመጣለሁ አሱና ወደ አውሮፓ ዘለቁ።

«የማይረባ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ»

ከማይጨው ደንብሮ ሱንዶን ገባላችሁ።» አሱና እነቀኝ ጊታ ዮፍታሄ ንጉሴ ተቀኙባቸው ይባላል!! ንጉሱ ሸሹ፣ ህዝቡን በክራ ቀን ከዱት ተባለ። ይባላል!! አንቱታው ቀረና 'ይቺ ተፈሪ' አስከመባል ተዳረሱ። የአምስቱ ዓመት የስደት ዘመን አበቃና «ጠሃዩ ጠቅል ነፃት ይዞ ይረስልን» ተባለ!! ይባላል!! ህዝቡም

«አርበኞች መምቶን ማን አስተማራቸው፣

ታሳቱ ጴጥሮስ ነው ባርከው የሰጣቸው፣

ሚካኤል መንገዱን አውቆ ቢመራቸው፣

በጠቅል ጉዳና ብርሃን ወጣላቸው።» ብሎ ዘመረ ይባላል!!!

ጉጃሜው በላይ ዘለቀ 'ከፋኝ' ብሎ ቢሸፍት 'ይኸ ከሃዲ ተብሎ' አየሰሌ! ተባለበት ይባላል!!! ታድኖ ተይዞ ሲሰቀል ኢትዮጵያ ዳር እስተዳር ተንሰቀሰቀች አሉ!

«ደ! በላይ ዘለቀ ደ! በላይ ዘለቀ፣

በአስር ሳንቲም ገመድ አንገቱን ታንቀ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰቀለ ቢሉኝ መውዜሩ ነው ብዬ ...
ኮበርታው ነው ብዬ ... ጠመንጃው ነው ብዬ ...
ሰኳስ በላይ ናሯል ትልቁ ሰውዬ
... በላይዬ ሸጋው በላይዬ ...» እየተባለ በዱር በገደል፣ በየመሸታው ሰፈር፣ አዝማሪ ተቋሞ ተዘፈነለት ይባላል!!

«ፀባይ መልቱ፣ ጣና መልቱ በደረቁ ላጪኝ፣
ራሌን ላያመኝ መደፊሬ ቆጪኝ ...»

አለና ድፍን ጉጃም ተጢስ አባይ ኋኩል አንባውን አንፏቃው ይባላል። እንግዲህ ይባላል አሉ!!

በ1953 ታህላስ፣ ጃንሆይ በወዲህ ሰጉ-በኝት ጥናም ሲል ምክር ስመቀበል ወደ አሜሪካ ወጣ ቢሉ አደሰመኝ መሰሉት፣ የልጅ አክል የሚያምኑትና የሚወዱት ጀኔራል መንግስቱ፣ ወንድሙን ገርማሜን፣ ፅጌ ዲቡን፣ ወርቅአ ገበየሁን፣ ይህ መፈንቅለ ዙፋን ሲሞክር ይሽ ዘመነ አመጣሽ ስልጣኔ ዘልቆኛል ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ ከፈሽታው ብዛት ... ሽንቱን በውስኪ እየበረዘ ተካፍሎ ጠጣ ይባላል!!። ኃይለስላሴ ወደ አዲሳባ ተመልሰው በስቅላት ቢቀጡት ...

«አባትህ ቁረንጮ እናትህ ለማኝ፣
የኃይለስላሴ አምላክ ጉድክን ሰሳያችኝ::»

እያለ ህዝቡ ሲሳለቅበትና ሲረግመው ሰነበተ አሉ!! ሲሰቀልም ግሎዝ አካሉን አክክክንቱፍ! አስበት አሉ!! «... አንተ የቁረንጮአም ልጅ ... ክቁርንጮ ለባሽነት አውጥተው ጀኔራልነት ቢያደርስህ ...» አሰና ተዘባበተበት ይባላል!! ይሽ ቀን አለፈና ስድሳ ስድስት ሲባይ እውነተኛው የኢትዮጵያ ልጅ ተብሶ ፎቶው ተባዝቶ፣ ከጥላሁን ግዛው፣ ማርታ መብራህቱ ፎቶ ጋር ስህዝቡ ታደለው ይባላል!! ግማሚውም ከአዝማሪው ጋር ...

«... ለተራበው አጉራሽ ሳጣ ሰው ደጋፊ፣
ሲሆን ያሳዝናል እንደ አፈር ርጋፊ::
ሞት ምርጫን ባወቀ እንዴት በወደድነው፣
ያለኛል እንዳንዱን ዳግመኛ ቢፈጥረው::» ሲል አንጉራጉረ::

ህዝቡም ድንኳን ጥሎ እንደ አዲስ ሰቅሶ ነጠላ አሸርጦ፣ በቤተመንግስት ፎቶ በገሃድ ወጥቶ፣ እነአማን እንዶም በየማዕረጋቸው ጫፍ የህዘን ጨርቅ አስረው «ወንድሜን! አለኝታዬን! መካሪዬን ...» እያሉ በገሀድ ትኩስ ለቅሶ አደረጉለት ይባላል!!

የአዲሳባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ይህቺን 'የዙፋን - ንቅንቃ' እንደ አቅጣጫ መጠቆሚያ በማየት፣ በጎቡዕ መደራጀት ያዙ:: በየአቅጣጫው ህዝቡን በነደፉት መርሐ ግብር ስር ለማሰለፍ ትግሉን ተያያዙት:: በሲሚናሩ፣ በግጥም ውድድሩ፣ በበራሪው ወረቀት ... «ዙፋኒቱን መነጥነጥ» ያዙ:: መሬት ለአራሹ ቢሰጥ፣ የአዬው ስርዓት ቢገረሰስ፣ ሶሻሊዝም ብቸኛ መንገዳችን ቢሆን፣ ፋብሪካዎችና ቤቶች የህዝብ ቢሆኑ! የመደብ ትግል ቢካሄድ፣ የብሄሮች እድል በራስ ቢወስን! ድህነት ካገር ይጠፋና ብልፅግና ይሰፍን ነበር» አልን! ተባልን! አስባልን! ይባላል!!

እንግዲህ ቀ.ኃ.ስ በነገሱ በአርባ ሶስት ዓመታቸው የ1966ቱ ወዳጃችን (ስም አይጠፉ) ክተፍ አለ:: ዙፋኗም 'ተንግጓገጨች' ቀ.ኃ.ስ ከወደ ግንባራቸው ቀንደኞች፣ ወደ ቁጣቸው ግድም ጭራ ቢጤ ተተክሎባቸው (በኳሪራ ቴክኒክ አንደ አቡነ መርቆሪዎስ ሽጉጥ) ብር ታቅፈው ውሻ ሲመግቡ የሚያሳየው ፎቶግራፋቸው በአስር አስር ሳንቲም ተቸበቸበ! አንደ ነርቭ አርዓቸው፣ ሽንታቸውን መከፈል አቅቷቸው ... ተባሰና አንደ ዶሮ በኦንገት ፍንችር ብለው ተገኙ! ተባለ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

ተማሪውም
«ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ
እንደነ ሆቺሚን ... እንደ ቼጉቬራ ...» እያሰ የቀሰቀሰው እሳት ፈስጉ ወደ ሶሻሊዝም እንዲያሳይ አድርጉ በህዝቡ መሀል አቀጣጠለው። ለመሸራፍ ድጉማ ወደ ቤተመንግስት ጉራ ብሎ የነበረው የጦር ኃይሉ ተወካይ «በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት» እንዲሉ ሆነና ሲያስበው የአገር ሁሉ አሰቃ የሚያደርገውን ግገርንት በሹልክታ ተቀዳደ። ተሜ - ያነሳችውን መፈክር ከአፏ እየቀለበ መልስ ይሰጥ ጀመር፣ ይባላል!! መሬትንም ሰአራሹ ሰጠናት። ዓሰምንም የወዛደሮች አደረግን አልን። አዜውንም ክነ ስርዓታቸው በትራስ እፍን አረግንና በቢሮአችን ስር ካንቻ መታንባቸው። ሶሻሊዝምንም ብቸኛ መንገዳችን አድርገን 'ቦፑሽኪን' በኩል ከሌኒን አሰክ መሳመድ ደረስን። 'ፋብሪካውንና ቤቱንም ሰህዝቡ አድለነው 'ተአምር' አሳየነው። የመደብ ትግሉንም በቀይ ሽብር አሳት ለኩስነው። የዳቦ ቅርጫትም አበጀን ... የተባለውንና የታሰበውን ሁሉ ሞከርን። ድህነት ግን፣ በእፍ በአፍንጫችን ገባና አንጀታችን ውስጥ፣ ከፍ ሲልም ሀሊናችን ውስጥ 'አከንዲራ' ይጫወት ገቢ።

ሁሉም ፖለቲከኛና የፖለቲካ ድርጅት 66 ዓ.ም የወለዳቸው አስተሳሰቦችና ድርጊቶች 'ፊታውራሪ' አኔ መሆን አስብኝ በማለት 'ስለውጥ ሐዋርያነት' ተጫጨደ፣ ተጨራገደና የማናዊም ፀጋማዊም በለስ ለቀናቸው ወታደሮች ዙፋን አበጅተው ጥግ - ጥጉን ያዙ። አብዮት ተወለደች... ዳይ ማለት ጀመረች።

... ደርሶ ማንኩራንር ልማዱ ነው ድሃ
ለየቃዘቃዘው የሚጠጣው ውሃ።
ሕምታለሁ ብሎ ሰው ምን ማዘኑ፣

ቅጠል አይበጥስ ካልደረሰ ቀኑ።
አበላለሁ ጮማ እጠጣለሁ ጠጅ፣
ልኔን ያስለቀሰኝ የድሃው ራብ አንጂ ...»

አያሱ 'ሦብዜራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ' የተባሉት 'ኢትዮጵያ - ትቅደም' የሚል መነሻር ሰክተው አየዘመሩ፣ በቢያሳው ሽኑበት ... በባርላማው ፈሱበት ... በቤተመንግስቱ ፀነሱበት ... ተባለ! ይባላል!!

አስተባባሪዎቹ፣ ተሜን 'ያው ሂዱ - አስተምሩት' ... አድንት በህብረት ለአውቀት ለሰራ ዝመቱ አሏቸው ይባላል!! አማን አንዶም፣ ተፈሪ በንቲ፣ አጥናፉ አባተ በየተራ 'ንጉስ' ይሁን አልተባለም? ህዝቡና ጦሩ 'ይቺም አለችና' ብሎ በደስታ ብዛት ታንክ እያሽከረከረ ፈነጠዘ ይባላል!! ዓመትም አልቆዩ ተራ በተራ ክነመኖሪያ ቤታቸው 'ንግስናቸውን' አስበው እንኪን ሳይጠግቡት በዚያው በፈንጠዝያው ታንክ ተደመሰሱ ይባላል!! ፅዮንቹን ጠኪንንት በማመንገሸከ የጀመረው የኢትዮጵያ ትቅደም 'ጥርሶች' የራሱን ጀኔራሎች በማላመጥ ጥንካሬውን አሳየ።

ብሄራዊ አስተባባሪ ደርጉን ከሁሉም በላይ የሚፈታተን ድርጅት ተፈጠረ። ምሁሩ ሰሁለት ተሰነጠቀና አንዱ ከደርጉ - ጉያ፣ ሲላው በግገባር ጦር መዘ ይተጋተግ ጀመር። ሌት ወንዱ 'ኢህአፓ ይሰምልም' አለና - ከፅንፍ ፅንፍ አረበበ ይባላል!! እኛም 'ይሰምልም' አልንና በደማችን፣ በሀብታችንና በአላባችን አለመለምን።

«ለዘመናት በጭቆና ማቅ ታስሬ
በማና ሰንሰለት ተጠፍሬ ...
እንዛለሁ በድል ጮኖና» የሚለውን በዘመርንበት አንደበት «ዲሞን በዲሞትፈር ...» አልን! ቀይሽብር መክርተፍ መሰልቀጥ መጠቅጠቅ ያዘች!! ... የኢትዮጵያ ትቅደም ጥርሶች ከመቼውም ይበልጥ ተንቀራጨጩ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀይ ሽብር! ... ጥቁር ሽብር! ... ነጭ ሽብር! ውኃ ስማያዊ ሽብር!! ውጦኔ ሽብር! የስታሊን በትር!! የማኦ ከዘራ! ... የሌኒን አርጪሚ!! የማርክስ ለበቅ!! የኤንግልስ ብረት ቦቅስ!! የቼጉቬራ ሲኬኒ፣ የሆቺሚኒ ዘንዘና!! የኪም ኢል ሱንግ ጠገራ!! ወጣቱን አጪደች!! ሰለጠቀች!! ... በህይወት የተረፈው የሚደበቅበት ጨነቀው። ወደ ጫካ የገባው «የኢህዓሰ» ሰራዊት በጫካ ውስጥ የራሱን ባላንጣ አፍርቶ ይሳደድ ገባ። በየከተማው የነበረ ወጣት ኩላይ ደፍ፣ ተስር ጉርፍ፣ ሆነበትና ነፍሱን ለማትረፍ ...

«ታርሰም ተሸምቶም ይበላል አንጀራ፣
እንደምነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ።
ያለአግባብ የሆነ ብዙ ጉደሰት ቢያውቅም፣
ሰው ርጥብ ነውና መቼም ንዶ አያልቅም።
አሰቅሳለሁ ባይኔ ሳዝን በወዳጅ፣
አንደሰማይ ኮከብ አየራቀኝ ከጅ።
ብለነው ብለነው ካልሆነ ንገሩ፣
ብርና ወንድ ልጅ የትም ነው ሀገሩ ...» እያለ በልቡ እየዘመረ የመጠለልን ያህል በኢማሌድህ፣ በውትድርና፣ በቀበሌ ተበትኖ አንድ ትውልድ 'አለፈ' ይላሉ ተንታኞች። ይባላል!! ... ስደቱ በሰፊው ቀጠለ ... በሰሜን ክፍል ቀድመው 'ብረት' ያነሱ፣ እኛም ጥርስ አለን እያሉ፣ በትሩ ሲያርፍባቸውም ሲመኩም፣ በምስራቁም ባእድ ወረረንና የእንጀራ እናታችን ምስር፣ ኩባ፣ የመን ተረባርበው የኢትዮጵያ ህዝብም ደሙን ገብሮ፣ 'በኢትዮጵያ ትቅደም' መነጠሩ ላይ 'አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት'ን ጨመረና ፊቱን ወደ ሰሜን አዞረ ይባላል!!

ሶስት ሲቃነ መናብርት በየተራ ሲመረጡ። «አልማዝን አይቼ - አልማዝን ባያት» ተብሎ ተዘፈነ ይባላል።

«ያለምንም ደም እንከኗ - ይውደም፣
በቀና መንፈስ ኢትዮጵያ ትቅደም» ተባለ!!
«... ተነሳ ተራመድ - ክንድህን አበርታ፣
ላገር ብልፅግና - ለወገን መከታ።
ወንዞች ይገደቡ ይዋሱ ለልማት፣
በክንቱ ፈለዋል ለብዙ ሺ ዓመታት ...» ተባለ እና ለልማት ለብልፅግና ተንደረደርን ይባላል!! «መንግስቱ ኃይለማርያም የጭቁን ልጅ ነው። ሰላምታ ሲሰጥ በግራ እጁ ነው። ቀይ - ስካርፍ አስሯል። የግራ ዝንባሌ ያለው ተራማጅ ሻለቃ ነው ...» አልተባለም? ... ሺህ መንግስቱ ብለው ተማሪዎች ስጋ - ሚጸ ድጋፋቸውን ሰጡት ይባላል!! አብዮት ስባ፣ ጉትታ፣ መቃበር ፈንቅላ፣ ቱምድሮስን - እንደገና ሽመቸው አልተባልንም'ንዴ? - በአንድ የሰነ ግጥም መድብል ውስጥ «... ታጠቅ ዘላለማዊ አንበሳ ... ካሳ፣ በመሶ ዓመቱ ቢያገሳ፣ ስንቱን ቀሰቀሰውሳ» ተባለለት ይባላል!! ይላሉ እንግዲህ። በቀይ ሽብር ማግስት የተሰባሰበው ማርክሲስት ሁላ ልዩነቶቻችንን አቻችለን 'በእከሲዶን' እንታገል አሉና ጠንካራ የወዛደር ፓርቲ ለመመስረት «ኢማሌድህ» ይጠንክር! ተባለ! ይባላል!! ... ጥቂት ሰንባበትንና ጭቁኖችን አፋጨ፣ ጠመንጃም አማዘዘ፣ ከጥራት በዘሃት አመነ ... ኢሮሮሮሮሮ! ተባለ!! 60ዎቹን አመነሻርኩ፣ እነአማንን ሰለቀ፣ ኢህአፓዎቹን ሰልትጠ፣ በነበረው ክፍት ቦታ፣ ጨንራው ውስጥ ... 'ኢማሌድህ' ዎችን አነባብሮ ፈጠራቸው። ዋጋቸውን አገኙ። አዲዮስ ተባለ። አንቱሱ ፎርሳም መደሻቸውን ብድግ አድርገው ራሳቸውን ወቀሩበት። የሚበላውን በላላና አዲዮስ!!

በኢትዮጵያ ትቅደም መነጠር ግራና ቀኝ እያየ ባቡሩ መጓዙን ቀጠለ። «ፈጣን ነው ባቡሩ ... ቆራጥ ያልሆናችሁ እንዳትሳፈሩ ...» ተባለ!! ኢሰፓአኮ ተቋቋመ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጓዱ ሁሉ ርችት አውጥቶ፣ ቴሌቪዥን ገዝቱ፣ አዲስ ልብስ አለፍቶ 'ኢስፓአኮን' አቋቋመ። የለበሰው ላያድፍ በአናቱ 'ኢስፓን' ደገመ። ያየኞ ዓይን ነች፣ የሰማችም ጆሮ!! ይባላል!!

እንግዲህ ኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊ ስርዓት የሚያስገባትን መንገድና የሰላት ሺ ዘመን ችግር፣ የሆነውን ወይም የነበረውን 'ፓርቲ' እና የፓርቲ አሰራር ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀባጀች። ተባለ!! ይባላል!! - የሰሜኑን ከፍለ ሀገራችንን ችግር ለመፍታት 'ቀይ - ኮከብ' ዘመቻ ብቸኛው አማራጭ ሆነና ጉድ ጉድ ተያዘ። ቢመች በሰላም፣ ቢያቅት በጉልበት ተባለ። እና አስመራና ምጥዋ በቀይ አጊጠው 'ቀይ' ተመከረባቸው። ህዝቡ 'ቀይ' አሰበ። መፍትሄውም 'ቀይ' ሆኖ ቀረ ይባላል!!

መንደር ምስረታ ቀጠለ። በዓለም ላይ ወደር የማይገኝለት ተግባር ነው ተባለ!! አሜሪካንም ለዚህ የበቃችው በስፈራ ነው ተባለ!! ትንሽ ተቆይቶ ህዝቡን በግድ ከመኖሪያ ፈንቅሉት ተብሎ ... እሪፊፊሪፊ! ተባለ!! ምህላ ተደረገ። ኪራይሶ!

በዓመቱ ኢህዲሪና ህገ መንግስት ተብሎ ህዝቡ 'ቀይ ሙታንቲ' በለማያዊ ከትና ሱሪ ለብሶ በንጠር ከተማ ጮማውን ቆረጠ - ጠጅ በሕሽንዳ ታደለው። ወይም ተራበ፣ ተሰደደ፣ ታረደ፣ አለቀ ... ይባላል!! በቃ ህዝቡ አካባቢውን ሊያስተዳድር ነው፣ ኢትዮጵያም ዓለም አቀፍ እውቅናን ተቀዳጀች ተባለ!! ተዘፈነ!! ተባለ!! መቼም ሁሉም ነገር ለ'ጉድ' ተባለ።

ቀጠለና በእኩሌታ ወሩ እርስ በርስ ተመራርጠው ራሳቸው 'ኢትዮጵያ ትቅደሞች' በመስኩት ወጡና በበር እንደ እንግዳ ገቡና እሞኙን፣ አጃጀሉን!! ተባለ! «ለምንት አንገለጉ አህዛብ» ሲሉ ጴጳሱ በሽጉጥ ሀገሪቱን ባረኩ። የሽንጉ አባል ሆኑ። ለሽንጉ አደሩ። ሽንጉውን ባረኩ።

ለሽንጉው ባረኩ። ሼኪውም ሶላታቸውን ሶሰቱ። ይባላል!! እንግዲህ የሰማነው ነው።

ደግሞ በዚሁ ሰሞን 'የጭቁን ነፃ አውጪዎች እየመጡ ነው' ተብሎ ህዝቡ በየመደቡ ላይ ሬዲዮውን እየጉረጉረ ሀልሙን፣ ምኞቱን፣ አውነቱን፣ ተስፋውን እያንደቀደቀ፣ የ«ሌራ ሰንጋውን» ጣለ እና የአደባባይ ሹክሹክታውን ቀጠለ ይላሉ!! እያልነሽ አያልነህ፣ ኢህአፓ፣ ሻዕቢያ፣ ህወሀት፣ ኢህድን፣ ኦህዴድ በየመደቡ ተራገቡ። ህዝቡ ሬዲዮ በጆሮው ደቅኖ ከረመ «አዲስ አበባም በስውር ገብተዋል» እየተባለ ሰው ሰድጋፍ መፈክሩን በቀለም ማደማመቅ ሲጀምር «አብጀክቲቭ - ኦንዲሽንስ» ስለለተሟሉ ነገሩ ቀርቷል ተባለ። ይባላል!! ይሽን ሰሞን ነው መሰለኝ፡-

«... ብሄደው ብጓዘው ይብስ ይገጥመኛል፣
የመጀመሪያዬን ማን ያመጣልኛል?...» የተባለው።

ሰንባበትንና እኒሁ ከዛሬ ነገ ደረሱ የሚባልላቸው ነፃ 'አውጪዎች' የኢትዮጵያን ባንዲራ ቀደዱ፣ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አናውቅም አሉ ... ተባለ!! ህዝቡ ተቀጨ፣ ተሰለፈ፣ ፎከረ፣ ምላጩን ሳለ፣ እንዝመት፣ እንግደል፣ እንሙት አለ። ሰያዥ ሰገራዥ አስቸገረ። መንግስትም - እም! ታጠቅ፣ ገመት፣ ግደል፣ ሙት! አለ። አገሬው ሁሉ ያገር ሽማግሌ ቢያጣ አሜሪካ 'መቼስ ዓይኔ አያየ' ብሳ ልትሸመግል በአጭር ታጠቀች። በወሩ ዮ'ኢህዲሪ' መንግስት ከተቃዋሚዎች ጋር ለመደራደር ፈቀደ። ዓለም ሁሉ ፈቀደ። ውጤቱንም ናፈቀ። በረሮዎችም በየአገልግሎች ውስጥ ፈነደቁ። ተልባዎችም በመቀጫ። እንደገና ዘፈን ሆነ። ትግሬና ሌላው ዘር ሁሉ በየጉዳናው ተቃቀፈ። ውስኪ ተገባበዘ። ፌሽታ ሚሽካ ሆነ። በእኩሌታ ወሩ «... ቁርሚአያ - ውዓአያ ... አብዚአበጥብጥ ... ዓይን ግልብፅብፅ ቁርሚአ!

t.me/OLDBOOKSPDF

...» ተባለ። ... ገንጣይ እና አላስገንጥልም ባይ ቢለዋወጡ በየኪሱ ደብቆ፣ የኖረውን የተለመደውን ሰላምታ ይሰጣጥ ጀመር።

«ለንቅና ትጥቅ ወደለሜን ምዕዋ አደጋ ላይ ወደቀች» ተባለ፣ ታጠቅ፣ ዝመት፣ ግደል፣ ሙት፣ ጥንትም ያባትህ ነበር» ተባለ!! ወዲያው እግር በግር የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ታወጀ። የሶሻሊዝምን ስም ያነሳ የሌኒንን ቀን ይስጠው ተባለ!! ይባላል። የኢኮኖሚው ፖሊሲ ወደር የሌለው ታላቅ አርምጃ ተብሎ እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ ጆሮዉ ቡሽና ጉርባሾቭ ሳይቀሩ 'ብፌክ' ደነሱ ይባላል!! ህዝቡ በቤት በአደባባይ ዘፈነ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ሲሲቱን ደብተራቸውን እያጋዩ 'ችቦ' ሲያበሩ አደሩ። የምዕዋን አደጋ ላይ መውደቅ የሰማው ህዝብ በበነጋው በየቀዬው፣ በየአደባባዩ ሰልፉና ድጋፉ 'ይሽ ነው' ለማለት አሸቸገረ። ባንዲራውን እያያት፣ እየጻፉላት፣ እያሸተታት፣ እየለበሳት፣ ደሟ እስተዳር ተንሰቀሰቀ! በቴምድሮስ ጊዜ ከደብረ ታቦር የጀመረ ድጋፍና ተቃውሞ እነሆ ቀጠሰ። ከ200 ዓመት ወዲህ በዕሁፍ የቀረበን መረጃ እንኳን ብናይ 'ምዕዋ መቼም ከአደጋ ነፃ ሆና አታውቅም። ይበሳት፣ ኧረ ይበሳት!! አሰይ! ድሮስ ካላጣችው ቦታ ከዚያ ጋ ማን ተፈጠረ አላት?...

አንድ ኢትዮጵያዊ ግፍ ቢበዛበት።

«... ምናለበት ነበር ምናለበት ነበር፣

ካላጣኸው ቦታ ሌላ አገር ብፈጠር» ብሎ ነበር ይባላል!!

የኢህዲሪ ምርጥ ሹማምንት፣ ሚኒስትሮች «ቀይ መጣህ» እያሉ መሸለኩን፣ ኤና ገመና ማውጣቱን በሰፈው ተያያዙት ተባለ!! 'ምርጥ ጀኔራሎች' መገልበጥ - መንግስት ሲሞክሩ ተደረሰባቸውና 'ሰፊው ህዝብ'

ለምላ ሲያስቡት ለቁርስ አደረጋቸውና የእነሱ ጉዳይ በዘህ ተደመደመ። ይባላል!! ጦሩም ታማኙና - ከሃዲው እየተባለ የገሪጥ 'ይነፋፍቅ' ጀመረ ይባላል!!

በተለመደው ስልት ትግሉ ቀጥሎ የምዕዋን አደጋ አልቅሰን ሳናባራ ጉንደር፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ አስከዛሬም ፍጀው ባልታወቀ ፍጥነት በ'አስገንጣዮች' ዛሬ ኢህአዴግ እጅ ወደቁ። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ አደጋ ያስሃየሰው ገባ። መከረኛይቱ አሜሪካ መቼም ቤትፈጠር - እንዴ - የድሃው ሁሉ አደጋ ተከታታይ አርጉ ፈጥሯታልና በምን አንጀቱ ብላ ለማሽማገል አቀበቆበች።

ህዝቡም፣

«... የሀገር ሉንድነት ... አየተሰፈፈ፣
ሉንድ በል ሉንታምላክ ...
ሰው ተጨፋጨፈ።»

እያለ በቤተ - አስላም፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በእግሉታ ከረመ ይባላል!!

የሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ከሰፈው ህዝብ ጋር በየማሰልጠኛው ከትተው 'ውደቅ - ተነሳ' አሉ። የንግስት ዘውዲቱ አልባሽ የኩይሪታ! የጠጢት የልጅ - ልጅ መ/ታ/ማ ተማሪዎችን እገ-በሻለሁ አሉና ሹፈሩን አስገድደው አውሮፕላን ጠልፈው፣ ወደ ዚምባብዌ ኩበለሉ ተባለ!! ጀኔራል ተሰሩ ገ/ኪዳን በትረ ስልጣኑን ተረክበው የሌኒንን ሐውልት በመገንደስ፣ ሶፕራዘሮንት መንግስቱን ፎቶ በመንቃቀል እና የጦር ኃይላቸውን በምስጋና በመበተን የስድስት ቀን ስልጣናቸውን ለአገድ ቤተ መንግስት ግቢ ለታሰረ አንበሳ አስረክበው በአስክሬን መኪና ተሰወሩ ይባላል!!

ኢህአዴጉችም በበዕር ሊገለፅ በማይችል ፍጥነት በአምቦ፣ በአዲስ ዓለም፣ በጣርማ በር፣ በኩታበር፣ በአጣዬ እንደ ኪስ እየነጠሩ አዲስ አበባ ገቡ። ለኤርትራ

t.me/OLDBOOKSPDF


ነፃነት ይዋጋ የነበረው «ህግሐኤ» በተመሳሳይ ሁኔታና ፍጥነት ከ2000 ሺህ ካላነሱ ምርኩኖች ጋር መላይቱን ኤርትራን ተረከበ። አስመራም ገባ። በወሩ - ኮንፈረንሱ ተዘጋጀ። ሊሰፓ፣ ደህንነትና ሰራዊቱ፣ ወንጀለኞችና የተሸነፉ መሆናቸው እና መበተናቸው ታወጀ። ጠቅላይ ሚንስትሩ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቱ የፖሊት ቢሮ አባላቱ፣ ይኸ ቱባ ቱባው ባለስልጣን በስልፍ አየሆነ እጁን ሰጠ። ዓይን አይታለች ጆሮም ሰምታለች።

በኮንፈረንሱ የህዝብ ተጠሪ ነን ብለው ለጊዜው የቀረቡ ድርጅቶች 'ቻርተር' አወደቁ። ይባላል!! ውል ተፈራረሙ። ወንበር ተደላደለ። የሽግግር መንግስት ተቋቋመ። ፕሬዝዳንት ተመረጠ። ጠ/ሚኒስትር ተሰየመ። ጊዜው የፈቀደውን ያህል ሹመት ተደለደለ። ስልጣን ለሁሉም 'ድርጅት' ለማታመስ ተሞከረ። ኢትዮጵያችንም በዲሞክራሲ 'ጉርፍ' ተጥሰቀለቀለች። ከአሰፓዎች፣ ከትምክህተኞችና ከነፍጠኞች በስተቀር ምድራችንና ህዝባችን ደስታ አናቱ ላይ ወጣና በሀሴት ቧረቀ!! ይባላል!! አስራ አራት የክልል መንግስታት እንዲቋቋሙ ተወሰነ። የፌዴራሊዝም ዘር ተዘራ። ቀዳማዊ እምጎ ስላሴም 'አይቧችሁ ልጠጣ ነው' ሲሉ ወኪሎቻቸውን ላኩ። ልጅ መስፍን ኢያሱም «አይሆንም ውትሮም አባቴን በግፍ ገድለው ነውና አሁንም ለምኒልክ የወራሽነት ቀጥተኛ መብት ያለኝ እኔ በመሆኔ 'ንግስና' የኔነች ...» ሲሉ አስጠነቀቁ። የጀነራሎቹም አሰማቸው ሲለቀም ያ! መከረኛ ሲታረድ የፈሰሰ እንባ እንደ ጅረት ዳግመኛ ፈሰሰ። ተባለ!! ይባላል!!


እንግዲህ በሽግግር ዘመን፤


«የሰዎች ህሊና የዘሩበትን ሁሉ ያበቅላል» የሚል ጥቅስ ያየሁበት መፅሀፍ ጠፋኝ እንጂ አይቻለሁ። እና እየተዘራብን የሚበቅለውን፤ እየተሳሳትን የምናስተካክለውን፤ እየተባልን የምንለውን ... ለማለት እድሜን ሰጥቶ የዚያ ሰው ይበለንና! «አልን - አስባልን! ተባልን! ይባላል!!»

መጣጥፍ



t.me/OLDBOOKSPDF





ግንቦት ዞሮ ሲመጣ

መኩሪያ መካሻ

ዞሮ የማይመጣ ነገር የለም። ወር፣ ዓመተ-ምህረት፣ ዘመን ይዞራል። ታሪክም ዞሮ ይመጣል። መንገድም ይዞራል። አዙሮ ይመልሳል። የቀለበት መንገድማ ዞሮ ያዞራል። ከወራት ደግሞ ወራት አሉ - ዞረው የሚገጥሙን። ዞረው የሚታወሱን። እንደ ግንቦት ያሉት ወራት ለሰርግ ባይሆኑም ለበዓልነት ይመረጣሉ። ከግንቦት አንድ ይጀምራል - የግንቦት መሞሸር። ከዚያም ይቀጥላል።

ያኔ ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት ልዩ ነገር የተደመጠው በወርሃ ግንቦት ነው። ፕሬዝዳንቱ በአንግሊዝኛ ተናገሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተባለ ጊዜ ሁሉም ነገር ብርቅ ሆነ። ብርቅ የማይሆንብን ነገር ምናለ? ልብስ ብርቃችን፣ ፈረንጅ ብርቃችን፣ ህንጣው ብርቃችን፣ መኪና ብርቃችን፣ ስፖንሰር ብርቃችን፣ ኢንቨስተር፣ ቶክሾው፣ ቢዝነስ፣ ኢንተርኔት፣ አሁን ደግሞ ሞባይል ብርቃችን እኛ ራሳችን ብርቆች። ብርቅ የሚሆንብን ደሞ እዚሁ ስልጣኔ አምብርት ውስጥ ያለን አዲስ አበቢያኖች ነን። ያኔ በግንቦቱ ኮንፈረንስ ፕሬዝዳንቱ በእንግሊዝኛ ሲናገሩ ጉድ፣ ያላስ አልነበረም በአዲስ አበባኛ። «ፎኦር ፕሬዝደንት ኩራባቸው – በእንግሊዝ አናግራቸው» ተብሎ ተዘፈነ አሉ - ያው በአዲስ አበቢኛው። ሊላም ዘፈን ነበር፣ ባለፈው ስምንት ዓመት። «አኑም አወትሀ-በት የመመላለሱን፣ ሲታሰር ወደ እኔ ሲፈታ ወደ እሱ» የሚለውን - የኢሠፓ አባላት ሚስቶች የእንቅርቱሮ ዘፈን። ታዲያ እነደዘህ ያሉ ዘፈኖችን የማስታውሰው ጠርሃ ግንቦት ሲመጣ ነው።

አዲሳባ የትውስታ ማህደር ናት። የባራ ሰሞንት ዓመት ወንበር መክፋፈል መጣ። ዮቃቅኑ ዱካውን፣ ፈርጠም ያለው አንዳሚውን። አንዳንዱ በርጪጭግውን ሲላው ኩርሲውን ተቀራመቱት፣ ተከፋፈሉት። ያው ሀገር ሊሸነሽኑ፣ መንግስትን በመንግስት ውስጥ ሊፈጥሩ፣ ኢትዮጵያዊነትን ሊደልዙ አሴሩ ተባለ በአዲስ አበቢኛ።

ብልጦች የታዩበት፣ ቀሽሞች የቢይ ተመልካቾች የሆኑበት ያኔ በወርሃ ግንቦት ነበር። አንዳንዱማ ብልጥ የሰፈሩን አደር ወክሎ በአቋራጭ ብቅ አለ። ብቅ ማለቱስ ባልከፋ - እንደ በረሽኞቹ ፀጉሩን አንጪፍሮ መቅረቡ ነበር አስቂኙ። አንድ የቅርቤ የምሰው ሰው «በክትፎና በአዲስ ቤራ» ያለጠለጠ ሰውነቱን ቀናንሶ ብቅ አለ። ልክ እንደ በክሰኛ ኪሎውን አስተካክሎ ከጭቁን ብሄር - ብሄረሰቦች የወጣሁ ነኝ ለማለት «ግርሻል አርትስ የስፖርት ማፅከል» ዱብ ዱብ ማለቱን አስተውዬአለሁ። ታዲያ አይስቁ ሳቅ ሳቅሁ።

መምሻውን የታጋይ ሽበጥ ተጫምቶ «ዝጉብኝ» ሳገኘውማ ተንፈራፈርኩ። እኒያ ሙጢ የአዝማሪ ቤት «ከታፈምች» ላይቶሩ አውሳከተዋል - የባራ ስምንት ዓመት።

ባራ እንኒ አንዳንዱ ከባቡል ላይ አንገናኛለን። አልፎ አልፎም መግለጫ ይሰጣል። በተለይ በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ማለትን ያመነልና «ሃይ!» እንባባላለን ባዲስ አበቢኛችን።

በዚያን በምርጫ ዋዜማ ወቅት አመራር ሲሰጠን «ምሪጡኝ» አሰን። ለመጀመሪያ ጊዜ በስንት ጊዜው ፓኘርሮውን ይዞ ብቅ አለ። ያኔ ግን ትልቅ ስጋት ላይ ነበር። ካልተመረጠ ወፍራም ደሞዝ፣ ለስላሳ ወንበር፣ መንሸራሸሪያ ፓኘርሮውን ይቀማል፣ ታዲያ ያኔ ሲጋቡን ተመልከቱ ነበር ባልጥልለትም በከንፈር መጠጣ ሸኘቼዋለሁ። ወይ አዲስ አበባ - የከንፈር መጣፈጭ ከተማ። ዳሩ እኔ ሁኜ እንጂ የሰፈር ሰዎች «ምን ሰርቶልን፣ የት አናውተውና» ብለው የግዚርን ሰላምታ ነፍገውት አልነበር? ሚጢጢዎቹ፣ የሰፈር ልጆች ሳይቶሩ የመኪናውን ጭማ አስተንፍሰው አበላጭተውታል። አስቲ አሱን ለቀቅ ላድርገውና ከግንቦት ጋር ተያይዞ የመጣውን ላስታውሳችሁ።

አዲስ አበቢዎች መጋፋት ልማዶችን ነው። ታክሲ ላይ ግፊያ፣ አውቶቡስ ላይ ግፊያ፣ ትያትር ቤት ግፊያ፣ ድራፍት ቤት ግፊያ ምን የማንጋፋበት አለ? ወንበር ላይም ግፊያ። በወንበር መክፋፈሉም ረገድ የአዲስ አበቢዎች ስንብግብነት አገረሸ። ኩርሲው አንዳሚውን ተመኘ፣ ባለ አግዳሚውም አነሰኝ ሲል ቡራ ከረዩ አሰ - የቡራ ከረዩ ልጅ፣ ባለ ኩርሲዎቹ ከአግዳሚው ሲፈነገሉት ቋመጡ። ከወያኔ ጋር አበሩ ተባለ። አልፎ ተርፎም ከፈረደበት ወያኔ ጋር ተዳበለው «ከቻ ኩሰ» ሰጡት ተብሎም ተናፈሰ። ተጠሰ። የዲሞክራሲን ሙዳ ተከፋፈሉት አሉ - በቁርኛ። ያው «አሉ »ነው የእኛ ነገር ...

ሁሉም በየንጡ፣ በየጉጥ - ስርንጉጡ እርይታን ሲጀምር

t.me/OLDBOOKSPDF

አዲስ አበባ በቁንጮነቷ ማላገጧን ቀጠለች። ድራፍት የሚወርደው አዲስ አበቤ ቁንጠኛ ነው። ታዲያ የቁንጣ ብዛት ቸርችል ጎዳና ላይ ሆኖ ቁልቁል ያንሸራቀቀውል። ትንፍስ ይለል። ይህ እንኳ የታ አይለይም። ጭቁን ሴቶች ላይቀሩ የታሞ አኩልነታቸውን የሚገልፁበት ታላቅ ተላትፎ ነው ይኼ። «ተው ነውር ነው» የሚል ከተገኘ በዴሞክራሲያዊ መብት ላይ እንጻላገጠ ይቆጠራል። «ይህ የእግዚአብሄር ቤት ነው መሸናት ያስቀስፋል» የሚልማ ማስታወቂያ «ሠላባዊነት እንዴት አደርክ?» ተባለ በአዲስ አበቤኛ። ብቻ ተሸፈ - በዴሞክራሲ። ከሁሉ ግን በአብዮት ጠባቂ መዝለጥ ቀረ፣ ከሰዎን ይዳበሱ፣ መቀጫው አምስት ብር ነው የሚለው ማስታወቂያ ተነሳ። ከዚሁ ጋር ለዘመናት የተቆራኘን፣ አበጠ ያሰቃየን እንደ ጉም ተበተነ - ግንቦት መጥቶ ግንቦት ሲሄድ።

ግንቦት ቦሮ ሲመጣ የተከለከሉ ማስታወቂያዎች ተለጠፉ። የተከረቸሙ በሮች ተከፈቱ። በተሰደሚ የተዘጉ ቤተክርስቲያናት በራቸው በሰፊው ተከፈተ። ሰበካ ደራ። ሁሉም የመሲሁን ሰልጣን አገኘሁ አለ። ፈሞሽ ኖኅ ሲል በለምጣሞች ላይ ታበየ። እንዳንዱም ደፋር ባህታዊ «ኢትዮጵያ ያጣችው እግዚአብሄርን እንጂ ዲሞክራሲን አይደለም» አለ። ተናገረ፣ ሰበከ፣ አጓራብን - ባዲስ አበቤኛ። ሁሉ ባለማይክራፎን፣ ሁሉ ሰባኪ! አይ ያዲሰባ ነገር? ባህታዊ የሚከበርባት፣ አቡን የሚሸለጥባት። ወሻካች ሥጂያትባት፣ ደሳሳ ቱጃር የሆነባት አዲስአባ ይቅርታ ክልል። ያኔማ ቁከራችን ተሰመጠ «ዘራፍ የክልል 14 ልጅ!» ፎከርን። አወጋን። አሰክብቃን አማን። እኛ የሰም ላኢሶች - አዲስ አበቤዎች።

ምን ባዲሳባ ያልታየ አለ? ፓኅሮ ፈሰሰባት። ኢንቬስተር ፒፓውን አጨሰባት። ስፖንሰር ስሙን አስተዋወቀባት። የጨርቅ፣ የመዕሂት፣ የጋዜጣ ሰልባጅ ታየባት። ተለጣፊዎች በዙ። ተንዛዙ። በየጉዳናው ሚዛን መዛኝ በዛበት። አየር ባየሮች መራት ስመራት ጸሁ። ማስታወቂያዎች ወረሩን። አስተዋዋቂዎች ተውረገረጉብን። እንዲያው በዚህ ስምንት ዓመት ምን ያላየነውና ያልሰማነው አለ?

ከያኔው ትውስታዬ ሴላ ነገር ብልጭ አለብኝ - ቅሬታ ሰሚ። አምን ቅሬታ ሰሚዎች በየተበሉው እንደ እንጉዳይ ፈሉብን፣ በየቢሮው ጆሮአቸውን ሰጡን። ሰሙን። እንደ ሽማግሌ ስፖርተኛ ዱብ ዳብ አሉብን። ግን ምንም ላይፈይዱን - ባንድ ጆሮ ሰምተው፣ በሴላ ሊደፉ - ሰሙን ቅሬታችንን። እንደ ቁጥጥር ኮሚቴ ከዕለታት አንድ ቀን ከእንትልፋችን ስንነታ እነሱ ግን ለዘለዓለሙ እንቀላፋብን። አስታውሳለሁ ያን ሰሞን፣ ቢሮክራሲው አውቶማቲክ ሲሆን። ባለጉዳይ ትንፍስ ሲል። ግን በረዶ ዘነበበት። ያኔ ድንቅ ነገር ተፈጠረ። ለአምሮ የሚከብድ ታላቅ ነገር! ተላላኪው ባለስልጣንነት ተሰማው። ባለጉዳይ ተላላኪ ሆነ። ተበከነከነ። ዘበኛውስ ከማን አንሶ - «ለወዴት ነው?» ጥያቄ አሰለቸ። አንዲያውም ቆራጥ አመራርን መስጠት ጀመረ። ዘፋኝ በላ። ከታፈ በየስርቻው በቱለ። ጋዜጠኛው ፍርድ ቤትን ሊተካ ታጣው። ስፖርተኛ ሽቃጭ ሆነ። ውጤት ሳይሆን በሻንጣ ተሸካሚነት ሪኮርድ ሰበረ። ለትራፊክ ትራፊክ አስፈለገ። ፖሊሱም ዩኒፎርሙን በጥቁር ቆዳ ጃኬት ቀየረ። ቀመጡን ይህ ይዘንጥብን ገባ። አይ አዲስአባ - የዘንጠዎች አገር!

በአንድ ወቅት (ዛፉም ጭምር) የጎድ መንግስቱ ትንፋሽቸው ተሰማ። ፎቶአቸውም አሰሰች። ቁጡው፣ ሳቂታው መንግስቱ የጋዜጦች ማጸጠቂያ ሆኑ። ከእነ አስቴርና ኩኩ ጋር አሳቸውም ፋክክር ያዙ። የዘፈን ዜራቸውን ልክው ዘፈኑብን። የዘፈን ቃናው ግን እንደተለመደው ዙበነን ያለ ነበር። «ኑሃዜዬና ጨዝቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

የቁራ ሆኖ ቀረ» ብለው አላዘኑብን። አንዳንዱም ሆዴ ባባ ስሜቱ ተነሳሳ - «ዘራፍ የመንግስቱ አሽከር!» አያለ ፎከረብን። ኋላ ላይ ጎሹ ወልደዎም ከራቸውን ቸበቸቡልኝ። ማን ያልቸቦቸበልን አለ? ሰው ሁሉ ነጋዴ - ሀገር ሁሉ ገበያ ሆነ።

ኮሌጌሎቹ ምን ነካቸው? ያልንም አዲስ አበቢዎች ብዙ ነበርን። ደሞስ የፕሮፌሽን ለውጦ አድርገው የዘረን ኮሌክሽን ቢያስከመከሙን ምን ያንሳቸዋል? ያልንም ሞልተናል። ለነገሩማ - ዕድሜ ለነዛ ገበያ!

«ሳጅን ጋዜጦች» ባላቸው ልዩ ብቃት አንዴ በጋምቤላ በሌላ ጊዜ በጉንደር «ጥቁር አንበሳን» ይዘው ብቅ አሉ። ከዋሽንግተንና ከሎንደን ወያኔን በረሞት ኮንትሮል ማጥፋት እንደሚቻል ተነበዩ። የትንበያና የከዙብ ቆጣሪ አገር አዲስ አበባ።

ጋዜጦቹ ለወፌ ተሸቀዳደሙ። አንደኛው «መንግስቱ ምያሌ በቀለ ሞላ ሆቴል ተገናኝተው ወጡ!» ሲለን ሌላኛው «አይደለም! በጋምቤላ በኩል ሰሌን ባርነጣ ደፍተው ሾለኩ» አያሉ አዋከቡን። ሽቀጠጠብን። ተስቆባቸው አሳቁን።

አይ አዲሳባ?! የቀልደኞች፣ «የጋብሮቦች» ሁሉተኛ ምድር። ሌላውማ ሹልሉ ተክልሎ ይቆፍራል። ይሰራል። የምሩን ይወያያል። አዲስ አበቤዎች ግን ዝንተዓለም አንቀልዳሰን። አንወራራፋሰን። አፈር መግፋት የለ፣ አፈር መምሰል የለ! አድሜ ሰዜኒት ቅባት!

ቪቫ - ዕድሜ ለአዲሱ ኢኮኖሚ። ኪክ ቤቶች ፈሱ። ቡቲኮች ደሩ። ኢንቨስተሮች በዙ። ስፖንሰሮች ኮሩብን፣ ተጀነኑብን። ዘራፍ - ጅንኖቹ! በሊዝ የሚከራየው ነገሱብን። ኪክና ሻይ ቤት። ፎቶግራፍና ስቴሽነሪዎች ሊያዘምኑን ሉዲሳባ ላይ ፎቅ ሰሩ። ኪክ ገምጠው ኪነ ሊያስገምጡን ተቻኮሉ። ሊፍትካ መኪናዎች ፓኖራሮዎችን አስናቁ። ጥሎ ማለፍ ነገስ። አይ አዲስአባ የስልጡኖች አገር ...


ግንቦት ወጥቶ ግንቦት ሲገባ ለዘሪያ ያልሞሉ የትውስታ ከሮቼን አጠናጥናለሁ። ያኔ በግንቦት ጠመንጃ ሽንብቆ ሆነ። መሳሪያ የያዘ ያልተፈራውን ያህል መሳሪያ መያዝ ተፈራ። ታንክን ወደ ትራክተር፣ መድፍን ወደ ማረሻ መለወጥ ቀላል ባይሆንም ተሞክሯል። ሰላምና መረጋጋት ሰፈነ። እርጋታ ተባለ። ያቀጨኔመ ግንባር ተፈታ። ከል ለባሽ እናቶች በአዳ ለበሱ - ከማጀት ወደ አደባባይ ወጡ። ሀይወት መንተክተኪን ቀጠሉች።

ግንቦት አለፈ፣ ግንቦት ተተካ፣ ግን ለግንቦት መንገዱ ጨርቅ አልሆነም። መፈናቀል፣ ረሀብ ተከሰተ። ግን አልዘለቀም። መፈናቀሉ - በሴፍቲኔት፣ ረሀቡ በኤክስትንሽንና በግሎባል 2002 ተተካ። አያልፍ የለ አለፈ ... «ወያኔ እንደ ሱልጣን ኢብራሂም ሀገር የሸጠ ነው» የሚለው ሀሜትም ከሰመነ። እውነት ፈረጠመ። ፍቅር ደራ። ስለፍቅር ተዘፈነ። ስለ ፍቅር ካሴት ፈላ፣ ሲዲው አቀነቀነ። ስለ ሰው ሁሉም አንጉራጉረ። ህዝብና ሰው ይቅደም የሚለው መፈክር ተቀባይነት አገኘ። ፍቅር። ስለ ፍቅር በጆሮአችን ተንቆረቆረ። በግንቦት ምን ያልተደመጠ አለ? አዲስ ዘፈን! ከስምንት ዓመት በኋላ ተደመጠ። ለዘመኑ ተዘፈነ።

«ዘመኑ ምናሰኝ – ዘመኑ ወርቅ ነው፣
ፍቅር ያለቀለት – ጉዴ ነው፣ ጉዴ ነው
አትሸበር ልቤ ለሆነው ላልሆነው
ሰሰሰው ሰሰሰው ቀድጀ ልልበሰው ...» አየልን ዘፈንን፣ አስዘፈንን። ነገም ግንቦት ሌላ ወር ነው። ሌላ ፍቅር፣ ሌላ ሰው፣ ሌላ አዲስ ዘመን። ግንቦት!

መጣጥፍ

t.me/OLDBOOKSPDF



ቡዳ

አብይ ደምሴ

በሐምሌ 1955 (ኤ.አ.አ.) አንዳት ወጣት ሚክሰኳዊት «ሁዴ» ስመሆኗ በጉብረተሰቡ ታምኖበት በአሳት ተለብልባ አንድትገደል ተደርጉ ነበር። ከአጂንጋ መንደር ፈንጠር ብሎ በሚገኘው ደሳሳ ቤት ውስጥ በብቸኛነት ትኖር የነበረችው ይቺ ጾሲፈን የተባለች ወጣት የቡዳ መንፈስ የተጠናወታት ስመሆኑ በመንደረተኛው ዘንድ ጥርጣሬ ማደር ጀመረው። አንድ አረኛ ከብቶቹ ጠፍተውበት በሚያፈላልግበት ሊሊት፣ ሰው በሩቁ ይፈራው ከነበረው አንድ ዋሻ ፈት ሰፈት ያየውን ትርኢት ቤና ከሰራጨው

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ነበር። በዚያን ውድቅት ጆሴፊን እርቃኗን ምንነታቸው በግልፅ ባልተለየ ፍጡራን ተከባ፣ እንግዳ በሆነ ቋንቋ ስትጮህና ስታጓራ አብራቸው ስትጨፍርና ስትበል አስተውሱ ነበር።

ታዲያ ይህን ጉድ የሰማው መንደረተኛ በልጂቱ ላይ ልዩ ክትትል ማድረግ ጀመረ። ቀን ከሌትም ያንን ገለልተኛ ቤቷን በአይነ ቁራኛ መጠበቁን ቀጠለ። በዚህም መሀል ነበር አንድ ባሰትላር የነበረ ጉልማሣ መሸትሸት ሲል ወደቤቷ ሲገባ የታየው። ጉልማሳውም አንደገባ ቀልጠ በመቅረቱ ያደፈጠው መንደረተኛ ከየስርቻው በመውጣት ወደዚያ ቤት አመራ። በሩም ከውስጥ ተከርችሞ በመዚጋቱ መንደረተኛው ሰብሮ በገባበት ወቅት ጆሴፊንና ያ ጉልማሣ እንደ አውሬ እርቃናቸውን ከምድር ላይ ተቆላልፈው ተኝተው ነበር። አድማ ወግ አጥባቂ የነበሩት መንደረተኞችም ጉልማሳው ሚስቱን በመተው ለምን ይህን አጸያፊ ተግባር እንደፈጸመ ሲጠይቁት፣ የሰጣቸው መልስ ልጅቱ እንዴ ልቡን የበላችው በመሆኗ አደርግ የምትለውን ሁሉ ያለማመንታት ከመተግበር በስተቀር የማመዛዘን ኃይሉ ጨርሰውኑ የተገፈፈ መሆኑን በመናዘዝ ነበር።

በዚያን ጊዜ እጅጉን የቅፍድ ተይዛ የነበረችው ጆሴፊን ዘላ ልታንቀው ከሞከረች በኋላ በመጨረሻ ከንፈሯን በንዴት እየነከሰች ባልተለመደ ጮርናና ድምፅ «ቆይ! ባሬውኑ አሳይሃለሁ!» ስትል ዛተችበት። የሚገርመው ያ ወጣት በዚያኑ ሴሲት «እንቀትኝ፣ ገደለችኝ» እያለ አሪ ብሎ በመጮህ ላይ እንዳለ ሕይወቱ ማለፉ ነው።

መንደረተኛው ሰሚዜው በጆሴፊን ላይ ክትትሉን ከማጥበቅ በስተቀር እርምጃ አልወሰደባትም ነበር። በዚሁ መሀል አንድ ኮርቴና የተባለ ሌላ ጉልማሳ መንገድ ላይ

ያገኛትና በንዴት እየተንተገተገ «አንቺ ቡዳ! አንቺ እርኩስ! ጓደኛዬን እንደ ገደልሽው አንቺም ትሞቻታለሽ» በማለት አንገቷን ለማነቅ ይጠጋታል። አርሷ ግን ከቆመችበት ንቅንቅ ሳትል ትኩር ብላ አይኖቹን በማየት በፍርሃት እንዲርድና ወደኋላው እንዲያፈገፍግ ታደርገዋለች።

የከበበው ተመልካች ኮርቴናን ቢያደፋፍረውም እርሱ ግን በላብ ተዘፍቆ የኋሊት በመዞር ሸሸት ቀጠለ። ያን ጊዜም ነበረ ጆሴፊን «የትም ሮጠህ አታመልጥም!» ስትል የዛተችበት። አሁንም ፉከራዋ ሰመረና ወጣቱ ጠዋት ላይ በተኛበት ሞቶ ተገኘ።

ከዚህ በኋላ ነበር በድንጋጤና በፍርሃት የተናጠው የመንደሯ ነዋሪ ስብሰባ በማካሔድ ልጂቱን «ቡዳ» ናት ሲል ቢይፋ ያወጀው። ከምሬቱና ከቁጣውም የተነሳ አስከሬኗ ለቀብር እንኳን እንዳይበቃ የአሳት አራት ሆና እንድትቀር ወሰኑ። ምንም እንኳን በመሀሉ የፖሊስ ኃይል ጣልቃ ለመግባት ቢሞክርም ሕዝቡ ግን አልበገር ብሎ ጆሴፊንን ከቤቷ ጎትቶ በማውጣት ከግንድ ጋር አስሮ አሳት ለቀቀባት። አርሷም ሕይወቷ እስኪያልፍ ድረስ የአሳት ወላፈኑን ሰንጥቆ በሚሰማው ድምጿ እርግማኗን እንዳወረደችው ነበረች። ታዲያ ያ እርግማኗ ለለያዘሳትም ነው ይባላል የዚያኞ መንደር ነዋሪዎች ቀስ በቀስ እንደቅጠል ረግፈው በማለቃቸው፤ በአሁኑ ጊዜ በዚያች መንደር ውስጥ ሰወሬ ነጋሪ እንኳን አንድ ሰው አይገኝበትም። (ምንጭ Info. the strange - by Warren Smith) ይህን የሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሰሜን አሜሪካዊ ልምድ ለመጣጥፋችን መግቢያ ያደረግነው የቡዳ እምነት አለም አቀፋዊና እስከአሁንም ሥር እንደሰደደ ያለ ስምልክ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ቡዳ የሚለው ቃል በአርኬምሉ. ቋፋሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

በተደረሰባቸው የሱሜሪያን፣ የባቢሎናውያን የአራውያን ቅርፃ ቅርፆች ላይ ከመገኙቱም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በታልሙድና በቁርአንም ላይ የተጠቀሰ ስለመሆኑ የየሙያው ጠበብት ያረጋግጣሉ። እንደዚሁም ቡዳ የሚለው ቃል በጥንት ግሪኮች ዘንድ «ቦዮ ካኢያ» በላቲኖች «ፋሲናትዮ» በሮማውያን «ጀታቶሬ» እየተባለ ይጠራ እንደነበረ የታሪክ መጻሕፍት ይዘግባሉ። በአሁኑ ዘመን ደግሞ ለምሳሌ በእንግሊዞች «ሊቭልአይ» በፈረንሳዮች «ማሴቮናንት» በአሜሪካውያንና በአውስትራሊያን «አቨር ሉኪንግ» እየተባለ እንደሚጠራ ነው። እስኪ ስለአገራችን የቡዳ አምልኮት መንስኤና እድገት በዝርዝር ከመጋገራችን በፊት በተቀረው የአለም ክፍል ያለውን ግንዛቤ ለመዳሰስ እንሞክር።

ከአውሮፓ ስንጀምር ታሪክ ስማቸውን በቡዳነት ከሚዘከራቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል የሮግ ቤተክርስቲያን ፖፖች የነበሩት ፓየስ ፱ኛና ሊዮ ፲፫ኛ፣ እውቁ የእንግሊዙ የስነ ጽሑፍ ሰው ሶርድ ባይረን፣ የፈረንሳዩ ንጉስ ናፖሊዮን ፫ኛና የአስፒን ንጉስ አልፎንሰ ፲፯ኛ ጥቂቶቹ ናቸው። እንደዚሁም የሳቲን ዝርያ በመባል በሚታወቁት ደቡብ አውሮፓውያንና የስላቭ ዝርያ በመባል በሚጠሩት በምስራቅ አውሮፓውያን ዘንድ እስከ አሁን ድርስ «ቡዳ» የሚለው ቃል በአጋጣሚ ከጆሮአቸው ቢገባ፣ አንድም ተሸቀዳድመው ምራቃቸውን አንትፍ በማለት እርኩሱን መንፈስ ያንቋሸሹና ያወግዙታል፤ አለበለዚያም «አግዚአብሔር ጠብቀን!» ሲሉ በማማተብ ከአጠገባቸው አንዲርቅ ያደርጉታል። በተለይም ወግ አጥባቂ በሆነው በስላቭ ጎብረተሰብ ውስጥ ቡዳ ስለመሆናቸው የታወቀባቸው ግለሰቦች ሌላውን ሰው በአይነ ውግ እንዳያጠቁ ፊታቸውን በጥቁር ጨርቅ ለመሸፈን ይገደዳሉ።(በኋላም በጥልቀት

እንደምናየው በአገራችንም ቢሆን የጋኔን፣ የምትሀት፣ የቡዳነት መንፈስ የተጠናወታቸው ግለሰቦች፣ ባለአውልያና ባለዛሮች፣ የግድ ከጎብረተሰቡ ጋር መቀላቀል በሚኖርባቸው ጊዜ ከመሰሪዳቸው ወይም ከቀዬአቸው የሚወጡት አንድም በሻሽና በጃኖ ተከናንበው፣ አለበለዚያም ባርኔጣ ደፍተውና አይናቸውን በመነፅር ከልለው ነው።)

ወደ አሰያው ከፍለ አህጉር ስንሻጋገር ደግሞ በተለይም ለቡዳ አምልኮት ምንጭ በሆነችው በሕንድ፣ በአጉራባቾቿ በፓኪስታን፣ በቻይናና፣ በጃፓን ጭምርም እምነቱ በአሁኑም ጊዜ በሰፊው ሰፍኖ እንደሚገኝ እናጠናለን። ሌላው ቀርቶ ለቡዳ አምልኮ ወደ ኢትዮጵያ መግባትና መስፋፋት ጭምር መንስኤዋ ይቺው ሕንድ እንደሆነችና ይህም በፈላሾች አማካይነት የተፈጸመ ስለመሆኑ አለቃ ኪዳነ ወልድ የታሪክ ምንጭ በመጥቀስ ዘግበዋል። (ቡዳና ፈላሻ የሚሉት ቃላት ተመሳሳይነት ከዚህ ስለመመንጨቱም በስፊው ይነገራል)።

አሰያዊ በሆነው በአሪቡም አለም ቡዳ ከመታመንም በእጅጉ የሚፈራ በመሆኑ ሕዝቡ ሕግናት ልጆቹን ብቻ ሳይሆን ውድ የሆኑትን ግመሎቹን፣ የበግና የፍየል ጠቦቶቹን ከጥቃት ለማዳን በአንገታቸው ላይ የተለያዩ ከታቦችንና አስማታዊ ቅርፃ ቅርፆችን ያንጠለጥልባቸዋል። ሌላው ቀርቶ የቡዳው መንፈስ ወደ መኖሪያም ሆነ ወደ ንግድ ቤት ሳይገባ በሩቁ ለመከላከል ሲባል በየበራፉና በየግርግዳው ላይ ክቱርአን የተቀዳ ጥቅስ አጽፎ ማንጠልጠሉ በስፈቡ ጎብረተሰብ ዘንድ የተለመደ ነው።

በመጠኑም ቢሆን ስለ «ቡዳ» አምልኮ አለም አቀፋዊነት በዚህ መልኩ ገረፍ ካደረግን የምእራቡ አለም የቡዳን ጥቃት ለመቋቋም የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች ደግሞ እንይ።

t.me/OLDBOOKSPDF

* በድንገት በጓዳ ሰው በመንገድ ላይ ቢያጋጥም ተሸቀዳድሞ ምራትን ወደ አርሱ አቅጣጫ ጣቅ ብሎ ማለፍ።
* ቡዳው በመንገድ ላይ በሚዘዋወርበት ወቅት አይናቹን በጥቁር ጨርቅ እንዲከልል ማስደረግ።
* በገበያ የተደረደሩ ምግቦች ሰቡዳ አይነ ውግ የተጋለጡ እንኳን ቢሆን ከመመገብ በፊት ጸሎት ማድረስና ማማተብ።
* በተለይ በአዲስ ጨረቃና በብልት ቅርፅ የተሰሩ ሐብሎችን ማንጠልጠል።
* የቀኝ እጅን አውራ ጣትና ትንሺን ጣት አጥፎ የተቀሩትን ሰበቱን ጣቶች በመቀሰር በአይበሉባው በኩል ለቡዳው ማሳየት (ማኖ ኩርንችት ይሉታል)። ወይም የተቀሩትን ጣቶች በማጠፍ አውራ ጣትን በሌባ ጣትና በመሀል ጣት መካከል አሽቀኩ በመያዝ ማሳየት (ይህን ደግሞ ማኖ ፈነኒ ይሉታል) በእስያውያን ዘንድ ደግሞ የተሰመሩት የመከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው።
* በተለይም ሙሽሮች፣ ንፍስ ጠሪ ሲቶችና፣ ጨቅላ ሕፃናት ለቡዳ አይን እንዳይጋለጡ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ።
* በቡዳ የተለከፈውን ሕፃን ፈት በምራቅ መለቅለቅ።
* ለማያዊ መቁጠሪያዎችን በአንገት ማንጠልጠል።
* በግመሎችና በሴቶችም የቤት እንስሳት አንገት ላይ የአንቁራሪት የቀንድ ወይም የጨረቃ ምስል የተቀረፀባቸውን ክታቦች ማንጠልጠል።
* አስማታዊ ጽሑፎችን በማጸፍ በክንድ ማሰር፣ በክታ መያዝ ወይም በአንገት ማጥለቅ።

በአብዛኛው የአለም ጎብረተሰብ ዘንድ ባሪያም ቢሆን የሚታመነው ለሰይጣን ደለላ በቀላሉ እንድተራታቸው

እንደ ፍጥረታት እናት ሔዋን ሁሉ፣ በዘመናችንም ሴቶች ቡዳን ለመሳሰሉ አርኩሳን መናፍስት ጥቃት በቀላሉ የሚጋለጡ እንደሆነ ነው። ለዚህም የሚቀርበው ምክንያት ሴቶች በተፈጥሯቸው ያዩትን ሁሉ የሚመኙና ቀናተኛ ከመሆናቸውም በላይ አራሳቸውን ለመቆጣጠር የሚሳናቸው፣ በዚህም ድክመታቸው የተነሳ በቀላሉ በቡዳ መንፈስ ለመጠቃት እንደሚችሉ ነው። የዚህ ሐሳብ አራማጆችም አቋማቸውን ለማጠናከር በማስረጃነት የሚያቀርቡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ነው።

ታዲያ በሴላው አለም እንደሚታመንበት ሁሉ ወደ አትዮጵያም ስንመለስ በአመዛኙ «ለአርኩስ መንፈስ» ተጋልጠው የምናገኛቸው ሴቶችን ነው። በየከተማውና በየመንደሩ ድብዳብ ጉዘጉዘው፣ ሲጋኝ አንጠፈው፣ ቂጠማ አራቂውን ዙሪያ ገባውን ነስንሰው፣ ስኒ ደርድረው፣ ጀበና ጠምደው፣ እጣን ከርቤውን እያቡላቀቁ የጪንቃውን ችግረኛ ሁሉ እንደአመጣጡ የሚያስተናግዱት አንርሰው ናቸው። እንኳህም መሳለሱቹም «ምርጥ» አገልጋዮች ስኒደፊ፣ እጣን ወጊ - ጨሴላይ - ንቅሳት ወቃሪና... መዘቱ በሚባሉ የተለዩ የመግ የማስረግ ጠጠሪያዎች ይታወቃሉ።

ጽሩ ግን የቡዳው መንፈስ በተለይ ለሃፋት፣ ለትዝፈት ሲነሳሳ የሚመረጠውና የሚያጨው ከ15-30 እድሚ ያላቸውን ወጣት፣ ደመ ግዙ ሴቶች ይሆናል። እነዚህን መሰሉቹም ሴቶች በቡዳ ለመበላታቸው (ለመለከፋቸው) በገል የሚንበላረቱ የባህርይ ሰውለት እንደሚታዩባቸው በዚህ ዘርፍ ልዩ ጥናት ያካሔዱ የማህበራዊ ሕይወት ጠበብቶች ያረጋግጣሉ። ለምሳሌ ሳይመን ዲ ሚሰንግ የተባሉት አሜሪካዊ The high plateau of Amhara Ethiopia በሚል ርእስ ለዶክትሬት ዲግሪያቸው ማሟያ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ በቡዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሰከና በጠቋሚነት ሲያገለግሉ ይችላሉ ያሏቸውን የባህርይ ሰውቦች እንደሚከተለው አሰናድረዋል፡-

- የጥርስ ማንቀራፈፋ ወይም ማንሳጣጥ
- እንቅልፍ ማጣት፣ መነጋንና ማታገጥ
- መክሳትና መመንመን
- በራስ ምታት መሰቃየት
- ሳያታሰብ ከጣሪያ በሳይ አያስካከ መሳቅ
- እንደ ሕጎን ልጅ በእጅና በእግር መዳህ
- አያታን አለመንቀልና ፍዝዝ ብሎ መቅረት
- በንሰር መጠቃት
- ደከምከምና ያቅለቅለ ማለት
- ደጋግሞ ማዛጋትና ማታሰት
- በጋይለኛ ሳል መጠመድና ደም መትፋት
- በሆድ ቁርጠት መሰቃየት
- በእከክና በፎከት መወረር
- እንደ ጅብ መርሀ
- አዘናጉቱ ሰውን መንከስና መሳጠጥ
- ልብረር ልብረር ማለት
- አውራ ጣትን በመዳፍ ውስጥ ጨብጦ መያዝ

ባለሙያው ይህን ትንተና ያጠናቀሩት በእመቤት ኢትዮጵያውን የሆኑትን የክርስትና የአክልምና የሃይማኖት መሪዎች ተሟዘረው በማንጋገር ካገኙት መረጃ ሲሆን፣ በበኩላቸውም ካደረግነው መጠነኛ ጥናት የተገበረዘሩት ምልከቶች ቦንብረተሰቡ እንደሚታመንቸው ለማረጋገጥ ችሰናል።

በተጨማሪም የቡዳን መንፈስ ከተለከፈው ሰው ሳይ ማሳቱቱ እጅግ ፈታኝ ከለመሆኑም ለመረዳት በቅተናል። በዚህ ሙያ የሰለጠነው ደብተራ በቅድሚያ የሚወሰደው እርምጃ በቡዳ የተበላው ሰው በመወራጨት በእራሱም ሆነ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እግር

ከወርች ማሰሰር ነው። ከዚያም በብሉኩ በመጀቦን በገል ላይ የሚገተሰተሰውን የተሰያዩ እዖች ጠለ እንዳታጠን ያደርጋል። በዚያን ጊዜም የቡዳው መንፈስ ከሥጉትት የቱነላ መሰናሰና ይጀምራል። አድናቦ ገም ካለ ግን በጅራና መገራትም ጭምር እንደሚደርስበት ነው። በዚያን ጊዜም ሰቃዩ በእጅጉ ስለሚያይልበት «ለስማርያም ተውኝ! » ሲል መማፀን ይጀምራል። ደብተራውም በዚያኑ አጋጣሚ ቡዳውን ማንነቱን እንዲገልፅ ግለሰቡንም የትና መቼ አግኝት እንደተጠናወተውና ሰምንስ ምርጫው በእርሱ ላይ እንዳረፌ ካናገዘው በኃላ ሰቆ እንዲሄድ ያዘዋል። ቡዳው በዚህን ወቅት የሚናረው አማራጭ ምሱን እንዲያተርሁለት መጠየት ብቻ ይሆናል። ምሱም እንደተሰጠው ወደ ሰውየው ዳግመኛ ላለመመለስ ደብተራው የሚንገረውን መሐላና ግዝት ያፈጽማል።

በሴላው የአለም ክፍል እንደሚታመንበት ሁሉ በኢትዮጵያውያንም ዘንድ ለቡዳ መከላከያነት የሚወሰዱ የየንታቱ አርምጃዎች አሉ። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ከቤቱ ከመውጣቱ በፊት ነጭሽንኩርትና ጤና አዳምን የመሳሰሉ አሰዋት በያንኳ ቀኑን ሙሉ በቡዳ ሰበላው እንደማያችል ይታመንበታል። እንደዚሁም ከቤት ያሽበረቱ ልብስ ሰብሰ፣ አማሞርና አጋጊቦ መውጣት በቀላሉ ሰበዳ ምርኩኖንት ለለማሃናርግ በዚህም በኩል ጥንቱ ማናረግ እንደሚያሸ ይነገራል። ሌላው መከላከያ አስማታዊ ከታሆችን በአንገ ወይም በአንገት ማሰር ሲሆን ማንኑን በማያውቁትም ሰው ፊት ምግብ ከመመገብ መቆጠቡ ሌላው ዘዴ ነው። እንግዲህ ለስ ቡዳ የቱን ያህል የተባረና የተንገረ ቢሆንም ቅሉ በአሁኑ ዘመን ግን ከአፈታሪክነት አልፎ እንደ እውነተኛ ክስተት መቆጠር የለበትም የሚለው ወገን ቁጥር እየጨመረ ነው። ያሁን አንዷ በሃይማኖት ሰዎች ዘንድ ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

እምነቱ ከሱሮም ይብስ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ነው ለማለት ያስደፍራል።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ ወንጌል አርነት አጣያቱ ከርስትያናት መጋቢ የሆኑት ፓስተር የማነ ብርሀነ እንዳለ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ይሰጡበት ዘገጽ ጋብዘናቸው ነበር። አርሳቸውም ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች የሰጡን ምላሽ ባጭሩ የሚከተለው ነበር፣

«ቡዳ የሚባለው ነገር አፈታሪክ ሳይሆን በርግጥም ያለነገር ነው። አንዳንድ ግለሰቦች የቡዳ ጥቃት ያደረሰባቸውን ሰው ጠይቅ፣ ፈላሻ፣ ወዘተ አያሉ መላደባቸው ግን ስህተት ነው። ስለምን ሰው ጨርሶ ቡዳ ሆኖ ሊወለድ አይችልም። ይሁን እንጂ የቡዳ መንፈስ እንደተቀሩት የሰይጣን ጭፍራዎች ሁሉ የሰውን ልጅ ለማጥቃት ስለማይተኛ ደካማ ሆነው ባገኛቸው ግለሰቦች ላይ ያድራል። በዚህም ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር እንዲጋጩ እንዲጣሉ ይገፋፋቸዋል። በዚህን መሰሉ አጋጣሚ ታዲያ ኢትዮጵያውያን ቡዳ ብሰው የሚሳደቡት መንፈሱን ሳይሆን እንደ እነርሱው ሰብአዊ ፍጡር የሆነውን ሰው መሆኑ ተገቢ አይደለም» ይሳሉ ፓስተሩ።

«ታዲያ የነሰ አእምሮ ጠበብቶች (ሳይኪያትሪስትስ) ሂስቴሪያ ካታሌኝሲ፣ ሳይኮሲስ፣ ኒሮሲስ አያሉ የሚጠሩት የአእምሮ ቀውስ ከምን የመነጨ ናቸውን» የሚል ጥያቄም ለፓስተሩ አቅርበንላቸው ነበር። የፓስተሩ ምላሽ፣

«ሰይጣን በእጅጉ መሰሪ ተንኮለኛ እንደመሆኑ ማንነቱ እንዳይጋለጥ እጅግ በተራቀቁና በተለያዩ የማታለያ ዘዴዎች ያጠቃል። ከእነዚህም ዘዴዎቹ አንዱ በህክምናው የጥበብ ዘርፍ አስልቶ በመግባት ከመንፈላዊ ይልቅ በቁሳዊው አለም ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ ነው። ስለዚህ ለአንድ አእምሮ ቀውስ የተለያየ ስያሜ

ይሰጡት እንጂ፣ ሁሮ ሁሮ የበሽታው መንስኤ ያው ርኩስ መንፈስ ነው» የሚል ነበር።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሕክምና ባለሙያዎችንም አስተያየት መጠበቃቱ ወላኝ ነውና ወደ አማኑኤል ሆስፒታል በመሔድ ሳይኮሎጂስት ካለች ደምሴን አነጋግረን ነበር። ለውይይታችንም መግቢያ ያደረግነው ስለቡዳ መንፈስ የሚያውቁትን እንዲያብራሩልን በመጠየቅ ነበር። አርሳቸው ግን በቅድሚያ ቡዳ የሚባል ነገር አለመኖሩን በማስረገጥ ከገለጹልን በኋላ ሆኖም ኢትዮጵያውያን ከአገራቱ አምልኮና ልማድ ባለመላቀቅ በአሁኑም ዘመን ጭምር እንደሚያምኑበት አውስተውናል። ስለዚህም ኋላ ቀር አስተሳሰብ ተቀጣጫው ምክንያት የሕዝቡ ከመሃይምነት አለመላቀቅ መሆኑን ጠቅሰው ከዘመናዊ የሕክምና ዘዴዎች ጋር አለመተዋወቃንም እንደ ሁለተኛ ምክንያት በማድረግ አቅርበውታል።


ይሁን እንጂ ቡዳ የለም የሚሰውን ድምጻሚአቸውን አሜን ብለን ከመቀበላችን በፊት የቡዳ መኖር በተሰያዩ ከፍሰ አለማት የሚታመንበት መሆኑን በማስታወስ ማብራሪያ እንዲሰጡበት ታብዘናቸው ነበር።

አርሳቸውም ሰፋ በማድረግ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተውናል። «አርግጥ የአይን ብሌናቸው ጨረር የሚወረውር ወይም ከፍተኛ የአይታ ኃይል ያላቸው አንዳንድ ሰዎች በአለማችን ውስጥ አልፎ አልፎ ሚጋጠማቸው የማይካድ ነው። ለምሳሌ በቅርቡ በራሺያ ውስጥ አንዲት ሴት የዚህ አይነቱ ቁሬጥሮ አንጻላት ተደርሶበት ከሕክምና ጠበብት ዘገጽ እንድትቀርብ ተደርጎ ነበር። በእርሷም ላይ ልዩ ሲዩ ባለሙያዎች ባካሂዱት ምርመራ ከአይኖቿ ጨረር አከበራይ አይነት ጨረሮች እንደሚወረውሩ ሊ[illegible] ችለዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

በተጨማሪም ጨረሩ በስዎች ላይ በሚያርፍበት ወቅት በደማቸውና በነርቭ ሕዋሳቶቻቸው ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ለማወቅ ችለዋል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ ተመራማሪዎቹ የጨረሩን አወራወር ኃይል ለመገምገም በሌትዮዋ አይኖች ትይዩ ጥይቶች እንዲተኩሱት ቢያስደርጉም ጥይቶቹ ግን አቅጣጫቸውን በመቀየር ልልፊዎት ከመብረር በስተቀር ሊጉዷት አለመቻላቸው ነው። ጥይቶቹን ከሊላማቸው ያስፈነጣጥቸው ደግሞ ከአይኖቿ የሚረጨው ጨረር ስለሆኑ በሳይንቲስቶቹ ተረጋግጧል።»

እኛም ከዚህ ቀጠል በማድረግ ስለ ጨረሩ ምንጭ የታወቀ ነገር ስለመኖር አለመኖሩ እንዲያሳውቁን ጠይቀናቸው ነበር። ሆኖም የስጡን መልስ የምርምር ውጤቱ ከምን እንደደረሰ ያልታወቀ መሆኑን ነው። እንግዲህ ይህ ጨረር በደም ሿንቧ ገብቶ ልብን እስከነ፣ ነርቮን በማዝር ሀሊናን አስካሳተና ብሶም ደግሞ ምንጩን ለመለወር አስከተቻለው አበሾች ቡዳ በማለት ከሚጠሩት መንፈስ በምን ይለያል?



ደስተኛው

አንቶን ቼኮቭ
(ትርጉም) አፈወርቅ ዘለቀ

ከፒተርስበርግ ወደ ሞስኮ በሚወስደው የባቡር መስመር የመንገደኞ ባቡር የቦሎ•ይን ጣቢያ ሰቶ እየወጣ ነው። በሁለተኛ ማዕረግ አንድ ክፍል ውስጥ የነበሩ አምስት ተሳፋሪዎች በመቀመጫቸው ላይ ወደ ኋላ ተንጋለው እንደማሸለብ ከጅሏቸዋል።

በዚህ መሀል የክፍሉ በር ተከፈቶ አንድ ቀውላላ ዘንግ የመሰለ ሰውዬ ዘው አለ። ያደረገው ሰፌ ባርኔጣና የዕ ነበው ዘርፋፋ ኮት ሰውዬውን የኩ•ሚክ ፊልም ተዋናይ አስመስሎታል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውየው ከፍሉ መሀል ተገትሮ ቁና፣ ቁና እየተነፈሰ ለረጂም ጊዜ ክፍሉን ሲቃኝ ቆይቶ «አይ... ይሄም ትክክለኛው ፋርጉ አይደለም» ሲል ለራሱ አጉተመተመ። በመቀጠልም «ምን እርግማን ነው፣... የሚያበሳጭ... በፍፁም ይሄ አይደለም።»

ክፍሉ ውስጥ ከነበሩት አምስት ተሳፋሪዎች አንዱ መሣላቸው የተገተረውን እንግዳ በትኩረት ሲያስተውል ቆይቶ ደስታ በተሞላ ስሜት «ኢቫን አሌክሴቪች! አይደለህም እንዴ? ምን አግር ጣለህ»

ቀውላላው እንግዳ እንደተገተረ በጠያቂው ተሳፋሪ ላይ ሲያፈጥ ቆይቶ ድንገት ትዝ እንዳለው ሁሉ «አህ! ፒዬትር፣ ፒትሮቪች በስንት ጊዜያችን ተገናኘን ባክህ?

«ከተለያየን እኮ አመታት ተቆጠሩ፣ በፍፁም አገኘህለሁ ብዬ አላስብኩም ነበር። ለመሆኑ እንደምነህ?» ፒዬትር ጠየቀ።

«በጣም ደህና ነኝ። የባቡር ላይ ከፍሌን ከማጣቱ በቀር፣ አሁንስ የማገኘው አልመሰለኝም። ከዚህ ሁሉ ችግር በፊት» ቦግስት ገለሣውን ቀጠለ፣ ዘንግ የመሰለው ቀውላላው ኢቫን «ልክ ሁለተኛው ደወል እንደተደወለ ወሰዱን ስጠጣው በነበረው ብራንዲ ላይ አንድ መለኪያ ላክልበት ከባቡር ጣቢያው ወጣሁ። አንድ መለኪያ አስቀዳሁ። እስከ ሚቀጥለው ጣቢያ ያለው ርቀት ረጂም ነው ታዲያ ለምን አንድ አልደግምም ብዬ ራሴን አሳመንኩ። ተዚያ ወዲያ ሳስብ ስጠጣ፣ በሀሳብ ተመስጬ ብራንዲዬን ስቀመቅም ሶስተኛው ደወል በመደወሉ ቦጥድፊያ ሮጬ መጀመሪያ ያገኘሁት ፉርጎ ላይ ጉብ አልኩ- ምን አይነቱ ነፈዝ ነኝ ጃል!?»

«ደስ ያለህ ትመስላለህ። ለምን ትንሽ አረፍ ብለህ አንጫወትም?» አለው ፒዬትር የድሮ ወዳጁን።

ኢቫን ግን «ኖለም አልቀይም። ክፍሌን መፈለግ አለብኝ» አለው።

«ተው ይቅርብህ፣ በጣም ጨልሟል፣ ትወድቃለህ። ምሺቀጥለው ጣቢያ ባቡሩ ሲቆም ያደርስህል። አስከዚያው አረፍ በል» ፒዬትር ወተወተው።

ቀውላላው ኢቫን ላይመስለው ከፒዬትር ትይዩ ተቀመጠ። «ወዴት ነው የምትጓዘው?» ፒዬትር ኢቫንን ጠየቀው።

«ወደ ጠፈር!... ባክህ የምሄድበትን እኔም አላውቀው። አድል ወደመራችኝ ነው የምጓዘው»... ኢቫን በሞቅታ እያስካካ መለሰ። ኢቫን መዘላበዱን በመቀጠል «ለመሆኑ ደስተኛ ሞኝ አይተህ ታውቃለህ?... ካላወቅህ እንግዲያስ ተመልከት፣ ከፊት ለፊትህ የተጉለተው ከሚች ፍጡራን ሁሉ የበለጠ ደስተኛው ሰው ነው።... ምነው ደስተኛነቴ ከፊቴ አይነበብም?» ፒዬትር በጥያቄ ያፈጠጠበትን ኢቫንን አያስተዋለ መለሰለት «... ከፊትህለ በግልጽ መረዳት የሚቻለው...» ጣለት የፈለገውን ለማለት የፈራ ይመስል አቅማማ። በዚህ ጊዜ ኢቫን ነጠቅ አረገና፣

«አሰጠሊታ ይሆን እንዴ ፊቴ? መስታወት ባገኘሁና ማስጠሉኑቴን ባየሁት? ታታለህ፣ ነፈዝ አየሆንኩ ነው። በእውነት»

አሁንም አስካካ፣

«ብታምንም ባታምንም በጫጉላ ሽርሽር ላይ ነኝ።»

«የጫጉላ ሽር ሽር? አገባህ እንዴ?» ፒዬትር በመደነቅ ጠየቀው።

«አምን ዛሬ... ከሰርጋችን ላይ ተነስተን ነው ቀጥታ ወደ ባቡር ጣቢያ የመጣነው።»

ከዚያ በኋላ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክቶች ከተሳፋሪዎቹ ለኢቫን ጉረፉለት።

ፒዬትር ሙሽራው ኢቫንን ከላይ እስከታች ተመልክቶ ሲያበቃ፣

«ለዚህ ነዋ በአለባበስህ ሽክ ያልከው?» አለው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሽራው ፊቱን መለሰ አድርገ። «ከሚገባው በላይ ተደስቻለሁ። አስቲ ይታይህ ከደቂቃች በኋላ ወደ ፋርጉ እሄዳለሁ። እዚያ ከወደመስከሙ ጥግ ባለው መቀመጫ በአካልና በመንፈስ ራሳን ለእኔ አሳልፋ የሰጠች ጣፋጭ ፍጡር፣ ወርቃማ ጠጉር ያላት፣ ሰልካካ አፍንጫና አለንጋ ጣት የታደለች ውዴ ፍቅሬ የኔ እንቡጥ ጽጌረዳ... አቤት አግሯ! እምላክ... ደሞ አንደኛ ክቤላ አግር እንዳይመስልህ። ብሉኝ ብሉኝ የሚል እግር ... አህ! ዳሩ አንተ አይገባህ! አመለካከትህ ሁሉ ቁስ አካዊ! ቆሞቀር! ላጢዎች ስትባሉ ይሽው ናችሁ። ምናለ በሉኝ፣ ስታገቡ ያ ኢቫን የትደርሰ ይሆን? ማለታችሁ አይቀርም።

«... እሺ ጓዶች ወደ ፋርጉ መሂዱ ነው። በናፍቆትና በጉጉት ከምትጠብቀኝ ሙሽሪት ደማት አቀባበል ይጠብቀኛል። ከዚያ ትክሻዋ ላይ ራሴን ጣል አድርጌ ወግሷን አቅፍ ላረግ በምናብ ይታይህ። ያኔ አለምግ በቁጥጥሬ ስር ያዋልኩ ይመስለኛል። ባክህ አንድጠመጠ ምክህ ፍቀድልኝ ፒዬትር!»

ሁለቱ ጓደኛሞች ተሳፋሪዎቹ እየሳቁባቸው ተቃቀፉ። በደስታ የተሞላው ሙሽራው ኢቫን መራመጉን ቀጠለ...

«ለመሸሽልም ይሁን ግራ ለመጋባት ከወደ መጡበ አንድ ወይ ሁለት መለኪያ ስትከለብስ በአእምሮህ ውስጥ በተረት ተረት መፀፍት ላይ እንኳን ያላነበብካቸው አይነት ሁኔታዎች ይከሰታሉ። እዚህ ግባ የማልባል ዋጋ ቢስ ሰው ብሆንም አለምን በቁጥጥሬ ስር ያዋልኩ ያህል ይሰማኛል»

ምቅ ባለው ደስተኛ ሙሽራ የተነሳሳ መንፈስና ጨዋታ የሁሉም የክፍሉ ተሳፋሪዎች ስሜት ተስባል፣ ሲስቅ አያሳቁ ቁጭ ብድግ አያለ እጅን አያወናጨፌ ወጉን ሲጠርቅ ያዳምጡታል። ቀጠለ፣

«ዋናው ነገር ከሁሉን ሆይ፣ ብዙ አለማሰብ ነው። ይህን ትንታኔ ሰይጣን ድራሹን ያጥፋው... ሞቅ አንዲለህ ከፈለክ አንዷን መለኪያ ቀንድብ፣ ታዲያ መጠጥ ይጮዳል ይጠቅማል የሚለውን ፍልስፍና እንዳትጀምር... ፍልስፍናና ላይኮሎጂ ብሎ ነገር ዲያቢሎስ ድራሻቸውን ባጠፋው።»

የባቡሩ አስተናጋጅ በክፍሉ መህል ሲያቋርጥ ደስተኛው ሙሽራ ጠርቶት፣ «ወደ ክፍል ቁጥር 209 ስትደርስ በነጭ ወፍ ምስል ያጌጠ ግራጫ ባርኔጣ የደፋች ወይዘሮ ፈልግና አዚህ መሆኔን ንገራት» አለው።

አስተናጋጁ በትህትና «ታዛሽ ነኝ ጌታው። ግን አከ 209 ቁጥር አዚህ ባቡር ላይ የለም። ያሰው 219 ነው።... 219 አልከኝ?»

«ይሁን። ለውጥ የለውም። ብቻ እኔ ባሷ በደህና ሁኔታ ላይ መሆኔን ንገራት።»

በሞቅታና በደስታ የሚዘላብደውን ሙሽራ ካዳመጠ በኋላ ከተሳፋሪዎቹ አንዱ፣

«በዚህ ዘመን ደስተኛ ሰው ማግኘት ያልተለመደ ነገር ነው። አይጥ ተሽልማ ስትሂድ ያየህ አከ ነው የምትመስለው» አለው።

«አርግጥ ብለሃል ግን ደስተኛ ለመጥፋቱ ተጠያቂው ማነው?» አለ ኢቫን አግሮቹን እየዘረጋጋ። ማብራሪያውን በመቀጠል «ደስተኛ ካልሆንክ ጥፋቱ የራስህ ነው።... ከዙራን አናንተስ ምን ታስባላችሁ? ሰው የራሱ ደስታ ፈጣን ነው? አናንተም ደስተኛ መሆን ከፈለጋችሁ ደስተኛ መሆን ትችሉ ነበር። ግን መሆን አትፈልጉም። በአንዘህላልነት ፊታችሁን ከደስታ አዙራችኋል»

«አንዴት ባክህ?»

ታጻሚዎቹ በመገረምና ባለመስማማት ጠየቁት። «ዘዋይ» ቀላል ነው፤ በተፈጥሮ ድንጋጊ መስረት ኢያንዳንዱ ሰው በሆነ የአድሚ ደረጃ ላይ ሲደርስ በፍትር ይወድቃል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሁኔታ ሲከሰት በፀጋ ተቀብላችሁ ማፍቀር ሲገባችሁ ተፈጥሮን ባለመታዘዝ ሌላ ትጠብቃላችሁ። ሌላ ምን ቀረ? አም ሀጉ እንደሚገልፀው ማንኛውም ጤናዊ ዚጋ ማግባት እንዳለበት ያስረዳል። ያለጋብቻ ደግሞ ደስታ አይታሰብም። እናንተ ግን ጊዜያችሁን በዋፃ ፈፃፃ ማግባትና ትታችሁ ማግባት ሲገባችሁ አሳገባችሁም። አሁንም ሌላ ነገር ትጠብቃላችሁ።

«...በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ (ወይን ያስትፈስህ ልበ ሰፃ ተብሎ ተጽፏል። አናም ነሽጥ ሲያደርግህ አለያም በሞቅታ መምነሽነሽ ሲያምርህ ወደ አንዱ መሸታ ቤት ንሬ ብለህ መቀነዳደብ ነው። ዋናው ቁም ነገር ይግጥ ከፍልስፍና መራቅ ነው»

«በጥርስ ህመም ጥገጥነት ወይም በጨቅጫቃ አማት ንዘንዝ ደስታው ጠፍቶ ህዘን የሚያጠላበት የሰው ልጅ ሁኔታ አዛባልህን ጥያቄ ላይ ይጥለዋል። አንደኔ እምነት ሁሉም ነገር የሚወሰነው በአድል ነው። በአሁኑ ሰዓት የኩኩቭካው የባቡር አደጋ በኛ ባቡር ላይ ቢደርስ ህሳብህን ትቀይር ነበር» አለው ፒዬትር።

«ዋጋ ቢስ ሀሳብ» ሲል ሙሽራው የፒዬትርን ህሳብ አጣጣለ። በመቀጠልም «የባቡር አደጋ ከሰንት አንዴ ቢደርስ ነው። ከሰንት አንዴ የሚደርሱ አደጋዎች ደግሞ አያስፈሩኝም። ለመድረሳቸውም በቂ ምክንያት የለም። አንዲያውም በአሁኑ ሰዓት ስለ አደጋ ማውራት አልፈልግም። አታንሳብኝ።»

ጨዋታውን በመቀየር ፒዬትር፣

«አሚቀጥለው ከተማ ሳንደርስ የቀረን አይመስለንም። ስመሆኑ ወዴት ነው የምትጓዘው?» ሲል ደስተኛውን ሙሽራ ጠየቀው። «ወደሞስኮ ወይስ ወደደቡብ ትቀጥላለህ?» ሲል ጥያቄውን አራዘመ።

«ስመሆኑ ግን ወደ ሰሜን አያቀናሁ አደየኸኛ አንዴት

ወደ ደቡብ ትሄዳለህ ብለህ ትጠይቀኛለህ?»

«ሞስኮ ግን ወደ ሰሜን አንዳልሆነ አርግጠኛ ነኝ።»

«እሰ-ን አሳጣሁ-ትም፤ አየሄድን ያለነው ግን ወደፒተርስበርግ ነው» ሲል ሙሽራው ኢቫን ፊርጠም ብሎ መለሰ።

«ይቅርታህን አየተጓዝን ያልነው ወደ ሞስኮ ነው» አለው ፒዬትር።

«አንዴ!? አንዴት ወደሞስኮ ልንጓዝ አንችላለን?» ሙሽራው በመደናገር ጠየቀ።

«የሚገርም ነው። አሰኪ ቲኬትህን አምጣ ልየው? ፒተርስበርግ ይሽሞ ተሳስተሀል። የተሳፈርከው በተቃራኒ አቅጣጫ በሚጓዝ ባቡር ላይ ነው»

ለሰኮንዶች ፀጥታ ሰፈነ። ሙሽራው ተስፋ በመቁረጥ ተደመመ። «አው! አው! ሲል ፒዬትር ገለጣውን ቀጠለ። ባለፈው ጣቢያ ላይ ፊጥ ያልከው አተሳሳተ ባቡር ላይ ነው። አረቄህን ከገለበጥክ በኋላ አንዳች ነገር ካስብከው አቅጣጫ በተቃራኒው በሚሄድ ባቡር ላይ አንድትሳፈር አድርገሀል»

ሙሽራው ኢቫን ተስፋ በመቁረጥ ጭንቅላቱን ይዞ ተንከላወሰ።

«ምን አይነቱ ደደብ ነኝ ባካችሁ? የማልረባ ፍጡር! ድራሼ በጠፋ! አሁን ምን አባቴ ላድርግ? ሙሽሪት ብቻዋን በሌላ ባቡር... ካሁን አሁን መጣ እያሰኝ በስጋት ትጠብቀኛለች። ምን አይነቱ ነፈዝ ነኝ ሽል!? ሞቼ ባረፍኩት።»

የቅድሙ ደስተኛ ሙሽራ አሁን የአግር ጣቱን መጅ እንደረገጡበት ሁሉ የስቃይ ድምጽ አሰምቶ መቀመጫው ላይ ዘፍ አለ። «ምን ዓይነቱ ደስታ የራቀው ፍጡር ነኝ ባካችሁ! አሁን ምን አባቴ ላድርግ?»

«ሂይ ምንም አይደል»

t.me/OLDBOOKSPDF

መንገደኞቹ ሊያረጋጉት ሞከሩ።

«ለሚስትህ በቴሌግራፍ መልዕክት ላክባትና ከሚቀጥለው ጣቢያ ልዩ ፈጣን ባቡር ተሳፍረህ የመልስ ጉዞህን ወደ ሚስትህ መቀጠል ነው።»

«ልዩ ፈጣን ባቡር?» በማንቋረር ጠየቀ የራሱ ደስታ ፈጣሪ ሙሽራ። «ለፈጣኑ ባቡር ክፍያ ከየት አባቴ አመጣለሁ? ገንዘቤ በሙሉ ያለው ሙሽሪት ዘንድ ነው።»

ጥቂት ከተንሾካሾኩ በኋላ ከበውት ሲስቁ የነበሩት መንገደኞ «ለደስተኛው» የቲኬት መግዣውን አዋጡለት።










ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ

ዘመልከት ይበቃል

ሌላ አያሳልፉም ምሺግ ተራሮቿ
የታወቁ ናቸው አይፈሩም ጀግኖቿ።
ደብዱ አሳይተዋል ዓለም እስኪረዳ
ጀግኖቹ ልጆቿ በማይጨው ጦር ሜዳ።
«ቦንብ ቢፈነዳ መርዝ ቢበተንም
«ልጆቿ ተርብ ነን ጠላት አይደፍረንም።
እያሉ ፎክረው ጀግኖቿ እንዳንበሳ
ጠላትን አድርገው ራሳ በራሳ
ከዓለም ዳር እስከ ዳር ተስምቶ ዝናቸው
በወርቅ ተጽፏል ጋያል ታሪካቸው።
አገሬ እንደዚህ ናት እንከን የለባትም
በዓለም ላይ ምንጊዜም ጠላት አይደፍራትም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያባቶቼን መንፈስ ይገር ተወልጀ
እጠብቃታለሁ በፍቅሯ ነድጀ።
ተወልጀ አድጌ ማዕረግ አይቼባት
እኔ ሳልሞት ማነው በክፉ እሚያስባት።
ሀገሬ አካሌ ናት ስጋየና ደሜ
ምን ጊዜም የሷ ነኝ ሞቼም ሆነ ቁሜ።
ብቸገር ብሰቃይ ብጐዳም ብሞትም
እጠብቃታለሁ ጠላት አይደፍራትም።
ሀገሬ ትልቅ ናት ይህን ዓለም ያውቃል
ታሪክን በሰፊው መመልከት ይበቃል።



ሠሊባዊ ድክመት ምንድነው?

አለሙ በቀለ

ዶክተር ይሄይስ ወልደፃዲቅ ይባላሉ። ደርማቶ ቬኔሮሎጂስት፣ ማለትም የቆዳና የአባለዘር በሽታ ስፔሻሊስት የሆኑት በ1861 በተመሰረተውና በርሊን በሚገኘው አንጋፋው የሰሊክሳንደር ሁምቦልት ዩኒቨርሲቲ ነው። ወሲባዊ ድክመትን (ሲምፖተንስ) በተመለከተ እንዲህ ሲሉ ሙያዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ። በጥያቄና መልስ መልኩ አቅርበነዋል፦

«ዶክተር ይሄይስ እርስዎ የቆዳና የአባለዘር በሽታ ስፔሺያሊስት ነኝ ነው የሚሉኝ። የቆዳ፣ የአባለዘርና

t.me/OLDBOOKSPDF

የወሲባዊ ድክመት (ኢምፖተንስ) በሽታዎች ቁርኝት ታዲያ ምንድነው?»

«አንድሮሎጂ፣ ማያሕሎጂ፣ ቨኔሮሎጂ ወዘተ የተሰኙት የህክምና ዘርፎች ደርማቶሎጂ ከሚባለው አቢይ የቆዳ የአባለዘር በሽታ ህክምና ትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ በስፔሻላይዜሽን ደረጃ የሚሰጡ የህክምና ትምህርት ዘርፎች ናቸው። ስለዚህ አንድሮሎጂ ማለት የወንድን ወሲባዊ ባህሪያት ጉድለቶች ለማታናትና «የኢምፖተንስ» ወይም ወሲባዊ ድክመትን የሚያስከትሉ በሽታዎችን እነዚህ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ መፍትሄን ለማስገኘት የምንጠቀምበት የህክምና ጥበብ ነው።

«ወሲባዊ ድክመት ከምን ይመጣል? በስንት ደረጃ ይከፈላል?»

«ወሲባዊ ድክመት በተለያዩ ደረጃዎች ይከፈላል። ቀዳሚው (Loss of desire) ማለትም የሰውዬው የለ ፍላጐት ማጣት ወይም የተቃራኒው ታታ ስሜት መሳሸት ነው። ሁለተኛው ወንድየው የሴት ፍላጐት ጥሮት ብልቱ የማይታዘዝለት ነው።

ሶስተኛው ደግሞ ፍላጐት አያጣውና ብልቱም እየታዘዘለት ወደ ሴት ሲጠጋ ግን ሳይታሰብ ስፐርሙን (ዘሩን) የሚለቀው ነው። ይህን ወቅታዊ ያይደለ ፍሰት (pre-mature ejaculation) የሚያጠቃው ነው ማለት እንችላለን።

እንግዲህ መጀመሪያ ወደ ተነሳንበት የ«ፍላጐት ማጣት» ስንመለስ፣ የዚህ መነሻው «የቱስቴሮን እንድሮጂን» እጥረት ነው። በቀለሞ ውስጥ፣ በአንጐልና በተቀሩትም ስፍራዎች የሚመረት የአንድሮጂን እጥረት አለበት ማለት ነው። ይህም ብቻ ሊሆን ሰውዬው የተለያዩ ችግሮች ይኖሩበታል። የፍቅረኛ (የትዳር ጓደኛ) አለማግኘት አንዱ ምክንያት ነው። በህመምና ውጥረት

በሚያስከትሉ ስራዎች መጠመድም ግለሰቡን ስለወሲብ እንዳያስብና እንዲዘናጋ ያደርጉታል። ወደ ብልት መታዘዝ ስንመጣ ደግሞ የነርቭ ስርዓቶችና የደም ስሮች በሚገባ መስራትን እንመለከታለን። ይኸውም በሰውዬው የወሲብ መሻትና ሴቲቷን ባየ ጊዜ ሰውነቱ ላይ በሚንፀባረቀው የስሜት ፍላጐት (ሬፍሌክስ) ይታገዛል።

ሌላው ችግር የነርቮቹ ተግባር የተሳከና የተዋጣ ቢሆንም በአከርካሪው አካባቢ የደም ስርጭት አለመስተካከል ወይም አለመሟላት የብልቱ መቆምን ሂደት የተሟላ ሊያደርገው አይችልም።

ይኸም ብቻ አይደለም። ሰውየው በየቀኑ አልኮል አብዝቶ ከጠጣ፣ ሲጋራ በብዛት ካጨሰ ገና ወደሴቲቷ ብልት እንደተጠጋ ወትሮም ላልሆነ ፍሰት (ኢጃኩሌሽን) ይጋለጣል። ይህም ሰውዬው እንደፈለገ ብልቱ ዳግም እንዳይቆምለት ያደርጋል።

በ1980 ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ለመገንዘብ እንደቻልኩት የስኳር በሽታ ያለባቸው ህመማን እስከ 6 ዓመት ስኳራን በሚገባ ካልተቆጣጠሩት ሁለት አይነት የወሲብ ችግር ላይ ይወድቃሉ። አንደኛ «ኒውሮፓቲ» ማለትም የሰውዬው ነርቭ «ኢምፐልሰን» (ንዝረትን) መቀነስ፣ ሁለተኛው ደግሞ «አንድ ሪዮፓቲ» ማለትም የጥቃትን ነርቮች በሚገባ አለመስራትና በክህደም ሳቢያ የሚከተለው የቆዳ ቁስልና የቁስሉም ቶሎ አለመዳን ሰውዬውን ስሜተቢስ ሊያደርገው ይችላል።

ይኸም «ኒውሮስጂካል ዲስኦርደር» ትድም የነርቮች ቁውስን ስለሚያስከትሉ ያልናቸው «ሲምፓቲክና ፓራ ሲምፓቲክ» ነርቮች የሚፈለገውን «ኢምፐልስ» (ንዝረት) ወደሚፈለግበት ቦታ አያሰራጨም ማለት ነው።

የደም ብዛት ያለባቸው ሰዎች ለዚሁ በሽታ ሲሉ የሚመከሯቸው አንዳንድ መድኃኒቶችም የኢምፐልስ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንሸራሸርን በመግታት ሰውዬው የተሟላ ስሜት እንዳይኖረው በማድረግ ስወሲባዊ ድክመት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

ሰላው አስካሁን ሳልጠቅሰው የዘለልኩት «ፕሮላክቲን» ስለሚባለውና ጭንቅላታችን ውስጥ በተወሰነ አካባቢ የሚመረተው ሆርሞን ነው። እነዚህ ለደም ብዛት የሚወሰዱት መድኃኒቶች ጭንቅላታችን ውስጥ በአንድ ነፍል የሚመረተውን ሆርሞን ስለሚያነቃቁት በስሜቶቻችንና ፍላጐታችን ላይ የሚያካሂደውን ተግባር እንዳያከናውን ያስተጓጉለብታል።

ይህ ብቻ አይደለም። ሰሰ-ሰኝነት የሚጸርጉ መድኃኒቶችን፣ አለኮልና ሀሺሽ እንዲሁም ከፍተኛ የኒኮቲን ኃይል ያላቸውን ዕፆች የሚጠቀሙ ሰዎች በነዚህ ሱሶች ከጎፉ ስወሲባዊ ድክመት መጋለጣቸው የማይቀር ነው።

ለላው የቆለጥ በሽታን፣ እንደ ጀሮ-ደግፍ የመሳሰሉትን ህመሞች በጊዜው ካልታከመ አርካይትስ የተሰኘ የቆለጥ እብጠትንና መቆጣትን ያስከትላል።

እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቆለጥ ውስጥ ያሉት ሴሎች ይወድማሉ። ይህም በቆለጡ ውስጥ የሚመረተውን ስፐርም (ዘር) አደጋ ላይ ከመጣሉም በላይ «ጀኔቲክ ዲስ ኦርደር» ስለሚያስከትል የሰውየውም ቆለጥ መጠንና ቅርፅ እንዲመነምን ያደርጋል።

«ትራውማ» የሚባለው በሽታ ደግሞ ከተለያየ አደጋዎች በኋላ የሚመጣ ነው። አንድ ሰው በመኪና አደጋ፣ በጠብና በጨዋታ ብልቱ አካባቢ ጉዳት ከደረሰበት በዚያ የሚገኙ ሴሎች ይጐዱና የተሟላ አገልግሎታቸውን መስጠት ያቋርጣሉ።

ደማችንን ወደታችኛው ሆዳችን አካባቢ (ስብዶሜን) የሚያሰራጨው ዋናው የደም ስር በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰተጓጐለ በብልቱ አካባቢ ያሉት ሴሎች በቂ ደም

ስለማያገኙ ስፐርም (ዘር) በማምረቱ ረገድ መደበኛ ተግባራቸውን ሊያከናውኑ አይችሉም። ባጠቃላይ የነዚህና የሌሎች ድምር ምክንያቶች ለብልታችን አለመታዘዝ አፍራሽ ሚና የሚጫወቱ ናቸው።»

«ይህ የወሲባዊ ድክመት ህክምና በአገራችን ውስጥ በብዛት ይሰጣል?»

«ህክምናው በአገራችን እምብዛም አልተስፋፋም። ያልተስፋፋበትም አንድ ምክንያት በባለሞያ አጥረት ነው። ሌላው የታማሚዎቹ ወደ ሀኪም ቀርበው ችግራቸውን ይፋ በማድረግ የህክም እርዳታ ሰመጠየቅ አለመቻል ነው። በአስካሁኑ ተሞክሮዬ አንኳን አንዳንድ የራሴ ታካሚዎች ሳይቀሩ በትክክለኛው ስማችን ካርድ አናወጣም ይላሉ። በፈጠራ ስም ነው ለመታከም የሚፈልጉት። በጣም እፍረት ይሰማቸዋል። ይሄ ግን የሚያሳፍር አይደለም። እኔ ዘንድ የሚመጡት ብዙ ናቸው ሰማለት አልደፍርም። ጥቂት ናቸው። የመጡት ግን ጥሩ ውጤት አያገኙ ነው። «ተሽሎናል፤ የፈለግነውን አያደረገን ነው» ይሉኛል። ችግር ከሌለባቸው ተመልሰው አይመጡም። እኔ ዘንድ ከታከሙት መካከል አንድ ሁለቱ ናቸው ጥቂት የተመሳሰሉት። ሆተቀሩቱ ያዘዝኩላቸው መድኃኒትና የሰጠኋቸው ምክሮች ወዲያውኑ እንደሰሩላቸው ነው ያበሰሩኝ።

እኔ ወሲባዊ ድክመትን በሚመለከት የቀዶ ጥገና ህክምና አላደርግም። ለችግሩ የተጻረጉበትን ምክንያት ነው አስቀድሚ የምከታተለው። በዚህ መሰረት ጫት አዘዘተው የሚቅሙ፣ ሀሺሽ የሚጠቀሙ፣ አድሚው የተራዘመና ተገቢ መከላከል ያልተደረገለት፣ የስኳር በሽታ ያለባቸውና አንዳንዶቹም በአድሚ መማሩት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለዚህ ችግር ሲጋለጡ እንደሚችሉ በአስካሁኑ ከትትሉ ለማወት ችያለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላው ለዚህ በሽታ ምክንያት የሚሆነው በእባለዘር በሽታ በተደጋጋሚ መጠቃት ነው። የተደጋገመ የእባለዘር በሽታ ለመሀንነትም የበዛ አስተዋፅኦ አለው። በተለይ «ነኖሪያ ፖስተሪዬር» የተባለው የሽንት ቧንቧችንን በማጥፋትና ወደ ፅንጥም በመዝለቅ በዚያ የሚገኙትን ሴሎች ያጠቃቸዋል።»

«ወሲባዊ ድክመት በዘር ይተላለፋል?»

«በዘርስ አይተላለፍም።»

«የወሲብ ስሜታችን ሲነቃቃ ተራክቦ ካላደረግን ለወሲባዊ ድክመት በሽታ እንጋለጥ ይሆን?»

«ሰውዬው ፍላጐት አያለው ሩቃ በማይሰጥ ስራ በመጠመድ የበታ ርቀት ባላቸው ስራዎች የተነሳ ተገልሎ ከኖረና ከሴቶች ከራቀ ብልቱ እየቆመ እየወደቀ ኃይሉን በመጭመቅና በመጻከም «አትሮፊዶ ቱስቲስ» አሊያም የግላንድ አትሮፌ ሊያስከትልበት ይችላል። ይኸ አነጋገር ጠቅለል ተደርጐ ሲታይ የብልት አካባቢ ጡንቻዎችን መጻከም ያስከትላል ማለት ነው። አንድ ሦሳሊ ብንወስድ፣ ቀኝ እጃችንን አብዝተን ስራ ላይ ስለምናውለው ከግራ እጃችን ይልቅ በጣም ጠንካራ ነው። ግራ እጃችንን አብዝተን ስለማናሰራው ወደ «አትሮፊ» የጡንቻ ድክመት ነው የሚያመራው። እናም ለማንኛውም በተወሰነ ጊዜ፣ ማለትም ባስፈለገን ጊዜ ተራክቦ መፈፀሙ ይመረጣል። ለዚህ ደግሞ ጤናማው መንገድ በትዳርና በፅሚ ጉድኝት መጣመር ነው።»

«ይኸን በተወሰነ ጊዜ ያለነውን ጉዳይ በቀን በቀን፣ አሰልሶ አሊያም በሳምንት መደረግ አለበት ብለን የጊዜ ሰሌዳ ልናበጅለት ይገባል?»

«እዚህ ላይ የአያንዳንዱ ተፈጥሮ ልዩ ነው። በቀን በቀን የሚያስፈልገው አለ። አንዳንዱ ደግሞ በየሶስት ቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየአስራ አምስት ቀን ተራክቦ ለማድረግ የሚፈልግም አለ። አንግዲህ አንዳንዱ ሰው በተፈጥሮ በጣም ፍላጐት ሊኖረው ይችላል። የአንዳንዱ ደግሞ መጠነኛ ነው። የሌላው የቀነሰ ነው።

ሌላው ጉዳይ አንዳንድ ሰው በወጣትነት እድሜው ለፍልሰፍና ለሳይንስ ስራዎች ራሱን በማስገዛትና ሙሉ ጊዜውን በዚሁ ምርምርና ጥናት ላይ በማዋል ቀንና ማታ ይሽን ፈጥሬ ያንን አሻሽዬ በሚል ውጥረት ነገረ መሲቡን አርግፍ አድርጐ ሊተወው ይችላል።»

«ዶክተር፣ ቶሎ ቶሎ ወይም በቀን ከአንድ አስከ ሶስቱ ተራክቦን መፈፀም ከጤና ሁኔት ጋር ምን ግንኙነት ሊኖረው ይችላል?»

«አንግዲህ ደህና ከበላ፣ ጤናማ ከሆነ አምብዛም ለጉዳት አይዳረግም። ምግብ የማይበላ ከሆነ ጉዳት ላይ መውደቁ አይቀርም። በሌላ መልኩ ደግሞ አንዳንድ «ማኒያክ» (ጤናማ ያልሆኑ) ሰዎች፣ ማለት በአእምሮአቸው ጠዋት ማታ ስለመሲብ የሚያስቡ፣ የሚያልሙና ይሽንኑ የሚያደርጉ ሰዎች አይጠፉም። በተለይ ከ18-30 ባለው እድሜ አንዲህ አይነቱ የፍትወት ረሀብ ሊኖር ይችላል። ከዚያ በኋላ ግን «ማቹር» እየሆነ ሲመጣ (ሲበስል) አስተያየቱ፣ ስሜቱ ከሌሎች ተጓዳኝ ችግሮች ጋር ስለሚጣመሩ ስሜቱ ሊቀንስ ይችላል።»

«ስፖርም ራሱ የፓሮቲን ውጤት ነው ይባላል። ታዲያ እነዚህ እርስም «ማኒያክ» ያሉአቸው በሽተኞች ሰዎች በፓሮቲን ማነስ ሳቢያ የበሽታ ሰለባ ሊሆኑ አይችሉም ወይ?»

«ቅድም እንዳልኩት ሰውዬው ካልበላ እንኳን «ማኒያክ» ሆኖ ኖርማልም ቢሆን የጤና ችግር መኖሩን መሸሸግ አልችልም። ምግብ ካልበላ ስሜቱም ሊኖር አይችልም። ቢኖርም ለጊዜው እንጂ ቀጣይ አይደለም። አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ ሰውዬው ቀጥ ይላል። ፕሮቲን፣ ፋት፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርቦ ሃይድሬት በሚገባ ሰውዬው ህዋሳት ውስጥ ካሉ በምን አቅሙ ሊነቃነቅ ይችላል!?»

«ለጤና ጠቃሚ የሆነው የተራክቦ ጊዜ መቼ ቢሆን ይመረጣል? ሲነጋጋ፣ ቀን፣ ማታ ወይስ አኩለ ሌሊት ላይ?»

«ይሄን መመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። አንደ አውነቱ ከሆነ ተራክቦ በዚህ በዚያ ሰዓት መደረግ አለበት የሚለውን ከመሠፍት እንኳን ያገኘሁበት ጊዜ የለም። በኔ ግምት ግን ማታ ቢሆን ነው የምደግፈው። ምክንያቱም ሰውዬው በስራና በተለያዩ ጉዳዮች ሲደክም ው-ሎ- ሰውነቱን ለማዝናናት አስከሆነ ድረስ ማታ ቢሆን አይከፋም። ግን አሁንም ቢሆን ለተራክቦ የጊዜ ሰሌዳ መቀመር አስቸጋሪ ይመስለኛል።»

«ወሲብ ደስታን ይለግሳል ወይ ዶክተር?»

«(sex is psychological game) (ወሲብ የሰነ-ልቡና ጨዋታ ነው) በወሲባዊ እርካታ የሰውነታችን ውጥረት ሁሉ ይረግባል። አንድ ሰው በስራ ሲደክም ው-ሎ- ከገባ በኋላ ደህና ሚስት ወይም ጓደኛ ካለችውና ያንን ሁሉ ካጫወተችው ድካሙን ሁሉ ይረሳል።»

«ሴቶች በዚህ የወሲባዊ ድክመት በሽታ አይጠቁም ወይ?»

«ሴቶችን በሚመለከት ረገድ ብዙ ጊዜ የሚያጠቃቸው የፍላጐት ጉዳይ ነው።»

«ፍላጐት ሲሉኝ?»

«ለምሳሌ እኔ በነበርኩበት ሀምበልት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ይሽን የኢምፖተንስ ህክምና የሚሰጥ አንደ ፕሮፌሰር ስለበሽታው ወንዱን ሲያነጋግር ሴቷንም አይረሳትም።»

«አይረሳትም ሲሉኝ?»

«ለምሳሌ እርሱ (ባልሽ) ፍላጐት ኢያሰው አንቺ ትከለክይዋለሽ ወይ? ወይንስ እርሷ ፍላጐት ኢያላት አንተ

ትነፍጋታለህ ወይ? ይላቸዋል። ይሄም ጥረት እንግዲህ የፍላጐት መሳሽትን ችግርና ሁኔታ ለመፈተሽ ነው። ምክንያቱም «ሳይኮሎጂካል ኒርቫልና ጂኒቲክ ዲስ ኦርደር» (ስነ ልቦናዊ፣ ነርቫዊ ቀውስ) ያጠቃት ይሆናል ሴቲቷን። ባብዛኛው ግን ስነልቦናዊ ነው የችግሩ መንስኤ። ለምሳሌ የወንድ «አንድሮጂን» የሴቲቷ ኤስትሮጂን የሚባል ሆርሞን አለ። እና የዚህ ሆርሞን ችግር ካለበት ፍላጐት ላይኖራት ይችላል። በዚህ ጊዜ ስሜት ቀስቃሽ የሆነ የስሜት ማነቃቂያ (ማበረታቻ) መድኃኒት ይታዘዝላታል። ከመድኃኒቱም ባሻገር ዋነኛው ህክምና ስነልቦና መነቃቃት ነው። ለምን ቢባል ከሰቱም ከወንዱም ወሲባዊ አይናፋር ሞልቷልና፣ አንዱ ያለ ሌላኛው መኖር እንደማይችል ግንዛቤ የሚያገኙት ይኸ ስነልቦናዊ መነቃቃትና አድገት ሲኖር ነው። የሆርሞኑ በደም ስርጭትም ማነስ በሴቷም ላይ ሊኖር ይችላል። በዚህ ረገድ የሚሰጣት መድኃኒት ወሲባዊ ፍራቻዋን ያረክሰላታል። ወሲባዊ ቅመሞች ቡተገቢው መንገድ እንዲመረቱ የነርቭ አንቅስቃሴዎች የተሻሉ እንዲሆኑም ያደርጋል።»

«አንግዲህ ይኸ የስነ ልቦና ሽብር ከወሲባዊ ድክመት ጋር ተሳማጅነት አለው ማለት ነው?»

«ዋናውም በሽታ ይኸ ነው - የስነ ልቦናው ጉዳይ። አንድ ሰው ይኸን ሰምን አደርጋለሁ? ሰው ቢያየኝስ? በሚል ይሉኝታ ይወጠራል። መፍራትና ነገሮችን በአግባቡ ማድረግ መልካም ነው። ሁሉም ነገር አንደ አንስሳ ይሁን ማለት አይደለም። በርግጥ ነገሮችን ማመዛዘን መቻል ደግ ነው።»

«ማስተርቤሽን (ሴጋ) ለወሲባዊ ድክመት ይዳርጋል ወይ?»

«ሴጋ ማለት ሰውዬው ብልቱን በሞቀ ነገር ወይም በለስላሳ ነገር ስሲያም ከተቃራኒ ፆታ ጋር በመተሻሸት

t.me/OLDBOOKSPDF

ስፐርሙን የሚያፈስበት ዘዴ ነው። ይህ እንግዲህ ሰውዬው ስሜቱ ሙቦሮት ስሜቱ አስቸግሮት ያለተቃራኒ ፆታ ወሲባዊ እርካታን የሚሻበት ሌላኛው መንገድ ነው ማለት ነው። እንግዲህ ‹‹እዚህ ላይ ብዙም ሰማለት ባልችልም ምናልባት ወቅታዊ ላልሆነ ፍሰት (pre-mature ejaculation) ሊዳረግ ይችል ይሆናል ብዬ አንም ታለሁ። ምክንያቱም ከሰው ጋር ተገናኝተን የምንነጋገረውና ለብቻችን የምናስበው አንድ አይሆንም። ከሰው ጋር ተገናኝቶ ሀሳብ ለሀሳብ ተግባብቶ በስነ ልቦና ጥምረትም ውሳኔ ላይ መድረስ ሌላ ጉዳይ ነው። በማስተርቤሽን (ሴጋ) ወቅት ግን አንድ ሰው በራሱ ፈቃድ ከመቅፅበት የሚያፈስበት ሁኔታ ነው። ያ ሰው ግን የሽንገ የሚያደርግበት የተለየ ምክንያት ይኖረው ይሆናል።

ምናልባትም ከሴት ጋር የመገናኘት ፍራቻና ችግር ይኖረው ይሆናል። ለዚህ ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮችን ብንመለከ ሰውዬው የሌት ንደኛውን (ፍቅረኛውን) ወደ ሆቴል ወይም ቤት ወስዶ ለማስተናገድ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የስነ ልቦና ሁኔታዎች ሊሚሉለት ይገባል።››

ጨና



የኩላሊት ሚስት

ተስፋዬ ገብረአብ

ጊዜው 1968 ታህሳስ ወር ነበር። ከ23 ዓመት በፊት። አዲስ አበባ ሊሲ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ጀርባ በአንድ ቪላ ውስጥ የምትኖረው የኮሎኔሉ ማስት በዚያን ጊዜ የተፈፀመውን በሙሉ ልቅም አድርጋ ታስታውሰዋለች። «የጠነነ ችግር ላይ ነኝ» ብሎ፣ እንባቱን ደፍቶ፣ ለምኖና ተለማምኖ ዘበኛነት የተቀጠረውን ያን ሰው በፍፁም አትረሳውም። ምክንያቱም እንዲያ ድቁስቁስ ብሎ የነበረው ያ ምስኪን ሰው ጥቂት እንደቆየ ጥጋብ አምጥቶ ነበር። ስራውን በቅ ካሮረገ በኋላ እንገት ደፊነቱ ቀረ። ዘበኛ እንደመሆኑ መጠን አሜን ብሎ የሚኖር አልሆነም። ትራፊ ምግብ ሲተርብለት አይበላም። የሚፈበፍበ ነገር ይተበቀበበትና

t.me/OLDBOOKSPDF

«ብቃኝ» ይላል። በዚህ ላይ ከአንዲት የኮሎኔል ሚስት ፊት ቆሞ ቁጣ ሲወርድበት ጭራውን እንደ መሽንጦጥ፣ እንቁን እንደመስበር፣ እንደ ወይፈን ተፋጥጦ መልስ ይሰጣል። ይህ ታዲያ ጥጋብ ካልሆነ ሌላ ምን ሰም ይገኝለታል?

የአዲሱ ዘበኛ ባህርይ ኔያበሳጫት የመጣችው የኮሎኔሉ ሚስት በአንድ ዕዙታዝዝት ተሲያት፣ የበላች የጠጣችውን በአድብ ሙልጭ አደረገችው። ዘበኛው ግን የሚደነፍጥ አይነት አልነበረም። ስሜቱ ሳይለወጥ በፀጥታ ያዳምጣት ነበር—

«ስማኝ» አሰችው እንደ እሳት ምላስ እየተወናጨፈች «—የተቀጠርከው የግቢ ዕጽት ስራና ዘበኝነት ነው። ይህን ታውቃለህ?»

«አውቃለሁ እመይተይ—»

«ምን ታውቃለህ? ብታውቅማ ኖሮ ለጥ ለጥ ብለህ ስራህን ትሰራ ነበር። እንዲያው ሰመሆኑ በሰላሳ ብር የወር ደሞዝ ዘበኝነትና ግቢ የማፅዳት ስራ ማግኘትህ ታላቅ ዕድል መሆኑን አታውቅም?»

«እሪ አውቃለሁ እመይተይ— ግን ምናጠፋሁ?»

«ምፀጠፋሁ?» የኮሎኔሉ ሚስት ከበረንዳው በልሳ ወርጻ የዘበኛው አንጭ ስር ተጠግታ ታምባርቅ ጀመር «—አፍህን ሞልተህ ምናጠፋሁ ትለኛለህ? ተመልከት አስቂ ግቢውን? ያ የወደቀ ወረቀት ምንድነው? ይህ ቡትሑ ጪርቅስ ቀሸሽ አይደለም? ይህ በት የአንድ የተከበረ ኮሎኔል ቅፅር ግቢ መሆኑ አይገባህም?»

የኮሎኔሉ ሚስት በንዴት እያበደች በግቢው ውስጥ የወደደቁትን ወረቀቶች እያነሳች ትጮህ ቀጠለች፣

«—ይህን ቆሻሻ ታየዋለህ? ይህን መልቀም ይጉተ ስራ ነበር። ቤወር ለሳሳ ብር የሚከፈልህ ቆመህ ስታፈጥብኝ እንድትውል ይመስልሀል? ግዘው እንዲህ አህያ ሲፈነጭብት የኖሰ ሲመስል አንተ በግዴለሽነት ቆመህ ታፈጥብኛለህ!?»

«ትናንት እስ አዕድቼው ነበር እመይተይ— ዛሬ ዙየት እንደመጣ»

«አዝ ወረቀቶቹ እንደ ወፍ እየበረሩ ግቢያችን ውስጥ መሞላት ጀምረዋል በለኝ! ይኸው ነው የቀረህ! አሺ ደህና፣ የግቢውን ዕጽት ተወው— ሌሊት የመንደር ውሾች ሁሉ መስሎቱ ስር ተሰብስበው እንዴ ነሽ ንጹምን ሲጨፍሩ አንተ የት ነበርክ? ለጥ ብለህልኝ ነዋ የኔ ጌታ! ምን አሳብ አለብህ? ውሾቹ ግቢዬ ውስጥ ሲሉቱን ሙሉ እስከሰህ ሲወርዱ፣ አገሮገሪ አቁመው አለማቸውን ሲቀጩ አንተ እንደ ግንድ ተጋድመህልኝ ነበራ! በልንገረኝ! ይሄስ ህሰት ነው?»

«ወጭራሽ አልተኛሁም እመይተይ— እንዲያውም የውሾቹን መግቢያ ቀዳዳ ሁሉ ደፍኜዋለሁ። መቹም ውሾቹ እንዳሞራ በሰማይ በርረው አይገቡ—»

የኮሎኔሉ ሚስት በንዴት ተቃጥላ የከበሪት እንጨት አነሳች፣

«ንግግርህ ዕንዴት ነው? አንተ ገበራ! ስርተህ ማደር አትፈልግም? ቡዘራዋ ቀን የእንጀራ ገመድህን ልበየስ እንደምችል አትረዳም? የምን እንዙር እንዙር ነው? ደሞስ እኔን ውሽታም ለማለት መድፈርን ማን አስተማረህ? ወሾቹ ሳይጮሁብኝ ዋሽቼ ተናገርኩ? እኔ ውሽታም ነኝ!?»

«እሪ አልመጣኝም እመይተይ—»

«አልክኝ እንጂ! ውሽታም አልክኝ። ቀጣፊ አልክኝ። በልብህ ይሄኔ ስንቱን ብለገፍኸል። ቀልቃላ ክውላዋ! አሰብላቢት— ብለኸኝ ለሆን ይችላል። የወላዲት ያለህ! ስማኝ ልንገርህ አንተ ደህ ገበራ! እኔ አንተ በልብህ እንደምታስበው ተትረ ቀላል አይደለህም። የአንድ የተከበረ ኮሎኔል ህጋዊ ሚስትና አመቤት ነኝ። ውስጤ ከጀኔራሎች ሚስቶች ጋር መሆኑን ልታውቅ ይገባሀል። የነሬን አያርገውና ደሞ ከልዕላን ቤተሰቦች ጋር ራት የበላህበት አጋጣሚም ተፈጥሮ ነበር። ገባህ? አንተ ደሞ ዘበኛ 'ክ። ያኔ ስትቀጠር እንጀራ ፈላጊ ነኝ' ብለህ መትስክስህ ከሞነው ተረሳህ? መቀመጫህን ካደሳደልህ በኋላ ልብህ አበጠ።»

«እሪ አመይተይ— እኔ አሁንም የቸገረኝ ደህ ነኝ። ሚስቱ ሞታብኝ፣ ልጀ ጠፍታብኝ መንደሬን ትቼ ልጅን ፍለጋ ስመጣ—»

«አሱንማ ነግረኸኛል። ሰትድገምብኝ!»

«አሺ ይቅር ይበሉኝ እመይተይ። አጥፍቻለሁ—»

ይህን ጊዜ የኮሎኔሉ ሚስት ረገብ አለች።

«እንዲያው ጥጋብ ደግ አይደለም። ሰሊቱን ሹልክ እያልክ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደምትወጣ ደግሞ የማላውቅ አደምስልሀ። ተረጋጂም ሁሉቱ ሴቲት ብቅ በል እየቸህለህ።»

«ሽረ የትም አልሄድኮ እንዲሁ ጉዳናው ላይ ወጂያ መሄዱ እያልኩ ስጠበቅ ነው።»

«አትዋሸኝ፡ የተቀጠርክለው ለኔ ቤት እንጂ ለአዲሳባ ከዛማ ጥበቃ አይደለም። ሴት ስምደህ ይሆናል መቼም... እንኪን እቺ እኔ የተጋጫ ወንድ አይጠፋኝም።»

«ሽረ እንዲያው ሚስቱ ሞታ ገና ለዘቡ እንኪ ያልወጣልኝ።»

«ለሚስትህ አትደጋም ብኛ ብዬሀለሀ። ለማጭወውም ስራህን ቱር ብለህ ትሰራንደሀ ስራ። እንጥትህን ደፍተህ ትኖርንዲ ኑር። አሰልቢያ ምን እንደሚከተልህ ታውቃለህ?»

«ሰውቃለሁ እመይተይ።»

«እምነ ይሄ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው።»

ሆኖም ከዚህ ማስጠንቀቂያም በኋላ ዘበኛው ጠባዩን ሳያስተካክል ቀረ። እንዲያውም አንድ ቅዳሜ ጥን በጥቢሎ ቤታው ላይ በደከው ባለመገኘቱ፡ ለኮሎኔሉ መኪና በር የሚከፍት ወፍቶ ራስዮ የኮሎኔሉ ሚስት ዘበኛውን ወክለ በሩን ለመክፈት ተገደደች። ይህም ዘበኛው ላይ ለመጨረሻ ጊዜ እንድትጨክን አደረጋት። ያለማመንታት ልታባርረው ወሰነች። ከቀና ደገ ከመናገር አሰናበታው መገላገሉን መረጠች። የደሞዙ ጊዜ አሸ ቀናት ብቻ ነበር የቀረው። ስለዚህ በዚያ አሸር ተጎ ጊዜ ውሰዶ ተሰዋሚ ዘበኛ ፈልጋ ቅሽትዋን ያደበነውን ጥጋገቦ ባላገር ስራ እዋ ልታደርገውና በድንጋጤና በቱሮት አፍጉ ሲል ልታየው ችኮለች። ግን ምን ይሆናል? አሸርዋ ቀን ከማሰፍዋ በፊት ዘበኛው ረፉ የስራ መልቀቂያ ጥያቄ አቀረበ። ያኮሎኔሉ ሚስት የልብዋን በልብዋ ይዛ፡ በመቀደምዋ እየተንገበገበች፡

«ለት ልትሂድ ነው?» ስትል ጠየቀችው።

«ለላ ስራ አገኘሀ»

«ሕዙ ዬት?»

«ፒያሳ፡ ላውንደሪ ቤት ውስጥ። እና ቢቻልም ደሞዜን ቢለጡኝ...»

የኮሎኔሉ ሚስት በመቀደምዋ ብትበግንም፡ ቁጭትዋን

የመሙላ እንድ የመጨረሻ ዕድል ግን ነበራት። ደግሙን መፀልሰል፡ እና እንዲህ አሰችው።

«ሕዙን በድ ገንዘብ የለም። ሴላ ቀን ተመለስ...»

ዘበኛው የኮሎኔሉን ሚስት ተሰናበቶ ሂደ። ሆሄደ በአስረኛው ቀን እየዘዜ ዘበኛው ደምዙን ሊመስድ እንደሚመለስ የኮሎኔሉ ሚስት በረጋወንት ጠብቃ ነበር። ግን ሳይሆን ቀረ። ነዘራ ነገ ይመጣል እያለች ጠበቀችው። የውሳ ሽታ ሆነ። እንድ ወር እገደሞነ አለፈ። ሁለተኛው ወር ተቀላ። ሶስት ወር...

የኮሎኔሉ ሚስት ዘዳ ዘጠ ልብዋን ሚር አደረገው። «እንዲያው መኖሩ ገንዘቡን ነወሰድ። የደሀ ገንዘብ ለኔ ምን ያደገልኛል? እምላዙም አይወደውም» አለች ለራስዋ። ይህን ያለችው ከልብዋ ነበር። ዘበኛው ግን እንደጠባ ሳይመለስ ቀረ። የኮሎኔሉም ሚስት አሶቀች ስለ አስቸገረው ዘበኛ ፈለረሳ ረሳች። ጊዜው ግን ይሄዳል። አንድ ዓመት አለፈ፡ አሸር አመት፡ አስራ አምስት ዓመት...

* * *

ይህ ታሪክ በተፈፀመ በአስራ ስምንተኛው አመት፡ የደረግ ስርዓት ነወደቀ በሁለተኛው ወይም በሶስተኛው ዓመት፡ ታህሳስ ወር ላይ አንድ ሽበት የወረረው፡ ሙሉ ስወፅት ያለው ጠያም ስው በሶስት ታጣቂዎች እንደ ታይበ ከኮሎኔሉ ቤት ደጅ ላይ ቆመ። ሰውየው ባለስልጣን ሰመሆኑ ምንም ጥያቄ አልነበረውም። በአጃቢዎቹና በመኪናው ብቻ እንኪ ይህን መናገዝበ ይቻላል። አጀቢዎቹ ሶስት ነበሩ። ከሶታኛ ባለስልጣኑን ነበው ግራ ቀኙን፡ ፊት ኋለውን በየንታቂ ይጠብቁታል። ይህን ማድረቸው መቼም ተገቢ ነው። ምነንያቱም ሰውየው ኪህአዴግን ነመሪውት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች አንዱ ነበር።

የኮሎኔሉ ሚስት አርጅና ተመዟጭተአታል። ቢሆንም ራስዋን አልጣለችም። የቀድሞው የተቀናጣ ኑሮዋ ግን አብሮአት አልነበረም። የቅንጦት ዘመን እንደ ወጣትነትዋ ጥሎአት ነጽዶል። አንዲት ውብ ቀይ ቶዮታ ክሪሲዳ የቤት መኪና ቪራፍዋ ላይ በቆመችበት በዚህ ምሽት የኮሎኔሉ ሚስት በረንዳዋ ላይ ተቀምጣ ካናዳ ለሚገኝ የወንድምዋ ልጅ ደብዳቤ እየጻፈች

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። ገርበብ ያለውን በር ያለጥያቄ ከፍተው ወደ ግቢው የዝሎቂት ሰዎች ድንገተኛ ድንጋጤ ቢፈጥሩበትም፣ አንደ*ምንም* ራሳቸውን አረጋግታ ሶስቱ ታጣቂዎችና ባለስልጣን መሰሉ ሰው ላይ አይኖችዋን ተክላች፤

ስውየው ፈገግ አለ።

የኮሎኔሉ ሚስት ግራ እንደተጋባች አይኖችዋን ከንግደቱ ላይ እንደተከለች ነበረች፤

«አመይተይ_ ረስተውኝ ይሆን?» አለ ሰውየው።

«አንቺ ልጂ_ ማን ልበል ርስዎን?»

«እኔ ከ18 አመት በፊት እዚህ ቤት ርስዎ ዘንድ ዘበኝነት ተቀጥሬ ነበር_»

«ዘበኝነት?»

የኮሎኔሉ ሚስት ገፅታ ባንድ አፍታ አመድ መሰለ።

ያ ደሞዙን ያልወሰደው ዘበኛ ፊትዋ መጥቶ ድቅን አለ።

«አስታወሱኝ_?»

የኮሎኔሉ ሚስት ግን አንድ የተሳካ አረፍተ ነገር እንኩዋ መናገር ተስኖአት፤


«_እንዴት_ ታዲያ አሁን_ ያኔ ምን?» ከማለት ውጭ ከዙ የምትለው ጠፋት።

ቅኖት ቢጤ ሆነባት_

ከአስር ዩቂቃ በኋላ ሁለቱ በአድሚ የገፉ ሰዎች ዘመናትን ባሳለፈው የአርጌ ሸላ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጠው ስላለፈው መጨዜዋወት ያዙ። የኮሎኔሉ ሚስት የተድሞ ዘበኛዋን ረጅም ዮትንል ታሪክ ባጭሩ አዳመጠች። ከሁሉም ያስደነቃት ግን ያኔ አርስዋ ቤት በዘበኝነት የተቀጠረው ከበረሃ ሰድርድታዊ ስራ መምጮ መሆኑንና፣ ዘበኝነት መቀጠሩ ደግሞ ነፃብሌ መታወቂያ ለማግኘት ይረዳው ዘንድ እንደነበር፤ በዚያም ምክንያት በየሩሁኒታ ተሽሽሎ ስራውን እንዳቆመ በገለጸት ጊዜ ነበር። የኮሎኔሉ ሚስት አስገራሚውን ታሪክ አድምጣ ስታበቃ እንደው እንደ ዋዛ አንዲት ጥያቄ ጣል አደረገች፤

«ለመሆኑ ስምዎ ማን ይባላል?»

«ስማዘት ኒጋ።»



የመሳሳም ምስጢር

መኩሪያ መኳሻ

መሳሳም ተሳልና ተፈጥሮአዊ ነገር ይመስላል። ስለ መሳሳም ምን ያውቃሉ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ «ሁሌ እኖተሞ*ሚመ*ሟን ምን ያጠያይቀና?» በሚል ስሜት ሊፈግጉም፣ ሲገረሙም ይችላሉ። ጉዳዩ ግን እንዲህ ተሳል አይደለም። ለአውሮፓውያኑ መሳሳም የረሽም ጊዜ ልምድ ሆኖ የኖኖ ነው ቢባልም በአፍሪካ፣ በአሚሪካ፣ በአውስትራሊያና በጠዙዎች፣ የእስያ ሀገሮች አስክዚህም የታወቀ አልነበረም።

በአንዳንድ ሀገሮች «ሳአፍንጫ አሳሳም» አለ። በአፈ*ጮ*ኤቸው ሲሽተቱ መደም ሲዳሰሱ ብቻ ነው በትክክል ተሳስመናል የሚሉት። ይህ ዓይነቱ አሳሳም በሰሚን አውሮፓ ሕዝቦች በተለያም በስዊሞዎች (የበረዶ ሰዎች) አና በማሌዢያኖች ዘንድ የተዘውተረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው።

የአፍ መሳሳም አፅዋፍ በምንቃራቸው ምግብ ሲሳዋወጡ ከማዜት የተወረሰ ነው የሚል ግምት አለ። ለምሳሌ በቀጭ ደሴት አናቶች ለሕፃን ልጆቻቸው ከአፍ-አፍ ጡጋ በመሰጠት እንደሚያጠቧቸው ይታወቃል። ከዚሁ ጋር የአፍ መሳሳም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከእናቶች የልጆቻቸው አመጋገብ ጋር አየተናሰለ እንደመጣ ይገመታል።

አሳሳም ከመሀላ ጋር የተያያዘም ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ወንዶች «ከዚ ሐት እምላክ» አፈር ቀምሰው ሲምሉ ሴቶች ደግሞ መሬት በመሳም ሐቀኛነታቸውን ያስመሰክራሉ። በዕምነት ሰዎች ዘንድ የሚያምኑበትን ነገር መሳም «ሊጋን ከደመ» ሰግናናት የሚፈፀም አምልኮታዊ ጉዳይ ተደርጉም ይወሰዳል። መሳሳም የሐት መግለጫ ብቻ ሳይሆን ገምድናን በማጠናከር ረገድም ሰዘመናነ ሲያገለግል ቆይቷል።

መሳሳምን በሶስት ክፍሉ ማየት ይቻላል - የፍትሮ፣ የዕምነትና ሰነ ምግባራዊ መሳሳም በማለት። ሶስቱም የመሰያየታቸውን ያህል የመመሰሰልና የመወራረሀም ባህርይ አላቸው። በሌላ ጉኑ ደግሞ በፍትረጮች መካከል የሚፈፀመው መሳሳም ከሰምነት፣ ከልማድና ከስነ ምግባራዊው አሳሳም የተለየ ነው።

«ዙኮቱደስ አሳሳም አርከበራሳችሁ ሰላምታ ተሰላከሙ /ሮሚ ፲፩፤፲፮/ የሚለውን ቃል መሰረት በማድረግ ክርስቲያኖች ይሳሳማሉ። በአንዳንድ የሰላቭ ሀገሮች ደህ የስምነት ልማድ «ለሰ ክዚስቶስ መሳሳም» ተብሎ ይታወቃል።

ስነ ምግባራዊው መሳሳም ዙተሊያኑ ሀገሮች ትክሻ ለትክሻ ዘመሳሳም ሲገለጽ፣ በክንራችን ደግሞ ባርኔጣ በማንሳትና ከመዝ ዝት በማለት ይፈፀማል።

በአዘዙፓውያን ትውፊት /Folklore/ ዙትነ መሳሳም ሰርክስ ኦትዘንና ስሜትን ለመዋጋት እንደሚረዳ ይታመናል። ብዙዎች የአዘዙፓ ተረትና ምሳሌዎች ስዚህ ማስረጃ ይሰጣሉ። ሕማትን ለማዘዘል ሰነሳሳ ንስቻውን መሳሳም የተለመደ ነው።

መሳሳም ዘለሎች መካከል ወዳጅነትንና ሩትዛን ይገልፃል። በአንዳንድ ሀገሮች እንደተለምዶ ሆኖ ተለበት ካደረጉ ዚኃላ ለፎኛ የሰፍኖግሥቱን፣ ለፎኛጅቷም የለፎኛግን ደረት (ልብ አካባቢ) ዘመነም አለክዘዚያኛው አበረው እንኢኖሩ ታል ያገባሉ።

መሳሳም ከአንግዳ አቀባበልና ከመስተንግዶም ጋር የተያያዘ ነው። ኒኖርን የተባሉ ዜሐፊ ስለመሳሳም ሲገልጹ «ከመክለኛው ዘመን በአውሮፓ አንግዶች የእባወራውን ሚስት፣ ልጆችና ቤተሰቦች በመሳም የአንደምን አሳችሁ ሰላምታ ይሰጧቸዋል» ሲሉ ያወሳሉ። ጽርጀሽቱይን የተባሉት ዜሐፊ «ወደ መክለኛው አልፍኝ አንደወጣን የንሱ ልዩ አማካሪ ተተበሉንና እጃቸውን ሰጡን፣ ከእኛ ጋር ተሳስመውም ወደፊት መሩን» ሞግሰት በ፲፩ኛውና በ፲ኛው ክፍለ ዘመን በቤተ መንግስት ውስጥ የነበረውን የመሳሳም ልማድ ይገልጸሉ።

በስላቭ ሕዝቦችና በቮርሺኖች ዘንድ ከንፈር ለከንፈር የሚፈፀም መሳሳም እጅግ የመቀራረብንና ወዳጅነትን የሚገልጽ ነው። ይህ ዓይነቱ አሳሳም በአፈሰለሀ አቀባበል ጥምር በመተግበር ላይ ይገኛል። ጉዳዩ አንድ ታሪካዊ ሁኔታን ያስታውሰናል። ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ወደ ሞስኮ በሚመሰሰስበት ወቅት ብሬዥኒቭ አቀባበል የሚያደርጉላቸውና ከሰምምነት በኃላም ወዳጅነታቸውን የሚገልጸላቸው የመንግስቱን ከንፈር በመሞጫሞጭ አንደነበር ይታወቃል።

ትከሻን፣ እጅን ወይም አግርን መሳም የበላይነት ወይም የዝቅተኝነት መግለጫና የይትርታ መገለጫ ተምሰሌት ሆኖም ኑሯል። እጅን መሳምና አግር ላይ መውደቅ በጥንታዊውና በመካከለኛው ዘመን በአዉሮፓ ውስጥ ሰፊ ክፍራን የያዘ ቢሆንም ከዚዚ ዚኃላ ግን አግርን መሳሙ (ራሃር ላይ መውደቅ) ቀርቶ እጅን ዘመሳም ሳይ ብቻ ተመስርቷል። በአሁኑ ጊዜም ይህ የአጅ መሳም የዜብክርስቲያን አባቶችንና ሴቶችን በመሳም ተገድቧ ቀርቷል።

በተድሞው ዘመን በሊገሰግሰ ለዘናት የአጅ አሳሳም ትልቁን ክፍራ የያዘ ሲሆን አምባሳደሮች «በእጅ ላይ ይሁኑ» ከተባሉ በኃላ አለሲያዊ ንግግሮቻቸውን ያሰማሉ። የመሪዎችን አጅ መሳም ዓለም መንስት እንደ ትልት ክብር ሲቱይ የኖሮ ቢሆንም ክርስቲያን ያልሆኑ አምባሳደሮች ግን የአጅ ስሚያዙን ሲነፈጉ ነበር።

መሳሳም ሰምት አርነ በአርነ ሲሆኖች ብቻ ሳይሆን ሊሰጡም ይፈጠማል – የትም ያሁን ኑት በአሜኒተሮቸው የሚደበክስ መሣኑን ስመግለጽ ሲባል። ዘተጨማሪም ቱርማ ለተፈጸመ ስዘኑት የይትርታ ማሠሪያ ዘሌም ሆኖ ያገለግላል። ከዘሀራችን መግና ልማድ መሰያኑት ሕንደ ማኅ ታሳሽ ዘንድም ተያደርጉ ስለሚታይ እንደነደ መሳሳም

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰቅሶ ጋር ይታጀባል።

በቤተሰብና ቅርበት ባላቸው ሰዎች መካከል ስንብት ሲፈጽም በአብዛኛው ታናሽ ወደ ታላቁ ዘንድ ይሄድና «አስቀይሜህ እንደሆን ይቅር በለኝ» በማለት ተንበርክኮ ይማፀነዋል። ከዚህ በኋላ ሁለቱም ተሳስመው ይለያያሉ።

ስንብቱ ከሟች ጋር ከሆነ አስከሬን የሚሳምበት ሁኔታም አለ። ፒፒትሪያ «ሩሲኖች ሟችን ሙዮነት ባለው ስርዓት ይሰናበታሉ። የሟች ቤተሰቦች የሆኑት ወንድሞች፣ አህቶች፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ጓደኞችና ዘመንተኞች በየተራ አስከሬኑን እየሳሙ ይሰናበቱትና ወደ ዘለዓለማዊው መንገድ ይመሩታል» ይላል።


በጥንታዊው ዘመን ደግሞ የተቀደሰ ዕቃ የሆነውን ሁሉ መሳም የተዘወተረ ነበር። ግሪኮችና ሮማውያን የጣኦት አማልክቶቻቸውን ምስል እግር፣ እጅ፣ ጉልበትና አፍ ይስማሉ። ወደምስሉ መድረስ ባይቻላቸው እንኳ ከርቀት (የአየር ላይ ስሚያ) ይፈጽማሉ። ይህ ይዓነቱ መሳሳም ጥንታዊ ስለመሆኑ «ዐሐይ ሲበራ፣ ጨረቃም በክብር ስትሄድ አይቼ ልቤ በስውር ተታልሎ አፌም እጀን ስሞ እንደሆነ፣» (ኢዮብ 31፣26-27) በሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል።

የሰው ልጅ ሲሳሳም ከቅዱስ ነገር ጋር እንደተቀራረበ ወይም እንደተገናኘ ስለሚቆጥርም ለቅድስናው ኃይልንና ስልጣንን የሚሻ መንገድ አድርጉ ይመለከተዋል።

ከሚከበራዊ ልማድ አስነ ሥምልኮታዊ ስርዓት የሚደረገው መሳሳም የሰው ልጅ ስለመሳሳም የተለያየ ውስብስብና አስገራሚ ስሜት ያለው መሆኑን ያመለክተናል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአገራችን ሰዎች ሲገናኙ ጉንጭ ለጉንጭ ነበር የሚሳሳሙት፣ ቆየት ብሎ ደግሞ በተለይ ሴቶቹ የአፍ-ለአፍን መሳሳም አመጡ፤ በኩተማው ማለት ነው። የገጠሩማ የባህሉን ልዩነት ያህል ዛሬም የተለያየ ነው። የአፍ ለአፍም ቀረና ጉንጭና ጉንጭን ማነካካት ተጀመረ። ወደፊት ደግሞ ምን ዓይነት መሳሳም እንደሚመጣ አናውቅም። ተከታዩ ትውልድ በዛሬው መሳሳማችን ሳይደነቅ አይቀርም፣ ለማንኛውም መሳሳማችን ውድነታችንን ያጠንክርልን።

መጣጥፍ



ታሳቢቹ ዶሚጋዮች

ሽፈራው ዘለቀ

ወቅቱ ሁሉም እንደ አምነቱ የሚጠራው ሽብር የተጧጧፈበትና ፖለቲከኞችም ከቤት ወጥተው በሰላም መመለሳቸውን የሚጠራጠሩበት ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም በኢህአፓ የተቀናበረው ትእይንተ ሕዝብ ባብዛኛው የአዲስ አበባ ክፍል ተካሄደ። የውግዘት መፈክሮች በነበልባላዊ ስሜት ተገለጹ፤ ቤት ውስጥ የተመረቱ የጠርሙስ ፈንጂዎች ድምፅ አስተጋባ፤ የአፀፋውም መልስ ተንጣጣ።

ከአንድ ወር በላይ አልጋ ላይ የዋለ የአከስቴን ልጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳስታምም ያሰ እንቅልፍ በማምሸቱ ጋደም ብያለሁ። ብዙም ሳይቆይ የመኖሪያ ግቢያችን የውጪ በር በኃይል ተንኳኳ። ከአናላ እንትልፈ የቀነቀሰኝ የቶፍትዙ በር ድብደባ ከወትሮው ለየት ያሰ በመሆኑ ደንግጬ ለከፍት ስነሳ ቀድማኝ የነቃችው እናቴ ሃስማኝ መዝሊያውን ራሷ ከፈተችላቸው።

ቡድኑን የሚመሩት የተበሊው ሊቀመንበር ነበሩ። እንደገቡ በሀመሞተኛው ያነሰቱ ልጅና በኔ ላይ መሳሪያቸውን ደግነው ተስተንን ልብሳችንን እንድንለብስ አዘዙን። ሁኔታቸው ስላሳማረኝ የልጅን መታመም ገለፅኩላቸው። ምንም ሳይጎት ጋዘኔታ አለተሰማቸውም። ዊርሱት እውጪ ይጠባበት የገበረው ጋድል ገብቶ ግራዳ ቀኝ ተደትኖበነ እንድንወጣ ተገደድን። በሽተኛው የዘ ዓመት ወጣትም ሰለሰገሙና ሀሰፒታል እንደሚወስድ ሁሉ ተደገሮ ከውጪው በር ላይ አረፍ እንዲል ተደረጓ። ከአውሬያዊ ጥቂቱ እኛን ሲጠብቁ የተታሩት ከአጥሩ ጋር ወደተያያዘው የአጎታችን ግቢ ውስጥ በመግባት የሕሳናቱ ሞያተና የወሳሽቻቸው በእንባ የታጀበ መማሸን ቅንጣት ያህል ሳያራራቸው አራቱን ወንድማማቾች ጉተተው በማውጣት ከእኛ ጋር ቀላቀሉአቸው።

ከአራቱ ወንድማማቾች መካከል ሁለቱ የ12 እና የ13 ዓመት ልጆች ነበሩ። ቀጥለው ወደ ሌላኛው ግቢ ዘው አሉ። ሆኖም አልቀናቸውም። አመጣጣቸው ያላማረው ጉብል በመስኮት ዘሎ ተሰውሮ ነበር። በዚህ ልጅ ማምለጥ ከፋኛ የተበሳጨት አዳኞች ሌላ ግቢ ዘለው በመግባት ሁለት ወንድማማቾችን ከመኝታቸው ቀስቅሰው አያዳፉ በማምጣት ቁጥራችንን ወደ ስምንት ከፍ አደረጉት። ከዚያማ ሌሰች ስምንት ወጣቶችን በተመሳሳይ ሁኔታ ሰብስበው ናሮ በተጠናከረ አጀብ ወደመኖሪያችን ቀበሰ ጽህፈት ቤት ወስደው አነሩን።

ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ከሰድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የተሳከች የፖሊስ ኩምቢ ከህስዋኒን አጨናንቃ ጭናን እተጠቀሰው ጣቢያ አራገፈችን። የቀበሌው ሹማምንት የተቡተት የኢህአፓ መረፋዮችንና የፓርቲው አርማ ያለበትን ጨርቅ (ባነር) ይዘው ተከተሉን። ሆኖም የያዙት ጨርቅም ሆነ መረፋት ከኛ አጅ የተያዘ ስላልነበረ ከኛ ሊያቆራኙት መሞከራቸውን አጥብቀን ብንቃወምም ተቃውሞአችንን ከምንም ሳይቆጥሩት ፈትሸው አስር ቤት አገሩን። ሀመሞተኛው ተስፋዬ መሆንን ተደግፎ ሌሎቻችን በረድና ተሰልፈን ቁጥር አንድ ውስጥ ከሚገኙት አስረኞች ጋር ተቀላቀልን።

ከተበሊያችን ባንድ ቀን የታፈሰው መጣት ብዛትና የወንድማማቾቹም መበርከት ያስገረመው አስረኛ በሽተኛውን የአክስቱን ልጅ ሲንከባከብና አኛንም ሲያበረታታን ዋለ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ራት ከመብላታችን በፊት መኝታችንን በማዘጋጀት ላይ ሳለን ግን «ጠዋት ከተበሊ 23 የመጣችሁ ውጡ!» ተባለ።

«ሌታችንን ይዘን ነው ባዶ እጃችንን?»

«ብትፈልጉ ይሆናችሁ ባትፈልጉ ትታችሁ፣ ባስቸኳይ ውጡ!»

የሌሊት ልብስና ሳህኖቻችንን ለታቅመን እየተጣደፍን ስንወጣ ጣቢያው ግቢ ውስጥ የነበሩት የሰውነት ግዝፈታቸውና ቁመታቸው ከታጠቁት መሣሪያ ከምሽቱ ጨለማ ጋር እጅግ አስደንጋጭ ገፅታን ያላበሳቸው ወታደሮች በስደፍ እያጋጨ አሰለፉን። ከዚያም ጠዋት ከየቤታችን ከስበሰቡን የተበሊ አመራር አባላት ሶስቱ ስማችንን እየጠሩ ቆሞ ይጠብቀን የነበረው ሪዮ ላይ እያንገላቱ ጫኑን።

የሁላችንንም መሳፈር እንዳረጋጡም መኪናው መለል ላይ ተጉተን ብርድ ልብሶቻችንን እንድንሸፋፈን በአሸባሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ በማዘዝ እግሮቻቸውን ላያችን ላይ ጭነው ነፃ ቀጠልን። ሆኖም እኔና የእጮቴ ልጅ ደምሴ ብርሃኑ መኪናው መጠባበቂያ ጉማ ላይ የመቀመጥ አድል ገጥሞን ስለነበር የተሸፋፈንበትን ብርድልብስ ከጭላንጭል ባልበለጠ አይታ ገለጥ በማድረግ ወዴት እንደሚወስዱን ስንመለከት ወደ ቤተ-መንግሥት ይዘውን እንደገቡ ተረዳን። ለደቂቃዎች በጭንቀት የተጓዝንበት መኪና እንደቆመ አስወርደውን በአንድ ከፊት ሰፈቱ ዳገታማ መቀመጫ ካለበት ቦይ መሰል ጉድጓዳ ስፍራ በተራ ደረደሩን። ከእኛ ቀደም ብለው የመጡ ሌሎች ወጣቶች በግምት አስር ሜትር ርቀት ላይ በተመሰሳይ ሁኔታ ኩርምት ብለው ተቀምጠዋል። አሰፈሪ ፀጥታ በሰፈነበት በዚህ ጭለማ ውስጥ አልፎ አልፎ በሰደፍ ስንገጭና ከፊት ለፊታችን መሳሪያ የደገኑ ወታደሮችም ሲቀያየሩ ከሚሰማው ድምፅ በስተቀር የቃላት ልውውጥ ሳንሰማ አምሽተን ከምሽቱ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከየቤታችን ያፈኑን ሁለት የቀበሌያችን አባላት በላንድሮቨር ከች አሉ። ወዲያውኑ ፊታችንን ከኋላችን ወደሚገኘው ግንብ እንድናዞር በመሳሪያ ግተባበል የታገዘ ትእዛዝ ተሰጠን። ትእዛዙ ተግባራዊ እንዲሆንም በጥንድ በጥንድ በፖሊቲኒክ ሲባጎ እያቆራኙ ማሰራቸውን ተያያዙት። ወደመሀል ሲደርሱም ገነነ ነጋ የተባለውን የ12 ዓመት ልጅ አጥብተው ስላሰሩት እንዲያላሉለት ጠየቃቸው።

«ሆኖም ወረቀት ስትበትን ስምን አላመጠመህም?» በማለት በሰደፉ ያገጨት ጀመር። ይሽኒ ገነነ «ዱሮም ከፋሽሽቶች የምንጠበቀው ነው» በማለት መታደሩ ፊት ላይ ስሰተፋበት በእሰቃቂ ሁኔታ ተደበደበ። ያም ቢሆን ግን ከመነከላችን በእድማ ያነሰው ወጣት ድፍረት የሁላችንንም ልብ እሞቀው።

በዚህ መልክ ይካሄድ የነበረው ቁርኝት ቀጥሎ መሄዳችን ከተነሳንበት አስረኛች የመጨረሻው ስለነበርሁ ውጥር ጉዳይነት ከኔ ጋ የሚገዳኝ በመሆኑ ብቻዬን ያፈናኝ ታስራ። እኔ ዘለለም በቀለና መስፍን ጋይሌ በላንድ ሮቨር። የተተሩት ደግሞ ቀድሞ በመጣንበት ረዥ መኪና ተጭነን ከጂሳና ከፊት መትረየስ ባጠመዱ ጂፖች እንደ ታጅበን በስራት ኪሎው በር በዙሪል ወጥተን ወደፊት በር ስናመራ ትልቁን መኪና ብልሽት አጋጠመው። ፊቱን እዙሮ ወደመጣንበት እንዲመለስ ሲደረግም ወደ ቤተመንግሥት የሚመልሰን መስሎን ነበር። ነገር ግን እንደጠበቅነው ሳይሆን በቀጥታ ወደ ስድስት ኪሎ አመራ። ሆኖም የኩቲት 12 እደባባይን እንደሀረ ሊንቀሳቀስ ባለመቻሉ ቆመ።

በዚህን ጊዜ ያጀቡን የተበሉ አባላትና ወታደሮች ለስታችንን ከላንድሮቨሩ አውርደው ሪዮው ላይ ከወረወሩን በኋላ እንዲጠበቀን አንድ መትረየስ ያጠመደ ጂፕ ትተው ሄዱ። እንደተመለሱ ያመጧቸው ላንድሮቨሮች ውስጥ ከተቱን። ባዲስ ድልድል ቀድሞ አብረውኝ ከነበሩ ዘተፈጠረ ከነነ ነጋ ጋር አብሮት ተቆራኝቶ ከነበረው ሕመምተኛ የአስቴቱ ልጅ ከተስፋዬ መኮንን ጋር ተገናኘን። የተፈጠረቱ ነፍሳትን ያጨቁት ላንድሮቨሮች ከፊትና ከኋላ በባለ መትረየስ ጅፖች ታጅበው በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ገፈርሳ ጫካ ነጉዱ። እንደ ደረሱም በፈንጠዝያ እቸቸውን እያጠጡ የሚፈክሩ የአብዮት ጥበቃ አባላት ተቀበሏቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ አዐልይ ነበር። በመጨረሻ ግራና ቀኙ ድልድይ ብዙ ባለበት የገሀር ዛፍ ጫካ ውስጥ ስንገባ መኪኖች እንዲቆሙ ተደረገ። አቸቢያቻችን በፍጥነት በመውረድ ግማሾቹ በጥበቃ መልክ አካባቢውን ሲቆጣጠሩ የተቀሩት ደግሞ ከመጀመሪያው መኪና ላይ ተቆራኝተው የታሰሩትን ደምሴ ብርሃኑና በላይም በቀለን በማውረድ የሰበሱት ጋዜ እየተንዘላዘለ ወደ ጫካው መነጂቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ከፍተኛ የሩምታ ተኩስ ተሰማ። በዚህ ጊዜ ከኋላዬ ተቀምጦ የነበረው የአክስቴ ልጅ «የእኛ ነገር አበቃ» በማለት አንገቴ ላይ ተጠምጥሞ ሳመኝ።

ተኩሱ ቀጠለ። ብዙ የገደለ ይሸለማል የተባሉ ይመስል እየተሽቀዳደሙ ዘመቻውን ጥንድ ጥንዱን በማውጣት ከአስፋልቱ ጥቂት አልፍ እያደረጉ ይረሽኑታል። በመኳሰሉም የመሳከር ይሁን የሚተኩሱት ጠመንጃ የሙዚቃ ቃና አስደስቷቸው ገድለው-ም ሲመለሱ እውቶማቲኩን እያንጣጡት መምጣት ጀመሩ።

የጭፍጨፋውን ትእይንት ሰክታተል ከቆየሁ በኋላ የመጨረሻው ሟች ለመሆን ከመኪናው ወርጀ ከአስፋልቱ ቢታች ወደሚገኘው ቁልቁለታማ ስፍራ እንድሄድ ታዘዝኩ። ከተኩተሱኝ ሁለት የቀበሌአችን ገዳዮች አንዱ «ይሄ እንዳይሮጥብህ» ሲል ሌላው «የት አባቱ ይሮጣል» እንዳለ ወደ ኋላ ዞር ብዬ ለመናገር ስሞክር የአውቶማቲክ ተኩስ አሩምታ መረደብኝ። ወደቅሁ። ወድቄም ሳለሁ ጢዛ ላይ ያረፈው ጭንቅላቴ ስለቀዘቀዘኝ ደም የሚፈስ መስሎኝ የመጨረሻዋን የቁርጠኝነት መፈክር አሰምቼ ለመሞት ቆረጥሁ። ሆኖም ዝም እንድል ያደረገኝን ኃይል ባላውቀውም ሳልናገር ቀረሁ።

ገዳዮቹ «እዚያ ጋ የሚያንኮራፋውን ጨርሰው፤ ጭንቅላቱ ላይ በለው አንጂ! ያኛው እነ አልሞቀም ይንፈራገጣል ጨርሰው እንጂ ...» ሲባባሉ ቆይተው እኔ ጋ ሲደርሱ አንዱ «ይሄም ያጣጥራል ድገመው» ሲል የቀበሌዬ ነዋሪ የሆነውና አሁን በዋስ ተፈቶ የሚገኘው ገዳይ አንድ ጥይት ለጭንቅላቴ ተኮሰ። ነገር ግን አስፋልቱ ላይ ቆሞ ቁልቁል የተኮሳት ጥይት የኮኝ እግሬን የመካከለኛ ጣት ከጫፍዋ ላይ ቆርጣ ነበር የሄደችው። በመጨረሻም የንበረገዳዩ ሠራዊት በመጣበት አኳኋን ሲመለስ እኔ

የታሰርኩበትን ሲባጉ ፊትቼ ጸኬቴን በመቅደድ ከሚደማው ክንዴ በላይ በግራ እጁ እርዳታ ጥፍር አደርጌ ከአሠርኩ በኋላ የተነደለውን ጭኔንም እንዲሁ ከቁስሉ ጥቂት ከፍ ብዬ በማሰር ከሰውነቱ የሚወርደውን ደም በአብዛኛው ጣትቼ ራሳ ለመገንጠል ከመጡት ጅቦች ጋር ትግል ገጠምሁ።

ሊንጋጋ ሲል ግን የመኪና ድምፅ ስለሰማሁ ገዳዮቼ ራሳ ለማንሳት የመጡ መስሎኝ ወደቡራዩ የሚወስደውን መንገድ ይዤ ጫካ ለጫካ ጥቂት እንደሮጥሁ መኪናው አልፎ ስሳሄደ ወደ ዋናው መንገድ ወጣሁ። አሮጌ ጨርቆች የተሰጡብት በር የለለው ግዙ ይታያል። ዘው ብዬ ገብቼ በጨርቆቹ ደሜን ከጠራረግሁ በኋላ ቁስሌን የጠገንኩባቸውን ጨርቆች ቀይሬ ራሳምቼ ወደ ወደቁበት ሳመራ ከርስትና ለማስሳት ወደ ጊዮርጊስ ይሄዱ የነበሩ በርካታ ሰምች አዩኝ። በተለይ አንድ አዛውንት «ያማታው ጥይት እናንት ላይ ነው ያሉተው?» የሚለውን ጥያቄ ስለደጋገሙብኝ ዱርዬዎች ማታ በጨለቤ ክንዴ ላይ እንደወጉኝ በመግለፅ ለማሳመን ሙከራ በማድረግ ላይ ሳለሁ የተጨፈጨፉ ወጣቶች የወደቁበት ስፍራ ስለደረስን ሁሉም ተደናግጠው ይጯጯሁ ገቡ። ይኸኔ አብረውን ከነበሩት አንዲ አሮጊት «በአውቶብስ ሂድ» ብለው እጅ ላይ ሁለት ብር መርውረውልኝ ጫካውን አቋርጠው ተሰወሩ። ቆም እንዳልሁ አስፋልቱ ዳር ከሙታኑ የወደቀ አዲስ ጋቢ በማግኘቴ ጋቢውን ከላይ አስክታች ተከናንቤ መንገዱን ተከትዬ ስጓዝ እንድ ነጭ ሳትሰን ስትመጣ ስላየሁ ምልክት በመስጠት እንዲያቆሙልኝ ጠየቅሁ። በውስጧም የነበሩት ሁለት ወጣቶች የምሄድበትን ጠይቀው አሳፈሩኝ። ቀጣዩ ጭንቀቴ ደግሞ ከጥቂት ጉዞ በኋላ የሚያጋጥመንን ኬላ ማለፉ ነበር። ሆኖም ፍጹም ባልጠበቅሁት መንገድ ፍተሻው ተከናወነ። መስፍነ ሀረር መንገድ አደረሱኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጓደኞቼ ቤት እንደደረስኩ እጅግ ተደናግጠው ከአጣጠቡኝ በኋላ ልብስ ቀይረውልኝ ሰወዳጅ ዘመድ ስልክ በመደወል ላይ ሳሉ ቤተክርስቲያን ሊሰለሙ ሂደዋል የተባሉት የጓደኞቼ አባት በድንጋጤ እንደተዋጡ በራን በርግደው ገቡ። ምነ እንደተፈጠረ ከኛ ከተረዱ በኋላም እሳቸው ያጋጠማቸውን በዝረሜታ ገለጡልን። ለካንስ ጉራቤታቸው የሆኑ አብዮት ጠባቂ የለበስኩትን ጋቢ ዘልቆ ይታይ የነበረውን ደም አይቶ ናሮ ከቤተክርስቲያን ሲመለሱ አጠቃላይ ሁኔታውን በአንክሮ ሲከታተል አግኝተውታል። ለምን በር ላይ እንደቆመ ሲጠይቁትም «ከቤትም እንድ ጋቢው በደም የተነከረ ሰው ሲገባ ስላየሁ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጌ ነው» አሳቸው። ይኼኔ ብልሁ አሳውንት ቀድመው ያወቁት ነገር ባይኖርም «እኔም ለዚሁ ጉዳይ ድረስ ተብዬ የመጣሁት በጠዋት ዘመድ ቤት ሄጀ ሳሰ ስለነ ደውለው አሁን ያየኸውን ዘመዴን አኔን ለመጠየቅ መጥቶ ቤቱ ስለጠፋበት ሲዘዋወር ማጅራት መቺዎች በጩቤ ወግተው ጥለውት ሲነጋ ቤቱን አስታውሶ መጥቷል» ብለውኝ ነው በማሰት ጥርጣሬውን ይገፉሳታል። ሆኖም አብሮት ጠባቂው ሀሳቡን ሳይቀይር ወይም ሰው ሳያሻክር በፍጥነት ከአካባቢው መሰወር አስፈላጊ መሆኑን ስላመነበት በጓደኞቼ ቤተሰቦች መኪና ከግቢ በመውጣት ላይ እንዳለን ቆሞ ስላገኘነው ነገዱ ላይ በወሮበላ መወጋቱን ገልጡለት በመጀመሪያ ያገኘተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄጀ ካመለከትኩ በኋላ ወደ ሐኪም ቤት እንደምሄድ አስረዳሁት።

«አንኳን አተረፈህ» ብሎኝ ተሰያየን። ከዚያም ሰመሰወር አመቺ የሆነ ሥፍራ በመቀመጥ ወደቤተሰቦቼ መልእክተኛ ሳክሁ። በዚህን ጊዜም የአካባቢው ሕዝብ የወጣቶቹን ማሰት በመረዳቱ ከፍተኛ ዋይታና ለቅሶ ሆነ። በቀበሌው ክልል ትርምስ ስስተፈጠረም ሬሳዎቹን ከወደቁበት ሥፍራ በማንሳት ምኒልክ ሆስፒታል ሬሳው ቤት ሜዳ ላይ

ደደርጉዋቸው። እንድ ላይ ከወጣነው አራት የአጎቴ ልጆችና እንድ ያክስቴ ልጅ መካከል አንደኛው ብቻ በቤተሰብ ሰመቅበር ሲታደል ከአራቱ ወንድማማቾች ግን ሰሱቱ ሳጥን ውስጥ ገብተው የቀረው በመፈለግ ላይ ሳለ የደርግ ወታደሮች መትረየስ ጠምደው በመምጣት ሬሳውን ነጥቀው ሄዱ። «ለጥይት» የተከፈለውም ገንዘብ መና ቀረ።

ይህ በዘህ አንዳለ ቤተሰብ በሚያደርገው የለቅሶ ስነስርዓት ላይ የእኔ ስም ብዙም ባለመነሳቱ ጥብቅ ክትትል እየተደረገብኝ መሆኑን ተረዳሁ። ሁኔታውን መቀየር ስለነበረብኝ «ሂዳችሁ ለአናቴ ቆስሎ ድና ነበር። ነገር ግን ከሐኪም ቤት አውጥተው ገደሱት ብላችሁ ንገሯት» ብዬ ለምች ላክሁ። ተሳካልኝ። ክትትሉ ረገብ ሲል በቆሰልኩ በላምንቱ አዲስ አበባን ለቅቄ ምንሻር መደተባለው ሥፍራ ሄድሁ።

እዚያም ለስስት ሳምንታት ያህል በሰላም እንደተቀመጥሁ ዘጥርጣሬ አይን መታየቴ ስላልቀረልኝ ራት ወዳለና ገጠር ዘመዴ ሂድኩ። ሳምንት እንደተቀመጥኩ የደርግ ወታደሮች «ሽፍቶችን አንደመስሳሰን» ብለው አካባቢውን አጥለቀለቁት። እንድ ምርጫ ብቻ ነበረኝ – በአካባቢው ወደሚገኘው በረሀ መግባት። እዚያ ስደርስ የገጠመኝ ጉዳይ ግን የሕሊና እረፍት የሚነሳ ነበር። በረ ፈውዳል አደም የነበረኝ ሰውዬ ከፊውዳሎች ጋር ሰመሠላቀል ተገደድሁ – ለሁለት ወራት።

ሆኖም ቤተሰቦቼ ስኔ ምህረት ለማስጠትና ተመልሼም በሰላም እንድኖር ጥረት ያደርጉ ስለነበር ይኸው ጉዳዩ የተሳካሳቸው መሆኑን ስለገለጹልኝ ተሹለክልኬ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። የቆሰልሁ ጊዜ ያረፍኩበት ቦታ በመሆን ሁኔታውን በስሞና በመከታተል ላይ ሳለሁ መከላከያ ሚኒስቴር እንደተፈለግሁ ስለተነገረኝ የሚመጣውን ሁሉ ሳቀበል ቆርጬ ሄድኩ።

እዚያም ድርጊቱን የፈፀሙት አንዳንድ የቀበሌ አመራር

t.me/OLDBOOKSPDF

አካላት እንጂ መንግሥት ይህን ድርጊት የማያውቀው መሆኑንና ሁኔታውም መንግሥትና ሕዝብን የሚለያይ ተግባር ስለሆነ ፈፃሚዎቹ በቁጥጥር ስር እንደሚውሉና እኔም ሕዝቡ ፊት ቀርቤ ንግግር ማድረግ እንደሚገባኝ ተገለፀልኝ። መናገር የሚገባኝም ተዕፎ እንደሚሰጠኝና ከዚያ ውጪ ግን አንድም ቃል መጪመር ሌላ ችግር እንደሚያስከትልብኝ ተብራርቶልኝ አንድ ጥበት ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ– «በግድያው ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ ሁለት የፖሊስ አባላትን መንግሥት ሰሥራ ለሰሚፈልጋቸው በማናቸውም አይነት መንገድ ስማቸውን ብታነሳ ርምጃው ቀደም ብሎ ከየቸው የከፋ ይሆናል» የሚል። ነገሩን መንግሥት እያውቀውም እያሉ የእከሌ እከሌን ስም አታንሳ ሲሉ ከመታዘብ በስተቀር ማድረግ የምችለው ባለመኖሩ የተነገረኝን ሁሉ አሜንሙ የስብሰባውን ውጤት ስጠባበቅ በመጀመሪያው የሕዝብ ስብሰባ የተወሰኑ የቀበሌው አባላትና ተባባሪዎቻቸው በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ በሳምንቱ በተደረገው ስብሰባ ላይ በይፋ እንድገኝና የተዘጋጀውንም ጽሁፍ እንዳነብ ስለተነገረኝ የታዘብኩትን ሁሉ በመፈፀም ለጊዜው ሳልሸሽግ መኖር ጀመርኩ። ይህም ግን ብዙም ሳይቆይ ሌላ መልክ እየያዘ መጣ።

የልጆቹ ገዳዮች ነፃ መውጣት የነበረው ቤተሰብ ሠልፍ ወጥቶ ፍትህ ጠየቀ። በታሳሳቅ ድንጋይ ራሶች የተሞላው ደርግ ግን ስብስቦ አስር ቤት አጉራቸው። እኔም መሳሪያ እንደሆኖችው ሞከረው ፈቃደኛ ባለመሆኔ ታሰርኩ። በወቅቱ የቀይ ሽብር አስር ቤቶች ይደርስ የነበረውንም የመከራ ፅዋ ሁሉም ተጉነጨሁ። አዚያ ከራርሜም በአስረኞች የተመሰረተው የክፍተኛ 15 የኪነት ቡድን ተሳታፊ በመሆን ሕይወቴን አትርፌ ለመፈታት በቃሁ።

የአስፈሪዬ ኮሎኔል በሲዊትዙ

ሞሼ አሎን

ትርጉም – አሸቱ ተፈራ

የፈጠራ ስሙ ያዕቆብ የተባለ አስራኤላዊ የጦር መሳሪያ ደላላ ታህሳስ፣ 1990 ከአስራኤል ተነስቶ ኤርትራ ይደርሳል። ወደ ኤርትራ የሄደውም አርሱ የሚሰራበት «ኖአስራኤል መከላከያ ኮንስትራክሽን ኩባንያ» ለኤርትራ አየሌ የጦር መሳሪያዎች ሰመሸጥ ተዋውሎ ስለነበር የግርውን ሁኔታ ከገቡ ለማድረስ ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አንድ ችግር ተፈጠረ። የኤርትራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ከኩባንያው ጋር የተፈራረሙትን ውል ሰማፍረስ ፈለጉ። ስለዚህም የጦር መሳሪያ አቅራቢው ኩባንያ ውሊሶን ደላር የሚቆጠርና በቀበድ ስም የወሰደው ገዝዘብ ካልተመለሰላቸው በስተቀር የኩባንያው ወኪል የሆነውን ያዕቆብን ሰማገት ወሰኑ። ስለሆነም ያዕቆብ ያለፈቃዱ ለ81 ቀናት አስመራ ከተማ ውስጥ ታገተ። በኋላ ግን ድፍረት በተመላበት አፐሬሽን በአንድ የእስራኤል ጀልባ ነፃ ወጣ። ጀልባይቱም ያዕቆብን ይዛ በሰሞ በሱዳን ወደብ አረፈች። ከታጋቹ ያዕቆብ ጋር የተደረገው ልዩ ቃለ መጠይቅ አነሆ።

ጥር 10፣1990 ጠረተኛው ሴተና ኮሎኔል ያዕቆብ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደገባ ግልፅ ሆነለት። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሁሉም ነገር ሰላምና መስፀር የያዘ መስሎት ነበር። ከአንድ የኤርትራ መንግስት ባለስልጣን ጋር ሲነጋገር ግን ያልጠበቀው ጸብይና አጋጠመው። ያዕቆብ ከባለስልጣኑ ጋር በጥቂት ይዘናኝ ሰነበር ሰወያውን በሚገባ ያውቃቸዋል። ስራውን የፈፀመ ስሰሆነ በመጀመሪያው አውሮፕላን ወደ ሀገሩ ሰመመለስ እንደተዘጋጀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለባለሥልጣኑ ይገልፅላቸዋል። ይህ ጉንሽ ንግግር ወደ ከፍ ያለ ጠብ ተለወጠ። የኢርትራው ባለስልጣን ፈገግ ብለው አስራአለቃውን የጦር መሳሪያ ይላቸ ያልጠቀቡን መርዶ አረዱት። የኢርትራው ባለስልጣን «ኮሎኔል ያዕቡ፣ እዚያ ትቆያለህ፣ ሰቀቢው የከፈልነው ገንዘብ ካልተመለሰልን በቀር ከኢርትራ መውጣት አትችልም» አሉት። እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ያዕቡ ታጋች መሆኑን በይፋ የነገረው ለው አልነበረም። አሁን የኢርትራው ባለስልጣን ያዕቡ ታጋች መሆኑን በይፋ ነገሩት።

ያዕቡብ ለ81 ቀናት በአስመራ ውስጥ የሆቴል እስረኛ ሆኑ። ጦርነት ይነሳል የሚል ስጋት በመፈጠሩ አያሌ የውጭ ሀገር ዜጐች አስመራን እየለቀቁ በመውጣት ላይ ነበሩ። ያዕቡብ ግን የውሽት የሆቴል ኦፐገሰና አውነተኛ እስረኛ ሆነ። ይህንን ጉዳይ የሰሙት የያዕቡብ አስራአላውያን አሰሪዎች ጭንቅላታቸው ተቧጠጠ። ያዕቡብን ከአስመራ እንዴት በሰላም ማስወጣት እንደሚችሉ ተመካከሩ። በሁለት ነገሮች ላይ መከሩ። ምክሩም «የኢርትራውያንን ፕጸብ ያላግባብ ሳንዝርፍ ለያዕቡብ ማስለቀያም (Ransom) በሚሉኖች የሚቆጠር ዶላር ለኢርትራ ሳንከፍል ስራተኞችንን አንዴት ማስላት እንችላለን» የሚል ነበር። በመከሩ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ጦርነት በመፈንጥቱ ሁኔታውን በማም አደገኛ አደረገው። ስለዚህም ድፍረት የተሞላበት የነፍስ አድን ኦፐሬሽን ማቀድ አስፈላጊ ሆነ። የማቀዱ ስራ አለቀና በቅርብ ጓደኞቹ ብርታት ያዕቡብ ከአገታው ነፃ ወጣ። ያዕቡብን ከአገታ ነፃ ያወጡት ጓደኞቹ የአስራአል ተጠባባቂ ጦር መኮንኖች ናቸው። ከፍተኛ የጦር ልምድ ያላቸው የአስራ አል መኮንኖች ታጋቹን በሰላም ከአስመራ አስወጥተው በቅጽበ ባህር አድርሰው በደህና አስራአል መደብ አደረሱት። ይህ ኦፐሬሽን የተካሄደው በፐሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ሰፍኮጌ ጦር ነው።

ስለዚህ እፐሬሽን ሊሰካ ያደ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበ። የኢርትራ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአስራአል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፃፈው ደብዳቤም ይፋ ሲወጣ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። የኢርትራው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ደብዳቤ የከፋል ይቅርታ ጠያቂነት ባህርይ ይታይበታል። ደብዳቤው እንዲህ ይነበባል። «ውድ ክቡራን፣ በአኛና በአስራአል መከላከያ ኮማንትራክሽን ኩባንያ መካከል ሰሞኑን የተፈጠረው ውዥንብር አስመናሩን ለመግለፅ እንፈልጋለን። ከዚህ ቀደም የነበሩት አለመግባባቶች በፍፁም ወዳጅነት የተፈቱ ስለሆነ በአሁኑ ወቅት ከኮባንያው ጋር ያለን ግንኙነት መልካምና የሰመረ ነው። ከዚህ በታች በዝርዝር እንደምናየው ድርጊቱ የሚያመለክተው የሰመረ መፍትሂ መገኘቱን አይደለም። ለበስኩ ገበርኩ ቅጥፈት ብሎ ማለፉ ነው የሚተባው።

የታሪኩ አጀማመር ያሚያለየው ተራ የጦር መሳሪያ ድለላ ሂደትን ነው። የአስራአል ኩባንያዎች ከአፍሪካ ሀገሮች ጋር የሚያደርጉት የተለመደ የጦር መሳሪያ ግዢ ውል ነው። ታኅሳስ፣ 1990 ላይ የአስራአል የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ከኢርትራ መንግስት ጋር የጦር መሳሪያ ግዢ ውል ተፈራረመ። የቀይ ባህርን ደፀበ ከሶ ሚትር የሚቆጣጠሩት የኢርትራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በጦር መሳሪያ ግዢ ድርድር ውስጥ ቀጥተኛ ተዘፋይ ነበሩ። አቶ ኢሳያስ ድርድሩን ያካሄዱት ከአስራአሉ ኩባንያ መኪል ከጡረተኛው ሌተና ኮሎኔል ጋርቢ ፕሬዝ ጋር ነበር። ፕሬዝ ኩባንያውን ያቋቋመው ከ12 ዓመታት በፊት ነው። ከዚያን ወቅት ጀምሮ ፕሬዝ ለአያሌ የአፍሪካ ሀገሮች የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች በገፍ አቅርቧል። ከኢርትራ ጋር ያደረገው የጦር መሳሪያ ግዢ ግን ለፕሬዝ የመጀመሪያው ነው። በወቅቱ ኢርትራ የጦር መሳሪያዎች በአስቸኳይ ትፈለግ ነበር። ኤርትራ ጉረቤቷ በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ለመዝመት ትዘጋጅ ስለነበር የጦር መሳሪያ መግዛት ፈልጋለች። ኢርትራ አትዮጵያን እንደተቀናቃኝ ሀገር አድርጋ ነው የምትመለከታት። ከወቅቱ በአነባበሉ የወርንት ድባብ ሰፍኖ ነበር። የአስራአሉ ኩባንያ የጦር መሳሪያዎቹን ለኢርትራ የሚያቀርበው ከምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች ገዝቶ ነው። በዚያም ኩባንያው በብዙ ሚልዮኖች የሚቆጠር ዶላር ያትርፋል። ከዚህም ሰለ ከገዢና ከሻጭም የሰለውን የድለላ ዋጋ ይቀበላል። እነዚህ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኑ ኢርትራ በተበደ ሰም ሰኩባንያው ብዙ ሚልዮን ዶላር አቀድማ ከፍላለች። ቀሪው ገንዘብ የሚከፈለው ደግሞ ኢርትራ የጦር መሳሪያዎቹን በመሉ ስትረከብ ነበር።

በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገውን ውል ከገዙ ለማድለስ

t.me/OLDBOOKSPDF

የእስራኤል የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ወኪል የሆነው ኮሎኔል ያዕቆብ ህዳር 22፣ 1990 በአውሮፕላን አስመራ ገቡ። የቦር መሳሪያዎችን ለማስረከብም ተዘጋጅ። ያዕቆብ በእስራኤል መከላከያ ኃይል ውስጥ የንቡረ የአየር ወለድ መኮንን ሲሆን ከ12 ዓመታት በፊት ከጦር ሃይሉ ተባርሯል። በአሁኑ ወቅት የያዕቆብ አድሚ ፊ ደርሷል። ያዕቆብ ከመከላከያ ሰራዊቱ ከተባረረ በኋላ በአሰቃ የእስራኤል ኩባንያዎች ውስጥ አዋተቀጠረ ወታደራዊና የሲቪል ፕሮጀክቶችን በማካሄድ ረገድ የተዋጣለት ስፔሻሊስትነት ውጭ ፕሮጀክቶቹን ያካሂድ የነበረውም በአፍሪካ ውስጥ ነው። ያዕቆ ኢያሉ ቋንቋዎችን ይናገራል። ስራውን የሚያከናውነውም በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው፤ ልታይ - ልታይ አይልም። የጦር መሳሪያዎችን ግዢ ከሚያቀናብርለቸው አፍሪዝውያን መሪዎች ጋርም በቅርብ ተገናኝቶ አያውቅም።

ያዕቆብ «ሳን ቫይን» አሚባል ሆቴል ጡስኖ ነው ያደረው። ሆቴሉ የሚገኘው በአስመራ ስሞብርት ላይ ነው። ሆቴሉ ለአውሮላን ማረፊያውና፣ ለፕሬዚዳንቱ ቤተመንግስትና ለፅፅህሰ ሚኒስቴር በጣም ቅርብ ነው። ያዕቆብ ሆቴሉ ክፍል ከገባ በኋላ አብዛኛ ጊዜያት ለመቆየት በማሰብ የግል ሰዓቶችን በአገባቡ ዝመገ፣ በመጽሔትና ጋዜጣ አሪያ። የሰተላይት ቴለቪዥን ኮምፕዩተሩን በሚገባ ለአገልግሎት አዘጋጅ። አንዘሀን ሁለት መሳሪያዎች በሚገባ ማዘጋጀቱ ኋላ ላይ ያዕቆብን ጠቅሞታል። የጦር መሳሪያ ግዢ ሂደቱቹ ቀስ በቀስ መልክ ያዙ። ያዕቆብ በሁለት ሳምንት ውስጥ የአስመራ ከተማን ጎዳና ጉድጓዳ አየር አውቀ። አስመራ ዱጋ ላይ የተመሰረተች ከተማ ነች። በተራራ የተከበበች ናት። የአስመራ ከፍታ ከባህር ወለል በላይ 2400 ሚትር ነው። የአከሲጂን አየሩት ለልት ለመተንፈስ አስቸጋሪ ነው። ወበለሳ በዙል ግን መልከም ንጋርም ያጋጥማል። የኢጣልያኖች አደባባ ምንብ ሞልቷል፤ ሞጋሙም ርካሽ ነው፤ ምግቡም መልከም ነው። አጣልያኖች አረትራን በልኖ ማቆየት ያስተሳድሩ በለንበር፣ የሀገኩቹ ቅርያችና ሴራችም አያል ነጮች አስከፋሬ ድረስ የቅኖ ግዝውን ሀገር የአኗኗር ዘይቤ ያዝቦርቃሉም ያሉት ኮሎኔል ያዕቆብ ስለ አስመራ ከተማ ሲናገሩ።

ታህሳስ 5፣ 1990 ሁለት የእስራኤል የመከላከያ ኮንስትራክሽን

ኩባንያ ሰራተኞች አስመራ ገቡ፤ ያዕቆብም አብሳበል አደረገላቸው፤ አመጣጣቸውም የኤርትራ መከላከያ ሚኒስቴር የተገዙትን የጦር መሳሪያዎች ለመረከብ ነበር። መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው። በአንድ ሰምንት ቆይታ በኋላ ሁለቱ ከእስራኤል የመጡት የከባንያው ሰራተኞች ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ስለወሰኑ ያዕቆብን ተሰናበቱት። ነገር ግን ወዲያው ያልተጠበቀ ሁኔታ ተከሰተ። የኤርትራ ባለስልጣኖች ሁለቱን እስራኤሊውያን ከአውሮፕላን ወሰዋ ጦተው አመሯቸ፤ ጋዜጋርጉትም ተሚቸው። የወጥታ ሽሞቹ አስራኤሊውያኑን ለምን እንዲያዙ አንዲያደርጉ ከበሳይ አካል የተጠዙ መሆኑን ለእስራኤሎቹ ያመለከቱ ሲሆን የመሳሪያው የመጫጠቂያ ደጠል መሆኑ ነው። ከየቂት ጭቅጭቅ በኋላ ሁለቱ እስራኤሊውያን ከእገታ ተለቀቁ። ሁለቱ ለያት የተሰጠቱ ግን ያዕቆብን በመያዣነት እሲህሎ ነው። ያዕቆብ በመያዣነት ታግቶ የሚያየውም በኤርትራ መንግስትና በእስራኤል ኩባንያ መካከል ደተከሰተው አለመግባባት አልባት እሰኪያገኝ ድረስ ነው።

ነገሩን ያወሳሰበት የኤርትራው ፕሬዚደንት ኢሳያስ አፈወርቂ ናቸው። ከቶ ኢሳያስ ከእስራኤል መከላከያ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ጋር የተሞያዩትን ጉድጓን በመሰት በቀዮታ ከጦር መሳሪያ አምራቾ ሀገር ፋብሪካ ጋር ግንኙነት ይመሰርታሉ። የሚፈልጉትን የጦር መሳሪያዎችም በቀዮታ መጀ ከራቅ ያስገባሉ። በዚህም ኢሮ ኢሳያስ ለእስራኤል ከኩባንያ የከፈልኩት የተዘጅ ገንዘብ ይመለስልኛል የሚል እተ-ካሀር አስነሱ። ይህ ለእስራኤሉ ኩባንያ ትልቅ ፊተሥጋት ነው የሆነበት። ምክንያቱም ከኩባንያው አስተዳደር ሠንገዝት ጋር የተፈራረመውን ኮንትራት በመጣሳቸው የጦር መሳሪያዎቹን ለገዝው ግዙፍ አዞግችቷል። በዚህም ከኩባንያው አማዙኝ ወሰነ ጉበኛል። ሌላው ቢቀርና ከንትራቱ ከፈረሰ ኦኋላ ከኩባንያው የተሠሩን ገንዘብ ማስቀረት አስበት። ከቶ ኢሳያስ ግን ለዚህ ጉዳይ ቅብ ስልክቸውም። አቶ ኢሳያስ የተበደር ገንዘብ እሰኑት ከልተመለሰልኝ ምቂ አሰኝሰዙ አሉ። ስለሆነ ቀርፈውም ገንዘቡ በሲሻዊሂ ከልተመለሰ ዘገባ ሄሰብ ብሰድ እወደታለሁ በማለት ኗኑ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉልበት ማሳያነት ተተየረ፤ እድግ አደገኛ አየሆነም ሄደ። ከዚህ ውቅት ግን ስለ ያዕቡብ መታገት ለአሰራኤሉ የጦር መሪያ አቅራቢ ኩባንያ በይፋ የተገለጠለት ነገር አልነበረም። ነገር ግን ለኩባንያው ባለቤት ፒሬገና ለሼረኒ ኮሄን የያዕቡብ መታገት ግልፅ ሆኖላቸው ነበር። ያቀበድን ገዝዘብ ለማከመለስ የተደረገ ጫና መሆኑም ንብቷቸዋል። ቢሆንም የአሰራኤል ኩባንያ የተጠቀሰ ገዝዘብ ለአርትራ መንግስት ሰመመለስ ፈቃደኛ አልነበረም።

ስለ ሁኔታው አንድ የኩባንያው ከፍተኛ ባለስልጣን ሲናገሩ «ችግሩ በኩባንያው ላይ የደረሰው ከፍተኛ ያገዝዘብ ኪሳራ ብቻ አይደለም። የሚያናድደውና የሚያበግነው የማጭበርበር ተሻር መደፀሙ ነው። ስለዚህም በኢሳያስ መንግስት ላይ የጠለፀው አርምጃና የሚሰጠው ምላሽ ለወደፊቱ ከለሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ለሚደረጉ የኮንትራት ውሎች ወሰንነት አለው። ኩባንያቱ ለአቶ ኢሳያስ አይነት ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ነጮበይዱ እንደ ሽዘ መፈረክሰኛቸው አይቀሬ ነው» ብለዋል። የኩባንያው ስራ አስኪያጅ ስለጉዳዩ ዝርዝር መግለጫ መስጠት የሚቻላቸው ቢሆንም የደንሸቸውን ምስጢር መጠበቅ ስለሰባቸው ዝርዝር ሁኔታወን ስማብራራት ፈቃደኛ አልሆኑም። የአርራኤሉ ኩባንያ ያዕቡብ በሳተላይት ቴለፎን በቀቱ አያገኘ ስለሁኔታው ማብራሪያ ይሰጠው ነበር። በመጪረሻም ጥር 10፣1990 ያዕቡብ የኢሳያስ መንግስት ታጋች መሆኑን ኩባንያው በይፉ አረጋገጠ።

የታጋቹ የያዕቡብ ስሜት

«ከፍተኛ ጋዘን ተሰማኝ። የውርደትና የአቅመቢስነት ስሜት ተሰማኝ። የመነዋወር ነፃነትን እንደተነጠቅ ያለ አዘውቂ ነር የለም። ከዚቱ ከመጣው 50 ቀን ሆኖኛል። የኤርትራ መንግስት ታጋች መሆኔ በድንገት ሲነገረኝ ጋዘኑ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ። ያም ሆኖ የመነዋወርና የመናገር ነፃነቴን ለማስከበር የተቻለኝን ሁሉ አደረግሁ። ከኤርትራ ባለስልጣናት ጋር በምንገናኝበት ወቅት ቆጣ - ቁጣ ከማለት ለመቆጠብ ሙከራ አደረግሁ። የተረጋጋ መንፈስ ማሳየት ጠመርኩ። ውሳኔያቸውን በዚያ የተቀበልኩ መሰሙ እንዲታያቸው ለማድረግም ምክርኩ። ውሳኔያቸውን ላለመቀበል ሞገዳሪር ሁኔታውን ያባባሰዋል የሚል ፍርሐት

አደረብኝ። ሁኔታው ከተባባሰ ደግሞ ለከፉተኛ ችግር እገደማደርገኝ ተገነዘብኩ። እርፌ ግን ኤልተቀመጥኩም። ኤከመራ ለሚገኙት ለአሰራኤሉ እምባሳደር ስላለሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ በየጊዜው ማስታወቂን ቀጠልኩ። አስር ቤት ላለመግባቴ ማበረሻ ይሆን ዘንድ በየቀኑ ሚት ጧት በአራት ሰዓት ለአምባሳደሩ ስልክ ለደውልላቸው ተሰማማን። አሰራኤል ውስጥም የእኔን ጉዳይ የሚከታተል አክል አገደንበረም በሚገባ አውቅ ነበር። ለጉዳዩ መፍትሄ እንደሚያገኙለትም ሙሉ አምነት ነበረኝ። ከኩባንያውን የአርትራ መንግስት የጠየቀውን ገንዘብ ከፈሉና ነፃ አወጡኝ ብዙ አስበየነም። ይህንን ያደረግሁት ለኩባንያዬና ለዓደዋቼ ያለኝን ታማኝነት ሰመገለፅ ስል ነው። ከዚህም ሰለ አሰቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረና ለሀይወቱ አስጊ ሆኖ ከተገኘ ኩባንያው የተጠየቀውን ገንዘብ ከፍሎ ነፃ እንደሚያወጣኝ ሙሉ እምነት ነበረኝ። ይህ ታሳቅ ታሰፋና የመንፈስ ከራት ያሳደረብኝ ጉዳይ ነው። በኩባንያዬ በኩል ለደነገቱ ከፍተኛ ትኩረት አንደሚሰጠው እምናለሁ። በግለሰት ደረጃ ምልልስ ላደረገልኝ ጋዝጠኛ ስለሁኔታው አብራርቷል።

የጉጭን አሳሳቢነት፣ በመወዳደት አሰራኤል ውስጥ የጦር መሳሪያ አቅራቢው ኩባንያ ባለቤት የሆነው ፒሬገና ኮሄን ጓደኞቻቸውንና ኤክስፐርቶችን ለአቸቸይይ ስብሰባ ጠሩ።

ስብሰባው የተጠራው ያዕቡብን ነፃ ለማውጣት የሚያስችሉ አማራጮችን ለማፈላለግ ነው። በመጀመሪያ በአሰራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት ባለስልጣን ከአቶ አሰፎ ጋር በመነናኘት ለተጭር አልባት ያስገኙ ዘንድ አቡት ግለት አሰፈላጊ ሰለኝበር ኩባንያው ይህንኑ ገለፀ። ነገር ግን ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱ ፋይናክስ ሆነ። ጥረቱ በመከሸፉ ኩባንያው ያጅብን ነፃ ለማያወጣቸውን የሪሱን ምስጢራዊ አማራጭ አዘጋጀ። ስዘህም ያዕቡብ የአለመራን ከተማ በድንብ እንዲያጠናና የህዘብ እንቅስቃሴ የማይበገቸውን አዘዘኤዎች አስቦሮ እንዲያውት ተነገረው። ሲሳም ከሀገሪቱ ለመውጣት የሚያስችል ልል ከሳ ሪሞሩን እገሚሠግትር ታዘዘ። እንኳኑሰዉን ዋሺኖሬ በማያሳፍር ሚልኩ አንዲያደርግ ምክር ተሰጠው። የአሰራኤል የመከላከያ ሚኒስቴር ለኩባንያው ለሰጠው ስራውን አቁም ያዕቡብን ነፃ ከማውጣት ኩባንያ ለሰጠው ስራውን ስራውን አቁም ያዕቡብን ነፃ የሚያወጣበትን መንገድ ማፋጅ ጀመረ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የእንቅልፍ ጊዜያቸውን በመቀነስ አትዳቸውን ማቀነባበሩን ተያያዙት።

ያዕቆብና ብቸኝነት

«አስመራ ውስጥ ብቸኛ ነበርኩ። አስመራ ውስጥ ካሉ አብራኢያውያንም ራቅሁ። ከተማዋን ግን አንድ ባንድ ኮርኒት በአጭር ጊዜ ውስጥ 150 ኪሎ ሜትር ተንገዳዳሁ። ውስጥ የማላውቀው አውራ ጉዳናና የአገር መንገድ የለም። አስመራ ገብ በተጨማሪ መሣፍት አነብና ጅምናስቲክ አሰራ ነበር። በአብዛኛው ያነበብኩት የአንግሊገኛ መሣፍትን ሲሆን አንድ በላይ ኢንጅል የተሸፈና ገጠቀኝ አመጣሳሁ የተባሰ የአብራደስጥ ረኛም ልብወለድ አንብቤያለሁ» ይላል ያዕቆብ ብቸኝነትን እንዴት አንደተቋቋመ ሲያስረዳ።

በእስራኤል የሚገኘው የያዕቆብ ቤት ያለው በሽሮን አካባቢ ባለች ከተማ ውስጥ ነው። በአርሱ ቤትም ሆነ በአካባቢው ያዕቆብ አጠነነ ችግር ውስጥ ያለ መሆኑን ያውቀ አልነበረም። ከጣንያውም የያዕቆብ ባለቤትና ልጆቹ ያዕቆብ ስላለበት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲይስሙ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርገል። ይህም የተደረገው የያዕቆብ ቤተሰቦች ጭንቀት ውስጥ እንዲወገዙ በማሰብ ነው። የፔሬዝ ቡድን ያዕቆብን ነባ ለማውጣት አራት አማራጮችን አቀደ። የመጀመሪያው አማራጭ አስመራ ወስዶ፣ በመስራት ላይ ባለ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ በአውሮፕላን ማረፍ፣ ሁለተኛው አማራጭ ያዕቆብ መልኩን ቡሚክስና እንዲቀይር አድርጉ የሀሰት የንዛ ሰነድና ፓስፖርት ማዘጋጀት፣ ስለተሻለ አማራጭ የአርትራ አጉራባች በሆነ በአንዱ ሀገር ቮልኮ ወደ አርትራ መግባት አራተኛው አማራጭ በባህር በዙል ያዕቆብን ማስመለጥ አማራጮቹ በውል ከተጠኑ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሰስቱ አማራጮች ውድቅ ሆኑ። ይህም የሆነው ዓለም አቀፍ ሆነን ላለመሣሸን ሲባል ነው። ከዚህም ሴላ በኃይል ባለመጠቀምና ሽበር ላለመፍጠር አጠቃላይ በምንነት ተደርጉ ሰለነዘር የመጀመሪያዎቹ ሰስቱ አማራጮች ይወድቁ ዘንድ ግድ ሆነ። በመጨረሻ የተደረሰበት ውሳኔ አንዲት መርከብ ወደ ምሰሶ ወደብ መላክ ነዘር። መርከቢ የሞና ተለማማጅ ቱሪስቶችን የመሳነት አንድትመላለ

ለማድረግ ገቦንድት ተደረገ። መርከቢ ወደብ ላይ አንድትቆይ ተወሰነ። መርከቢ ወደብ ላይ አንዲለች ያዕቆብ ከአስመራ ሾልኮ መውቶ መርከቢ ላይ አንዲሳፈር ስምነት ላይ ተደረሰ። ከዚህ ገቦጅት ጉን ለጉን ስለ ተባሩ ገዝዘብ መመለስ ጉዳይ በከጣንያውና በአቶ ኢሰያስ አፈወርቂ መካከል ድርድሩ ተጥሎ ነዘር። ነገር ግን አንዳችም ስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም።

ከጣንያው በአቀደው መስረት ካፕቴን ሼምሶን ማሺያህ ከተባለ አሰራኤላዊ አንድ የቱሪስት ጀልባ ተከራየ። ጀልባዋ በኤይላት ጠሊሰጠ አካባቢ የንገድ ሰራ የምታካሄድ ናት። የቱሪስት መገሸሪያ በምትመስለው ጀልባ ላይ ዘመናዊ የግንኙነት መሳሪያዎች፣ የቅበብሹሽ መሳሪያዎች፣ የሳተላይት ቴሌፎኖች፣ በሮስማ የሚያሳይ ልዩ መሳሪያ፣ ምግብ፣ የህዝምና መሳሪያዎችና ሁለት ፈጣን ጀልባዎች ጉልድ ቱሪስት ጀልባ ላይ ተጫነ። ፈጣኖቹ ጀልባዎች ጋይሰኛ ተጨማሪ ሞተርም ተገዥሞላቸዋል። ፔሬዝ ጀልባው ባለቤት ቡቱይ ባህር አካባቢ ሰሽርሽር የሚሄዱ መሆኑን ለጀልባው ባለቤት ቡቱይ ባህር አካባቢ ሰሽርሽር የሚሄዱ መሆኑን ነገረው። በመጨረሻ ግን የጉዞውን ምስጢር ነገረው። ጉዞው አደጋ ያለበት በመሆኑ የከፍያው ጥጋም ጨመረ።

መርከቢ ወደ ምዕዋ በመንገ ላይ አያለች ያዕቆብ ጥንቃቄ የተመላበት ገቦጅት አንዲያደርግ መመሪያ ተሰጠው። ያዕቆብም በቀቱ የሆቴሉ እንግዳ ተቀባይ አንዲያየው አደረገ። ለአንገሳ ተቀባዩ ጊጣ ጊጠች፣ ወርቀቅና ገዝዘብ በአደራ አንዲያስቀምጥለት ለጠው። ከጥቂት ቀናት በኋላ መሆቱ አንደሚጀመሩና ቸው በመግለፅ ልብሳቸን ሆቴሉ ላውንደሪ ውስጥ አስገባ። ያዕቆብ ሰጥቷት ቀናት ከአስመራ ከተማ ወጣ አንደጣል ነገራቸው። መርከቢ ወደ አርትራ ጠረፍ ስትቃረብ አንድ አፍሪካዊ ምንጭ ቦምፕስቱ በዓዝም ያልተጠበቀ ነገር በምስራት አፍሪካ አካባቢ አንደሚከሰት ለፔሬዝ ደወሉ ነገረው። ስለ ያዕቆብ ደህንነት በጥብቅ አንዲያስጠበቅትም አሰጠነቀቀው። ፔሬዝ ያዕቆብን ከአርትራ ለማውጣት የተነደፈውን ፕላን ሰከተኛ ወገን አውቆታል በማለት ደመደመ፣ ድንጋጤም ተሰማው። ሰሰዚህም ፔሬዝ ጀልባዋ ወደ አሰራኤል አንድትመለስ አዘዘ። ቡግንስቱ በኢትዮጵያና በአርትራ መካከል ጣርንት ተነሳ። ሚሀን ወቅት ነው የአፍሪካ ምንጩ የነገረውን ማስጠንቀቂያ ባልሆነ መንገድ ሙተርጉሙን የተረዳው። አዲስ በተፈጠረበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ ምክንያት ጉዟውን ለሶንድ ሁለት ቀን ማዘግየቱ ተገዷ ሆነ ተገኘ። ለዚህም ጉዟው እንዲዘገይ ተደረገ።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ጠርነት ከፈነዳ በኋላ አብመራ ሙሉ ትርምስ ተፈጠረ። አስመራ የነበሩ የውጭ ሀገር ተቁዋሞች ሠራተኞች፣ አምባሳደሮች፣ አንግሊዘኞች፣ ፈረንሳዮች ከኤርትራ ወጡ። ቦንቴ ግን አያሌ የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ያሉበት መደነዘሪያ ሆቴል መጉረፍ ጀመሩ። ያዕቆብ ከነበረበት ጥጉጥትም በላይ ሠራተኛ አዲጋ ላይ መደቀቹ። ያዕቆብ አስመራ በኢትዮጵያ አየር ኃይል መደብደብ አይታሮም ቦምብስ ሲጋት ላይ ወደቁ። ያረፈበት ሆቴል ይደበደብል የሚል ጥርጣሬም አደረበት። ያዕቆብ ከሻንጣ ጋር አስመራ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአስመራ አውሮፕላን ማረፊያን መደብደቡን በዓይኑ አይታል። ቦርቱ በተጀመረበት አስት ያዕቆብ ለሆቴሉ ሐንሃላ ተቀባይ ወደ ምዩ ለቸርቸር እንደሚሂድ ገለፀለት። ወደ ሦስዋ መሂድ የተሰጠ ነገር ስለሆነ ያለከተሰው ጥርጣሬ አደነበረም። የመጡሩ ከአምስ በሙሉ ጥብቅ ሩጥጥር ይደረግባቸው ስለነበር ያዕቆብ ለማሠስ ይሞክራል ብሎ ያሰበ አደነበረም። ያዕቆብ 2000 ያህር በየሩ ገዝብ አንገሳ ሠቀብሆ ኃሩፊው ዘንድ አደነቅመጠ፣ መኝታ ክናሩ ጠብጥ ያነበሩትን ዕቃዎችም አዘጋጀው ተቁጥው፣ የወሰደው የሩቱላይት ቴሌፎንን ብቻ ነው። ያዕቆብ የሰቱሳይት ቴሌፎን አንድ ቀን ይነጥፈራል የሚል ከሳተና ሩጋ ቻ ነበረበት።

ያዕቆብ ነፀሃት ለፊተኞች ትተራት ሰመጀን ቦይ ወደ ምዩ የተጓዘው በፈረስ የተሰሩ ታክሲዎች ነበሩ። ያዕቆብ ቢናር ሞኖሃ (ዘነጋም ሆነ ወህሪያት በጣም ትሞታሉት) የመሩቱ መጠ አስነ ጋን ጂገሬ ሲንሂገሬድ ይደደርሰል። በተሳይ ክሰኔ ጀሰ ጠፈፋም በሱ ብዶተች የሙትቱ መጠን ሶስነ ናሳ ጂገሬ ሲንሂገሬድ ይጀደርፈሉ። ምሰዋ የነሳም የመፈጨረቡት ጥታታማ ከተመሠ ሰዓሆነ ኑተቀርም። ብሂይ። ያዕቆብ ምሰዋ ገዛቡ ሃገቡን አንድ ሆቴል ወሰሰ ኦደረ። በዋሄቱ ወሰሰ ታዮችው ተደረቡን ያደነዘዎቻቸውን በዘወደቱ ሳይ ያቁሙ ነሳጭሞች ነበሩ። ኑተደረቡቱ ጋር ለመጠዎጀት ያዕቆብ ገቢ ኦደሰዘወደዝተም ምሰዋ ደደሰበት ፊሰተ ዘሠሰት የሆሳጉ ቤሮች ነሙ ባሬን ማዜቶች ጋር ተጠጠጀተ ነበር። ከሰረው ጋር የጀደነ ኦሳደጨት ኢንዲሸሩሸሩ ያቀደሰሩቸውን ግብሟ ግን

ለይሰሰቱት ቁሩ። ቡታግስቱ ግን ከሁለት የቤልጂያም ዜጋ ከሆኑ ባልና ሚስቶች ጋር ተገናኘ። በሲንድ ጀልባ ሆነው በቀይ ባህር ላይ መንሸራሸር ጀመሩ። አነዚህ ባልና ሚስቶች ሰባት ቀን ሙሉ ከያዕቆብ አልተለዩም። ያዕቆብ ነፃነቱን አስከተጉናፀፈበት ዕለት ናት።

ያልጠረጠሩ ባልና ሚስቶች

ሠቅቡም አልጠረጠሩኝም። የንርኂቸውን ታሪክ እንዴለ ነው የተቀበሉኝ። በጥርነት መካከል የተገኘሁ ጋዜጠኛ መሆኔንና አዘበው በፍጥነት ለቅቂ ለመውጣት የምፈልግ መሆኔን ነበር ያጫወትኂቸው። ለሰባት ቀን በጀልባቸው ስላንሸራሸሩኝ ግን መጠነኛ ገንዘብ ስጭያቸዋዋለሁ። የሰተሳይት ቴሌፎኔን ግን ስልብ ተመኑዋዋት ነበር። ቴሌፎኗን እጡሻቸው ቤልጅየም ከሚገኙት ቤተሰቦቻቸው ጋር ተነጋግረው ነበር። በግለት ያዕቆብ ሁኔታውን ያብራራል።

ጥርጣሬ ላለማሳደር

ስለሠዎቹ ላይ ጥርጣሬ ላለማሳደር በመጀመሪያ በስተደቡብ በሚዙቲ አቅጣጫ ያልነበቸውን አንኡተገበሩ ለነልና ሚሄቱ ሃገራቸው። ጥሬት ቀይዶ ግን ለደዱት የሚሄው ወዳጅቹ በጀልባ ከአይሉት ከሮገመጡና ከአስበበደ ደሩቶች በአንዱ ላይ አንደሚጠብቋቸው ለነገሩት ባልና ሚሄቱ አንዲተባበሩት በአክብሮት ጠየቃቸው። ተስማሙ። ጌራዝ ስለልጂ ጀልባ በየተሳይት ቴሌፎን መልዕክቱ አንደደረሰው የተገሩያትን የሰደራኢሳን ጀልባ ያፈቀበን ታሪኩ ዘንድ በአሰተዓያ መደ ቢራሽሄግ ጀልባ ሳክት። በመሳከሉ ግን ያዕቆብ በየነጀ ሳይ አያሰ አብቸ ጋሪ ሁኔታ ሞነሣት ነበር። ያዕቆብ ከሰነጋው ቢያተራሪ የመጋበተሰውን ብኩል።

«በመጀመሪያው ቀን የቤልጅዓ ጀልባ መቅበሩ አንደጀመረች በአሰሪ ኢሪ መረጋበበ ሳይ የተሰራሩ ሞኦርትራ መጥሩጀች አጋበመጡ። የባህር መረጋዘ አነዥ ፋዘ ጋር በመጀነት ለመመሳሪት በአያሌው ፈሰገ። ሠማንሰው በሲንዲት ደሴት ሳይ አሩን ባልጃዘት መኝት ነገ ተነ ከመረጋዘ ወደሞ በመምጣት ከሮ ጋር በሩ ጠሳ። የባህር አነዥ ኦሰራንሰሩ መሆኔን አወቋቋል፣ ግን ለሰጌ የመሰከለው

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳችም ነገር የለም፤ በጣም አስፈርቶኝ የነበረው ግን ዳኮቴ የሳተላይት ቴሌፎኔን ያይብኝ ይሆን? የሚለው ሲጋት ነበር። ከጀልባው ላይ ሆኜ አስመራ ወደሚገኘው ሆቴል በሞባይል አየደወልኩ መልክት እንዲለኝና እንደሌለኝ አጣራ ነበር። ባለቤቴም ከእስራኤል ወደ ሆቴሉ አየደወለች መልክት ትታው ነበር። አስመራ ለሚገኙት የእስራኤል አምባሳደር በሞባይሉ አየደወልኩ በመልክቱ ሁኔታ ላይ መሆኔንም አነግራቸዋለሁ፤ ከአገልግሎቱ ነፃ ሲያወጡኝ ባለመቻላቸውም አመቅሳቸዋለሁ።»

አስራኤል ውስጥ የሚገኘው የእስራኤል የመከላከያ ኮንስትራክሽን ከፋንያ ቢሮዎች ወደ ኦፐሬሽን ማዕከልነት ቀየየሩ የነፋንያው ባለቤት የሆነው ፒሬዝም ከአገዢት የኢርትራ እንዲቋቋ ከሆነች ሀገር ውስጥ ገብቱ የኦፐሬሽን ማዕከል አቋቋመ። ፒሬዝ የቢልሺየሚን ጀልባ አንቅሰቃሴ በሚገባ መከታተል ያዙ። ፕሬዝ ቀደም ብሎ የተከራያት ጀልባ ከኢይላት ወደብ ተንስታ በቀይ ባህር ውስጥ ትገኝ ስለነበር ስለሚጠበኗቸው እርምጃ በጽሁፍ መመሪያ ያስተላልፍ ነበር። ያሱቡን ከአገታ ነፃ ለማውጣት በሚደረገው እንቅስቃሴ ላንክ ቢያጋጥም ችግሩን ለመቋቋም ዝግጅት ተደርጉ ነበር። ችግሩን የመፍቻው ቁልፍ መንገድ ወፍራም ገመ ለአርትራ ባለስልጣኖች መስጠት መሆኑ ታምኖበታል። ስለሆነም ለጉቦ የሚሆን ከፍተኛ ገንዘብ ተዘጋጅቶ ነበር።

የያሱቡና የቢልሺየም ባልና ሚስት የባህር ላይ ሽርሽር ቆርሰ ደስ ነበር። ይህ የሆነው ለምቹ በደሴቶቹ ላይ አየወረዱ ኢፍ በለሚሉና ብዙ የዋህ ልምምድ ስለሚያደርጉ ነው። በአንድ ወቅት ቢልሺጋሙያኑ ቱና የተባለ የዓሳ ዘር አየምደው ጥሬውን ዓሳ በልተዋል። ጣፋጭነቱ አጅ ያስቆረጥማል ሲሉም ተስምተዋል። ያሱቡ አብሃኛውን ገንዘብ ያሳለፈው በጀልባዋ ውስጥ ነው። ያሱቡ ይህንን ያደረገው ብዙ ሰው አንዲያውቅና ጣጣ ውስጥ እንዳይገባ በማሰብና የባህር ላይ ህይወት ልምድ በማልነበረውም እንዳይታመም ጥንቃቄ ለማድረግ ነው።

እነ ያሱቡ ለስምንት ቀናት ያህል በባህር ላይ ሽርሽር ሲያደርጉ እንደቆዩ በዜድስተናው ቀን የጀልባዋ ሞተር ተበላሸ። ያም የእንያሱቡን ንብ ቀድሶ አንዲሆን አደረገው። በተይ ባህር ውስጥ ከፍተኛ ማዕበል በመጣሩ ምክንያት የእነያሱቡ ጀልባ ከአንዱ


ሁለቱ ወደመገልበጥ ተቃርባ ነበር። የጀልባዋ ችግር እየከፋ በመምጣቱ እነ ያሱቡ አማራጭ ስላጡ ሱዳን አጠገብ በሚትገኝ ሰንጋራ - ሪፍ በሚትባል ከፍራ ላይ ለማረፍ ተገደዱ።

ከዚህ በኋላ የተንደፈው አቅድ ያተከረው ያሱቡን ነባ አውጥቶ ወደ አስራኤል ጀልባ የማሠውሩ ጉዳይ ነው። ገዘውውሩ በሲሲት መሬም አንጂለስ አጠቃላይ ስምንት ላይ ተደርጓል። የካቲት ፩፤1991 ከመንፈቀ ለሊት በኋላ ያሱቡ የአስራኢሊን ጀልባ ከራት ተመለከተ። በዚህን ጠት ከአገታ ነባ የሚወጣበትና ከጭንቀት የሚገላገልበት ሰዓት መቃረቡን በማሰብ ለልቡ ሀሬት ተሰማው። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሁለቱ ጀልባዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ በተመለበት አኒኋን ተቀራረቡ። ልክ ከሊሊቱ ለሀ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ያሱቡ በለሣም ከጓንያው አተከራያት ጀልባ ውስጥ ገባ። በጀልባዋ ውስጥም ከአገታ ነባ ሲያወጣው የመጣውን የልብ ጓደኛውን አገኘው። ሁለቱ ተያያዘው ቀላቀሱ፤ ተሳሳሙ። ከዚህ በኋላ ፒሬዝ ሊያሱቡ ባለቤት ደውሎ ያሱቡ ወደ አስራኤል ውስጥ አንደከረመ በገር ገር አነራት። ያሱቡ ወደ አስራኤል ያደረው ጉዞ ግን አሌጋ በአሌጋ ነው መንገዱ የሚባለለት አይነት አለነበረም። ነአነ ያሱቡ ጀልባ ሙት ደርገበት በኤይላት ወደብ አየባበ ከፍተኛ ወሽበ አጠራጭነቱና ማዕበል ተከሰቶ ነበር፤ በዚህም ሰቢያ ያሱቡና ጓደኛው ከሩሳ ታመመ። በዝመሙ የቀነሳም ህሊናቸውን ሳተ። ቀስ በቀስ ግን ነፍስ አየዘሩ መጡ። ከዘኑ ውጣውረድ በኋላ እነያሱቡ በሰላም ኮኢይላት ወደብ ደረሱ። ያሱቡ ከወደቡ ሲደርስ ያነጥነንያው አባሉች በታላት ክበር ተቀበሉት። ከፖሊት ደቂቃዎች በኋላ አጠሮፐላን ተሳፍሮ ወደ ሰዲዶቭ አውሮፐላን ማረፊያ በረረ። ከአውሮፐላኑ ሲወርድ ባለቤቱና ሊጆቹ በታላት ፍጽር ተቀበሉት።

ያሱቡ ከአገታ ነባ ወጥቷል። አሁን የቀረው አንድ ነገር ብቸ ነው፤ ሰአነሪቭ አደጋለም ለአርትራ ባለስልጣኖች መንገር። ለዚህም የያሱቡን ከአገታ ነባ መውጣትና በሰላም አስራል መገት ለአርትራ ባለስልጣኖች አንዲነግሯቸው ፒሬዝ ለከተዛንያው ባለስልጣኖች መመሪያ አስተላለፉ። ከዚህም ለባ በኋጋኒት መጀመ ተጎሰበት ለተበር ከዮከፈለው ገንዘብ ውስጥ በርካታ ፕገዘብ ለአርትራ መንገስት እንዲመለስ ፒሬዝ አስራኤል የሚያሰውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ባንኩን አዘዘ። ፔሬዝ የኤርትራ ባለስልጣኖች ለወደፊቱ በአራው ላይ አንቅፋት እንዳይፈጥሩ አስጠነቀቀ። አቶ ኢሳያስ አፈወርቂን ሁለት ነገሮች አስገርመዋቸዋል። በመጀመሪያ ያስገረማቸው ከኤርሳቸውና ከባለስልጣኖቻቸው አፍንጫ ስር ያዕቆብ ከአንታ አምልጦ አስራኤል መግባቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ያስደነቃቸው ነገር ደግሞ ድፍረት የተመላበት የፔሬዝ የአጉራሽን ኤርትራ ዝግጅትና አፈፃፀም ነው። አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የፔሬዝ ወዳጆችም በሁኔታው የፕሬዚዳንት ኢሳያስን ያህል ተደንቀዋል። ብዙዎቹም «ያዕቆብን ከአንታ ነፃ ካወጣህ በኋላ ለምን በርካታ ገዝብ ለኤርትራ መንግስት ተመላሽ እንዲሆን አደረግህ?» በማለት ፔሬዝን ጠይቀውታል። ፔሬዝ ያንን ያደረገው በኤርሱ ኩባንያና በኤርትራ መንግስት መካከል ቂም በቀል እንዳይኖር አስቦ እንደሆነ ይናገራል። ከዚያ በኋላ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ ተወካይ ለአስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በላፊው ደብደቤ የኤርትራ መንግስት በአስራኤል የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ላይ ምንም አይነት ቅሬታ እንደሌለው ገልጿል። ከኩባንያው ጋር የነበረውም አለመግባባት ፍፃሜ ያገኘ መሆኑን አብራርቷል። በገርገር በቀረበው አይነት ሁኔታ ኦፕሬሽን ኤርትራ ለአታማ በሆነ መንገድ ተፈፅሟል።



ገንዘብና ፅውቅት

ሲሳይ ንጉሡ

ርዕሱ ቤት ለለመታ·ልኝ አንድ መስመር ልጨምርበትና ሙሉ ላድርገው።

ገንዘብና ዕውቅት፣ የተራራቁ ሉት
ገንዘቡም ወዮለት፣ ዕውቀቱም ወዮለት

ነገርዬዋ ቅኔ ባትባልም ተፈላጊውን መልዕክት ያዘለች ተራ ግጥም ናት። ከወደዳችሁ ሊሳችሁ ጨምሯት፣ ከጠላችኋትም በካልኝ አሽቀንጥራችሁ ጣሏት።

ጠንቅ አሰምሮ ያለን ሰዎች እንደምንገምተው ከሆነ ዕውቀትና ገንዘብ መጣመም አለባቸው፣ የሁለቱ ፍቅር

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓለምን ያፋቅራል፤ ያቀራርባል። የሁለቱ ፀብ ዓለምን ያጣላል ፤ ያራርቃል። ይህንን ማጣጣም ያልቻለ ሀገርና ህዝብ ሁሉም እንደተዘረጠጠ፤ ሁሉም ቁልቁል እንደወረደ ይኖራል።

«ቀልዱን ተው እባክህ፤ ገንዘብማ ዕውቀት መቼውም ተገናኝተው አያውቁም» ይለሉ። የጠረራቸው ምሁራን የአንዳንዶቹ ምሬት ምክንያታዊ ነው። ዕውቀትን አግባተው፤ ለዕውቀት በማደራቸው ገንዘብ ጥምድ አድርጎ ጠልቷቸው ስለራቃቸው ይሆናል። የአንዳንዶቹ ምሬት ግን አንዲያው ጉንጭ አልፋ ነው። ገንዘብ ሰግዶ ሲመጣ እየናቁት ከሸሻቸው በኋላ ያለቃቅሳሉ። ዕውቀት መከበር የሚፈልገውን ያህል ገንዘብም መከበር እንደሚፈልግ ይዘነጉታል። ንቀው ሲመነዝሩት አሰም ንቋቸው ይሸሻል።

የሁለቱ ፍልሚያ የሚጀምረው ከአፈሳጠራቸው ነው። መጀመሪያ ማን ተፈጠረ? ዕውቀት ወይስ ገንዘብ... ብዙዎቻችን ዕውቀትን እናስቀድማለን። ገንዘብ ደግሞ እንዳሁኑ በወረቀት መልክ ባይኖርም ቅሉ፤ ቁሳቁስ መልክ ከዕውቀት ቀድሞ እንደነበር ይነገራል። ወርቅን፤ አልማዝን፤ ዕንቁን ጠቅሶ ያቀርባል፤ ጥቅም ላይ ያልዋለ የጥሬ ሀብት ክምችት በቀዳሚነት መኖሩን ደግሞ ይነቅፋው መንገድ ያጠቁማል።

ከሁሉም በፊት መሬት ነበረች። ያለች ሁሉን ቻይ መሬት ሆኗበፊ መሬት... ጥሬ ሀብቱን ለምቃ ይዛ ነበር። የሰው ዘር ራቁቱን መጣና ሰፈረባት። አሰፋፈሩ አላማራትም። በሳም ፈጣን በሆነ ሁኔታ እንደሚያሞላቀልቃት ገመተች። በዚያ ላይ ራቁቱን ስለሆነ ልብስ ያስፈልገዋል፤ መጠለያ ያስፈልገዋል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ፋታ የማይሰጠውን ሆዱን ያህ መምጣቱን ታውቃለች። እርስ በርሱ ተከላልቶ እንዲያልቅ ወይንም አራዊቱን በአደን ከምድር ዛፅ እንዳያጠፋርስ ፣ሄሞን ከፍታ

የማይነጥፍ ሀብቷን አሰየችው። አካባቢውን እንዲያውቅ ጋበዘችው። እንዲቆፍርና እንዲዘራ፤ እንዲያመርትባት ደረታን ገልብጣ ሰጠችው። ሰው ሀብትን አወቀ። መሬት ውስጥ የተደበቀውን ሀብት ሰርስሮ እያወጣ ከመሬት በላይ አዋለው። ከአለት ጉርሱ ወደኪሱ ተሸጋገረ። በኪሱ ሊይዘው የሚችለውን ገንዘብ ከግንባቡ በኋላ ፈጠረ። አንዱ የሌላው (inter dependent) መሆናቸውን በዚህ ሂደት እንረዳለን።

ይህ ዑደት የሰው ዘር ከተፈጠረ ጀምሮ ያለ ነው። እናት መሬት አሁንም ሊጋስቷን አላቋረጠችም። ወንዞቿን፤ ተራሮቿንና ማዕድናን ለሰው ዘር ክፍት አድርጋ ዕውቀትና ገንዘብ ተባብረው እንዲሰሩበት ትጋብዛለች። ሆኖም ግን ጥጋቹ ገንዘብና ትዕቢተኛ ዕውቀት ሁሉን ቻይ መሬት ላይ ተቀምጠው ሲፋለሙ ለትገብት መዳረጋቸው አልቀረም። ዋ... መሬት የለገሰች ለታ፤ ሁለቱም መግቢያ ያጡና አንገታቸውን ወደላይ አንጋጠው መለመን ያጀምራሉ። ዋናው ነገር የቆሙባትንና የሚያልፋባትን መሬት ያለማስመረር መሆኑን ዕውቀትም ሆነ ገንዘብ ቢያውቁት ጥሩ ነው።

ጥጋቹ ገንዘብ አንዳንዴ የሚሰራውን ያላጣዋል። ዕውቀትን ቁልቁል ልርገጥህ ይለዋል። ከመጠን ያለፈ ኃይል ይሰማዋል። ጥጋቡ ከሆዱ አልፎ ጭንቅላቱ ላይ ስለሚወጣ ያሰክረዋል። ከማንም፤ ከምንም በላይ የሆነ ይመስለዋል። ፈላጭ-ቆራጭነት ያዳጃዋል። ትዕቢተኛ ዕውቀትም ከዚህ አይተናነስም። ገንዘብን ያለአግባቡ ይንቀዋል፤ ይገላመጠዋል። «ቁሳቁስ» ብሎ ያንቋሽሸዋል። የሚኖርበት ዓለም ቁሳቁስ መሆኑን ይዘነጋዋል። ማንም የማይደርስበት፤ ማንም የማይደፍረው ይመስለዋል። በትዕዚት ተወጥሮና በበላይነት ስሜት ሰክሮ ከገንዘብ ጋር እንደተጣላ ይኖራል።

ዛሬጣ ገንዘብ የመኖሩን ያህል ስለተም ለውቀትም

t.me/OLDBOOKSPDF

ምልድል። ገብጋባ ገንዘብ ከኪስ ላለማውጣት ይንቀጠቀጣል። የተፈጠረው ለሰው ልጅ አገልግሎት መሆኑን ይዘነጋዋል። በመቅበርና በመቀርቀር ያምናሉ። የቁሳቁስ አምልኮቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ስለሚደርስ ከጌቴአቸውም ይራራቃል። ስነታቸው ዕውቀትም አንድ ሂሳብ ውስጥ ታምቆ ወደ ሌሎች ሳይደርስ በብቸኝነት ይንከባለፋል። ግለኝነት ስለሚያጠቃው ክሌሎች መውሰድ አንጂ የራሱን መስጠት አይፈልግም። በተለምዶ «የጋ ውስጥ መብራት» ሊያሉ ይጠሩታል። ሌሎች አንዲያውቁ፣ እንዲነቁና አንዲደርሱበት አይፈልግም። ዕውቀት የሚያልቅ አየመሰለው ይፈነታል። የዕውቀትን ያለማለቅ የሚያውቀው ከስኩቱ ተለቆ ቸርነትን ሲለበስ ብቻ ነው። ገብጋባ ገንዘቡ ሆነ ስኬታም ዕውቀት ሊዘነጉት የማይገባው ነገር መስረታቸውና ግባቸው የሰው ልጅ ፍላጎት መሆኑን ነው። ከሰው ልጅ ፍላጎትና ግልጋሎት ወጪ ሁለቱም ዋጋ የላቸውም።

ምቀኛ ዕውቀትና ሸረኛ ገንዘብ አንድ ናቸው። ሁለቱም የሚውሉት ለጠለፋ ተግባር ነው። ከልማት ይልቅ ጥፋት፣ ከደግነት ይልቅ ክፋት ይቀናቸዋል። የሌላውን ዕድገት አይወዱም። የሳረቤቶቻቸውን ቤት ለማፍረስ ዕንቅልፍ አጥተው ሲባንኑ ያድራሉ። ምቀኛ ዕውቀት የተንኮል እሽት ሲያመርት፣ ሸረኛ ገንዘብ ገበቶ ያከሩፍልለታል። አንደኛው ክብራት ሲጭር ሌላኛው ቤዝነን ያርከፈክፍለታል። አንደኛው በቁም ሲገድል ሌላኛው መቃብር ያዘጋጅለታል። ለከፉት ሲሉ ያልከበራቸውንና የሌላቸውን ወዳጅነት ይመሰርታሉ። ሁለቱም ሀጢያታቸው እንዲሰረይላቸው ያም ፀሎት ያስፈልጋቸዋል።

ጨቋኝ ገንዘብን ለመዋጋት አመፀኛ ዕውቀት መከሰቱ የግድ ነው። ጨቋኙ የሌላውን ጉልበትና ዕውቀት በፍርፋሪ መግዛት ሲፈልግ አመፀኛው ደግሞ አምቢ ይላል። አቃጉቶ

መብራት የሚችለውን ሆነ ብሎ ያንጋድደዋል። ጨቋኝ ገንዘብ በተለያየ መንገድ ጉልበቱን ሲያላይ አመፀኛ አውቀትም ልግመቱን ያንፀባርቃል። ለሁለቱም የሚበጀው ከመጋደዳት ይልቅ መረዳዳትና መተሳሰቡ ነው። ያኔ ዕርቅ ይወርዳል።

አስራፊ ዕውቀትና ጉረኛ ገንዘብ በአብዛኛው ይመሳሰላሉ። ሁለቱም በውስጣቸው ክፋት የለም። ችግራቸው «አነብሩን፣ ተንከባከቡን፣ አንቱ በሉን፣ እሹሩሩ በሉን» ማለታቸው ነው። እንዲህ ለተንከባከባቸው የቀሆች ናቸው። ደረታቸውን ነልጠው፣ ልባቸውን ከፍተው ይሰጣሉ። አስራፊ ዕውቀት እሹን ኪሱ ከትቶ፣ ለንቦጩን ጥሎ ያለስራ ሲቀመጥ ራሱም ሆነ ሀገሩን በመጠኑም ቢሆን መጉዳቱ አይቀርም። ጉረኛ ገንዘብም ስሙን ብቻ በሚሊዮን አያስጠራ ሳይንቀሳቀስ ከተቀመጠ በድን ኮረብታ ነው።

ጅንኑ ዕውቀትና ተብራራው ገንዘብም ከዚሁ ጎራ የሚመደቡ ናቸው። አንደኛው «ገንዘብ የማይሸው ዕውቀት» ብሎ ራሱን ሲያኩራራና ሌላኛው ደግሞ «ዕውቀትን የሚገዛ ገንዘብ» ቦግለት ራሱን ደስኩሳል። ሁለቱም ጉረኞች ናቸው። «ቢጠራት የማይሰማ» ቀብራራ ገንዘብ ውልደቱንና ዕድገቱን የዘነጋ ነው። ሲጠሩት አዘት ሲልኩት ወዴት የማይል ገንዘብ ከባዱ ወረቀት ምንም አይሻልም። ጅንኑ ዕውቀት «ከሌላው መውሰድም ሆነ ለሌላው መስጠት አልፈልግም» ብሎ ይጀነናል። እንዲያው አይቀርም። ማንም ከመስጠትና ከመቀበል ውጭ ሊሆን አይችልም ከተፈጥሮ ህጋጋት አንዱ ይህ ነው።

«መዝናት አለምን ይገዛሉ» ያለው ቮልቴር ነው። ቀብራራው ገንዘብ ይህን ሲሰማ ይናደድ ይሆናል። በገንዘብ ያልተደገፈ ዕውቀት የትም እንደማያደርስ ልቡ ያውቀዋል። «ብዕር ይበልጣል ከብር» ብለው የሚሸነፉም አሉ። መፅሐፍትና ብዕሩን የሚገዙትም ሆነ የሚሸጡት በገንዘብ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን ይዘነጉታል። ለነገሩ መበላለጥን ምን አመጣው? ምድራችን የምትፈልገው የሁሉን መከባበርና መፋቀር ነው።

«ዋናው ጥቅሩ ነው» ይላል አበሻ አርስ በርሱ እየተዘራጠጠና እየተጋደለ። እየተጠላለፉ ጥቅር፣ አፍአዊ እንጂ ልባዊ አይደለም። ዕውቀትም ሆነ ገንዘብ እንደመሬት የዋህ ሰፈና ቻይ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ጥጋቡም ሆነ ትዕቢት እንዲሸርድ፣ ትቢጋነት እንዲጠፋ፣ ጭቆናና አመፅ እንዳይስፋፋ የዘውትር ዐሳታችን ነው።


ሁሉ የማይስማሙ ከሆነ አግዚአብሔር መኖቱን እንደሚያወርድባቸውና ድምጥማጣቸውን እንደሚያጠፋው መዘንጋት የለባቸውም። የመራት መንቀጥቀጥ፣ አውሎ ነፋስ፣ መብረቅ፣ አሳተሞራና የውሀ መላት የመሳሰሉ መሳሪያዎች አሉት – ለትጣት በቂ ናቸው። ይህንን ደግሞ ገንዘብም ሆነ ዕውቀት ሊድኗመት አይችሉም።

አግዚአብሔር ይህ ሁሉ መሳሪያ አያሰው ዕውቀትና ገንዘብ ደግሞ የራሳቸውን መሣፊያ ጨምረውሰታል። አቶሚክ ቦንብ፣ ኒትሮን ቦንብ፣ መዘቱ... ታዲያ ከላይም፣ ከታችም፣ ከውስጥም፣ ከውጭም፣ በአሳት የተከበቡት ገንዘብና ዕውቀት ተፋቅረው በመኖር ፈንታ እየተጣሉ አመድ ለመሆን ለምን እንደሚችኩሉ አይገባንም።

ህይወት ዕውቀትም ናት፣ ገንዘብም ናት። አንደኛውን ብቻ ልትሆን አትችልም። ሁሉቱ ከተከባበሩና ከተፋቀሩ እንደ ምድሩ ሁሉ መደፊት የለማይ በሮችም ይከፈታሉ። ህዝብም ይሰፍርባቸዋል። ይህንን ተስፋ ይዘን በስንኝ ቋጠሮ ዕሁፉን እንደምድመው።

ገንዘብና ዕውቀት የተፋቀሩለት
ምድራችን አበባ፣ ዓለማችን ገነት።

መጣጥፍ



ብዙት ስበክ ርግብ

ተስፋዬ ገብረአብ

ይህ አጭር ግለ - ታሪክ የፈጠራ ድርሰት አይደለም። ከአሲስ አበባ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ቢሾፍቱ ወይም ደብረዘይት ተብሳ በምትጠራው ቀየ በትክክል የተፈፀመ አውነተኛ ታሪክ ነው። እኔ ራሴ የቢሾፍቱ ልጅ እንደ መሆኔ አንግዳ ጀቢር ወይም በትዕል ስም «ብረት ለበስ ርግብ» ተብሎ የሚጠራውን የዘመናችን ሰው በአካል አውቀዋለሁ።

የአንግዳ ጀቢር የህይወት ታሪክ ይገር ቢባል ከሶስት መሸመር የማይልጥ ቁም ነገር አይወጣውም። እንግዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጆቢር በቢሾፍቱ ከተማ ተወልዶ እስከ ሰመንተኛ ክፍል ከተማሪ በኋላ ትምህርቱን አቋርጦ በአንድ የግል ጋራዥ ውስጥ የመካኒክነት ሙያ ተማረ። በአጭር ጊዜ ውስጥም በሙያው ስመጥር ለመሆን በቃ። ሀያ አምስት ዓመት ሲሞላው ትዳር ይዞ አንዲት ሴት ልጅ ወለደ። ትምህርቱንም ማታ ማታ እየተማረ የ12ኛን ክፍል አጠናቀቀ። የአንግዳ ጆቢር ታሪክ ይሸው ነው። በርግጥ ከ200 ጊዜ በላይ በክባድ ፀብ ውስጥ ገብቶ መቡዋቀስ፣ 25ጊዜ መታሰሩ፤ በቁን አንድ አንሰራ ጠላ ቢጠጣ እንኳ ትምም እንደማይለውና የለየለት ገለባጭ ስለመሆኑ ሲጠቀስ ይችል ይሆናል። የቢሾፍቱ ሰዎች ግን ከነዚህ ሁሉ ባሻገር አንግዳ ጆቢርን አስመልክቶ አያሌ ትዝታዎች አሏቸው። ወደ ቢሾፍቱ ብቅ ያለ ሰው «አንግዳ ጆቢር ምን ዓይነት ሰው ነው?» ብሎ ቢጠይቅ ከማንኛውም ሰው እንዲህ የሚል ምላሽ ያገኛል። አንግዳ ጆቢር አመፀኛ፣ እውነተኛ፣ የዋህና ቅን ሰው ነው።

እኔም ላወጋችሁ ያሰብኩት ስለእነዚህ ባህሪያቶቹ ነው። በርግጥ ከተጠቀሱት ባህርያቶቹ በተጨማሪ አንግዳ ጆቢር አፈንጋጭ መሆኑም ይሰማኛል።

የቢሾፍቱ ህዝብ አንግዳ ጆቢርን ብረት ለበስ ርግብ አያለ ነው የሚጠራው። ግን ለምን?

ቢሾፍቱ የወታደሮች ከተማ ናት። በመሆኑም ንግግሮች፣ ቀልዶችና ቅፅል ስሞች ብዙውን ጊዜ የወታደራዊ ቃላት ጠረን አላቸው። ለአብነት የቢሾፍቱ ሰዎች አንድን ሰው «በጣም ተናደደ» ለማለት ሲፈልጉ «ጀት ሆነ» ነው የሚሉት። ጀትና ንዴትን ምን አንዳነናኛቸው ግን የቢሾፍቱ አምላክ ይወቅ።

ጠንካራ ሰው ሲገጥማቸው ደግሞ «ብረት ለበሰ» ሲሉ ያደንቁታል። አንድ የቢሾፍቱ ምድር ሰው ድንገት በጨዋታ መሀል «አንተ አኮ ሚግ ነህ» የሚል ንግግር ቢያመጣ

መደንገጥ አያስፈልግም። «ፈጣን ነህ» ማለት ስለሆነ መደሰት ነው የሚገባው። የቢሾፍቱ ሰዎች ሌላ አስቂኝ አባባልም አላቸው። ለአብነት አንዲት የቢሾፍቱ ከሪዳ ስቬል መምህር የሆነ ፍቅረኛዋን «የኔ ጆኔራል፣ የኔ ፓይለት፣ የኔ ኮሎኔል» ብትለው መደነቅ አይገባም። ይልቁን፣ «የኔ ቆንጆ፣ የኔ ውድ፣ የኔ ሽጋ» ማለትዋ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ለአንግዳ ጆቢር «ብረት ለበስ ርግቤ» የሚል ቅፅል ስም ያወጡለት ሴትኛ አዳሪዎች መኖራቸው ይነገራል። «ጠንካራና ደግ» ለማለት ፈልገው ነው። አንግዳ ጆቢር ይህን ስያሜ ማግኘት የቻለው ለተጠቀት ሁሉ ስለሚያዝንና በተለይ ሴቶችና ህፃናት ሲበደሉ ሲመለከት በቁጣ ስለሚጋጭ መሆኑ በድፍን ቢሾፍቱ ይነገርለታል። ሀሪም ቀረ የአንግዳ ጆቢርን ልዩ ባህርያት አስመልክቶ የማውቃቸውን ጥቂት ጣፋጭ፤ ልብ የሚነኩና፣ የሚያስቁ ወጐች ላቃምሳችሁ፤

* * *

አንግዳ ጆቢርን አመፀኛ ያሰኘው የአይበገሬነት ባህርይው ነው። የቢሾፍቱ አየር ወለድ ከማንዶዎች ጠጥተውና ሰክረው ከተማዋን በሚያምሱበት የቅዳሜና የእሁድ ምሽቶች ቢሾፍቱ ላይ ነፃ ሆኖ የሚጠጣው አንግዳ ጆቢር ብቻ ነው። በጡንቻቸውና በድብደባ ሙያቸው የሚመኩት የአየር ወለድ አባላትም ታዲያ ባንኮኒ ይዘው ሲጠጡ አንግዳ ጆቢር መኖር አለመኖሩን ማጣራት ባግባቡ ለምደዋል። አንግዳ ጆቢር ካለ አንገታቸውን ደፋ፣ ድምፃቸውን ዝቅ ማድረጋቸው የታወቀ ነው።

ከአለታት አንድ ቀን ቱሪስት ሆቴል የተፈፀመውን ግንፃ አይረሳውም። ብረት ለበሱ ርግብ በጨዋ ደንብ ባንዜኒ ተደግፎ ሺን በመጠጣት ላይ ሳለ አስር የአየር ወለድ አባላት ግር ብለው ይገቡና መጠጣት ይጀምራሉ። ወታደሮቹ፣ አብዛኞቹ አንግዳ ጆቢርን በማየታቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳመጣጣቸው እየቦረቁ መጮኻቸውን አልቀጠሉም። ከመካከላቸው አንዱ ግን የብረት ለበሱን ማንነት ባለማወቁ አንደ ልቡ ይሳደብና ይደነፋ ጀጠሰ። ባጋጣሚ ደግሞ ባንኩኒውን የተደገፈው ከአንግዳ ጀቢር አጠገብ ነበር። ብረት ለበሱ ጩዋሂውን ወታደር አንደዋህ አያስተዋለ ቆየ። ወታደሩም አንግዳ ጀቢርን ከአንዴም ሁለት ጊዜ ገረመመው። በዚህ መሀል በአንግዳ በራስ መተማመን የተመላበት አቀማመጥ ያልተደሰተው ወታደር የቢራ ጠርሙሱን ብድግ አድርጉ ከብረት ለበሱ ርግብ አናት ላይ ክስቀመጠ በኋላ፣

«ሽንቴን ሽንቼ አስክመለስ ይዘሀት ጠብቀኝ» ብሎት ይወጣል። አንግዳ ጀቢር የወታደሩን የቢራ ጠርሙስ አናቱ ላይ አንደያዘ ይዞ ጠበቀው። ሴትኛ አዳሪዎቹና ወታደሮቹ የሚከተለውን በመገመት የሚገበብቡት ጠፍቷቸው የሚሆነውን ለማየት ትንፋሻቸውን ውጠው ጠበቁ። ታዲያ አንደተፈራው ወታደሩ ሽንቱን ሽንቱ ወደበታው ሲመለስና የቢራ ጠርሙስ ግንባሩ ላይ ሲፈነዳ አንድ ሆነ።

አንግዳ ጀቢር በዚህ ድርጊቱ ሁለት ወር ታሰረ። ወራው ግን የአየር ወለዶችን ካምፕ ናጠው። ብረት ለበሱ ርግብ ከተቆጣ አሸቢዎቹና ደጋፊዎቹ ከየት አንደሚፈሱ አይታወቅም። ሴትኛ አዳሪዎች ሳይቀሩ ባዶ ጠርሙስ አያንጠለጠሉ ብቅ ይላሉ። ደክሞኞ ሲበደሉ ይደርሳል' የሚል ስም በማግኘቱ ወዳጆቹ ስፍር ቁጥር የላቸውም።

ሁለት የአየር ወለድ ኩማንዶዎች ከብረት ለበሱ ጋር ቡጢ ገጥመው የደረሰባቸው ውርደትም በድፍን ቢሾፍቱ ሰወራት ያህል ተወርቷል። አነዚያ ሁለት ወታደሮች ለውርደት የበቁት አንዲት ወጣት ሴት በምሽት አጣንና ቡና ልትጠዚ ስትሄድ ወታደሮቹ የባቡር ሀዲድ ስር ጠብቀው ሲያፍኑዋት፣ አሪታዋን በማትለጥዋና የአንግዳ ጀቢር ጀሮ ድንገትና በአጋጣሚ ክርቀት የልጅትን የአሪታ ድምፅ

በመጮለፉ ነበር። ብረት ለበሱ ርግብ አንደዝቋላ ፈረሶች አየጋለበ የአሪታ ድምጽ ከሰማበት ቦታ ሲደርስ፣ ወታደሮቹ የልጅቱን ልብስ ገንጣጥለው በገዛ የልብስዋ ቅዳጅ አፍዋን አፍነው አብትተው፣ ሊደፍሩዋት ሱሪያቸውን ተስዝግበው በማውለቅ ላይ ነበሩ። አንግዳ ጀቢር ለግማሽ ሰዓት ያህል ከወታደሮቹ ጋር ባደረገው ግብግብ ሁለቱንም ሁኖ ቦታ ላይ ከቱኖ ስላገኛቸው ራሳቸውን ስተው ወደቁ። ብረት ለበሱ ወታደሮቹን ዘርሮ ሲያበቃ በድንጋጤ ራስዋን ለመሳት የተቃረበችውን ምስኪን ኩሪዳ ልክ አንደ አህል ስልቻ ተሸክሞአት ጉዞ ጀመረ። ልጅቱ ነፍስዋ መለስ ብላላት ሩህዋን ስታውቅ፣

«የት ነው ቤትሽ?» ሲል ጠየቃት።

አየተንቀጠቀጠችና አየተንተባተበች፣

ጠብረት ለበሱ ኸ?» ስትል ጠየቀችው።

«ኑኝ አምን፣ አንቺስ ማነሽ?»

«ስርጉት ነኝ። የአማዋይሽ ልጅ።»

አንግዳ ጀቢር ልጅቱን ተሸክሞ ቤትዋ አደረሳት። ከዚያም ፖሊስ ጣቢ ሄዶ የፈፀመውን ተናዘዘ። ፖሊሶች አንግዳ ጀቢርን የአለቱ አለት አስረውት ሲያበቁ፣ የወደቁት ወታደሮች አንዲነሱና ወደሆስፒታል አንዲወስዱ አደረጉ። ወታደሮቹ ፊጣን አርዳታ በማግኘታቸው ከሞት ተረፉ። የዘር ፍሬያቸው መገዳቱን ግን ተነገረ። በዚህም ሳቢያ አንግዳ ጀቢር አስር ቤት ውስጥ መረሳት ጀመረ። ያስ ዋያቂ ሁለት ወር አለፈው። የሶስተኛ ወር የአስር ቀኑን በጀመረበት ማለዳ ግን ያልተጠበቀ ሁኔታ ተከሰተ።

የቢሾፍቱ ድሆች አስፈሪ ድምፅ አያለሙ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ጉረፉ። ብዛታቸው ከሁለት መቶ ይበልጥ ነበር። አብዛኞቹ ጠላ ሻጮች፣ የጉሊት ቸርቻሪዎች፣ ሴትኛ አዳራዎችና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ኑሮ አለታ - ሞታ ውን የሚጠብቱ ጡረተኞች ነበሩ። ድሆቹ ስርዓት በሌለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሉነ ስለሚንቀሳቀሱ የሚናገሩትን እንኳ በትክክል ማዳመጥ አያስቻልም ነበር።

መራዓት የሚቻለው መቆጣጠሯን ዘንድ ነበር። ዙሪ በሀያ ወገን ከማለትም አያቅላቷው ተወራርቶው በመሃረና፡ ማሰሻ ላይ የሀያሊን ጉርጉ መስለው የጋሊስ ጣዘያውን ደጃፍ አጥለቀለቁት።

ያጋሊስ ጣዘያው አዘዥ ባለተለመደው የህዝብ ቁጣ ንግግር እጅግ በመገረሙ፣ የጣዘያው በረንዳ ላይ ቆሞ፣

«ምን ፈለጋችሁ?» ሲል ጠየቃቸው።

«አንግፃ ጀቢር ይፈታ!»

«አንግፃ ጀቢር ወንጀለኛ መሆኑን አታውቁም?»

«ወንጀለኞቹ ወታደሮቹ ናቸውህ» የሚል የፈዘዝ ድምፅ የጣዘያውን ሀገባ አናወጠው። ጋሊስ ግን ረዝ አላለም። ይልቁን «ተስብሰባችሁ ስሰተጋጫችሁ አንግፃ ጀቢር የሚሉት ደመሰሳችኋል?» ሲል ደነፋ። በዚህ ጊዜ አንድ ጠራተኛ አዛውንት በቁጣ የሚንተከተኩት ድሆች ረገብ እንዲሉ ከአግባቡ በኋላ ወደፊት ወጥተው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፣

«የተከበሩት አስርአለቃ፣ እኛ ብረት ለበሱ ርገብ ይቅርታ ይደረግለት ዘንድ ለመለመን መጣን እንጂ ማመጣችን አይደለም። የአማጥይቭ ልጅ ስርጉት በወታደሮች ስትታፈን አንግፃ ጀቢር ዓይደርስላት ኖሮ ይህን ጊዜ ሞታ ነበር። ወይም ገና በአሰራ አምስት አመት ዕድሜዋ ስፅንስ በተዳረገች ነበር። ይህን ስናስብ የብረት ለበሱ በአስር መማቀቅ እንቅልፍ ነሳን። አባነም ይለመትን እዚህ ያለነው እቅጠ ቢስ ደሆች ነን። ከመካከላችን ጠገበ የሚያድር አንድ ስኳኩዋ የለም ...»

ሪ ሲሉ አንግፃ ጀቢርን በዋስ ፈትቶ ለቀቀው። መቸም የብረት ለበሱ የብረት ለበስነት ዝጠመኝ አያሉ ነው። ግን ስንቱ ተተርክ ይቻላል? ይልቁን የጋህነቱን፣ ቅንነቱንና

ግልጽነቱን አለያም አፈንጋጭነቱን ስለሚያመለክቱ አንዳንድ አስቂኝ ድርጊቶቹ ጥቂት ላጫውታችሁ፣

* * *

አንግፃ ጀቢር የ12ኛን ክፍል የፈጸረሰው የማታ እየመሸ ነበር። ታዲያ ስራ ውለ ያነሞት ነበር ወደ ትምህርት ቤት የሚገባው። የትምህርት ሳለገቱ ከፍተኛ ነበር። ስለዚህ ፈት መንበር ላይ ተቀምጠ መምህሩ የሚናገረውን በጥንቃቄ ያደምጣል። ቁመቱ ረጅም በመሆኑ ግን ከኋላው የሚቀመጡ ተማሪዎች ሰሌዳውን ለማየት በመቸገራቸው ወደኋላ ይቀመጥ ዘንድ ጠየቁት። አንግፃ ጀቢር ግን እንኳንን ከተቀመጠበት ሊነሳ ቀርቶ ለጥያቄያቸው መልስ ሳይሰጥ ቀረ። ስለዚህ ከኋላ የሚቀመጡት ተማሪዎች ለክፍል ሀላፊው መምህር ከሰሱ። መምህሩ ከሱን ስምጥ ውላኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ግን ጀቢር ከተቀመጠበት ተነስቶ እንዲህ የሚል ንግግር አደረገ፣

«... የተከበሩት መምህር! አሁን እኔን በማሳቀል የተናገረው ጉሪምላ ጋጠወጥ መሆኑን ላረጋግጥሎት እሻለሁ። ቀን ቀን እያውደለደለ ማታ ማታ ሴቶችን ለመሞንተል የሚመጣ አለሌ ነው። እኔ ደግሞ መካኒክ እንደመሆኔ ቀን ቀን ከብረት ጋር ስታገል ነው የምውለው። ሞተር አውርዶ መልሶ መግጠም ምን ያህል ክብድ እንደሆነ አዚህ መናገር የለብኝም»

ተማሪዎቹም መምህሩም በእንድነት ሳቁ። ጀቢር ግን ላይስቅ ቀረ። ከልቡ ነበር የሚናገረው። ሌላው ቀርቶ ምን እንዳሳቃቸው አልገባውም። መምህሩ የአንግፃ ጀቢርን ስሚት ላለመተዳት ሊሉ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሳይሰጡ ማስተማራቸውን ቀጠሉ። መምህሩ ከወጡ በኋላ ታዲያ ከኋላ ያሉት ተማሪዎች ከአንግፃ ጋር ብሽሽቅ አማራቸው። ወጣቶቹ ወንዶች ተማሪዎች በሌት ድምፅ «ጀቢር ኩ ቢስሙ ይጣራሉ። ለቀልድ ጊዜውን ከቶ ስዮቶ የማያውቀው

t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዳ የአባቱ ስሙ ሲጠራ ድንጋጡን ወደ ሶማቡት እትጫጫ ዘወር ይላል። የህብረት ሳቅ ነበር የጠበቀው። እንግዳ እየቀለዱበት እንደሆነ ሲገነዘብ ከተቀመበት ተነስቶ የተቀመጠበትን መንበር አነሳ፤

«ስሜን የጠራውን ስው ካልጠቆማችሁ፣ መንበሩን በእሳ ሰጥ አወረውረዋለሁ። መንበሩ በኔ ላይ ከቀለደው ስው አናት ላይ እንደሚያርፍ አልጠራጠርም» ይላል።

ተማሪዎቹ ያደርገዋል ብለው ስላልገመቱ ተማሪውን አሳልፈው ሊሰጡ አልፈቀዱም። እንግዳ ጀቢር መንበሩን ከአናቱ በላይ እንደያዘ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። ሳይጠቁሙ ቀሩ። አላመነታም፤ መንበሩን ወረወረው። የአንድ ተማሪ ጭንቅላት ተፈነከተ። ከፍሉም በግርግርና በጩኸት ተመሳ። መምህራንና ዘበኞች ደርሰው ክፍሉን አረጋጉት። የፀቡን ምክንያትም ጠየቁ። በአድሚ የነቱ ተማሪዎች የግርግሩን መነሻ በቅደም ተከተልና በዝርዝር አስረዱ። የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እንግዳ ጀቢርን ወደ ቢሯቸው ወስደው ገስፁት፤ መከረውት ሲበቁ ታዲያ እንዲህ አሉት፤

«እንግዳ ጀቢር፣ መስለህ ማደርን ተለማመድ። ስላንተ ብዙ ነገር አውቃለሁ። ባላውቅህ ኖሮ ድርጊትህ ለቅጣት ባበቃህ ነበር። ንብቱህል የምልህ? አካባቢህን መስለህ ለመኖር ሞክር። ምርጫ የለህም...»

* * *

የደብረዘይቱ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሰኪር በርካሽ ይሸጣል ' የሚል ወሬ ሰምቶ ከረጢት እንጠልጥሎ ከሄደ በኋላ የፈፀመውም ስወግ የሚበቃ ነበር።

እንግዳ ስኳር ከሚሸጥበት ቅፅር ግቢ ሲደርስ የቤተክርስቲያኑ ቅፅር ግቢ በሰው ተጥለቅልቆ ነበር። ሰጥቂት ደቂቃዎች ተስፋ ቆርጦ ጥምዝምዙን የወረፋ ሰልፍ ሲያስተውል ቆየ። ሰዓቱን አየ። ማለዳ ነው።

ማምሻውንም ሊደርሰው አይችልም። ከሰዓት በኋላ ደግሞ ስራ ግቢ ነው። ስራ ጉዮ ሰስኳር ግዢ ተሰልፎ ሊውል አይችልም። እንግዳ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ከረጢቱን እንደገመሰመለ ወደ ሰልፉ ጫፍ ገሰገሰ። አላመነታም። ሰልፈኛው ሁሉ አያየው «አንደኛ» ተሰለፈ። ሰልፈኛው ይህን ሲያይ ክዳር አዳር ተንጫጫ። የተታውም ሩጫትና ጩኸት በረከተ። ዘበኛውም እንግዳን ከሰልፉ አስወጣው።

በዚህ ጊዜ የጀቢር ልጅ ምን ያደረገ ይመስላችኋል?

እጁን አጨበጨበና ሰልፈኞቹ ከመንጫጫት ታቅበው ፀጥ አንዲሉ አደረገ። ከዚያም እንዲህ ሲል ንግግር አደረገ፤

«አንድ ጊዜ አድምጡኝ! እኔ ፊት ሄጀ የተሰለፍኩት ሀግ ለመጣስ ብዬ፣ አለያም ብልጣ ብልጥ ለመሆንና የማይገባኝን ጥቅም ለማግኘት ብዬ አይደለም። ከሰዓት በኋላ ስራ ግቢ ሰለሆንኩና ሰለምቸኩል ብቻ ነው።»

ሰልፈኛው ባልተሰመደው አይነት የእንግዳ ጀቢር ንግግር በሳቅ አውካኩ። ምክንያቱም እዚያ ከተሰለፉት መካከል የማይቸኩልና ፈጥኖ ገዝቶ ወደቤቱ ሰመሄድ የማይሻ አንድም ሰው አልነበረም። ሆኖም ላበረከተላቸው የላቅ ቁራጭ ሲሉ ድርሻውን ገዝቶ ይሄድ ዘንድ ፈቀዱለት።

* * *

እንግዳ ጀቢር ትዳር ይዞ ልጅ ከወለደ በኋላ ደግሞ አንድ አስገራሚ ድርጊት ፈፅሟል። የልጁ ስም ከዚህ ቀደም በሌሎች ሰዎች ዘንድ ያልተሰማ መሆን እንደ ሚኖርበት አመነ። ስለዚህ ከመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ መርጦ «ናዕማ» ሲል ጠራት። ታዲያ ወረ ስድስት ዙትባት ሲያስከትባት ይዞአት ወደ ጤና ጣቢያ ይሄድና ክርድ ሲያወጣ የልጁን ስም ይጠይቁታል። የልጁን ስም ከመረጠ ገና ሁለት ቀኑ ስለነበር ረሳው። ቢያስብ፣ ቢሞክር «ናዕማ» የሚለው የሚለው ስም አልም አለበት። ለነገሩ «ናዕማ» የሚለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ስያሜ በቀላሉ የሚያዝ ስላልነበረ ቢረሳው የሚያስደንቅ አልነበረም። ሆስፒታል ስለሆነ ሰጊዘው አንድ ስም ነግሮ ክትባቱን ጨርሶ ሊመለስም ይችል ነበር። አንግዳ ጆቢር ግን ይህን አልፈፀመም። የልጅን ስም እንደረሳው ለመዝጋቢው ሰው ነግሮና ይቅርታ ጠይቆ፤ ልጁን ሰልፍ ለሚጠብቁ ሴቶች በአደራ ሰጥቶ ስልክ ፍለጋ በረረ። መኖሪያ ቤቱ ስልክ ስላልነበረውም ወደ ጐረቤት ደውሎ ስልኩን ላነሱት ሰዎች እንዲህ አላቸው፣

«ሚስቴን ሄዳችሁ፣ ከመዕሀፍ ቅዱስ ገፅ ሶስት ላይ የልጁ ስም በቀይ ስክሪቢቶ ተሰምሮበታልና አይተሽ ቶሎ ንገሪኝ በያት። መረፋ እንዳያመልጠኝ ፈጠን በሉ!»

በዚህ መንገድ «ናዕማ» የሚለውን የልጁን ስም አስታውሶ ክትባቱ ተከናወነ። ይህ ድርጊት ግን ሰወራት ያህል በድፍን ቢሸፍቱ እንደ ተረት እየተነገረ ቆየ። በዚያው ሰሞን እኔ ቢሸፍቱ ብቅ ብዬ ስለነበር፤ በአጋጣሚ አገኘሁትና ጉዳዩን እንደ ዋዛ አነሳሁለት፣

«ሚስትህን ወደ ስልኩ አስጠርተህ ቀስ ብለህ ለምን አልጠየቅህተም?» አልኩት።

«ለፍጥነት ነዋ። ምን ሰውጥ አለው?» ሲል መልሶ በጥያቄ አፋጠጠኝ። ከልብ ከመሰቅ ውጪ ላሳምነው የምችልበት ነጥብ አልነበረኝም። በርግጥም አንግዳ ጆቢር እንደ አእዋፍት በነፃነት የሚኖር ሰው ነበር። በትል ውስጥ ራሱን ደብቆ አያስመሰለ ከሚኖር ሀብረተሰብ ውስጥ ያፈነገጠ ነበር። አንግዳ ጆቢር ዘንድ አንድ ሲደመር አንድ ምንጊዜም ሁለት ነው።

* * *

«ናዕማ» የተባለችው ልጁ ሶስት ዓመት የሞላት ሰሞን ፈፀመ የተባለውም ለወግ የሚበቃ ነው። ፅሁቱ ፋሲካ ነበር። አንግዳ ጆቢር ከሚስቱና ከጐረቤቶቹ፤ አንዲሁም ከጉዋደኞቹ ጋር ቤቱ ነበር የዋለው። ሲያለ ሲጠጣ ተዋለ።

ተሲያቱ ላይ ታዲያ አንግዳ ጆቢር ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ይንጠራራ ጀመር።

አፋሽኮና ተንጠራርቶ ሲያበቃ «በሉ ልሄድ ነው» ይለል። ይህን ጊዜ ጨቅላዋ «ናዕማ» እየተኩላተፈች፣ «ሾት ልትሄድ ነው?» እያለች ትወተውተው ጀመር። እንዲያውም አንዲያ መናገር የምትችልም አልነበረች። «ሾት ልትሄድ ነው?» ለማለት የተወሰኑ ፊደላትን ብቻ ነው የተጠቀመችው። እንግዳ ጆቢር ታዲያ ጉንጯን እየሳመ «አሁን ተመልሼ እመጣለሁ፤ ከረሜላ ገዝቼልሽ እመለሳለሁ» ብሎ ሊሸነግላት ሲገባ፤ የሚከተለውን መልስ ነበር የሰጣት፣

«እንዴነትና፣ ቀኑን ሙሉ ታዲያ እዚህ ታሸኔ አውላለሁ እንዴ? ወጣ ብዬ እየር ልተበላ!»

* * *

ብረት ለበሱ ርግብ ትዳር ከመያዙ በፊት በጠጪነቱ የታወቀ ሰው ነበር። ታዲያ ብቻውን አይጠጣም። ኪሱ እስኪራቆት ጓደኞቹን መጋበዙ የተለመደ ነበር። ከአለታት አንድ ቀን እንደወትሮው ጓደኞቹን ሲጋብዝ ውሉ፣ መሰርገሳቸውን አብቅተው ግሮሰሪውን ለቀው ሲወጡ ጓደኞቹ ወደ መፀዳጃ ቤት ጉራ ይላሉ። እንግዳም እነርሱ እስኪመለሱ ከግሮሰሪው ደጃፍ ላይ ካለች ላንድሮቨር ላይ ደገፍ ብሎ ይጠብቃቸው ጀመር። ይህን ጊዜ የመጥ ቤቱ ዘበኛ፣ «መደገፍ ከልክል ነው። ተነስ!» ይለዋል።

«ምናገባህ!» ሲል ይመልሳል ብረት ለበሱ።

«ዘበኛ ነኝ፤ ለምን አያገባኝም!»

«ዘበኛ ከሆንክ ጥሩ፤ ከሁለት ደቂቃ በኋላ እዛዳለሁ»

«አይቻልም። አሁኑኑ ዘወር በል» ይለል ዘብ። እንግዳ ጆቢር ተቆጣ።

«አልነሳም ብልህ ምን ልትሆን ነው?» ይለዋል።

ዘበኛው ዱላውን እያወዛወዘ መልስ ሰጠ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንቆራጥጥሀለሁ!»

ጆቢር ነብር ሆነ።

«...እኔ ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ?» ይለዋል በቁጣ።

«አሱ ችግርህ ነው! የፈለከውን ሁን። አሁን ከመኪናው ዘወር በል»

« እንኩዋን መኪናውን» አለ አንግዳ ጆቢር «...አንተን ራስህን እደገፍሀለሁ!»

ይህን ብሎ ወደ ዘበኛው ሲጠጋ ጓደኞቹ ደርሰው ያዙት።

ግርግሩ ጦፈ፤

«ልቀቁኝ ልደገፈውና የሚሆነውን ልይ?» ብሉ አስቸገረ።

ዘበኛው በበኩሉ፤

«ልቀቁትና እስኪ ሊደገፈኝ ይሞክር!» እያለ ተንጐራደደ። ጓደኞቹ ግን ሳይለቁት ቀሩ። ይዘውት ሲሄዱ ታዲያ አንግዳ ዘወር ብሉ ዘበኛውን እንዲህ አለው፦

«ነገ በዚህ ሰዓት ጠብቀኝ። መጥቼ እደገፍሀለሁ!»

«እናያለን!» ሲል መለሰ ዘበኛው።

በነጋታው በርግጥም በሰዓቱ ሄዶ ዘበኛውን ይቅርታ ጠይቆት ጋብዞት ተመለሰ።

* * *

አንግዳ ጆቢር ልጅ ከወለደ በኋላ ተደባዳቢነቱን እንደቀነሰ ይወሳል። አንዳንድ ጊዜ ግን ወደ ጠብ የሚገፉ ሁኔታዎች ይገጥሙት ነበር።

አንድ ቀን፤ በዕለተ ቅዳሜ፤ ቱሪስት ሆቴል ብቻውን ተቀምጦ በጨዋ ደንብ ቢራ እየጠጣ፤ ሙዚቃ እያዳመጠ ሳለ አንድ ጥጋበኛ ጐረምሳ ድንገት ዘው ብሉ ይገባና፤

«ሙዚቃውን ሰውጪው!» እያለ ይጮህ ጀመር።

«የማን ይሁንልህ?» ይሉታል አስተናጋጆች።

«የቡጢ ማርሌይ!»

«እሱ የለንም።»

«ከየትም ወልዳችሁ አንጡ!»

በዚህ ጊዜ ብረት ለበሱ ጣልቃ መግባት ግዴታው ሆነ።

«ያኔ ወንድም፤ አንተ ያልከው ዘፈን የለም ስለተባለ፤ ወይ ቀኝ ኋላ ሁረህ ውጣ፤ አሊያ ደሞ አርፈህ ይህንኑ አፅምጥ፤ አሻፈረኝ የምትል ከሆነ ደግሞ ንገረንና የሚሆነውን እናደርጋለን።»

ጮቅ ያለው ጥጋበኛ ጐረምሳ አንግዳ ጆቢርን በቅጡ ሊያጤነው ከቆየ በኋላ፤

«ለመሆኑ 'አሻፈረኝ' ብል ምን ታደርጋለህ?» ሲል ይጠይቀዋል።

«አሻፈረኝ ካልክ፤ ጠባይህን ለማስተካከል እገደዳለሁ» ሲል በጨዋ ደንብ ይመልሳል።

«እንዴት ነው ጠባዬን የምታስተካክለው?»

ጐረምሳው አንግዳ ጆቢርን የዝቅዝቅ ተመለከተው።

«ጆሮህን በደህና ቁንጥጫ እመዘለግህለሁ።»

በአንግዳ ጆቢር በዚህ አነጋገር ወጣቱ ጐረምሳ ከት ብሎ ይስቃል። ሆዱን በሁለት እጁ ይዞ ስቆ ስቆ ሲያበቃ፤

«ይህን የተናገርከው እንዴት ብትደፍረኝ ነው!?» ሲል የወታደራዊ በሚመስል ኩራትና ድንፋታ ተናገረ።

«አሁን አትረብሸኝ! ቡና ቤቱንም አትበጥብጥ። ውጣ»

ወጣቱ ግን ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ፤

«መልካም! እዚህ ሰው መረበሽ የለብንም። እኔና አንተ ግን ደጅ እንውጣና ይለይልን!"

«አትረብሸኝ ብዬሀለሁ! ከፊቴ ዘወር በልልኝ!»

«ይለይልን ወንድ ከሆንክ ወደደጅ ውጣና ይዋጣልን!»

በዚህ ጊዜ አንግዳ ጆቢር እንዲህ አለው አሉ።

«ጥሩ! ይዋጣልን ካልክ ይዋጣልናል። አሁን ግን ራሴን ማገናናት ስለምፈልግ ከፊቴ ዘወር በል። ወይም ደጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠብቀኝና እኔ ተገናንቼ አብቅቼ ወደቤቴ ስሄድ አገረመንገዴን አነሳሥቼሏ አልፋለሁ።»

በዚህ አነጋገሩ የቱሪስት ሆቴል ተስተናጋጆች ከፋን መሰታቸውና ወጣቱ ጉረምሳም በዚህ አስቂኝ አነጋገር ንዴቱ ዘርዶለት ጠቡን ትቶ በሰላም መዘናጉቱን እንደቀጠለ ያንብራል።

* * *

አንግዳ ጀቢር በ1980 ከረምት ሳይ ህመም ቢጤ አጥቅቶት ድቱስቴስ ብሎ ነበር አሰ። ከህመሙ ተረፎሰ ገና በማገገም ላይ ሳለ፣ አንድ ቅጽማ አየር ለመቀበል ወደ አደባባይ ወጣ ያላል። ታዲያ ተደም ሲል የብረት ለበሱን ከንድ የተመሰሰ አንድ ባለጋራው፣

«ጀቢር፣ ምነው ባለቤት የለለው ሴት ውሻ መስልሽ» ሲል በሰው ፊት አሳንጠበት።

ብረት ለበሱ ይሆን ንግግር ኩፉ ሊታገስ ባለመቻሉ አንደ ነብር ተወርውሮ የተሳደቢውን ጉሮሮ ለማነቅ ይሞክራል። ግን አልቻለም። በባለጋራው ጡጫ ከፉኛ ተመትቶ የኃሊት ወደቀ። ግን አልተዘረፈም። አንደገና ተነስቶ ህመም በገዳው አትም ሊያጠቃ ሞከረ። ስሁለተኛ ጊዜ ተመቶ ተፈነገለ። በአካባቢው የነበረው ሰው የሁለቱን ተሳላሚ ወገኖች ግብግብ ለማዘጋጀት መነበብ ጀመረ። ጀቢር መሸነፉን ሲያውቅ፣ ድንገት ፍለጋ መራቱን ይኮኖኖኖ ገባ። እጁላይ የሚገባ ድንጋይ አጣ። በአካባቢው ግን የግንብ አጥር ተጠግቶ የበቀለች የግራር ዛፍ ችግኝ ቢጤ ነበረች። ጀቢር ወደዚያ ችግኝ ተንደርድሮ ሄዶ ሊንቅሳት ይታገል ጀመር። ግራራቱ ችግኝ ትምስል አንቪ ስር መስደድ፣ እሾህ ማብቀል ጀምራ ኖሮ በቀላሉ ሳትመነገል ቀረች። ብረት ለበሱ የግራር ችግኝዋን ሊነቅል ይተናነቅ ገባ። ፍልሚያውን ሲያይ መሰባሰብ የጀመረው ሰው ወደ ጀቢር አያና ይሰት ጀመር። እንዲያውም ከበቡት።

ከአንግዳ ጀቢር ጋር ይሩለም የጠረው ሰው ሳይቀር ከሱላው ጋር ተቀላቅሎ የብረት ለበሱንና የግራርዋን ትንትንት ይመለከት ጀመር። የግራርዋ ጥንካሬ ሊላ አልህ ውስጥ ያስገባው ጀቢር ከአምስት ደቂቃ ከባድ ትንትንት በኃላ ግራቱን መንጭቆ ነቅሎ ወደ ኃላው ተፈነገለ። ግንባሩ በሳብ ረሶ ነበር። ነቅሎ ሲያበቃ ግን አንዲህ ሲል ተነፈሰ፣

«ደኽ ድዊ፣ ደ ሚ ሰዘችህ»

ግራርዋን ለምን ለመንቀል እንደፈለገ ረስቶት ኖሮ ታዲያ መዲያ መረመራት። የከበበው ሰው በሳቅ ሲያውካካ ግን ጀቢር የጀመረውን ፍልሚያ አስታውሶ ግራርዋን ፍለጋ ሲንደረደር ግላጋዮች መነከል ላይ ገቡ። ተሳዳቢው ሰው ብረት ለበሱን ይቅርታ እንዲጠይቅ አግባብተውም አስታረቋቸው።

* * *

ደርግ ከወደቀ በኃላ የፈፀመው አንድ አስቂኝ ድርጊትም አለ። ጉረቤቱ የሆነ «ማሞ ታምሬ» የተባለ የስምንት ዓመት ልጅ ድንገት ከቤት እንደወጣ ሳይመለስ ይቀራል። የማሞ አባት «ልጁ ጠፋ!» ብሎ አረታውን ያቀልጣል። አንግዳ ጀቢር ታዲያ «ስመጥር ጉረቤት» እንደመሆኑ የማሞን አባት አፅናንቶ ልጅን ፍለጋ ይወጣል። አንግዲህ በድፍን ቢሾፍቱ እንደ ተልድ በየጊዜው የሚነሳው፣ አንግዳ ጀቢር የጠፋውን ልጅ ለመፈለግ የተጠቀመበት መንገድ ነው። አንገዳ በቀጥታ ወደ ቀበሌ ፅህፈት ቤት ሄዶ ድምፅ ማጉያ ተዋሰ። ከዚያም በፈረስ የሚገ-ተት ጋራ ተከራየ። ምን ቀረ? ምንምነ አንግዳ ጀቢር ጋሪ ላይ በኩራት ተቀምጦ በድምፅ ማጉያ የሚከተለውን ይለፍፍ ጀመር፣

«ውድ የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች ሆይ፣ ማሞ ታምሬ የሚባል የአቶ ታምሬ ሶስተኛ ልጅ ድንገት ከቤት ወጥቶ ስለጠፋ፣ አንዱ ግንብ ጥግ ስር ተቀምጠ እያለቀሰ ሲሆን ስለሚችል ያያችሁ አባቱቸሁ ብትጠቁሙን ምልክቱ ልጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠማጋና ኩስማና ቢጤ ነው። የለበሰው ልብስ ቀይ ሹራብ ሲሆን፤ ሹራቡ ሆዱ ላይ ተበትርፏል!»

ቢሾፍቱ በሳቅ ፈነዳች።

አያሌ ሰዎች ከየቤታቸው ብቅ አያሉ ባለፉት ፵፬ ዓመታት ውስጥ ከቶ ያልታየውን አስቂኝ ቴአትር ለማየትና ለመስማት ተጋፉ። አንግዳ ጀቢርን ለማየት ተሽቀዳደሙ። አንግዳ ጋሪው ላይ በኩራት ተቀምጠ ልፈፋውን ቀጠለ። የህዝቡን ከየቤቱ ብቅ ማለት መልዕክቱን ለማስተላለፍ አንደሚረዳ መልካም አጋጣሚ ነበር የቆጠረው። ከደርግ ውድቀት ወዲህ የድምፅ ማጉያ ልፈፋ የራቃት ቢሾፍቱ ተነቃቃች። ጀቢር ግን ከቶ ምንም የተለየ ነገር እንደፈፀመ አልተረዳም። ልፈፋውን በሞራል ቀጠለ፡

«የተከበራችሁ ክቡራንና ክቡራት የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች ሆይ!...»

* * *

ህዳር 1991 አካባቢ አንግዳ ጀቢርን በአጋጣሚ አዲስ አበባ ጉተራ አካባቢ አግኝቼው ነበር። እጁን በሀይለኛ ሁኔታ ጨብጦ እየወዘወዘ የሞቀ ሰላምታ አቀረበልኝ። እኔም ስለ ስራው ጠያየትሁት። አንግዳ ጀቢር እንዲህ ሲል አወጋኝ፤

«...ከምሰራበት ድርጅትማ ተባረርኩ። ምን መሰለህ፤ እኔ ስራ ከሆነ መለገም አላውቅም። ልቤ እስኪጠፋ እሰራለሁ። ሲያዝመኝ ደግሞ እንደ ታጠበ ቲታ ተዘረጋግቼ እተኛለሁ። ይሽው ነው። ግን ምን ሞጋ አለው። ቆዳው እንደ እንቱራራት ግላ የለሰለሰ ሽባ ቢጤ አለቃ ነው የነበረኝ። ስራ አያውቅም። መሥሪህ ብቻ ነው። ሊለሙ፤ ስራተኞች እሱ ሲመጣ በስራ ላይ ያሉ ለማዘመሰል ደፋ ቀና ያለሉ። እኔ እንደዚያ ማድረግ አልችልበትም። ከልብ መስራት፣ ከልብ ማረፍ፣ የኔ እምነት ያዚ ነው። አንድ ቀን ታዲያ ያስጦኛ ተኛቼ መጣ፣ ንዘሃ ተጋድመሃልን? የአባትህ ማለ መሰለህ?» ብሎ ደነፋብኝ። እኔ ነኝና የጀቢር ልጅ፣ ብድግ አልኩና ጉሮሮውን አነቅሁት። አጀ ላይ ሊሞት ነበር። ስበብ ሳይሆንብኝ ለቀቅሁት። ጉሮሮውን ሉቀቅሁና ሁለት እግሩን ይዤ አንደ ብርድ ልብስ አራገፍኩት። ኡስታውን ሉቀሙ ያው የአሉቱ ሉት ከስራ አባረሩኝ፤ ሰራተኞች ሊከራከሩልኝ ፈልገው ነበር። ግን ዋጋ አልነበረውም። ተባረርኩ። እንዳልኩህ ነው። የዚያን ለስላሳ እንቁራሪት አፍታዬ ሳልሰበር ቀረሁ። ለልጅ ስል ነው። ልጅ መውለድ ሌት ያደርጋል።»

«አለመደባደብ ሴት መሆን ነው እንዴ?» ስል መቸትሁት።

እንግዳ ጀቢር እንደመደናገር አለውና፤ «እንዴያ ማለቱ እንኳ አይደለም። ለአባባል ያህል ነው። አባባል ነው።»

«ለሁን ስራፈት ሆነህል ማለት ነው?»

«እስከዛሬዋ አለት ስራፈት ነበርክ። ይገርማል በእጋጣሚ... ዛሬ ተሳክልኝ። ይኼ ድራጋዴስ የሚባለው የመንገድ ስራ ድርጅት... እነዚህ የአዲሳባ አዋሳን መንገድ የሚሰሩት የውጭ ዜጎች ከዘፈቱ ደሞዜ በእጥፍ ቀጠሩኝ። እውነቴን ነው የምልህ... ዘመድ የለኝ... ምን የለኝ። ፈቱኝ፣ ሙያዬን አዩ፣ ተጠሩኝ። ነገ ስራ እየጀመርኩ ነው። እንዲያውም አሁን ወደቢሾፍቱ ለመሄድ ስድሳ ቮየር አጠቃቀስን እየጠበቅሁ ነው ያገኘሽኝ።»

«ልጅህስ እንዴት ናት?» ስል ጥያቄዬን አራዘምኩ።

«ናሰማ ልጅ ጉብዝ ተማሪ ሆናለች። ግና አፈት ኅመትዋ ቢሆንም የሰውኒቲን ከባሰሎች በመሰሰ በእንግሊዘኛ ታንበለበልልህለች። እኔን ከትወደኝ ድግሞ ጉድ ነው። ያለኔ መኖር ከቶ አትችልም። ቱንጀናሞስ ደግሞ ጠላዲትን መለእስ መስላለች።»

«ላለቤትህስ?»

«ያዝኑ ናት። ምን ትሆናለች ዘለዉ ነው? ዘርግዋ ከስራ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተባረርኩ ስሞን ውለሎ ሀሉ ማልቀስ ሆኖ ነበር። ሴቶች እንዲያ ናቸው። ፃሚትና ለቅሶ ይወዳሉ። ዛሬ ስረ አንዳገኘሁ ስነግራት ደግሞ አንድ ሳምንት ሙሉ ያለማቋረጥ መሳቋ የማይቀር ነው። ሴቶች እንዲያ ናቸው። መሳቅና ዘርላ ማንጠልጠል ይወዳሉ። ገንዘብ ሳይኖራቸው እንዲያው ቦርላውን አንጠልጥለው ቢሸጡት አፋፍ ላይ አንደበቀለ አክርማ መወላወዘ ይወዳሉ።»

በደማቅ ፈገግታ ተዋጥሁ። እንግዳ ጀቢር አልተለወጠም። ብረት ለበሱ ርግብ!

ሻለ ታሪክ




ትጠጡ፣ ጠጡ


አሸቱ ተፈራ

መጠጥ የሚባለው ብዙ ነው ዓይነቱ
በኔ በኩል ግና፣ ባልኩሉ ላይ ብቻ ይሆናል ትኩረቱ።
ከጌሾ ከብቅል ከአሀል ዘር አወጣጥኑ
ከሚሉቱ ቀምሞ ድንት ስምም ሰጥቶ፣
ለጠጭ ያቀርበዋል አጣርቶና አስማምቶ።
የጠጪው-ም ባህርይ ይለያል በብርቱ
እንደየተለምዶው እንደየ ስሜቱ።
አንዳንዱ ሲጠጣ አምርሮ ያለቅሳል
ሌላኛው ሲጎነጭ ፍቅር ያስታውሳል።
አንዳንዱ ፉት ሲል ድፍረት ይጨምራል
ሌላው ሲሰረግብ ቀልዶችን ይፈጥራል።
ለው ይጠጣ አይጠጣ የሚለው ክርክር
ከዮንት ጀምሮ ያለነው በምድር።
ካያም የሚባለው የፋርስ ፈላስፋ
መጠጥ ጠጡ ይላል አእምሮ እንዲሰፋ።
እርሱ ያለው-ን ታል ሳላበዛ ባጭር
ቀየሶ አሰፍራለሁ እንዲሆን ምስክር።
«ቁራሽ ዳቦ በቀኝ በግራ ብርሌ
ትንቡሽቡሽ ያለች ልጅ ባለ መልካም ዳሌ፣
አነዚህ ሶስቱቹ ሲኖሩ አጠገቤ
አረካለሁ በጣም መንፈሴን መግቤ።
ያሻህን ተናገር ወዳጄ ወገኔ
ብርሌ ስጨብጥ እጅግ ይቀርበኛል አኔነቱ ለኔ።»

t.me/OLDBOOKSPDF



ሄዋን ሰሳሳተችኝ



ትንሹ እንጆሪ

ከወሰን ይሄይስ

አሉላችሁ ትልልቅ ሆቴሎች፣ እንኳን በልተውባቸው ስለታዩ የሚያጠግቡ የሚመስሉ። በእምነ በረድ የተንቀለቀለ ህንፃ! የሰራ አካላቱ ይላም የመሰለ፣ ይላስ የመሰለ፣ ሞልታል ህንፃ ሆቴል የተባለ። «አላመጣው የለኝ አልቀላውጠው ...» አለ አሉ ገጣሚ። ጊዜ እንጂ ህንፃን ያመጣው፣ ሆቴልን ያበዛው ... ተይዞ ነበር፣ ተሰቅዞ። እኔን ምን ቸገረኝ — ስለአመጣጣቸው። ወይ አልበላባቸው፣ ወይ አልጠጣባቸው፣ ወይ አልተኛባቸው። ትንሽም ጥቅማቸው ድሃ መቅጠራቸው፣ ዋነኛው

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቅማቸው ለባለቤታቸው። ደሞ የዋጋቸው - የአተማመናቸው። ይበላ ይመስል እምነ በረዳቸው፣ ይጠጣ ይመስል መስተዋት ደጃቸው። ይዟ ትልቅ ሆቴል ጠ/ነኛ አይደለም፣ ድሃ ድህሙን ሰጪ አያስተናግድም። ሮበት ይመስል ብረት ይበላዋል፣ ማገኢያውን ቧካውን ይኖረድረዋል። እና በዋጋው ውስጥ አብሮ ያለዋል።

የአስተናጋጆቹ መልካም ትህትና «ምን ልታዘዝ» ሲሉ ሳቅ - ሳቅ ይሉና «ሚኒ» ያቀርቡና ይሄም አንደ ምግብ አብሮ ይሰላና፣ መቀመጫው ወንበር ትንሽኬ ነውና አሱንም አንደወጥ አብሮ ያስባና ... ለሁኔታው መከፈል፣ ሽር ጉዱን መብሳት ምግቡ ይቀርና - እናሳ ነውና!! ምን አይነት ግሩም ነው - ሀብታም ሆድም የሰውን ያሰው ሀገምንት የድሆች ብቻ ነው? ... ከጥራቱ ይሆን ከምግብ አይነቱ? ሀብታም ከጥራቱ፣ ድሀ ከበዛቱ? የወደቀን ማነሳት የበዛንን መቅጠር፣ ትልቅ ሆቴል መክፈት የሀብታሞች ጅምር፣ የሀብታሞች ምክር። ትልልቁ ሆቴሎች ከሩቅ ይጣራሉ፣ የሩቅ ኢንቨስተሩን ያስተናግዳሉ፣ ምኞት ይሰጣሉ፣ ያበረታታሉ፣ ተሰፋ ይሰጣሉ፣ በገምትም ቢሆን ገቢውን ያሳሳሉ።

አንድ ነገር አለ። ብዛት ጥራት አይደል፣ ብዛት ድከመት አይደል፣ ብዛት ሽንፈት አይደል። ግን ድሃ ብዙ ነው፣ ድሃ ደክማ ነው። የድሃ ጥናው ድህነቱ ከንቱ ምኞቱ ሲሆን ይችላል። ሀብት ባይኖረው ጉልበት አለው። ስለዚህ የራሱን መንገድ ከተከተለ ዋጋ አያጣበትም። ያድሃ ዋናው ጠላቱ ከንቱ ቅናቱ ሲሆን ይችላል። ይሄ ሀብረተሰብ በስርዓተ - ግዙቱ በአኩልነት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑ አያታወቀ፣ የዚህ ሀብረተሰብ አባላት ልቡና ለመበላለጥ በሚሽቀዳደሙ ጥቂት ሰዎች ግላዊ ብልጫና የተጋለበና የተኩላመነ መሆኑ አየታወቀ፣

አብሮም ሀብትና ድህነት አንደአፈጣጠራቸው ተፈጥረዋልና እንደ አጠፋፉቸው እንደሚጠፉ የህሊና ተሰፋ መኖሩ አየታወቀ፣ ተወነጃጅሉና ተናንቆ የትም እንደማይደረስ አየታወቀ፣ ስልት ቀያሾች በየአቋራጭ መንገዶቻቸው ድህሙን ሀብታም ሀብታሙን ድህ ሲያደርጉት አየታየ ... ምልዐተ - ድሃ ግን በምቀኝነትና በቅናት አስር ቤት ይማቅቃል። ለነገሩ ድሃም እውነት አለው። ምቀኝነትም ሆነ ቅናት የብሶት መግለጫው ነውና!

የጉልት እንጀራ ላስቲኩን ለብሶ መንገዱን ከትሮ በየአላፊ አግዳሚው የድሃ ዓይኖች ሲበላ መዋልና ማምሸት አያስደስተውም። እሱም እንደ ሆቴል እንጀራ እንከብካቤ ተደርጉለት፣ ማስታወቂያ ተበጅቶለት፣ አስተናጋጅ ተቀጥሮለት፣ ተሽሞንሙኖ መቅረብ ሊፈልግ ይችላል። ይሄ ቅናት ነው። እንጀራም ይቀናል ማለት ነው - አንደባለቤቱ። አንዳንዶቹ የጉልት እንጀሮች ደሞ የሰፈር - ድሃ ዜጉች ባልታጠቡ እጆቻቸው ሲያገላብጧቸው ይበሳጫሉ፣ ይሸነሽናሉ፣ መልካቸው ይለወጣል። በዚህም አይደሉቱበትም። ምንም እንኳን እንጀራ በራሱ ጥንታዊ ዘመን አመጣጡ ከአፈር መሆኑ ቢታወቅለትም ያ ዘመን ሩቅ ነውና ከአፈር ጋር ተለያይቷል፣ አፈር ለእንጀራ ቀሻሻው ነው - አሏራው። ስለዚህ ማንኛውም እንጀራ አፈር ሲነካው አይወድም። ይሄ ከንቱ ምኞት ነው። ከእንጀራው የበለጠ ባለቤትየዋ ተመኝታ የምትለውጠው የሳትም።

ከምድርም እድላም አለ። ዋና ዋና ከተሞች ሁልጊዜ እየበለፀጉና እየታደሱ ይሄዳሉ። አስከሙቹ ድረስ መሆኑን ማንም አያውቅም። እንዲያውም ገጠሮች ነዋሪዎቻቸውን እያስፈነጠሩ ወደ ከተማ ባጉረፏቸው ቁጥር ከተሞች ይበልጥ እየደመቁ ይታያሉ። ምናልባትም ከብዙ ጊዜ

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ የሰው ልጅ ህይወት የተጀመረው በከተሞች ውስጥ ነው ተብሎ ሊታመን ይችላል። ገጠር ከወደመ፣ ነዋሪው ከጠፋ፣ ከተማ ከአደገ፣ ነዋሪው ከሰፋ፣ ምድር በሙሉ ከተማ ትሆን ይሆናል። ማን ያውቃል? እና ስለዚህ በምድር ረጅም እድሜ ውስጥ ገጠር ከጥንትም ያልነበረ ሊመስል ይችላል። ታዲያ በዚያን የሩቅ ትንቢት ዘመን ዓይን ይህን የዛሬዎቹን ሆቴሎች ብዛትና ጥራት ሲያዩት ምን ያክል ያንስ ይሆን? ምናልባት የሰው ልጆች ብዛትና የምግብ ፍላጐት የሚገታበት አንዳች አይነት ጥበብ የማይመጣ ከሆነ ሆቴሎች ዓለምን ለማጥለቅለቅ ሳይችሉ አይቀሩም - እንዲያውም ላይገደዱ አይቀሩም።

ዋናው ነገር ዛሬ ስለሆቴሎች፣ ባለሆቴሎችና ተገልጋዮቻቸው ይባባሉበት። የጥራትና የብዛት ጉዳይም ከገበያ ሌላ ጭኛ የለውም። ምንም እንኳን ባለሆቴሎችና ተገልጋዮች በቁጥር አናሳ ቢሆኑ የሀብት ብዛታቸው የብዙ ብዙ ያደርጋቸዋል። በባለፀጐች መንደር ጥራት ብዛት ነው። ንብረት ስም ውሽት ነው፣ እድልም ቅጥፈት ነው፣ ስራም ማጭበርበር ነው። ብቻ ግን በአንድ በኩል ዓለም ብዙ ለመብላት የሚታገሉባት ትልቅ ሆቴል ነች። በሌላ በኩል ለመኖር የሚሞደቁባት አንድ እንጀራ ነች። ያውም የጉሊቱ! ያውም የቂርቆሱ ... ከዚህ በላይና በዚህ በታች ዓለም መኖሯም አለመኖሯም መታወቁን እንጃ።

የትልልቅ ሆቴሎች ተገልጋዮች የስራ ጠባይ የተለያየ ነው። ከዚህ ውስጥ ደላላው፣ ጡረተኛው፣ ነጋዴው፣ ጆሮ ጠቢው፣ ፅሁፍ አዟሪው ... ይገኙበታል። የሌላ አገር ሰዎችም ይስተናገዱበታል። ስደተኞች፣ ልዑኮች፣ ወኪሎች፣ ገብኝዎች፣ ሰጋሽች ... ይገለገሉበታል። በአቅራቢያ የሚገኙ የታላላቅ መስሪያ ቤቶች አለቆችም

ይጠቀሙበታል። መቀጣጠሪያቸው፣ ሻይ መጠጫቸው፣ ስራ - ነክ ጉዳዮች መነጋገሪያቸው፣ የመነቃቀፊያ - የመደጋገፊያ ሀሳብ ማመንጫቸው፣ የአቋም መግለጫቸው፣ ጋዜጣ፣ መፅሄት መቀባበያቸው ... ያው ሆቴሎች ናቸው። የትልልቅ ሆቴል አስተናጋጆቹ፣ ከሌትም ከወንድም መልክ - መልካሞቹ፣ አምሪው ተኳኩለው እንደ ሆቴሎቹ ፈገግታ አይሰስቹ።

የአንድ ሆቴል ትልቅነት የሚታወቀው እንደተርከካሪው መሆኑ አይጠረጠርም። የማበሳለጫ እንደ ጉዳይ አገልግሎት አቀራረብ መሆኑም የታወቀ ነው። የእንግዳ መቀበያ፣ የመመገቢያ፣ የመኝታ፣ የመፀዳጃ፣ የጥበቃ ... ይሉታል። በአንድ ትልቅ ሆቴል ውስጥ ለመፀዳዳት የቆመ ሰልፈኛ ማየት ግን እያድርስ ነው። ትልቅነቱን በአንዴ ለመናድ የሚተናነቅ ሀሳብ ያስከትላልና!


መለስተኛ የሆኑ ምግብ ቤቶችም ቢሆኑ ጉዳቱ አለባቸው። የመታጠቢያ ክፍላቸው ሰልፍ የምላ ሰዓትን የሚሸማ ሆኖ ይታያል። ስራተኛ ከስራው ሰዓት ቀደም ብሎ የሚወጣበት ምክንያት ቢሻ አላንዳች አይደለም። ይሄ የሰዓት ሌብነት ባይባል ይሻላል - የምግብ ጉጉት እንጂ! ምክንያቱም የምግብ ቤቶች አገልግሎት ከሰራተኛው ከምላ ሰዓት ጋር አልተደራደሩማ!

ይሄ በዋና ከተሞች የመሰባሰቡ ጉዳይ የሆቴሎች ብቻ አይደለም እንጂ ፍርሃት ነው። ሀብታም ሲደፍርም ሲፈራም ወደር አይገኝለትም። የተፋፈገ፣ በሰው የታጨቀና አንድ አይነት ችግር ያለበትን አካባቢ ላይወዱት አይቀሩም - ምናልባት ጉላ ብለው ለመታዘዣና ለመከበር ብለውም ይሆናል። ሆቴል ደሞ ወንደላጮችን በአሉበት የሚያቅይ ለመሆን ይጣጣራል። አገዳንዴማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከትዳርም ያፈናቅላል።

ክፉውን ደጉን የምታላይና የምታለማ፣ የምታላስብና የምታስፈፅም ምንድናት? በዓለም ላይ በየቤቱ፣ በየቡና ቤቱ፣ በየሆቴሉ የማትታጣ ወይም ስትታጣ የምታስጨንቅና የምታንቆራጥጥ ምንድናት? ማንኛውንም ሰው ልትደልልም ልታበሳጭም የሚቻላት ታላቋ ጉዳይ ምንድናት? ሀይወትን ላይቀር ለመቆጣጠር የሚቻላት ለዘብተኛ መሳይ የነፍስ ጠባቂ ምንድናት? ገበሬው፣ ምሁሩ፣ ነጋዴው፣ ሰራተኛው ያታም ሆነ እድሜ ሳይለየው የሚጣጣርላትና የኔ የሚላት ምንድናት? አንድ እንጀራ ንብዝ! ትእግስቱም፣ ችሎታውም ለአንድ እንጀራ የሆነበት ሰው አይስታትም። እንጀራን የያዘ ደሞ አብሮ ይታወሳል። ሆቴል የዚህ ጓዝ ነው - መሰብ። ሆቴል እንደሰው ነው - እንጀራ እንደ ሆድ። አናም ይችን የዕለት አንድ እንጀራ ፍለጋ ሆቴልን ስመቃኝት መገረድ አለ።



በጠፉ የተጠጋ ልብ

ካሳሁን ወልደዮሀንስ

ስጋና ደም ላይኖርህ፣ አጥንትህ ከስጋ፣ ስጋህም ከደም ላይዋሃድ፣ ደምህም ከመንፈስ ላይዛመድ በአስትንፋስህ ሽውታ ነፍስ የምትዘራ ከቶ አንቱ ምንድን ነህ? መንፈስ ነህ እንዳትባል ስለመናፍስትትህ በቀመር ተሰልቶ፣ በድንጋጌ ተሰፎ የተገኘ አንዳችም መረጃ የለም። ነገር ግን ፍጡራን ከተፈጠሩ ጀምሮ በልብና በሆም ውስጥ ተሸኑተህ በገዛ ራስህ የመኖርና የማኖር ስልጣንህ ከቶ አላቋረጠም።

ከፍጥረታት ሰራት ወደ የትኛው እንደምታዘነብል የታወቀ ነገር የለም። እግር የለህም ትራመዳለህ፣ ክንፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

የለህም ትበራለህ፤ አትዳሰስም ግን ትዳስሳለህ፤ ነፍስ የለህም አስትንፋስ ትረጫለህ፤ መኖሪያህ አይታወቅም ሆኖም በደም ውስጥ ሰርገህ በልቦና ጓዳ ጉድጓዳ ትፈነጫለህ። አስህ ሲሉህ ትርጉም የሰሽ ሆነህ ትሰወራለህ፤ ሲያቸህም እንደ ማለዳ ጀንበር ፈክተህ ዝማሬ መላዕክትን ታንቀረቀራለህ። ሲልህም እርግማን ሆነህ የጭንቃ ጭንቆችን ተራራ ቆልለህ አፈር እየማሰክ ከርሰ መቃብር ትቀፍራለህ።

ፈጣሪ ‘ክ እንዳትባል ምድርን ስለማነፅህና ሰውን ከጭቃ ጠፍጥፈህ ስለመፍጠርህ አለዚያም ከዋክብትና ፕላኔቶችን፤ ፀሐይና ጨረቃን በሀዋ ላይ እንደጠፍ ስለመዝራትህ የተባለ ነገር አልተሰማም። በምግባርህ ግን ይህን ሁሉ ለማድረግ የሚለንህ አትመስልም።

ቀን ከሌሊት በአፅዋፍ ዝማሬ መሃል በየዛሩ ላይ ተንወለዋለህ ፍቅር ነኝ እያልክ ታዜማለህ፤ በውሃ ኩሬዎች ከእንቁራሪቶች ጋር ታንቋርራለህ። ከዓሶች ጋር ትዋኛለህ፤ በአንበሶች ዋሻ ውስጥ ታግሳለህ፤ በጀግና ልብ ውስጥ ትደነፋለህ፤ በመንግስተ ሰማያት ከhሩቤሶችና ከሱራፌሎች መሐል ሆነህ ዝማሬ መላዕክትን አየዘመርክ ጠብ እርግፍ ትላለህ፤ በክብረ ነክስታት ክዘፋኖቿ የገቢናት መንበር ላይ ተኮፍሰህ አሸቀልቁለህ ትመለከታለህ።

ነገር ግን በሊሶች ውስጥ መስለህና ተመሳስለህ አለው እያልክ ከመጮህ በቀር አካላዊ ግዕታህ ምን እንደሆነ አይታወቅም። እዚህ ላይ አንተ ባትናገረውም ወሬተኛ ነህ።

በተናዳፊ አባቦች ክብ ለክብ፤ በቀበኛ አይጦች ጉድጓድ ለጉድጓድ፤ በመርዘኛ ጊንጦች ሚዳ ለሚዳ፤ በተተናኳይ ተኩላ ዱር ለዱር ስትቅበዘበዝ አንዳችም ቀን ስለ አርኩሰነትህና መሰሪነትህ ካፍህ ቃል ሲወጣ የተሰማበት ጊዜ የለም። ፍጥረታትም ያንተን አፀብ ድንቅ ግዕታ

አያነሱ ሊያንቆለጳጵህ እንጂ ሊረግሙህ አልደፈሩም።

ሙዚቀኞች በሙዚቃቸው፤ ደራሲያን በድርሳናቸው፤ ሰዓሊያን በስዕላቸው ስለደግነትህ፤ ስለታላቅነትህና ስለረቂቅነትህ እንዴን ከሌላው ሳያቃጉ ልስላሴህን ብቻ አያጋነኑ ስላንተ የማይገሰስ ግርነት ይሰብኩልሃል። ሁሉ አብረቅራቂና ተስረቅራቂ የልብ ውስጥ ጌጥ እንደሆንክ አድርገው አታሞ ይደልቁልሃል። ማነኝ? ብለህ አራስህ ለራስህ መልስ ትሰጥ እንደሁ እንጂ ሊቀፍጥረታትም ቢሆኑ ወጥ የሆነና ሁሉንም የሚያስማማ ቀመር ሊያገኙልህ ከቶ አልተቻላቸውም።

በዚህ ወደር በሌለው ውስልትናህ የፍጥረታትን ልብ አያማለልክ የጠራ ደም እንዳለህና ንፀህ የምንጭ ውሃ የመሰለ ገፅታህን ብቻ አያነሳሱ ቢያሞካሹህና ቢያወዳድሱህም ከዲያቢሎስ ጋር የባህርይ ገምድና እንዳለህ ገሀድ ያልሆነ አይምሰልህ። በዲያቢሎስ ጥቁር ልብ ውስጥ ክፋትን የማፍቀር ሚስጥር መኖሩ ተደርሶበታል። አንተ ግን ወተት በሚያመነጭው ምላስህ ማር በሚያፈልቀው አንደበትህ መሃል መርዛም እባህ መኖሩን ትንፍሽ ብለህ አታውቅም።

ደም የመጠማት ፍቅር፤ የመግደል ፍቅር፤ የተንኮለኛነት ፍቅር ያንተው ስራት መሆናቸው ያሉበትና የኖሩበት ይናገሩት እንጂ አንተማ ገሐዱን አውነታ ሸሽህ ጉድህ እንዳይፍረጠረጥ ቀን ከሌሊት በመባዘን ላይ ትገኛለህ። በሩህሩህነት ጥላ ስር ተጠልለህ ዓላኝ ቅቤ አንጓችነትህ ክፍጥረታት ጆሮ እንዳይደርስ በነናናው ምትህትህ አንደበቶች እንዳይናገሩ ምላሳቸውን ቆልምመህ፤ ክፉ እንዳይወጣቸውም በጌትነት አርካብ ላይ ተፈናጠህ ሱሌህ እንዲሆኑ አስገድደሃቸዋል። ካንተ የገቢናት ስልጣን አፈንግጠው አልገዛም በሚሉ ፍጥረታት በአደባባይ የሚያቀርቡትን ስሞታ እያስተባበልክ ሻካራ ጉንህን

t.me/OLDBOOKSPDF

በተቅለብላቢ ምላስህ እያለሳለስክ ፍጥረት ሁሉ ላንተ እንዲንበረከኩና በፈርጣማ ክንድህ እየደቆስክ ስላንተ ከፉ እንዲያወሩ ከአግርህ በታች ረግጠሃቸዋል። የሚያወሩ ቢኖሩ እንኳ ይህን ሊያደርግ የተፈቀደለት ፍቅር ሳይሆን አፍቃሪ ነው እያልክ ባንተ የመጣውን ጦስ በሌላው ላይ እያላከክ መኖርህን ገፍተህበታል። ይህን የሚያምታታ ወንጀል ከኮግስረጃው ቢቀርብልህ ያንተን የክስ መዝገብ ለመዝጋት ይረዳልና ከላቫህን ለመክሰስ እንዳትበቃ እነሆ አማኝነቱ ይሽውልህ።

ቢረሳ ቢረሳ ‘አቴሎ’ በተባለው ቴአትር ውስጥ የሰራኸው በደል የሚረሳ እንዳይመስልህ። በዚያ ምድር ቤጠበው የዴዝዲሞናና የአቴሎ አብረቅራቂ ፍቅር መሃል ኢያጐን የመሰለ መርዘኛና ጥላቻን አፍቃሪ ሰይጣን አስቀምጠህ ያንን ሁሉ መዘዝ ያስከተልክ አንተው እንደሆንክ በመድረክ በተዘራው ነፍስህ አራስህን አጋልጠሃል። አቴሎን በፍቅር አሳውረህ፣ የህሊናውን ሚዛን አዛብተህ በሚወዳት የነሳች አፍሪቃው ላይ የሞት ሾተሉን ሲመዝና ፍቅሩን በልቧ ጉያ አንደያዘች ወደ ሞት ሲሸኛት በዴዝዲሞና ላይ የወረደውን መዓት ሰመታደግ አንኳ ሙከራ አለማድረግህ ከማስተዛዘብ አልፎ ቢያወቃቅስና አንተን ቢያስወግዘህ የትኛው ልብ ነው አግባብ አይደሰም ብሎ ላንተ ጥብቅና የሚቆመው?

በእውነቱ በደልህ ክበደልም በላይ ነው። በዚያ ብልጭልጭ ነገር ግን እጅግ መራራ በሆነ ውስጣዊ ስብዕናህ ፍቅርን ከፍቅር ጋር ስታገዳድል ታሪክ እጅ ክፍንጅ ይሠሃል። እርስ በርስ እየተቃረንክ ከደሙ ነባ ነኝ ስትልም ተደምጠሃል።

እየሱስ ክርስቶስ ስለፍቅር ብሎ ለፍቅር ሲሞት አብረኸው ለመሞት አልደፈርክም። እርሱ በቃራኒዮ ነፍሱን አሳልፎ ሲሰጥ አንተ ግን በፍርሃት አግሮችህ ሽቅብ አያየህ ቁልቁል ፈረጠጥክ። ጌታ ‘ኤሎሄ! አሎሄ!’ አያለ ሲማፀንና ጮኮ በጦር ሲወጋ አይኔን ግንባር ያድርገው! ብለህ እንዳላየ ለመሆን ሞክርክ። ቅዱስ አስጢፋኖስ ሲወገርም ሞትን በሚፈሩ ነገር ግን ግድያን በሚያፈቅሩ አኩያኖች መሃል ተሸሽገህ የመውገሪያውን ድንጋይ ማቀበልህ አንሶ ይወገር! አያልክም ጮህክ።

ውበት ሆነህ በውበት መግልህና መገዘትህ በራሱ ያስወገዘበትም የታሪክ አጋጣሚ ፍንትው ብሎ ታይቷል። ከሊዮፓትራ ባንተ ስር ተጠልላ በስልጣን ፍቅር በጣ ባሏ ላይ ጦርነት አስከማወጅ ደርሳ ለሞት ስታበቃውና ስንቱን ንጠዛዝት አያራደችና አያሽመደመደች በኋላ በኣፍስ በላነት ስትታብዝ አንተ ግን በኩራት ተክፍህ ትሳሰት እንደ ነበር ተመስክሮብሃል።

በዚህ ጠሰኛ አስማትህ በስልጣን ፍቅር ውስጥ ራስህን አጉልተህ ጦርነት ትቆሰቁሳለህ፣ በገንዘብ ወዳድነትና በሃብት አምላኪነት ስም ዘርን ከዘር ታጫርሳለህ፣ በሃገር ፍቅር ስም ሃገሮችን ከሃገሮች ታባላለህ፣ ብሔርን ከብሔር ታናጫለህ፣ በሀይማኖት ስም ለውን ከለው ልጅ ታጨፋጭፋለህ። በጦርነቶች መሃል አይሂችሁ እያልክ ወኔ ከመሆን በቀር ጣቶችህ የመሳሪያ ቃታ ለመሳብ የሞክሩበት ጊዜ የለም። ወደር በሌለው ፍርሃትህ ከማዶ ላይ ሆነህ በሞት ፊት አሙራሪነት መንበር ላይ ተክፍለህ የነዛዙ ዶሴ ታግላብጣለህ፣ ነፍስ ስታሻቅብና ደም ከአፈር ሲደባለቅ ዳኛ ሆነህ ጥፋተኛውን ለመቅጣት ትነክለኛ ነኝ የሚለውንም ለማራራት አልሞክርክም።

በዚህ የነፍስ በላነት ባህርይ ማንም ሊወቅስህና ሊሞግትህ የደፈረ አለመኖሩ አርግጥ ቢሆንም በሁለት ቢላዋ የምትበላ ቀልማዳ መሆንህ ተግባርህ ራሱ በቂ ምስክር ነው። ፍቅርን መስለህ በፍቅር ውስጥ መኖር

t.me/OLDBOOKSPDF

ታውቅበታለህ፣ በርኩሰት ውስጥም የርኩስነትን ፍቅር ፀንለህ የጉራማይሌ ዝብርቅርቅ ገፅታህን ገዛድ ታውጣለህ።

እንዳትከሰስ ከሳሽ ነህ። እንዳትወነጀል ዳኛ ነህ፣ እንዳትታጠል ነበልባል ነህ። ፍቅር ነህ ብለው ሲያፈቅሩህ ነፍስን ከስጋ እየሞገትክ፣ ቅንነትን ከቅናት እየቀየጥክ የስቃይ ምክንያት ትሆናለህ፣ ስትጠላ እንደ ጥላ እየተከተልክ በደጉትና በትሁቶች የልብ ጓዳ የውዳሴና የሙጋሴ ፅናፅል ታንሿሿለህ። ሲንቁህ አሾልቀህ እየገባህ በቤተመቅደስ ከቀሳውስት ጋር ዳንኪራ ትረግጣለህ። ሲርቁህ የገዳማትን ዓለቃ እያስተባበርክ ሱባኤ የገባን መነኩሴ ከዓላማው እንዲዘናጋ የማጥመጃ መረብህን ትዘረጋለህ። በሁሉም ነገር ውስጥ መስለህ ትገኛለህ፣ አራስህን ከማንኛውም ነገር ጋር ታስማማለህ፣ እንደ ሳሙና ትሙለጨለጫለህ፣ እንደ አስስት ትለዋወጣለህ።

አውነተኛና ፃድቅ መስለህ በውበት ነፀብራቅ ተሸሞንሙነህ ልብን እንደ ቅቤ የማቅለጥህን ያህል ራስህን በጥቁር ሻሽ ከፍነህ አንደበት የመለገም ትንግርትህ በመፅሐፍ ተዕፎ ለእማኝነት በቅቷል።

እንዳይሆን የለም፤ ሁሉም ሆኗል። አያልፍ የለም ያለፈውም አልፏል። አንተ ግን ማለቂያ የሌለው ታሪክህ እንደቀጠለ ነው። ሙታንን ቀብረህ በአዲስ መንፈስ መለምለምህ አላቋረጠም። ማደሪያ ስለማታጣ ጉዞህ ያለስንቅ ነው። የሚገርመው ግን ዛሬም ቢሆን ብዙ ልቦች አንተን ፍለጋ በመዋተት ላይ መሆናቸው ነው። ነገር ግን በፍለጋ ለሚቃብዙ ነፍሶች መልስ አትሰጥም። ለተጠሙትም መጠጥን እንጂ እርካታን የማስገኘት አቅምህን አመንምነህ አድሏዊ ሆነህ አየኖርክ ነው። የማያልቅ ሀብት ይዘህ ለአንዱ በማንኪያ እየሰጠህ ለሌላው ባካፉ ትሞጅርለታለህ።


ያን ምስኪን ወዳጀን የዓይን ፍቅር፡ በሚሉ ደደብ

የፍቅር ልክፍት ለክፈህ በጠራራ ፀሐይ ከጉዳና ላይ ገትረኸው ሞቱን ስታስመኘው ከመቼውም የበለጠ አገኘሁብሃለሁ። ምን ቢበድልህ ነው እንዲህ ያለውን የፍቅር መጋኛ ያስመታኸው? እንዳንዴ እንደ በሽታም ትሆናለህ ቢባል አውነት አለው።


ብቻ አግዚአብሔር ይይልህ! ያንተ ጨካኝነት ገሐድ የወጣው አርማዬና ብቸኛ መታወቂያዬ "በጦር የተወጋ ልብ" ነው ብለህ አዋጅ ያስነገርክ ለታ ነው። በጦር ተወግቶ ተግባሩን በትክክል ማከናወን የሚችል የትኛው ልብ እንደሆነ አዋቂ ነኝ ብለሃልና ሚስጥሩን አንተው ፍታው። ከዚህ በተረፈ በምድር ላይ ፍፁማዊ የሆነ ፍቅር ይኖራል የሚል ተስፋ ለመኖሩ አጠያያቂ የምታደርገውን ይሆን ዘንድ ዱስታውን እዚሁ ላይ ቢበቃህ ይሻላል። አለዚያ ይህን ባህርይህን እንደያዝክ የምፅዓት ቀን ከተፍ ይልብሃል። በዚያን ጉለት ወዮልህ!

መጣጥፍ

t.me/OLDBOOKSPDF







ለድንበር ግጭት - ሰላማዊ መፍትሄ



የስግዚአብሔር ስጦ?

ዮሐንስ ዘለቀ

ወንድ እንደመሆኔ የሴት ልጅን ውብት አደንቃለሁ፤ ዕድሉ ገና ባይገጥመኝም ውብ ሚስት ትኖረኝ ዘንድም እመኛለሁ። ግን ችግሩ ደግሞ ከውበት ጋር መልካም ባህርይ ጥሩ ጭንቅላት፣ አሊያም መጣጣምና መግባባት የሚባሉ ተከታዮች ስለሚኖሩ ብዙውን ጊዜ ፍላጐት ግቡን ሳይመታ ይቀርና ህይወት እንደተዘበራረቀች ትቀጥላለች።

እኛ ወንዶች የውበት ዛር የፈሰሰባት ሴት ልጅ ስንመለከት «ይህቺን አግዚአብሄር እጁን ታጥቦ ነው የሰራት» ማለታችን መቼም የተለመደ ነው። በርግጥ እንዲህ ማለት ኩሉ ክፋት የለውም። ምክንያቱም ውበ ነገር ሁሉ መልካም ነው። ማንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ውብ ሆኖ መፈጠርን ይመኛል። ግን ደሞ ሁሉም ውብ ሆኖ ሲፈጠር አይችልም። ታዲያ ይህንን ጉደሉ ነገር ሰማክሳስ ወዘት እንደተመልከቹ ነው። የሚል አባባል ፈጥረን በዚያ መፅናናትን ስምደናል። አንወሻሽ ካልን ግን ሁላችንም የምንስማማበት ውብትና አስቱያሚነት አለ። አንድ ዘፋኝ ሙሰም የየራሱን ሲያደንቅ አሰማለሁ፤ የሙ የኔ እኮ ናት እኮራባታለሁ፣ ሲል ማቀንሥት ትገ ይሰኛል። ማፅናኛ ነው። አንወሻሽም ተባበለናል።

ፍቅርና ውብትን ማነናነት ያለብን አይመስለኝም። አንድ ወንድ ከልላ ሴት ጋር ፍቅር የሚይዘው በውብትዋ ብቻ ላይሆን ይቸላል። አንድ ወንድ ያንዲትን ሴት፣ መልከ፣ ገጸበብ፣ ባሀርይ፣ ድምፅ፣ ስልጣን፣ ጭንቅላት ሊያፈቅር ይችላል። ያሻውን ያፍቅር! ዘሮ ዘሮ ግን ፍቅር ያው ፍቅር ነው። ደረጃ የለውም። በርግዋ ዘላቂ ነው አይደለም የሚል ክርክር ሲነሳ ይችላል። አሱን ግን ለጊዜው አንተወው።

በዚህ መንደርደሪያ አስደንጋጭ የሆነ ገጠመኜን ሳወጋችሁ ነው ይተነሰሡት።

በአንድ አሰቱ – ስንዘኑ በአካባቢዬ ካለ ራስቱራንት ውሰዶ ምሳ በመመገብ ላይ ሳለሁ አያናቹ ካልተጠበቀ አስገራሚ ሁኔታ ጋር ተጋፈጩ። ወደ ራስቱራንቱ ሶናት ሲሶች ዘለፉ። ሁለት አረጋውያን አንዲት ሴት ልጅ አስከትለው ገቡ። ባልና ሚስት ሊሆኑ ይቸላሉ። ሴቲ ደግሞ ልጃቸው። ልጅቱን ገና ሳያት ልቤን አመመኝ። ልጅቱ መግለፅ በማይቻል መልኩ አስቱያሚ ነበረች። ስለአስቀያሚነት ብዙ አውቃለሁ። ድህነት ራሱ አስቱያሚነትን እንደሚያጉናፅፍ፣ ምጥት ውብትን እንደሚያላብስ አረዳለሁ። እናትና አበትዋን ተከትላ የመጣችው ይህች ወጣት ግን ከዚህ ሙሎ በልዩ ሁኔታ አስቱያሚ ነበረች። ገፅታዋ ላይ የሚታየው ቅርፅ ራስ የሚይሰምም ነበር። አቃዙር እያወጣሁ አይደለም። እኔ ስአካለ ጉዳሎነት የምስጠው ዮተለየ ክበር አለ። ይህች ወጣት ሴት ግን አካለ ጉደሉ አልነበረችም። በአደጋ ዮተጐዳ የሰውነት ክፍልም አልነበራትም። ዮተሟሉ አካል አላት። አለባበሷ ልዩ ነው። አረንጓዴ ሻቢትና ሙብ ጂንስ፣

ኮማሪ ነጭ ስኒከር ጋር ሳብሳለች። ቀጭን ናት። ቁመትዋ ተመጣጣኝ ነው። ለግሊጋ ወጣት ናት። ጠጉርዋ ጥቁርና አጭር ቢሆንም ያማረ ነው። ዓይናችዋ ግሩም ናቸው። ከዚድ የተፈጥሮ ስህተት ዮተከሰተባት አፍዋ አክብቢ ነበር። የታችኛው ከንፈርዋ አንደ ማስመሪያ ቀጭን ሲሆን፣ ሁለቱ የፊት ጥርሶችዋ አያንዳንዳቸው የኢትዮጵያን ሙሳ ሳንቲም ያክላሉ። ሰፋፊና ረጃጅም ጥርሶችዋ ቁልቁል ወርደው አንደ ማስመሪያ የቀጠነ ከንፈርዋን ሸፍነውት ልጅቱን ከንፈር አልባ አስመስለዋልታ።

የገፅታዋ ስህተት በዚህ ቢያበቃ ደሆና። የላይኛው ከንፈርዋ ወርዱ በመርዝመና በትርፍ ሲጋ በመዋለቅለቁ የጌመል አፍ የታገጠመላት መሰላለች። ድንገት ለሚመለከታት የአፍዋ ቅርፅ እጅግ አስደንጋጭ ነበር። ልጅቱን ያለማቋረዋ ትከ ብሎ ማጤን ከቶ አይቻልም። ሁኔታው ስሜትን ይረብሻል። ሆድን ይገለበብባል። ለደቂቃዎች ያህል ስለ ልጅቱ አሰብኩ። ልጅቱ የህያ ዓመት ወጣት ብትሆን ነው። እድግ አስቱያሚ ናት። እና ታዲያ ከአሎቾዋ ያን አይነት ስሜት እየተሰጣት ይሆን? ወጣቶች አፍቅረዋት ያወቁ ይሆን? እርስዋስ ፍቅር ይህስት ያጡቃል?

የልጅቱን ተፈጥሮ እየተመለከትሁ በጉዳዩ ላይ ያየልቅ አሰብኩበት። የሰውን ልጆች መልክ የሚመርጠው ማነው? እግዚአብሔር? ቸንጅና አስቱያሚነትን የፈጠረው በርግዋ እግዚአብሄር ነው? እግዚአብሄር እጅን ታጥቦ የሰራቸው የመጥራቸውን ያህል በቸሸ እጅ እንደነኩ አድርጎለሰ እንዲወለዱ ያደረጋቸው ሰዎች አሉ ማለት ይሆን? ግን ለምን?

አንዳንድ ሰዎች ወብታቸው ታይቶ አይጠገብም። እጅግ አስቀያሚዎችም ሞልተዋል። ገጣጣ፣ ደፍጣጣ፣ ድዊ፣ ቀውላላ፣ አገጫም፣ ድዲም የመሳሰሉት ስድቦች ሁሉ ለአስቱያሚነት የተሰጡ ሲሞሚጭ ናቸው። ማርያም፣ መልአክ፣ ሞናሊዛ፣ ሽበላ፣ መሰለ፣ አሳ መሳይ፣ ዕዝራ ዘተባለ ደግሞ ውበት መሆኑ ነው። ይሁን

ዘሮ ዘሮ ምሳ በመመገብ ላይ ሳለሁ ከዘዐደጮቸዋ ጋር ስለመጣቸው አስቱያሚ ወጣት ሴት በማሰብ ላይ ነኝ። ልጅቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

መጀመሪያ ነመሰከታት ወሰፉቱ ሁሉ ተቀልፎ ነበር። እንዲያውም «እግሊኣብሄር በቆሻሻ እጹ የሰራት» የሚል ምኞት የማይሰጥና ለፈጣሪ የማያከብ የቀልድ አባባል ነበር ወደአስምርኒ የመጣው። ልጅቱን በመደነቅ ደጋግሚ ማየት ስጀምር ግን ቀስ በቀስ እየለመድኳት መጣሁ። ቢያንስ ሲያጥወሰወሰኝ የደረሰው ስሜት ረገበና ጋብ ማለት ጀመረ። ተረጋግቼና አይኔን ሞልቼ ልጅቱን ማየት ጀመርኩ። ትክ ብዬ ባየሁዋት ቁጥር ስለተፈጥሮ ማሰላሰሌን ገፋሁበት። ተፈጥሮ የዚህችን ምስኪን ወጣት መልክ ለምን እንዲህ አዘበራረቀው? እኮ ለምን? ለማን ጥቅም? ለምን ሲዎች ሁሉ ውብ አልሆኑም?

ልጅቱን ትክ ብዬ ማየቴን በቀጠልኩት ቁጥር ግን ውብት ማለት የተሰየኳለሁ ተፈጥሮ መሆኑን በግልፅ ተረዳሁ። ለአብነት የዚህች ወጣት ሴት ሁለት የፊት ጥርሶች የኢትዮጵያን ሀምሳ ሳንቲም ማክል አልነበረባቸውም። የታችኛው ከንፈርዋ እንደማስመሪያ መቅጠኑና፣ የላዩው ደግሞ እንደ ግመል ከንፈር እንዲያ መትረፍረፉ ከዙ ምን የሚሉት ነው?

ስዘዘሀች ልጅና ቤተሰቦችዋ ሰላ ያስተዋልሁት እውነትም ነበር። ልጅቱ ገምተኛ ናት። እንደ ሀውልት ድርቅ ብላ የመቀመጥ ባህርይ ይስተዋልባታል። አልፎ አልፎ ግን የላይኛው ከንፈርዋ ሀምሳ ሳንቲም የሚያክሰው ጥርሶችዋን ለመሸፈን ከላይ ቁልቁል ሲነጠፍና መልሶ አየተምዘገዘገ ወደነበረበት ስፍራ ሲመለስ ይታያል። ይህን ግፆት በአድጉ አሰቃቂና ሆድን የሚያንሰገሰግ ነበር። የልጅቱን አስቀያሚ ተፈጥሮ እንደዋዛ ላልፈው ከቶ አልፈተድኩም። በተለይም የገመተችዋት ጠባይዋ ከአስቀያሚነትዋ ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን እንደሚችል ስለገመትሁ ሰሰ ልጅቱ በጥልቀት ማሰበን ቀጠልሁ። ልጅቱ ሁሉት ጊዜ ያህል ዘወር ብላ ተመለከተችኝ። አይኔን ከርስዋ ላይ አለመንቀሌ እንዳስደሰታት ተገነዘብሁ። ያዘ ድግም ስሚቱን ጉዳው። ወጣት ሴቶች የጉልማሳ ወንዶች አይን ሲያርፍባቸው እንደ ዝቋዋላ ፈረስ ጋማቸውን እንደሚነሰንስ ከልምድ አውቃለሁ። ይህች ግን የኔ አይን በስትከሮት ሲያርፍባት ተከፋች። ግን ለምን? ግልፅ ነው። አስቀያሚ መሆንዋን

አውቃለች። ወንዶች ከቶ በፍቅር ሲያስተውሷት እንደማይችሉ ተረድታለች። ምናልባትም በአስቀያሚ ተፈጥሮዋ ሳቢያ ነፍሰድ ቁስሉችን አትርፋ ሊሆን ይችላል።

ሶስቱም ምግብ አዘው መብላት ጀመሩ። የልጅቱ እናትና አባት «መልኮም» ቅርፅና መልክ ነበራቸው። የልጃቸውን ስሜት ሰመጠበቅ የሚያደርጉት ጥረትም በግልፅ ይታይ ነበር። አባትዋ ከራሳቸው ምግብ በሽካ ጠቅልለው ደጋግመው አጉረሰዋት። እናት ደግሞ ቀልዳ ቀልዶችን በመፍጠር ልጃቸውን ለማሳተፍ ጥረት ሲያደርጉ ይታዩ ነበር። ሁሉቱ በአድሚ የገፉ ባልና ሚስት በሞሞት ሀያ ዓመት የሚሞላትን ኮረዳ አንደ ለምስት ዓመት ህፃን ሲያቆላምጧት ሲሞክሩ በጥንቃቄ አስተዋልሁ። የአስቀያሚይቱ ኮረዳ ወላጆች በኑሯቸው የተቻላቸው ሰመሆናቸው የሚያጠያይቅ አልነበረም።

አስቀያሚዋና ገምተኛዋ ልጅ ያዘዘችውን አሮስቶ ጥቂት ቁማምሳ «ቢታኝ» አለች። አባትና እናት አየተቀባበሉ «ብይ እንጂ» አያሉ ይወተውቷት ያዙ። አሻፈረኝ አለች። እናት «አሞሽ ይሆን?» ሲሉ ጠየቋት። «ምንም አልሆንኩ» ስትል መለሰች። በዚህም አላበቃች። ወደአባትዋ አየተመለከተች «አናንተ ተመግባችሁ አስከትጨርሱ መኪና ውስጥ አቆያለሁ። ቁልፍ ስጠኝ» ስትል ጠየቀች።

አባትዋ ቃል ሳይተነፍሱ የመኪናቸውን ቁልፍ ከኪሳቸው አውጥተው ሰጧት። አስቀያሚዋ ልጅ ፊስቶራንቱን ለቃ ወጣች።

* * *

ከአስር ደቂቃ በኋላ እኔም ሂሳቤን ከፍዬ ወጣሁ። ስለ ልጅቱ በጥልቀት አያሰብኩ ነበር። በተለይም «እግሊኣብሄር በቆሻሻ እጹ የሰራት» የሚል ያልተሰመደና መልሶ ራሱኑ የሚያስደንግጠኝ አባባል ደጋግሞ ወደ ጭንቀላቴ እየመጣ አስቸገረኝ። መጀመሪያ ሲዮት እንዲያ አስድንጊጣኝና አቅሰሽልኝ እንዳልነበር ፊስቶራንቱን ጥላ ከወጣች በኋላ ግን ልጅቱን ማየት ናፈቀኝ። «ማንም የማይፈልጋት አስቀያሚ ወጣት ሴት» ስል ደጋግሚ አሰብኩ። ግን እግሊኣብሄር ይህቺን ሴት በዘህ መልኩ «ለበሳሽቶ» ፈጥሯት ሲያበቃ ለማኮከስ ለሱች «ቦነሸድት» ሴቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

የሌላቸውን ልዩ ስጦታ አዘጋ... ር ያለውን ነፍስ አሰብክ። ግን ያውቃል? እግዚአብሔር ሳያናግሽ ያውቃል?

ሂሳቤን ከናኋ ከፈጠራቸው እንደመጣሁ አስታዘብ ልጅነን ፣ፍሪ ተቅበዘበዝ። ኑሀሮ ተነስ ከሚጠራው ውብ ቅኔ መኪና ወረደ ተብሞ እሰሠማት። ድንቅ ሳሎች አዘጋጅትዋ ልቡን አስመሰኘ። ከዚያም አልፎ ዝረኛ። ከሰዓቷ መሰ ያለን መስል አስቀያሚነት ተመልክቼ አሳሰቅም። ዘንግ ፊታቸው ዘመም አልያም ሀይሌን የተባባሽ ወንጌሉ እሳ ጉያልምችን አያይያለሁ። ያ ሁሉ ግን የተለየ ነው። አዲ ነው – ተፈጥሮ አያያለም። በአዲስ ዘመም ናሚአሰት የፈት መሳሸት የሚፈጥረው ልዩና ከሀድ ስጦት ሃሰም። ከዚያ ከሌ ሰምች በአዲ አሳ ጉያሉ ዘሀንም የወሰት አሻራቸውን ከዙ አያሳም። ተፈጥሮ ስሀን ግን ስሚትን ያጉዘራል። ያዘቺ ከተቻሳቸው ዜተሰቦች ያተገኙተው አስቀያሚ ሴት በመልሙ ኑሮ ወሰሮ እንሃምትገኝ ገልዕ ዝዘ። ግን አስቀያሚ ናት። ምናልባትም የሚያፈቅራት ከዙ ሳያገር ይችላል። የስዘሸችው ልዘዘና የተያልያል ሀሃወትዋ ሲሸናንሳት ያልቻለ አስቀያሚነትዋ እንደ ማሰዳ ደንዘር ፍጉትው ብሎ ያተያል።

ከፈጠራቸው እንደመጣሁ አያን ለአያን ተጋፈጨ። አዋቂነ አሀሀዋት። ተያየን። ፈትሞን መሳሰቸብኘ።

ቃል ሳልተነፍስ ወደመኪናዉ አመራሁ። ሞተር ቀስሾ ሳዜው ፊቱን ወደ ልጅቱ መለሰዙ። ዘወር ብላ አየቸኝ። አሀሀዋት። እንደገና ተያየን። ዝረኛ አስቀያሚነትዋ። የሰው ልጅ እንዲህ ሆኖ ይፈጠራል? ይዜ የጥፈረትና የንሀቦ ጉዳይ አይደለም። በደፈናው አስቀያሚነት ብቻ ነው።

መኪናዉን ሳላነቃንቅ አይኖቼን ልጅቱ ላይ ተክዙ ተረሁ። እንደገና ዘወር ብላ አየችኝ። ሳለሰዉ በእጇ «ሂይ» ስል በምልክት ጠራሁዋት።

ፈገግ አለች።

ፈገግ ስትል አስቀያሚነትዋ ይበልጥ ይገላል። አይናችዋ ግን ይደምቃሉ። ጥርስዋን ሳያስዙ አይኖችዋን ብቻ ማየት ከተቻለ መልካም ነው። ግን ደግሞ ዘጠና በመቶ የፈገግታ

ደረሻ የጣንስ ነው። ድጋሚ ሠልክት «ሀሃ አልኩዋት።

አያዋን ብድግ አደረጉ ሳትዋን ግራቀኝ አያጠጋጋት ሠልክት «አያሠገም» አሰኙኝ። አነም በእያም ሀገንዘቧም እንቱን ላይ ታች በመነቅነቅም ሚያረ «ሰምገ» አልኳት። ሳትዋን ወደ ፊቦራሁ ጠቀመችኝ። አናትዋ አዙት ሙናራትዋን ተረዳሁ።

ሳያቸን በአፈኑ በያዙዉ ላይ በቁልቁን ቅረሽ ሀገዝዘመሠ «እንደየወል» አልኳት። በዚህ ጊዜ አስቀያሚዋ ልጅ በእሽታ ፊዘዋን ላይ ታች በመነቅነቅ መልሳ ፈገግ አሰች። ምነው ፈገግ ሳትል? ፈገጋሁዋ ያስፈራል። ግን የሰው ልጅቱን መልክ የማወሰው አግዚአብሔር ከዘን ደጉቺ ልጅ በዚህ መልክ አስቀያሚ ትሆን ዘንድ እምላክ ሰምን ወሰነ መልክ አፈልጋለሁ።

ሠድጋሚ ሠልክት «እንደየወል» አልኳት። ደህን ጊዜ ግን እንቱትዋን በመዚናው መሳዙት ብቅ ሀማድረግ የፈዘዙራቱን ዘዙ ጠራችው። ፈገግ ተጠጋት። አንድ ነገር ነገረቻው። ዘዙው ወደኔ አቅጣጫ መልክት አሰና እያመነታ መጣ፤

«ስዜት» አልኩት።

«ልጅቱ ይጠራሃል ብላኝ ነው። ፈለጥኝ» አሰኝ።

«አም። ስልጅቱ መልዕክት እንድትነገርልኝ ፈልጌ ነው»

«እሺ፤ ምን ልበላት?»

«ሞኖናችን እንድናወራ እፈልጋለሁ፣ ይልቅል በላት» አልኩት። ዘዙዉው ሂዶ ነገርአት ፈገግ ተመለሰ፣

«ምነሰችህ?» ስል በጉጉት ጠየቅሁት።

«ስልክ ቁጥርህን ሳክልኝ፤ ስሚ ትዕግስት ደክሳል ብላሀች።» አሰኝ። በቱራሮ መረቀት ላይ ስልክ ቁጥሬንና ስሜን ጫጭሬ ከሰጠሠዋት በኋላ እንዲህ አልኩት፤

«ማክሰኞ እስክ ስድስት ሰዓት ባለው ጊዜ ደውይልኝ ብሎኛል በላት።»

ይህን ብዙ መኪናዉን አስሃስቼ ተፈተለክሁ። በመንገድ ላይ አሰደ ጉዳዮችን ሳወጣና ሳወርድ ነዘር። እንዳለፈቀርኳት ገልዕ ነዘር። ግን አፍቅሬያት ይሆን እንዴ? የሰው ልጅት፣ ውበትን፣ ገንዘብን፣ ስልጣንን፣ ባህርይን ያፈቅራሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አስቀያሚነትነክ ሊያፈቅሩ አይችሉምን? ለምን አይሆንም?

በሳቅ ፈነዳሁ። ጤኛ ሳቅ ግን አልነበረም። እንዲህበድ ጭምር ፈራሁ። ልጅቱ አድግ አስቀያሚ ናት። ተፈጥሮዋ ስሜትን ይጭዳል። ታዲያ ለምን እንድትደውልልኝ ፈለገች? ታሪክዋን ለማጥናት ይሆን? አውነተኛ ፍቅር ከርስዋ ዘንድ አገኝ ይሆናል ብዬ በማሰብ ይሆን? ምንድነው ፍላጐቷ? አስቀያሚነት ምን ምን እንደሚል ለመቅመስ ፈልጌ ይሆን? ከዚ ስሜቱ ምን ይሆን? ወይስ ሩህሩህ ልቤ አዘነላት? ይህን ለማለት እንኪ አልደፍርም። ምክንያቱም ራሴን አስዞግዘዋለሁ ድረስ ራስ ወዳድ ነኝ። ፍጹም ነገር አወዳለሁ። ሰውነት ነገር ሚች ነኝ። ይህ ከሆነ ታዲያ ለአስቀያሚዋ ልጅ ለምን ድነው ስልክ ቁጥሬን የሰጠሁዋት? በውነቱ አላውቅም።

* * *

ማክሰኞ ደርሶ ልጅቱ ደወለች። ግን ላዋራት አልቻልኩም። ለምን? አሁንም አላወቅም፣ ግራ ተጋብቼያለሁ። የምፈልገውን አላውቅም፣

«ትሰማለች» አለች።

«ማንን ፈለጉ?» ስል ተነፈስኩ። ስሜን ጠራች።

«ሕጉ ብለው ደወሉ?»

ቁጥሮቹን ተናገረች። የኔው ነበሩ። «ቁጥሩ ልክ ነው። እንዲያ የሚባል ሰው ግን በዚህ ቁጥር የለም» ስል ተነፈስኩ። ከዘዲያኛው በኩል ከባድ የመተንፈስ ድምፅ ሰማሁ። ትንሹዬ ሲቃይና ናፍቆት እንደመቶ ታወቀኝ። በርጋታ ስልኩ ተዘጋ። አልሾኝ ነበር። ስልኩ በዚጋም ያ አሰቃቂ ምስል ግን ከራቱ አልጠፋም። ቢሆንም የመላጓል ስሜት አደረብኝ። ነው ግን እንሽ አይናቹ በእባ ተጋርደው ነበር። እንዲህ ስል ለራሴ ማንሸካሸኪንም አሰታውሳለሁ። «አምላኬ ሆይ ይህቺን ልጅ ለምን በድልነት? ወይስ አስቀያሚ መሆን በድል አይደለም?»

ልቦለድ



ዶስቶየቭስኪ

ዕዝራ እጅጉ

የዝኾው ደራሲ የፊዮዶር ዶስቶየቭስኪ የስነ-ዕውቁ ስራ መታየት የጀመረው በሩሲያ የባህል እንትስቃሴ ታሪክ ባበበት በመጀመሪያዎቹ አስርት ዓመታት ውስጥ ነው። በዘኾው ሙቱ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አጋማሽ ላይ እነ ቤሊንስኪን የመሳሰሉ ዝነኞች የሩሲያ የስነ-ዕውቁ ጥናት ሊታውንት መገለት የጀመሩትም ያኔ ነው።

ዶስቶየቭስኪ በስራዎቹ የሰው ባህርይና ነፍስ ጥልቀት ባለው የጥልስጥና ትንተና አትኩሮ በመመልከት ልብ ወለድ ታሪክ እንደስሙ ልብ ወለድ ብቻ ሳይሆን መስረታዊ

t.me/OLDBOOKSPDF

የራሱ የሰው ጥናት እንዲሆን አድርጓል። በአንድ ወቅት፣ «ፍልስፍናዊ አምነቱ ደካማ ነው» ሲል ለአንድ ጓደኛው በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል። የደራሲው ሀይወት ባጭሩ ምን ይመስላል?

ፌዮዶር ዶስቶየቭስኪ በኖቬምበር 11ቀን 1821 በሞስኮ ከተማ ተወለደ። ወላጆቹ ሐኪሞች ነበሩ። ለወላጆቹ ሁለተኛ ልጅ ነው። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ በሞስኮ ከሚገኙት የግል ትምህርት ቤቶች ባንዱ ገብቶ ትምህርቱን መከታተል ጀመረ። ገና በልጅነቱ ዘወትር ትንከባከበው የነበረችው እናቱ በመሞቷ በ16 ዓመቱ ወደ ፒተርስበርግ ተላከ። እዚያ በሚገኘው የጦር ምህንድስና ኮሌጅ ገብቶ ይማር ጀመር። በኮሌጁ በመማር ላይ ሳለ ስንብት ጠየቀ። ይህ ደራሲ ወደ ስነ-ፅሁፍ ዓለም ለመግባት ገና ከጧቱ የፀና ህልምና ምኞት ነበረው። ከኮሌጅ ሰቀ እንደወጣ «ደሀ ሰዎች» የተሰኘውን ልብ ወለድ መፅሀፍ ኤ.ኤ በ1846 አሳተመ። በ1846 ዶስቶየቭስኪ ከተምኔታዊ ሶሻሊስቶች ጋር ተቀላቀለ። የነርሱም ተከታይ ለመሆን ቻለ። በ1849 የተምኔታዊ ሶሻሊስት አራማጆች በቁጥጥር ስር በዋሉ ጊዜ ዶስቶየቭስኪ አብሮ ተያዘ። ዶስቶየቭስኪና ጓደኞቹ ለስምንት ወራት ያህል ለእስር ተዳረጉ።

ዶስቶየቭስኪ የሞት ቅጣት እንዲበየንበት ቢወሰንም ቅጣቱ ወዲያው በአራት ዓመት ከባድ ስራ ተቀየረ። ሳይቤሪያ በሚገኘው እስር ቤት ለአራት ዓመታት ከባድ ስራዎችን ሰራ። አራቱን የቅጣት ዓመታት ከጠናቀቀ በኋላ በሳይቤሪያ የጦር ስራ ውስጥ ግልጋሎት መስጠት ጀመረ። ደራሲው ዶስቶየቭስኪ በ1857 ማሪያ ኢሲቭ የተባለችውን ሴት አገባ። ከዚህች የ29 ዓመት ወይዘሮ ጋር ዶስቶየቭስኪ ሰላማዊ ኑሮ እንዳልነበረው ነው የሚነገረው። ጋላ ላይ ከኤሲቮ ሞት በኋላ የ22 ዓመት ወጣት አግብቶ እንደኖረ ይነገራል። ዶስቶየቭስኪ ታይም በተሰኘው መፅሄት በአርታኢነት ይሰራ እንደነበር

ይታወቃል። ደራሲው የሚጥል በሽታ እንደነበረበት ከያሉ የደራሲያን ታሪክ ዘጋቢዎች ፅፈዋል።

ዶስቶየቭስኪ በርግጥ ሰህተመት ባደረቃም አንድ የባልነቱን መፅሐፍ በሙተርጉም ነው ወደ ስነ ፅሁፍ ዓለም መዝለቅ የጀመረው። «ድሃ ሰዎች» የተሰኘው የመጀመሪያው መፅሀፍ በ1940 ኤ.ኤ ለህትመት በቃ። ይህ ድርሰት በዚያን ጊዜ በነበሩ አንባቢዎን ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት ከማሳደሩም በላይ ለሩሲያም ሆነ ለውጭ አገር በጠቅላላው በኋለኛው ትውልድ ዘንድ ተወዳጅነቱን እንደያዘ ቀርቷል። «ድሀ ሰዎች» ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተረጉሞ በአድናቆት ተሸክሏል - ወደ እማርኛ ቋንቋ ጭምር ተተርጉሞ በመፅሀፍ መልክ ታትሞአል። ስንቶቻን አንብበንለት ይሆን?

ዶስቶየቭስኪ የበኩር ስራውን ሲያሳትም እድሜው 24 ነበር። የደራሲው የመጀመሪያ ስራ ይህን ያህል ከፍተኛ ግምት ማትረፉ ለምንድነው? ሙቶ ዓመታት ያለፈው ስራ ተወዳጅነቱን ሳይለውጥ እስካሁን የቆየው ለምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እያሉ ሃያሲያን ያነሱት ነበር።

«ድሃ ሰዎች» በሚል ርዕስ ዶስቶየቭስኪ ያቀረበው ድርሰት ለየት ብሎ በደብዳቤ ስልት የቀረበ ልብወለድ ታሪክ ነው። በደብዳቤው ልውውጥ ታሪክ ላይ የሚያነሳቸው ሰዎች ዝምግሊው ተራ የቢሮ ፀሐፊ ማካር አለክሲያኪች ደቩሽኪንና ያለ ወላጅ የቀረችው ቫሬንካ ናቸው። ቀደም ሲል በ18ኛው ሙዩ ክፍለ ዘመን ገደማ በሩሲያም ሆነ በምዕራብ አገሮች ስለፍቅር ስሜትና ውዳቤ ልብ ወለድ ታሪኮችን በደብዳቤ ስልት ማስፈር በደራሲያን ዘንድ የተለመደ ነበር። እነዚህ ደራሲያን ልብወለድ ጀግኖቻቸውን ደጉች፣ ጨዋዎች፣ በጋስ ፍቅር የሚነዱ፣ መልክ ቀናዎችና ውቦች ግለትና ስሜት ያለባቸውን ሰዎች ፈለልገው ዕሁፋቸው ላይ ያስቀምጡአቸው ነበር።

ሆኖም የጀግኖቻቸው ባህርይና ፀባይ የሚነካ፣ የሚዳስስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም የሚጨበጥ አልነበረም። የነበራቸው ቋንቋና አገላለፅም ለፍጡራን ከሚሰጠው የራቀ ነበር። ቆየት ብሎ የተፈጠረው ዶስቶየቭስኪ ግን በጊዜው ከነበረው የተለመደ አተካኩ ወጣ ያለ ደራሲ ነበር።

በ«ደሃ ሰዎች» ውስጥ ያሉት ደብዳቤዎች በመካከሉ ምጥ ውስጥ ስለሚገኘው ሰው አሰቃሰቡ ይገልፁ። ይህ ትንሽ ሰው ከዚህ የመከራ ምጥ ለመውጣት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል።

ይህ «ደሃ ሰዎች» የተሰኘ ስራ በጠንካራ ስነ ፅሁፋዊ ጉልበቱ ይታወቃል። ቢሊንስኪይ የተባለው ሃያሲ «ዶስቶየቭስኪ የድሃ ሰውን እድለ ቢስነት ብቻ በማሳየት የሚወሰን አይደለም» በማለት ስለመፅሀፉ ያለውን ግላዊ አስተያየት ሰጥቷል።

በ1848 እ.ኤ.አ ያስከተለው «ብርሃናዊ ሊሊት» የተሰኘውን ስራውን ነው። በዚህ ድርሰቱ ዘለቄታ ያለው ሩቅ ሀሳብ ወይም ምኞት በአጭር ግላዊ ደስታ እንዴት እንደሚቀጭ አሳይቷል። በዚህ ድርሰቱ ያቀረበልን ዋናው ሰው ከፍተኛ የመንፈስ ሀብት ያለው ህልመኛና ባለቅኔ የሆነ አንድ ድሃ ምሁር ነው። የአዝዘሊያንን አስምሮ የሚግርከው ይህ በዘፍተኛ ቋንቋና አገላለፅ የቀረበ ድርሰት ደስ በምትሰኝ ናስቴንካ ቡተላሸች ልዝገረድና በምሁሩ ሰው መሀከል ስለነበረው ፅኑ ፍቅር ይገልፅልናል።

ዶስቶየቭስኪ ከሳይቤሪያው እስር ቤት ከወጣ በኋላ ለስት ጉልበት ያላቸው ረጅም ልበለዶችን ፅፏል። እነዚህም፦ «የተዋረደው»፣ «ዮተሰደበው» እና «ደሙታኖች ቤት» የተሰኙት ናቸው። በተሰይ እነዚህ ስራዎቹ የሳይቤሪያ እስር ቤትን ስፋላዊ ገፅታ አሳይተዋል።

«ወንጀልና ቅጣት» (በ1866)፣ «አብዱ» (በ1868) እና «የካራማዝቭ ወንድማማችት» (በ1879-80) ተከታትለው በወጡት ድርሰቶቹ ዶስቶየቭስኪ በሩሲያና በዓለም ስነፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዘ ደራሲ ለመሆኑ ስራዎቹ በቂ ምስክር ናቸው።

ዶስቶየቭስኪ በድርሰቱ ውስጥ በዓለማችን የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተናቁና የተዋረዱ ሰዎች፣ በችግር፣ በረሃብ ብሎም በሲቃይ እንዲኖሩ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ በዕሁፉ አሳይቷቷል። «ወንጀልና ቅጣት» የነሀሁ ሁኛ መሰረታና ተደናቂ የዶስቶየቭስኪ ስራ ነው።

ሮዳን ራስኮሊንኮቭ በሴይንት ፒተርስበርግ ዩኒቨርስቲ የሚገኝ ተማሪ ነው። ይህ ወጣት ተማሪ የችግረኛ ልጅ ነው። እናቱን የሚረዳቸው የለም። ደህም ጉዳይ ያላስዘዋል። ያስጨንቀዋልም። በዚህም ፕንዘብ ይፈልጋል። አንዲት የፓንዘብ አበዳሪን አሮጊት አስክ አህቷ ይገድላል። ሁሉን ሴቶች ከገደለ በኋላ ወርቅ ይዘርፋቸዋል። በዚህ ወቅት ወጣቱ ተማሪ ደስ ይሰኛል። ቤተሰቡን ከድህነት አረንቋ ለማውጣት ይዘጋጃል። ሮዲን ሁሉን ሴቶች ከገደለ በኋላ ወደ ክፍሉ ሲገባ የፖሊሶችን ድምፅ ይሰማል። በዚህን ጊዜ በድንጋጤ ይሞላል። ገዳይ መሆኑንም ለመናገር ይዘጋጃል። ፖሊሶቹ የመጡት ለሌላ ጉዳይ መሆኑን ሲያውቅ ሀሳቡን ይቀይራል። ከሰዎቹ የሰረቃቸውን ወርቆች ይደብቃቸዋል።

ተማሪው ራስኮሊንኮቭ በአንድ ወቅት የነፍስ ገዳዮች ዝርዝር ያለበትን ጋዜጣ ያነባል። ይህም ለፖሊሶቹ ጥርጣሬ ፈጠረ። የራስኮሊንኮቭን ወዳጆች ባደረጉት ግብግ ዕለት ዝያኖቸው ራስኮሊንኮቭን በሁለቱ ሴቶች ግድያ ይጠረጥሩታል። መጠርጠሩንም ያውቃል። ሶንያ በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማራች ወጣት ናት። ከአሷም ጋር ወጣቱ ተማሪ ይዛዴል። በኑሮዋም በጣም ያገናኛል። እየቀረባትም ይመጣል። ደብልጥ ሲቀራረቡም ወንጀለኛ መሆኑን ትረዳለች። ሶንያ፣ ሮዲን ወንጀለኛ መሆኑን እንዲናገር ትለምነዋለች። ዘውትር በሚንፉት ላይ የሚገኘው ሮዲንም በሶንያ ቤት ወንጀሉን መፈፀሙን ይናገራል። ፖርት ፋኖሪ ደግሞ የወንጀል መርማሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። ይህ ስው ሮዲንን ሁልጊዜ በመስቀለኛ ጥያቄ ያዋክበው ነበር።


ራሽሊንዝ ወንጀለኛነቱ ይፈጋገጣል። በሳይቤሪያ እስር ቤትም ለስምንት ዓመታት አንዲቆይ ይፈረድበታል። ሁለም ወዳጀቹ በጣም ያዝናሉ። እህቱ ዶንያና ባለቤቷ ሩዚሚሂን ሀብታም አሳታሚዎች ይሆናሉ። በሴተኛ አዳሪነት ስራ የተሰማራችው ሶንያ ወጣቱን ተማሪ ልትጠይቅ ሳይቤሪያ ትሄዳለች። ዘውትርም እስረኛውን ታዕናናዋለች። ህይወቷንም ዙፋው በሳይቤሪያ ለማሳለፍ ቁርጥ ውሳኔ ትወስናለች።

ይህ 'ወንጀልና ቅጣት' የተሰኘው የዶስቶየቭስኪ ስራ ስኬታማነትን በማግኘቱ ይታወቃል። ደራሲው ዶስቶየቭስኪ «መፅሀፉን ለመፃፍ ምን ያህል አንዳደከመኝ የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ። «ወንጀልና ቅጣት»ን ከመስራት ከባባድ ስራዎችን መስራት ቀላል ነው» በማለት በእንድ ወቅት በፃፈው ደብዳቤ ገልጿል። «ደስታ የሚገኘው ከሞንፉት ነው» የሚል ፅንሰ ሀሳብ ያዘለ ልቦለድ ነው። ይህ የደራሲው አምነት ለመሆኑ መገመት አያዳግትም።

ዶስቶየቭስኪ ለዓለም ስነ ፅሁፍ እድገት አስተዋፅኦ አበርክቷል። በተለይ ስነ ልቦናዊና ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸው ስራዎቹ የሃያሲያንን አትኩሮት አግኝተዋል። መፅሀፎቹ አብዛኞቹ በእንግሊዝኛ ተተርጉመዋል። እሱ ግን ባንራ ቋንቋ ነው የሚፅፈው።

ይህ የደራሲው ሙሉ ታሪክ አይደለም። የራሱ ታሪክ ተፅፎ አያልቅም። እንደው ምናልባት ደራሲውን በጨረፍታ ያስተዋወቅ እንደሆን እንጂ።

ማለ - ታሪክ



ዛፎች

ኸርማን ሄሰ
(ትርጉም) አቁባይ ከፍላይ

ለኔ መቸም ቢሆን ዛፎች ከሁሉም የበለጠ ልብን የሚነኩ ስባኪዎች ናቸው። በቤተሰብና በጎሳ ሆነው፣ በጫካና በደን ሲኖሩ ለነሱ ትልቅ አክብሮት አለኝ። ብቻቸውን ሲቆሙ ደግሞ አክብሮቴ የላቀ ነውና እንደብቸኛ ሰዎች፣ አሠ-ያኔ በእንዳንድ ድክመት ሸልከው እንደሚሄዱ መናኛች ሳይሆን ከዓለም እንደተለዩ ታላላቅ ሰዎች - እንደ ቤትሆቭን እና ኒትሽ ናቸው። በትርንጫፎቻቸው ጫፍ ዓለም ትርመለመሰለች፣ ስሮቻቸውም በማያልቀው ጥልቀት ውስጥ አሉ። ይህም ስለሆነ ራሳቸውን እዚያው

t.me/OLDBOOKSPDF

አልቀበሩም። በሕጋቸው መሰረት ራሳቸውን ለማሟላት፣ የራሳቸውን ቅርጽ ለማነጽና፣ ራሳቸውን ለመወከል ይታገላሉ።

ውብ ከሆነው ጠንካራ ዛፍ የበለጠ የተቀደሰና ምሳሌ መሆን የሚችል ምንም ነገር የለም። አንድ ዛፍ ተቆርጦ የሞት ቁስሉን ለፀሐይ በሚያሳይበት ጊዜ ብሩህ በሆኑ የግንድ ቀለበቶቹ ሙሉ ታሪኩን ማንበብ ይቻላል። በዓመታት ክብ ቀለበቶቹ፣ በቁስሎቹ ላት ትግሉ ሁሉ፣ ስቃዩ ሁሉ፣ ሕመሙ ሁሉ፣ ደስታና ብልጽግናው ሁሉ በእውነት ተጽፈዋል። የጭንቅና የተድላ ዓመታቱ፣ ያላለፋቸው ውጊያዎችና የተቋቋማቸው ማዕበሎችም ተቀርጸዋል። እያንዳንዱ የገጠር ልጅም ከሁሉም ኃያልና ታላቅ የሆነው ዛፍ ከሁሉም የተጠጋ ቀለበቶች እንዳለው፣ በተራራዎች ክፍታና በማያቋርጠው ሕዶ ጋም የማይበገረው፣ ጠንካራና ፍጹም የሆነው ዛፍ እንደሚበቅል ያውቃል።

ዛፎች መጠጊያ መሸሸጊያ ናቸው። ማንም ከእነርሱ ጋር መነጋገርን ቢያውቅ፣ ማንም እነርሱን ማዳመጥ ቢያውቅ እውነቱን መማር ይችላል። መመራመርንና ማገናዘብን አይሰብኩም፣ በዚህና በዚያ ልዩ ባሕርይ ሳይሰናክሉ ቋሚውን የሕይወት ሕግ ይሰብካሉ።

እንድ ዛፍ እንዲህ ይላል «በውስጤ ቡጥ፣ ብልጭታና አሳቤ ተደብቋል። እኔ ከዘለዓለማዊው ሕይወት የሆንኩ ሕይወት ነኝ። ዘለዓለማዊቷ እናት በእኔ ላይ ያደረጉቸው ጥረትና ሙከራ፣ ለእድል አሳልፋ የሰጠቸው ነገር ከሁሉም የተሰየ ነው።»

እንድ ዛፍ እንዲህ ይላል «በርታቴ እምቱ ነው። ስለእቦቼ አንዳችም ነገር አላውቅም። በየዓመቱም ከእኔ ስለሚወጡት በሺህ የሚቆጠሩ ልጆችም ምንም አላውቅም። የነፈን ምስጢራት እስከመጨረሻው አናራለሁ፣ ስለሌላ ነገር ግድ

የለኝም። አማዚአብሔር በውስጤ እንዳለ አምናለሁ። ድኅሜ ቅዱስ መሆኑን እምናለሁ። ከዚህ እምነት የተነሳም እናራለሁ።»

በተሰበርንና ሕይወትን መታገስ ባቃተን ጊዜም ዛፍ የሚነገረን ነገር አለ «ገዘም በል፣ እኔን ተመልከት፣ ሕይወት ቀላል ነገር አይደለም፣ ሕይወት አሸቻጋሪም አይደለም። እነዚህ የልጅነት አስተሳሰቦች ናቸው። አማዚአብሔር ካንተ ጋር ሲናገር ሐሳቦቹህ በዝምታ ይዋጣሉ። መጪኔትህ መንገድ ከእናንተ ከቤት ስለሚያርቅህ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ አርምጃና እያንዳንዱ ቀን መልሶ ወደ እናትህ ይወስድሃል። ቤትህ እዚህም ሆነ እዚያ አይደለም። ቤትህ በውስጥህ ነው። አልያም ቤትህ የትም የለም»


አመሻሹ ላይ ዛፎች ሲንሾካሾኩ ስሰማ የመሄድ ናፍቆት ልቤን ያስጨንቀዋል። ለረገፎም ጊዜ ካዲመጣኪቸውም ይህ ናፍቆት ውስጡን፣ ትርጉሙን ያሳያል። ስቃዩን የመሸሽ ነገር ቢመስልም ስቃዩን የመሸሽ ነገር አይደለም። ሴትን፣ የእናት ትገፃን፣ ለሕይወት አዲስ መግለጫን የመናፈቅ ነገር ነው። እያንዳንዱ መንገድ ወደ ቤት ያመራል፣ እያንዳንዱ መቃብር እናት ነው።

እናም በሕሣንት ሐሳቦቻችን ስንጨነቅ ዛፎች ሹክ ይሉናል። ከኛ የረዘመ ዕድሜ እንዳላቸው ሁሉ በሕርጋታ በረጅሙ የሚተኮሩ ሐሳቦች አሏቸው። አነርሱም እስክዳመጥነን ድረስ ከኛ ይልቅ ጥበቡ ሆነው ይኖራሉ። ዛፎችን ማዳመጥ ስንማር ግን የሐሳቦቻችን አጥረት፣ ፍጥኮትና ልጃልጅነት ወደር የለለው ደስታ ይይዘናል። ዛፍን ማዳመጥ የተማረ ማንም ቢሆን ዛፍን መሆን አይሸም። ከሆነው ነገር በቀር ለለ ምንም መሆንን አይሸም። ያ ራሱ ደስታ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF



የጦርነት አሻራ



ውስታ

ሮይ ኤስ ሚለር
(ትርጉም) ግርማይ ወልደጊዮርጊስ

«ይህ ደግሞ የምን ቀለበት ነው አያቴ?»

«አስቲ አምጪው ልየው። አዎ አስታወስኩት። ሳጥኑን ውስጡን ካየሁት ረኻርም ጊዜ ሆነኝ።»

«ሚትዝቫህ የሚል ቃልም አውስጡ ተፅፎበታል። ምን ማለት ነው?»

«ኦብራይስጥ ነው። 'ውለታ' ማለት ነው።»

«ለምንድነው የያዝከው። በቤተሰባችን ውስጥ የአይሁድ ደም አለ እንዴ?»

«የለም። ግን ሊኖር ይችል ነበር።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እዚህ ላይ የሆነ ታሪክ ይሸተኛል። ምናልባትም የፍቅር ታሪክ ሳይሆን አይቀርም። እባክህ እያቴ ንገረኝ።»

«ደግ። ግን ላትወጂው ትቺያለሽ። ደግሞም ለኔ ያለሽን አመለካከትም ሊቀይረው ይችላል።»

«ሞኝ አትሁን። አንተኮ ሁሌም እንከን የሌለህ ጨዋ እንግሊዛዊ ነህ።»

«የ23 ዓመት ወጣት ሆነሽ እንዲህ ያለ ልብ የሚነካ እምነት መያዝሽ እንዴት ግሩም ነው። ለመሆኑ በዚህ እድሜሽ ስንት እንከን የሌላቸው እንግሊዞችን ነው የምታውቂው?»

«በኔ መሳቅህን አቁምና ንገረኝን»

...ጦርነቱ ሊጀመር አካባቢ ነው። በርሊን ውስጥ እንግሊዝኛ አስተምር ነበር። ያኔ ሂትለር ከእንግሊዞች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረው በጣም ይፈልግ ነበር። እናም ማንኛውም የእንግሊዝ የሆነ ነገር ይወደድ ነበር። ያኔ እኔ የ28 ዓመት ወጣት ነኝ። ረሽኖም ቁመትና የተስተካከለ ተክለ ሰውነት ነበረኝ። ጀርመኖች እንደሚወዱት አይነት ፀጉሬ ወርቅማ ዓይኔም ሰማያዊ ነው። በዚህም ልሳተፍባቸው ከምችላቸው በላይ የሆኑ የአራትና የዳንስ ምሽት ጥሪዎች ይጉርፉልኝ ነበር። እንግሊዝኛ ለመማር የሚፈልጉትን የተማሪዎች ብዛትም ለመቀበል እስከማልችልበት ደረጃ ድረስ።

አንድ ቀን ጥቁር ፀጉር ያላት ቆንጆ ወጣት ቢሮዬ ውስጥ ተቀምጣ አገኘሁዋት። እንግሊዝኛ እንዳስተምራት ነው የፈለገችው።

«አዝናለሁ» አልኳት «የኔ ክፍል ሙሉ ነው፤ ቦታ የለኝም።»

በጣም አዘነች «ከመደበኛው ክፍያ አጥፍ አድርጊ እከፍልሀለሁ» አለችኝ።

«የገንዘብ ጉዳይኮ አይደለም» አልኳት «ኮሌጁ ገንዘቤን ይከፍለኛል»

«ኮሌጁ ውስጥ ለመማር አልፈለኩም። በመኖሪያ ቤትህ ውስጥ በግል አንድታስተምረኝ ነው የምፈልገው።»

«አዝናለሁ» አልኳት «ምንም ጊዜ የለኝም»

ትንሿ የግራ ጣትዋ ላይ የአልማዝ እንቁዎች ያለው ቀለበት አድርጋ ነበር። አወለቀችና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው።

«ይህ ቀለበት በጣም ውድ ነው። በእንግሊዞች ገንዘብ 300 ፓውንድ አካባቢ ያወጣል። እቤትህ ልታስተምረኝ ፈቃደኛ ሆነክ ውሰደው» አለችኝ።

ቀለበቱን ወደሷ ገፋ አደረኩትና። «ቀለበቱን አድርጊው። ደግሞም ሞኝ አትሁኝ» አልኳት። በጣም ቆንጆ ልጅ ናት። ዓይኖችዋ እንባ አቀረሩ።

«ማዘን የለብሽም» አልኳት «እንግሊዝኛ የሚያስተምሩ ብዙ ጓደኞች አሉኝ። ወደ አንዱ ላስተላልፍሽ እችላለሁ።»

«አንተ እንድታስተምረኝ ነው የምፈልገው» አለችኝ።

«በግል አላስተምርም። በቂ የቀን ተማሪዎች አሉኝ። ማታ ለማስተማር አልፈልግም።»

«ለኔ ስትል ጥያቄዬን ልትቀበል አትችልም?» ስትል ተማፀነችኝ።

«ሌላ ምክንያትም አለኝ» አልኳት «ያክራዩኝ ሴትዮ ቤቱ ውስጥ በግል እንዳስተምር አይፈቅዱልኝም። ወጣት ወንዶች ወጣት ሴቶችን ቤት ዘግተው ማስተናገዱ ላይ ያላቸው አመለካከት ጠንከር ያለ ነው።»

«እሺ ወደቤቱ ለመምጣትም ትችላለህ»

ተከላከልኩ። ከተማዋ በሚያስደስት ስሜት ተውጣ እያሰች እኔ ደግሞ በሰው አገር በብቸኝነት እየኖርኩ ነው። ይቺ ቆንጆ እንግዳዬ ከፋት ያላት አትመስልም። ግን ደግሞ የሆነ የራሷን ጨዋታ እየተጫወተች ይሆናል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባትም የክሊኗ ስራየን ልታሳጣኝ እየደለሰችኝ ይሆናል። ወይም የእንግሊዝ መንግስትን ሊያስቆጣ ወደሚችል ሁኔታ ልትከተኝ እያዘጋጀችኝም ይሆናል። እንዲህ እንዲህ ያሉ ጉዳዮች እንደሚፈጠሙ ሰምቻለሁ። ግን የልጅቷ ሁኔታ ሳያስገርመኝ አልቀረም። ሰምንድነው እንግሊዝኛ ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያደረባት? ለምንስ ነው እኔ ብቻ እንዳስተምራት የፈለገችው? ይህንን እድል ለማግኘት ከመደበኛው ከፍያ የበለጠ ለመክፈል ዝግጁ የሆነችው?

«ወደ ቤትሽ አልመጣም» አልኳት «አንድ ሀሳብ ግን አለኝ። ያከራዩኝ ሴትዮ በየሳምንቱ ሮብ እህታቸውን ለመጠየቅ በመሄድ ከምሽቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ይቀያሉ። ወደ ሰስት ሰዓት አካባቢ ለመምጣት ከፈለግሽ ለግማሽ ሰዓት ያህል አስተምርሻለሁ። ያከራዩኝ ሴትዮ እህታቸውን ለመጠየቅ ካልሄዱ ደግሞ ከተማሪዎቼ አንዷ መሆንሽንና ይህንን መፅሀፍ ለመመለስ እንደመጣሽ ትናገሪያለሽ። ስሜና አድራሻሎ በመፅሀፉ የፊት ሽፋን በውስጥ በኩል አለልሽ» በማለት በከርኔ የተደገፍኩትን የእንግለዘኛ ለጀማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ሰጠሁዋት።

እንግዳዋ በጣም ደስ አላት «ስለዚህ ነገ በሶስት ሰዓት አካባቢ እመጣለሁ ማለት ነው።»

«ስምሽን ግን አልነገርሽኝም» አልኳት።

«ኢቫ ኮስትሰር» ካለች በኋላ «ስለ ክፍያውስ?» ስትል ጠየቀችኝ።

«ስለ ክፍያው ኋላ እንነጋገራለን። በጣም እንደማልትሽ ግን ቃል እገባልሻለሁ።

የመጀመሪያው ትምህርት በጥሩ ሁኔታ ተከናወነ። ኢቫ ለመምሰል ከምትፈልገው በላይ የእንግለዘኛ ችሎታ እንዳላትም ከፍተኛ ጥርጣሬ አደረብኝ።

የሁለተኛው ቀን ትምህርትም ከፊተኛው በበለጠ ሁኔታ

ተጠናቀቀ። ፍርሀቱም ስለለቀቃት በጥሩ እንግለዘኛ መናገር ጀመረች። ስለ ፖለቲካ ሁኔታዎች፣ ከእንግሊዝ ጋር ቦርነት የሚካሄድ ስለመሆኑና ስለመሆኑ፣ በርሊን ውስጥ ስላሉ አይሁዶች ፅጣ ፈንታ፣ እንግሊዝ ውስጥ አጮኛ ወይም ፍቅረኛ ያለችኝ ስለመሆኑና ስለመሆኑ አወራን።

በመጨረሻ «ኢቫ ድብብቆሽ አየተጫወትሽ ነው ያለሽው። እንግሊዘኛሽ በጣም ጥሩ ነው። ትምህርት አያስፈልግሽም» አልኳት።

ፈገግ አለች «አንተን ለማግኘት እንደ ሰበብ የተጠቀምኩበት ነው። ላምንህ እችል እንደሆነ ማወቅ ነበረብኝ»

«ለምንድነው የምታምኚኝ» ብየ ጠየኩዋት። በቀጥታ አልመለሰችልኝም። «ዘዚህ ወር መጨረሻ ላይ ክሊጅ ይዘጋል» አለች «ምን ለማድረግ አስበሀል? እዚህ ለመቆየት ወይስ ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ?»።

«ወደ ሀገሬ እሄዳለሁ እንጂ። ጦርነት ከተነሳ እዚህ እንድታሰር አልፈልግም።»

«ስትሄድ ትወስደኛለህ?»

በመገረም ተመለከትኳት። ቶሎ ብላም «እንድታገባኝ አፈልጋለሁ። የሀሰት ጋብቻ። ከጀርመን ለመውጣት እንዲያስችለኝ ብቻ ነው ጋብቻውን የምፈልገው። በአሁኑ ወቅት ሳገባች ሴት ከጀርመን መውጣት ያስችግራታል። ብዙ ጥያቄዎች ትጠየቃለች። ለምንድነው አገር ለቃ የምትወጣው? ወዴት ነው የምትሄደው? ከማን ጋር ነው የምትገናኘው? መቼ ነው የምትመለሰው? እና በመጨረሻም አይፈቀድላትም። ካገባች ግን በተለይ ደግሞ እንግሊዛዊ ከሆነ ችግር አያጋጥማትም። ካገባሽኝ በኋላ እንግሊዝ አገር እንደደረስን ሁለተኛ አታየኝም። ሰንደን ውስጥ የሚኖር አጉት አለኝ። በእጅ ቦርሳዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ አንድ ልዩ ቅፅ አለኝ። ስሞቻችንን መመሳሳት ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ብራንደንበርግ ውስጥ ያለው የማዘጋጃ ቤቱ ፀሐፊ ጓደኛዬ ነው። በአስር ደቂቃ ውስጥ ሊያጋባንና የምስክር ወረቀት ሊሰጠን ይችላል። ፓስፖርቴንም ሚስትህ መሆኔን በሚገልፅ መንገድ ያዘጋጀዋል። ነገ ጠዋት መሄድ እንችላለን። ከኮሌጁ አንድ ጓደኛዬ ስለሞተ ለቀብር መሄዴ ነው ብለህ የአንድ ሰዓት ፈቃድ ጠይቅ። አምስት ሰዓት ላይ ለመመለስ ትችላለህ። ማንም አያውቅም። ሰንደን ውስጥ ያለው አገሬ በጣም ሀብታም ነው። በደንብ ይከፍልሃል።»

«በጉቦ ልታግባቢኝ መሞከርሽን አቁሚ» አልኪት «የምረዳሽ ከሆነ ካንቺ ሰማግኘት በምጠብቀው ጉዳይ አይሆንም። ግን ይህ እያቀረብሽልኝ ያለሽው የጋብቻ ጥያቄ አስደንጋጭ ነው። ሳስብበት፤ ትንሽ ጊዜ ያስፈልገኛል።»

በድንገት አንድ ሀሳብ መጣልኝ።

«በፖሊስ ትፈለጊያለሽ? የፈፀምሽው ወንጀል አለ?» አልኪት።

ፈገግ አለች። የሀዘን ፈገግታ። «የፈፀምኩት ወንጀል ቢኖር እዚህ አገር መኖሬ ብቻ ነው። ሳጣድፍህ አልፈልግም ፒተር። ጊዜ ግን አያመለጠ ነው ያለው። ለኔም ላንተም። ለዚህው አንግሊዞች እዚህ አገር ሰመቀየት ይፈቀድላቸዋል። ይህ ሁኔታ አስከ መቼ እንደሚዘልቅ ግን ማን ያውቃል?»

«የስልክ ቁጥር ስጪኝ» አልኪት «ነገ ማታ እደውልልሻለሁ። ግን እባክሽ በኔ መተማመን የለብሽም። እዚህ ጉዳይ ላይ እጅን ማስገባት እንዳለብኝም ርግጠኛ አይደለሁም።»

እንግዳ በሆነ አመለካከት ስትመለከተኝ ቆየችና እንባዬ ላይ ጥምጥም ብላ ላመቻኝ «ተስፋዬን አንተ ላይ ጥየዋለሁ

ፒተር» አሰችኝ ለስለስ ባለ ድምፅ «እባክህ ከንቱ አታስቀረኝ።»

እውነቱ ፈጥኖ ሊገለፅልኝ ያልቻለው በጣም ደደብ ስለነበርኩ ሊሆን ይችላል።

በበነጋታው ጥዋት የኮሌጁ ዳይሬክተር ወደ ቢሮው አስጠራኝ። እድሜው 60 ዓመት አካባቢ ይሆነዋል። በጣም ቀጥ ያለ ቁመናና ያቀመቀመ ሪዝ አለው። በአንድ ዓይን ላይ የሚለካ መነፅር ይጠቀማል። ፀጉሩን በጣም ያሳጥረዋል። አንግሊዘኛውን ያቀላጥፈዋል።

«ሚስተር ራስል ከአይሁዳዊው ከጆሴፍ ሜንደል ሴት ልጅ ጋር ጓደኝነት መመስረትክን ልገዝብ ችያለሁ» አሰኝ። በመገረም ተመለከትኩትና «ስለምን እንደሚናገሩ አልገባኝም ዶክተር» አልኩት።

«አላወቅክም?»

ጭንቅላቴን በአሉታ ነቀነቅኩት።

«ኮረግስራስ ላይ ያለውን የትልቁ መጋዘን ባለቤት ነው።»

«ሳው?» አልኩት ምንም ስሜት በሌለው መንፈስ። ቀደም ብሎ አንድ ማታ በኮረግስትራስ ሳልፍ በመጋዘኑ ግድግዳዎችና መስኮቶች ላይ 'አይሁድ' የሚል ተፅፎበትና የዳዊት ኮከብ ተስሎበት አይቻለሁ።

«ክሴት ልጁ ከራሄል ማንደል ጋር እንደምትገናኙ መካድህ ነው?»

«በፍፁም ግንኙነት የለኝም» አልኩት።

«ወደ መኖሪያ ቤትህ ትመጣለች።»

«ተሳስተሃል ዶክተር» አልኩት «አንዲት ወጣት ተማሪ ለትምህርት ብላ እኔ ዘንድ ትመጣለች። በየሳምንቱ ሮብ ነው የምትመጣው። ስሟ ግን ኢቫ ኮስትሰር ነው።»

ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ክላስር ከፈተና ፎቶራፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

አውጥቶ ፊት ለፊቴ አስቀመጠ።

«ራሄል ማንደል ይችውልህ። ወደ ቤትህ የምትመጣው ይቺ ናት?»

ፎቶግራፉን ተመለከትኩ። ሆዴ ተገለባበጠብኝ። ኢቫ ኮስትሰርና ራሄል ማንደል አንድና አንድ ናቸው። በአጭር ጊዜ ውስጥም ይቺ ምስኪን ወጣት ጓደኛዬ ሊያጋጥማት የሚችለው አሰቃቂ አደጋ ታየኝ። ለምን እኔን ለማግባት ከፍተኛ ፍሶጉት ጌንጎ ረባት ተረዳሁ።

ዶክተሩ አተኩሮ እየተመለከተኝ ነበር። በተቻለኝ መጠን ተረጋግቼ ፎቶግራፉን መለስኩለት። «ይቺ አይደለችም። እንደነገርኩዎት የኔ ተማሪ ኢቫ ኮስትሰር ነው የምትባለው»።

ወደኋላ ተስጥሞ ተመለከተኝ። ውሸታም ይሰኛል ብዙ አሰቢ ነበር። «ጥሩ ሚስተር ራስል» ሲል ተነፈሰ «ያልከኝን ተቀብየዋለሁ። ግን በጓደኛ አመራረጥህ ላይ ጥንቃቄ አድርግ። አሳዛኝ ሁኔታ ሊያስከትልብህ ይችላል። አንድ ነገር ልጨምርልህ። በዓለም አቀፉ ሁኔታዎች ምክንያት ክሊጹ የስራ ኮንትራትህን ላያድስልህ ነው። እንደሚገባህ እርግጠኛ ነኝ።»

ጉዳዩ እንዲህ ነው ማለት ነው? እኔስ ከጀርመን ለመውጣት እችላለሁ። ግን አንድ ሴላ ችግር አስብኝ። ኢቫን እንዴት አደርጋታለሁ? ወደቤቱ ሶትመጣ ክትትል ይደረግባት እንደነበረ ግልፅ ነው። የዶክተሩ ማስጠንቀቂያ ዛቻም ጭምር ነበር። ዳግመኛ ካሠጣት በኃላ እጇ የችግር ያለህ እያልኩ መጣራቴ ይሆናል። ዶክተሩንና የጀርመን ባለስልጣኖችን መቃወም ያሞጣልን? የእይሁዶች ደጋፊ መሆን በጣም አደገኛ ነገር ነው። ጀርመኖች እነዝም "አይሁድ" የሚል ሰሞ ለጥፈው-ቢኝ እንደ አይሁዶች ሊያስጥንቁኝ ይችላሉ። በሙቦዎች የሚደጠሩ አይሁዶች ጀርመኖቹ ወደጋጠሚያ ስፈር ብለው ወደመጠራት የኮንሶ

ሰፈር በየቀኑ ይላካሉ። ከነሱ አንዱ ለመሆን አልፈልግም። ኢቫ ኮስትሰር ወይም ራሄል ማንደል ቶንጀ ልጅ ነች። በዚህ በተዋወኩዋት አጭር ጊዜም ወድጃት ነበር። ግን ህይወቴን ለሷ ስል አሳልፌ ለመስጠት ተዘጋጅቻለሁ?

ያንን ማታ አልደወልኩላትም። እሷም ወደ ኮሲጁም ወደ ቤቱ በመምጣት ወይም በመደወል ልታነጋግረኝ አልሞከረችም። በዓይነ ቁራኛ እየተከታተሉዋት መሆናቸውን አውቃ እንድትርቀኝ ተስፋ አደረግኩ።

ከሁለት ቀን በኋላ በፖስታ ቤት በኩል አንድ ጥቅል መልዕክት ደረሰኝ። ለኢቫ የሰጠቷት የእንግሊዘኛ መማሪያ መፅሀፍ ነበር። መፅሀፉ ውስጥ በራምፐል ስቲልስኪን በተፃፈው ተረት ላይ የመፅሀፍ ገፆች መለያ ሪባን ተደርጉብታል። ሪባኑ ባለበት አካባቢ ላይ ከተረቱ ውስጥ «ድንክየው ጫካው ውስጥ ባለው ትንሽ ጉጆ ይኖር ነበር» የሚለው አረፍተ ነገር ተሰምሮበታል።

የኢቫ ወላጆች ብራንደንበርግ ባለው ፓርክ ውስጥ መኖሪያ ቤት እንዳላቸው አውቃለሁ። እዚያ እንደተደበቀች ለኔ መንገርዋና እንዳድናት መማፀንም ነበር። አንድ ቀለበትም በመፅሀፉ ገፆች ላይ በተሰራው ቀዳዳ ተደብቆ አገኘሁ። ቀለበቱ በርግጥ እኔነቴን ለመፈተን ነበር የተላከልኝ።

በምላ ሰዓት መፅሀፉን ከምድር በታች ወደነበረው ከፍል ወስጀ አቃጠልኩት።

ማታ ላይ ወደ ጫካው ውስጥ ወደሚገኘው ቤት ገሰገስኩ። የሚከተሉኝ ሰዎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደብኝም። ባርኔጣ ያደረጉና ካፖርት የለበሱ ሁለት ሰዎች እየተከታተሉኝ ነበር። ልለወራቸው ብሞክርም አልተሳካም። ከሁለቱ አንዱ ሁሌም ከኋላየ ነው። ብራንደንበርግ ላይ አምፊቴአትር አለ። ስለዚህ የማታውን ትርኢት ለማየት እንደመጣሁ አስመስዬ ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቴአትር ቤቱ ገባሁ። ትርኢቱ ካለቀ በኋላም ስዎቹ ከቦታው አልተንቀሳቀሱም። ወደቤቴ ሊሸኙኝ እየጠበቁኝ ነበር።

አቫ ጋር ስመድረስ ብዙ ጊዜ ሞክርኩ። ግን በቅርብ እየተከታተሉኝ ነበር። በመጨረሻም ሙከራዬን አቆምኩ። ትንሿ መኖሪያ ቤት ድረስ ሰመዝለት ከቃጣሁ በቀጥታ ወደ አቫ እየመራሁዋቸው መሆኔ ግልፅ ነበር። ይህ ደግሞ እርሷን ከመርዳት ይልቅ መጉዳት ይሆናል። ስለዚህም ሀሊናዬን በማረጋጋት ማድረግ ያለብኝን እያደረግኩ መሆኔንና ብርታት የተሻለ መሆኑን ራሴን አሳመንኩ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ወደ እንግሊዝ አገር በመመለስ ለጥቂት ወራት ቢቢሲ ውስጥ ስሰራ ቆየሁ። የ1939 (ኤ.ኤ.አ) አጋማሽ ላይ በእንግሊዝና በጀርመን መካከል ጦርነት እንደሚጀመር ለሁሉም ግልፅ ነበር።

አንድ ቀን ሚስተር ሮምፔል የሚባሉ ሰው ወደ ቢሮዬ መጡ። ሽማግሌ ናቸው። በመካከለኛ እድሜ ውስጥ ነበሩ። ፀጉራቸው ጥቅጥቅ ያለና ሊማቸውን ሙሉ በሙሉ ያሳደጉ ሰው ናቸው። «ሚስተር ራሰል ከወንድሜ ልጅ ከራሄል ማንደል የተላከ መልዕክት ይገርልህ መጥቻለሁ» አሉኝ።

«ውይ» አልኩኝ «እንዴት ነች? በርሊን ውስጥ ሰላሟር ጊዜ ተዋውቂያት ነበር።»

«አሷና ወላጆችዋ ተገድለዋል። ወደ ማጐሪያው ተልከው ነበር።»

«ጠማም ነው የማዝነው» አልኩ።

ፎቶግራፍ ሰጡኝ። ፎቶግራፉ በሚያሳዝን ሁኔታ የተበጣጠሰ ልብስ የለበሱና የብረት አጥር ባለበት ሰፊ ግቢ ውስጥ የቆሙ የሰዎች ምስል ያሳያል። ቦዝቢው መረት በዝናም ውሃ እንደራሰ ውሃ ካቆረ ኩራምቹ ለማወቅ ይቻላል። ሰዎቹም ምስኪኖች ጫማ የላቸውም።

«መሃለኛዋ ራሄል ነች» አሉኝ ሚስተር ሮምፔል «ሁለቱ ደግሞ ወላጆችዋ ናቸው።»

ይቺ ፀጉሯ የተላጨ እስከሚመስል ድረስ የተሸለተውና በተሟጠጠ ፊቷ ላይ ከብላላ ዓይኖች የሚታዩባት ምስኪን ፍጡር እንደ አቫ ኮስትሰር የተዋወቅኩዋት ንቁና ደስተኛ ሴት ነች ብሎ ለማመን ያስቸግራል። ዓይናቹ እንባ አቀረሩ።

«ፎቶግራፉን ከበስተጀርባው እየው» አሉኝ ሚስተር ሮምፔል። ስገለብጠው እስክማስታውሰው ድረስ እንዲህ የሚል ተፅፎበት ነበር።

«ውድ ፒተር። ጥሩ ጊዜ እያሳለፍኩኝ ነው። አየሩ ጥሩ ነው። ምግቡም የለመድነውን አይነት አይደለም። ካምቹ ሁላችንም የምንሳተፍባቸው የፈንጠዚያና የደስታ ዝግጅቶች ያዘጋጃል። በአሎቻችን ከተለመደው ውጪ የተራዘሙ ናቸው። ወደ ቤታችን እንዲመልሰን ጠይቀን ነበር። የኳምቹ ኋላፊ ግን ሊያዳምጡን አልፈለጉም።

«ፓርኩ ውስጥ ወሳላው ጫካ መጥተህ ዝር? የተቻለኝን ያህል ጠበቅሁህ። እንደሞከርህ ርግጠኛ ኖኑ። ግን ቦታው ሳይጠፋብህ አይቀርም። ደህና ሁን ፒተር! ጭግም እንገናኛለን»

ሚስተር ሮምፔል፣

«ፒተር እስቲ ንገረኝ? ፓርኩ ውስጥ ወደነበረው መኖሪያ ቤት ስመሄድ ሞክረህ ነበር?» ብለው ጠየቁኝ «ራሄል እንግሊዝኛ ለጀማሪዎች በሚል መፅሀፍ ውስጥ መልዕክት ልካልህ ነበር»

«አውቃለሁ» አልኩዋቸው። «ጀርመንን እስክለቅ ድረስ ወደ ቦታው ለመሄድ በተደጋጋሚ ሞክሬ ነበር። ነገር ግን ሁለም ቀንና ሲሲት ሁለት ሰዎች ይከታተሉኝ ነበር። እና እስክ መኖሪያ ቤቱ ድረስ ሰመዝለቅ አልደፈርኩም። በቀጥታ እርሷ ዘንድ እንዳልመራቸው ሲጋሁ። ለደህንነትዋ ስል ብተዋት እንደሚሻል ነበር የገባኝ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስተር ሮምፔል የምለውን እንደተቀበሉት ጭንቅላታቸውን በማወዛወዝ አረጋገጡልኝ

«ብትችል ኖሮ እንደምታድናት አርግጠኛ ነበረች ራሄል። እንግሊዛዊ እንድታገባ የመከሯት ወላጆችዋ ነበሩ። እነሱ በጣም የታወቁ ስለነበሩ ከበርሊን የሚያመልጡበት እድል አልነበራቸውም። የመኖር ተስፋቸው የመነመነ ነበር። ጭንቀታቸው ብቸኛዋ ልጃቸውን እንዴት ለማዳን እንደሚችሉ ነበረ። ፎቶግራፉን ልውሰደው? እሱ ብቻ ነው እነሱን የሚያስታውሰኝ።» አሉኝ።

ፎቶግራፉን ሰጠኋቸውና ጨብጠውኝ ሄዱ። ከዛ ቀን በኋላ አይቻቸው አላውቅም...

«እንግዲህ ይኸ ነው ታሪኩ። አሁን ያንቺን ጨዋ እንግሊዛዊ እንዴት ነው የምትፈርጂው? ከፊትሽ እንደማነበው ከሆነ ጥሩ አልሰራሁም። እርግጥ ነው እሷን ማግባት ነበረብኝ። ግን በጣም ሰግቼ ወይም በጣም ፈርቼ ነበር። ልረዳት ስወስን ደግሞ ጊዜው አምልጦኝ ነበር። እንደ የፊልም ተዋናዩ ስካርሌት ፒምፐርነል ከጀስታፖዎች አፍንጫ ስር በማውጣት አዳንኩዋት ብዬ ሳወራልሽ ችዬ በሆን ኖሮ ደስ ይለኝ ነበር። ይህ ግን አውነተኛ ታሪክ ነው ጁሊያ ... የፍቅር ልብ ወለድ አይደለም። ብራንደንበርግ ወደነበረው ጉዞ ሄጀ በሆን ኖሮ አሁን እዚህ አልቀመጥም ነበር። አንቺም እንዳሁ!»

«አያቴ ታሪኩን ስለነገርከኝ በጣም አመሰግንሀለሁ። ይህንን ቀለበት ልውሰደው? ልኪ ነው? ምናልባት አንተ ያልፈፀምከውን ነገር ለማካካስ አንድ ቀን ለተቸገረ ሰው ውሰታ አውል ዘንድ ሊያስታውሰኝ ይችላል።»

ልቦለድ



የገበፈሞች ልብ

ተስፋዬ ገብረአብ

በገበራና በአርሶ አደር መካከል ልዩነት መኖሩን ባለሙያዎች ይናገራሉ። በተለምዶው አነጋገር ግን አርሶ አደርና ገበሬ ልዩነት የላቸውም። ከተሜው አርሶ አደሩን ገበሬ አያለ ይጠራዋል። ከተሜው ሲላ ብዚልም አለው። አንድን ሰው «ያልሰለጠነ» ወይም «አላዋቂ» ነህ ብሎ መሰደብ ሲሻ «ገበሬ!» ይለዋል። እንግዲህ አርሶ አደሩን ገበሬ አያልን ጥቂት ስለገበሬዎች ልብ እናውጋ።

ሰመሀኑ «መስልጠን» ምንድነው? «አላዋቂነትስ?» በርግጥ ገበሬ ምን ያውቃል?

t.me/OLDBOOKSPDF

ገበሬ ጉንዳን ነው። ገበሬና በሬን ምን ለየው? ገበሬዎች ዱላ ይዘው፣ አህያ እየነዱ የሚጉዋዙ ሰው መሰል ፍጡሮች ናቸው። ልብሳቸው ያደፈ፣ ባርኔጣቸው የነተበ፣ በረባሶ ጫማቸው የተነቃቀለ፣ አህል - እንጨት - ኩበት - ጭድ - ክሰል - ገለባ በአህያ ጭነው ከገጠር ወደ ከተማ የሚተሙ የሰው ጉርፎች፣ የሚንጋጉ ጋጋታም ፍጡሮች። በፅዳታቸው ከአህዮቻቸው ያልተሻሉ፣ የተቀደደ ብር የማይቀበሉ ማይሞች። ማንበብ የማይችሉ አላዋቂዎች፣ አህልና ኩበታቸውን ሸጠው ሲያበቁ ጠጅ ወይም አረቂ ጠጥተው እየሰፈሰፉ ተራሮች ወደበዙባቸው አካባቢዎች ወደሚገኙ የገጠር ጉጀዎች የሚጉዋዙ .. ለአውሬዎች የማይደነግጡ ... ከአውሬዎች ጋር የሚኖሩ ሰው መሰል ሰዎች ... ገበሬዎች! «ገበሬ ምን ያውቃል?» ይላል ጥራዝ ነጠቁ የከተማ ሰው። «መኪና ሲያይ የሚደነብር፣ የተቀደደ ብር የማይቀበል፣ አሳንሰር አጠቃቀም የማይችል፣ ብልጭልጭ ቀለም የሚወድ፣ ገበሬ! ያልሰለጠነ!»

ገበሬን ተጠግቶ ያላየው ስለ ገበሬው አንዲህ አንዲህ እያለ ሊያስብ ይችላል። ጥቂት «ተማርክ» ያሰ ደግሞ ገበሬን አንዲህ አንዲህ እያለ ባይሰለውም «ገበሬ ምን ያውቃል?» ብሎ መጀመሩ ግን የተለመደና የማይቀር ነው።

በርግጥ ገበሬ ምን ያውቃል? ማረስ - መዝራት - ማረም - ማጨድ - መከመር - መውቃት - ማበራየት - ያን ሸጦ አረቂና ጠጅ መጠጣት - እና አንደገና ማረስ - ማረስ - ማረስ - በርግጥ ገበሬ ከዚህ ሌላ ምን ያውቃል?

ይህ ጥያቄ በቁራጭ መጣጥፍ ምላሽ ያገኛል ብዬ ታጥቂ አልነሳም። ሆኖም የስልጣኔና የተሻሰ ህይወት ሁሉ ምንጭ ገበሬ መሆኑን የራሱን የገበሬውን አውቀትና ልምድ፣ ህይወትና የጉሮ ዘይቤ ጠቅሼ፣ ካንብቡት አለያም ከሰማሁት ጥቂት እውነታዎችን ላካፍላችሁ እወዳለሁ።

በርግጥ ገበሬ ምን ያውቃል?

* * *

ገበሬ የአየር ጠባይ አዋቂ ሊቅ ነው ...

በኢህአዴግ የትጥቅ ትግል ዘመን በትግራይ ምድር የተፈፀመ ገጠመኝ ልንገራችሁ። የህወሀት ታጋዮች የደጀን ቦታ ለውጥ ለማድረግ ቁሳቁሳቸውን በአጋሰስ ላይ ጭነው ሲጉዋዙ ያልተጠበቀ የነገሮጉዋዴ ድምፅ ተሰማ። ሰማዩም በጥቁር ደመና ተሞላ። ታጋዮቹ ተረበሹ። አያሌ ሰነዳችን በመያዛቸው ዝናቡ ከዘነበ ወረቀቶቹ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ ብለው በመስጋታቸው መጨነቃቸው በረከተ። ቢያንስ አሰራ ሁለተኛን ክፍል የጨረሱት፣ አሰያም ኮሌጅ ቀመስ የሆኑት እኒህ ወጣት ታጋዮች ክፉኛ በመረበሻቸው ግርግር ሆነ። የታጋዮቹ መሪዎች ሰብሰብ ብለው መላ መዘየድ ያዙ። በአካባቢው የገበሬዎች ጉጀዎች የሉም፣ መጠለያ የለም! ዝናብ ሙጥቱአል። እነዚያን ውድ ሰነዶች በድንገት ከመጣው የዝናብ ዶፍ እንዴት ነው ማዳን የሚቻለው? እወጡ፣ አወረዱ! መፍትሄ ግን አላገኙም። ጭንቀት ነገሰባቸው። ታጋዮች ተተረማመሱ። ከፊሉ በሩጫ እንገስግስና የአርሶ አደር ጉጀ ወይም ቤተክርስትያን አንፈልግ ሲል፣ ሌላው ልብሶቻችንን ቀጣጥለን ድንኳን እንስራ ይል ጀመር። ይህን ሁሉ ጭንቀትና ትርምስ ዳር ቆሞ ይመለከት የነበረ አንድ አልፎ ሂያጅ መንገደኛ ገበሬ «ምን ችግር ገጠማችሁ?» ሲል ይጠይቃቸዋል። ችግራቸውን እንደዋዛ ነገሩት። ገበሬው ግን እንዲህ ሲል ያልጠበቁትን ምላሽ ሰጣቸው።

«ይህ የዝናብ ደመና እዚህ አይዘንብም። ወደ ሽሬ አቅጣጫ የሚጉዋዝ ነው። ስለዚህ አትስጉ፣ እዚህ አንዲት ጣሳ ዝናብ አንኳ ጠብ አትልም።»

ኮሌጅ ቀመሶቹ ታጋዮች ግራ በመጋባት አንዴ ገበሬውን፣ መልሰው ደግሞ የጠቆረውን ሰማይ ይመለከቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጀመር። ገበሬው ጠንቋይ ወይም ነቢይ አይደለም። ገበሬ ነው። የፊደልን ዘር አያውቅም። ሰሰ አየር ትንበያ የተፃፉ መዝሀፍትን ማንበብ ቀርቶ እንዲያ ያለ ነገር ስለመኖሩ አንዳችም አውቀት የለውም። አራሽ ገበሬ ነው። ልብሱ ያደፈ፣ ያለጫማ የሚሄድ ተራ ገበሬ። የህወሐት ታጋዮች ምንም የተሻለ አማራጭ ስላልነበራቸው ሰማይ ሰማዩን እንጋጠው እየተመለከቱ መጪውን ይጠብቁ ጀመር። ማምሻያው ላይ ግን ዝናብ ያዘለው ደመና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሲጉዋዝ ተመለከቱ። እየቆየ ሰማዩ ጠራ። አንድ ጣሳ ውሃ እንኳ ጠብ አላለም። ገበሬው ታዲያ ይህን እንዴት ሊገነዘብ ቻለ? የህይወት ልምድ!

* * *

ገበሬው የህክምናን ጥበብ ያውቃል!

አሁን ደግሞ ጉንደር ልውሰዳችሁ። አማራ ገበሬ ዘንድ። አስራ ሁለት ያህል የእድገት በህብረት ዘማቾች በሴሊት ጉዞ እያደረጉ ነበር - ለአንድ ተልዕኮ። ጨረቃ የሌለችበት ድፍን ያለ ሌሊት ነበር። ወጣቶቹ በጉዞ ላይ ሳሉ ከፊት ይጉዋዝ የነበረው ወጣት ዘማች ጨለማው አላስቆት የቁልቁዋል ተክል ከበቀለበት ጉድጉዋድ ውስጥ ወደቀ። ቀሪዎቹ ተማሪዎች የወደቀ ባልደረባቸውን ጉትተው አወጡት። የዘማቹ ሰውነት በቁልቋል እሾህ ተጠቅጥቆ አሪታውን እያቀለጠው ነበር።

ጉዞው ተቋረጠ። ሲነጋ ዘማቾቹ በቁልቁዋል እሾህ የተወጋውን ተማሪ ሊረዱት ሞከሩ። ግን አንድ የቁልቋል እሾህ በነቀሱ ቁጥር ዘማቹ ህመሙ ሊያሳብደው እየደረሰ አሪ ይላል። የህክምና ሙያ የተማረች ጤና ሪዳት ተጠርታ መጣች። አልኮል ቦናጥ አድርጋ ሰውነቱን ገና ስታሸነካ ወጣቱ ተማሪ በአልኮሉና በእሾሁ ድምር ታጠሶ እየተለበለበ በስቃይ ሊሞት ሆነ። በመላ ሰውነቱ የተጠቀጠቀውን

እሾህ ነቅሶ መጨረስም የሚሞከር አልሆነም። እንግዲህ በዚህ መካከል ነበር አንድ ተራ ገበሬ ከተፍ ያለው። ጤና ሪዳትዋና ፊደል የቆጠሩት ዘማች ተማሪዎች ህመምተኛውን ዙሪያውን ከበው የሚሰሩትን ተግባር የተመለከተው ገበሬ ሁሉም ዘወር እንዲሉለት ጠየቀ። ገበሬው በቁልቁዋል እሾህ የተወረረውን ሰው አገላብጦ ካየ በሁዋላ «በሐይ ላይ አውጡት!» ሲል አዘዘ። ተሸክመው አወጡት። «የቁልቁዋል ገቡቴ አምጡልኝ» ሲል ደግሞ አዘዘ። አመጡለት። ገበሬው ከቁልቁዋሉ ገቡቴ የሚገለገለግ ፈሳሽ እየጨመቀ የተማሪው ሰውነት ላይ ያፈሰው ጀመር። የሙጫ ባህርይ ያለው የገቡቴው ፈሳሽ በዘማቹ ሰውነት ላይ ከተጠቀጠቁት እሾሆች ላይ ሲያርፍ እንደ ማሚት እያንዳንድዋን እሾህ እያነቀ ቅርጫሊስ ሲላ ገቡቴ ሰራ። ገበሬው የዘማቹ ሰውነት ላይ የገቡቴውን ፈሳሽ አርከፍክፎ ከጨረሰ በሁዋላ ለአንድ ሰዓት ያህል ፀሐይ ላይ እንዲቆይ አደረገው። ከዚያም ወደቤት እንዲያስገቡት አዘዘ። ጥቂት ደቂቃዎች ጠበቀ። የፊደልን ዘር የማያውቀው ገበሬ አሳት ነክቶት ሲቀዘቅዝ መልሶ እንደሚደርቅ ፕላስቲክ ወደ ጠጣርነት የተለወጠውን የገቡቴ ፈሳሽ ጫፍ ይዞ መዘዘው። የገቡቴው ፈሳሽ እያንዳንድዋን እሾህ ከዘማቹ ሰውነት ላይ እየመዘዘ ይዞ ተነሳ። ህክምናው አበቃ። ይህን ጥበብ የሚያውቀው ያ «አላዋቂ» ገበሬ ነው። የተቀደደ ብር የማይቀበል፣ ያ አሳንሰር አጠቃቀም የማይችል፣ ቂል መሰሉ ገበሬ። ያደፈ ልብስ የለበሰው፣ መጫሚያ የሌለው፣ ከማረስና ከመጐልጐል፣ ጠላ ከመጠጣትና አህያ ከመንዳት ሌላ አውቀት ያለው የማይመስለው ገበሬ፣ ግን ይህን አውቀት ከየት አገኘ? ከህይወት ልምድ!

* * *

አሁንም ሰሚን ኢትዮጵያ!

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮሌጅ ተመሰ ዘማቾች በአንድ ወቅት ስብሰባ ብለው ሲያወጉ፣ ስለ ገበሬው አኑዋኑዋር አነሱ።

«ገበሬው ለምንድነው ቤቱን ከረብታ ላይ የሚሰራው? ይህ ድንቁርና ነው። መሀይምነት ነው። ጉጅን ከረብታ ላይ መቀለስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት ኩዩ አይመችም። ውሃና መብራት ለማስገባት አንቅፋት ይሆናል። ስለዚህ ገበሬው ቤቱን ሜዳ ላይ እንዲሰራ ማስተማር አለብን።»

ኮሌጅ ተመሶቹ ወጣቶች በዚህ ተስማሙና ገበሬውን ስብስበው ይህን «ወርቃማ አውቀት» በጣፈጠ ቋንቋ አስተማሩ። ገበሬዎቹ በዝምታ አዳመጡ። ኮሌጅ ተመሶቹ ሚዳማ ቦታ ላይ ጉጅን መቀለስ ያለውን ጠቀሜታ ተነተኑ። በውነቱ ትንታኔው ግሩም ድንቅ ነበር። እንዲያውም ንግግሩ ባማባቡ ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ ለመፅሄት የሚሆን መጣጥፍ በወጣው። ግን ምን ዋጋ አለው፣ አንድ ሽምገል ያሉ ገበሬ እሽቸውን አውጥተው በተናገሩት ሶስት አረፍተ ነገር ያ ሁሉ ጥበብ የተላበሰ ትንታኔ ውሃ ጠጣ፣

«የምትሉትን ሁሉ አሳምረን እናውታለን» ሲሉ ጀመሩ ገበሬው፣ ቀጠሉም - የፊደልን ዘር የማያውቁት ገበሬ «... እኛ፣ ጉጆዎችንን ተራራ ላይ የምንሰራው እንደ ጠላ ጽገት መውጣት አምሮን፣ አለያ የዝንጀሮ ዘር ናሮብን አይደለም። ሜዳ ላይ ከሰፈርን ወባ ትጨርሰናለች። ስለዚህ እዚያ ሜዳው ላይ ሐኪም ቤት ስሩልን። እኛ መካሪም አንፈልግ - ከረብቶቹን ለቀን ወደ ሜዳው እንወርዳለን።»

ገበሬዎች ከወባ ጋር ለዘመናት ታግለው አሸንፈዋታል። የወባን በሽታ ተቋቁመው ህይወት አንድትቀጥል አድርገዋል። ግን ገበሬው ይህን የመሰለውን መጣን የመከላከል ጥበብ ከየት አመጣው? ከህይወት ልምድ!

* * *

ገበሬው የአመራርን ጥበብ ያውቃል!

በ1977 ሱዳን ድንበር ላይ የተፈፀመ ታሪክ ላውጋችሁ። የሰሜን ኢትዮጵያ ገበሬዎች በድርቁ ምክንያት ቀያቸውን ለቀው በሱዳን ምድር ላይ ተሰብስበው ነበር። በወቅቱ የደርግን መንግስት ለመጣል ሽምቅ ውጊያ ያካሂዱ የነበሩ ታጋዮች የገበሬዎችን ህይወት ለማትረፍ አርዳታ ጠይቀው በሚሊዮን የሚቆጠር እሽግ ዓሳ ለገበሬዎቹ አቀረቡ። ገበሬዎቹ ምንም እንኳ በሞትና በህይወት መካከል ቢሆኑም ጊዜው ያም በመሆኑ ዓሳውን አንደማይመገቡ ተናገሩ። ነባርና የበሰሉ ታጋይ ካድሬዎች ገበሬውን ሰብስበው ህይወታቸውን ለማትረፍ ዓሳውን መመገብ እንደሚገባቸው በገበሬው ቋንቋ ተናገሩ። ግን ሳይሆን ቀረ። እኒያ የገበሬውን ስነልቦና ጠንቅቀው «የሚያውቁ» ካድሬዎች የተለያየ መንገዶችን በመጠቀም ገበሬውን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት ከሸፈ። ማጣፊያው አጠረ። ዓሳ አያለ ገበሬው በረሀብ ሊሞት ሆነ። ገበሬው «ለአምነቱ አሞታለሁ» አያለ አስቸገረ። ነባር ካድሬዎች የሚያደርጉት ጨንቆዋቸው ግራ በተጋቡባት ደቂቃ አንድ ገበሬ ጠጋ ብሎ ምክር ለገሳቸው፣

«መፍትሄው ቀላል ነው» አሰ ገበሬው «... ዓሳውን እዚሁ ሜዳው ላይ ትታችሁት ሂዱ!»

ካድሬዎቹ የገበሬውን ምክር ሰሙ። በቆርቆሮ የታሸገውን ዓሳ ስደተኞቹ በሰፈሩበት አካባቢ ጥለውት ሄዱና በማለዳ ተመልሰው መጡ። ገበሬዎቹ ሴሊቱን ዓሳውን ቅርጥፍ አድርገው በልተውት እድረዋል - ማንም ሳያይ። ጠዋት ግን «ዓሳ ያለመብላት» አቋማቸው አንደተጠበቀ ነበር። ሌሊቱን ግን በልተዋል። ስለዚህም ገበሬው የአመራርን ጥበብ ያውቃል። የሰውን ልጅ ስነልቦና ይረዳል። ግን የት ተማረው? ከህይወት።

t.me/OLDBOOKSPDF

* * *

ገበሬው የመሬትን ጥቅም ያውቃል ...

ከማንም በላይ መሬትን የሚያውቃት ገበሬው ነው። አንድ ባለሀብት ገበሬውን አታልሎ መሬቱን ሊገዛው ከቶ አይችልም። ከነተረቱ «በሚስትና በርስት ቀልድ የለም» ይላል የጐሸም ገበሬ። ስለሆነም ገበሬ ተታልሎ መሬቱን አይሸጥም። መሬት መሸጥና መለወጥ እንደሌለበት ገበሬው አሳምሮ ያውቃል። መካሪ አይሻም። ገበሬ መሬቱን እንደዋዛ አይሸጥም። ስለተመከረ፣ አለያም ሀግ ስለወጣ አይደለም። መሬቱን መሸጥ እንደሌለበት ስለሚያውቅ መሬቱን አይሸጥም። ገበሬ በመሬት ጉዳይ ላይ ጥንቁቅና ብልህ ነው። ፐርል ኤስ በክ የተባለች ደራሲ «The Good Earth» በተባለ መፅሀፍዋ የቀረፀቻቸው ሁለት ቻይናውያን ባልና ሚስት ገበሬዎች ለዚህ አባባሌ መልካም አብነት ይሆኑናል። ባል ዋንግ ሉንግ ይባላል። ሚስት - አላን። ቁራጭ መሬት ነበራቸው። ሆኖም ድንገተኛ የገሃናብ እጥረት በመከሰቱ ረሀብ መጣ። የሚላስ የሚቀመስ አጡ። ልጆቻቸው ከሱ፤ ጠወለጉ። በሞትና ህይወት መካከል ባሉባት ደቂቃ የከተማ ጮሌ ባለሀብቶች ድንገት ከተፍ ብለው «ለምትሞቱ መሬታችሁን እንግዛችሁ?» ሲሉ ጠየቁዋቸው። ዋንግ ሉንግ በቁጣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤

«ከቶ መሬቴን አልሸጥም። ይልቁን ቀስ በቀስ መሬቴን እየቆፈርኩ አፈሩን ለልጆቼ አበላለሁ። ሲሞቱም በመሬቴ ላይ እቀብራቸዋለሁ። እኔም ሆንኩ በተሰቤ በዚች በተወለድንባት ምድር ተመልሰን እንገባበታለን» በማለት ተንሰቅሰቆ ያለቅስ ጀመር። ባለቤቱ አላን ደግሞ እንዲህ ስትል አከለች፤

«መሬታችንን ፈፅሞ አንሸጥም። አሁን ህይወታችንን ለማትረፍ ወደ ደቡብ እንሰደዳለን። መሬታችንን ከሸጥን

ከደቡብ ስንመለስ ልጆቻችንን ምን ልንመግብ ነው? የምትገዙ ከሆነ ጠረጴዛና ወንበሮቻችንን እንሸጥላችሁ። ከዚያም ጐላችንን እንሸጣለን፤ ዶማና መንሻችንን ግን ከቶ አንሸጥም።»

ዋንግ ሉንግና አላን ገበሬዎች ናቸው። የቻይናን የፊደል ዘር አያውቁም። የመሬትን ጥቅም ግን ከማንም በላይ ይረዳሉ። ምክንያቱም እነርሱም መሬት ናቸው። የገበሬዎች ልብ ለመሬቱ ቅርብ ነው።

* * *

ገበሬዎች የዴሞክራሲን ዕንሰ ሀሳብ ያውቃሉ፤

ለአብነት የኦሮሞ ገበሬዎችን ልምድ እንመልከት። የቦረና ገበሬዎች የእኩልነትና የዴሞክራሲ መሰረት ነበሩ። ቦረናዎች በሸንጐ ይተዳደሩ ነበር። የቦረና ሸንጐ አሰራር ማንኛውም ሰው የራሱን ፍላጐት በሌሎች ላይ እንዲጭን የሚያግዱ ህጐችና ደንቦች እንደነበሩት ዶክተር ማርክ ባሲ የተባለ ኢጣሊያዊ የአንትሮ ፖሎጂ ምሁር አረጋግጠዋል።

የቦረና ኦሮሞዎች በዓመት አንዱ የሚሰበሰብ ሸንጐ ነበራቸው። የሸንጐው የስብሰባ ጊዜ ከወር በላይ ሲዘልቅ ይችላል። በዚህ ጉባኤ የቦረናዎች የጐሳ አባሎች በሙሉ የመሳተፍ መብት ነበራቸው። ከዚህ ከዋናው ጉባኤ ቀደም ብሎም በቤተሰብ ወይም በመንደር ደረጃ መለስተኛ ስብሰባዎች ተደርገው ችግሮች ይመክርባቸዋል። ከጉባኤው በሁዋላም እንደገና የመንደር ስብሰባዎች ተጠርተው ውሳኔዎቹን እንዲያውቁ ይደረጋል።

በጐሳ ሸንጐዎች ላይ የግል ችግሮች፣ የቤተሰብ አለመግባባቶች፣ የህብረተሰቡ ቁልፍ ችግሮችና እንገብጋቢ የሆኑ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በዝርዝር ይመከርባቸዋል። የውርስ ጉዳይ ይነሳል። እቅመ ደካማ ለሆኑ ወገኖች ወላድ ከብቶች ስለሚለገሱበት፣ ከጐሳው አባላት ለተለያዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

አላማዎች ስለሚስከበሱ የመዋጮ ጉዳዮች እየተነሱ ከተመከረባቸው በሁዋላ አስፈላጊ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል። ታዲያ የቦረና አርሞች ዛሬ ከፖለቲከኞች እንደበት የማይጠፋውን የዴሞክራሲ ዕንስ ሀሳብ ከየት አገኙት? ከህይወት ልምድ!

* * *

ገበሬዎች ቅኔ ያውቃሉ!

«ገበሬ ምን ያውቃል?» ለምን እንላለን። ገበሬዎች ቅኔ ያውቃሉ። ካሻንም የገበሬውንና የምሁሩን ግጥሞች ጎን ለጎን አኑረን ማወዳደር እንችላለን። እንዲያውም በተመሳሳይ ዓመትና ወራት የተፃፉና የተቀኙትን ግጥሞችን ቀነጫጭበን እንይ፤

ዶክተር ፈቃደ አዘዘ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነ ዕሁፍ ባለቅኔና ምሁር ናቸው። መስከረም 30/1983 እንዲት አጭር ግጥም አስፍረዋል። የፖለቲካ ትኩሳቱ በናረበት በዚያ ወቅት ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ያለፈሩት ግጥም ርዕስ «ለስጋ ውድነት» የሚል ነበር። ግጥሙ እነሆ፤

ፍየል ምልኮ፤ ፍየል ተርፎ
ላሙ ምልኮ፤ በሬው ተርፎ
በጉ ምልኮ ...
ምን ቢመጣ፤ አዲስ ታምር፤ አዲስ ነገር፤
ከብት ይወደድ፤ በከብት ሀገር።

«አያ ጉሽሜ» በሚል ርዕስ ከታተመው መፅሀፍ ላይ ያገኘሁትን ይህን ግጥም ከገበሬዎች ግጥም ጋር አወዳድራችሁ ተመልከቱ።

የግጥሞቹ ባለቤት የሆኑት ገበሬዎች ስም የላቸውም። በደፈናው የፊደልን ዘር የማያውቁ የአማራው ምድር ገበሬዎች ናቸው። ግጥሙን ያቀነቀኑበት ጊዜ የ1983 ዋዜማ ነው። ዶክተር ፈቃደ ስለ «ስጋ መወደድ» ቅኔ

በተቀኙበት ዘመን ማለት ነው። ገበሬዎቹ ግን እንደ ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ስንኞቸውን በወረቀት አስፍረው የመደለዝና የማስተካከል አድሉ የላቸውም። ከአንደበታቸው እንደወረደ ያቀነቀኑት ግጥም፣ ይዘት፣ የቋንቋ ጥራትና ዜማ እነሆ፤

አነ ዶሮ ምሳው፤ አነ አንቋላል ቁርሱ
ወልዲያ ቢተኩሰ፤ ደሴ ላይ ደረሱ፤

* * *

ለላሳ ሰራ ለስኪያጅ - በለላሳ ኮቢ እየለቃለቃ
ሰራም ለልተሰራ - ደህው ጉኑ ለለቀ።

* * *

ቀና ብዬ ባየው - ሰማዩ ቃለሰኝ
እሱንም ሰፈራ - ወሰጹት መሰለኝ።

* * *

በግር ለልሆን ሲለው - መጣ በሰማይ
መሬት ከለቀቀ - መንግስት ለለ ወይ?

* * *


ደርግን ሞት ሲሸተው - ሲታየው ውድቀት
ለይባል ሰላምታ - ለይባል ናፍቆት
ይነሰንስ ጀመር - ብጣሽ ወረቀት
ደብዳቤስ ለመፃፍ - የኔም ልብ ይመኛል
ታዲያ ወረቀቱን - ማን ያደርስልኛል?

* * *

እና ገበሬ ቅኔ ያውቃል። በቋንቋዎችና በስነ ዕሁፍ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ዲግሪ ባይኖረውም መልካም ቅኔ ያውቃል።

ገበሬን «ለላዋቂ» የሚለው ከተሜና ፊደል የቆጠረው የህብረተሰብ ክፍል ባዶ የመኩራራት ልማድ ሲያጸበር እንዳልቀረ ይለማኛል። ለ«ፅውቀት» የምጓጓው ትርጉዋሜ ሚዛኑን እንዳልጠበቀ ማጤን ይገባናል። በርግጥ አጠቃቀሙን በቅጡ ባናውቅበትም በየቢሮአችን ኩምፒዩተር መገተሩን

t.me/OLDBOOKSPDF



ሽርሙጥና

አሸቱ ተፈራ

በዮንት ዘመን አንድ ወንድ ብዙ ሴቶችን ማግባት በመቻሉና ጋብቻም በወጣትነት ዘመን ይፈፀም ስለነበር ሽርሙጥና በመሠዳደረያነት አያገለግልም ነበር። ሆኖም በዮንቱም ዘመን ቢሆን በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይካሄዱ የነበሩ አስገራሚ ሁኔታዎችን ማውሳት ይቻላል።

ማርገራት ሚድ የተባሉ እውቅ የማህበራዊ ኑሮ ሊቅ እንዳጠኑት የተማረኩ ባሪያ ሴቶችን እያከራዩ በገቢ ምንጭነት የሚገለገሉባቸው ፈንጋዮች እንደነበሩ ይናገራሉ። በእያንዳንዱ ህብረተሰብ ደግሞ የከረዶች ሽርሙጥና በግልፅ

ትያዝበትም። ወንጀለኞችን ላይ ናኑይል አልበሰንም ቢሆን እድረግል። ያም ካለ ተስክሌን ቢሆንስ ከሙ ፒዩተርን በጎደናችን ለማየት ቻችተናል፡ ሀሳችን ነበተናል። ያም አልሆም ቢባል ቢሆንስ ቢሆንስ ብለ ከ ተንሳደናል። እና ስልጥናል። አኖር ሆንል። ሽራ አደረለንም፡ ደህ ግን ሰዳ አደረም። ሰብን ማጎሳል አየጂ። ወጪሬ ምን ሳውቃል አየልን መቀበል ከቮ አደጋለንም። የፈርልን ዘር ያልለየው፣ መሳሽ ያካከለው ገሪ ብዙ ነዝር ያውቃል።

ደግኑ ስናሽሙቀዋለው ዘንውልም ገሸሬው አደሎግንም። አያገኝም። ለላው ሳሪት ደህ መቀየሩ እጂ ገሸሬሞ ዘንር አርፈረሽም። ቢሆነውም በገሸሬው ህደውት ላይ ሶሚያመላው ለውዋ ሃለም። ገሸሬው አድኮሚ ስራ አለበት። ምሮሪቱን ሚረስ እድግ ከባር ተግባር ነው። አደረጅም ሥዲያ ገም አደልም። አንር ዶንቱ ውሚያዙ ቃላት፣ አንር መሪና ውሂልስ ሮማህ ቅኔ ያጨልቃል። ምነው ምንኛ ስራቱ እደን ውብ ቃላት መልሰም በዘን?

እግሩህ ከ በኩል አለቱ። ለመሮምሲሚያ ግን ሶሞቱው የሩሲያ ደራሲ እቮን ቱርጌኔቭ ምሽው የህዘብ አካል ስለሆነው ገሬ ያስፈራትን አንድ አባባል ላስተውሳችሁ።

ሕዝቦቹ ነዝበት ላይ መቀለድ ይቻላል ብለትሁ አታስቡ። ህዝቡን ቅንጣት ታህል ማቀለል አደቻልም። ህዝብ ከኛ ከእናንተንችን የነቢነበ ብልሀ ነው። ስህዝቡ ሁሉንም ነዝር ራሳችሁን ለስተቻችሁ፣ ደማችሁንና ላብችሁን አፍሳችሁ፣ ለስራችሁት ስራ፣ ህዝቡ ስራችሁ ከየኩሩና ድኮማችሁንም ሞጋ ስለነው፣ እናንተንም ማስተማል ከጀመረ የነቢነበ ስህዝቡ ባለሙለት መሆን አለባችሁ። ደህ ሰው ነው። ነቢነበ ልናገኝ ህዝቡ ለእናንተ ያስፈልጋችኋል እንጂ ስህዝቡ እናንተ አታስፈልጉትም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይካሄድ እንደነበር ይወሳል። የዚህ ምክንያቱ ከስፍራ ስፍራ ይለያያል። በአንዳንድ አካባቢ ልጃገረዲቱ ለእቅመ ሂዋን መድረሷን የምታሳውቀው ሀዘን በማስነሳስ ሲሆን ድርጊቱንም ሁበረተሰቡ የሚደግፈው ፍቁድ ባህል ነበር። ልጃገረዲቱ እየሸረሞጠች የምታጠራቅመው ገንዘብም በየሱሺ መልክ ሰባሷ ይከፈላል።

የአንግሊገሸው የአክስፎርድ መዝገበ ቃላት ሽርሙጣ የሚለውን ቃል «ገንዘብ በመቀበል ገላዋን የምትሸጥ» ሲል ይተረጉመዋል። ሽርሙጥናና ግልሙትና ይቀራረባሉ አንጂ አንድ አይደሉም። ሳጤ ሴቶች ተፈጥሮአዊ ፍላጉታቸውን ለማርካት ወንድ መሄዳቸው አይቀርም። ገንዘብ አስካልተከፈላቸው ድረስ ግን ሽርሙጠኞ አይባሉም። ጋለሞታ ሊባሉ ይቻላል፣ ዝሙት አዳሪ ማለቱ ግን አያስኬድም።

በዘሊሎንና ቆጵሮስ የባዕድ አምልኮ በሚካሄድባቸው ስፍራዎች መሸርሞጥ እንደ ቅዱስ ተግባር ይቁጠር ነበር። በዘሊሎንውያን ባህል መሰረት እገሌ ከእገሌ ሳይባል ሁሉም ሴት ኤስተር በተባለችው ሴት-አምላክ መቅደስ ተገኝቶ መሸርሞጥ ከኃይማኖታዊ ተግባሩ አንዱ ነው።

ሩክቤ ሲጋው የሚፈፀመው ከአልር ሊያድ መንገደኛ ጋር ብቻ ሲሆን ሰውየው ከተኮሰኮሱት አንዲን የሚመርጠውም ፍራንክ ጭኗ ላይ በማስቀመጥ ነበር። ገንዘቡ አነስ በዛ ተብሎ ክርክር መግጠም የለም፣ የተገኘውን አመስግኖ መቀበልና መተኛት እንጂ። አንዳንድ መልከ-ጥፉ ሴቶች ወንድ በቀላሉ ስለማያገኙ ከመቅደስ ሳይወጡ ብዙ ዓመትን ያሳልፉ ነበር። ወንድ ካለተኛቸው የኃይማኖት ግዴታቸውን እንደተወጡ አይቆጠርምና። ገንዘብ ተቀብለው ሩክቤ ሲጋ ከፈፀሙ በኋላ ግን ግልጋሎታቸውን መፈፀማቸው ተረጋግጦ ሽርሙጥናው ይቆማል።

በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ሀዘ ያልተነሰሰ ልጃገረድን ያገባ ወንድ ከፉ ዕጣ ያጋጥመዋል ተብሎ ይፈራ ስለነበር ልጃገረዶች ድንግላቸውን በግድ ማስጠፋት ነበረባቸው። አሁንም ቢሆን በአንዳንድ ስፍራዎች ድንግልናዋን የጠበቀች ልጃገረድ የማትፈለግበት ሁኔታ አለ። ስለዚህም ልጅቱ ለአቅመ ሂዋን መድረሷን የምታሳውቀው ሀዘን በግዝለስና በመሸርሞጥ ነው።

በአይሁዶች ዘንድ ግን ዘርንና የኃይማኖትን ቅድስና ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት የተነሳ የተለየ ባህል ነበር የሚታውቀው። ሽርሙጥና የተፈጠረው የውጭ ሀገር ተወላጅ ለሆኑ ሴቶች ብቻ ሲሆን አይሁዳውያን ካህናት ልጆቻቸው በሽርሙጥና ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ይከላከሉ ነበር። (ሌዋ፣19:29፣ ዘዳግ፣23:17፣ ሌዋ 21፣9) ያም ሆኖ ፍልስጤም ውስጥ የሽርሙጥና ስራ በስፊው ይካሄድ እንደነበረ የሚጠቁሙ ዕሁፎች በአሪት ውስጥ በብዛት ይገኛሉ።

ሽርሙጦች በኢየሩሳሌምና በቤተአምልኮዎች አካባቢ እንዳይገኙ ቢከለከሉም አውራ ጉዳናውን ግን ያጥለቀለቁት እንደነበር ብዙ ማስረጃዎች ይናገራሉ። በሽርሙጥና ተግባር ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ለማስታወቅም የተለየ ልብስ ሰብሰው የተለየ ጌጥም ያደርጉ ነበር። በፍልስጤም የነበሩት ቅሬዎች ግሪኮችና ሮማውያን መሆናቸውንም ታሪክ ይዘግበዋል። ግራም ነፈስ ቀኝ ሙሴ የህዝቡን ጤንነት ለመጠበቅና የእባለዘር በሽታን ለመከላከል ሲል ሽርሙጥናን ከለከሉ። (ሌዋ፡25)

ሴቶች ለወንዶች ጥሎሽ እንዲከፍሉ መደረጉ ሽርሙጥናን በጥንት ዘመን እንዲስፋፋ እንዳደረገ ጠበብት ይናገራሉ። የሊዲያ ወጣት ሴቶች ለጥሎሽ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሽርሙጥናን በስፋት ተያይዘውት ነበር። ፓላው የሚባለው ደሴት ነዋሪዎችም ከሽርሙጥና የሚገኘው

t.me/OLDBOOKSPDF

ገንዘብ ስለጣማቸው ልጆቻቸውን በሽርሙጥና ተግባር ላይ በብዛት አሰማርተዋል። የጥሎሽ ገንዘብ ለመስጠትና ሲሉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአልጀሪያ የሚገኘው የኡሊድ ናይል ጉሳ ተወላጆች ልጆቻቸውን ያስሸረሙ ነበር። ለዚሁ ተግባርም ወደ ጎላልት ከተሞች ሂደው በመሸርሞጥ ጠቀም ያሰ ገንዘብ ከሰበሰቡ በኋላ ወደ መንደራቸው ተመልሰው በወግ በማዕረግ ይዳራሉ። መልኩም ባል የሚያገኙትም በርከት ያለ ገንዘብ በጥሎሽ መልክ ሲያበረክቱ እንደሆነ ይታወቃል። የሽርሙጥና አጀማመር ከኃይማኖት ጋር የተያያዘ ቢሆንም እያየለ የመጣውን ግን በኢኮኖሚ ምክንያቶች መሆኑ ግልፅ ነው።

ለአብነት ያህል በግሪክ አገር ሶሎን የተባለው ገዢ ቤተ-ግልሙትናን የመንግስት ሞኖፖሊ በማድረግ በገቢ ምንጭነት ይጠቀምበት እንደነበር ይታወቃል። ቦታ ከልሎ፣ ህግ ደንግጐ ሽርሙጥናን ያካሂድ ነበር። ሽርሙጥቹ የሚኖሩበት ስፍራ ግን የተለየ መሆን ስለነበረበት ከተማይቱ መሀል መቀመጥ አይፈቀድላቸውም። የተለየ ልብስ እንዲለብሱና በቤተ አምልኮዎች አካባቢ እንዳይገኙም ማዕቀብ ነበረባቸው። ቢሆንም፣ ህጉን በሚገባ ለማስከበር በጣም አዳጋች እየሆነ ስለመጣ አስተዳደራዊ ሁኔታው እየተወሳሰበ ችግር ተፈጠረ። አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣኖችም መንግስት በሽርሙጥና ተግባር ውስጥ እጅን ማስገባት የለበትም ሲሉ በግልፅ መቃወም ጀመሩ።

በርም ግን ሁኔታው ለየት ያለ መልክ ይስተዋልበታል። ጋብቻንትን መቃወምና ሞራልን መጠበቅ ትልቅ ዋጋ ይሰጠው ነበር። የዘር ንፅህና መጠበቅ አለበት የሚሰውም ፍልስፍናቸው ከአይሁዶች ጋር ይቀራረባል። በመሆኑም ከሽርሙጦች ጋር መታየት ታላቅ ውርደት ነበር። ሽርሙጥናን የሚመለከተው ህጋቸው ጠበቅ ያለ ሲሆን ሽርሙጦች በጠቅላላ በፖሊስ እንዲመዘገቡ ይደረጋል።

የተለየ ልብስ እንዲለብሱ፣ ወጉራቸውን ልዩ ተለያ እንዲተቡ ወይም በጫጌ ሚገ እንዲያጠልቁም ይታዘዛሉ። ህገኑም ይጫናቸዋል። መንግስትም ከፍተኛ ግብር በመጣል ይቆጣጠራቸዋል። ይህ ከፍያ ለብዙ ዘመናት ቆይቶ የተቋረጠው በአራተኛው ክፍለ ዘመን ነው። ይህም የተወሰነው አንድ የቫስሪንስ ተወላጅ ባለፀጋ ከሽርሙጦች የሚገኘውን የቀረጥ ገንዘብ ከግል ገቢዉ እከፍላለሁ በማለቱ ነበር። በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ግን የሽርሙጥና ታክስ ጭርሱኑ ተሰረዘ። የሽርሙጦችን ስም ዝርዝር የያዘው የከተር መዝገብም ወይፋ ተቃጠለ። በሽርሙጥና ይተዳደሩ የነበሩ ሴቶችን መልሶ ለማቋቋምና ከህብረተሰቡ ለመቀላቀል ሙከራ ቢደረግም ጥረቱ ግን እምብዛም አልተሳካም።

በመካከለኛው ዘመን ሽርሙጥና ፍቱድ ሆነ። ቢሆንም በጣም እንዳይስፋፋ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። ቡተስይ የክርስትና ኃይማኖት የጋብቻን ቅድስናና የአመንዝራነትን ሙጥፎንት አጥብቆ ያስተምር ስለነበር በሽርሙጥና ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም። የአንድ ላንድ ጋብቻን አስፈላጊነት በመሰበኩም ቀስ በቀስ ሽርሙጥናን ለማዳከም ችሏል። ፈፅሞ ማጥፋቱ ግን አልተሳካለትም። በኋለኛው ዘመን ታላላቅ የቤተክህነት መሪዎችና ቅን አሳቢ ምእመናን ሴቶችን ከሽርመጥና ለማውጣት ከፍተኛ ትግል አድርገዋል። ሴቶቹ ንስሀ እንዲገቡና ከህብረተሰቡ እንዲተላቀሉ ከመጣራቸውም በተጨማሪ ኑሯቸውን ለማቃናት ይችሉ ዘንድ በርካታ መጠለያዎችን አቋቁመውላቸዋል። ጥሎሽ ሳይቀር እየከፈሉ ለደህና ደህና ባል ድረዋቸዋል። ፓፓ ኢ ኖስንት ሳልሳዊም ህገዙን ለማስፈፀማቸው በማሰብ ሽርሙጣ የነበረች ሴትን ያገባ የተከበረ ነው በማለት ይሰብኩ ነበር። አንዳንድ ቋሳሳትም የቤተ ግልመትና ኃላፊዎችን በየቤተክርስቲያኑ እየተገኙ ኃላ እንዲሰብሰቡ ከመከማት እንዳይከለክሏቸው ያደርጉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠንድ ለነገስታት ደብዳቤ ልከዋል።

ወንደላጤዎች ንክህ የገቡ ሽርሙጥቶን እንዲያገቡ ግፊት እንዲደረግባቸው፣ አሻፈረኝ ካሉ ደግሞ ለማግባት እንዳልፈለጉ ተቆጥረው ገዳም እንዲገቡ እንዲደረግ መንግስታት ያስገድዷቸው ዘንድ ሙከራ ተደርጓል።

ፊውዳሊዝም በነገሰበት ዘመን ጋብቻ የማፍቀርና የመፈቀር ጉዳይ ሳይሆን መሳፍንትና መኳንንት ግዛታቸውን ለማስፋትና ስልጣናቸውን ለማጠናከር የሚጠቀሙበት መሳሪያ ስለነበር የሚወስነው በተጋቢዎቹ ሳይሆን በወላጆች ፈቃድ ነበር። ይህም በተጋቢዎቹ ዘንድ ፍቅር እንዳይኖር አደረገ። በዚህም የተነሳ ቅምጥ ማስቀመጥ እየተለመደ መጣ። ለባል ያልታደሉ የባላባት ልጆችም መልክ መልካሙንና ዝሆኑን ወጣት በማጥመድ ቅምጥ ሆኑለት። ይህም በባልና ሚስት ዘንድ ሊኖር የሚገባውን ፍቅርና መተሳሰብ ቀነሰው። ሚስቱ ያልጣመችው ወንድ ቢወሸም ሊፈፈጽበት አይገባም ወደሚል አዝማሚያ አመራ። በሙያ ማህበር መደራጀት ሲጀመር ሽርሙጥቶም በየኩሳቸው በማህበር ለመደራጀት ሙከራ አደረጉ። እንዳንዶቹ ቤተግልሙትና ሲያቋቁሙ፣ የቀሩት ደግሞ የወታደሮችን ዱካ በመከተል ተዘዋዋሪ ቅሬዎች ሆኑ። በዚህን ዘመን ሽርሙጥና ህጋዊ ስራ ብቻ ሳይሆን ጥበቃ የሚደረግለትም ተግባር ሆነ። በመሆኑም ቀዝቀዝ ብሎ የነበረው የሽርሙጥና ተግባር እንደገና አገረሸ። ከሽርሙጥና የሚገኘውም ቀረጥ ለብዙ መንግስታት በጀት መደጉሚያነት ዋለ።

በፈረንሳይ አገር ሽርሙጦች በደረታቸው ልዩ ምልክት (ባጅ) እንዲለጥፉና በጭም ደማሪ ልብስ እንዳይለብሱ፣ የወርቅ ጌጣጌጥችም እንዳያደርጉ ተከለከሉ። የሽርሙጥና ተግባራቸውን የሚያከናውኑባቸው ስፍራዎችም ተከለሉ። በመንግስት የሚተዳደሩ ቤተ ግልሙትናዎች በቱሉስ፣ በእቢግናና በሞንትፔሊዩ ተመሰረቱ። በቱሉዝ ከሽርሙጥና

የሚገኘው ገቢ ለክተማይቱና ለዮኒቨርስቲው ግምጃ ቤቶች ይከፋፈላል። የፈረንሳይን ቤተ ግልሙትና የመሳሰሉ ድርጅቶች በብዙ አውሮፓ አገሮች ይገኙ ነበር። ለምሳሌ በኢጣሊያና በስፔን የነበረው ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላል። እንዲሁም በጀርመን።

አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ብዙ መሻሻሎች የታዩበት ወቅት ነበር። ባላባቶች የደከሙበትና ነገስታት ያየሉበት ዘመን። ከዚህም ሌላ የሴቶች መብት እንዲሻሻልና የወሲብም ጋጠወጥነት እንዲገታና ምግባሪ ሰናይ እንዲጎለብት ጥረት የተደረገበት ወቅት ነበር። ቤተ ክህነት ሽርሙጥናን መፍቀድ ማለት ምህረት የሌለው ሐጢአትን መፈፀም መሆኑን ሳታሰልስ አስተማረች። በዮኢካባቢው የነበሩ ቤተግልሙትናዎች ክፍተኛ ቁጥጥር ሲደረግባቸው፣ በየካቴድራሉ ገረገራ ተከማችተው የነበሩ መለኩቶችም ክስራ እንዲባረሩ ተደረጉ። እ.ኤ.አ ወደ 1536 ገደማ ግልፅ ሽርሙጥና በመጠኑም ቢሆን በቁጥጥር ስር የዋለ መሰለ። በ1650 ዓ.ም ግድም በአንዳንድ ሀገሮች ሲሸረሙጥ የተገኘ ሁሉ በአስራት ሲቀጣ፣ በዚህ ያልታረመ ደግሞ የሞት ቅጣት ይፈረድበት ነበር። ዘግየት ብሎ ግን ሽርሙጦቹ ግርግርና ረብሻ ከላስነሱ በስተቀር ተከስው መቀጣታቸው ቀረ። በመንፈሰ ጉባኤ መፈረዱም ተሰርዞ ጉዳያቸው ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሀረ።

በዘጠኛው ክፍለ ዘመን ፖሊስ በዘመናዊ መልኩ ተቋቋመ። ስለዚህም በሽርሙጥና ምክንያት የሚነሱትን ወንጀሎች እየተከታተለ ያዘ። ኢንዱስትሪ እየተስፋፋ ሲመጣ የሽርሙጥና ፕሮብለምም ዓይኑን አፍጦ ወጣ። ገጠራው ስራ ፍለጋ ወደ ከተማ መጉረፍ ስለጀመረ በደሳሳ ጉጅዎች ውስጥ ተሰፍንግ መኖር መጣ። ሰዎች ክስራ ውጭ የሚገናኙበት ብዙም ገንር አልነበረም። በዚያ ላይ ስራው አሰልቺና የመንፈስ ደስታ የማይሰኝበት ነበር። ስለዚህም

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋነኛው የጊዜ ማሳለፊያ ስፍራ መሸታ ቤት ሆነ።

የህብረተሰብ ሊቃውንት ሽርሙጥትን በሶስት ይከፍሏቸዋል። የመጀመሪያዎቹ ቅምጦች፣ ሁለተኛዎቹ ቤት ተከራይተው አልጋ ዘርግተው የሚሸረሙጡ ሲሆኑ ሶስተኞቹ ደግሞ በቤተግልሙትና ተቀምጠው የሚተዳደሩ ናቸው። ከነዚህም ውጭ አማተር ሽርሙጦች የሚባሉ አሉ። ሌላ መተዳደሪያ አያላቸው አልፎ አልፎ ገንዘብ በመቀበል ወንድ የሚተኙ። ይህም የቤት ሰራተኞችንና የህፃናት ሞግዚቶችን ያጠቃልላል። በዘመነ ኢንዱስትሪ የቁጭራ ሰፈሮች መብዛትና የመጠጥ መዘውተር የሽርሙጦችን ቁጥር አያበረከተው መጣ። የዳንስ ቤቶችና የምሽት ክበቦች መበርከት ዝሙት አዳሪነትን መረን ለቀቀው። ዳንስ ቤት ጉራ አያሉ ማመንዘርም የማያሳፍር ተግባር ሆነ። ቢሆንም ሴቶቹን በማስተማርና ህብረተሰቡን በማንቃት ሽርሙጥናን ለማዳከም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በተለይ የኃይማኖት መሪዎች በፅኑ ለፍተዋል። የሆነ ሆኖ ሽርሙጥና መተዳደሪያቸው የሆነውን ክፍሎች ማሳመን አልቻሉም። ለሴቶቹ ተለዋጭ መተዳደሪያ ስለአልተፈጠረላቸው ደረቅ ስብከት ብቻውን ምንም ሊፈይድ አልቻለም።

በ19ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመን ጠንካራ ሀግ በማውጣትና የፖሊስ ኃይል በመመደብ ሽርሙጥናን ለመግታት ተሞክሯል። ነገር ግን ብዙ ሽርሙጥናን የሚደግፉ ቡድኖች ሁኔታውን ስለተቃወሙ በአንዳንድ ሀገር ሽርሙጥናን ለመቆጣጠር የወጡ ህጐች እንዲሰረዙ ተደርጓል። የተቋቋመውም የፖሊስ ኃይል በሽርሙጦች አካባቢ ወንጀል እንዳይሰራ ከመከላከል በቀር ሌላ ተግባር አልከለከለውም። በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ «ሞራል አሰጠባቂ ፖሊስ» ተቋቁሞ ነበር። ይህም ፖሊስ የተመዘገቡና ያልተመዘገቡ ሽርሙጦችን መቆጣጠር ነበር ተግባሩ።

እየቆየ ሲሄድ ግን ጉቦ መብላት በመጀመሩ ራሱ ችግር ፈጣሪ አካል ሆነ። በሌሎች ሀገሮች ደግሞ አሸሀን በአሸሀ በሚለው ዘይቤ መሰረት ሽርሙጦችን የሚቆጣጠሩ ሴት ፖሊሶች ተመልምለው ነበር።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ ሀገሮች ቤተግልሙትናዎች እንዲዘጉ ቢደረግም ብዙ ችግር በመፈጠሩ በወታደር ካምፖች አካባቢ እንዳሉ እንዲቆዩ ተደርጓል። በአሜሪካን አገር ሽርሙጥና በብዙ ግዛቶች ውስጥ ያስቀጣል። ሽርሙጥና በህግ የተከለከለ ቢሆንም በድብቅ ግን በስፋት ይካሄዳል። በየሀገሩ ሽርሙጥና ፊፀሞ 'ይከልከል' በሚሉና 'አይከልከል' ግን በህግ ይመራ በሚሉ ወገኖች መካከል ክርክሩ እንደተጧጧፈ ነው። ሽርሙጥና በህግ በተከለከለበት ሀገር የአባላዘር በሽታዎች ከመቀነስ ፈንታ ይጨምራሉ። ዝሙት በድብቅ ስለሚካሄድ ሴቶቹን አማኝቶ የጤና ምርመራ ለማድረግ ያዳግታል። ሽርሙጥናቸው በይፋ ከታወቀ ግን በየሳምንቱ የጤና ምርመራ ማድረግ ይቻላል። ግራም ነፈስ ቀኝ የሽርሙጥና ፕሮብሌም በየሀገሩ ያለ ትልቅ ችግር ነው። ከህግ፣ ከሞራልና ከጤና አኳያ ሲታይ የተወሳሰበ መልክ አለው። ሽርሙጥናን የህግ አዋቂዎች የማህበራዊ ኑሮ ሲቃውንትና የስነልቡና እንዲሁም የስነ ዓይምሮ ጠቢብት የሚመለከቱት በተለያየ ዓይን ነው።

የስነ ልቡና ጠቢብት ሽርሙጥናን የሚመርጡ ወንዶች በአንድ መወሰኑ መሰባዊ እርካታን ስለማያስገኝላቸውና «ስለሚሰለቹ» ነው ይላሉ። ሴቶችም በአንድ ሲወሰኑ እንክብካቤ እናጣለን ብለው ያስባሉ። ወንዱ የሚፈልገን የራሱን መሰባዊ እርካታ ለማግኘት እንጂ የኛን ስሜትና ፍላጐት ለማርካት አይደለም ብለው ይሟታሉ ይላሉ። የተወሰኑ ሴቶች ደግሞ ጋብቻ የሚጠይቀውን ከባድ ኃላፊነት በመፍራት ከጋብቻ ይልቅ ሽርሙጥናን ይመርጣሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወሲባዊ ፍላጐታቸውን ከአልፎ ሂያጅ ጋር በማድረግ ስሜታቸውን ያረካሉ፣ ሀብትም ይሰበስባሉ። ሴሎቹ በትምህርት ወይም በጋብቻ ታዋቂነትን ማትረፍ ሲሳናቸውና በሽርሙጥና በኩል ይህንኑ ለማግኘት ይሞክራሉ ይላሉ ጠቢባቱ።

መደበኛ ብለን ባንጠራቸውም አመንዝራ ሴቶች በብዛት ይገኛሉ። ከወንድ ገንዘብ አይቀበሉም፣ ግን ከአንድ ወንድ መርጋት አይፈልጉም። ወንድ የመቀያየር ባህሪ የተጠናወታቸው በብዛት ይገኛሉ። ሀብት ሞልቶ የተረፋቸውና ወንዶችን አያባበሉና ጉርሻ እየሰጡ የሚወሽሙም አሉ። ግልሙትናን እንደሙያ ይይዙታል። ስለ ሽርሙጥና ሲነሳ አንድ የሚያስገርም ነገር አለ። እጅግ የተዋቡና የዕለት ራት የሰላቸው፣ ያጡ የነጡ ሴቶች ሆነው በሽርሙጥና ተግባር የማይሰማሩ አሉ። ይህ ሁኔታ ሲታይ የሽርሙጥና መነሾ የኢኮኖሚ ችግር ብቻ ነው ብሎ ስመደምደም በጣም ያዳግታል። የሽርሙጥና መነሾ ግን በአመዛኙ ኢኮኖሚያዊ ነው ማለት ያስደፍራል።

ሽርሙጥናን አድሜ ይወስነዋል። አብዛኞዎቹ በ18 ዓመት ቢጀምሩም የሚያዋጣቸው ግን እስከ 30 ዓመት ገደማ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ተፈላጊነታቸው እየቀነሰ ስለሚመጣ አንዳንዶቹ ያገባሉ፣ ሴሎቹ ቤተሰሙትና ይከፍታሉ። የተቀሩት ደግሞ ለለ አይነት ድርጅት ከፍተው «የተከበሩ» ሴተላጪዎች ይሆናሉ። አድባር ፊቷን ያዙረችባቸው ጭርስኑ አቃጣሪ ሆነው ያርፉታል።

ሽርሙጥናን የሚያበረታቱ ወንዶች አምስት ዓይነት ናቸው። ወጣት ወንዶችና ተማሪዎች፣ ከሚስቶቻቸው ለተወሰነ ጊዜ በስራ ምክንያት የሚለያዩ፣ መቃደሮች፣ ተንቀሳቃሽ ነጋዴዎች፣ ሽፈሮች፣ ያገቡና ሚስቶቻቸው በአልጋ ያልተስማሟቸው ወይም በሽተኛ የሆኑባቸው እንዲሁም አለልጥ የሆኑ መልክ ቀና ወንዶች።

ሽርሙጥና ሌላም ስነልቦናዊ ምክንያት አለው። ወንዶች ሞራላቸው ሲላሸቅ ወንጀለኞች እንደሚሆኑት ሁሉ ሴቶችም ሞራላቸው ሲወድቅ በሽርሙጥና ተግባር ላይ ይሰማራሉ። ወንጀል ከመሰራት ይልቅ ሽርሙጥናን እንደተሻለ አማራጭ አድርገው የሚወስዱ አያሌ ሴቶች ናቸው። ባጭሩ ሽርሙጥና እጅግ አስቸጋሪና የተወሳሰበ ማህበራዊ ችግር ነው። እኛስ አገር ይህ ተግባር እንዴት ተጀመረ? መፍትሄውስ?

በአፄ ልብነ ድንግል (1508-1540) ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያን የጎበኘ ፖርቱጋላዊ ካህን እንደዘገበው ከሆነ የሽርሙጦች መጠሪያ አማሪት ነበር። ትርጉሙም ሴት አረሆ ወይም ደናሽ ማለት ነው። ሴቶቹ ሀብታሞችና በአዳ ልብስን የሚያዘወትሩ ሲሆኑ ቁጥራቸውም በርካታ ነበር። በንጉሱ ድንኳን አካባቢ አየደከኑም ነበር የገመቱት ተግባራቸውን የሚያሟጡፉት።

የጐንደር ከተማ በ1636 ከተመሰረተች ወዲህ ሽርሙጥና መስፋፋት ጀመረ። የአፄ ኢያሱ (1682-1706) መዋዕሰ ዜና ዘጋቢ በ1696 አላት አንዲት ጋለሞታ ቤት ተነስቶ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ፅፏል። (ኮማሪት የሚለው ቃል በጋለሞታ መተካቱን እዚህ ላይ ያጤኗል።) በ1830ዎቹ ትልቁ የመደሰቻ ስፍራ ቤተቨርሙጣ አንደነበረም የወቅቱ የውጭ አገር ጉብኝዎች ገልፀዋል። እነሀ ቅሬዎች በጣም የተከበሩ እንጂ የተናቁ አልነበሩም። በዚህም የተነሳ ቁጥራቸው በጣም ሊጨምር ቻለ።

በአፄ ቴዎድሮስ (1855-1868) ዘመነ መንግስት ግን ነጋዴዎችና ደብተሮች ትሬዎችን ማስቀመጥ ስለጀመሩ በየጊዜው እየተራበሹ ከተማይቱን ያበጣት ገቡ። ቀስ በቀስ ሽርሙጥናም በደብረታቦርና በአድዋ በተለይም የወታደር ከምችትና የንግድ እንቅስቃሴዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች እየተስፋፋ መጣ። ይሁንና በሽርሙጥናና

t.me/OLDBOOKSPDF

በማስተመጥ (ቅምጥ በማድረግ) መከከል ያለው ልዩነት እምብዛም ባለመታወቁ አምሮትን ለመወጣት ገራ ሲሉ በዱላ መፈለጥ፣ በስለት መወጋት ነበር።

በገ-ዙና በዘመቻ ጊዜ መኪንኑና መሳፍንቱ ሚስቶቻቸውን ወይም የጭን ገረዶቻቸውን አያስከተሉ ሲሄዱ ተራው ሀዘብ ግን ሲጣሙን ስለሚሆን የተፈጥሮ ፍላጐቱን ለማርካት ወደ ሽርሙጥጥ ገራ ማለቱ አልቀረም። የወትሩ ሽርሙጠኛ ሞቅ ያለ ገንዘብ ያገኙ ስለነበርም ትዳር የመያዝ ፍላጐት አልነበራቸውም። በደምግባታቸው የነሆለለ «ተልት» ሰው እንኳ ለጋብቻ ቢጠይቃቸው ፈቃደኛ አይሆኑም። ሽርሙጥና መልካም የገቢ ምንጭ መሆኑ አየታወቀ በመምጣቱም ተግባሩ በሽሞ በተለይም በፍቼ ተስፋፋ። ይህ የሆነው ከተማዪቱ የንግድ እንቅስቃሴና የወታደር ከምችት የበዛበት ስለነበረች ነው።

የዘመኑ ሽርሙጠኞ ሲበዛ ውብ ነበሩ። ልብሳቸው ድንቅ፣ በሳምም የተከበሩ - በንብሱ ንብር ላይ ሳይቀር የሚገኙ። የአገልግሎት ዋጋቸውም ጠነን ያለ ሲሆን ሚሚለዱም በቀላሉ የሚሳክላቸው ነበሩ። የከፎለ ሁሉም አያገኛቸውም፣ ሲበዛ ኩሩ ናቸው።

በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሽርሙጥና በጨቅላው ነበር ማለት ዚቅለም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ግን እንደ ስደድ እሳት ተስፋፋ። በሐረር፣ በአጋዴንና በአፋር ምድር ተከሰተ። የሞንቱ መጠሪያዎች ረጋለሞታ፣ ደንከጠር፣ ጠሳበቢያና ዘማ ቀርተው ከአረቡኛ የተወረሰው «ሽርሙጣ» የሚለው ቃልም መደበኛ መጠሪያቸው ሆነ።

በተለይ በ1907 ገደማ በአዲስ አበባ ባንዲት አነስተኛ ሳር ከዳን ቤት ውስጥ አበኔ አምስት የሚደርሱ ጋለሞቶች አየተስባሰቡ ሽርሙጥናውን ያካሂዱባት ጀመር። ደንበኛ ለመሳብም አደገኛ ቀመጣ ያንተራተራሉ። ስለዚህም በወቅቱ ጥሩ ሽርሙጣ ለመባል ድምፅ አስተዋፅኦ ነበረው።

በርዕሰ ከተማችን ለሽርሙጥና መስፋፋት የጠጅ ቤቶች እንደ አንዳይ መፍለት ትልቅ ድርሻ አለው። በ1908 ከ50 የሚያንሱ ጠጅ ቤቶች ከምስት ዓመታት በኋላ 100 ደረሱ። በ1929 ደግሞ በመቶ አጥፍ ጨምረው 1000 ሆኑ። በየጠጅ ቤቱም በርከት ያሉ አልጋዎች መዘርጋት ጀመሩ። በድራዳዋም እንዲሁ የጠጁ ንግድና ሽርሙጥናው ደራ። የሽርሙጥጥ የዱሮ «ክብራቸው» ግን ቀነሰ። «ሽርሚ» የሚለው ቃል ስድብ ሆነ።

* * *

ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ያሰለፈቻቸው ወታደሮች ጉረምሶች ስለነበሩ ቀሚስ ያጠለቀች ሴት አታልፋቸውም ነበር። በዚህም የተነሳ የሽርሙጥጥ ተፈላጊነት ጨመረ። ኢጣሊያ ሶማን ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረች በኋላ በአድዋና በአክሱም ብዙ ሴቶችን አስገድዳም አግባብታም ወደ ወታደር ካምፖች አቅራቢያ አመጣች። የአባለዘር በሽታ እንዳይሰፋፋ የህክምና ቁጥጥር አየተደረገላቸውም በአንድ አካባቢ ተቀምጠው የወታደሮች መደሰቻ እንዲሆኑ ተደረገ። እንዳይጠፉም ጥብቅ ቁጥጥር ይካሄድባቸው ነበር። መቀሌ በጠሳት እጅ ከወደቀች በኋላ በከተማዪቱ ውስጥ ሽርሙጥና እንዲስፋፋ የፋሽስት ባለስልጣናት ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠታቸው የአመንዝራነት ተግባር እጅጉን ተስፋፋ። ለሽርሙጠት የሚሆኑ ከ200 በላይ ሳር ቤቶችም በከተማዪቱ ውስጥ ተሰሩ። ፋሽስት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አየገሩ ሲመጣም በደሴ በርከት ያሉ ቤተ-ግልሙትናዎች ተከፈቱ። መልክ ቁና ከረጅችም በዘሙት ተግባር ላይ ተሰማሩ።

መናገሻ ከተማዪቱ አዲስ አበባ በጠሳት እጅ ከወደቀች በኋላ ሽርሙጥና መስፋፋቱ ግልጽ ነበር። በርካታ ወጣት ሴቶቻችን የጣሊያን መታደሮች መደሰቻ ሆኑ። ከጥቂት ጊዜ ቢኋላም 1500 የሚሆኑ የራሳቸው ቤት ያላቸው ሴተኛ አዳሪዎች በጠሙ ሽ የሚቆጠሩ ተዘዋዋሪ (ሆንትሮ - ሞሮዎች) እና 47

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈረንጅ ሽርሙጥና ከተማዋን አጥለቅልቋት።

ሦስም ከወሰኑ ወረራ በኋላም በሀገሩ ሽርሙጥና መስፋፋቱ አልተረፈም። በሞያ፣ ናዝሬት፣ ሐረር፣ ድሬዳዋ፣ ሰቀጦትና ጅማ ተስፋፋ። አጣሊያ በዘዙ ሙቱ ሽ. የሚቆጠሩ ወታደሮችንና ሰራተኞችን እገዘዘዘሳ መሞላቷ በመላው ሀገሩ ሽርሙጥና እንዲስፋፋ ታላቅ አሉታዊ አስተዋፅኦ አድርጓል። ዘመኑንም ሆነ በሩቦች ላያም የሞራል ልሽቀት አሳይትሳል።

* * *

ከሩሽቦት ወረራ በኋላ ሽርሙጥና በመላው አትዮጵያ ተንሰራፍቷል። ኮረዶች ዘሙ ብሰው የሚገዙበት ሕንፃ ሰርቷል። በየሙቱ ከገዘር ወደ ከተማ ከድስ በመቶ ሰው ያፈልሳል። ከዘህም ወሰን አብዛኞቹ ሴቶች ናቸው። በአሰግሃቱ መኩሪያ፣ በላቶች ድራስና የህዘባዊ ኑሮ አድገት ጥናትና መሰረት የሴቶቹ ዋልሰት ሞኝ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የገዘር ሴቶች ወታደሮችንና የከብሮ መኪና ሾፌሮችን እገዘቱተው ከተማ መምጣትና መፈታት፣ ከዚያም ከተማ ተረጉ መሸርሞጥ፤

2. ከባለቮቸው ኖተፋቱና ባሉቮቸው የሞቱቸቸው ሴቶች ትዳር ለመመስረት አሊያም በራ ዋስጋ ወደ ከተማ መፍለስ፤

3. የወጣት ሴቶች ገጠሬ ባሉቮቸውን ፈትተው ከተማ መመሸግ፤

4. ኖጠሩ ኑሮ ኋላቀር በመሆኑ ያንን ሁኔታ በመሸሽ ከተማ መግባት፤

5. የገጠሬ አፈር ለምነት መቀነስና የከፋ ደህነት መከሰቱ፤

6. የከተሞች መስፋፋት።

የህዘባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር በ1974 ሳይ. 22 ከፍተኛ ከተሞችን አሳውቆ 3715 መደበኛ ሽርሙጥቮችን መዘገቧል። (በዚህ ወሬሔ ግምት ያሀ ቁጥር ዙሞም አሽከተኛ ነው) የተጠኑት

ከተሞች ህዙብ ብዛት 2,000,000 ገደማ ሲሆን የሽርሙጥቮ ቁጥርም ሁለት በመቶ ነበር። በዚህ ስሌት ከሃድን በአሁኑ ጊዜ በከተሞች ውስጥ ከ100,000 በላይ መደበኛ ሽርሙጥቮች ያገኛሉ ማለት ነው።

* * *

ሽርሙጥና በግላጭና በሽፋን ይካሄዳል። በጠላ፣ ጠጅ፣ ኑቲላ፣ በግሮሰሪ፣ ቡና ቤትና ሆቴል ቡተሰኙ የደስመላ ንግድ ሽፋኖች ሽርሙጥና ሲካሄድ ባንዛሩ ደግሞ በግላጭ ዝብዘኝ (ሲነራቮ) በመክፈት ቤት አዕድቱ አልጋ ዘርግቶ ወንድ በመጠበቅ፣ መንደር ላይ (ድራፌ) በመዞር ይካሄዳል። ሴሰኞች ደግሞ በአቃጣሪ የሚጠቀሙና በዘቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የበደሮ ሰራተኞች እንዲሁም ወጣት ሴት ተማሪዎች አይታጡም።

በየቡና ቤቱ የሚሸረሙጡት ራሳቸውን አሻሻጭ እንጂ ሽርሙጣ ብለው አይጠሩም። በየማታ ክበቡ የሚገኙትም ራሳቸውን «ዳንሲሬ» ብለው ሲሰይሙ፣ የራሳቸው መጠኛ ቡና ቤት ያላቸው እሚቱያች (ማዳያሶስ) ደግሞ ነጋዴዎች ነን ባሮች ናቸው። ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ። ሽርሙጥና በሞንም መልክ ተካሂደ በሞንም ሽፋን ማህበራዊ ጠንቅ ከመሆን አያልፍም።

በሽርሙጥና የተሰማሩ የወንጀል ድርጊቶች ደብዘቱታሉ፣ ጋብቻ ይፈርሳል። የአባላዘር በሽታዎች ይስፋፋሉ። በተለይ መድኃኒት ያልተገኘለት አድስ አንዲስፋፋ ሽርሙጥና አሉታዊ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ሽርሙጥና ሴሰኛትንና የአልኮል ሱሰኝነትንም ያበረታታል።

* * *

ብዙዎቹ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሽርሙጥና ተግባር ላይ ከተሰማሩት ውስጥ 75 በሙቶው ከገጠር ባሉቮቸውን ፈተው ከተማ የገቡ ናቸው። ትዳራቸውም የፈረሰው በወላጆቮቸው አስገዳጅነት የማያውቱቸውን ወንዶች

t.me/OLDBOOKSPDF


በሚገባቻቸው የተነሳ ነው። ስለዚህም ሴቶች በህገኑት አንዳይዳሩ መንግስትና ህብረተሰቡ አገዳ ማድረግ አለባቸው። ሴቶች ባሉቻቸውን የመምረጥ መብታቸውም ሊረጋገጥ ይገባል።

በሽርሙጥና ላይ ከተሰማሩት 95 በመቶው መጎይምና ከስድስተኛ ክፍል በታች ስለሆኑም ሴቶች ልጆች በትምህርት እንዲገፉና መተዳደሪያ የሚያስገኛላቸውን ሙያ እንዲያጠኑ ማበረታታት የግድ ይሆናል።

በአሁኑ ጊዜ በሽርሙጥና ላይ ከሚገኙት የ82 በመቶው አድሜ ከ15 እስከ 39 ስለሆነም መጠነኛ ስልጠና ተሰጥቷቸው በተለያዩ የስራ መስክች ላይ ሊሰማሩ ይገባል። ሆኖም ይህ ጉዳይ ሰመንግስት ብቻ መተው የለበትም። የኃይማኖት፣ የፖለቲካና የምግባሪ ሰናይ ድርጅቶች መተባበር አለባቸው። ትን ልቡናውና አትም ያላቸው የውጭ መንግስታትም እርዳታ ሊለግሱ ይችላሉና። በተደረገው ጥናት መሰረት ከሽርሙጦቹ 75 በመቶው በሌላ ስራ ላይ መሰማራትን ይፈልጋሉ። ይህ መልካም ዝንባሌ ነው። ትዳር ለሚፈልጉትም በመቶ ዘጠናው ለማግባት ፈቃደኛ መሆናቸውን እናበስራለን። በስራ ላይ መሰማራት የማይፈልጉ ግን በጣም ጥቂትና ጉበረት ያላቸው አሚሉም ናቸው።

የነጠር ኑሮ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑም ኑሮ የሚቀልበት መንገድ መፈለግ አለበት። የስነ-ማና የገጠር ሀይወት እንዲቀራረብ መጣር ያስፈልጋል። የአፈሩ ለምነት ሊሻሻልበት መንገድ ተቀይሶ ምርት የሚዳብርበት ሁኔታ ሊፈለግ ይገባል። ከላይ የተዘረዘሩት መፍትሄዎች ከተተገበሩ ሽርሙጥናን ፈጽመን ማጥፋት ባንችልም አንኳ በእጅጉ መቀነስ እንችላለን።

መጣጥፍ



የመጦር ዕቅድ

ጄክ ለንደን
(ትርጉም) ቪ.ራው. ክበደ

በብርድልብስ ተጠርፎ ከትከሻቸው ጋር የተቆራኘ አዝትና ጠመንጃ ያነቡት ሁለት ሰዎች ተዳፋቱን ወርደው ከጅረቱ ድንጋያማ ዳርቻ ወደቱ። የህመምና የጉስቁልና አሻራ የታተመበት ፊታቸውን ከሸክሳው፣ ዓይናቸውን ከአለታማው ምድር ላይ ተክለው መራመድ ሲጀምሩ «ከነዚያ ጥይቶች ሁለቱ እንኳ በአጃችን ቢኖሩ ምን ነበር?» ብሎ ተናገረ ሁለተኛው ሰው። አንደበቱ ቁጭቱን የሚገልጽ ቅላጼ ቢጎድለውም መናገር የፈለገው ከሚስጥራዊ ማሰቀመጫ ውስጥ ስለተዋቸው ጥይቶች ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ጅረቱ በማዘገም ላይ የነበረው ሰው ግን መልስ አልሰጠም። የኋለኛው ሰው የፊተኛውን እግር ተከትሎ ከጅረቱ ውስጥ ገባ። ውሃው እንደበረዶ የቀዘቀዘ ቢሆንም ሁለቱም ጫማዎቻቸውን እላወለቁም። በቅዝቃዜ የበደኑ እግሮቻቸውን እያፈራረቁ የውሃውን ግፊት ተቋቁመው በመውተርተር ላይ ሳሉ ነበር የኋለኛው ሰው የረገጠው ድንጋይ አዳልጦት ለጥቂት ከመውደቅ የተረፈው። የተዛባ ሚዛኑን ለመቃኘት በመወራጨት ላይ ሳለ ክፉኛ ኢቃስቶ ነበር። ራሱን የሳተ በመሰለበት በዚያን ቅጽበት በእንደኛው እጁ አየሩን መደገፍ ቃጥቶት ነበር።

ቀጥሎ አቋሙን አደላድሎ መራመድ ጀመረ። ነገር ግን አሁንም ተንሸራቶ ከመውደቅ ለጥቂት ተረፈ። ከዚህ በኋላ ግን እንቅስቃሴውን አቋርጦ ሌለውን ሰው መመልከት ያዘ። ወደ ጉዞ አቅጣጫው እንዲ ወደ ኋላው ተገላምጦ አላየም ያኖው። አንዳች ነገር በመወሰን ላይ እንዳለ ሁሉ ለአንድ ሙሉ ደቂቃ እዚያው ቆሞ ቆየና «እግሬን ተሳድቻለሁ ቢል!» ብሎ ጮኸ።

አንት በመስለው ውሃ ውስጥ የሚጸከረው ሰው ፊቱን መልሶ ሳይመለከተው ቀረ። የኋለኛው ሰው የቆሰለ እንስላ ባስመስሉት ዓይኖቹ በመራት ላይ የነበረውን ባልደረባውን ተመለከተው።

የፊተኛው ሰው ጅረቱን ተሻግሮ፣ የዳርቻውን ተዳፋት አንባደ፣ አዲስ የጉዞ ምዕራፍ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ወደ ኋላው አልተገላመጠም። የኋለኛው ሰው ጀርባውን ለጥቶት በመንገዝ ላይ የነበረውን ባልደረባውን በመመልከት ላይ ሳለ ከንፈሮቹ በጥቂቱ ተንቀጠቀጡ።

«ቢል!»

የአንድ ብርቱ ሰው የሲቃ ጥሪ ቢሆንም ዞሮ ለማየት አልፈቀደም ቢል። ጋራውን ተከትሎ አድማስን ወደሚያካልለው መስመር በማቸቀብ ላይ ሳለም

ተመለከተው። አቀበቱን ጨርሶ፣ ቁልቁል ወርዶ ከአይታው እስኪሰወር በአይኖቹ ከሸኘው በኋላ ግን አይታውን ዙሪያውን ወደከበበችው ትንሽ ዓለም መልሶ አካባቢውን መመርመር ያዘ። ብቻውን ቀርቷል! ቢል ርቆ ሄዷል!

ወደ ምዕራብ በማዘቅዘት ላይ የነበረችው ፀሐይ ከሞላ ጎደል በደመና ግርዶሽ ተሸፍና ነበር። ክብደቱን ወደ አንደኛው አግሩ እያዛወረ ሰዓቱን ተመለከተ። ከቀኑ አስር ሰዓት ሆኖአል። የሰኔ ወር መጨረሻ ወይም የሐምሌ መጀመሪያ ነበር ጊዜው። ግምቱ ከትክክለኛው ቀን በአንድ ወይም በሁለት ሳምንት ቢዛነፍም ከፀሐይቱ አቀማመጥ የሰሜን ምስራቅን አቅጣጫ ለማገናዘብ ያህል በቂ ነበር።

ወደ ደቡብ ተመልክቶ ታላቁ የድቦች ሃይቅ ከአረብታውቹ ማዶ እንደሚሆን ከሀሊናው ጋር ተማመነ። ከነዚያው አረብታዎች በስተጀርባ የአርክቲክ ንፍቀ-ክበብ የሰሜን ካናዳን ጠፍ ሁዳዶች አቋርጦ እንደሚያልፍ ያውቅ ነበር። ይሄኛው (የቆመበቱ) ጅረት ወደ ኮፐር ማዮን ወንዝ ይፈስና በተቀላቀል ወደ ሰሜን አቅንቶ ከአርክቲክ ውቅያኖስ ይደባለቃል። ከዕለታት አንድ ቀን ካርታ ላይ ከተመለከተው ውጪ ግን ያንን ሥፍራ በአካል አያውቀውም ነበር።

በዙሪያው የነበረችውን ዓለም ታኝቶ ጨረሳት። አይታው ማራኪ አልነበረም። ማየት አስከቻለው የመጨረሻ ርቀት ስብርቱ ፍርሃት ኑዳረገው የትዬለሌ ባዶነት በስተቀር ዓይኖቹ ከምንም ነገር ላይ አላረፉም። ዙሪያ ገባው የዛፍም ሆነ የሳር ምልክት አልነበረውም።

«ቢል!» ለራሱ ብቻ በተሰማው ሹክሹክታ ተጣራ።

ግዑዙ ዓለም ሊሚያንቀጠቅጥ ፍርሃት ዳረገው። የጠመንጃው ከእጁ ማምለጥ ወደ ገሃዱ ዓለም ባይመልሰውማ ከናካቴው ልቡን ሊነሳው ዳድቶት ነበር። ፍርሃቱን ታግሎ መርታትና ራሱን መቆጣጠር ሲችል ግን ጠመንጃውን ከውሃ ውስጥ ፈልጎ አገኘው። ሸከሙን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ግራ ትከሻው ገፍቶ የክብደቱን የተመሰነ ክፋይ ከተሸከመው እግሩ ካራቀ በኋላ በዝግታና በጥንቃቄ መራመድ ጀመረ።

ጅራቱን ተሸክሮ፣ የጸርቻውን ተዳፋት ወጥቶ ከጨረሰ በኋላም አልቆመም። በሀመም አየተደቆሰ ወደ ኮረብታው አናት የሚያዘልቀውን አቀበት ይዞ ሽቅብ ሲኒትን ቀየ። ባልደረባው ከተሰወረበት የአቀበቱ ማብቂያ ደርሶ ቁልቁል ሰመመልከት ጓጉቶ ነበር። እዚያ ደርሶ የተመለከተው ግን የጠበቀውን አልነበረም። አራን ከፍቶ ከተዘረጋ ግኡዝ ሽሰቶ በሰተቀር ምናምኒት የህይወት ምልክት ሳያይ ቀረ። እንደደራሽ ውሃ ሥጥለቀለቀውን ድንዝር የሰሽ ፍርሃት በድጋሚ ታማሎ ሳቸነፈ በኋላ ሽከሙን ወደ ግራ ትከሻው ገፍቶ ቁልቁል መውረድ ጀመረ።

የሽሰቱው የሥረኛ ምድር አርጥብ ነበር። ጥቅጥቅ ብለው የበቀሉት ጥቃቅን እጽዋት አርጥበቱን ጠብቆ እንዲቆይ ሪድተውታል። በየርምጃው ጣልታ ከአግሩ ሥር የሚንዠረገርሩትን ትናንሽ ወራጅ ውሃዎች አያሰፈ ጉዞውን ተጠሰ። በርጥቡ የእጽዋት ዓሰም ውስጥ ትናንሽ ደሴት በሰሩት አሰዩች ላይ የታተሙትን የሰለ ሰው የእግር አሻራዎች ተከትሰ ሽሰቡን ማቋረጥ ያዘ።

ብቻውን ቢሆንም ሰመጥሩት አደጋ አልተጋስጠም። የደረቁ የዕድ ዛፎች ከሚያዋስኗት ክትንሿ ሃይት ጸርቻ መድረስ አይሳነውም። ያ አካባቢ በገጠሩ ዳንቋ ‹የትናንሽ እንጨቶች ምድር› ተብሰ ይጠራል። አንድ አንስቶኛ ጅረት ወደ ሃይቁ ይረሳል። ግራና ቀኙ በሰር የሚታጀበውን ይዜንን ጅረት ቅርንጫፍ እስከሚያዘርቡበት ይከተሰውና ወደ ምዕራብ የሚያቀናውን መንትያ ተከትሰ ይጓዛል። ጅረቱ ከዲዝ ወንዝ ጋር ከሚደባለቅበት አቅራቢያ ባፍጢሙ የተደፋውን ጀልባና ከጀልባው ስር በበርካታ አለቶች የተደፈነውን ማከማቻ ያገኘዋል። ጥይት፣ የእሳ

ማስገሪያ መንጠቆ፣ ዱቄትና ጥቂት ሥጋ እንዲሁም ምግብ ለማግኘት የሚረዱትን አስፈላጊ ቁሳቁሶች ከማከማቻው ውስጥ ያገኛል።

ቢል እዚያ ደርሶ እሱ በመጠባበቅ ላይ ሊሆን ይችላል። ከዚያ በኋላ የደቡብን አቅጣጫ ተከትለው በዲዝ ወንዝ ላይ ወደ ታላቁ የድቦች ሃይቅ የሚቀዝፉበትን ጀልባ ያገኛሉ። አሁንም ደቡብን ሳይሰቁ ወደ ማኬንዝ ወንዝ ያቀናሉ። ወደ ደቡብ! ሁል ጊዜ ወደ ደቡብ! ቅዝቃዜው በደረታም፣ ጅረቶች በረዶ ቢሰራም፣ ክረምቱን አየቀደመ ይጓዛሉ። ወደ ደቡብ። የተሻለ መቀት ወዳለበት፣ የዛፎች ቁመትና ግዝፈት ወደሚጨምርበት፣ ም ግብ ወደማይታጣበት አማን ምድር።

ከመንገዱ ጋር ትግል የገጠመው ሰው የሚያውጠነጥናቸው ሃሳቦች እነዚህ ነበሩ። ከሀሲና ጋር የሚያደርገው ግብግብ ከሰውነቱ ጋር ከሚያደርገው የሚተናነስ አልነበረም። ቢል እንዳልከዳው ብቻ ሳይሆን ቆሞ እንደሚጠብቀውም ራሱን ማሳመን ነበረበት። አሰዚያ ለጉዞው ምክንያታዊ መሆን አይችልም። ተስፋ በሳደሰው ሀሊና ተጋድሞ ሞቱን ከመጠበቅ ውጪ እማራጭ አይኖረውም። እናም ማድረግ የሚገባውን ነበር በማድረግ ላይ ያሰው።

ዩሐይ ወደ ሰሜን ምዕራብ በማዘቅዘቅ ላይ ሳለች እሱና ቢል ከከረምቱ ጋር አየተሽቀዳደሙ ወደ ደቡብ ያደረጉትን ጉዞ አንድ በአንድ አስታወሰው። ከሚስጥራዊ ማከማቻቸው ውስጥ የደቡቱትን ምግብም ደግሞ ደጋግሞ አሰበው። በቂ ምግብ ካገኘ በርካታ ቀናት ማሰፋቸው ብቻ ሳይሆን ከናካቱው እህል ከቀመሰም ድፍን ሁለት ቀናት ተቆጥሮ ነበር። አልፎ አልፎ ከምድር አየሰቃቀመ ወደ አፉ ከሚሰካቸው መስኪጅ ፍሬምች ውጪ ሲበሳ የሚችል አንድም ነገር አልነበረም። መስኪጅ ፍሬ ማሰት በጠቅታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውሃ ውስጥ ያለች ትንሽ ፍሬ እንጂ ምንም ማለት አይደለም። ከተሞክሮው በላይ የሆነ ተስፋ ዕናቱን ሰጥቶት እንጂ ከዚያች ወዲያውኑ ከምትሚሸሽ ጠብታም ሆነ አፉ ውስጥ ከምትቀረው ጭማቂ ፍሬ አውነተኛ የምግብ ንጥረ ነገር እንደማያገኝ ጠፍቶት አልነበረም።

ያፈነገጠ ድንጋይ የአገር አውራ ጣቱን ያነጎደው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ነበር። እንቅፋቱ በድኩም ለላሸቀ ሰውነቱ ቀላል ፈተና አልነበረም። ሰተወሰኑ ጊዜያት በወደቀበት ተጋድሞ ከቆየ በኋላ ሽክሙን አራግፎ ተቀመጠ። ቀጥሎ ደንገዘገዘ ባለው የምሽት ብርሃን ታግዞ የደረቁ እጽዋትን ለቃቅሞ አሳት ካያያዘና የተጠረፈ ዝቡን ከፈታ በኋላ የክብሪት እንጨቶችን መቁጠር ያዘ፣ ስድሳ ሰባት የክብሪት እንጨቶች። አርግጠኛ ለመሆን ሦስት ጊዜ ቆጠራቸው። ቀጥሎ ከሦስት ቦታ ከፋፍሎ በወረቀት ከጠቀለላቸው በኋላ ከተለያዩ ቦታዎች አስቀመጣቸው። አንደኛውን ክፋይ ከባዶ የሲጋራ ፓኬት ውስጥ ሌላውን ከባርኔጣው፣ ሦስተኛውን ደግሞ ከሸሚዙ። ነገር ግን በትክክል መቁጠሩ አጠራጥሮት አያንዳንዱን ጥቅል ፈትቶ በድጋሚ መቁጠሩ አልቀረም። አሁንም ስድሳ ሰባት የክብሪት እንጨቶች!

የጉተቡና የተቀደዱ አርጥብ ጫማና ካልሲዎቹን በአሳቱ ሙቀት አደረቃቸው። አግሮቹ በመድማት ላይ ነበሩ። ከተረከዝ እስከ ቅልጥሙ ባለው አካባቢ ብርቱ ህመም ይሰማው ነበር። እንደ አንዳች ነገር ያበጠ ቁርጭምጭሚቱን ከብርድ ልብሱ በቀደደው ሪድም አራፊ ጠቅልሎ ካሰረ በኋላ ጫማና ካልሲውን ለማገዝ ከብርድልብሱ ተጨማሪ ቅልታይ ቀድዶ በአግሮቹ ዙሪያ ጠመጠመው። በብረት ጀበና ያፈሰውን ሙቅ ውሃ ከጠጣ የእጅ ሰዓቱን ካሰረ በኋላ ግን በብርድልብሶቹ ተጠቅለሎ ተኛ።

እንደ ሞተ ሰው ነበር የተኛው። ከአንቅልፉ ሲነቃ ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሆኖ ነበር። የሌሊቱ ጨለማ ቦታውን ለንጋት ፀሐይ ቢለቅም በሰሜን - ምስራቅ በኩል የወጣችው ፀሐይ በግራጫ የደመና ግርዶሽ በመዋጧ የነጋው በሩቡ ሰማይ ላይ ብቻ ነበር የሚመስለው። በደርባው ተንጋለ በወጭታ ሰማይ ሰማዩን በመመልከት ላይ ሳለ በቅድሚያ ያጠኳው ጉዳይ ክፋኛ መራቡን ነበር። ከንዶቹን ተመርኩዞ ሰውነቱን ለማቅናት በመታገል ላይ ሳለ በድንገት ያምባረቀ ድምጽ ቀልቡን ገፈፈው። በዚያው አፍታ በአስራ አምስት ሜትር ርቀት ቆሞ ወደሱ ያተኮረውን አጋዘን ሰየው። ዓይነ - ህሊናው ከአሳት ላይ ተጥዶ የሚንጨረጨር ትኩስ የአጋዘን ሥጋ ምስል ያሳየው ከዚህ በኋላ ነበር። ባዶውን ጠመንጃ በደመነፍስ አፈፍ አድርጎ ወደ አጋዘኑ አነጣጠረ። አጋዘኑ ፈረጠጠ። አለታማውን ምድር አያቆራረጠ የሚጋልበውን ፍጡር በዓይኖቹ ከመሸኘት ውጪ ምንም ማድረግ ያልቻለው ሰው አዘነ።

ቆሽቱ ያረረው ሰው ባዶውን ጠመንጃ ወደ መሬት ወረወረው። ቀጥሎ የደቀቀ ሰውነቱን ተሸክሞ ለመቆም ባደረገው ጥረት ክፋኛ አቃሰተ። የሞት ሞቱን በአግሮቹ ከቆመ በኋላ እንደማንኛውም ሰው ቀጥ ብሎ መቆመም ራሱን የቻለ ፈተና ነበር።

ከአንዲት አነስተኛ ጉብታ ላይ ቆሞ አካባቢውን ለመቃኘት ሞከረ። በዙሪያ ገቡ የጣውም ሆነ የቁጥቋጦ ዝርያ አልነበረም። ከሳር መሰል ግራጫ አጽዋት፣ ከግራጫ አለቶችና ከግራጫ ጅረቶች ውጪ ምንም ነገር አይታይም። ሰማዩ ሳይለዋር ግራጫ ነበር። ዐሐይ ብቻ ሳትሆን የዐሐይ ተስፋም አልነበረም። እናም ሰሜን ወደየት እንደሆነ ለማወቅ መቸገሩ የግድ ሆነ። ከናካቴው እንዴት ወደዚህ ገደም እንደመጣም ዘንግቶት ነበር። ነገር ግን አሁንም

t.me/OLDBOOKSPDF

አልጠፋም፡ «ከትናንሽ እንጨቶች ምድር» የሚደርስበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ከበስተግራው ሩቅ ከማይባል ሥፍራ ላይ እንደሚገኝ ጠርጥሯል። እንዲያውም ከሚቀጥለው ጋራ በስተጀርባ።

ዓዙን ሰማሰናዳት ወደነበረበት ተመለሰ። ሦስት ቦታ ከፋፍሎ ያስቀመጣቸውን ከብራቆች በየቦታቸው መኖራቸውን ከማረጋገጥ አልፎ በድጋሚ ከመቁጠር ራሱን ማገድ አልቻለም። ቀጥሎ ከአጋዘን ቆዳ ስሰተሰፋው ኮሮጆ ማውጠንጠን ጀመረ። ኮሮጆው ከሰባት ኪ.ግ. በላይ ከመመዘኑ በስተቀር ያን ያህል ትልቅ ሊባል የሚችል አልነበረም። ወደ አንድ በኩል ዘወር አድርጎ ካስቀመጠው በኋላ ዓዝ ማሰናዳቱን ቀጠለ። ነገር ግን ከቀሪው እክት የማይተናነስ ከብደት የነበረውን ያንኑ ኮሮጆ ለመቃኘት ሥራውን ማቋረጡ አልቀረም። ጨካኙና ጨንጋፊው ምድር እንዳይወስድበት የሰጋ ይመስል ተገለማምጦ ዙሪያውን ቃኘና ቀልጥፎ አነሳው። መጨረሻ ላይ ከቀሪው ዓዝ አቆራኝቶት በጀርባው አዘለው።

በየጣልቃው መስኪጅ ፍሬያቸው ለመመገብ ከመቆሙ በስተቀር ግራውን ይዞ መጓዝ ጀመረ። ቁርጭምጭሚቱ ተነርቶ ነበር። ነገር ግን ከሆዱ ህመም ጋር ሲነጻጸር ምንም ማለት አልነበረም ህመሙ። ረሃቡ አእምሮውን አረጋግቶ ወደ «ትናንሽ እንጨቶች ምድር» በሚያደርሰው አቅጣጫ ላይ ማተኮር አስቪለነው ድረስ ፀንቶበት ነበር። በየጣልቃው የሚያላምጣቸው መስኪጅ ፍሬዎች ከመጎምዘዝ አልፈው ረሃቡን ለማስታገስ የሚያግዙ አልነበሩም።

ከድንጋያማ ሥፍራ የሚነሱ ወፎች ወደሚታዩበት ሸለቆ ደረሰ። «ክር-ክር-ክር» የሚል ድምጽ ያላቸው ወፎች። ድንጋይ ወርውሮ ግዳይ ለመጣል ያደረጋቸው ሙከራዎች ከሽፉ። ሽከሙን አራግፎ እንደ አዳኝ ድመት

ከኋላቸው እያደባ ወፎቹን መከተል ያዘ። ሱሪውን እያለፉ በሚሽረከቱት ሥለታም አሎቶች የሚደሙ ጉልበቶቹ ጎያሱን ረሃብ አልፎ ለሚሰማ ህመም አልዳረጉትም። የሰራ አካላቱን ባረጠቡት አጽዋት መካከል እያደባ ሲሹለከለክ ቆየ። ምግብ የማግኘት ጉጉቱ እርጥበትም ሆነ ቅዝቃዜን የማገናዘብ ብቃቱን ሰልቦት ነበር።

ሁልጊዜም ቀድመውት የሚያፈተልኩት ወፎች የሚስቁበት ይመስል «ክር-ክር-ክር» እያሉ ይበራሉ። አንድ ጊዜ ግን ከአንደኛው ምናልባትም አንቅልፍ ከወሰደው ወፍ አጠገብ ደርሶ ነበር። ከድንጋይ ሥር አፈትልኮ ባጠገቡ ሽው አሰካለበት አፍታ ድረስ አሳየውም ነበር። በዚያው ቅጽበት ከአየሩ ጋር የጨመደዳቸው ሦስት የጭራ ላባዎች ከጭብጡ ውስጥ ሲቀሩ አምልጦት ነጎደ ወፉ። ላባዎቹን ትቶለት የበረረውን ወፍ በጥላቻ ስሜት ከማየት አልፎ ቃላቱ በደል የፈፀመበት ያህል እዘነበት ሰውየው። ቀጥሎ ዓዙን ወደ ተወበት ተመልሶ፣ እክቱን በጀርባው አዝሎ ጉዞውን ቀጠለ።

ቀኑ በመግፋት ላይ ሳለ ሃያ ወይም ከዚያ በላይ አጋዘኖችን በቀላል የተኩስ ኢላማ ርቀት ከተመለከተበት ሸለቆ ደረሰ። በሩጫ ቢከተላቸው ሊይዛቸው እንደሚችል የሚያስብ ደመ-ነፍስ በውስጡ ዳብሮ ነበር። በአፉ ወፍ ያንጠለጠለ አንድ ትንሽ ጥቁር አንስሳ ወደሱ በመምጣት ላይ መሆኑን ሲያጤን በጩኸት አስደንግጦ ግዳዩን ሊያስጥለው ሞክረ። ጩኸቱ አስፈሪ ነበር። የበረገገው አንስሳ ግን ወፉን እንደያዘ አግሬ አውጪኝ አለ።

ከሰዓት በኋላ ጥቅጥቅ ብለው በበቀሉ ሳሮች መሃል የሚፈስ አንድ ጅረት ተከትሎ ተጓዘ። ሳሮቹ ያለትክልት ዝርያ የሚመስል ነጭ ድቡልቡል ቋር እንዳሰላቸው ሲያጤን ከሥራቸው መንግሎ ተስገብግቦ ወደ አፉ ላካቸው። የላይኛው ሽፋናቸው በቀላሉ የሚታኘክና የምግብነት ተስፋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለው ይመስል ነበር። ውስጣቸው ግን ቃጫና ጠጣር ብቻ ሳይሆን እንደ መስኪጅ ፍሬዎች ሁሉ ምናምኒት የምግብ ፋይዳ የሌለውም ጭምር ነበር። ነገር ግን በእጅና ጉልበቱ እየዳኸ እንደላም እየነጨ ተመገባቸው።

በጣም ከመድከሙ የተነሳ የማረፍ ፍላጎቱ ከፍተኛ ነበር። ነገር ግን ከ«ትናንሽ እንጨቶች ምድር» ለመድረስ ከነበረው ፍላጐትም በላይ ረሃቡ ነበር የሚጎዳው። ድካሙ ሁሉ ፍሬ ቢስ ሆነበት እንጂ የሚበላ ነገር ለማግኘት አያንዳንዱን ኩሬ ከማሰስ አልቦዘነም ነበር። አመሻሽ ላይ ግን ከእንደኛው ኩሬ ጡስጥ እንዲት ትንሽ አሳ ተመለከተ። እጅን ሰዶ ለመያዝ ያደረገው ሙከራ ሲከሽፍ ጭቃውን ሳይቀር እያማሰለ በደመ-ነፍስ ማሰሱን ቀጠለ። ነገር ግን ከመስንበገቡ ብዛት ኩሬው ውስጥ ከመደፋት ውጪ ያተረፈው ነገር አልነበረም። ከዚህ በኋላ ግን ድፍርሱ ውሃ አይታውን ስሊጋረደው አሰኪጠራ ለመጠበቅ ተገደደ።

ኩሬው በጭቃው እስኪደፈርስ በድጋሚ ውሃውን አተራመሰው። ከዚህ በኋላ ግን ጭቃው እስኪዘቅጥ ወይም ውሃው እስኪጠራ መታገስ አልቻለም። የቆርቆሮ ጣሳ አውጥቶ ውሃውን እየጨለፈ ከኩሬው ውጪ ሰመድፋት ተጣደፈ። ውሃው ተመልሶ ወደ ኩሬው እንድሚገባ ቢያጤን ግን ተረጋግቶ ሥራውን ቀጠለ። ራሱን ስማረጋጋት ያደረገው ጥረት የልቡን ምትና የአፎቹን እንትጥቅጠሽ ስማለዘብ አልረዳውም። ከግማሽ ሰዓት ጥረት በኋላ ኩሬው ከሞላ ጎደል ተጋብቶ ነበር። የቀረው ውሃ አንድ ኩባያ እንኳን የሚሞላ አልነበረም። አሳው ግን የለም!

የተረገመ አሳ! ከድንጋይ መሃል ባሰኙ ጠባብ መሿለኪያ ወደ አጎራባች ኩሬ ጎበቱ ኖሯል። ይሄኛው ኩሬ ሙሉ ሲሊትና ሙሉ ቀን ቢቀዳም ያሚያልቅ አልነበረም። ቀድሞውኑ ጠባቧን መሿለኪያ በድንጋይ ደፍኗት ቢሆን ኖሮ ምን ነበር!

ሀሊናው በቁጭት ተብከነከነ። አዘነ። አናም ከአርጥቡ መሬት ላይ ተቀምጦ አሰቀሰ። መጀመሪያ ዝግ ብሎ ሰራሱ ብቻ ነበር ያለቀሰው። አየቆየ ግን ጮክ ብሎ በዙሪያው ሰነበረው ምህረት የለሽ ባዶ ምድር አለቀሰ።

አሳት አደይዘ ሙቅ ውሃውን አየተነነጨ በውኑቱን ከሚሚታ ቢኒሳ ባለፈው ሌሊት እንደደረገው ሁሉ የድንጋይ ከብ ገንብቶ መስፈሪያውን አበጀ። የመጪሪሻ ተግባሩ ከብራቶቹ ደረቅ መሆናቸውን ማረጋገጥና ሰዓቱን መመላት ነበር። ቁርጭምጭሚቱ በህመም ነቅሟል። እሱ ግን ከፉኛ መራቡን ብቻ ነበር የሚያውቀው። እረፍት የለሹን አንቅልፍ በሚያስንመሽር የምግብ ቁልል ከተንከሸበሸ ህልም ጋር አባለፈው።

ከእንቅልፉ ሲነቃ ታሞ ነበር። በርዶታልም። ባዶውና ግሉዙ ዓለም ዛሬም ለበሐይ በረከት አልታደለም። የምድር ስማዩ ግርጣት ብሶበት ነበር። ቀዝቃዛ ነፋስ ይነፍሳል። የከረብታ ጫርቾ በበረዶ ነጥተዋል። አሳት አደይዘ ውሃ በማፍለት ላይ ሳለ የአካባቢው አየር ሳይቀር የበረዶውን ንጣት መሳበሱን አስተዋለ። ከሞላ ጎደል አርጥብና ከፊል ዝናብ የሆነው ባረዶ ጅምር ላይ መራት እንደነካ ይቀልጥ ነበር። አየቆየ ግን አየበረታና ምድሩን አየሸፈነው መጥቶ እሳቱንም አጠፋበት።

ከለመድረሻው የሚያውቀው ነገር አለመኖሩ እንጂ እየሆነ ያለው ሁሉ ቅራቅንቦውን አገለሎ በአስቸኳይ ጉዞ መጀመር እንዳለበት የሚጠቁም ምልክት ነበር። በዚህ ሰዓት በለ «ትናንሽ እንጨቶች ምድር»ም ሆነ በለ ቢል ወይም ኩዲዝ ወንዝ አጠገብ በአራ ከተደፋው ጀልባ ሥር ስለሚገኘው የንበረት መደበቂያ ከሚጨነቅ ህሊና ጋር አልነበረም። ምህረት የለሹ ረሃብ ልቡን ነስቶታል። ሲላው ቀርቶ በአሁኗ ሰዓት ሽለቆምቹን ብማቋረጥ ላይ መሆኑን እንኳ አቅጣጫውን አላጤነውም ነበር። ዋነኛ ጉዳዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውሃማምቹን መስኪድ ፍሬምች እያጣጣመ፣ ባሰቋሩን ሳር እያሻመደ በአርጥቡ በረዶ ላይ መኪተን ብቻ ነበር። ጎምዛዛው ፍሬም ሆነ ጣዕም የሰሹ ሳር ረሃቡን የሚያስታግስ ፋይዳ የላቸውም። ነገር ግን እነሱኑ ከመብላት ውጪ አማራጭ አልነበረውም።

ውሰሙን ያሳረገበት ምሽት መጥፎ ነበር። እሳትም ሆነ የሞቀ ውሃ አልነበረውም። በረሃብ የተነጀሰውን ሴሊት በአንቅልፍ ለማሳለፍ በብርድልብሶቹ ተጠቅልሎ ተኛ። በረዶው ወደ ቀዝቃዛ ዝናብ ተለውጦ ነበር።

የሴሊቱ ጨለማ በፀሐይ አልቦው ግራጫ ቀን ተተካ። ዝናቡ አላርቷል። ሲከረትፈው የባጀው ሥለታም ረዛብ ወደ ደነዝ ህመም ተቀይሮ ነበር። ህመሙ ቀሳፊ አልነበረም። እንዲያውም ፦ልብ ገዝቶ ስለ «ትናንሽ አንጨቶች ምድር»ና ከዲዝ ወንዝ አጠገብ ስለሚገኘው የንብረት መደበቂያ ማሰብ ችሎ ነበር።

የአንደኛውን ብርድልብስ ቅሪት ተልትሎ አንድ ቁራጭ በመድማት ላይ ከነበረ እግሩ፣ ሴሳውን ካበጠ ቁርጭምጭሚቱ ላይ ጠምዮሞ ለሙሉ ቀን ጉዞ ተዘጋጀ። ጓዙን ከማንሳቱ በፊት ግን ኮሮጆውን መያዝ እንዳለበት ለመወሰን ተቸግሮ ቆየ። ሆኖም በስተመጨረሻ ከቀሪው አክት ጋር ተሸክሞት ጉዞውን ቀጠለ።

ከክረብታ ጫፎች በስተቀር በረዶው ሁሉ ቀልጦ ነበር። ፀሐይ ወጥታለች። አቅጣጫ ስቶ እንደነበረ የተረዳው በዚህ ጊዜ ነበር። እናም የሳተውን አቅጣጫ ለማጣጣት ቀኙን ይዞ ብዙ ርቀት መጓዝ ነበረበት።

ረሃቡ እንዳለፉት ቀናት ባይከረትፈውም ክፉኛ ስለተዳከመ በተደጋጋሚ ማረፉ የግድ ነበር። በነዚህ ጊዜያት መስኪድ ፍሬምችና ሳር ይበላ ነበር። የልቡ ምት ስለም አሳጥቶታል። ጉዞ በጀመረ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ክፉኛ ከመደለቁም በላይ ህሊናውን ሲስት አስኪዳው ድረስ

በጥሞትና በተከታታይ ይንደቀደቅ ነበር።

ኣሁሉ ቀን ላይ ከአንድ ትልቅ ኩራ ውስጥ ሁለት ትናንሽ አሶች ተመለከተ። ውሃውን ጨልፎ ኩራውን ማጋባት የሚቃጣ አልነበረም። ነገር ግን በዚህ ጊዜ በተሸለ ሁኔታ ተረጋግቶ ስለነበር አሶቹን ለመያዝ ቻለ። መጠናቸው ከትንሿ ጣቱ የማይበልጥ መሆኑ አሳሳቢ አልነበረም። የረሃቡ ብዛይ ካለፉት ቀናት በእጅጉ ተለውጦ ነበር። የሆዱ ህመም ይበልጥ ከመደንዘዙም በላይ ከናካቴው ሆዱ ከቀሪ ሰውነቱ ተነጥሶ በአንቅልፍ ላይ ያለ መስሎ ነበር። አሶቹን በክፍተኛ ጥንቃቄ ተመገባቸው። የሚመገበው ስለራበው ሳይሆን በሌላ ራሱን በቻለ ምክንያት ነበር። የምግብ ፍላጎቱ ቢከስምም ስመኖር መብላት እንዳለበት አሳምሮ ያውቅ ነበር።

ምሽት ላይ ተጨማሪ ሦስት ትናንሽ አሶች ይዞ፣ ሁለቱን ተመግቦ ሦስተኛውን ሰቁርስ አሳደረው። እጽዋቱ በፀሐይ ሙቀት በመድረቃቸው አሳት ለማያያዝ አልተቸገረም። በዚያን ዕለት የተጓዘው ጠቅላላ ርቀት ከነፋ ኪ.ሜ የሚበልጥ አልነበረም። በሚቀጥለው ቀንም ልቡ ችግር ባልፈጠረባቸው ጊዜያት ብቻ እየተጓዘ የሸፈነው ርቀት ከሰባት ኪ.ሜ አልበለጠም። የሆዱ ህመም ሙሉ በሙሉ ከስሞ ነበር። እውነትም እንቅልፍ መስዶት ነበር ሆዱ። በእሁት ጊዜ የአጋዘኖች ቁጥር ከበረከተበትና ተኩላዎች ካሉበት ገጠር ደርሷል። ጨኽታቸው ገጠሩን እያቆራረጠ ከጆሮው ይደርስ ነበር። አንድ ጊዜ ሦስት ተኩላዎች መንገዱን አቋርጠውት ሲሄዱ ተመልክቷል። አሁንም መሽቶ ነጋ። ህሊናው ይበልጥ ምክንያታዊ በሆነበት በዚህ ጠዋት ከአጋዘን ቆዳ የተሰፋው ኮሮጆ የታሰረበትን ጠፍር ፈታው። ኮሮጆው ውስጥ የነበረውን ቢጫ የወረቀት አቧራ ከብርድልብሱ ላይ ዘርግፎ ከሁለት ቦታ ከፈለው። ቀጥሎ አክሲታውን በብርድልብስ ቁራጭ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠቅልሎ ከአንድ የአለት ቁልል ስር ደበቀው። ቀሪውን ከፋይ ወደ ኮሮጆው መለሰው። መጨረሻ ላይ በተረፈችው አንዲት የብርድልብስ ትልታይ እግሩን መጠምጠም ያዘ። አሁንም ጠመንጃውን ይዞት ነበር። ምክንያቱም ከዲገ ወንዝ አጠገብ ከነበረበት መደበቂያው ውስጥ ጥይቶች ነበሩና።

አለቱ ደመናማ ነበር። ተኝቶ የሰነበተው ረሃብ የተቀሰቀሰበት ቀን! ከፋኛ ደክሞታል። እናም መውደቁ ያልተለመደ ክስተት አልነበረም። አንዴ ባጋጣሚ ከአንድ የወፍ ጎጆ ላይ ወድቆ ነበር። አደሚያቸው ከአንድ ቀን የማይበልጥ አራት ትናንሽ ጫጩቶች የነበሩበት ጎጆ! አራቱም ከአንድ ጉርሻ የሚያልፉ አልነበሩም። ተስገብግቦ ከጎረሳቸው በኋላ ከነነፍሳቸው አንደ አንቁላል ቅርፊት እዳሽቃቸው ጫጩቶቹን። እናቲቱ ወፍ ዙሪያውን እየተሽከረከረች በቁጣ በመጮኽ ላይ ሳለች በጠመንጃው ሰደፍ ከአየሩ ጋር ሊቀዝፋት ሰጥቷት አመለጠችው። ነገር ግን አዘታትሎ ከወረወራቸው ድንጋዮች በአንዱ ክንፏ ላይ አገኛት። የተሰበረ ክንፏን እየጎተተች ምድር ሰምድር ሸሸች ወፏ። ተከተላት።

ጫጩቶቹ በየትዬለሌ ረሃብ ሰተፈተነ ከርሱ ምንም ማለት አልነበሩም። በሀመም በነቀዘ ቁርጭምጭሚቱ እየዘለለ ድንጋይ በወረወረ ቁጥር ይጮህ ነበር። እየወደቀና እየተነሳ፣ የዓይኖቹን ብሽቦታ በመዳፉ እያበሰ በከፍተኛ ትዕግስት ተከተላት። ብሽቦታው ራሱን ሊስት የመቃረቡ ምልክት ነበር።

ወፊቱ ወደ ሸለቆው ዝቅተኛ ምድር ስትመራው አይታው በእርጥቡ ሳር ላይ ከታተሙ የእግር አሻራዎች ላይ አረፉ። የሱ ዱካዎች አልነበሩም። የቢል መሆን አለባቸው! ቆሞ ሰማረጋገጥ ግን አልቻለም። ምክንያቱም ወፏ በመሮጥ ላይ ነበረች። ከያዛት በኋላ ተመልሶ

ይመረምረዋል ዱካውን።

አዳኝና ታዳኝ ተዳከሙ። እናቲቱ ወፍ በሳኗ ተጋድማ በማለከለከ ላይ ነበረች። ሰውዬውም እንደዚያ። በበርካታ ጫማዎች ርቀት በጎኑ ተኝቶ በማለክለክ ላይ ነበር እሱም። ሰውዬው ሲያገግም ወፊቱም ታገግማለች። አጠገቧ ደርሶ በተራበ እጁ ሊጨመድዳት ሲቃጣ አፈትልካ ትርቀዋልች። ደኅማው የምሽት ብርሃን ወደ ሙሉ ጨለማ ሲለወጥ ግን ሙሉ በሙሉ አመለጠችው። በድካም በላሸቀ ሰውነት አጥፍ ዘርጋ ሲል የቆየው አዳኝ ወድቆ ፊቱ ተገጠበ። ቀጥሎ ወደ አንድ ጎን ተከንብሎ ሰዓቱን ከሞላ በኋላ እስከጠዋት ድረስ እዚያው ተኝቶ አደረ።

ሌላው ግራጫ ቀን ተጀመረ። የብርድልብሱን እኩሌታ ለእግር መጠቅለያ ተጠቅሞበት ግማሹ ብቻ ነበር የተረፈው። የቢልን ዱካ ፈልጎ የማግኘት ሙከራው አልሰመረም። ጥቅምም አልነበረውም። ሰውዬው በሀሊናው ሳይሆን በረሃብ መነዳት ከጀመረ ቆይቷል። እኩለ ቀን ላይ የገዙ ክብደት ከአቅም በላይ ሆነበት። እናም በድጋሚ ወርቁን ከሁለት አካፈለው። በዚህ ጊዜ ግን እኩሌታውን ከመሬት ነበር ያፈሰሰው። ከሰዓት በኋላ ደግሞ የተረፈውንም ወረወረው። የቀሩት ንበረቶች የብርድልብሱ እኩሌታ፣ አንዲት ስስ የቆርቆር ጣሳና ጠመንጃው ብቻ ነበሩ።

አእምሮው መዘባረቅ የጀመረው ከዚህ በኋላ ነበር። ከጠመንጃው ውስጥ አንዲት ጥይት ስለመኖሯ ማሰብ ጀመረ። ጠመንጃው ባዶውን መሆኑን ግን ያውቅ ነበር። ሆኖም ቅዥቱ ካለማቋረጥ ቀጠለ። ሰሰዓታት ከታገለው በኋላ ጠመንጃውን ከፍቶ ለመመልከት ተገደደ። ባዶውን ነበር።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ አንደገና አገረሽ ቅዠቱ። አሁንም ሲታገለው ቆየ። መጨረሻ ላይ አእምሮውን ለማሳረፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲል ብቻ አሁንም ጠመንጃውን ከፊተው። አሁንም ባዶውን ነበር ጠመንጃው።

ሀሊናው በከፋ ሁኔታ የዘባረቀባቸው ጊዜያትም ነበሩ። ሆኖም ሆዱን የሚከረትፈው ስለታም ረሃብ አእምሮውን ወደ ገዛዱ ዓለም የመመለስ ብርታት ስለነበረው የምናቡ ተውኔት ለረዥም ጊዜ አይቆይም ነበር። አንድ ጊዜ ግን ጭልጥ ካለ የቁም ቅዠት ጎትቶ የመለሰው ራሱን ሲያስተው ምንም ያልቀረው ድንገተኛ አጋጣሚ ነበር። አንድ ፈረስ ከፊት ለፊቱ ቆሞ ነበር። ፈረስ! አይኖቹን ለማመን የተቸገረው ሰው እይታውን የጋረደውን ጉም በፍጥነት አበሰው። የለም፣ ከፊት ለፊቱ የተጋረጠው ፍጡር ፈረስ አልነበረም። ድብ እንጂ። ታላቁ ቡናማ ድብ! አይናቹ ሰውዬውን በመመረመር ላይ ነበሩ።

የሚያደርገውን ከማጤኑ በፊት ጠመንጃውን ግማሽ መንገድ ወደ ትክሻው አምጥቶት ነበር ሰውዬው። ጠመንጃውን መልሶ የአደን ካራውን ከአፎቱ መዘዘው። ሥጋና ሀይወት ነበር ከፊቱ የተንተረገ! የካራውን ጠርዝና ጫፍ በጣቱ ዳሰሰው። ጠርዙ ስለታም፣ ጫፉም ሹል ነበር።በድንገት ተወርውሮ ሊዘክገክው እንደሚችል እርግጠኛ ነበር። ነገር ግን ያ ጠንቀኛ ልቡ መደሰቅ ጀመረ። መደሰቅ ብቻ ሳይሆን በፍጥነትና በተከታታይ መንደቅደቁንም ቀጠለ። ራሱን ወደመሳት ተቃረበ ሰውዬው።

ጭፍን ልበ ሙሉነቱን ታላቅ ፍርሃት የተካው ከዚህ በኋላ ነበር። በዚህ ድካም ላይ እውሬው ቢያጠቃውስ? ካራውን እንደጨበጠ ተንጠራርቶ ቁመት ሰመጨመር ሞከረ። ድቡ ሁለት እርምጃ ወደፊት ተጠጋ። ሰውዬው ቢሮጥ ድቡ ይከተለው ነበር። ሰውዬው ግን ባሰበት ቆየ። ፍርሃት - ወለድ ልበ ሙሉነት ፅናቱን ሰጥቶት እዚያው ቆመ።

ከአስፈሪ ድምፅ ጋር ገለል አለ አውሬው። የዚህ የማይፈራ ፍጡር ሁኔታ አስግቶት ነበር አሱንም። ሰውዬው የአደጋውን ማለፍ ካረጋገጠ በኋላ የሚብረከረክ ቋንጣዎቹን አጥፎ በእርጥቡ ሳር ላይ ተንበረከከ።

ከቆይታ በኋላ ራሱን መቆጣጠር ቢችል ግን ጉዞውን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ከአስከባሬው የተለየ ፍርሃት ተጫጭኖት ነበር። በምግብ እጦት የመሞት ሳይሆን የሌሎች ከረሃብ ውጪ ያሉ አደጋዎች ፍራቻ። ግአዙን ገጠር አቆራርጠው ከጆሮው የሚደርሱትን የተኩላዎች ጩኸት እንደዋዛ ማለፍ አልቻለም።

የሁለት - ሦስት ተኩላዎች ቡድን በተደጋጋሚ መንገዱን አቋርጦት ነበር። ለጥቃት የሚያደፋፍር ቁጥር ሰላልነበራቸው ብቻ ሳይሆን አጋዘን በማደን ላይ መሆናቸውም ከአደጋ ጠብቆታል። አጋዘን ጠንክሮ አይፋለማቸውም። ይሄ በሁለት አግሮቹ የሚሄድ እንግዳ ፍጡር ግን ይናከስ ይሆናል።

ከሰዓት በኋላ ተኩላዎች ከአንድ ሰዓት በፊት ሙልጭ አድርገው የጋጡዋቸው አጥንቶች ከነበሩበት ስፍራ ደረሱ። በውስጣቸው ከነበረው ሃምራዊ የህይወት ቅሪት በስተቀር ምናምኒት የሥጋ ቅንጣት ያልነበራቸው አጥንቶች። ጅምበር ከመጥለቋ በፊት እንደዚህ እንደማይሆን ምን ዋስትና አለው አሱስ? በማናቸውም ሰዓት አንደጨዛ ሊረግፍ ይችላል ማለት ነው! ግን እኮ የሚያመውም ሆነ የሚያስቃየው ህይወት ነበር። በሞት ውስጥ ስቃይ የለም። ሞት አንቅልፍ ነው። እረፍትም። ታዲያ ሰምንድነው የማይሞተው? ለምንድነው ሞትን የሚሸሸው?

በዚህ ጉዳይ ላይ ለረዥም ጊዜ አላሰበም። በሁለት እጆቹ አጥንት ይዞ ከሳር ላይ ከተቀመጠ በኋላ ሃምራዊውን የህይወት ቅሪት በጥርሶቹ ነከሰው። ጣፋጩ የሥጋ ጣዕም አሳበደው! አንዳንድ ጊዜ አጥንቶቹ ሌላ ጊዜ ጥርሶቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

እየተሰበሩ ሲቆረጥም ከቆየ በኋላ ነበር አጥንቶቹን በድንጋይ አድቅቆ የመመገብ ሃሳብ የመጣለት። የማድቀቁ ሂደት በድንጋይ ከተቀረጠፉ ጣቶቹ ላይ ከባድ ጉዳት አለመድረሱ አስገረመው።

ከዚህ በኋላ አስፈሪዎቹ የበረዶና የዝናብ ቀናት ተከተሉ። መቼ እንደሰፈረ፣ መቼ እንደተንቀሳቀሰ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። የትም ሆነ የት በወደቀበት ቦታ ውሉ ያርፋል፣ በሞት ላይ የነበረ ህይወቱ ሲያንሰራራ ደግሞ ጉዞውን ይቀጥላል። እንደ ህያው ፍጡር በገፃራሱ ሳይሆን በውስጡ በነበረውና ሰመሞት ፈቃደኛ ባልሆነው የህይወት ቅሪት ነበር የሚነዳው። ህመም ወይም ስቃይ አይሰማውም። አእምሮው ግን በዝብርቅርቆሽና በእውር ቅዠት ተሞልቶ ነበር።

ሆኖም ሰቃቅሞ የያዛቸውን የተፈጨ አጥንቶች ከመብላት አልባነኝም። ተጨማሪ ኮረብታ ሳያቋርጥ በአንድ ሰፌ ሽለቆ መሃል የሚወርድ ትልቅ ጅረት ተከትሎ በመጓዝ ላይ ነበር። ነገር ግን ጅረቱንም ሆነ ሽለቆውን አሊያቸውም። መያዣ መጨበጫ ከሌለው ዝብርቅርቆሽ በስተቀር የሚታየው ነገር አልነበረም።

በአንደኛው ጠዋት በጀርባው ከድንጋያማ ሥፍራ እንደተኛ ከብሩህ አእምሮ ጋር ከእንቅልፉ ነቃ። ብሩህና ሞቃት ፀሐይ ወጥታ ነበር

ክርቀት የአጋዘን ጩኸት አዳመጠ። ቀጥሎ ዝናቡን፣ ንፋሱንና በረዶውን አስታወሰ። ነገር ግን በዚያ ሁሉ ውርጅብኝ ውስጥ የቆየው ለሁለት ቀናት ይሁን ለሁለት ሳምንታት የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

በፀሐይ የተፈጥሮ በረከት እየተዝናና ከተኛበት ሳይንቀሳቀስ በዚያው ቆየ።መልካም ቀን አሰ በሀሳቡ። ምናልባት ያለበትን ማወቅ ይችል ይሆናል። ወደ ግ ለመገላበጥ ባደረገው ትግል አቃሰተ።

ከዚያች ወንዝ መኖሩን ሲመለከት ግራ ገባው። ከሁለቱ መሃል ታጥፎ አድማሱን ወደሚያካልለው ከፈኛ ነፋና በኋላ ወደ አንድ ብሩህና አንፀባራቂ ባህር በመፍሰስ ላይ የነበረውን ይሄን ተአምረኛ ወንዝ በጎደናቹ ተከተለው። የሚያየውን ማመን አልቻለም። የተስመደው ምናባዊ ተውኔት እንጂ ከቶም ግዛድ አውነታ እንደማይሆን አሰበ። ከአንፀባራቂው ባህር ላይ መርከብ ሲመለከትማ ባሰበት። አይናቹን ጨፍኖ ገለጣቸው። በአይታው ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አለመኖሩ አሰገረመው። ከጠመንጃው ውስጥ ጥይት እንደሌለ የሚያውቀውን ያህል አዚህ ግድም ባህርም ሆነ መርከብ እንደማይኖር ያውቅ ነበር።

ከበስተጀርባው ድምፅ ሰማ። - ሳል! በብዙ ችግር ወደዚያኛው ጎኑ ተንከባሎ ለመመልከት ሞከረ። ምንም ዓይነት ፍጡር በአቅራቢያው አልነበረም። በትእግስት ጠበቀ። ያው ድምፅ በድጋሚ ተሰማው! በዚያው አፍታ ከአለቶች መሃል ቀሞ በመጨናበስ ላይ የነበረውን አንስሳ ተመለከተው። ተኩላ ነበር። - ሞንቅሳቱን የከበደው፣ አይናቹ የባዘኑና ጆሮዎቹ የተገለፈለፉ ግራጫ ተኩላ። በወሐይ ብርሃን የተጥበረበሩ ዓይቹን እያጨናበስ እሱን በማየት ላይ ነበር። ታሚል።

በዚህ ጊዜ ግን እይታውን አልተጠራጠረውም ነበር። ተጥሎ በምናቡ ዝብርቅርቆሽ ተጋርዶ የቆውን ትርጓት ለመመልከት ፊቱን ወደ ቅድመ- አቅጣጫ መለሰ። አንፀባራቂው ባህርም፣ መርከቡም አዚያው ነበሩ። አይታውን ወደማመኑ ተቃረበ። ዓይኖቹን ጨፍኖ ለረኸርም ጊዜ ካብለለሰ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ተገለፀለት።

ሳይታወቀው ወደ ሰሜን አያደላ፣ ከዲገ ሰርጥ አያፈነገጠና ወደ ኮፐርማይን ሸለቆ አየተጠጋ ሲጓዝ ቆይቶ ኖሯል! ወደ ሰሜን። ይሄ ታሪክኛ ወንዝ ኮፐርማይን ነበር። ያ አንፀባራቂ ባህር ደግሞ አርክቲክ ውቅያኖስ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መርከቧም ከማኬንዘ ወንዝና ከውቅያኖሱ መገናኛ ተነስታ
ወደ ምስራቅ በትንሳፈፍ የቆየች አሳ አጥማጅ ጀልባ መሆኗ
ነው። እሁን ያለችበት ሥፍራ የኮሮኔሽን ሰላጤ ነበር።
ከረሻም ጊዜ በፊት የተመለከተውን ካርታ አስታወሰው።
የሚታየው ሁሉ ግልጽና አሳማኝ ነበር።

ከተጋደመበት ተነስቶ በመቀመጥ በአጣዳፊ ጉዳዮች
ላይ ለማተኮር ሞከረ። ከእግሮቹ ላይ የተጠመጠመውን
የብርድልብስ ትልታዮች ተቀዳደዋል። እግሮቹ ቅርፀ ቢሷ
ሙዳ ስጋ መስለዋል። ከቆርቆሮው ጣሳ በስተቀር
የብርድልብሱ ቅሪት፣ ጠመንጃው፣ ካራውና ባርኔጣው
ጠፍተዋል። ከባርኔጣው ውስጥ የነበሩት ክብሪቶችም
እንደዚያው ። ከሸሚዙ ውስጥ ያሉት ክብሪቶች ግን በጥሩ
ሁኔታ ላይ ነበሩ። ሰዓቱን ተመለከተው አምስት ሰዓት
ይል ነበር። የሰዓቱ አለመቆም ሲያመራምር የሚችል
ጉዳይ ነበር። በየጊዜው ይሞላው ነበር ማለት ነው?

ከመጠን በላይ ቢዳከምም የህመምና የረሃብ ስሜት
አልነበረበትም። በዚህ ቀን ምንም ሆነ ምን ሰሚያደርገው
ሁሉ ምክንያታዊ ነበር። የሱሪውን ጨርቅ እሰከ ጉልበቱ
ድረስ ቀድዶ በእግሮቹ ዙሪያ ጠመጠመው። በእንፀባራቂው
ባህር ላይ መደሚንሳፈፈው መርከብ ከማቅናቱ በፊት ውሃ
አሙቆ መጠጣት ነበረበት።

ከእንቅልፉ እንዳጋሚነት በተጨማሪ የበሽተኛ ያህል
መንቀሣቀሱም ራሱን የቻለ ችግር ነበር። የደረቱ ባር
ለመቃረም ወስኖ ለመነሳት ሲቃጣ ነበር መቆም
እንደማይችል የተረዳው። በተደጋጋሚ ያደረገው ሙከራ
ሲከሽፍ በእጆቹና በጉልበቶቹ ለመዳህ ተገደደ። አንድ ጊዜ
ወደ ህመምተኛው ተኩላ ተጠግቶ ነበር። መተጣጠፍ
በተሳነው ምላስ ፊቱን በማበስ ላይ የነበረው እንስሳ ገለል
ብሎ መንገድ ለቀቀለት። ምላሱ የተለመደው ዓይነት ቀይና
ጤነኛ አልነበረም። ወደ ቢጫ የሚያደላ፣ ቡኔ ቀለም

ያለውና በከፊል በደረቀ ልጋግ የተሸፈነ መሆኑን አጤነ
ለውጡው።

ውሃ አሙቆ ከጠጣ በኋላ ለመቆም ቻለ። መቆም ብቻ
ላይሆን በመሞት ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ማድረግ
የሚችለውን ያህልም መውተርተር ጀመረ። በእያንዳንዱ
ወይም በየሁለቱ ደቂቃ እረፍት መውሰዱ ግን የግድ
ነበር። መሽ። አንበባራቂው ባህር ሙሉ በሙሉ በጨለማ
ሲዋጥ ቀሪው ጉዞ ከሰድስት ኪሚ አንደማይበልጥ ገመተ
ለውጡው።

የበሽተኛው ተኩላ ሳልና የኢጋዘን ኮርማዎች ድምፅ
በሊሊቱ መሃል ይሰማው ነበር። ከሱና ከተኩላው በስተቀር
አካባቢው በጠንካራና በቤናማ ህይወት የተሞላ ነበር።
ተኩላው «በቅድሚያ ህመምተኛው ሰው ሊሞት ይችላል»
በሚል ተስፋ አንደሚከተለው ያውቅ ነበር። ጠዋት ላይ
ዓይኖቹን በገለጠበት አፍታ አንደተከፋ ውሻ ጭራውን
ከቅልጥሞቹ መሀል ሸጉጦ በተራቡ ዓይናቹ ሲመረምረው
ተመልክቶታል።

ወደመርከቡ መንገዝ በጀመረበት ሰዓት አካባቢው በብሩህ
የጠዋት ዐሐይ ፈክቶ ነበር። ዘለቂታውን መተንበይ
ቢያስቸግርም የአየሩ ሁኔታ ግሩም ነበር።

ከሰዓት በኋላ የሌላው ሰው ዱካምቾ ከታተመበት
ስፍራ ደረሰ። አየተራመደ ሳይሆን አየዳኸ አየተንፏቀቀ
መጓዙን የሚያመለክቱ ነበሩ ዱካምቹ። ስለ ቢል የማስብ
ፍላጎት ባይኖረውም አነዚህ ዱካምች የሱ አንደሆኑ
መገመቱ አልቀረም። ስሜትና ውስጣዊ ግፊት ከአእምሮው
ውስጥ ሳይለው ነበር። ሌላው ቀርቶ የህመምን ስሜት
ማገናዘብም ተስኖታል። እጅግ በጣም ደክሞታል፣ ከውስጡ
የነዘረው፣ ለመሞት ያልፈቀደ ህይወት ግን ወደፊት
ይገፋዋል። አምን፣ አሁንም መስኪጅ ጥሬዎችና ቱናንሽ
አሰጉን ይመገባል፣ የሞቀ ውሃ ይጠጣል፣ ህመምተኛውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ተኩላ በዓይናቹ ይጠባበቃል።

ዱካውቹን መከተል ጀመረ። ነባር ግን ከፍጻሜው ስመድረስ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ሳርማው ምድር በበርካታ ተኩላዎች የአግር አሻራ ከተጠቀጠቀበት ሥፍራ ምናምኒት የሥጋ ቅሪት ያልተረፋቹው የሰው አጥንቶች ተመለከተ። በሹል ጥርሶቹ የተሸረካከተ የቆዳ ኮሮጆ ከአጥንቶቹ አጠገብ ወድቋል። - ከአጋዘን ቆዳ የተሰፋ ኮሮጆ ከባድ ቢሆንም የግዱን አነሳው። ቢል አስከፍጻሜው ተሸነሞት ነበር! እሱ ደግሞ አስከ መርከቡ ድረስ ተሸክሞት ሊጓዝ ይችላል! ሳቀ። የሰብዓዊ ፍጡር በማይመስል በረጅሙ በመንከትከት ሳይ ሳለ ተኩላውም አብሮት ጮኸ። ነባር ግን ሳቁ በድንገት ከለመ። እንዴት በቢል ሳይ ይስቃል? ወደነዚህ አጥንቶች የተቀየረው በርግጥም ቢል ከሆነ...?

ተመልሶ ወደ ጉዞ አቅጣጫው አቀና። ቢል ከህይት ፈጽሞበታል። ሆኖም ወርቁን መውሰድም ሆነ አጥንቱን መበሳት የለበትም። በፍፁም! ነገ የተገላቢጦሽ ቢሆኑኖሮ ግን ቢል እንደዚህ ከማድረግ የሚመለስ ሰው አልነበረም።

ከአንድ ኩሬ አጠገብ ደርሶ ዓሣ ለመፈለግ ባቀረቀረበት አፍታ የተመለከተውን ትዕይንት ከቶም ማመን አልቻለም። ነባር ግን የገዛ ምስሉን ነበር ከውሃው ውስጥ የተመለከተው። ማገናዘብ ያቆመ ህሊናውን ወደ እውነታ የመመለስ አቅም እስኪኖረው ድረስ አስገራሚ ነበር ትዕይንቱ።

በኩሬው ውስጥ ሦስት ዓሦች ነበሩ። ውሃውን ቀድቶ ማጋባት የሚሞክር አልነበረም። አሦቹን በቀርቀሮ ጣሳ ለመያዝ ያደረጋቸው ሙከራዎች መክሸፋቸውን ሲያጤን ተነስቶ ቆመ። በድካም በላሽቀ ሰውነቱ ከኩሬው ውስጥ እንዳይደፋ ሰግቶ ነበር የቆመው። ከወንዙ ዳርቻ ከነበሩት በርካታ ግንዲላዎች በአንዱ ተሳፍሮ በመንሳፈፍ ከወንዙ ጋር ቁልቁል ለመውረድ ያልደፈረውም በዚሁ ምክንያት ነበር። ከቶም በራሱ መተማመን ከሚያስችለው ሁኔታ ጋር አልነበረም።

በዚህ ዕለት በሱና በመርከቡ መካከል የነበረውን ርቀት በአምስት ኪ.ሜ ማጥበብ እንደቻለ አርግጠኛ ነበር። በተከታዩ ቀን ግን እንደቢል አየዳኸ ለመጓዝ በመገደዱ ከሦስት ኪ.ሜ በላይ መሸፈን አልቻለም። አምን፣ በአምስተኛው ቀን መገባደጃም ገና በኪሎ ሚትሮች የሚሰላ ርቀት ይቀረው ነበር። የአየሩ ሁኔታ ሰላማዊ በመሆኑ ብቻ ጉዞውን ቢቀጥልም በቀን ከአንድ ኪ.ሜ በላይ መጓዝ አልቻለም። በሹተኛው ተኩላ ከኋላ ከኋላው እየተንቀረፈፈ ያስል ነበር።

ጉልበቶቹ ልክ እንደ ውስጥ አግሩ ቀይ ስጋ መስለው ነበር። ሽሚዙን ከበስተጀርባው ቀዶ በጉልበቶቹ ዙሪያ ጠቅልሎታል። ነባር ግን በሚደህባቸው ሳሮችና ድንጋዮች ላይ ቀይ ምልክት እየተወ ነበር የሚያልፈው። አንድ ጊዜ ተገላምጦ በተመለከተበት አፍታ ተኩላው ከሳር ላይ የቀረውን ቀይ ምልክት ተስገብግቦ ሲልስው ተመልክቶታል። ይሄንን ቀፋፊ ፍጡር አስክልገደለው ድረስ ፍጻሜው የከፋ ሊሆን አንደሚችል አሰበ። የከንግዲሁ ትርጓት ታይቶም ሆነ ተተርክ የሚያውቅ አልነበረም። - ሁለት የታመሙ ፍጡራን በመሞት ላይ የነበረ አካላቸውን እየጎተቱ፣ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ያደቡበት የአንድ ግሉገ ምድር ትርኢት!

ተኩላው ጤኛ ቢሆን ያን ያህል ባልተጨነቀ ነበር ሰውዬው። በዚህ ሰሞት በቀረበ ማስጠሉ ፍጡር መበላት ግን በእርግጥም ዘግናኝ ነበር። የአእምሮው ገብርቅርቆሽ በድንገት አገረሸ። መያገ መጨበጫ ከሌለው ቅገቦት ውስጥ የሚቆይባቸው ጊዜያት እየበረከቱ፣ በትክክል

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያስብባቸው ጊዜያት እያጠሩ መጡ።

አንድ ጊዜ ጭልጥ ካለ አንቅልፍ የቀሰቀሰው ኪሮው አጠገብ የተሰማው የተኩላው ሳል ነበር። የሰውዬው መንቃት ያስደነገጠው አንሰሳ ወደ ኋላው ለማፈግፈግ በሞከረበት ቅጽበት ተወለካከፎ ወደቀ። ትርኢቱ ሊያስቅ የሚችል ነበር። ሰውዬው ግን አልሳቀም። አልፈራምም። ነግ ሆኖ ነገሮችን ማገናዘብ ችሎ ነበር።

ዓይኖቹን አብሶ ከ6.5 ኪ.ሜ ከማይበልጥ ርቀት ላይ መርከቡን ተመለከተው። ባሁሩን እየከፈለች በመንሳፈፍ ላይ የነበረችውን ትንሽ ጀልባ ማየት ቻለ። ስድስት ኪ.ሜ ተኩል ቀርቶ አንድ ተኩሱን አንኳ መሸፈን እንደማይችል ያውቅ ነበር። ነገር ግን የግዱን መቻል ነበረበት። መኖር ነበረበት፣ የዚህ ሁሉ ስቃይ ማሳረጊያ ከቱም ሞት መሆን የሰበትም። በፍጹም! ይሄንን የሚያስበው ከሞት ጭበጥ ውስጥ ከገባ በኋላ መሆኑ ነበር አሳዛኙ ጉዳይ። ዓይኖቹን ጨፍኖ ራሱን ለማፈጋጋት ሞከረ። ለመተኛት የነበረው ብርቱ ፍላጎት አስፈርቶታል። ከተኛ በዚያው እንዳይቀር ሰግቷል። እናም ከእንቅልፉ ጋር ትንንቅ ገጥሞ ነበር። እንቅልፉ እንደ ባህር ነበር። እንዳንዱ ባለ በሉስ አትመ አየተወራጨ በውስጡ ይዋኝና የግዱን ከመሰመጥ ይተርፍ ነበር።

ሳይንቀሳቀስ በጀርባው ተኝቶ በቆየባቸው ጊዜያት የህመምተኛው እንሰሳ ትንፋሽ ቀስ በቀስ ለጆሮ ሊሰርብ ይታወቀው ነበር። በስተመጨረሻ የተኩላው የደረቱ ምላስ ፊቱን ስበስው? እጆቹን ሰንዘረ ሰውዬው፣ ነገር ግን የተኩላውን ማንቁርት ሳይሆን አየሩን ነበር የጨመደደው። አምጋ፣ ፍጥነት ጥንካሬን ይጠይቃል። ሰውዬው ግን ተፈላጊው ጥንካሬ አልነበረውም።

ድምጽ አጥፍቶ በትእግስት መጠባበቅ ለተኩላው ቀላል ፈተና አልነበረም። ለሰውዬውም እንደዚያው። ኃያሉን

አንቅልፍ ተቋቁሞ ለማሸነፍ ቀን ካለ አንቅልፍ ቆየ ሰውዬው። የተራብ ዘርሱን ሊያሟሽበት ያኮበኮበውን አውራ ክሰብዓዊ ፍጡር ችሎታ በላቀ ትዕግስት በመጠበቅ ላይ ነበር። አንቅልፍ አያጥላው በህልም ዓለም ውስጥ የሚዋልልባቸው ጊዜያት ቢኖሩም የሚያንኳርፈውን ትንሩሽ ከማጸመጥ አላገዱትም።

በዚህ ጊዜ ግን አጅን በማሰስ ላይ የነበረው የተኩላው ምላስ አንጂ ትንሩሽ አልነበረም ከህልም ዓለም የመለሰው። አሁንም በትዕግስት ጠበቀ ሰውዬው። ዝግ ብሎው የጀመሩት የተኩላው ጥርስ ጠበቅ አድርገው ነከሱት። ሊከተለውና ሲጠብቀው የቆየውን ምግብ ለመገከስ የሚችለውን ያህል በመታገል ላይ ነበር ተኩላው፣ ሰውዬው የአንስሳውን አፍ በእንድ እጁ አጋጥሞ ከያዘ በኋላ በላሸቀ ጉልበት በመወራጨት ላይ የነበረውን አንሰሳ በለላው እጁ ያዘው። ግብግቡ ቀጠለ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ የሰውዬው ክበደት ሙሉ በሙሉ ከተኩላው በላይ ሞሰ። የተኩላውን ማንቁርት ፈጥርቆ ለመያዝ እጆቹ በቂ አልነበሩም። እናም የጥርሶቹ አርዳታ የግድ ነበር። አፉ በበጉር እስኪሞላ ድረስ አሞንብሶ ማንቁርቱን ነክሰው፣ እየቆየ ትኩስ ደም ወደ ጉሮሮው ሲወርድ ታወቀው። ታናው ጥሩ አልነበረም። ተንከባሎ በጀርባው ተንጋለለ ሰውዬው።

...ቤድ ፎርድ ከተባለችው መርከብ ላይ የተሳፈሩት የሥነ ፍጥረት ተመራማሪዎች ከባሀሩ ዳርቻ በተመለከቱት አንግዳ ነገር ላይ አተኮሩ። ነገርዬው ከባርቻው ምድር ወደ ባህሩ ጠርዝ በመንሳቀቅ ላይ ነበር። የምርምር ሰዎች እንደመሆናቸው ከአስተኛ ጀልባ ላይ ተሳፍረው ወደዚያው ለመቅዘፍ ጊዜ አልወሰደባቸውም። የሚያዩትን ነገር ሰውብሰው መጥራት አንጂ ሀያው ፍጡር መሆኑን ማወቅ አላስቸገራቸውም። ማየት ብቻ ሳይሆን የሚሰራውንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ማወቅ የተሳነው እንግዳ ፍጡር በደረቱ ተጉዶ ካለማቋረጥ በመወራጨት ላይ ነበር። እንደዚህ ተወራጭቶ የሚሸፍነው ርቀት ግን በሰዓት ከ20 ጫማዎች የሚበልጥ አልነበረም።

...ከሦስት ሳምንት በኋላ ሰውዬው ከአሣ ማጥመጃ ጀልባ ውስጥ ተጋድሞ ማንነቱንና ባለፉት ጊዜያት የደረሱበትን ችግሮች ምንም ሳያስቀር ተናገረ። ፊቱ በአምባ እየታጠበ ስለ እናቱና ካሊፎርኒያ ውስጥ በአበቦች መሃል ስለሚገኝ መኖሪያ ቤቱ ሳይቀር ተናዘዘ።

ከተመራማሪዎቹና ከመርከቧ ኦፊሰሮች ጋር በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ የተቀመጠው ከጥቂት ቀናት በኋላ ነበር። በዚህ ዕለት የተትረፈረፈው ማዕድ በፈጠረለት ሃሴት ሁለመናው ፈክቶ ነበር። ነገር ግን ከማዕዱ ላይ የተተከሉ ዓይኖቹ እያንዳንዱን ጉርሻ በንቃት ከመከታተል አልቦዘኑም። በእያንዳንዱ ጉርሻ የሚጎድለው ምግብ ከገጽታው ላይ የሃዘን ምልክት ይተው ነበር። በምግብ ሰዓት አዚያን ሰዎች መጥላቱ ግን የአብደት ምልክት አልነበረም። የምግብ እጥረት እንዳይከሰት የመከጋት እንጂ። ስለአቅራቡቱ አስተናጋጁን፣ ወጥ ቤቱንና ካፒቴኑን አነጋግሯቸዋል። የምግብ እጥረት አለመኖሩን ብቻ ሳይሆን እንደማይኖርም ደግመው ደጋግመው አረጋግጠውለታል። ነገር ግን ሊያምናቸው አልቻለም። እናም በራሱ ዓይኖች ለማረጋገጥ ወደ ማዕድ ቤቱ መሄዱ አልቀረም።

በእያንዳንዱ ቀን ሰውነቱ እየሰፋ፣ እየገዘፈ፣ እየወፈረ ሲመጣ ተስተዋለ። ተመራማሪዎቹ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ ምክራቸውን ከመለገስ አልፈው የሚቀርብለት ምግብ በልኩ እንዲሆን አደረጉ። ያም ሆኖ ክብደቱ ካለማቋረጥ መጨመሩን ቀጠለ።

ነገሩ የገባቸው የመርከቡ ሠራተኞች ይስቁ ነበር። ተመራማሪዎቹ ሰውዬውን መከታተል ከመጀመራቸው

ነበር ሚስጥሩ የተገለፀላቸው። ከቁርስ በኋላ በመርከቧ ውስጥ ሲንሳፈፉ በአንኮሮ ይከተሉት ነበር። አንዱን የመርከቧን ሠራተኛ እጁን ዘርግቶ ሲለምነውና ሠራተኛው ከፈገግታ ጋር ቁራሽ ዳቦ ሲያቀብለው ተመለከቱት። ስስታም ሰው ወርቅ ሲያይ የሚሆነውን ያህል ዳቦውን በፍቅር ተመለከተው ሰውዬው።

ተመራማሪዎቹ በጀመረው ሁኔታ እንዲቀጥል ትተውት በሚስጥር መኝታውን መፈተሽ ያዙ። በዳቦ ቁልል ተሞልቶ ነበር አልጋው። እያንዳንዷ ጥጋት በዳቦ ተሞልታ ነበር። ይሄም የማበዱ ምልክት አልነበረም። ሊያጋጥመው ለሚችል ለሌላ ረሃብ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ እንጂ። ተመራማሪዎቹ ችግሩ እያደር እንደሚተወው ተናግረው ነበር። ነገር ግን ቤድ ፎርድ ወደ ሳንፍራንሲስኮ የባህር በር ከማቅናቷ በፊት ሙሉ በሙሉ ተሻለው።


ልቦለድ

t.me/OLDBOOKSPDF

እውነተኛ ፍቅር

አሸቱ ተፈ

እየኮረኮረ ስሜት እየነካ
እውነተኛ ፍቅር ያስጨንቃል ለካ።
የግሉ መሆንሽን ሕሊናዬ ቢያውቅም
ሳጣሽ ይጨንቀኛል ሐዘን ከኔ አይርቅም።
ችግር አይሉብኝ ዘወትር ባልበላም
አጠገቤ ስትሆኝ አገኛለሁ ሰላም።
መጥፎ ተናግሬ ሰዎች ባላስቆጣም
አንቺ ስትርቂኝ ይከፋኛል በጣም።
ስሜት ታክብሪያለሽ ፍቅር አትንቂም
አልማዝ ነሽ እንቁ ነሽ ማጭበርበር አታውቂም።
ጉልበቱ እየራደ ያንቀጠቅጠኛል
ላንዲት ሰከንድ እንኳ ብለይሽ ያመኛል።
ውሃ እነቀኝ ብዬ ሰይምሰል ባልዋሽም
ስላንቺ ሳላስብ አይነጋም አይመሽም።
ጨረቃና ፀሐይ ይሰበሩ ወድቀው
ስላንቺ ብቻ ነው እኔ እምጨነቀው።



የመጣቱ ፈተሰኛ ፍፃሜ

ግዛው ዓለማየሁ

ስንት ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ባለፉት 17 ዓመታት መተኪያ የሌላትን ህይወታቸውን አጡ? ብሰን ብንጠይቅ፤ የምናገኘው መልስ ቤቱ ይቁጠረው የሚል ይሆናል። የውጣት መስፍን ታሪክም ይህንኑ ያረጋግጥልናል። አባቱን ረሽነው ንብረታቸውን ሲዘርፉ ስለፈሰጉ እናቲቱን መህኒ ጨመሯቸው። ወጣቱ ፈረሰኛም ይሽኔ ወታደራዊ ፖሊስ እስር ቤት ወረደ። እናትየው ከስድስት ወራት በኋላ ቢፈቱም ንብረታቸው ከመወረስ፣ ልጃቸውም ከርቸሌ ከመውረድ አልዳኑም። ከዚያን ወዲህ እናትና ልጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልተገናኙም፣ እንደተለያዩ ቀሩ።

ወጣቱ ፈረሰኛ ከአባቱ ጀኔራል ደበበ ኃይለማርያም እና ከእናቱ ከወይዘሮ ሶስና አበበ ሀዳር 12ቀን 1949 ዓ.ም ኮሪያ በመባል በሚታወቀው አካባቢ ተወለደ።

መስፍን በ1966 ዓ.ም በተቀበለው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በሰባቱም የትምህርት አይነቶች እጅግ ከፍተኛ (A) ውጤት በማግኘት ነበር ያለፈው። ሆኖም ዩኒቨርስቲ ሊገባ አልቻለም። በኮሎኔ ፈንታ ወህኒ ከአድኅት ይልቅ ያላግባቡ ሞት ተፈርዶለት የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኖ ቀረ።

መስፍን በህዝብ ዘንድ ይበልጥ ይታወቅ የነበረው በኢትዮጵያ የፈረስ ዝላይ ውድድሮች ሲሆን ይህንንም የስፖርት አይነት የጀመረው ገና የስድስት ዓመት ልጅ ሳለ ነበር። ሰባት ዓመት እንደሞላውም ወደ ጂቡቲ በማምራት በወጣት ኢትዮጵያዊ የፈረስ ዝላይ ውድድር ተሳትፎ ሻምፒዮን ሆነ። የመልሱንም ግጥሚያ እንዲሁ በተመሳሳይ ውጤት ሀገሩ መዲና ላይ ደገመው። ስለሆነም ከንጉሱ ያሸናፊነቱን ዋንጫ የአሸናፊዎች አሸናፊ በመባል ተቀዳጀ።

በተደጋጋሚ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ይደረጉ በነበሩ የፈረስ ዝላይ ውድድሮች ይካፈሉ የነበሩት የጂቡቲ የፈረንሳይ፣ የጣሊያን፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ ተወላጆች ቢሆኑም መስፍን ክብረወሰኑን ሳያስደፍር ለአምስት ተከታታይ ዓመታት ሻምፒዮን በመሆን ቆይቷል። ወጣቱ ፈረሰኛ በጠቅላላው 230 ውድድሮችን አካሂዶ 120ውን በአንደኝነት፣ 78ቱን በሁለተኝነት፣ 30ውን በሶስተኛነት ሁለቱን ግን በተለያዩ ምክንያቶች ከጨዋታ ውጪ በመሆን አስደናቂ ውጤቶችን ያስመዘገበ ነው። በመሆኑም ከልዩ ሽልማቶች በተጨማሪ 5 የወርቅ ሜዳሊያዎችን 120 ዋንጫዎችንና 108 የፈረሰኛ ሊሽናችን አግኝቶአል

የዚህ ፈረሰኛ መጨረሻው ምን ሆነ? ከርቸሌ ሳለ በወቅቱ የመሀኒ ቤቱ ፖሊስ አዛዥ በነበረው ኮሎኔል ይጠራል። ኮሎኔሉም «ያንተ አድሚ ስምንት ቀን ብቻ ናት ጠብት!» ብሎ ነበር በጊዜው የፎከረበት። ይህን በተናገረ በአምስተኛው ቀኑ አዛዡ ከቀንደኛው ነፍሰ ገዳይ ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ጋር በመመሳጠር የግድያውን እቅድ ዘረጋ። በእቅዱ መሰረትም ከኢህአፓና ከሌሎች የደርግ ተቀናቃኞች ጋር ቀላቅለው ከሁለት ዓመት እስራት በኋላ ሀዳር 21ቀን 1970 ዓ.ም ሌሊት ላይ ረሸኑት።

ስለመሞቱ ግን ለቤተሰቦቹ ምንም አይነት መረጃ ሳይሰጣቸው ቆየ። ስለዚህም ቤተሰቦቹ የልጃቸውን ፍጥሚ ለማወቅ ላይ ታች ሲሉ መገደሉን ተረዱ።

ይኸኔ የህዝብ ደህንነት ኃላፊ ወደነበሩት ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ በመቅረብ ልጁ ምንም አይነት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ያልገባ መሆኑን ገልፀው ሊገደል የቻለበትን ምክንያት ይጠይቃሉ። ኮሎኔሉም ጉዳዩን አጣርተው የደረሱበትን ውጤት ሲገልፁ «ግለሰቦች በግል የፈፀሙት ጉዳይ ስለሆነ በጣም አዝናለሁ፣ ይቅርታም እጠይቃለሁ» በማለት ቤተሰቡን ሸኙት።

t.me/OLDBOOKSPDF



ለፈገግታ

ጆሮዎቹ የተቃጠለ ሰው ለህክምና ወደ ሆስፒታል ሄደ።

ዶክተር፡- ምነው? እንዴት ነው ጆሮህ ሊቃጠለ የቻለው?


ታካሚ፡- ልብስ እየተከስኩኝ ሳለ ስልክ ተደወሰ። መነጋገሪያውን ያነሳሁ መስሎኝ ካውያውን ወደ ጆሮዬ አስጠጋሁት።

ዶክተር፡- ሁለተኛውስ እንዴት ተቃጠለ?

ታካሚ፡- አምቡላንስ ለመጥራት ስደውል።

.....

ባል ቤቱ አላደረም። ጠዋት ወደ ቤት ሲመጣ ሚስት በመናደድ የት እንዳደረ ትጠይቀዋለች። ባልም ያደረው በስራ ምክንያት ጓደኛው ቤት መሆኑን ይነግራታል። ሚስትም ጉዳዩን ለማረጋገጥ ቶሎ ብላ ጓደኛው ቤት ስልክ በመደወል ጓደኛውን «ባለቤቴ አንተጋ ነው ያደረው?» በማለት ጠየቀችው። ጓደኛው ሲመልስም «አዎን እዚህ ነው ያደረው አሁንም እኔ ጋ ነው ያለው» ብሎ መለሰ።



ጉዞ ወደ ተስፋ ምድር

ቶማስ አርጋው

ተራሮችዋ በጉም ተሸፍነውና በጭጋግ ተጀቡነው፣ ወደ ረባዳው የቀይ አፈር ምድር የሚያንቆረቁሩት ዝናብ እየተጠራቀመና እየተጠራራ ተሰባስቦ ጉርፍ እየፈጠረ የከተማዋን ጥጋጥግ፣ ጉድባና ሸለቆ በማሰስ ይነጉዳል።

እኒህ የምድር ክምሮች የብሳናና የዝግባ ብልኳቸውን፣ የዋንዛና የወይራ መገኛዐፈያቸውን ደርበው የደን ነገስታት እንደሆኑ እስከዛሬ ቆይተዋል — ርቃኑን የቀረውን፣ ተመንጥሮ የተጋለጠውን ዙሪያ ገባ መሬት እያስቀኑ!!

ይህን ምድር ያልረገጥነውና ከፊት ለፊታችን የምናየው

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆንም የደቡብ ኢትዮጵያ መዓዛ ግን አያወደን ከሻሸመኔ ክበረ መንግስት ለመግባት በመቃረብ ላይ ነን። አውቶቡሱ ጠመዝምዝውን ጠጠራማ መንገድ በዝግታ እየተጓዘ አቀበት በወጣ ቁጥር ግን ያቃስታል።

ከጉኔ የተቀመጠው ተሳፋሪ አድሚው ወደ ሰላሳዎቹ የሚጠጋ ወጣት ነው። አለባበሱ እንደነገሩ ሲሆን በውጪው የተፈጥሮ ትርኢት አይኑና ሃሳቡ እንደተተከለ ነበር የሚገዘው። አልፎ አልፎ ብንጨዋወትም በየራሳችን ሃሳብ ውስጥ የምንመሰጥበት ጊዜ ይበዛ ነበር።

በመሰረቱ እኔ የምገገበት ጉዳይ አለኝ። ጋዜጠኛ ነኝ። ሙያዬ ከሰው ልጅ ጋር በዕኑ የሚያቆራኝኝ ነው። መነሻም ሆነ መድረሻዬ ሰው እስከሆነ ድረስ ታዲያ ምን ይዘጋኛል?

«ሀገርህ ወደእዚህ አካባቢ ነው ወይስ...» ሳልጨርስ ተውኩት፣ ተመቻችቼ ወደ አርሱ እየዞርኩኝ።

«እዚህ አካባቢ እንኳን አይደለሁም። ግን ተመላልሼበታለሁ»

«ሰጋዬ ነህ?»

«ነግጄ እንኳን አላውቅም። ለሌላ ስራ ነው የምመላለሰው»

«ምን አይነት ስራ? የመንግስት ወይስ...»

«ወርቅ እንሰራለን»

«እንዴት? እንሰራለን ስትል...»

«ወርቅ እንቆፍራለን ማለቴ ነው»

«ከዚህ በፊት ብዙ ሰርተሃል?»

«የአሁኑ ሶስተኛዬ ነው»

«አልቀናህም ማለት ነው?»

«የቀናኝም፣ያልቀናኝም ጊዜ አለ። የወርቅ ስራ ሎተሪ ማለት ነው። በርግጥ ሎተሪ የምታገኘው እጅህን አጣምረህ ተቀምጠህ ነው። በወርቅ ስራ ግን አየሰራህም ቢሆን አድል ያስፈልግሀል።»

«እንዴት?»

«አንዳንዱ ሁለትና ሶስት ዓመት ቆፍሮ የቀለቡን ወጪ ከመሸፈን የማያልፍ አለ። አንዳንዱ ደግሞ አንድ ወር እንኳን ሳይደክም በሺ የሚቆጠር ብር ይዘቃል»

«ገባኝ። አንተስ ይህን ስራ ከጀመርህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?»

«ከሁለት ዓመት በላይ ይሆነኛል»

«አስከዛሬ ታዲያ ምንም አላገኘህም?»

«አግኝቻለሁ። ባለፈው ዓመት ከአንድ ሺ ብር በላይ አግኝቻለሁ። አሁን ደግሞ ወደ ሰምንት መቶ ብር ያህል አግኝቼ ቤተሰቦቼ ዘንድ ደርሼ መመለሴ ነው። ይሄንን በወርቅ ስራ ስርነቀል አይደለም» ብሎ ፈገግ አለ።

«ስርነቀል ስትል ምን ማለትህ ነው?»

«የዚህ አይነቱ አድል ልብስ ለመልበስ ወይም ቤተሰብህን ለመደገፍ ካልሆነ በስተቀር ስርነቀል ለውጥ ሊያስከትል አይችልም። ስርነቀል የሚባለው ደግሞ ወደ ቁፋሮ የማይመልስህ ብዙ ሺ ብር እንድታገኝበት የሚያስችልና ኑሮህን የመለወጥ አቅም ያለው ወርቅ አድልህ ጀባ ሲልህ ነው»

«ያን ያክል የሚያገኙ አሉ ማለት ነው?»

«ሞልተዋል። ግን ምን ዋጋ አለው?! ገንዘቡ መቼ ለስራቡት ይመጣል ብለህ ነው?»

«እንዴት?»

«አስርና አስራ አምስት ሺ ብር አግኝተው አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ይጪፍሩበትና የገቡትን ልብስ ሳይቀር ሸጠው በባዶ እግራቸው ሰቁፋሮ የሚመጡ አሉ»

«ከዚህ በፊት ምን ትሰራ ነበር?»

«ወታደር ነበርኩ»

«የወርቅ ቁፋሮ ስራ አድካሚ ነው ይባላል። ከቀድሞ ስራህ ጋር ስታመሳገዝነው ምን ይመስላል?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለመስረቱ በውትድርና ያላሰፍኩት ሕይወት ከምንጭ
ነገር ጋር ሊነፃፀር አይችልም። ይህ ስራ የጉልበት ስራ
ነው። የፈለገውን ያህል ቢከብድህም ግን ማየት ያለብህ
በነፃነትና በተስፋ ተሞልተህ የምትሰራው ስራ መሆኑን
ነው።»

«በነፃነትና በተስፋ ስትል ምን ማለትህ ነው?»

«በነፃነት ስልህ ስሜትህ ደስ እንዳለውና እስኪደክምህ
ስራህ ስትል ትሰራለህ። ከደከመህ ደግሞ ትተኸው
ታርፋለህ። እንዲህ አድርግ፣ እንዲህ ሁን ብሎ የሚያዝህ
የሚጮህብህ ገላጣጭ የለብህም። ሶስትና አራት እየሆንን
በቡድን ተመካክረን፣ ተዛዝነንና ተፋቅረን ነው
የምንሰራው። የምናገኘውም ውጤት የጋራችን ነው።
በተስፋ ነው ያልከህ ደግሞ ሁልጊዜ ነገን የምታስባት
ዛሬን የምትኖራት መንፈስህ በአዲስ ተስፋ እየታደሰ
እገኛለሁ በሚል ስሜት ተሞልተህ ስለሆነ መንፈስህ
አይዝልም፣ ጉልበትህ አይደክምም ለማለት ነው። በርግጥ
ስራው ከባድ ነው። ሃያና ሰላሳ ሜትር፣ እንዳንዴም ከዚህ
በላይ የምድርን ከርስ መበርበር ቀላል ስራ አይደለም።
ቢሆንም እንዳለፈው ጊዜ በያንዳንዱ ሰከንድ ሞትን
እያሰብኩ አልሰራም። ሁልጊዜ የሚታየኝ ብሩህ ተስፋ
መኖር ነው። ስለዚህ ሞትን እያሰብኩ ቅንጣት የወደፊት
ተስፋ በማይታይባት ጨለማ ሕይወት ውስጥ
የማቀትሁበትን ውትድርና እንዴት ከዚህ ጋ
ልታመዛዝነው ትችላለህ?» 'ድንቅ' አልኩኝ በውስጤ
አገላለፁ ደስ አሰኝኝ።

«ሞኝ አትበለኝና ወረቁን የምታወጡት እንዴት ነው?»

«ለመጀመሪያ ወደታች ጠልቀህ መቆፈር ትጀምራለህ
አድስኛ ከሆንክ በቅርብ ርቀት የወርቅ አፈር ልታገ
ትችላለህ። አንዳንዴ ግን ብዙ ጥልቀት መቆፈር
ይኖርብሃል።»

«የወርቅ አፈር የተለየ ነው?»

«አምን! ብዙ አይነት ቀለም ያላቸው አፈሮች አሉ።
እንግዲህ ተገዝህ ተገዝህ የወርቅ አፈር ላይ ስትደርስ
ወደታች መቆፈርህን ታቆምና ያን የወርቅ አፈር
እየተከተልክ ወደጉን መቆፈር ትጀምራለህ። ታዲያ ያን
የወርቅ አፈር አንድ አፍኝ አንኳን ማባከን የለብህም።
በጥንቃቄ እያፈሰክ በሳፋ ወይም በአንጨት ገበቴ ላይ
አያደረግህ ማጠብ ትጀምራለህ። አፈሩን በውሃ
በምታጥብበት ጊዜ የወርቅ ብናኝዋ ሳትቀር ከገበቴው ስር
ትዘቅጣለች። የመጨረሻዋ ደቃቃ ብናኝም እንኳን ብትሆን
ከውሃ በላይ አትንሳፈፍም። አንዳንዴ ታዲያ መጠኑ ከፍ
ያለ አንኳር ስታገኝ ሳፋውን (ገበቴውን) በምታነቃንቅበት
ወቅት ደቂ የሚል ድምፅ ይሰጥሃል። በዚህ አይነት ሁኔታ
አየመረመርክ ከሳፋው ላይ ትሰትማለህ ማለት ነው»

«ከዚያ በኋላስ? ያገኛችሁትን ወርቅ አጠራቅማችሁ
ትመለሳላችሁ ማለት ነው?»

«አይደለም፤ ወርቅ ይዘን አንወጣም። ወርቅ ይዞ
መውጣት ክልክል ነው»

«እናስ?»

«መንግስት በሕጋዊ መንገድ ይገዛናል»

«ለሕጋዊ መንገድ ስትል እንዴት?»

«ያ መንግስት ራሱ ደክሮልሃል»

ተከፋፍሎ እንጀለ ይሰላል። የወላይታ ልጅ ነው። እንዲህ
አየተጨዋወትን ከብረ መንግስት ገባን።

ከብረመንግስት እንደስማ ያማረችና የደመቀች ከተማ
አያደለችም። የቤቶቹ ቆርቆሮ ጣሪያዎች ጠቁረውና
የገድግዳዎቹ የቀይ አፈር ምርጊት ተሸንቁሮ ሲታይ
አርጅና የጠናባት ከተማ መሆኗ ያስታውታል።

ከብረ መንግስት ተስፋን በልባቸው አርግዘው በምጭት

t.me/OLDBOOKSPDF

እየማለሉ ወደ ደብብ! ተስፋቸው አውን ሆኖና ምኞታቸው
ተሳክቶ በደስታ እየዘለሉ ወደ ሰሜን የሚተላለፉትን
ወጪና ገቢ ፍጡራን ሳትታክት ማስተናገድ ቋሚ ስራዋ
ነው።

አሁን ከቀኑ አስር ሰዓት ሆኖአል። ከአውቶቡሱ
የወረዱት አብዛኞቹ ተሳፋሪዎች እየተቻኮሉ ወደ ትናንሽ
አይሱዚዎችና ላንድሮቨሮች ይጋላሉ። ፋታ የላቸውም።
ወደ ተስፋ ምድር ይነዳሉ። ከሚመለሱት ጋርም
ይተላለፋሉ። ከተመላሾቹ አብዛኞቹ ፊታቸው ሁሉ ጥርስ
የሆነና የሚስቁና የሚቦርቁ ናቸው። ጥቂቶቹ ብቻ
ፊታቸው እንደጨፈገገ ጓደኞቻቸውን እየተከተሉ
ያዝንማሉ።

ከሁኔታቸው እንደሚታየው የተስፋ ምድር ፊት
የነሳቻቸው ይመስላሉ። ተስፋዬ እንጀሱን ብማትር ሳገኘው
አልቻልኩም። ተንጠላጥሎ ነጉዷል። እኔም ወዲያው
ተሳፈርሁ።

ያ ጥቅጥቅ ብሎ ይታይ የነበረው ደን እንደ አባ
የምታሽሎከሎከውን ቀጭን የመኪና መንገድ ግራና ቀ
አስጨንቆ ሲውጥ እንደተዘጋጀ አውሬ አሰፈራ ግርማ
ሞገሱን በሰው ላይ እየጫነና የውበት ድባቡን እያደበ
እንዳንዴ መንፈስን ያስጨንቃል። የፊት ለፊቴን ባሳጡኝ
አስክ አሁን ሳዱላ ከምታካክል የግጦሽ ቦታና ከእህል ማ
በስተቀር ባድማ መሬት አምብዛም አላየሁም።

በሃራችን ላይ የገዛ ሀገሩን ለመገበኘት፣ የራሱን ምድ
ለመቃኘት አቅምና እድሉ ላልገጠመው የሀገር ልጅ ይህ
ውበትና እውነታ ለማስተዋወቅ መሞከሩ ምንኛ መሰላች
የብአር ጉልበት የሚጠይቀው!?

የተስፋ ምድር መዳረሻ የሆነችውን ትንሿን ቆሬና
ከተማ እየተቃረብኩ ነው። ይህች የቀይ አፈር ምድ
የሞዛ እንዳትመስልሞ። ምናልባትም በማያውቁት ዘመ

ወቅት፣ በማይጠረጥሩት ቀንና ሰዓት በአንድ አጋጣሚ
የዚያ አፈር ባለሙቦት፣ የዚያ ምድር ባለቤት በመሆንም
ብናኝም ብትሆን ከዚያች አፈር የድርሻዎን ሳያገኙ
አልቀሩም። አሊያም ግን ሲመዘበርና ሲመነተፍ
በማንበብም ወይም በመሰማትም ቅሽትም ተቃጥሎ
ይሆናል።

ከመግቢያ በሯ ላይ እያስገመገመ ዙሪያ ገባዋን አጥቦ
የሚወርደውን ወንዝ ተሻግሬ አፈሯን ረገጥኩ። በቃ!
ወደምልምት መዳረሻ ከተማ ገባሁ። በክልል አራት ሲዳሞ
ክፍለ ሀገር ትገኘሰች - ሻኪሶ! ቢያንስ ስሟን ያውቃሉ
ብዬ እገምታለሁ። ከእኔ ጋር ከቆዩ ደግሞ ይበልጥ
አስተዋውቅዎታለሁ።

ምሽት ላይ ነው። ምሽት ደግሞ ማረፊያን
ያስታውሳል። ከከተማዋ ጥበት ጋር እያነባበሩ
የሚተራመሰውን ወጪ ወራጅ ሲያስተውሉት ይህ ሁሉ
ጉድ የት ገብቶ ያድር ይሆን ያሰኛል። ደግኑቱ ሻኪሶ
የሚስነበት አንግዳ የለባትም። አብዛኛው ወጪና ገቢ
መንገደኛ ነው። እነዚህን ወጪና ገቢ እንግዶች
ለማስተናገድ ሻኪሶ መጨነቅ መጠበብ ጀምራለች። አንኖን
ተስፋ አላሚዎች ሰበረንዳ ውርጭና ለሌት ቁር አጋልጣ
ላለመስጠት ትጨነቃለች።

እንግዶቿን የምታስተናግድባቸው ሰፋፊ የጅባና የስሌን
ምንጣፎች የተዘረጉባቸው ወና ቤቶች ሞልተዋል። አንሰላ
አልብሰኝ፣ ብርድልብስ ደርቡልኝ ብሰሙ ነገር የለም። በአንድ
ብር ይሀን የሚመኝስ የቱ ቂል ነው? ነገ አንደሁ ሁሉም
የወርቅ አዝብስ ወደሚናፍቅበት ወደ ሞነኛው የተስፋ
ምድር ይጓዛል።

አዚያች የሰለን አዳራሽ ውስጥ ጥቅጥቅ ብለው ታጉረው
ጉናቸውን ሲያሳርፉ ታዲያ አያወሩም፣ ጫጫታም የለም።
ለነገሩ ማን ማንን አውቆ ያወራል? አልፎ አልፎ ከአንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንደር ክፈለሱትና ቀያም ሲል በስራ ቦታ ከሚተዋወቁት በስተቀር አብዛኛዎቹ አይተዋወቁም። የሚገርመው ግን እንደ እናት ልጅ ሰግስግ ብለው ተቃቅፈው በፀጥታ መተኛታቸው ነው። ችግር በቅቤ ያስበላ የለ? ወይስ ወርቅ በተስፋ ያስተኛል እንበል?

ሌላው ያስደነቀኝ የብሄር፣ ብሂረሰቦቹ ጥንቅር ነው። ኮንሶ፣ ኮይራ፣ ቡርጂ፣ ቦረና፣ ገሬ፣ ጉራጌ፣ ትግሬ፣ ከምባታ፣ አማራ፣ ሃዲያ፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ... እነዚህን ሁሉና ከዚያም በላይ የሆኑትን ውሁድ አድርጋ፣ ተስፋ በወል አዋሀዳ፣ አስተቃቅፋና አዛምዳ በአንድነትና በፍቅር አስተኝታቸዋለች።

ሁሉም የሰማውን ሳይቀር (ቡኮሰይ ጀማሪው) ማለም፣ መቃኘት፣ ማሰብ፣ ማውጠንጠን፣ ማውጣትና ማውረድ ይጀምራል። መላኤ እድሉን በባዶው የሃሳብ አለም መገንባትና ማፍረስ የዚያች ሌሊት አቢይ ሀልም ነው። ሁሉም ስለዚያች የተስፋ ምድር ሪጭ ባለው ሌሊት በዝምታ ተውጦ ያውጠነጥናል። አይኖቻቸው ተከድነው ዓይነ ሕሊና ቦው ይበረገድና ካደጉበት መንደር ተነስተው የኢትዮጵያን ሽለቆና ተራራዎች፣ ወንዞችና ጅረቶች፣ እድባራትና መንደሮች በሃሳብ እየዞሩ በምናብ መነፅራቸው ቀጥታ ወደ ተስፋ ምድር ይዘልቃሉ። የተስፋ ዜማ፣ የተስፋ ዋሽንት እያዳመጡ።

መልሰው ደግሞ ፀሎትና መማፀን ይጀምራሉ። የገረጀፉበትን የድህነት ዘመን እያሰቡ፣ የጓዳቸውን ጥቁር ገመና፣ የአድላቸውን ሽፋኝ ደመና እንዲገፍላቸው በዚያች ሌሊት ለፈጣሪያቸው ሱባኤ ይገባሉ። እንደ ቁጥራቸው በበዛ ቋንቋ።

ያቺ ምድር ላባቸውን መጥጣ የመዳፋቸውን ቆዳ ልጣና ፈግፍጋ ከበላች በኋላ እንደ አድለቢሶቹ ያለ አንዳች ተስፋና ውለታ፣ ያለምንም ወሮታና ስጦታ አክ! እንትፍ! ብላ


ተፍታ ወደነበሩበት ጐስቋላ ኑሮ እንዳትወረውራቸው በውስጣቸው አያለቀሱ ይማፀናሉ።

እናም በዚህ መውጫና መግቢያ፣ መነሻና መድረሻ በሌለው የሃሳብ ደን ውስጥ ሲፍገመገሙ ማሸለብ ይመጣል። ሕሊና የማያርፍበት ሽልብታ።

አዎን፣ ወደዚያች ምድር ፊቱን ያቀናን፣ ደማና አካሉ ተሸክሞ መንፈሱን የመራን ፍጡር ሁሉ ተስፋ እንደዚህ ይሰራዋል። ተስፋ እንደዚህ ያደርገዋል! «ተስፋ የሌለው ሰው ዘሙት ይቆጠራል» ይሉን አልነበር አንድ የህገራችን ደራሲ? እውነት አላቸው። ተስፋ ሕይወት ነው።

የጉዞ ማስታወሻ

t.me/OLDBOOKSPDF



ወጣትነትና እርጅና



የጉቴ ቢቅ

ኤፍሬም አንዳለ

ሲጋራ አያያዙ ለብቻ ነው። ማለቴ አለ አይደል... ቴንጠኛ አንደማን ልበልሎት... አንደ ጀምስ ቦንድ። ሲጋራውን ማግ አድርጐ ጭሱን ቡልቅ ሲያደርገው በአጓጓስ ውድድር አሸንፎ «ሊሮ የኛ ልጅ» ተብሎ የተጨበጨበለት ይመስላል።

«አና...» ይልምታ·ል ወጉን ሲጠርት። «በራዘራ ዋሽንግተን ትልቅ ሠቴል አለው።»

«አውነት!» ይላሉ የተገረሙ መስለው። «ለመሆኑ የተማረ ነው?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታሸፋለህ!» ይልዎትና አንደ ከሰል ባቡር ሁለቴ ጭስ ቡልቅ ቡልቅ አድርጉ ጉራ ንስኳውን ይቀጥላል «ሁለት ዶክትሬት አለው። ኒው ዮርክ ካለው የታወቀ ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ በዲስቲንክሽን ነው ግራጁኤት ያደረገው።»

«ሕህ... ነው!» ብለው በረጅሙ ይተነፍሳሉ። ሰውየውስ (ባለ «ትልቅ» ሆቴል ቤቱ) አንኳንስ ሁለት ሥራ ሁለት ዲግሪ ይኑረው። ብቻ የሚከነክንዎት ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ከእንግሊዝ ወደ ኒውዮርክ የመጣበት ተአምር ነው።

ዘንድሮ እኮ የማይሆን ነገር የለም!!

ግን ብቻ የሰውዬው ጉራ። 'እፋጠው፣ አፋጠው' ይልዎታል።

«ለመሆኑ» ይላሉ በኅዘን ፉት ካሉ በኋላ «ለመሆኑ ሴሎች ወንድሞችና እህቶች አሉህ?» ይሉታል፣ እንደ ጨዋታ እያስመሰሉ። እንግዲህ መመክር ደግም አይደል!

«አፍረርስ» ይላል እጆቹን እንዳሞራ ክንፍ እየዘረጋጋ። «ሴሎች ሁለት ወንድሞች አሉኝ። አንደኛው ስዊድን ውስጥ የታወቀ ዶክተር ነው። ሴላው ፓይለት ነው»

እሱ ጉራውን ሲተረትር የአርሶ ሀሳብ ምድር ሰቅ ይሄዳል። «እንዲያው ለመሆኑ» ይላሉ በሆድዎ። የሰው ወንድም በሙሉ ፓይለትና ዶክተር ከሆነ በየሴላው ሥራ ያሰው ቪህ በቪህ ሰው የማን ወንድም ሲሆን ነው! ሰውየው ቀጥሏል። «እህቱ ሆስቴስ ነች...»

ይሄ ሰውዬ ቀስ ብሎ «አየር መንገዱም የኛ ነው እንዳይለኝ» ብለው ይሊጋሉ – በሆድዎ።

እኔ እንኳን ስለ ሰው ባህርይ የማውቀው እምብዛም ነው። ብቻ ደሞዝ ከተለመደው አንድ ቀን ቢዘል ጭምቱ ሁሉ ቀንድ ሲያበቅል አያለሁ። ሰለ ደግሞ እንትኑን ስለ ጉሪምሳ እባብሎ የነጠቀበት ጉብል ሉበቻው ሶስተኛ ዓለም ጦርነ ሊያስነሳ ሲሞክር አያለሁ። መቼም ጨዋታን ጨዋታ ያሰኛዋልና ብዬ ነው እንጂ እንዲያው የመነጣጠቂያን ነገ

ተከድኖ ይጠሰል ማለት ነው። የሚገርም ትውልድ ነው። ወንዱም የሰው ቀንጅ መጐተት... የሰውም ቀንጅ ብትሆን በሽወዳ ቢጐትታት እየተሽከረመመች መሄዱል... አይገርምም። መስረቅ... መሰረቅ... መሰራረቅ የሚወድ ትውልድ አይገርማችሁም?

ከናንተ መጨዋወት የፈለግሁት ስለጉረኞች ነበር። ነገር ነገርን አየገሙተ አጉል ርዕስ ውስጥ ዶለኝ አንጂ። እና ይኸውላችሁ ጉራ መዝፍት የሚወዱ ሰዎች ሲዋሹ (የአራዳው ልጅ «ሲረግጡ» እንደሚለው) ቅንጣት ታህል አፍረት የላቸውም።


ስለ መጽሐፍ ከተነሳ ከነሱ በላይ የመጽሐፍ ወዳጅ አግር አስዚኔታ ቢሔድ አይገኝም። «ጆን ዊይን የጻፈውን መጽሐፍ አንብበህል?» ብለው ቢጠይቁት «ያውም ገና እንደታተመ» ይልዎታል። ጉድ! ጉድ!..' ብለው አፍዎን በእጅዎ ግጥም አድርገው ጭጭ ነው። «እረ አባክህን ጀን ዊይን እኮ የፊልም ተዋናይ ነው በሉና እሱቲ ሞክሩት' «ኦ... እኔ እኮ ስለ ደራሲው ጀን ዊይን የምታወራ መስሎኝ ነው» ይልዎታል። 'መሸነፍ የምትባል ቃል መዝገበ ቃላታቸው ውስጥ የለም።

ጥንት ጥንት አውሮፕላን በሰማይ ሲበር «አገሬ እንዳያምኑ!» እያሉ 'መደነቂያ' የሚፈልጉ ነበሩ። ዘንድሮ ዘዴው ተሰወጠ እንጂ ጉራ እንደሁ በሽ በሽ ነው – በነፃ። ኢያምጣው ነው እንጂ አንዳንዴ ኑሰግይ ስባሪ የሚያህለው ሰው አንደ አሥራ አምስት ዓመት ሰብ ሰብ ጉረምሳ ጉራውን ሲተረትር ይገጥምዎታል። እና እሺ ይሂን ምን ይሉታል? ጉረኛ ነዋ!


ምን የሚመስለኝ ይመስልዎታል? የአንዳንዶቻችን አንምሮ ጉራ በማመንጨት ችሎታው የሚሰተካከለው ያለ አይመስለኝም። የሳይንስ ሊቅ ባይኖረንም «ዮጉራ ሊቅ» ሞልቶናል።

መጣጥፍ

t.me/OLDBOOKSPDF



ትርፍ



በኪሳራ ማግስት



ስዚዛ

ሞሐመድ ኢል - ቢሳቴ
(ትርጉም) ኤፍሬም ተሰማ

ወደ ሥፍራው ስትመጣ ለሁለተኛ ጊዜ ነበር። ፖሊሱ ፈረሱ ላይ እንደተቀመጠ ቁልቁል አፈጠጠባት።

ጊዜው ከቀትር በኋላ ነበር። ቢጫ ቀለም የተቀባው የግምብ አጥር ከአውራ ጎዳናው ትይዩ ተንጣሏል። ግቢው ውስጥ ሦስት ፎቆች ያሉት ባለ አራት ማዕዘን ህንፃ ይገኛል። ተመላላይነት ያላቸው ትንንሾቹ መስኮቶች ከመስኮትነት ይልቅ ብርሃን ማስተላለፊያ ቀዳዳ ይመስላሉ። ሲትዮዋ ከፈረሱ ጥቂት እርምጃዎች አለፍ ብላ ቆማለች። ፖሊሱ ወደ ኋላው በመገላመጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደመስኮቱ፣ ከዚያም ወደሲትዮዋ ተመለከተ። ወዲያው ሁለት እጆቹን ከኮርቻው የፊት መደገፊያ ላይ አሳረፈና አይኖቹን ጨፈናቸው። ፈረሱ ከነበረበት እንደመንቀሳቀስ አለ። ቀደም ብሎ የቆመው ከአውራ ጐዳናው መሃል ነበር። ከጥቂት ቆይታ በኋላ በከፊል ዞር በማለት ተንቀሳቅሶ ከመንገድ የመጨረሻ ዳርቻ ሲደርስ እንደገና ቆመ።

ሴትዮዋ ወደፊት ሁለት እርምጃ ተራመደች። ፈረሱ ከፊት እግሮቹ አንዱን አጠፈ፣ ወዲያው ደግሞ በዝግታ ከነበረበት መልሶ አሳረፈ።

«የሃምሳ አለቃ! እባክህ ሁለት ቃላት ብቻ ላናግረው።» አይኖቹ እንደተጨፈኑ ቀርተዋል። እጆቹም ከኮርቻው መደገፊያ ላይ እንደነበሩ አልተንቀሳቀሱም።

ግንቡ ከላይ በኩል ዳር እስከ ዳር በሽቦ የታጠረ ሲሆን በስተመጨረሻው ከእንጨት የተሰራ የዘብ መጠበቂያ ማማ ነበረው። ከማማው ውስጥ አንድ የታጠቀ ወታደር ቆሟል።

ሴትዮዋ እንደገና ወደፊት ራመድ አሉች።

«ምን መሰለህ - ከዚህ ተዛውሯል...»

ፀሐይዋ የሰማዩን እኩሌታ በመሻገር አቀልቁሰሰች። ይህም ሆኖ አካባቢው ገና ይሞቅ ነበር። ቨጣጣ ቅርፅ ያለው የጥላ ክፋይ ከግንቡ የውሃ ልክ በመታከክ ረቧል።

ሴትዮዋ ሀሳቡን ወደ ትክሻዋ አዛወረችው። የፖሊሱን ፊት በድጋሚ ፋና ብላ ስታይ ግባሩ ላይ ሳብ የወረደበት ቀጭን መስመር ተመለከተች።

ከፈረሱ ፊት በፀጥታ እየራቀች የግንቡን ጥግ ይዛ ተራመደች። ከግንቡ አጋማሽ ላይ ስትደርስ ከሀንባው ትይዩ ከሚገኝ የታኮስኮስ ድንጋይ ላይ አረፍ አሰች።

አስረኞቹ አጥበው በእድገና በግርጌ የሰሯቸውን

ልብሶች መስኮቱ ላይ ከተሰደረው ቋሚ ብረት ዘልቀ ለመመልከት አዳጋች አልነበረም። አልር አልር ነፋስ የሚነፍስ ቢሆንም ልብሶቹ አብዛኞውን የማይወዛወዙበት ጊዜ ይበልጣል።

ሲትዮዋ ለራሷ አንሾካሾከች፣

«እርጥብ መሆን አለባቸው!»

ሀሳቡን ከጭኗ ላይ አሳረፈችው። ዐይኖቿ ነፋሱ በቀስታ ከሚያወዛውዘው አንድ ጀለቢያ ላይ ለአፍታ ተተከሉ። እግሯን ወደፊት ዘርግታ ጣቶቿንና በላያቸው ላይ ተመርጉ የደረቀውን ጭቃ ተመለከተች። እግሮቿን እርስ በእርስ አፋትጋ ስታበቃ በድጋሚ ተመለከተቻቸው።

አራሷን ወደኋላ አዘንብላ አይኖቿን ገርበብ በማድረግ ከሀንባው ሦስተኛ ፎቅ ላይ የሚገኘውን መስኮት ተመለከተችው። በማማው ውስጥ የቆመው ወታደር አንድ እርምጃ ወደፊቱ ተራመደ። ከዚያም ጭንቀላቱን ከእንጨት አጥሩ ጫፍ ላይ አስደገፈው ወደ ሰማዩ፣ ወደ ቢቱቹ ጣሪያዎች፣ ወደ አውራ ጐዳናው ከዚያም ወደ ቆመው ነጭ ፈረስ ተመለከተ።

በድንገት አንድ ጨኽት ፀጥታውን አደፈረሰው። ሴትዮዋ ፈጥና እግሯን ሰበሰበች። ከሦስተኛው ፎቅ መስኮት ከሁለት ቋሚ የብረት ተራዳዎች መሀከል አንድ እርቃን ከንድ ሲወናጨፍ በአይታዋ ውስጥ ገባ።

«አዚዛ! አዚዛ! አሸር ነኝ»

አንድ እረምጃ ወደ ግንቡ ተጠግታ በፀጥታ መስኮቱ ላይ አፈጠጠች።

«አሸር ነኝ - አዚዛ! አሸር።»

ሌላኛው ከንዱ በመስኮቱ ሾልኮ ወደውጭ ሲዘረጋ አየች። በተዘረጉት ሁለት ከንዶች መሀከል አንድ ነገር ለይቶ ለማየት አይኖቿ ተንከራተቱ። እናም መስኮቱን ወደውጭ የሚገፋ አንድ ፊት ቀስ በቀስ ተከሰተላት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዘላያና፣ ከጐኑ ሴሎች ፈጥተም ያታዩ ነበር።

«አዘጣ ተሳውፈአለሁ። ደብዛዜ ደረሰሽ በአራት ቀናት ውስጥ ከዚህ አሳወራለሁ። ሁሉን የሰውነ ዛርች አሰቀነጠሻቸው ወደ ሀግድና ሳኒ የት አሱ አምነ ያሸሻቸው አልመሳሰሎ ተሳውፈአለሁ። ሠሚድ የት አለሽ»

በድንገት ወደ ኋላው ዞር አምባረቱ፣

«እሰኪ, አረፋ፣ ሰያጣኖት»

ሲሎሁ ከመሰከተ ሳይ የነበሩት ፈቶች መሳያው ተሰወሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፈቱ በድጋሚ በመሰከተ ሲያዶልት ሲሎቹ ፈቶች ከዘላይ ሆነው ወደ ውጪ, ያመለከተ ጀመረ።

«ከዚያ»

ፈረሱ ሳይ ወደ ተቀመጠውና ሚግው ውስጥ መሳው ወዮደር በዞተራ ተመለከተች።

«ማነው አንተ የያዝሽኝ? ሽለርገ አዘሃ» ሚንትሳቲን ሁለቱ አመጠች።

«መደላይ አንሽው፣ መደላይ ከኖ አርገሽ አንሽው።»

ሀጉን በእያሂ መሀል ያሳ ከአራሳ በሳይ አንሳችው። ከንዶቹ ወደ ውስጥ በፍጥነት ተመልሰው አያቹ የመከፋቱን ቋሚ ብረቶች አጥብቀው ሰይዙ ተመለከተች። ወሳያውኑ ፈቱ ከእያታ ተሰወረ። ቁልቁል ከሚመለከቱት ፈቶች መካከል የሱን ለመለየት ለአንድ አፍታ ታጠች። ከንዶቿን በመጠኑ ወደታች ከታወርድ ከመሰከቱ ሳቅና ሁካታ ሰማች። ከንሱ በድጋሚ አንዴ ወደው፡ሮ ሰዘረጋ ለየችው። ቀጥሎ ፈቱ መሀል ለመሀል ፍጥትው ብሎ ታየ።

«ከፍ! አዘጣ ከፍ አርጊው። በቅው እንዲታየኝ ፈቱን ወደ ዐሐይዋ ዘወር አርጊልኝ።» ከንሯን ለአፍታ ወደ ታች አንደማውረድ ብላ መልሳ ወደ ሳይ ከፍ

በማድረግ ፈቱን ወደ ዐሐይዋ አዙሪ ያዟችው። ፈትሳው አያዋቹን ፈፈንና ለቅሰውን ለቀቀው።

«አያሰቀሰ ነው»

አየሳቱ ወደኋላው ዞረ።

«ልዘ አያሰቀሰ ነው ፈትሳው አንዱን አዘጣ ሰጥዋ አስለቅሽው»

እጀዋን በአፉ ዙሪያ ዝዘዘ አደረጉ ጮኸ።

«ያልቅበ ተያው»

አንደገና ሳቁን ለቀቀው። ጥቂት ደምጾች ከአርሱ አካባቢ, ጉሳ ብለው ያሰሙ ዝዘር። ፈሽኮቹውና ሁካቸው ለአርዓያ ያሰማታል። ከዚያም በቋማዎቹ ብረቶች መሀል ትልቁ አናጋጩው ብቅ ብሎ ታያት።

«ሲትየ፣ አትዘዘኩ በቃሽ ሀጉን ሽፍኒ - ምች ታሳመችዋለሽ»

ሀጉን ወደ ደረቷ አሰጠጉኑ አያቀፈች ሚግው ውስጥ በመግባት ሳይ የነበረውን ወዮደር አየት አደረጉው።

«ሁሉን የሰውነ ዛርች አሰቀነጠሻቸው ወዮ?»

ሚንትሳቲን ንቀነቀች።

«እኮ ለምን? አትሳዛሪም እንዲ ከዚህ እያሳውሩኝ ነው። በአሁ አሰማኤል ደጀ ሰታልፈ የአከብሮት ሰላምታዮን አትርቢልት። ውሰኑ እንዲሆነው ሰመዙን ይቀንየብልሻል። አትመጪ, ዋቂት ለውነ ይዘሽ መምጣት ትችያለሽ። ሲጋራውን አመጣሽልኝ?»

በእጇ ምልክት ሰጠችው።

«ተናገሪ እንጂ፣ ምን አልሽኝ?»

«ይደርሳሳል።»

«ሲትየ፣ ድምፅሽን ከኖ አርጊ።»

«ያደርሰሳል። ልኬልሀለሁ።»

«መቼ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን!»

«አሁን? ቆይኝ፣ እንዳተንቀሰቀሺ!»

በቅፅበት ተሰወረ። መስኮቱ ላይ ሁለት ፊቶች ብቻ ቀርተዋል። ከሁለቱ አንደኛው ከንዱን ወደ ውጭ ዘርግቶ እጆቹን በብልግና ያንቀሳቅሳቸዋል። አይኖቿን ወደታች ሰብራ ወደተኮለኮለው ድንጋይ በድጋሚ አመራች።

«አዚዛ!»

ድምፁ የማን መሆኑን ባትለየውም ቀና ብላ ወደመስኮቱ አየች። ሰውየው ፈገግታ በማሳየት እጆቹን እንደቀድሞው እያንቀሳቀሰ ነበር። ሁለተኛው ሰውዬ ተንበርክኮ ጀለቢያውን ከጭኑ በላይ ገልቦታል። ጥሪው ዘልቆ ይሰማታል።

«አዚዛ! ተመልከች!»

ፈገግ አለች። ፖሊሱ የሚያንቀሳፋ ቢመስልም ፈረሱ ላይ ተሰተካክሎ ተቀምጦ ነበር። የወታደሩ ጭንቅላት ከጉን በኩል ባለው የማማው መስኮት በከፊል ይታያል።

ብዙ ድምጾች ባንዴ ሲጠሯት ይሰማታል። በተከፈተው መስኮት ውስጥ በሚንቀሳቀሰው የወታደሩ ጭንቅላት ላይ አይታዋን አሳርፋ በንቃት ታዳምጣለች። ጥሪያቸው ተደጋጋሚና ብልግናም የተቀላቀለበት ነበር። ወታደሩ ብረት ቆቡን ቢደፋም ከመጠበቂያ ማማው አልወጣም።

ወዲያው ጫጫታቸው እረጭ አለና ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ባሷ ትንፋሹ እየተቆራረጠ ጥሪው ከጆሮዋ ደረሰ።

«አዚዛ! አምስት ነበር ያልኩት - አምስት ፓኬት እንደምፈልግ አልነገርኩሽም?» ፀጥ እንዳሰች ቀና ብላ አፈጠጠችበት።

«ሴትዮ! ሦስት ፓኬት ምን ይሠራል?» በእጇ ምልክት አሳየችው

«ምን እያልሽ ነው?»

«አምስት - አምስት ልኬልሃለሁ»

«አምስት?» በንዴት አምባረቀ። «ሰይጣኖች!»

ወዲያው ጠፋና ጥቂት ቆይቶ እንደገና እየጮኸ ብቅ አለ።

«ቆይ! እንዳትሄጂ!» ፊቷን ወደ ማማው መስኮት መለሰች። ለጥቂት ጊዜ አልነበረም፤ አሁን ግን ተመልሷል።

«ይሁን - አዚዛ። ምንም አይደል! አምስት - ልክ ነው፤ አምስት ነበር። ምንም አይደል፤ ሁለቱን ወስደውታል። ይሁን። ስሚኝ ... ምን ልልሽ ነበር?» ፀጥ አለ።

በመስኮት ወደ ውጭ በፀጥታ አፍጥጦ ሲመለከት አየችው። ጥቁር መጐናፀፊያዋን አራገፈችና ወደ ግንቡ ፊት ለፊት ተራመደች። ፈገግ አለ።

«አዚዛ! አንድ ነገር ልልሽ አስቤ ነበር።»

ራሷን ዞር ስታደርግ ከፊል ገጿን የፀሐይ ጨረር እረፈበት። የራስ መጐናፀፊያዋን በመጠኑ ሳብ አድርጋ ፀሐይዋን ተከላከለች።

«ሁለቱን ፓኮዎች ወስደዋቸዋል። ምንም አይደል - አዚዛ፣ ተይው!»

ሳቀ። ድምፁ እየተረጋጋ ነበር። ከበላዩ የነበሩት ሌሎቹ ፊቶች ሁሉ ጠፍተው አንዱ ብቻ ከጉን በኩል ይታይ ነበር።

«ግንቡን አስገነባሽው እንዴ?»

«ገና ነው።»

«ለምን?»

«አጐት አህመድ የማንደጃውን ሥራ ሲጀምር ጥቂት የሸክላ ጡቦች ይሰጠኛል ብዬ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ይሁን! መኪናው ላይ ስትወጪ ተጠንቀቂ። ህፃኑን በደንብ ያሻርው!!» በነበረችበት ቆማ ቀረች።

«የምትፈልጊው ነገር አለ?»

«የለም።»

ፊቱን ትኩር ብላ አየችው - ትልቅ አፍንጫውን፣ እርቃን ከንዶቹን። ፈገግ አለች። ከጐኑ ያለው ፊት በአዕፋው ፈገግ አለ። ወዲያው አንባረቀ።

«ደብዳቤዬ ደረሰሻል? ከዚህ ሊያዛውሩኝ ነው!!»

«ወደየት?»

«አላወቅኩም።»

«መቼ? »

«ይታይሻል! እሥር ቤቱን እያፈረሱት ነው።»

«ወዴት ነው የሚወስዱህ?»

«እግዜር ይወቅ - የትም ሊሆን ይችላል። ማንም ለያውቅም።»

«መቼ?»

«በሁለት ወይ በሶስት ቀናት። ዳግመኛ እዚህ አትምጭ። የምዛወርበትን ጊዜ እኔ አልከብሻለሁ። ህፃኑን እንቅልፍ ወሰደው እንዴ?»

«አይ። ነቅቷል።»

ዝም ብሎ ለጥቂት ጊዜ ወደእሷ አፈጠጠ።

«እዚዛ!»

እንደገና ፀጥታ ሰፈነ። ከጐኑ የነበረው ፊት ፈገ አለ። ከዚያም በዝግታ ወደኋላ ሸተት ብሎ ተሰወረ ባለቤትዋ ቀዋሚ ብረቶቹን በከንዶቹ መሀል እንደ ፀጥ ብሎ ቀረ።

ወዲያውኑ ወደኋላ ተገላምጦ በፍጥነት ከንደቹ ወደ ውስጥ መለሳቸው። እንድትሄድ ምልክት አሳይቷ ከመሰኮቱ ኋላ ተሰወረ።

ወደኋላ እንደማፈግፈግ ብላ መልሳ እንደቀድሞ

በመቆም አንጋጣ ወደ መስኮቱ ተመለከተች።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ እግሮቿን ዘርግታ ከተኮለኮለው ድንጋይ ላይ ተቀመጠች። ከዚያም ጡቷን አውጥታ ህፃኑን አጠባችው።

ጥላው አውራ ጐዳናውን አቋርጦ ነጐዷል። የመጨረሻው ክፍል እግሯ ላይ አርፎ እንደነበር አስተዋለች። እግሯን በቀስታ ሰብሰብ አደረገች። አካባቢው ፀጥ ብሏል። የተሰቀሉት ልብሶች በነፋሱ ኃይል በዝግታ ይንቀሳቀሳሉ።

በድጋሚ እግሯን ስትመለከት ጣቶቿን የጥላው የመጨረሻ ጠርዝ አልብሷቸዋል። ተነስታ ቆመች።

ወታደሩ አሁንም ከማማው ውስጥ አልወጣም። የቦት ጫማው ፊት ከእንጨት የተሰራውን ወለል ጫፍ አልፎ ይታያል። ፈረሱ ቆሞ ከነበረበት ሥፍራ ከመድረሷ አስቀድሞ ወደኋላዋ ተገላመጠች። መስኮቱ ግን ኦና ሆኖ ነበር።

ፖሊሱን በዝምታ አየችው። አይናቹ ተከድነው እጆቹ ከኮርቻው የፊት መደገፊያ ላይ አርፈዋል። ፈረሱ ከነበረበት ላይንቀሳቀስ ተገትሯል።

በጠባቡ መተላለፊያ ቁልቁል ወደ አውራ ጐዳናው ነጐደች።

አዚዛ!

ልቦለድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለፈገግታ

ሚስት ስባልዋ፦ «...በመ/ቤታችን ሲወራ እንደሰማሁት በቅርቡ ቦሚሙጣ መመሪያ መሰረት 10ልጆች ላሉዋቸው ወኒጆች ብዙ ክፍሎች ያሉት አዳዲስ ቤቶች ይሰጣል ይባላል። የወለድከውን ዲቃላ ልጅ ብታመጣው አስር ይሞሉልኝ አድሱን እናገኛለን» ትሰዋለች።

ባልም በነገሩ ተስማምቶ የወለደው ዲቃላ ልጁን ለማምጣት ይሄዳል። ከሁለት ቀን በኋላ ባል ልጁን ይዞ ሲመጣ ሚስት ለብቻዋ ቤት ውስጥ ቁጭ ብላለች ባል ግራ በመጋባት «ልጆቹስ?» ቦማለት ቢጠይቃት

ሚስት፦ «ትናንት የሁለም አባቶች መጥተው የየራሳቸውን ልጆች ይዘው ሄዱ» ብላ መለሰችለት።

.....

- ዳኛ «ምስክር! አድሜዎ ስንት እንደሆነ ሊነግሩን ይችላሉ?»

ምስክር፦ «ከባሌ ጋር ስንጋባ እድሜዬ 20 ነበር፤ የቤቱ ደግሞ 40፤ ማለትም የኔ እድሜ የሱን ግማሽ ነበር ማለት ነው አሁን እሱ ሰባ አመቱ ነው። እንግዴህ አሁን ቤቱ እድሜ 35 መሆኑ ነዋ!»



አሸቱ ተፈራ

ግጥም ውላ ጠጣ

ችግር ያጠቃቸው አንድ መምህራችን
ሰኞ ቀን ማለዳ ገብተው ክክፍላችን፣
..ስለችግር ጻፉ አስር መስመር ግጥም
..ስሜት የሚነካ ለጆሮ የሚጥም..
ብለው አዘዙና ክፍሉን በድምሩ
ወንበር ላይ ተቀምጠው መተከዝ ጀመሩ።
በሀሳብ ተውጠው መንኖ አሳባቸው
በግልጽ ይታይ ነበር ግራ እንደገባቸው።
በርእሱ ስፋት ስለተቸገርኩኝ
ስለሳቸው ችግር ለመጻፍ ወሰንኩኝ።
«የሰላሌ ጉብል ባሏ የሞተባት ባለትንሽ ልጇ
ትዝ አለኝ አስታወስኩ ያንጎራጎረችው ቁጭ ብላ
ከደጇ።

t.me/OLDBOOKSPDF

..ስርዶው ደርቆ እምቢ አለ ልረስ ወይስ ልንቀል
.. ሕዓት አለቀሰ ላሳድግ ወይ ልጣል።
..ካዘንን በስተግራ ከደስታ በስተቀኝ
..መሃከሉን ማለፍ አልቻልኩም ጨነቀኝ።»
«በልግፉ በልግፉ በል ግፉ ጨምር
ያልፋል አንድ ስሞን ችግርና ጦር..
እንዳለው አዝማሪ
ቀበቶ ማጥበቅ ነው የኔታ አስተማሪ።
አልኩና ጫጭሬ ወዲያው ብስጣቸው
ቁጥር ፈታ እያለ ጠቆረ ፊታቸው።
..ግጥሙ እንከን የለውም ይሆናል ላብነት
..ከየት መጽሐፍ ላይ እንደገለበጥከው አስረዳ
በፍጥነት»
አሉና የኔታ አስነሱ ክርክር
አልተሳካልኝም ራሴ እንደጻፍኩት ላስረዳ ብሞክር
ያልተጻፈ ነገር ከየት አገር ላምጣ
ንስር ዜሮ ሰጡኝ ግጥም ውሃ ጠጣ።
የማወቅን አድማስ በድሜ መገደቡ አይጠቅምም
ይጎዳል
የፈጠራን ክህሎት መቀመቅ ያወርዳል።



ሻዊታሞ ክርስቲያን

ስብሀት ገብረእግዚአብሔር

ድሮ በደርጉ ዘመን አንድ ጓደኛዬን ሰላም ለማለት ወደ አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ጉራ ስል የማገኛት ብዕአት የምትባል ሴት ነበረች። ቀይ ወፈር ያለች ሆና የደስ ደስ ያላት ናት። ጭንቀትም ጉስቁልናም የሌለባት ነባ ሰው። ያውም የስራ ኃላፊነቷ ገንዘብንና ሃገርን በቀጥታ የሚመለከት ሆኖ። እሳ ምን ቢገዳት!? በስራ በሚትወጠርበት ሰዓት ፈገግታና ላቅ ነው።

አሁን ይሆን ስዕፍ ለአንባቢ ለመንገር ፈልጌ «ከብዕአት ጋር ስመቀራረብ የደረስነው እንዴት ነበር?» ብዬ ራሴን

t.me/OLDBOOKSPDF

ብጠይቅ መልስ የሰም። ክክባችን ስለገጠመ ነው እንዳልል አሷም አኔም በክክብ ቆጣሪ እናምንም።

ሂደቱንም ሁኔታውንም እኔ ሳላስተውለው እቺ ብፅአት እንደ ስሟ ብፅአት ሰው መሆኗ ሲሰማኝ ወይም ሲታየኝ ወይም ሲታወቀኝ ጀምሯል። የሷ ነገር ልገልፀው በምችል አኳኋን አይገባኝም። እኔ የማውቀው በንፁህ ወንድማዊ ፍቅር እንደምወዳት ነው። እና የሷ ነገር ትዝ ባለኝ ቁጥር ያስገርመኛል። ታድያኮ ላስብበት ምንም ሊያስገርመኝ አይገባም። ክርስቶስ በተወለደ በሁለተኛው ሺ ዓመት እንዲያውም ክርስቲያን ባያጋጥመን ነው ለደንቀን የሚገባው።

ብፅአት ልዩ ነች - እውነተኛ ክርስቲያን ነች። ያውም ዛሬ በሰማንተኛው ሺ። እንድ ቀን «ምን ሆነሽ ነበር ከትላንት ወዲያ? ያለ ወትሮሽ በሀሳብ ተውጠሽ ነበር» አልኳት። «እንዲያው ሆሮብኝ ይኸውልህ አለቃዬ በማላውቀው ምክንያት ጠምዶኛል። እና ዕቃ ስጣ ያመጣሁት ደረሰኝ የት እንዳረግኩት ጠፋኝ። አለቃዬ ቢጋታው ጧት ደረሰኙን ውለጂ ይሰኛል ብዬ እየተጨነቅኩ ነበር። ቅበጠበጥኩ ነው፣ እንጂ ጌታ እያለልኝ ምን አሳሰበኝ? ሲመሽ አልጋዬጋ ተንበርክኬ ፀሎት አድርጌ ስጨርስ "ጌታ ሆይ፣ ደረሰኙን የት አስቀምጬው ነው? አልኩት። ጎትኛው መሳቢያ ውስጥ። እታች ያለው ፋይል ውስጥ አለኝ። ሳቅ አልኩ —እፎይታ አየተሰማኝ። ሲነጋ ሰራ እንደገባሁ እዚያው እሱ ያለኝ ቦታ አገኘሁት — ደረሰኙን።»

ከአንድ አምስት ስድስት ሳምንት በኋላ የብፅአትና የአለቃዋ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ደረሰ። እንደልማዷ ማታ ተንበርክካ ስትፀልይ «ጌታ ሆይ፣ ይሄ አለቃዬ ፈተና ሆነብኝ እያናደደኝ። ሌላ ስራ ልፈልግንዴ?» አለችው።

«እዚሁ ስራሽን ቀጥይ። ከአንድ ወር በኋላ አለቃሽ ይዛወራል» አላት። ይህን በነገረችኝ በወሩ አለቃዋ እድገት አግኝቶ ወደሌላ መስሪያ ቤት ተዛወረ። ይህን ስፅፍ የሚያምኝ ሀበሻ አንባቢ አለ ብዬ ሳይሆን፣ አስቲ እውነት ልናገርና ደስ ይበሰኝ ብዬ ነው።

ስኔ ብፅአትና ቅዱስ አጐስጢኖስ ይቀራረቡብኛል። እሷም እንደሳችው በወጣትነቷ ጊዜ «ላይቷን ቀጭታለች፤ በመጨረሻው ፋሽን አለባበስ ዘንጣለች።» ብታየው ብታየው ታዳያ ይሄ ሁሉ ቅብጠት አዲስ አየመሰለ ሁልጊዜ ያው ነው። ከንቱ ነው። የትም አያደርስም። ከልብሶቿ አንዱን እንደምታወልት አወለቀችና ጣሰችው። ቤቱ። ይህን ጊዜ ነበር ጌታን የተቀበሰችው ...

የመጀመሪያ አርግዝናዋ አየከበደ ሲሄድ ብፅአት የማታ ፀሎትዋን ስታበቃ፣ «ጌታ ሆይ፣ አንግዲህ የምታረስበትን አህል ለመሸመትና ለማስፈጨት ወደ መርካቶ ልሂዳ» አለችው።

«እርፈሽ ቤትሽ ተቀመጪ። የሚያስፈልግሽ ሁሉ ጊዜው ሲደርስ ይመጣልሻል»

ከመርካቶ ሁከትና ጫጫታ ተገላገለች። ጊዜዋ ሲደርስ የሚያውቁት ክርስቲያኖች የማያስፈልጋትንና ከዚያም በላይ አያመጡ ሰጧት።

ወራቱም ዓመታቱም እያለፉ ሄዱ። አነሱ ቤት የብፅአት ባለቤትና አሰክ አስር የሚደርሱ ሌሎች ክርስቲያኖች እየተሰበሰቡ እየዘመሩ ይፀልዩ ነበር። አንዳንድ ጉረቤት ሳይደርሱብኝም ለምን አልደረሱብኝም ብሎ ቂመኝ ታጥቆ ይነሳል። «አንዚህ ሰዎች ጴንጤ ወደ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወረዱ።

ማታውኑ ብፅአት በለሎትዋን ከጨረሰች በኋላ ጌታን ስለዚህ ጉዳይ ብትጠይቀው «ምንድነው ጌታ ሆይ?»

«አደጋሽ ሰስራ ተልከው ነው» አላት። እውነትም፤

t.me/OLDBOOKSPDF

እዚያ በቆዩበት ጊዜ በአስረኞቹ መሀል ሰጌታ መስከረው አያሌ አስረኞች ጌታን ተቀበሉና ቋሚ አባላት ሆኑ።

ከብፅአት ጋር በምተዋወቅበት በዚያን ወቅት አንድ ቀን አንድ መነኩሴ ላንዳፍታ አጋጥመውኝ ነበር። ብፅአትን ሳስታውስ ትዝ ይሉኛል። አሳቸውንም ሳያቸው «እኚህ ሰው ዓድቅ ናቸው» የሚል ስሜት አውስጤ አድሮብኛል። እንዲሁ ከመፌት ተነስቼ የደብረ ሊባኖስ መነኩሴ ናቸው ብያለሁ ሰራሴ።

በአንድ የሰፈር መንገድ ስሄድ ከወዲያ ሲመጡ አየኋቸው —እኚህን መነኩሴ። በእጃቸው ሙሉ ጭብጥ ሽምብራ እሸት ይዘዋል። መጀመሪያ ላገኙት ልጅ ግማሹን ሰጡት። የቀራቸውን ግማሽ ቀጥሎ ላገኙት ልጅ ግማሹን ሰጡት። የተረፈውን ግማሽ ደሞ ግማሹን ለሚቀጥለው ልጅ ሰጡት። እኔጋ ሲደርሱ አንዲት ብቻዋን ቀርታቸው ነበር፣ እሷን ሰጡኝ።

ማንም ቂስ መስቀል ሊያሳልሙኝ ቢፈልጉ እሺ ብዬ አሳለማለሁ'ንጂ እንዲያሳልሙኝ ጠይቄ አላውቅም። እኚህ መነኩሴ ግን እንዲያሳልሙኝ ፈለግኩ። ግን ብመለከት መስቀል የላቸውም።

«መስቀል አልያዙምንዴ አባ?» አልኳቸው።

«ይገርለሁ'ንጂ። እየኝስቲ» አሉና እጆቻቸውን ወደገጣ ዘረጉ። «እኔ ራሴ መስቀል አይደለሁም? በለማይ የሚበሩት ወፎች ክንፋቸው ተዘርግቶ ለታይ መስቀል አይደሉም? በባህር የሚዋኙት አሳዎችም መስቀል ናቸው። ወዴትም ብትመለከት መድኃኒታችንን መስቀሉን ታየዋለህ» ብለውኝ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ትውስታዬ ውስጥ ቆንጆ ቦታ አጠገብ ላጠገብ የሚቀመጡ ሶስቱ እህቴ ብፅአት፣ እኚህ የደብረ ሊባኖስ ቂስ ሽምብራ እሸት የተቀበልኳቸው መነኩሴ፣ እና ቅዱስ

አጐስጢኖስ ናቸው። አሳቸውም ለሮማዊት ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለኛ አቡነ ተክልዬ የሚይዙትን ቅዱስ ስፍራ ይይዛሉ።

ከ354 እስከ 430 ሲኖሩ፣ በጉርምስናቸው ዘመን እስኪቆቸው እቺን ዓለም ተደስተውባታል - አበባን አያለዋወጠ እንደሚቀሰም ንብ ሴት ልጅን እያቀያየሩ ከእቅፏ የጎኑትን ደስታ ቀስመዋል። ከፅለታት አንድ ቀን ግን ቪጋው አጐስጢኖስ ይዜ ሁሉ ስጋዊ ደስታ የትም የሚያደርስ ባዶ ድግግሞሽ መሆኑ ወሰለ ብሎ ታየው። ዓለም ከንቱ አለ። ዓለም በቃኝ አለ። ፊቱን አዞረ፣ እውነትን ፍለጋ ፈለለ።

ይዜ ኑሮ ምንድነው? ማን ነን? ከየት መጣን? ወዴት እየሄድን ነው? ለምን? እኮ ለምን?

አንድ ቀን እንዲህ አያብጠለጠለ እያለበ በባህር ዳር በአግሩ ሲዘዋወር አጐስጢኖስ አንድ ትንሽ ልጅ ባህሩ ዳር ጉድጓድ ቆፍሮ በእጹ ውሃ ከባህሩ እያፈለ ወደ ጉድጓዱ ሲጨምር አየ።

«ምን እያረክ ነው ማሙሽ?»

«ባህሩን በሙሉ ብጨምርበት ጉድጓዱ ይሞላ'ንደሆን ለማየት ብዬ ነው»

«አይ ማሙሽ፣ በል ቻው!»

«ቻው!»

አጐስጢኖስ አልፍ ካለ በኋላ ነበር ልጹ ምን እንዳለው የተሰማው። እንዴ!! ብሎ አጐስጢኖስ ወደ ልጹ ዘወር ቢል -

ልጅየው እዚያ የለም። ለካ መልአክ ኖሯል በልጅ ተመስሎ ነው'ንጂ። መልዕክቱ ገባው። ባህሩ ፈጣሪና ጥጥረቱ በመላው ነው። የትንሹ ልጅ ጉድጓድ ደግሞ የአጐስጢኖስ ጭንቅላት አእምሮ፣ ሀሳብ፣ እውቀት።

ከዚያ በኋላ አጐስጢኖስ «አመን - ከዚያ በኋላ ይገባሀል»

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ በእምነቱ ወና። አየፈለግከው ያለኸውን አውቀት ታገኘዋለህ።

ቅዱስ አገስጢኖስ በአድሚ ከገፉ በኋላ Confessions (ኑዛዜዎች) የሚል የህይወት ታሪካቸውን ፃፉ።

እኔምላችሁ፣ «ምነው ነብሴ ወጣት ደራሲ በሆነችና እቺን ብዕሌን ሰልሆነ ወይም ለተውኔት ዋና ገፀ ባህሪ አድርጌ በመሰድኳት!» አያስብልም?

መጣጥፍ







የተስፋ ቃል ት

ተስፋዬ ገብረአብ

ከአስራ ሁለት አመታት በፊት የተፈፀመ አንድ ግለ-ታሪክ ላውጋችሁ።

ወርሀ ነሐሴ - 1979።

በወቅቱ የአስራ ዘጠኝ አመት ሰው ነበርኩ። ያጣሁ፣ የነጣሁ። የተገላቆልኩ፣ ልብስና ጫማዬ የነተበ። እንዲያም ሆኖ ግን የተከፋሁ ሰው አልነበርኩም - ህልም ነበረኝ። ጋዜጠኛና ደራሲ የመሆን ህልም። እና አዕፋለሁ - አነባለሁ። ብዙ አነባለሁ - ጥቂት አዕፋለሁ።

ረጅምና አጫጭር ልቦለዶችን፣ መጣጥፍና ግጥሞችን

t.me/OLDBOOKSPDF

እፅፋለሁ። እየሣቁኩ በአሮጌ የአንጨት ሳጥኔ ውስጥ አጠራቅማቸው ነበር። በርግጥ ወዶ ኩራዝ አሳታሚ ብቅ ብዬ ድርሰቶቼን ያዩልኝ ዘንድ ለማነጋገር መሞከሬ አልቀረም ነበር። ግን ዋጋ አልነበረውም። እንኳን ድርሰቶቼን አይተው 'ይሆናል አይሆንም' ለማለት ቀርቶ እንደሰው በቅጡ ሊያናግሩኝ እንኳ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው አሳታሚ ድርጅቶች ላይ የነበረኝን ተስፋ ሙሉ በሙሉ ሰርገፍው ነበር።

ይልቁን ሴላ አማራጭ ለመጠቀም አሰብኩ። አንጋፋ ደራሲያንን የማማከር አሳብ ነበር ወደ አይምሮዬ የመጣው። ሳወጣ ሳወርድ ቀልቤ ወደ ሀዲስ አለማየሁ ተሳበ። የፍቅር እስከመቃብር ደራሲ፣ ሀዲስ አለማየሁ - የኢትዮጵያ ብርቅ ልጅ። ታላቅ ሰው። ደራሲ ሀዲስ።

ነሐሴ 1979 አጋማሽ ላይ አምስት ያህል የተመረጡ ድርሰቶቼን ይዤ ወደ አንጋፋው ደራሲ መኖሪያ ቤት አቀናሁ - አስመራ መንገድ።

በጉልማሳ ረዳታቸው በኩል አንዲት ማስታወሻ ቢጤና ድርሰቶቼን ተቀበሉኝ። በዓፍኩላቸው ደብዳቤ ጋዜጠኛ የመሆን ፍላጐት እንዳለኝ፣ አጫጭር የፈጠራ ስራዎቼንም እንዲያዩልኝና መልካም ከሆኑ ለሀትመት የሚበቁበትን መንገድ እንዲጠቁሙኝ ተማፅኗያቸው ነበር። ድርሰቶቼና ደብዳቤዬ በደረሳቸው በሳምንቱ ሊያነጋግሩኝ ቀጠሮ ያዙልኝ። አንድ ረቡዕ ማለዳ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ከሚገኝ ፅሀፊት ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩኝ።

አንጋፋው ደራሲ ጋቢ ለብሰው ነበር። ቢሮአቸው ውስጥ የታላቁን ደራሲ ደረጃ የጠበቀ ሆኖ አገኘሁት። በቀኝ በኩል ከመስታወት በተሰራ የመፅሀፍ መደርደሪያ ውስጥ ወፋፍራም ጥራዝ መፃህፍት በስርዓትና በንፅህና ተቀምጠዋል። በቆዳ ቁልብጦ መስታወት ካረፈበት የቢሮ ጠረጴዛቸው ትይዩ ሁለት አረንጓዴ የአንግዳ መቀበያ

ወንበሮች ይገኛሉ።

ደራሲ ሀዲስ፡

«እንደምን አረፈድህ?» ሲሉ አክብሮት ባልተለየው ድምፅ ተቀበሉኝ። ምላሽ ሰጠሁ። አያይዘውም፣ በእጃቸው እያመላከቱ እንድቀመጥ ጋበዙኝ።

ከዚያም ወግ ጀመርን። ያዩልኝ ዘንድ ስለሰጠኋቸው አጫጭር ልቦለዶችና በጋዜጠኝነት ሙያ መስራት በመፈለጌ ዙሪያ አወጋን።

አንጋፋው ደራሲ እንዲህ አሉኝ፣ «በስነ ፅሁፍ ዘርፍ ተሰፋ ያላቸው ወጣቶች ሁሉ ይህን ይጠይቃሉ። ሀገራቱ ግን የእነዚህን ወጣቶች ፍላጐት ማስተናገድ ይትርና ልብ እንኩዋ አትላቸውም። ይልቁን ትኩረት ያሰው ጦርነቱ ላይ ነው። ወጣቶች ለዘመቻ እንጂ ይህን ለመሰለ በጐ ተግባር አይታጩም። እጅግ አሳዛኝ ነው...»

ደራሲ ሀዲስ እንደመተከዝ አሉ!

«በቀጥታ ወደጉተ ጉዳይ ስንመለስ ከኔ ሁለት ነገሮችን እንደምትሻ ነው የተረዳሁት። በጋዜጠኛነት ሙያ አካባቢ መስራት ትፈልጋለህ። ይህን እኔ ክቶ ልፈፅምልህ የሚቻለኝ አይመስለኝም። ምክንያቱም» አሉ ሀዲስ አለማየሁ «ሰሞኑ እኔን ያውቅኛል እንጂ እኔ ባለስለጣኖቹን አላውቃቸውም።»

አያይዘውም በርጋታ ያወጉኝ ገቡ፣ «...ያመጣህልኝን አጫጭር ፅሁፎች ላያቸው ሞክሬ ነበር። ግን ሳልችል ቀረሁ። ጊዜ አያጠረኝ ነው። ከማለፌ በፊት የጣልያን ወረራ ዘመን ትዝታዎቼን የተመለከተ መፅሀፍ ለማሳተም በሩጫ ላይ ነኝ። ያለማቋረጥ እየሰራሁ ነው - ኖኔ ልጅ። ብረዳህ ግን ደስ ባለኝ። ፅሁፎችህን ጥቂት ለማየት ሞክሬ ነበር። አያያዝህ መልካም ይመስላል። ግን ምን ልረዳህ እችላለሁ?»

ሀዲስ አለማየሁ ይህን ብለው እንደመተከዝ አሉ። እኔን ለመርዳት ያላቸው ፍላጐት በግልፅ ገፅታቸው ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይነበብ ነበር። ግን ጊዜ የላቸውም። አድሜያቸው ገፍቷል።
በህይወትና በሞት መስመር ላይ ናቸው። ጊዜያቸውን
በቅጡ ካልተጠቀሙበት ያሰቡትን ሳይጨርሱ በመካከሉ
ላይ ሁሉም ነገር ሊቆም ይችላል። ይህን ተረዳሁ። ሊረዱኝ
እንደማይችሉም ተገነዘብኩ። ግን ደሞ ደስተኛ ነበርኩ።
እንጋፋው ደራሲ የአስራ ዘጠኝ አመቴን ወጣት አከብረው
በማነጋገር ላይ ነበሩ። ይህ ብቻውን ለኔ ከፍተኛ ሞራል
የሚሰጥ ሆኖ ተገኘ።

አንጋፋው ደራሲ አይኖቻቸውን በመስኮት አሻግረው
በግቢው አፀድ ውስጥ ከሚገኙት ወፋፍራም ዛፎች ላይ
ተክለው ነበር።

ድንገት «ፅድሜህ ስንት ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ።

«አስራ ዘጠኝ»

«ገና ልጅ ነህ»

ገዘም አልኩ።

«ወደ መቼፍ ነው የምታዘነብለው ወይስ ወደ ማንበቡ

«በማንበብ የማጠፋው ጊዜ ይቆዛል።»

«ጥሩ ነው» አሉ። ደገሙት ይህንኑ «በጣም ጥ
ነው።»

እንደገና ተመስጠው ቆዩ። በተስፋ አይን አይናቸው
አይ ቀጠልሁ፤

«እንግዲህ እኔ ልረዳህ ባይቻለኝም፤ ቢያንስ ግ
ሊያግዝህ ወደሚችል አንድ ጉልማሳ ደራሲ ዘንድ
አልክህለሁ። ታውቀው ይሆናል። ብርሀኑ ዘርይሁን
ይባላል። አሁን እንኳ እንገናኝም። ቀደም ብሎ ግን እዘ
ይመጣ ነበር። አሁን እተቀመጥክባት ቦታ ነበር እሱ
የሚቀመጠው። ወጣት ደራሲያን መታገዝ እንዳለባቸ
ደጋግሞ ይናገር ነበር። ብርሀኑ መልካም ሰው ነው። ጥ
ደራሲም ነው። በተለይም ወጣቶችን ለማገዝ ያለው
ፍላጐት አደንቅለታለሁ። አሁኪ ወደርሱ ሂድና እ

እንደላክህህ ንገረው። አርግጠኛ ነኝ ይረዳሀል። እንዲያውም
ጥቂት ማስታወሻ ቢጤ ብፅፍለት ሳይሻል አይቀርም።»

ከግማሽ ሰዓት በኋላ አንጋፋውን ደራሲ ከልብ
አመሰግኜ ስመሄድ ተነሳሁ። የታሸገ ፖስታ ይገዙ ነበር።
የተስፋ ፖስታ።

«ቆይ!» አሉኝ ደራሲ ሀዲስ።

ተመልሼ ተቀመጥሁ።

«እንደማይህ ኑሮ የተመቸው ሰው አትመስልም።
ልብሶችህና ጫማዎችህ መናኛና ያረጁ ናቸው። ምናልባትም አውቶብስ የምትሳፈርበትም ሳይኖርህ
ይችላል...»

ይህን ካሉ በኋላ እጃቸውን በጋቢያቸው ስር አሾልከው
ከደረት ኪሳቸው ጥቁር ሳሳ ያለች የእጅ ቦርሳቸውን
አወጡ። ከዚያም ሶስት ድፍን የአስር ብር ኖቶችን
አውጥተው ጠረጴዛው ላይ አኖሩልኝ።

«ጋሼ ሀዲስ ከልብ አመሰግንዎታለሁ!» ስልተናገርኩ።

«ምንም አላደረኩልህም ልጄ!»

«ግን አከብረውኖል።»

«ያሚተኩን ወጣት ፀሀፊዎች በእጅጉ ያስፈልጋሉ።»

ሰላላውን ብር ኪሴ ከትቼ በተስፋና በደስታ ተሞልቼ
የሀዲስ አለማየሁን ቅፅር ግቢ ሰቅቄ ወጣሁ።

* * *

ይህ በሆነ በአምስተኛው ቀን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
ሀገባ ሰባተኛ ፎቅ ላይ ተገኘሁ። ቁመተ ረዥሙ ብርሀኑ
ዘርይሁን በአክብሮት ነበር የተቀበለኝ። ፖስታውን
አስረክብኩት። ሀዲስ የፃፉለትን አንብቦ ሲያበቃ ወግ
ጀመርን። ሀዲስ አለማየሁ ዘንድ እንደ ቆየሁ፤ ፍላጐቴንም
ጭምር በዝርዝር አጫወትኩት። በትዕግስትና በጥሞና
ካዳመጠኝ በኋላ፤ እንዲህ ይለኝ ጀመር፤

«አንዳልከው እዚህ አገር በቂ ኩሌጆች ባለመኖራቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

መልክም ቦታ መድረስ ይችሉ የነበሩ አያሌ ወጣቶች ከቆኖ እየተቸገሩ ነው። ግን ምን ማድረግ ይቻላል?»

እርሱም ለስኩንዶች ያህል በገሞታ ተመስጠ ቆየ።

«ሀዲስ መታገዝ እንደሚገባህ ዕፈውልኛል። ልክ ናቸው። ወጣት ፀሀፍት መኮትኮት አለባቸው። ሀዲስ እኛ ወጣት በነበርንበት ጊዜ አግዘውናል። አንጋፋዎች ወጣቶችን መደገፍ አለባቸው። ለማንኛውም አስኪ ፅሁፎችህን ልያቸው። ከዚያም የሚሆነውን እንነጋገራለን ይህን ካለኝ በኋላ በቀጠሮ ተለያየን።

* * *

በአስረኛው ቀን በቀጠሮዬ ሰዓት ብርሀኑ ዘርይሁን ቢሮ ተገኘሁ። በቢሮው አልነበረም። ፀሀፊው ዘንድ ግን የወረቀት መልዕክት ትቶልኝ ነበር። የታሸገችውን ብጫ ወረቀት ከፍቼ አነበብኳት፣

«ዛሬ ማምሻውን 12:30 ላይ፣ ፒያሳ አሺፕ ግሮሰሪ አጠብቅሀለሁ። ብ.ዘ.» ይላል።

የሰራ አካላቴ በደስታ ሰሜት ተወረረ። ግን ለምን ቆይቼ ነበር ምክንያቴን የተረዳሁት። ታዋቂው ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሀኑ ዘርይሁን እኔን አክብሮ ማስታወሻ ስለተወልኝ ሳይሆን አልቀረም - ያን የመሰለ የደስታ ስሜት የናጠኝ።

በተባለው ሰዓት አሺፕ ግሮሰሪ ተገናኘን። ብርሀኑ ጂን ነበር የሚጠጣው። ለኔ ቢራ አዘዘልኝ። በዚያን እለት ቢራ ስጠጣ ሁለተኛ ጊዜዬ ብቻ ነበር። ከዚያ ቀደም በአንድ አጋጣሚ ሁለት ቢራ ጠጥቼ ነበር። ባለጌ ወንበር ላይ ተቀምጠን ቢራና ጂን እየኮመኮምን ወግ ጀመርን። አብዛኛውን ብርሀኑ ነበር የሚያወራው፣

የታንጉት ምስጢር በሚል ርዕስ መፅሀፍ ማዘጋጀቴን በቅርቡ ገበያ ላይ እንደሚውል ነገረኝ። አያይዞም እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

«የቴዎድሮስ እንባ የተባለ መፅሀፌን አንብበኸዋል?»

«አዎን አንብቤዋለሁ» አልኩት። አያይዤም «የሀገር ውስጥ ደራስያን ስራዎችን በሙሉ አላመሰጠኝም» ስል አከልኩ።

«ያን መፅሀፍ መነሻ አድርጌ ነው የታንጉት ምስጢርን የሰራሁት። ታትሞ ሲወጣ ታነበዋለህ። የምትወደው ይመስለኛል።»

ከዚያም ወሬያችን በቀጥታ ወደኔ ጉዳይ ተሸጋገረ።

«አነበብካቸው?» ስል ጠየቅሁት - የሰጠሁትን አጫጭር ልቦለድ ታሪኮች ማለቴ ነበር።

«አዎን!» አለና የጂን መለኪያውን አነሳ። ብርሀኑ ዘርይሁን ደረቁን ጂን ሲጉነጭ አይናቸን ጨፈን — ከፈት ጨፈን ያደርጋቸዋል። ደጋግሞ ተጉነጭጭ፣ አስተናጋጅቹ ይደግሙት ዘንድ አገዛ ሲያበቃ እንዲህ አሉኝ፣

«ስለ አሳታሚ ድርጅቶች ወይም ስለ ሳንሱር መናገር አልፈልግም። ስነ ጽሑፍን ማድነቅ ያስፈልጋል። እኛ ግን ለዚህ የታደልን አይመስለኝም» ይህን ብሉ ሲያበቃ በጂን የተሞላ ብርጭቆው ላይ አይናቸን ተክለው ቆየ፣ እጅግ አሰልቺና የሚያናድድ ርዕሰ — ወሬ ነው። ይልቁን ስለ ውበት፣ ስለቃላት፣ ስለገፀባህርያት ባጫውትህ ይሻለኛል።

«ምን መስለህ... ማነበር ያልከኝ ስምህን? ... አዎን... ልሸነግልህ አልፈልግም። ከልብ አመነኝ፣ እንድ ኩነት ልንገርህ? አንተ እኛን ትተካናለህ!»

የመጨረሻዎቹ የተሰፋ ቃላት ከአንጋፋው ደራሲ ከብርሀኑ ዘርይሁን እንደበት ሲወጡ ያደረብኝን የሚነዝር ስሜትና፣ ሲቃ የሚያሲዝ ደስታ ከቶ እንዴት በቃላት ልገልፀው እችላለሁ? ብርሀኑ ረጋብሎ ያወጋኝ ቀጠለ።

«... ቋንቋህ ጥሩ ነው። አጫጭር ናቸው - አረፍተ ነገሮችህ። በርግጥ ፅሁፎችህ ሁሉ ያስቀላቸው መልክም

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው ማለት አይደለም። እምቅ አትምህን ግን በጎሀድ ያሳያሉ። በተለይም... የልደት በዓል ጥሪ የሚለው አጭር ድርሰት እጅግ ልብ የሚነካ ሆኖ ነው ያገኘሁት። እንዲያውም ፈጠራ አይመስልም። የራስህን ገጠመኝ የቁርስ መስሎ ነው የተሰማኝ። ነው ግን?»

ይህን ብሎ ከልብ ሳቀ።

ከኔ መልስ ከማግኘቱ በፊት ደሞ ቀጠለ፣

«...ምን መሰለህ፣ እኔ ወጣቶች ጥሩ ሲፅፉ ተስፋ ያድርብኛል። ምናልባትም እኮ እኛ አንጋፋ ከምንባለው ፀሀፍት የተሻለ ተስጥኦ ያላቸው ሲሆኑ ይችላሉ። ግን ያውቃል? ብዙ አስባለሁ። ግን ይህ መልካም ፍላጐት ብዙውን ጊዜ ምኞት ሆኖ ነው የሚቀረው። ምክንያቱም... አለና ባለመጀመሪያ መልኩ ፊቱን አጨፈገገ። የጀመረውንም ሳይጨርስ ቀረ።

ብርሃኑ ዘርይሁን በዚያን አለት ከመሰያየታችን በፊት እንዲህ አለኝ፣

«እኔ ዘንድ ያሉትን አጫጭር የፈጠራ ድርሰቶች ኩራዝ ሳለ አንድ ወዳጄ አስጥልሀለሁ። ለመሆኑ ለራስህ ኮፒ አስቀርተሃል?»

«የለኝም»

«ኦ! እንደኔ የለየልህ ስነፍ ኖረሃላ! ወይስ መገልበጥ ሰለቸህ? ለማንኛውም ብዙ አያሲጋም። ሰወደፊቱ ግን ኮፒ ማስቀረት ልመድ። የኩራዝ አሳታሚ ሰምቾ ከሌሎች አጫጭር ልቦለዶች ጋር አጣብለው አንዲያወጡልህ እንማፀናቸዋለን። በጋዜጠኝነት ሙያ መስራትም ፈልገህል። ጥሩ ይሆን ነበር። ግን ይህን እንዴት እንደምናደርግ አንጃ! አዲስ ዘመን ጋዜጣ አካባቢ በአራሚነት እንድትጀምር እሞክርልህሰሁ። በርግጥ ቡቲ የዘመድ ቤት ነው። ግን እስቲ እንደምንም ከተቻለ...»

ሆኖም ሁለቱንም ጉዳዮች ዳር ሳያደርስልኝ ብርሀ

ዘርይሁን ዘሞት ተቀደመ። የአንጋፋውን ደራሲ ዜና - እረፍት በቴሌቭዥን ሲነገር የሰማሁ አለት በተቀመጥኩበት ጨንቀቱን አቀለጥኩት። የብርሃኑ ሞት ለኔ እጅግ መራራና ተስፋ አስቆራጭ ሆነብኝ። ግን ከዛ ምን ማድረግ ይቻላል?

በማንስቱ ራስ መቀንን ድልድይ አጠገብ አጂፕ ግሮሰራ ፊት ለፊት ከሚገኘው የብርሀኑ ዘርይሁን የመኖሪያ አፓርታማ ሄጀ ቤተሰቦቹን አስተዛዘንኩ። ከብርሃኑ ዘርይሁን ጋር በነበረኝ የቀረበ ግንኙነት ሳቢያ ከቤተሰቡ ጋር ቀደም ብዬ ተዋውቂ ነበር። በተለይም ከወንድ ልጁ ጋር። ሚሹል ይባላል። በአድሚ ጥቂት ብበልጠው ነበር። በሳልስቱ ሚሹል ስለ አባቱ አመሞሙሞት ሲያወጋኝ ከቆየ በኋላ እንዲህ አለኝ፣

«...በነገራችን ላይ በኑሃዜ ደብተሩ አንተን በተመለከተ የተፃፈ ነገር አለ። የሰጠንው አጫጭር ፀሁፎች ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ ለሚሰሩ ሰው እንደሰጠ አስፍሮአል» ብሎ የአርታኢውን ስም ነገረኝ።

ፅሁፎቹ ይጠፋሉ የሚል ሰጋት እንኩዋ አልነበረኝም። ቢጠፉም የምደነግጥበት ሁኔታ አልነበረም። የእንድን ጀማሪ በሀፊ አጫጭር ልቦለዶች የሚሰርቅ ቀርቶ የሚያነብ እንኩዋ እንደሌለ ነበር የማስበው። ምንም ሆነ ምን ብርሃኑ ካረፈ በግምት ከአርባ ቀን በሁዋላ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ከከፉት አርታኢ ዘንድ ሄጀ ፅሁፎቼን ጠየቅሁ። አርታኢው ጊዜ ወስደው እንኪ ጥቂት ሊያናግሩኝ ሳይፈቅዱ ቀሩ።

ይህን በመሰለ አኩዋሁዋን ነበር ያስተናገዱኝ፣

«አዎን፣ ብርሃኑ የተወሰኑ አጫጭር ፅሁፎች ሰጥቱኝ ነበር። ግን አሳንብበኩዋቸውም። መልሰህ ብትወስዳቸው ነው የሚሻለው።»

ከዚያም ከጠረጴዛቸው ጫፍ ላይ ከተቆለሉት ወረቀቶች መሀከል ጥቂት ፊላልገው አንድ ላይ የተሰፋትን የኔን እምበት አጫጭር ልቦለድ ድርሰቶች በችኮላ አቀበሉኝ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጽሁፎቹን ይገፍ የህንፃውን ደረጃዎች በመውረድ ላይ ላለሁ ግን ብርሃኑ ዘርይሁን የኔን ዕሁፎች ለአርታኢው ሲልክ አያይዞ የላካት ማስታወሻ አብራ መኖርዋን አስተዋልኩ። እንዲህ ትነበባለች...

«ይህ ወጣት እጅግ ጥሩ ይዕሩል። እኔ አንብቤለታለሁ። በእውነቱ ግሩም ናቸው። ጥቂቶቹ አንኩዋ ሊታተሙለት ቢችሉ ልጁ ሊደፋፈርና ሊያድግ ይችላል። እስኪ አያቸውና አንድ ነገር አድርግ? ብዘ.»

ከዚያ ወዲያ ክፉ መንፈስ የሰፈረበት የመቃብር ስፍራ ወደመሰለው የኩራዝ አሳታሚ ህንፃ አልተመለስኩም። ማንበብና መፃፍ ግን ቀጠልኩ...

«ማን ያውቃል? አሳታሚ ድርጅቶችም እንደ አረፋ ቤቶች የሚፈስበት መልካም ዘመን ይመጣ ይሆናል» የሚል ተስፋ ነበረኝ...



ሽሽት

ቶማስ አርጋው

ወደሚያፈቅሯት ዓለም ከመጡ 100 ዓመት ሞላቸው። ባራም ህይወትን ያፈቅራሉ። አፍላ ፍቅር ላይ ናቸው።

ፀሐይ ስትወጣና ስትገባ ማየት ይፈልጋሉ። ከተፈጥሮ ዐጋ ምንም አይነት ኃይል እንዲሰያቸው አይፈልጉም። ሞትም ቢሆን! ለሞት እጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉም። ሞት በእግዚአብሄር እንደሚታዘዝ እርግጠኛ ቢሆኑም ከሞት መሸሽ መደበቅ ክፉ አይደለም ባይ ናቸው። አቶ ንብረየስ ሸዋንግዛው።

ከተወለዱባት መንዝ (ደንዝዜ) በልጅነታቸው ሲያርሱ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲጮሀጉሱ፣ ሲኮተኩቱ፣ ሲዘሩ፣ ሲያጭዱ፣ ሲከምሩና ሲወቁ ለወግ ማዕረግ በቁ። እናታቸው በልጅነታቸው ስለሞቱ በእንጀራ እናት እጅ ነው ያደጉት። ያለምንዳና ጥሪት የሰው ገ-ተራ ሲሞሉ እንደኖሩ ይናገራሉ። ለአቅመ አዳም ሲደርሱ ትዳር መስረቱ። የመጀመሪያዋን ሴት ልጃቸውን እንደወለዱ መንገዝን ለቀው ወደ አዲስ አበባ መጡ። አቶ ገብረየስ ማለቂያ የሌለውን የአገር ጉዞ ከተያያዙት 50 ዓመት ሊሆናቸው ነው። ይሄዳሉ! ይሄዳሉ! ይሄዳሉ! ... ጀንበር ወጥታ አስክትጠልቅ ያለመታከት ይኳትናሉ። እንደ ምስማር በቀጠኑ ግን በጠነከሩ እግሮቻቸው ይሸመጥጣሉ። እየተገላመጡ ከአንዳች ነገር ይሸሻሉ። ተፈጥሮን ቢወዷትም እምነት የጣሉባት አይመስሉም። ይጠራጠራሉ።

ያገኟቸው አመቺ ቦታ አልነበረም። የሚያውቋቸው የመንደር ልጆች ይበዛሉ። ተቀምጠን ስንጫወት ድንገት ይመጡና የሆነ ቃል ሲናገሯቸው ደንብረው ይነሳሉ። የሚውጣቸው (ቀዳዳ) ይፈልጋሉ።

ቁመታቸው አጭር ነው። ከወገባቸው ገ-በጥ ብለው ቡሚደሟት ምርኩዝ እየታገዙ ሲራመዱ ፍጥነታቸው ሰጉድ ነው። አንገታቸው ጭንቅላታቸውን መሸከም ያቃተው ይመስላል። እጆቻቸውም ይንቀጠቀጣሉ።

«ህመም ይሰማዎታል አቶ ገብረየስ?»

«አያመኝም ልጅ! አያመኝም። የሚያንቀጠቅጠኝ በሽታ የወረሰኩት ከአባቴ ነው። ዲአላ (ዲቃላ) ነኝ። ዲአላ ልጅ ደግሞ የአባቱን ባህርይ ይወርሳል ይባላል። ከአባቴ የወረስኩት ነውይ ጤነኛ ነኝ»

«ለመሆኑ ዕድሜዎ ስንት ነው?»

«አራት መንግሥት አሳልፌለሁ። እንግዲህ የከርሞ ሰው ካለኝ 102 ዓመት ይሆነኛል»

«ብዙ ኖረዋላ!»

«ተው! ተው! በግዚሃር ስራ አትግባ! ይህች ምን አላት?»

«እሺ ይቅር ለመሆኑ ቁርስ በልተዋል?»

«ከቤት? በስመአብ!» (የማይደረገውን የሚሉ ይመስላል)

«እንግዲያው ቁርስ ይብሉ»

«የለም! የለም! ትላንት አብልተኸኝ የለምን? ይሄማ ነውር ነው»

«ትላንት ከበሉ ዛሬ አይበሉም?»

«ጠዋት አንድ ቦታ ጥሩ ሽንብራ አሽት ሰጥተውኝ ደህና አድርጌ ጠርጥሬያለሁ» (አየተግደረደሩ ቁርሱን ቀማመሱ)

«ለመሆኑ የሚነሱት ከየት ነው?»

«ከ05 ከጋራው መድኃኒዓለም»

«ሰምቻ ከአቃቂ ነው የሚመጡት ብለውኝ ነበር»

«አኮ ጋራው መድኃኒያለም ማለት አቃቂም አይደል?»

«በስንት ሰዓት ተነስተው ጉዞ ይጀምራሉ?»

«የመጀመሪያዋ ትልቅ አውቶቡስ ስትነሳ እኔም እነሳለሁ»

«ከዱከም ነው የሚነሱት የሚባለውስ?»

«አይ አሳቸው ሞተዋል»

«ያውቋቸዋል? ሊላም ነበሩ ማለት ነው?»

«አውቃቸዋለሁ ኧረረረረ! አሳቸውኮ በፊት ሐና ማርያም ነበሩ። ያየህ አንደሆነ አንጂ ጅት ነበር የሚበሩት። አይ ሲሄዱ! አይ ሲሄዱ! ከዱከም ተነስተው በአንድ ቀን ነበር አዲስ አበባ የሚገቡት። አይ ሲሄዱ! አኒኮ ማይም ነኝ። አሳቸውን ያየህ አንደሆን በርናሳቸው ስር የሚሽጉጡትን ዳይት ያንበለብሉታል።»

«የተማሩ ናቸዋ!»

«አን-ንዴ-ንዴ-ዴ!! አኔኮ ሀሁን አላወ-ቅም፣ መድኃኒያለምን»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ልጆች ወልደዋል?»
«ኸረ የታባታቸው! ስለነሱ አታንሳብኝ!»
«ለምን?»
«የማይረቡ ናቸው»
«ስንት ወልደዋል?»
«አንዷን ሞት ነጠቀኝ አንቺ እምስት ወልጄ ነበር»
«አሁን የሚረዳዎት ልጅ የለም?»
«አንቷ ብቻ»
«ኖት ነው ያሉችው?»
«አዚሁ እኔ ዘንድ ነች። እናትየውም አለች፤ ባለቤቴ። እሷው ጋር ነው የምንኖረው። ሁላችንንም የምትጠር እሷው ነች።»
«ሌሎቹስ ልጆች?»
«አድያ! ያው እሷው ነች የምትረዳቸው። አንደኛው አሰራ ሁለተኛን ሊጨርስ ሲል ዘንድሮ አልሆነለትም። ተናደድኩ። አንደኛው ደግሞ የሚውለው ከሀብታም ልጆች ጋር ነው። መጥፎ መጥፎ ነገር እያመጡ ይህንን ሽጥልን ይሉታል። ታዲያ በጥቆማ ተያዘ። ወንጀሉን መፈፀሙን አመነ። ሌሎቹ ካዱ። ልጄ ልሙትልህ! ይኼው ያስያዝከኝ ጠበል (ሻዶን) ምስክሬ ነው። እነሱ አንድ ቀን ሳይታሰሩ በዋስ፣ በዋስ፣ በዋስ በዋስ... አድርገው በቀጠሮ፣ በቀጠሮ በቀጠሮ ሹልክ ሲሉ እሱ አንድ ዓመት ሙሉ ታሰረ»
«ከመንዝ የወጡት በልጅነትዎ ነው?»
«ገና በወጣትነቴ ነው። ይህች ሽበት እንኳን አልነበረችብኝም» (የክር ባርኔጣቸውን አንስተው በራቸውን አያሳዩኝ)
«ለምን ወጡ ከመንዝ?»
«ምቀኛ!! ምቀኛ ነው ያስወጣኝ»
«እንዴት ምቀኛ?»
«ኸረረረረ... አገራችን ጥጋበኛ ነው! እንድ እኛ አገር

ጥጋበኛ አለ ብለህ ነው? ሚስቴን አየህ ብሎ ነገር ነው። ተላዳቢ ነው! ታዲያ ሚስቴን መንገድ ላይ አድፍጠው ደበደቡብኝ። ኧኸ! ሰው አገሩ መቀመጡ ሊከበር ነውይ... በቃ ከዚያ ወድያ እልህ ያዘኝና ከብቶቼን ሸጬ ወጣሁ።»
«የዛን ጊዜ ወልደው ነበር?»
«ይህች አሁን የምትጦረኝ ልጅ ያኔ ታገለላ የምትሄድ ነበረች»
«ወንድም አህትስ የሎትም?»
«አገር ቤት ሁለት ታላቅ ወንድሞቼ አሉ»
«የርስም ታላቅ!?»
«አንግዲያስ!»
«ግን ለምንድነው ሁልጊዜ ጠዋት ተነስተው የሚመላለሱት?»
«ለዚሁ ላልኩህ»
«ለዱቱ? ከሞት ለመሸሽ?»
«አንደሱ አይባልም። ጊዜ ለማሳለፍ ነው የሚባለው»
«ግን እውነት ሞትን ይሸሻሉ?»
«ተው! ተው! ልጄ ስሙን አትጥራብኝ»
«እሺ ሲመላለሱ አይደክሞትም?»
«አይ አሁንስ ደክሞኛል። በዚች በታች በኩል አድርጌ እሄዳለሁ። ተላንትም በሳሪስ በኩል ነው አየተሽሎከለኩ የሄድኩት»
«ለምን መንገዱን ቀጥታ ይዘው አይሄዱም?»
«አንዱ! እንደዚያማ አይሆንም። ስንት ክላባ አለ፣ መኪናው አለ፣ አብዱ አለ። ቢተናከለኝስ? ያው መሆኑ አይደል? በሩቁ መሸሽ ነው የኔ ልጅ።»
«ለምን እዚህ አድረው አይሄዱም?»
«አላድርም። አድሬም አላውቅ። ለታቦት ንግስ ብቻ ነው የማድረው። ለጥምቀት። በቃ ከያ ወዲህ የትም አላድርም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን እንደማዮት ገና ጠንካራ ኖት፤ ገና ብዙ ዓመት...?»

«አያያይ! በቅቶኛል! በቃኝ።»

«እንዴ ጤኝኛ ከሆኑ ምነው ሰው 120ና 130 ዓመት ይኖር የለም እንዴ?»

«አይደለማ! ትንሽ የማልደብቅህ ነገር አለ። ጨጓራ በሽታ አለችብኝ። ሌላ ግን ጤኝኛ ነኝ። አይኔ በርግጥ ይህቺ የግራዋ አታይም። በቃኝዋ ነው ፋ÷የው። እውነቱን መናገር ጥሩ ነው።»

ከየት መጣ ሳልለው የሚያውቃቸው የሰፈር ልጅ «አባባ ሞት መጣ! ሞት መጣ!» ብሎ አስደነገጣቸው። የያዙትን ጸቦ በቁማቸው ለቀቁት። አንገታቸው ላይ ባለች አራፊ ጨርቅ ፊታቸውን እየሸፈኑ ካንድ ስርቻ ገብተው ሰመደበቅ ተጣደፉ።

«ተወኝ! ተወኝ! ተወኝ ልጅ! አፈር ልሁን የኔ ልጅ! ምላጩን ልብሳበት ተወኝ! በአፍህ ሌላ ነገር ተናገርበት!» ሲሉ ልጁን ተማፀኑት።

«ይሄን ያህል ከሞት ምን ያሸሽታል?»

«እንዴት!? ማን ወደሞት የሚሮጥ አለ የኔ ልጅ! አንተም አትጥራው፤ ደስ አይለኝም»

«ሰው'ኮ ያለቀኑ አይሞትም። ለምን ይፈራሉ?»

«ተወኝ ስልህ! ሲያነሱብኝ አልወድም፤ ማታ ይመጣል! ጠሞት ይመጣል፤ አይታወቅም። ተጠንቀቁ ነው ያለው ጌታ። ሌላ ሌላ ጨዋታ ሲያነሱብኝ ነው ደስ የሚለኝ»

«ግን ሰው መቼም ኖሮ ኖሮ መሞቱ ይቀራል?»

«አይይ! ተው፤ ተው፤ አታንሳው ስልህ፤ ማንሳት አይገባም»

የአምቡላንስ ጩኸት ተሰማ።

«ምንድን ነው ኡው... የሚለው?» አሉ አቶ ገብረየስ ጀሮአቸውን ቀሰሩ፤ አይናቻቸው ፈጠጡ።

«ምን መስሎዎት ነው?»

«ምን ይታወቃል? ስንት መዓት ጠሪ አለ። አሱኑ (ሞት) መምጫው አይታወቅም። ጌታም መምጫው አይታወቅም ያለው ለዚህ ነው»

«የማን መምጫ ነው የማይታወቅ?»

«አያይ! ሰሙን ምን አስጠራህ»

«ከአንግዲህ 10-15 ዓመት ቢኖሩ ደስ አይሎትም?»

«አሱማ... ጌታ ከፈቀደ መኖር ደስ ይለኛል።»

«እኒያ ከዱከም የሚመጡት ሰውዬ ከሞቱ ቆዩ?»

«አዎ በደርግ ጊዜ ነው ያረፉት።»

«አሳቸውም እንዲሁ ይህን ነገር አይወዱትም?»

«አሳቸው!? በስመአብ! አንድ ቀን አንድ ልጅ 'ሞት መጣ' ቢሳቸው 'አረ ወይዱ ልጆቼ ሞት ለማን ይበጃል?' አሉና እልም ብለው ሮጡ። ሞት ለማን ይበጃል ብለው ሮጡ።»

«ታዲያ ያው ሞቱ አይደል?»

«ደከሙዋ! ባይደክሙ አይዛቸውም ነበር። አይ ፍጥነት እንደ ጀት ነበር የሚበሩት»

«በመሸሽ ማምለጥ ይቻላል?»

«አህ! ታዲያስ! አዝጊዛር ጥቃት ይሰጥሃል። አሁን ሮቢላ ሲመጣ ዋሻ ውስጥ ተገብቶ ይዳናል። የዚያ ቢጤ ነው። ሮቢላ ከሰማይ መጥቶ ሊመታ ሲል ዋሻ ውስጥ ይገባል። ሰው ሚዳ ላይ አይሞትም። ሄዶ አዚያ ውስጥ ነው የሚሸሸገው።»

«ይሄማ የሚታየው ሞት ነው። የማይታየው ሞት ሲመጣስ እንዴት ነው የሚሸሹት?»

«አያያይ! ገብርኤል አያምጣው! ዓይኔን አጨፍናለሁ። (አይናቸውን አየያዙ) ድንገት ሞት ሲመጣ በህልሜ ያሳየኝ ይሆናል። ማን ያውቃል? በዓይኔ አያየሁ አልሞትም! በህልሜ ካሳየኝ ጭፍን ብዬ ነው የምጠበቀው። በህልሜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ነገር ያሳየኛል።»

አቶ ገብረየስ ለመሊድ ተቁነጠነጡ።

«ዛሬ በመኪና ነው የሚሄዱት። እኔ አሳፍሮታለሁ።»

«ኸረ ጉዴ! ምን በወጣኝ። እዚያ ውስጥ ምን መዓት እንዳለ ይታወቃል? ልጄ እድሜ ይስጥህ። ተባረክ። እንግዲህ ልሂድ። አንድ ቦታ ብዙ መቆየት ጥሩ አይደለም። በል አንተም መርቀኝና ልሂድ»

«ምን ብዬ ልመርቆት?»

«ዕድሜ ይስጥህ፣ ዕድሜ በጣም አድርጉ ይስጥህ፣ እግዚሃር ዕድሜና የሰው መውደድ ይስጥህ በለኝ ልጄ» አሉ።

«ግን ምነው ቸኮሉ?»

«ኸረ! መቸኮል ነው እንጂ! አንድ ቦታ ብዙ አትቆይ። ደግ አይደለም። መሊድ ጥሩ ነው። አያገኝህም፣ ትጠፋብታለህ። አንድ ቦታ ብዙ ከቆየሁማ ከመጣ ያገኛኛል። የለም፣ የለም፣ አሁንም ብዙ ቆየሁ ልሂድ የኔ ልጅ!»

ተነስተው ሲወጡ ሀፃናት «አባባ ሞት መጣ» እያሉ ጮሁባቸው። ጀሮአቸውን እያራገፉና አንገታቸውን እያርገፈገፉ መሸሽ ጀመሩ። በአጭር ቁመናቸው ፍንጥር፣ ፍንጥር እያሉ በሚያስገርም ፍጥነት ሮጡ። በቃ! አቶ ገብረየስ ሞትን አመለጡ። ትኩር ብዬ ሳያቸው አሳዘኑኝ። በአይኔ እየሸኘሁ በልቤ መረቅኋቸው።

ዕድሜ ይስጣቸው! አቶ ገብረየስ ከዚህች ዓለም ሀብት፣ ንብረት፣ ንዋይ... አልጠየቁም። ዕድሜ ብቻ ነው የጠየቁት። አንድዬ አባክህ ዕድሜ ስጣቸው!!



ስብዱ ቄሰርና ጌጁኛው

የቴሽግ ቢቅ

ስብሀት ገ/እግዚአብሔር

የጥንታዊት ሮማ ቄሳር ኒሮ ከ37 እስከ 68 አመተ ምህረት የኖረ ሲሆን፣ በአብደት ምክንያት አስራ አራቱ አመት የግዛት ዘመኑ ለዚጋዎቹ እንደ ሲኦልም እንደ ቅዠትም ነበር። በተለይ በክርስትና ሀይማኖት ታሪክ ውስጥ እንደ አርኩስ የሰይጣን ወኪል ይቆጠራል። የመጀመሪያውን የሮማ ጳጳስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስን፣ በ64 ዓ.ም በስቅላት አስገደለው።

ጴጥሮስም «እንደ ጌታዬ መሰቀል ክብሩ ይበዛብኛል። መልኩም ፈቃዳችሁ ይሁንና ቁልቁል ስቀሉኝ» ብሎ ለምኖ

t.me/OLDBOOKSPDF

እግሩ ወደ ላይ ራሱ ወደታች ሆኖ ተሰቀለ ይባላል።

«ኖኔ እሴት ወይም ታላቅነት በአርቲስትነቱ ነው እንጂ ንጉስ መሆኔን ከቁብ አልቆጥረውም» ይል የነበረው ኒሮ፣ የከተማዋ የድሆች ሰፈር የነበረው ጭርንቁሳም ጌቱ «አርቲስት ነብሰ-ን» ስላስቀየማት በምስጢር እንዲያቃጥሉት አዘዘ።

ቃጠሎውን እያየም በበገና ዝማሬ አወደሰው፤ ሰፈሩ በሙሉ አመድ ሲሆንለት፣ አመሀሉ ላይ «ወርቃማው ቤት» የተባለ እጅግ በጣም ትልቅና ውብ ህንፃ አሰራ።

የአብደትና የወንጀል የብልግና ዘመኑ ባጭሩ እንዲህ ይዘረዘራል።

ኒሮ አባት በሀያንኑ ስለሞተ እናቱ ከላውድዮስ ቄሳርን አገባች። እንጀራ አባቱም አልጋ ወራሹ አድርጎ ሾመው። እናቱ ቶሉ እንዲነግስላት ፈልጋ ክላውድዮስን በሚወደው የእንጉዳይ ወጥ መርዝ አብልታ ገደለችው። ኒሮ በአስራ ሰባት አመቱ ነገሰ። የእንጀራ አባቱን ልጅ አክታቪያን አገባ። በ59 ዓ.ም ያነገሰችውን እናቱን አስገደላት። በሰይፍ ሊገድሉዋት ሲሉ፣ ማህፀኗን እያሳየች፣ «ያንን ጉድ የወለደውን ይህን ማህፀን ውጉት!» አለች።

ቁጥሉ ሚስቱን አክታቪያን ፈታትና፣ ፖፒያ ሳቢናን ለማግባት ነፃ እንዲሆን ፈልጎ አስገደላት። ከጥቂት አመት በኋላ እቺኛዋን ሚስቱንም አስገደላት።

ብዙ ሴነተሮች (መኳንንት የምክር ቤት አባላት) ደፍረው «ይሄ ሁሉ ግድያክ አላስፈላጊ ነው» በማለታቸው ተገደሉ። በ65 ዓ.ም ኒሮን ለመገልበጥ ተጠንስሶ የነበረው ሴራ ስለተደረሰበት ሌሎች ብዙ መኳንንት ተገደሉ።

ጉድ የማያልቅበት ኒሮ ቁሳር ሮማውያኑ ላይ ከዘሙ የከፋ አልቂት ሊያደርስባቸው ይፈልግም ይችልም ነበር። አማልክቱ በመጠኑም ቢሆን ሲታረቁዋቸው፣ ፒትሮንየስ የተባለውን ጓደኛውን ላኩላቸው እንጂ። አንድ ምሳሌ እንጥቀስ

መሀል ከተማ ላይ የተሰራ፣ ከብ ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ነበረ፣ ኮሎሲየም (Colosseum) የሚባል። የልዩ ልዩ ስፖርት መጫወቻ ነበር፣ ሃምሳ ሺ ተመልካች የሚያስቀምጥ። ህዝቡ በጣም ከሚወዳቸው «ጨዋታዎች» አንዱ ግላድየተር (gladiator) የሚባሉ ሁለት ጉልቤዎች የመረጡትን መሳሪያ ታጥቀው የሚጋጠሙበት ነበር። አሸናፊው የተሸነፈውን ይገድለዋል። ወይም ይምረዋል። ይህን የሚወስነው ቁሳሩ ነው። ቀኝ እጁን ጨብጦ፣ አውራ ጣቱን ይቀስራል። እና ዙርያውን ይመለከታል ወደ ህዝቡ። የወደቀው ተፋላሚ ቢሸነፍም ድንቅ ግጥሚያ አሳይቶ ከሆነ ህዝቡ እቸቸውን ጨብጠው አውራ ጣታቸውን ወደ ላይ ያመለክታሉ። ምህረት ይገባዋል ማለታቸው ነው። ነሳስደሰታቸው ግን በአውራ ጣታቸው ወደታች ያመለክታሉ። ሞት ይገባዋል ማለታቸው ነው። ቁሳርም እንደ ህዝቡ በአውራ ጣቱ በማመልከት ሞት ወይም ምህረት ይፈርዳል።...

...ኒሮ ቁሳር ገብቶ ዙፋኑ ላይ ይቀመጥና፣ አረንጓዴ መነፅሩን ወደ አይኑ ያስጠጋል (አንደ ዛሬ ክቡሮ ጋር የተቆራኘ መነፅር ሳይሆን፣ በእጅ ወደ አይን የሚያስጠጉት ነበር) ዙርያውን በመነፅሩ ይመለከትና እንዲህ እያሰ ይነጫነጫል።

«ወዴትም ብመለከት የሚታየኝ ያው አረንጓዴ አፍንጫ ነው!»

ግላድየተሮቹ (ቀን ጉድሰላቸው በሰር ሚዳ የተማረኩ፣ እጣ ፈንታቸው ለባርነት የዳረጋቸው ናቸው) ስይፋቸውን በሰላምታ ወደ ቁሳር እያመለክቱ «ሰላም ላንተ፣ ቁሳር ሆይ! አሁን የሞቱት ሰላም ይሉሀል!» ይሉታል። ስሮማውያኑ ደስታ ተፋላመው ተሸናፊው ሲወድቅ፣ ኒሮ ዙሪያውን ይመለከታል። ህዝቡ በአውራ ጣቱ ምልክት ምህረት ከፈረደ፣ ኒሮ ሆን ብሎ በአውራ ጣቱ ሞት

t.me/OLDBOOKSPDF

ይፈርዳል። ድል አድራጊው የወደቀውን ተፋላሚውን ይገድለዋል። ህዝቡ በንዴት ሲጮህ ኒሮ አንጀቱ ይርሳል። የሚቀጥለው ፍልሚያ ሲያልቅ ህዝቡ ሞት ከፈረደ ኒሮ ምህረት ይፈርዳል።

እንድ ጊዜ ህዝቡ በንዴት ሲጮህ ኒሮ «ምነው ይሄ ህዝብ አንድ አንገት ብቻ በኖረውና በጉራዴ በቀላሁት» አለ።

«አምላክነትዎ ሆይ፣ ይቻላልኮ» አለው የነብር ዘቡ አሸኛ፣ «መውጫዎቹን በሮች ዘግተን አንድም ሳይተርፍ ልንፈጃቸው እንችላለን።»

ኒሮ በጥልቅ ፍስሀ ፈገግ ሲል፣ አጠገቡ ተቀምጦ የነበረው ጓደኛው ፔትሮንየስ «አይሆንም» አለ በቆራጥ ድምፅ።

«እንዴት አይሆንም?»

«አንተኮ ተራ ቂሳር አይደለህም። አርቲስት ነህ። ተውኔትህን ስትጫወት፣ በገናህን ስትደረድር፣ በሰረገላህ ስትሽቀዳደም፣ ይሄ ህዝብኮ ነው የሚያይህና በአድናቆት የሚጮህልህ።»

«እውነት አልክ፣ ፔትሮንየስ አንተ ባትኖረኝ ራስን ጉድ ሰርቼው ነበር።» አለ ኒሮ፣ የዘብ አዛዡን በግልምጫና በአሽ እንቅስቃሴ ወደዚያ እያባረረ።

ከአርቲስትነቱ ቀጥሎ፣ ኒሮ አስፖርተኛ ነኝ ባይ ነበር። ዋናው የሮማ አስፖርት ደሞ ጉብዝቹ በአራት ፈረስ በሚጎተት ሰረገላ ላይ ቆመው የሚሽቀዳደሙበት ነበር። ኒሮ የግሪክ አገር ግዛቶችን ለመገበኘት ሂደ።

አቴንስ እንደገባ አቴናውያን ሰሰረገላ ጉሽቅድምድም ጋበዙት። ተማክረው ሆነ ብለው ተቀደሙለት። ኒሮ በዚህ ድል ከመደሰቱና ከመኩራቱ የተነሳ «አቴናውያን ለመጪው አምስት አመት ከግብር ነፃ እንዳሆኑ ወስነናል» አለ።

«አቴንስ የአምላክነትዎን ሙሉ ለዘለአለም ያስታውሳለች» አሉት።

ስፖርታዉን ሲገዙኝ እዚያም በስረገላ አሽቅድምድም ድል አደረግና ከተማያቱ ለአምስት አመት ከግብር ነፃ ሆኝ። እንዲህ አደለ በሂደት አየተደመ የግሪክ ግዛቶቹ በሙሉ ለአምስት አመት ከግብር ነፃ ሆኑ።...

...ኒሮ ቀሳር ከዘዚህ የግሪክ ግዛቶቹ የበለጠ የሚወደው፣ እና ከማንም ሰው በላይ የሚያደንቀው ሰው ፔትሮንየስ ነበር። ለሱ ለብቻው ልዩ ሽመት ሸለመው። «ፔትሮንየስ አርቢተር» አለው። «ፔትሮንየስ የፋሽን ንጉስ» እንደ ማለት ነው።

ሰው በውርስ እና በየረት ተራ ዝናን ሲያተርፍ፣ ፔትሮንየስ በስራ ፈትነትና በግድ የለሽነቱ ብቻኛ ልዩ ዝነኛ ሆነ። ግን በችሎታ ጉደለት አልነበረም። ለምሳሌ. ቢቲንያ የተባለ አዝር አስተዳዳሪ ሆኖ ተሹሞ ችሎታውን አሳያቲል። በ62 ወይም በ63 ዓ.ም የሮማ ዋና (ቀደማዊ) ጎኖ ሆኖ ጭትህን በትጋት ፈፅሚል።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን Satyricon (ምፀቶች) የተባለውን የመጀመሪያውን ፈጠ ተዳጅ የአውሮፓ ልቦለድ የደረሰው ፔትሮንየስ አርቢተር ነው። ባለዘንጮቹ፣ መሳፍንቱ፣ እና መኳንንቱ የለሰም ፕዘምች ሮማውያን ሲዘሉ፣ ሲጠጡ እና መሲብ ሲፈፅሙ ሲያሳዮን እያስሳቀ እንድንተዘፍቸው ያጋብዘናል። ሲዘሉ ሲጠጡ ሰአቶች ያሳልፉና፣ ቁንጣን አስከደላቸው ይጠግባሉ። ከዚያ ተነስተው ወየተው፣ ለዚሁ ሲባል ወደ ተሰራው ክፍል ሂደው ያስታውካሉ። ባዶ ሆድ ሲሆኑ፣ ወደ ምግብ አዳራሹ ተመልሰው ድጋሚ አስከጠገቡ ይበላሉ ይጠጣሉ።...

ፔትሮንየስ አርቢተር እውነትም የፋሽን ንጉስ፣ የማሂኖና የማስዚኖ ሲት ነበር። አሱ ዛሬ አዲስ ልብስ ከለበሰ፣ በሳምንት ውስዋ የሮማ የዘነጣ ወጣቶችና

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉልማሶች እንደሱ ካልለበሱ እንደ ፋራ ይቆጠሩ ነበር።

ፒትሮንየስ ዘናጭ ብቻ ሳይሆን በጣም መልካ መልካምና ጨዋታው ወጉ እፍ የሚያስከፍት ስለነበረ፣ ክሊት አገልጋዮቹ እንዲ ፍቅር ያዛት። አስተዋይ ነውና ሁኔታዋን አይቶ «ምን ሆነሽል?» አላት።

«ከጌታዬ ጋር ፍቅር ያዘኛል።»

በመጀመሪያ አዘነላት። ግን አሷም ሲበዛ የተዋበች ስለነበረች ቀስ እያለ ወደዳት። ሀጋዊ ሚስቱ ሆነች።...

... አርቲከሉ ኒሮ ግጥም ወይም ተውኔት ሲፅፍ፣ ወይም ዜማ ሲፈጥር፣ መጀመሪያ ለፒትሮንየስ ያስማሞል። ፒትሮንየስ አርቢተር ጥሩ ነው ካለው ደስታው ሙሉ ያዘናል። አንዳንዱን የግጥም መስመር ፒትሮንየስ «እንደዚህ ብትሰውጠው ደሞ የበለጠ ያምራል» ሲለው ያለማመንታት ይለውጠዋል።

ፒትሮንየስ አርቢተር እንደዚህ በመወደዱ ምቀኞች ተማክረው የውሸት ወንጀል አላከከቡት። ኒሮ ቂሳርን ለመገልበጥ ሴራ እየጠነሰሰ መሆኑን የሚያረጋግጡ የውሸት መረጃዎችና ምስክሮች ያዘው ቀረቡ። ኒሮ ተታለለ፣ አመናቸው።

ፒትሮንየስ ሳይያገዝ በፊት ወዳጆቹ መጥተው መርዶውን ነገሩት። የቅርብ ወዳጆቹን አራት ጋበዘና ሲበሉ ሲጠጡ ሲያወጉ አመሹ። በመጨረሻም ፒትሮንየስ ተሰናበታቸውና ባኛው ውስጥ ገቡ። የእጅቱን ደም ስሮች በምላጭ ቆረጠ፣ ቀስ እያለ ሞት እንደ እንቅልፍ እንዲጠናደው።

ውቢቱ ሚስቱም «ያላንተ መኖር አያስፈልገኝም፣ ፍቀድልኝና ለዘለአለም አብሬህ ልተኛ» አለችው። ባኛው ውስጥ አጠገቡ ተቀምጣ አሷም የእጅቷን ደም ስሮች በምላጭ ቆረጠች። ፍቅረኞቹ ቀንጀምጭ በወዳጆቻቸው ተከበው አብረው አንቀላፉ።

በነጋታው ጧት መልእክተኞች መጥተው ኒሮን «እመላክትዎ ሆይ፣ ፒትሮንየስ አርቢተር ሞተ» ሲሉት

«ፒትሮንየስ ሞተ? ሳያስፈቅደኝ?... አስቲ የእንባ ብልቃጤን አቀብለኝ» አለ። ብልቃጡን ከፍቶ «ፒትሮንየስ እንዲት ጠብታ እንባ ላንተ፣ እንዲት ጠብታ ለኔ» አለና ከአይኖቹ ሁለቱን ጠብታ እንባ ወደ ብልቃጡ ጨምሮ ዘጋው።

«እምላክነትዎ፣ ፒትሮንየስ የላከው ደብዳቤ ይኸው» ኒሮ በማህተም የታሸገውን ደብዳቤ ከፍቶ ቢያነበው እንዲህ ይላል፦

«ኒሮ፣ ያህና ሁነህ ቀኑን ሙሉ ሲደብሩኝና ሲያሰለቹኝ የኖሩትን አልባለ. ግጥሞችህን፣ ተውኔቶችህንና ዜማዎችህን ከመስማት ስለገላገሉኝ አማልክቱ ምስጋና ይግባቸው። ቻው - ቻው!»

የአብዱ ቂሳርና የፋሽኑ ሊቅ ጓደኝነት እንደዚህ አከተመ።

መጠጥና

t.me/OLDBOOKSPDF



ግርማ ጉደታ

እኔስ እሰኝ ፍቅር

እንደልብ ምቱ – ሕይወት የሚነዝር
እኔስ አሰኝ ፍቅር – አንጀቴን የሚያስር
ዓይኔን የሚያስነባ
ሆዴን የሚያባባ
እግሬ በመፈለግ – ከሌላ የማይዞር
ባለበት የሚረግጥ – ወንቶ የሚዳክር
አይኔ ሌላ ሽቶ – ጉልቶ ያልፈጠጠ
በዝሙት ለመጥቀስ – ስሌላ ያልቋመጠ
እኔስ አለኝ ፍቅር
አንጀቴን የሚያስር
እጄ የጥላቻ – ዱላ ማይሠነዝር
የሚያቀርብ የሚያቅፍ – ባንድ ሚያስተሳስር
እኔስ አለኝ – የፍቅር ሀሊና
ሲንቁት ፈቃዱን – ታግሶ ሚፀና



የችስችዩ ስረፍት

ማክሲም ጐርኪይ
(ትርጉም) መኩሪያ መካሻ

ይህን ማስታወሻ የፃፍኩት አሌይዚ ከተማ ሆኜ ነው። በጊዜው ሊዮ ቶልስቶይ ጋስፐሬ ውስጥ ይኖር ነበር። ያኔ በጣም ታምሚ ነበር፤ ጋላ ላይ ግን አገገምኩ። ማስታወሻዎቹ በጥንቃቄ ያልተፃፉና በተለያዩ ብጭቅጫቂ ወረቀቶች ላይ የሰፈሩ ናቸው። የተወሰኑትን ሰሞኑን አገኘኋቸው። ከዚያም ሊዮ ቶልስቶይ ወደ ያስናይ ፖሊያና ሄዶ ከዚህ ዓለም «ጡተለየን» ጊዜ ያደረብኝን ስሜት ባማስታወሻዎቹ አካትቼያለሁ። አንዲትም ቃል ነሳስተካክልኩም፤ እንዳለ አቅርቢያቸዋለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያስገርመው አጀቡ አሉት። አያምሩም፣ ያባበጡ ስሮቹ እጀቹ ላይ ተጋድመው ልዩ መግለጫ አላቸው። የፈጠራ ኃይሉን ያሳያሉ። ሲኦ ናርዶ ዳቪንቺም አንደዚህ አይነት እጀት ሳይኖሩት አልቀረም። በዚህ አይነት እጅ ማናቸውንም ነገር መስራት ይቻላል። አንዳንዴ አያወሬ ጣቶቹን ያንቀሳቅሳል፣ ቀስ ብሎም ይጨብጣቸዋል። ከዚያም በድንገት ይዘረጋና የረቀቁና ክብደት ያላቸውን ቃላት ይወረውራል። ከአማልዕክት ጋር ይመሳሰላል። ሳቫአፍን ወይም የኦሎሚፕያድ አማልክቶችን ግን አይመስልም። «በወርቅ ወንበር ላይ የተቀመጠ» የሩሲያን አማልክት መስሎ ይከፈላል። ከአማልክቶቹ ሁሉ ሀያል ባይሆንም ብልጣብልጥ የሆነ አማልክት ነው።

* * *

ከሱለር (በወቅቱ የነበረ ደራሲ ነው) ጋር ያለው ግንኙነት ለሴቶች እንደሚደረግ እንክብካቤ ያህል ነው። ቹኮቭን በለርበኝነት መንፈስ ይወደዋል። በዚህ ፍቅር ውስጥ የፈጣሪነት ኩራት ይታያል። ሱለር ግን ስሱነትን፣ ዘላቂ ወዳጅነትንና አድናቆትን ያሳድርበታል። በዚህ ስሜት ውስጥ ባልቴቶች ለጉጉቶች፣ ለውሾችና ለድመቶች ያላቸውን ፍቅር የሚያሳይ ጥቂት አስገራሚ ስሜት አለ። ሱለር - የሚያስደንቅ የሌላ ዓለም፣ ያልታየ ዓለም ወፍ ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በመቶዎች ቢቆጠሩ ነው። እንደነዚህ ያሉት የክፍለ ሀገር ከተማን መልክና መንፈስ መለወጥ ይችላሉ። ሱለርን መውደድ ቀላልና አስደሳች ነው። እኔ እንደተመለከትኩት ሴቶች ጥንቃቄ አያደርጉለትም። በዚህ ጥንቃቄ ጉድለት ውስጥ የተደበቀ ጥንቃቄ አለ። ሱለር - አይተማመንም። ነገ ምን ያደርግ ይሆን? ምናልባት ቦምብ ይጥል ይሆን ወይስ የትራክተር ዘፋኙን ይቀላቀል ይሆን? የእሱ ኃይል መቼም - የሶስት ክፍለ ዘመን ያህል ነው። የህይወት እሳት ህልቆመሳፍርት

የለውም ይባላል። የእሱ ነገር ከጋለ ብረት በሚወጣ ሙቀት በላብ የመደፈቅ ያህል ነው።

ቶልስቶይ አንድ ቀን ሱለርን ተቀየመ። በተዘበራረቀና በሚንቀለቀል ስሜት ሱለር ስለ ግለሰብ ነፃነት ይከራከራል። ሊዮ ቶልስቶይ በዚህ ጊዜ ስሜቱ ይነካል። ሱለር እሱን በሙሉ ሰለ አናርኪዝም ጠቃሚነት እያነሳ ይፈላሰፋል።

«ኦህ! ሱለር አቁም፣ ሰለቸኝ» - በማለት ሊዮ ቶልስቶይ በብስጭት ተናገረ። አንደ ጉጉት አንዲት ቃል የዚህ ነፃነት፣ ነፃነት፣ ትላለህ። የታሰ ውስጣዊ ትርጉሙ? ባንተ ትርጓሜ ነፃነትን አገኛለሁ ካልክ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ይታይሃል? በፍልስፍናዊ ይዘቱ መጨረሻ የሌለው መቀመቅ ውስጥ ትወድቃለህ። በህይወትም፣ በተግባርም ሰነፍና ለማኝ ትሆናለህ። በአንተ አመለካከት የአስተሳሰብ ነፃነት ከሰዎችና ከህይወት ጋር የሚያስተሳስር ይመስልሃል? ተመልከት - ወፎች ነፃነት አላቸው የራሳቸውን ጉጅ ይቀልሳሉ። አንተ ግን ጉጅ መቀለስ አንኳ አትችልም፣ እንደ ውሻ ቅንዝረ - ፍትወትህን የትም ለመፈፀም ትፈልጋለህ። በጥልቀት አስብ፣ በትክክለኛ ትርጉሙ ነፃነት ማለት ባዶና ወሰን የለሽ መሆኑን ታያለህ፣ ትረዳለህ።»

በንዴት ያኮርፍና ለደቂቃዎች ዝም ይላል። ቀጥሎ ደግሞ በገሃታ «ክርስቶስ ነፃ ነበር፣ ቡደሃም ነፃ ነበር። ሁለቱም የዓለምን ሃጥያት በራሳቸው ላይ ተቀበሉ። በፍላጐታቸው የዓለማችን ሀይወት ምርኮኞች ሆኑ። ቀጥሎስ - ማንም አልተከተላቸውም፣ ማንም። አንተ፣ እኔ - የታሰን?! ሁላችንም ከትርቦቻችን ካለብን ግዴታ ለመሸሽ ነፃነትን እየፈለግን ነው። እነዚሁ ግዴታዎች ናቸው እኛን ሰዎች ያደረጉን። እነዚህ ስሜቶች ባይኖሩ ኖሮ እንደ አውሬ በኖርን ነበር ...»

ይስትና መልሱ፡-

t.me/OLDBOOKSPDF

«በነገራችን ላይ እንዴት በተሻለ መንገድ እንደምንኖር እየተከራከርን ነው። ንግግራችን ይህ ቀረው የሚባል አይደለም። ከእኔ ጋር ይኸው ተጣልተህና አኩርፈህ አፍንጫህ ቢጫ መስሎአል። አትደበድቦኝም፣ ሊላው ቀርቶ አትቆጣኝም። በትክክል ግን አንተ ነኅ መሆንህን ተረድተኸው ቢሆን ኖሮ ለእንዴና ለመጨረሻ ትገድለኝ ነበር።»

* * *

እንዴ የፃፍኩትን እጥር ልብወለድ አነበብኩለት። ከእንጀቱ ሳቀና ስለ «ቋንቋ አጠቃቀምማ» አሞ ጋገሰኝ።

«የቃላት አጠቃቀምህን ግን አልቻልክበትም። ሁሉም ገፀ-ባህርያትህ በሚያስደንቅ ችሎታ ይናገራሉ። በህይወት ግን የጅልና ተራ ናቸው - ምን ለማለት እንደፈለጉ በቀላሉ መረዳት አይቻልም። መልካም ገፀ-ባህርይ ችሎታውን ወዲያው አያላይም፣ ምክንያቱም እያስፈለገውምና። ወደ ጅል ሰው በቀላሉና በግልፅ መቅረብ እንደሚያስፈልግ ያውቀዋል። በግልፅ ከፊት ለፊቱ ስትቆም ደካማ ጉንህን ወዲያው ያየዋል። ... ግልብና ታማኝ ያልሆነን ደራሲን ማንም አያነበውም። ለማንም አጅህን አትስጥ፣ ማንንም አትፍራ - ያኔ ሁሉም ነገር መልካም ይሆንልሃል ...»

* * *

ስለ አምላክ፣ ስለ ገበሬዎችና ስለ ሴቶች አውርቶ አይጠግብም። ኪሃየበብ ለአርሱ ባዳ እንደሆነ ሁሉ አልፎ አልፎና በጥቂቱ ነው የሚያወሳው። በእኔ አመለካከት በሴቶች ላይ ግን ጥላቻ አለበት። ሊቀጣቸው ይፈልጋል። ልክ «በእና ካሬኒና» መፅሀፉ ውስጥ እንዳለው ጥላቻው ከፍተኛና ቀዝቃዛ ነው ...»

* * *

ለእሱ መቼም ገበሬዎች የተለየ ጠረን አላቸው። ሁሉ ስለ እነሱ ያስባል፣ ሳያስበው ስለ እነሱ ያወራል።

* * *

አስቸጋሪና ፈታኝ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይወዳል፡-

- ስለ ራስህ ምን ታስባለህ?
- ሚስትህን ትወዳታለህ?
- በአንተ አመለካከት ልጅ ሊቭ - ጉበዝ ነው?
- ሶፊያ አንድሬቭና ደስ ትልሃለች?

አሱን መቼም መዋሸት አይቻልም። አንድ ቀን ደግሞ «ለመሆኑ ትወደኛለህ?» አለኝ ...

* * *

ትላንት ምሽት ከጀኔራልዋ ሚስት ከኮርኔ ጋር የነበረንን ጥል ስነግረው አንባውን አያዘራ፣ ደረቱ አስኪታመም በሳቅ ፈነዳ።

በአካፋ! በ ... አካፋ? አንዲያው በ ... በሰፊው አካፋ?!

ትንሽ እረፍት ወሰደና በትኩረት፡-

«ጥሩ አድርገህ መተሃታል፣ ሴላ ቢሆን ጭንቅላታን ይፈጠፍጥ ነበር። በጣም አያዘንክላት ነው። ለመሆኑ አንደፈለግችህ አውቀሃል?

- አላውቅም፣ አላስብምም ...
- አንዴት ባክህ! ግልፅ አኮ ነው።
- አንዲያ አልነበረማ ኑሮዬ
- አንዲያ አትኑር አንጂ - ያው ነው! አንተ ለነገሩ አንደምትታየው ሴታውልነት የለብህም። ሴላ ወንድ ቢሆን ግን ቤቱን ወርሶ፣ አቅፏት ይተኛ ነበር።

ጥቂት ዝም አለና፡-

«አስቂኝ ሰው ነህ። አትቀየመኝና - በጣም አስቂኝ ሰው፣ በጣም በሚያስደንቅ ሁኔታ ክፉ ሰው መሆን ስትችል ግን ደግ ሰው ነህ። አምን፣ ክፉ መሆን ትችል ነበር። ጠንካራ ነህ - ይህ ደግሞ መልካም ነው ...»

ጥቂት ዝም ብሎ አንደገና የሚከተለውን አከለ፡-

«እኔ እንደሚገባኝ ጭንቅላትህ ውስብስብ፣ ልብህ ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዋቂ ነው ... አም፣ ልብህ አዋቂ ነው!»

መግለጫ፦ ካዘን ውስጥ ስኖር የጀኔራል ሚሲት የነበረችው የኮርኔ ዘበኛና አትክልተኛ ነበርኩ። ኮርኔ ፈረንሳዊ ፊት ወጣት ሴት ናት። ሞንዳሳዋ ኮርኔ አስገራሚ የሆኑ ቆንጆ ዓይኖችዋ እረፍት የላቸውም። ሁሌ እንደተራቡ ናቸው። አስክታገባ ድረስ ኑጋዴ ወይም ባለምግብ ቤት ሳትሆን አትቀርም፤ «ለደስታ የተፈጠረች ጉብል» እንደሚባለው ናት። በጥዋቱ ትደነብቅና ወደ ጊቢው ወይም ወደ አትክልት ስፍራው ትወጣለች። ብርትኳንማ ጋዎንዋን ከላይ ደርባ የታታሮችን ቀይ ጫማ ትጫማለች። ቸምቸሞ ፀጉሯም ናት። ፀጉሯ በጥንቃቄ ያልተበጠረ በመሆኑ ጉንጮችዋና ትከሻዋ ላይ ይበታተናል። ሽጋ ወጣት ናት። የፈረንሳይን ዘፈን እያንጎራጉረች ግቢው ውስጥ ትዘራለች። እኔ እንዴት እንደምሰራ አጥብቃ ትከታተላለች። ወደ ኩሽናው መስኮት ጠጋ ብላ «ፖሊን አስቲ የሆነ ነገር ስጠኝ» ትለዋለች።

«የሆነ ነገር» - ያምትለው የታወቀ ነገር ነው - አንድ ብርጭቆ ቪኖ በበረዶ ...

በታችኛው የቤቱ ክፍል ውስጥ ሶስት ሴጣ ሴት ልጆች ተክራይተው ይኖራሉ። ጀኔራሉ አባታቸው ወደ አንድ ስፍራ ሄዷል። እናታቸው ሞታለች። ኮርኔ ሴቶቹን አትወዳቸውም፤ ታሰቃያቸዋለች፤ ተንኮል ትሸርብባቸዋለች። ሩሲያንኛ ቋንቋ በሚገባ የማትችለው ኮርኔ ስትሳደብ ግን እሳት የላሰች ነች። ከገራሞቹ ሴቶች ጋር ያላት ግንኙነት አያስደስተኝም። ሴቶቹ አገለውና ደንግጠው መከታ አልባ ሆነዋል። አኩለ ሱን ላይ ሁለቱ ሴቶች አትክልቱ መሀል ሲዘዋወሩ ኮርኔ በድንገት ከቮፍ አሰች። ውሻው እነሱ ላይ መጮህ ጀመረች። ከአትክልቱ ውስጥ አባረረቻቸው። ሴቶቹ ግን ገሸም ብሰው ጥለዋት ሄዱ። እሷ ግን በሩ ላይ ቆማ ፈረሶችን እንኳ

በሚያስደነብር ተራ የሩሲያ ቃላት ሞለጨቻቸው። ከቁጣዋ እንድትበርድና ሴቶቹን ለቀቅ እንድታደርጋቸው ለመንኳት። እሷ ግን እያንባረቀችብኝ «አላውቅህምና ነው፣ ሲመሽ እየጠበክ በመስኮት ትዘል የሰ ...» አሰኘኝ።

በጣም ተናደድኩ። ትክሻዋን ጨምድጀ፣ በሩን አስለቀቅኳት። ግን ከእጄ እፈተለከችና ወደእኔ ሀራ ጋዎንዋን ወረወረች፣ ሽሚዟን ወለቅ አድርጋ «ከእነዚህ ምናምቴዎች እኔ እሻላለሁ!» ብላ ደነፋች።

በዚህ ጊዜ ፍፁም ተከንኩ። ወደራሴ ሳብኳትና በያገኙት አካፋ ከወገቧ በታች ገረሰርኳት። በሩን አልፋ ወደ አልፍኙ ውስጥ ገባችና ሶስት ጊዜ - «አ!አ!አ!» አያለች ጮኸች።

ከዚህ በኋላ ከባለሚልዋ ክፖሊን አጅ መታወቂያዬን ተቀብዬ፣ ዕቃዬን ሸንቀፌ በአልፍኙ ውስጥ አልፌ ወጣሁ። በዚህ ጊዜ በመስኮት ላይ ሆና ቃይ መሀረብ በእጅዋ ይዛ «እንዳንት ላለው መናጢ ፖሊስ አልጠራም! ብትመለስ ይሻልሃል ... መፍራት አያሻም ...» ስትል ተንጣጣች።

* * *

ቶልስቶይ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ካርታ ይጨወታል። የሚጫወተው ከልብና በሞቅታ መነፈስ ተሞልቶ ነው። ካርታ ሲቀበል ወርችን በአጅ የሚይዝ እንጂ ግውዝ ካርታ የሚወስድ አይመስልም።

* * *

«ማወቅ ማለት ምንድነው? ይኸው እኔ ቶልስቶይና ጀራሲ መሆኔን አውቃለሁ። ሚስትና ልጆች አሉኝ። ሽበቶ ፀጉር፣ አስቀያሚ መልክ፣ ዒማም ነኝ - ይህን ሁሉ በመታወቂያዬ ላይ ይፅፉሉ። ስለ ውስጣዊ ልቤ ግን መታወቂያ ላይ አይፅፉም። ስለዚህ እኔ አንድ ነገር አውቃለሁ - ልብ ለአግዚአብሄር መቅረብን ትፈልጋለች። አግዚአብሄር ምንድነው? አግዚአብሄር የመንፈሴ አንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

አካል ነው። ቢቃ ይሽው ነው። መመራመርን የተማረ ሰው ሰማመን ይቸግረዋል፤ በአግዚአብሄር መኖር የሚቻለው በእምነት ብቻ ነው። ተርቱላን እንዳለው ማስብ ክፉ ነው።»

* * *

ከቼኮቭ ጋር በስልክ ...

ወሬ ለእኔ መልካም ዕለት ነው። መንፈሴ በጣም በመደሰትዋ አንተም እንድትደሰት ፈልጌያለሁ። በተለይ - አንተ፣ አንተ በጣም ጥሩ ሰው ነህ፤ እጅግ በጣም ጥሩ! -»

* * *

ሊዮ ቶልስቶይ ሞተ።

ቨተላክልኝ ቴሌግራም ላይ የተለመደ ቃል ሰፍሯል - «እርፏል» ይላል። ይህ ቃል ልቤን ወጋው። በቁጭትና በናፍቆት ሶሚት ጮህኩ። ይሽው አሁን በግማሽ አእምሮና ባልሰከነ መንፈስ እንዴት እንዳወቅሁትና እንደማየው አስባለሁ። አያስጨነቀኝ ስለእሱ መናገር ያምረኛል። የመቃብር ስፍራው እንዴት እንደነበር አስታወስኩ። ተጋድሟል። በጠበበው ጉድጓድ ውስጥ እንደ ተጠረዘ ድንጋይ ተዘርግቷል። ቡትንገረገገው ዊሙ መሀል ሰማንም ባዳ የሆነ - ሽፍጠኛ ፈገግታ ይታያል። እጆቹ፣ አፉን እኒያ እጆቹ ተረጋግተው ተጣምረዋል።

እኒያን ስል ዓይኖቹን አስታውሳለሁ። የጣቶቹን እንቅስቃሴ፣ ከእሱ ጋር የነበረኝን ቆይታ፣ ጨዋታው፣ ተወዳጅ ወንዳወንድ ቃላቶቹ፣ በምንም አይነት መፈረጅ የማይቻለው ድምፁ ይታወሰኛል። ህይወት የዚህን ሰው ሁለመናውን እንዴት አቅፋ ደግፋ እንደያዘች በእዝነ ልቡናዬ ይመጣብኛል። ወሰን የለሽ ችሎታውና አስፈሪ ወንዳወንድ ገፅታውም እንዲሁ።

በአንድ ወቅት ማንም ሰው አሱን ተመልክቶ በማያውቅ

መልኩ አየሁት። ወደ ጋስፐር የባህር ዳርቻ ሂድኩኝ። በፋልማው ድንጋዮች መሀል ተቀምጧል። ያስባል። በእጭር አጀመ፣ በዙብ ሰውነቱ ላይ አተኮርኩ። አገዛኑን እያሻሸ ተቀምጧል። በጣቱቹ መሀል ብራማ ሂመ ይፋተጋሉ። ዓይናቹ ወደ ሩቅ፣ ወደ ባህር አማትረዋል። ዕለቱ ዝብርቅርቅ ያለ ነው። የደመናው ጥላ ድንጋዮቹን አሞተመላለሰ ያስብሳል። ከድንጋዮቹ ጋር የሽማግሌው ገስታ እንዴ ሲፈካ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ያጠላበታል ... ባህሩ የህይወቱ አንድ አካል ሆኖአል። በሌጣው መሬት ላይ ያጠላው ቁጋግ፣ የባህሩ ሞገድ፣ የደመናውና የጥላው ሽርሽር በድንጋዩ ላይ ይንሳፈፋሉ። በደፈናው ሽማግሌው የዚህ ሁሉ እምብርት ሆኖ ስፍራውን ምትሀታዊ የተፈጥሮ ድባብ ወርታል። በአንድ ቡተወሰነ ፍጥነት ልዩ ሰሚት ተሰማኝ። አሁን ብድግ ብሎ እጅን ቢያወራጭ ባህሩ ተነስቶ አካባቢውን የሚሸፍን፣ ቋጥኙቹ እየተንጋገ የሚጮሁ፣ ዙሪያ ገባው ሁሉ የሚገለባበጥ፣ የሚጮህ፣ እያንዳንዱ በየቋንቋው ስለ ራሱ እያወራ በእሱ ላይ በባላንጣነት የሚነሳ መሰለኝ። በወቅቱ የተሰማኝን በቃላት መግለፅ አስቸጋሪ ቢሆንም በውስጤ ግን ፍርሃትና ጭንቀት ተከምሮ ቀስፎ ወጋኝ። «ይህ ሰው በዚች መሬት ላይ እስካለ ድረስ ባይተዋር አይደለሁም» የሚል ስሜት አበረታታኝ።

ሽማግሌውን ከሠሰቡ እንዳላገኘነው ብዙ ኮሽታ ሳላሰማ ወደኋላዬ አፈገፈኩ። ዛሬ ግን ይሽው እግለማውታ ሆኜ መቅረቱ ይሰማኛል። አፅፋለሁ። አሰቭሳለሁ። በህይወቱ ይህን በመሰለ ሰያኸር ሰገናኝር ባስችገረ መራራ ሀዘን ተውጬ አላውቅም። አላውቅም፣ አወደው ነበር እንዴ? አዎ፣ ሰመሆኑ ለእሱ ፍቅርም ሆነ ጥላቻ ቢኖረኝ አስፈላጊ ነውን? ውስጣዊ ነፍሴን በማነሳሳት፣ እኔን ሀልመኛ በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው። አልፎ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

አልፎም የሚተመገበዘ ጥላቻን በመጫር ጭምር በውስጣ
ስፍራ ይሏል። በድንገት ከእልፍኝ ውስጥ ወይም ከእንድ
ጥጋት ወጣ ብሎ ሲጓዝ እንዴት ያለ ሰው ነበር? አጣር
ባለ፣ በቀለለና መሬት ላይ በመንዝ ልምድ ባለው የሰው
ልጅ ፈጣን አካሄዱ እየተራመደ በትላልቅ ጣቶቹ ወገቡን
ይዞ ለደቂቃ ይቆማል። ብፈጣን እይታው አካባቢውን
አጣርቶ እሺስ ነበር ሲመለከት - «እንደምን አሰህ?! ይላል።
በዚህ ጊዜ እኔ «እንደምን አለህ - ሰላምታው ሰእኔ ታላቅ
እርካቱ፣ ለእንተ ግን ከቁበ የሚገባ ባይሆንም - እንደምን
አለህ» አለዋለሁ ሁሌም።

በአካሉ ትንሽ መስሎ ይታያል። ወዲያው በአሱ
አንጣር የቆመ ሰው ይለሰምናል። ወንዳወንድ ሊሙ፣
ሻካራ ግን የተለየ እጅ፣ ዘጥሶ ልብሱ ይህ ው-ጭያዊ
ዲምፈራትነት ወዲያው የብዙዎችን ቀልብ ይስርቃል።
የሩሲያኖች የነጠር፣ የዘውትር ልምድ ...

- «ደስ አልልህም እንዴ?» ሲል ጠየቀኝ።

- «አዎን! ደስ አትልም» ብሎ መናገር ያስፈልገኝ
ነበር።

- መልሶ «አትወደኝም እንዴ አንተ አኔነ?» - «አዎ!
ዛሬ አልወድህም» አልኩት።

ስጥያቄ ወድኋላ አያልም። ለመልስ ግን ቱጥብ ነው
- አዋቂ ሰዎች ሁሌም እንደሚያደርጉት ሁሉ።

ስላለፈው ነገር በሚኖም መልኩ ይተርኳል፣ ከሁሉም
በላይ ስለ ቱርጌኔቭ። ስለ ፉዩት በሆደባሻነት፣ በሚያስት
መልኩ ሲገልፅ ስለ ኒክራሶቭ ያለው አይታ- ግን የተዘዘዘ
በዮርማሬ የተሞላ ነው። ሌሎች ደራሲያን ባጠቃላይ የርስ
ልጆች እንደሆኑ፣ አርስ አባት እንደሆነ ሁሉ
ድክመታቸውን በሞላ ጥርት አድርገ ያውቀዋል።
አስቀድሞ መጥፎ ጐናቸውን አጠንክሮ ይተቻል።

ኦስፐንስኪ የሚባለው ደራሲ ቡቲላ ድንቁ የሚፈውን

ድርስት አየተቸ ምንም ተስጥኦ እንደሌለው ሲያስረዳ
ነበር። እኔ በተገኘሁበት ስፍራ ደግሞ ለቼንቭ - «ይህ
ነው ደራሲ! በእትሙ ይስተየብስኪን ያስታውስኛል፣
እርግጥ ይስተየብስኪ ፖለቲካ አጠቢይል፣ ግን በሚማርክ
ስልት ዕቄል። የዚህ ግን ተራና ግልፅ ነው። እግዚሞሀርን የሚያምን ቢሆን ናሮ የቤተክርስቲያን ደዋይ
መሆን በቻለ» አለ።

- «ታዲያ ከዚህ ቀደም የቱላው ደራሲ ችሎታ የለውም
ብለህ ለምን ተናገርክ?»

ዓይኑን ሊሙ ውስጥ ለመደባበት አየሞከረ «ሞራ
አልፈልም» ሲል መለሰ። «ምን ቋንቋ አለው? ከታላቁ
ይልቅ ታለ አጋኖው ይዘባል። ተስጥኦ ማለት - ፍቅር
ነው። የሚያፈቅር ሁሉ ተስጥኦ አለው። ተመልከቱ
ፍቅረኞሞችን - ሁሉቸም ተስጥኦ ያላቸው ናቸው።

ስለ ዶስተየብስኪ ግን አምቡላም አያወጋም።
እንዳንዱም ስሙን ሲያወሳ አይፈልግም።

ላበኩበን ለምን እንደሆነ እንጃ አያዝቡትም፣ ግን
የተዋጣለት ደራሲ ነው። «ለመሆኑ አንብበኸዋል?»

«አዎን በጣም አመደዋለሁ» - «ቡተለያ ቋንቋው»

«ቋንቋው ተአምረኛ ነው። አሱን መውደድህ የሚገርም
ነው። አንተ ብቻ ... ሩሲያዊ ያልሆንክ ሰው ነህ፣ አንተ
ሩሲያዊ አስተሳሰብ የለህም - ይትርታህ አንዲህ በማለቱ
አስተነሞከህ አንዴ። እኔ ስለሽመገልኩ ሃጢአውን ሰነ ሰዞኛ
መረዳት ያቸግረኛል። ግን አንደሚመስለኝ ሰነ ሰዞኛ
ሩሲያዊ አደደለም። አሁንማ ለማን አንደሆነ የማይታወቅ
ለዋት ያለ ሰነ ግዋም መዛር ጀምረዋል። ሰነ ግዋምን
ከፑሽኪን፣ ከቱትቼቭ፣ ከሼንሸን መማር ያስፈልጋል»
ወደ ቼንቭ ዘወር ብሎ ደግሞ «አንተ ግን - ሩሲያዊ ነህ
አሠ ወላም፣ ወላም ሩሲያዊ ነህ።»

ቼንቭን አየደባበሰው ትከሻውን አተፈ። ከዚያም

t.me/OLDBOOKSPDF

ወሬውን ሰውም ስለ ቤቱና ስለ ታታሮች ማውራት ቀጠሉ።
ፍቅቭን ሁሌም ቢሆን በጣም ይወደዋል። ፍቅቭን ከአስር ዓይት ይመስከተው ነበር። ከአለታት አንድ ቀን ፍቅቭ ከአሌክሳንድራ ልቨቭና ጋር በመናፈሻው ውስጥ ሲንሸራሸር ቶልስቶይ ታሞ ነበር። በረንዳው ላይ ከተቀመጠበት ተነስቶ እየተከተላቸው በግማሽ ድምፅ ሕንዴት ያስ ውብ፣ አስደሳች ሰው ነው። አትሀቱ ርዕስ የሰፊነቱ፣ ጠቢቅ እንደ አመቤቶች ነው! ሲራመድ እንደ እመቤቱ። እንዲያው ተስምረኛ ሰው!» አለ።

* * *

ልጅር፣ ፍቅቭ፣ ሰርጌይ ልቨቪችና አንድ ሌላ ሰው መኪና ውስጥ ተቀምጠው ስለ ሴቶች ያወጋሉ። በፀጥታ ሲቆጣጠሩው ቆየና በድንገት ሕኔ ስለ ሴቶች አውነትን ያምናሰው በአንድ እናፅ መቃብር ውስጥ ቆሜ ነው. መቃፅ ውስጥ እጄንና ከጭኑን ላዩ ላይ እከድናለሁ። ስደም - ውሳኔኝ እሁን» አላታለሁ። ይሀን ሲናገር ሜይን ደፍጣ ያለው ስለነበር ሁሉም ሲደቂቃ ትንፍሽ ሳይሉ ደንገጡ ሪሩ

* * *

በአንድ የበደይ ወር ሞስኮ ውስጥ በፀጥታማው ጠባብ ጉዳና አንቶቭ ነበር። አንዲት ባልቴት ተመለከትኩ። ይመንገዱ ጥጋት ላይ ተጋድማለች። ጠምቢራዋ ዘሯል። በጨቀየው ስፍራ ላይ በጀርባዋ ተንጋላ ትንከባለላለች። ደስም መነሳት አልቻለችም። አንዲያው በቀዝቃዛው ጭቃልቅልቅ ውስጥ ትወራጫለች።

ቶልስቶይ ሲመለከታት ደነገጠ። ግጥም አድርጉ ዓይኑን ጨፈነ። ጭንቅላቱን ይዞ በለሆሳስ «አዚህ ቁጭ በሊ ቡሞ አስደንጋጭና መራር ነገር ነው - የሰከረች ቤሴቱት» አለ። እኔ ደጋፌ ላነሳት ብዙ ሞከርኩ። አልቻልኩም፣ ራሴው ተጣጠፍኩ። ተጨመላልቃ እንደ

ቋጥኝ ተከብዳለች። መቼም አሷን በአጯ የነካ በወርም እጯን አጥቦ አያጠራም። አሰቃቂ ነው! አንድ ገው የፈካ፣ ዓይኑ ሰማያዊ የሆነ ወጣት አጠገቧ ተቀምጧል። ቡጉጮቹ አንባ ይጉርፋል። ልጯ በደከመ ጉልበት «ማም ... ማምዬ ... ተነሺ አንጂ ...» አያለ ይጮትታታል። አሷ ግን አየተገላበጠች፣ ጭንቅላቷን ብድግ ታደርግና ተመልሳ ቆሻሻው ውስጥ ትዘፈቃለች።

ቶልስቶይ ገም ብሎ እየተመለከተና አካባቢውን አየቃኘ በለሆሳስ «አምን፣ አም ይህ አሰቃቂ ነው! ብዙ ሰካራም ሴቶችን ተመልክተሃል እንዴ? አቤት አምላኬ! ስለዚህ ግን ፍፁም እንዳትፅፍ! አያስፈልግም!»

- ለምን?»

- «ትኩር ብሎ አየተመለከተኝና ፈገግ አደለ - 'ለምን' የሚለውን ጥያቄ ደገመ። ከዚያም ዝግ ብሎ እያሰበ 'አላውቅም - አንዲያው መስሎኝ ነው ... አሳፋሪ ነው ስለ ፍሬከርስኪ ነገር መፃፍ። መልሶ ደግሞ፣ አም - ለምን አይፃፍም!? አይሆንም - ሀሉንም መፃፍ ያስፈልጋል። ስለ ሁሉም መፃፍ አለብህ።»

ዓይኖቹ አንባ አቀረሩ። አንባውን አየጠራረገና ፈገግ አያለ መሀረቡን ተመለከተ፣ አንባው ግን መጉረፉን አላቆመም።

- «አለቅሳለሁ» አለኝ መልሱ። «እኔ ሽማግሌ ነኝ። አስደንጋጭ ነገርን ስመለከትና ላስታውስ ልቤ ላይ ተመላልሶ ይጋልባል። በዝግታ ይሞርደኛል። ይሽው አንተ ግን - ህይወትን ኑርባት፣ ያኔ ከእኔ በጎይ ታለቅሳለህ። ሁሉንም መፃፍ ያስፈልጋል፣ ስለሁሉም ነገር መፃፍ፣ ካለበለዚያ የተመለከትከው ልጅ ይተየማል፣ ያጣራል፣ አውነት አይደለም፣ ሁሉም አውነት አይደለም ይልሃል። ልጅ አውነትን አይለቅም» ብሎ ብድግ አለ። ከዚያም በሰከነ ድምፅ «አስቲ የሆነ ነገር ተርከልኝ - አንተኩ ጥሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሬሲ ነው። ስለ ልጅ፣ ስለ ራስህ። አዬ ኮመንም እንጂ እንኮም እስ ልጅ ነበርክ፣ የተለየህ ፍጡር። ግን ዛሬ ቢደክ ቅልቅ ሆነህ የተወለድክ ትመስላለህ። በእስተሳሰብህ፣ የጨቅላነትና ያልበሰለ ነገር አለብህ። ግን ስለ ሀያውቅ ብዙ ታውቃለህ። ከዚህ በላይ አያስፈልግህም። አስቲ ተረዝልኝ ...»

* * *

- «አንተን አንባቢ ነው ይለሃል - አውነት ነው? ኮፊልሽ መዚኖኛ መሆኑን ታውቃለህ?»

- «አደመልሽም፣ አዘውቅም»

- «አ'ኮውቅም? ድርስቶቹ ያስደስቱሃል?»

- «አም፣ በጣም»

- «አንተ በተቃራኒው ነው። የእስ ዕሀብሮች እንደ ሚነም ናቸው። ዌልድማንን አንብበኸዋል?»

- «አም»

- «አውነት አደደል? ጥሩ ደራሲ ነው። ትክክለኛ፣ ታታሪና ግንት የማያጠፋ ደራሲ። ከገጮል ግን በልጠ አደውቅም። ገጮል ባልዝክን ያውቀዋል።»

እኔ ግን ጎጮል የሆፍማን፣ የስተርን፣ ምናልባትም የዲከንስ ተፅዕኖ እንዳለበት ስናገር - ትኩር ብሎ ተመለከተኝና «ደሀን የሆነ ቤታ ላይ እንበበኸዋል? አይደል? ትክክል ሳይሆን አይቀርም፣ ጎጮል ዲክሰን ሳያውቀው አይቀርም። አንተ ብዙ አንብበሃል - ግን ንባብ ቀሳፊ ነው። ከልሰብ የሞተው በዚሁ ነበር።»

አትር እያሸኘ ሳመኝና «አንተ አውነተኛ ሰው ነህ፣ ይህ ባህርይህ በደራሲያን መሳል ብዙ ችግር ያስከትልብሃል። ግን ፊዕሞ አትፍራ። የሚሰማህን ከመናገር ወደኋላ አትበል፣ በእርግጥ ድፍረት ሆኖ ቢታይብህም ምንም አይደል፣ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ይረዱሃል» ሲል መከረኝ። አስታውሳለሁ። ሱስርን በአንድ ወቅት - «አንተ

አተንበም፣ ጥሩ አይደለም አለማንበብህ፣ ማንበብ ግላዊ ዜቅትን ያጎናፅፋል። ተመልከት ጎርኪ ብዙ ያነባል። ደህም ጥሩ አይደለም። ራስን ካለማመን የሚመጣ ነው። እኔ ብዙ ፅፋለሁ፣ ደህም ጥሩ አይደለም። ምክንያቱም ከሽምግልናዊ ራስወናድነት የመነጨ ነው። ሁሳችሁም እንደእኔ ብታስቡ ምኞቱ ነው። እርግጥ ነው እኔ ስለ ራሴ ብዙ አስባለሁ። ጎርኪ ደግሞ ያህ መጥሬ መሆኑን ነው የሚያስነው። አንተ ግን ሱስር ምንም አታስብም። ዝም ብለህ ታፈጣለህ - ያህ ደሞ ማነቆ ነው። ቺንዝ «ዱሽቹክ» የተሰኘ መልካም ድርሰት አለው። ልክ አንተ እንደዚያች ዝብርያ ነህ።»

- «ለምን?» አለው ሱስር አየሳቱ።

- «ማፍቀር - ትወዳለህ - መምረጥ ግን አትችልም፣ ስለዚህ መደማደረብት ትጣላለህ»

- «ቢታ ይኸው ነው?»

- «ቤታ?» ሲል ቶልስቶይ ደገመ። «አይደለም፣ አደደለም፣ አደብታም»፣ መልሶ እኔን ባልተጠበቀ ጥያቄው «ለምንድነው በእግዚአብሄር የማታምነው?»

- «እምነት የለማ - ለድ ቶልስቶይ»

- «አንተ በተፈጥሮህ አማኝ ነህ፣ ካለ እግዚአብሄር መኖር አትችልምና አስብበት። ዓለም የተፈጠረችው አንተ በፈለከው መንገድ አደደለም ... አንደ ፍትር ሁሉ እምነትም ድፍረትን፣ ጉብዝናን ይጠይታል። ለራስህ፣ ለውስጥህ እምናለሁ በል። ያኔ ሁሉም የተሳካ ይሆናል። ከዚያም ፍትር ወደ እምነት ይለወጣል። ሲትን ሲያፈቅሩ በዓለም ላይ እንዳለች ብቸኛ አበብ ድንት አድርገው ነው ማፍቀር - ይህ ታዲያ እምነት ነው። ኢ-አማኒ ሊያፈቅር አይችልም። ዛሬ አንዷን፣ ከዓመት በኋላ ሌላዋን ያፈቅራልና። የእንደዚህ አይነት ሰዎች መንፈስ ጨንጫጌ ነው - ፍሬ አያፈራም። ይህ ደግሞ ክፉ ነገር ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF


አንተ አማኝ ሆነህ ነው የተወለድከው ስለዚህ ራስህን አትስበር። ይኸው ስለቁንጅና ታወራለህ። ቁንጅና ምንድነው? ታላቁና ፍፁሙ ቁንጅና እግዚአብሄር ነው።»

ከዚህ በፊት በዚህ ርዕስ ላይ ከእኔ ጋር ተነጋግሮ አያውቅም። የንግግሩ ያልተጠበቀ መሆን ፍፁም ለወጠኝ። ዝም አልኩ። ሶፋው ላይ ተቀምጦ እግሩን ሰብስቦ ድል እድራጊ ፈገግታውን በሚሙ መሀል እየመገበኝ «በዚህ ጉዳይ ላይ ዝም አትበል፣ ፈፅሞ ዝም አትበል!» ሲል በጣቶቹ አስጠነቀቀኝ።

እኔ ኢ-አማኒው ሰውዬ በጥንቃቄ እየተመለከትኩት፣ ትንሽም ፈራ ተባ እያልኩ «ለካስ ይህ ሰው - ለእግዚአብሄር የተሰጠ ነው» ስል በውስጤ አብሰለሰልኩ።

ግለታሪክ





የጣታቸው ቢጫ

ቺንጊዝ አይትማቶቭ
ትርጉም - መኩሪያ መኸሻ

ለመጀመሪያ ጊዜ ነው አባቱን ፊልም ውስጥ የተመለከተው። ያኔ ገና የአምስት ዓመት ጨቅላ ነበር።

ይህ ሁኔታ የተካሄደው በአንድ ትልቅ አዳራሽ ሲሆን በዚህ ስፍራ በየዓመቱ ጡች ይሸለታሉ። አዳራሹ የጡበ ክዳን ሱበሷል። ከዝቢት አርሻው በታች፣ ከተራራው ጀርባ መንቡዱ ዶር ተከፍሷል። ልጁ ከእናቱ ጋር ወደዚህ ሰፍራ ይመላለሳል። እናቱ ጀንጉል የሕብረት አርሻው ስልክኛ ናት። የሽለታው ጊዜ ከመጀመሩ በፊት በየበጋው ወደዚህ የመሸለቻ ጣቢያ ሰራተኞች ይሰባሰባሉ። ለዚህም ስትል የቀንና የለሊት አረፍትዋን ወስዳ አስከመጨረሻው የመሸለቻ ቀን ትሰራለች። የሽለታው ክፍያ ዳጉስ ያለ በመሆኑ ደህና ገቢ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይገኝበታል። ለአንደሷ ላለ ወታደር ባልዋ ለሞተባት ሴት እያንዳንዷ ትርፍ ቤላ አንዴት ያለ አስፈላጊዋ ነው! ምንም አንኳ ቤተሰብ ብዙ ባትሆንም ቤተሰብ መቼም ቤተሰብ ነውና ለከረምት የሚሆን ማንደጃ፣ ዱቄት መግቢያ ያስፈልጋታል። የታረዘች ባትሆንም መልበሻ፣ መጫማት ያሻታል ደ ሞስ ኑሮ ኣዳው ጉበሳ ነው የሚባልለት አይደለም።

ልጇን እቤትዋ ጥላ መምጣት አልተቻላትም። ይዛው ነው የመጣችው። እዚህ ሙሉውን ቀን በሽላቾቹ፣ በአረጮቹና በወሽቃቸው መሀል አንደ አንዱ ሲደር ይውላል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር በአዳራሹ መሀል ፊልም አንደሚታይ ያወቅውና ይህን የደስታ ደባብ ለመከፈል የታደሰው።

ፊልም ሊታይ ነው፣ ፊልም!

ከራ አልቆ ደንገዝገዝ ሲል ፊልም ማሳየት ተጀመረ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ግን በጥቢቃ ተሰላችቶ ነበር። ፊልሙ የጦርነት ታሪክ ነው። በአዳራሹ መጨረሻ በሁለት አንጨቶች በተወጠረው ሼራ ላይ የውጊያ ታሪክ መታየት ጀመረ። ተከስ ተሰማ። ርክቶች ተወገጨቱ። ጥቀርሻ የመሰለ ጭስ አካባቢውን አፈነ። በሸራው ላይ መሬት የያዙ ሰዎች ታዩ። ሮኬቶች ተንጀዱ። ሰዎች ኖገም ተነስተው ወደፊት ተረማመዱ። መትረያሶቹ አዘታትለው የአጨዳ ተክስ ሲያስመ የልኝ መንፈስም አዘር ተረጩ።

ይህ ነው ጦርነት!

ከአናቱ ጋር ሆነው ከሌሎች ታዳሚዎች ደርገ ቦታ ይዘዋል። በሚገባ ይታያል። በአርግጥ ልጅ አንኳ በመጀመሪያው ረድፍ መቀመጥን ፈልጉ ነዘር። ምክንያቱም ከዘባረት አርቫው የተሰበሰቡ ልጆች እዚያው ይገኙ ኖሯልና ነው። ወደ አነሱ ነልሂድ ብዙ ቢያስቸግርም አናቱ ግን በገዴት - ብቻህን አናነዋት አስክ ማታ ከአነሱ ጋር አይደል ስትራገዋ የምታውለው፣ ከአነሱ ጋር ሁን ብለው ጭኗ ላይ አዘቀመጠችው።

የፊልም ማሳያው ያጠነዋናል። ጦርነቱ ቀጠሏል። ታዳሚው በተወጠረ መንፈስ ይከታተላል። አናትዋዋ በረሻርሙ ተጉደስ በድንጋጤ ለውንትዋ ተዝለፈለፈ። ልጇን ጭምድድ አርጋ ጠይራበዋ ስቃኳቢጋ ታዝዙ በሞታ አፈጠዙን አስረገዛም ጠደ አነሱ ያነጣጥር

ነበር። አንዲት አጠገባቸው የተቀመጠች ሴት ራስዋን መቆጣጠር አቅቷት «አምላክ! ምን ይፈጠር ይሆን? አቤት አምላክ...» ስትል አዮተመለከች።

ለልጁ ግን አስደንጋጭ አልሆነበትም። በተታራኒው ነው። አንዲያውም አንዳንዴ ፋሽስቶቹ ተመትተው ሲወድቁ ልቡ በዳንሽነና ትሞላ ነበር። የወገን ጦር አባላት ከወደቁ በኋላ ቀጥሎ ተነስተው እንደሚንደፈደሩ ይገምታል።

ብዙ አንዲያው ሰምች በውሊያ ውስጥ ሲወድቁ የሚደንት ነው። ልክ ፖሊስና ሰባ ብለው አንደሚጫወቱት ነዘር። አሱም ቢሆን አንዲህ መውደቅና መነሳት ይችልቢታል። አንዱት አንደሚጉዳዱ ያውቃል። አንደሰውነቱ ከዘን በልጆች የጦርነት ጨዋታ ውስጥ መውደቅ አለ። ምንም አንዳልሆኑ መነሳት። ማጥቃት፣ ሰለመቁሰል ሳያስቡ ወደፊት መረማመድ። አነዘህ በፊልም የሚታዩት ግን አንዱ ከወደቁ አይነሱም። መሬት ይዘው ሳይንቀሳቀሱ በዚያው ይቀራሉ። በልጆቹ ጨዋታ ውስጥ ግን በጥይት ሆኖቸውን የሚመቱ ነበሩ። ታዲያ ውዲያው አደወድቁም፣ መጀመሪያ ላይ ሆዳቸውን ይይዛሉ። ከዚያም ጉበጥ ብለው በዝግታ ሳሩ ላይ ይዘረራሉ። ቀኖሉ መሳሪያቸው ከአጃቸው ላይ ይወድቃል። ከዘህ በኋላ አንዱ «አትግደለኝ» ሲል ያዛል። የውጊያው ጨዋታ ይሎዮሳል። አነዘህ ግን የተለዩ ሆነብት - አንዱ ከተዘረሩ አይነሱም።

ጦርነቱ ተጠለ። የፊልም መሳሪያው ያጠነጥናል። አሁን ደግሞ ሼራው ላይ መድረኞች ታዩ። በተዙሱ፣ በፍንዳታውና በጭሱ መሀል ሀረ ታሪክ መድፉን ሉተክሳ አዘጋጁ። መድፎቹን ከተጻሩቱ አጠጡ። ተጻሩቱ ረሻርምና ሰፊ ነው። ልክ አንደ ግማሽ ሶማይ። በዘህ ረሻርምና ስፊ ተጻሩት ጥልማሞት በመሰል ፍንዳታ ውስጥ መድፈኞቹ በቡድን ተንቀሳቀሱ። አንቅስቃሴያቸው ሲታይ ደረት ውስጥ የታተፈውን ልብ ያስደሰቃል። መንፈስ በከራት ይሞላል። አንድ ከፉና ታላቅ ነዘር ይጠበቃል። ስባት ወታደሮች ነበሩ። ልብሶቸው ላያቸው ላይ ነትቧል። ከመድፈኞቹ መሀል አንዱ ሩሲያዊ አይመስልም። ልጁ በዘህ ሰው ላይ ትኩረት አሳደረ ይሆናል። አናት ግን ቀነታቢታለች።

«ተመልከት፣ ይህ አባትህ ነው...» ስትል አንሾካሾከች። ከዘህች ደቂቃ በኋላ ይህ ሰው አዘቱ ሆነ። ከዘህ በኋላ መሀሙ የፊልሙ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታሪክ ሰሰ አሱ፣ ሰሰ አባቱ ሆነ። አባቱ እንደ ሁሪት አርባው ጐሪምሶች ወጣት ነበር። አጭር፣ ከብ ፊትና ዓይነ ፈጣን ነው። ፊቱ ላይ ከነበረው ቁሽሽና ጥቁርሻ ጭስ ውስጥ ዓይኑ ብርሃን ይረጫል። እንደ ድመት ጠንቃቃ ነው። ይሽውና፣ በትከሻው የመድፉን ጉማ ሰክሀ ቱቫሳቱ ውስጥ ወዲ ሰው «ዋይት፣ ጭስን ጥይት» አያሰ ይጮሣል። ከዚያም ድምፁ በአዴስ ፍንዳታ መሳል ሰልም ይለል።

«አማዬ ይህ ነው አባቴ» ሲል አቫልበህ እናቱን ጠየቀ።

«ምን?» ጥያቄው አልገባትም። ወዘዎታ ቁጭበል። አርፈህ ተመልከት።»

«አባቴ መሆኑን ነግረሽኝ የሌ...»

«አዎን - አባትህ ነው። ብቻ አንተ አትለፍልፍ፣ ሰሉትን አትረብሽ።»

ለምን እንዲህ ተናገረች? ለምን? እንዲያው ሳታስበው ገጭ ብላ ይሆናል። በዚች ደቂቃ አሳስቧትስምም ይሆናል። ወይም ደግሞ ባልዋን አስታውሳ ተረብሻ ይሆናል። አሱ ግን አምናት ተቀብሏል። በጣም ተደስቷል። በዚህ ባልተጠበቀና ባልተሰመደ ደስታ የአባቱ፣ የዚህ ወታደር ሁኔታ የልጅ አእምሮውን በኩራት ወጠረው። ይህ ነው አውነተኛ አባት፣ ሰሉች ልጆች ግን አባት የሌሰው በመሆኑ ይገረሙ ነበር። አሁን ግን ይኸው አባቱን ይመልሰዙ፣ አረኞቹም ቢሆኑ ይመልከቱት እንዚህማ የተራራ ላይ አረኞች ልጅን ፈጽሞ አይገዘበም። አነሱ እየታገሱ ሲጣሙት አሱ ግን የበኮቹን መንታና ውሻቸውን ይጠበቅሳቸዋል። ቃሊያ በጥያቄ ቋምስትሱን ያሳቦታል። እያንዳንዱ አረኛ በዛለም ላይ በሚናርበት ቦታ ሁሉ የሚከተለውን መጠሠሩ የተሰመ ነው።

«አንተ ጨለ ማነው ስምህ»

«አቫልበህ»

«የማን ልጅ ነህ?»

«አኔ የቶክቶሱና ልጅ ነኝ»

አረኞቹ ግን ነገር ቶሱ አይገቧቸውምና «ቶክቶሱና?» ይለሙ በአርቾቸው ላይ አጉንበለው። መልሰው ይገሞ

«ማነው ቶክቶሱና?»

«አኔ የቶክቶሱና ልጅ ነኝ» ሲል ያረጋገጥላቸዋል። አናትህ

ሁሌ እንዲሁ እንዲመስል ነው ያስተማሪችው። አውርዋ አያቱም ሳይሎሩ የአባቱን ስም በመርሳቱ ቅጥተውታል። ጀሮው አሰኪደማ ቀንየጠወታል። ክፉ!

«ኖን እሰቲ፣ ቆይ፣ ቆይ - አንተ የሰልዙዋ ልጅ አይደለህም፣ ታዲያ አንዴት አንዚህ ሆነ?»

«አይደለም፣ እኔ የቶክቶሱና ልጅ ነኝ» በማለት በመልሱ ፀና።

ዘዚህ ጀሳ አረኞቹ ወደየግላቸው ትርጉሜ ጉበተው ሁኔታውን ያወጋሉ።

«ትክክል፣ አንተ የቶክቶሱና ልጅ ነህ ጉበዝ፣ እንዲያው እኛ ልገፈትህ ፈልገን ነው። አትቀየም ጨለው፣ እኛ እንደሆን ዓመቱን ሙሉ ተራራው ላይ ነን። አናንተ ግን ሁሰም አንደ ሳር አዚሁ በቅሳችሁ አዚሁ ነው የምታድጉት። ስለዚህ የማን ልጅ መሆህን ማወቅ ያስቸግረናል።»

ዘዚህ ቢኋላ ለረዥም ጊዜ የአባቱን ስም አያስታወሱ ደጨዋወታሉ። አያንዳንዱ የልጁ አባት በወጣትነቱ ወደጦር ግንባር እንደመተና አሁን ግን አብዛኛው የአካባቢው ህዝብ እንደሚያስታውሰው አወቱ። ልጅ መውለዱና ስሙን መትከሉ በፎ እንጂ ብዙ ልጆች ያስአበት፣ ያስመጠሪያ ቀርተዋል።

እናቱ «ተመልከት ይህ አባትህ ነው» ብላ ከነገረችው ውዲህ ስለዚህ ሰው ማሰቡን ቀጠለ። አባቱ በወታደራዊ የደንብ ልብሱ ከጎኑው ፎቶግራፍ ጋር ዘልዶ ይመሳሰላል። ፎቶውን አሳድገውና መስታወት ውስጥ ከትተው ሰቅለውታል።

አቫልበህ አባቱን በልጅ ዓይኑ መመልከቱን ቀጠለ። የፍቅርና የሰኩት ትዝታ ማዕበል ተንስቶ የህፃን መንፈሱን አመሰው። ሽራው ላይ ያለው አባት ልጁ አሱን እንደሚከታተሰው ቢያውቅ ኖሮስ? ጦርነቱ ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ለልጁ አስነራሚ አልሆነበትም። ስዎች ሲወድቁ ማየቱም አስደናቂ አልነበረም። ጦርነቱ የምር ውነተኛ፣ አስጨናቂና አስዘፊ ሆኖበታል። የስጋው ክፋይ የሆነውን ሰው ዘዚህ ሁኔታ መመልከቱ የፍርሃት ስሜትን ለቀቀበት።

የፊልም ማሳያው ያጠነጥናል፣ ጦርነቱ ቀጥሏል። ዘፊት ሰፊት አጥቂ ታዝቾ ታቂ። ሊንቀሳቀሱ ያስፈራሉ። መሬቱን በሰንሰለታቸው እያዝኑና አናታቸው አሞተሸከረከረ ከመድፎቸቸው አረር ይተፋሉ። የወገን መድፈኞች መድፎቻቸውን ከተጻፉቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

አያወጡ ነው። «አባቴ! ፍጠን፣ ፍጠን! ታዝቶች እየመጡ ነው፣ ታዝቶች!» ሲል ልጁ አባቱን አቻኮለ። በመጨረሻም መድፎቹን ወደ ግቦው መሬት አውጥተው ታዝቶቹን ደበደቡ። ታዝቶቹም በተራቸው እፀፋውን መለሱ። ብዙ ነበሩ። አጅግ አስፈሪናቂ ነው። በዚህ ወቅት እዚያው አባቱ አጠገብ በተኩሱና በአስቀያሚው ጦርነት መሐል እንደተሰለፈ ሆኖ ተሰማው። ታዝቶች ተቃጥለው ጥቁርሻው ጢስ ሲንቦለቦል፣ ሰንሰሰቱ እተበጣጠሰ ሲላቀቅና መንቀሳቀስ ተስኖአቸው ሲገተሩ ከአናቱ ጭን ላይ በድንገት ተነሱ። የወገን ወታደሮች ደግሞ በየመድፎቻቸው ሩጫ ወደተው በዚያው ለዘለዓለም ሲያንቀላፉ ሲመለከት ዝምታ አፈጠው። ተሸማቀቀ። ከዚህ ወዲ ጊዜ የወገን ጦር ቁጥር እየተመናመነ መጣ፤ አናቱ በፅዝ ታጠበች። ፊቷ ረጥቦ ይፋጅ ነበር።

የፊልም ማሳያው ያጠነጥናል፣ ጦርነቱ ቀጠሏል። ውጊያው በአዲስ ኃይል ተቀጣጠሉ። ታዝቶች ከምንዘውም በላይ እየተቃረቡ መጡ። አባት መድፍ ተሸካሚው ላይ ሆኖ እየጮኸ በሽቦ ሚዳ ስልክ ያወራል። በዚህ ድብልቅልቅ ሁኔታ የሚሆነውን ማጣራት አይቻልም። አንድ ወታደር መድፉ ላይ ወድቋል። ለመነሳት ይጣጣራል። ግን አልቻለም። መሬቱ ላይ ተዘረገፈ። መሬቱ በወታደሩ ደም ጠቆረ። ሁለት ብቻ ቀርተዋል - አባትና ሌላ አንድ ወደታር አንደምንም ብሎው አንድ ጥይት ተኮሱ። ከዚያም ሁለት ጥይቶችን አዘታትሰው ተኮሱ። ግን ታዝቶቹ በርትተዋል። አንድ ጥይት መድፎቹ አጠገብ ወደቀ። ፈነዳ። እሳትና ጭስ። ከመሬት ላይ ብድግ ያለው አንድ ብቻ ነው - ይኸውም የልጁ አባት። ወደ መድፉ ብቻውን ተመለሰ። ራሱ አጉረሰው፣ ራሱ አነጣጠረ። ይህ የመጨረሻ ተኩስ ነው። ጭጋም ፍንዳታው የፊልሙን ሽራ ሞላው። የአባትየው መድፍ ብትንትኑ ወጥቷል። አሱ ግን በህይወት አለ። በገፀታ ከመሬት ተነስቶ ጭስ ሰብሶና ዘበተሉ መስሎ ታዝቦን ሊጋፈጥ ቀጠለ። በአጁ ቦምብ ይዟል። ምንም አያይም፣ ምንም አያዳምጥም። ለመጨረሻ ጊዜ ያለ የሉለ ኃይሉን አሰባሰቡ።

«ቁም፣ ከዚህ አታልፍም!» ሲል በምቡን ጠረወረ። የአባትየው የጥላቻና የህመም ገጽታ ለዋቂት ደቂቃ ታየ። አናትየው በዚህ ጊዜ ልጁን ጨምድዶ ያዘች። ልጁ አፈትልክ አባቱ ላይ ቢጠመጠም ደከታው ነበር። ዳሩ ግን ከታዝቡ ላይ ከሚተኮስ ሪሻም የመትረየስ

ዕሩምታ አባትየው ተመትቶ እንደ ተቆረጠ ዛፍ ወደቀ። መሬት ላይ እየተሳበ ለመነሳት ሞከረ! ጭጋም ተመልሶ ተዘረጋ...

የፊልሙ ማሳያ ሆኖ አለ። ጦርነቱ ቆመ። የፊልም አፕሬተሩ መብራት አበራ።

አዳራሹ ውስጥ መብራቱ እንደበራ ታዳሚው ዓይኑን እያዘበ ከፊልም ዓለም፣ ከዚያ ከጦርነት ዓለም ወደ ገሀዱ ዓለም ተመለሰ። በዚህ ጊዜ ልጁ ቦሚያስበረግግ ድምፅ -

«ልጆች - ይህ አባቴ ነው! አያችሁት? አባቴን ነው የገደሉት...» አለ።

ማንም ይህን የጠበቀ አልነበረም። ምን እየተካሄደ እንደሆነ ማንም ሊያስብ አልቻለም። ልጁ ወደ ፊልም ማሳያው ሽራና ኃይኖቹ ወደተቀመጡበት ረድፍ እየተንደረደረ ሮጠ። ለአጭር ጊዜ በአዳራሹ ውስጥ ያልተጠበቀ፣ አስደናቂ ሆኖታ ወደቀ። አባቱን ፈጽሞ አደቶ የማያውቅ፣ የዚህ ልጅ ፍንደቃ ለምን እንደሆነ በማንም ታዳሚ አእምሮ ውስጥ ሊከሰት አልቻለም። ሁሉም ግራ ተጋብቶና አፉ ተለጉሞ የሚሆነውን ይከታተላል። ፊልም ከሚያሳየው ስውዱ አጅ የፊልም መያገርውና ክሩ ተቡዘኑ። ማንም ተዘረት አላደረገም። ራሱ የፊልም አፕሬተሩ እንኳ ለማንሳት ስልፉዝውም። የወታደሩ ልጅ ግን ስለአባቱ ማረጋገጫ መስጠቱን ተያያዘው።

«አያችሁት አይደል - አባቴ ነው!... አባቴን ገደሉት» ሲል ጮኸ። ተሰብሰቢዎቹ ግን አሱ ስለ አባቱ ቡተናገረ ቁጥር አርጭ ብለው ይሰሙት ጀመር። ለምን እንደአሱ ሊደሱቱ እንዳልቻሉ ፊሽሞ ሊገባው አልቻለም።

አንድ ደከተኛ ያልሆኑ አዛውንት፣

«ችችች! ገሸበል - እንዲህ አትበል» አሉት።

አንድ ከጉናችው ያለ ሰው ደግሞ «ምንድነው ነገሩ? አባቱ ጦር ግንባር ነው የሞተው። ዕውነት አይደለም እንዴ?»

አንድ ከጉት ያለ ተማሪ ዕውነቱን ለልጁ ለመናገር ወሰነ።

«ይህ አባትህ አይደለም። ለምን ትጮሃለህ? አባትህ ሳይሆን ተዋናይ ነው። ከፈለክ የፊልም አፕሬተሩን ጠይቅ»

አዛውንቶቹ የልጁን መራርና አስደናቂ ራዕይ ሊያስናክሱበት አልፈለጉም። የፊልም አፕሬተሩ ዕውነታውን እንዲል እንዲያነቃቃው

t.me/OLDBOOKSPDF

ታዳሚው ሰፈሰፈ። ሁሉም ከበቡት። ዳሩ አፐሬተሩ ገፀ-ታሪኳን መረጠ። ወደ ፊልም ማሳያው መሳሪያ ላይ ተደፍቶ በአሪፉ የተጠመደ መሰለ።

«አባቱ ነው! የእኔ አባት ነው» እያለ የጠቃቀሰው ልጅ ገፀ-ታውን አደፈሰሰ።

«ያትኛው ነው አባትህ? የትኛው?» ሲል ጮሆም አዘገበ የነበረው ልጅ ጠየቀው።

«ቆምብ ደህ ታንዙን ሲያታዮል የሄደው ነዋ። አላየኸውም እንዴ? እንዲህ ነው የጠፋተው» ብሎ አባቱ እንደጠፋተው መሬት ላይ ውድቆ ተንዘፍስሶ። ልክ ፊልሙ ላይ እንደተመለከተው ነበር ያሳየው።

ተመልካቹ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት በሳቅ ተንከተከተ። ልጁ ግን እንደ ሞተ ሰው ተንጋሏል። ፊጽሞ አደብቅም። ጭራ ያልተወለደ ገፀ-ታ ሰፈነ።


እነዚና ኩስትር ብላ ዓይኗ ዕንባ እንዳቀረረ የልጁ እናት ጀንጉል ወደ ትዕይንቱ ስፍራ አመራች። ልጇን ከመራቱ ላይ አነሳች።

«እንሂድ ልጅ፣ እንሂድ። አባትህ ነው ልጅ» እያለች በጠየታ ንዝረቻው። እጁን ጉትታ ከዚያ ሰፈ አናራሽ ይዛው ወጣች።

ጨረቃዋ ደምቃለች። ርቃለች። ከርቀት የማታየው አድማስ ጥቁር - ሰማያዊ ዳፍል ለብሏል። ከታች የተንሳለለው ሜዳ ተዘርግቷል። እንደ ጉድጓድ ውሃ ለእይን ይታከተኛል...

ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘየውቱ ኮሚከዲው ሲው የመለሰት ታሪኩ አንበሸሸው። በድንገት ቁጭት ተሰማው። ሀጠም አየንቱ ድሰ ዘለቀ። ከዚያ በውሂዮ ለጠፍቀ አባት ዛዘን ንላው። እናትም በድንገት አትፋው ለማልቀስ ዱዳት። አቡው ለማልቀስ ቦጣም ተመገች። ግን አልቀለችም። ሰንዝሮን ዋጠች። አሱም ገፅ አለ። አድቅን ጨዛጣ ከሰንዝው ጋር ታገለ።

ለ/ዘር



ፀሎተ-ጦርነት

ማርክ ትዌን
(ትርጉም) ተፈራ ገዳሙ

መንድ የመለደች እናት የንዘሥቸበት ታላቅ የፍስሐ ዘመን ነበር። የመጀመሪያይቱ ጥይት ባርቶ አገራቱ ጦርነት ባህር ውስጥ ትዋኛለች! በአያንዳንዱ ልብ ቅዱስ የአርበኝነት እሳት ተቀጣጥሏል። ኒጋራት ይጉስማል። ዘማርያኑ ዜማውን ያዜሙታል። ሁሉም ነገር እንደ ተኩስ ነበር። ጥምር ርችቶች ሽቅብ ወጥተው ይንቮቮሉ! ከእያንዳንዱ አጅ እየደበዘዙና እየሳሱ ወዲያ ማዶ ከዘለቁት ጭሮችና ስንቱቶች የተመዘዙ ባንዲሮች እያብለጨለጩ ያውለበለቡታል። በየቀኑ የደስደስ ያሳቸው ወጣት ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘማቾች በአዲስ የደንብ ልብሶቻቸው አጊጠው ሰፈ
ጐዳናውን ይሂዱ ታል። የኮሩባቸው አባቶቻቸው፣
እናቶቻቸው በደስታ ስሜት ታጥነው አልልታውን
ያቀልጡታል። በምሽት አሐዛብ ታጉረው ትንፋሻቸው
ቁርጥ ቁርጥ አያለ የልባቸውን ማአከል የሚቀሰቅስ
አርበኛዊ ንግግር ላጭር ጊዜ ብቻ በነገ-ድጓዳማ
ጭብጨባቸው እያቋረጡ አንባቸውም እንደ ጐርፍ ቁልቁል
አየቀጀ ያደምጡታል። በየቤተስኪያኑ ካህናት ለባንዲራና
ለሀገር ማገልገልን ሰበኩ። መላውን አድማጭ በማረከ
ልሳት፣ በተባ አነጋገር፣ የጦርነቶችን አምላክ ተማፀኑት፣
ለጥሩ አላማውም አርዳታውን ለመኑት። በእርግጥ ደስ
የሚልና የሚማርክ ጊዜ ነበር። ጦርነቱን ላሰመቀበል
የደፈሩትና ቅዱስነቱን የተጠራጠሩት አኩሌታዎቹ ችኩል
መናፍስት ወዲያውኑ ጥብቅ የቁጣ ማስጠንቀቂያ
እንደማግኘታቸው ሰደሀንነታቸው ሲሉ በፍጥነት ከዓይን
ተሰወሩ። ዳግም በዚያ መንገድ መተነኳኮላቸውንም
ተውት።

ዕለተ እሑድም ሆነች። ነገ ጦሩ ወደ ግንባር
ይንቀሳቀሳል፤ ቤተክርስቲያኗ ከአፍ እስከ ገደፏ
ሞልታለች። ወዶ ዘማቾቹም እዚያው ናቸው - ለጋ
ፊታቸው በጦርነት ሕልም፣ በፍልሚያው፣ በድንቱኛ
ማጥቃቱ በሚያብረቀርቁት ሽምላዎች፣ በጠላት
መፈርጠጡ፣ በሁካታው፣ በጢስ መሽፈኑ፣ በከረረው
ግሳደዱ፣ እጅ መስጠቱ፣ ከዚያም ጀግነው፣ ተመልስው፣
በወርቃማ የድል ባህሮች ሰምጠው «በጉሮ ወሸባዬ...»
ከጦርነት መልስ ከወዶ ዘማቾቹ ጐን ለባንዲራ ለመውደቅ
ከቡር የሞቶች ሞት ለመሞት የሚልኳቸው ልጆች ወይም
ወንድሞች በሴሏቸው ጐረቤቶችና ወዳጆች የቅናት ዓላማ
የሆኑት፣ ኩራት ኩራት ያላቸው ውዶቻቸው
ተቀምጠዋል።

ዕለቱ ቀጠሰ።

ከብሶ-ይ ኪዳን የጦርነት ምአራፍ ተነበበ።
የመጀመሪያውም ዕለት ሆነ። ተከትሎ በመጣው
የዘማርያኑ ድምፅ ግብረ ሕንፃው ተናወጠ። በአንድ ልብ
ሕዝበ - ክርስቲያን ተሃበዩ ቆመ። በብራህ አይናችና በልቦች
ድውታ መሠልም ያንን ታሳቅ ልመናቸውን አቀረቡ።

ትእዛዝህ የማይነጥፈው ኃያሉ አግዚአብሄር ሆይ፣
መለከትህ ነጐድጓድ ጐራዴህም መብረቅ ይሁን፣

«ረሻ'መ» ዕለትም ቀጠለ። እንዲህ ፍውም የጋለ
ስሜት ያለው ልመና መሳጭና ውብ ቃል ከቶ ወዴት
ታይቷል? የዘለቄም ፍሬ ነገር መሀሪውና ቸሩ አባታችን
ወጣት ወታደሮቻችንን እንዲጠብቅ፣ በአርበኝነት
ምግባራቸው እንዲረዳቸው፣ እንዲያዕናናቸውና
እንዲያበረታታቸው፣ እንዲባርካቸው በጦርነት ቀንና
በአደጋ ሰዓት እንዲመክትላቸው፣ በኃያል ክንዱ
እንዲችሳቸው፣ ብርቱና ልበ ሙሉ እንዲያደርጋቸው፣
በዚያች ደም በምታሩስሰው የማጥቃት ሰዓትም
እንዳይበገሩ፣ ጠሳትንም ለመደምሰስ እንዲረዳቸው፣
ለራሳቸው፣ ለባንዲራቸውና ለአገራቸው፣ የማያልፍ
ክብርና ሞገስ እንዲሰጣቸው...

አንድ ረሻ'መ ገላቸው መራት አስኪነካ ድረስ የወረደ
ልብሶ-ታከሀኖ የደረቡ፣ ሽበታቸው ቆብ ካልደፋ ራሳቸው
ተመዘ እንዳረሩማ ሄጅቱ ወደ ትከሻቸው የወረደ፣ ከልኩ
ባለፈ አንደ መገርጣቱ ጣረሞትነት የዳሰሰው የተጨማደደ
ፊት ያላቸው ሽማግሌ አንሃዳ ይገቡና ዓይናቸውን በደብር
አሰታው እንደተከሱ በገቦታና ድምፅ አልባ አርምጃ በዋናው
መተላለፊያ አመሩ።

አልፍ ዓይኖች በመገረም አየተከተሳቸውም ያለማቋረጥ
በፀጥታ ተራምዷው ወጡና ከሰባኪው ጐን ቆመው
መጠባበቁን ጀመሩ። ሰባኪውም እንግዳው እንደሌሉ ሁሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

አይናቸውን ከድነው መሳጭ ፀሎታቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻም«ጠራችንን ባርክ፣ ድሉንም ስጠን ጌታ ሆይ፣ አምላካችን የአገራችንና የባንዲራችን አባትና ጠባቂ!» በሚሉት ስሜት ቀስቃሽ ቃላት ደመደሙት።

አንግዳውም የደብር አለቃውን እጅ ነክና ዘወር እንዲሉላቸው አመለከቷቸው። የተደናገጡት አለቃም ቦታውን ለቀቁላቸው። ለተወሰነ ጊዜ ፀተመስጦ የረጉትን አድማጮች እንግዳ ብርሃን በሚፈነጥቁ ኮስታራ አይኖች ዳሰሳቸው። ዝግ ባለ ድምፅም እንዲህ አሉ።

«እነሆ ከዙፋኑ መምጣቱ ነው-የጋያሱ አግዚአብሄርን መልእክት ይገፍ»

ቃላቱ ቤቱን በድንጋጤ አናጉት። አንግዳው ልብ ቢሉትም ከምንም አልቆጠሩትም። «የአገልጋዩን የአናንተውን አረኛ ፀሎት ሰምቶታል። የምኞታችሁም ፍሬ ነገር ሙሉውን እኔ መልእክተኛው ከገለፅኩላችሁ በኋላ ያላችሁት እንዲሆን ፈቃዱ ነው። አብዛኛው የሰው ልጅ ፀሎት ሲባል ያው አንድ ነው - ሰው ቃም ብሎ ካሰበ ከሚለው ይልቅ የሚጠይቀው ይበዛልና፣

«የአግዚአብሄር የአናንተም ሁሉ አገልጋይ ፀሎቶቻቸውን ፀልየውታል። ግና ቃም ብለው አስበውታል? ኩቶ ፀሎቱስ አንድ ነውን? የለም ሁለት አንጂ። አንዱ የተባለው፣ ለላው ያልተባለው። የተነገረውና ያልተነገረው። ሁሉንም ልመናዎች መስማት ከማይሰነው አምላክ ጆሮ ደርሷል። አሰላስሉት፣ አስታወሱትም፣ ለራሳችሁ ምርቃት ስትሰሙ ተጠንቀቁ፣ በዚያው ሳታስቡት በጉረቤታችሁ ላይ አርግማን እንዲሆን አየለመናችሁ ነውና። ዝናብ ለሚፈልገው ሰብላችሁ ብትፀልዩ በዚያው ምግባራችሁ ዝናብ ለማይፈልገውና በምዕዓቱ ሊጠፋ ቡሚችለው በአንዱ የጉረቤታችሁ ሰብል ላይ አርግማን እንዲሆን እየፀለያችሁ ሊሆን ይችላልና፣

«እናንተም በልባችሁ በስሜት ግና ካላዋቂነትና ካለማስተዋል በዞጥታ የፀለያችሁትን ለላውን ጉዮ በታላት አንድልላችሁ ክአግዚያብሄር ተልኩያለሁ። አግዚያብሄር እንዲሆን ፈቅዷል። አነዚህን ቃላት ሰምታችሁ የለምን? ድሉንም ስጠን፣ ጌታ ሆይ፣ አምላካችን አሚሉት። ይህ በቂ ነው። የተባለውም ፀሎት አንዳለ በአነዚህ አርጉሃ ቃላት ተሰንዓል። ቢንሣ ምን ይጠቅማል? ለድል ስትበልዩ ድልን የሚከተሉት፣ መከተል ያለባቸው- ንሪ አንዲያውም በኋላው ለሚንፏቀቀኑና ላልተጠቀሱ አልፍ ፍጥሚያዎችም ፀልያችኋል። ያልተነገረው የፀሎቱም ጉን በዛ አድማጭ የአግዚአብሄር አባታችን ነፍስ ላይ አርፏል። በቃላትም አንድሰው አዞኖል። ስሙኝ፣

«ጊታ ሆይ፣ አባታችን፣ ወጣት አርበኞቻችን የልቦቻችን ጣኦቶች ወደ ጦርነት መውረዳቸው ነውና ክአጠገባቸው ሁንልን። እኛም ከሚያምረው የውድ ቤታችን ሰላም ጠሳትን ለመደምሰስ በመንፈስ ከነሱ ጋር ተንቃሳቅሰናል። ጌታ አምላካችን ሆይ ወታደሮቻቸውን በመድፎቻችን አንበሚጭ ቃቸው ዘንድ አርዳን፣ ፈንጣቃ የተላበሱ ሚዳያቸውን በድብዝዝ የሙታን አርበኞቻቸው ክምር ማልበስ ይቻለን ዘንድ አርዳን። የመድፎችን ነጭድጓድ በስታይ ከሚንፈራፈሩት ቁስለኞቻቸው ጩኸት እናዋህደው ዘንድ አርዳን። ምንም ያልበደሉ የሙት ሚስቶችን ልብ በዳር የሰሽ ሐዘን እንወጥረው ዘንድ አርዳን። አልባሌ ቤቶቻቸውን በእሳት ሰደድ እንደመስለላቸው ዘንድ አርዳን። ከትናንሽ ልጆቻቸው ጋር ቤት አልባ አርገናቸው ቡቱቶዋቸውን ሉበሰው በረሃብና በጥማት በበጋ ፀሐይ ንዳድ፣ በክረምት ቁፌን በመንፈስ ላሽቀው ግብአተ-መሬታቸውን እንድታፈሳነው ቢማሀኑህም ለእኛ ለምናመልክህ ለትል ነስተሀቸው ወና መሬታቸውን ከለአጋር እንዲደባክኑበት አርዳን።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጌታ ሆይ ተስፋቸውን አጨናግፈው፣ ሕይወታቸውንም አምክነው፣ መራር ስደታቸውን አርዝመህ አርምጃዎቻቸውን አዝግመልን። መንገዳቸውን በእንባቸው ጉርፍ ሙላት፣ በቆሰሉት አግሮቻቸው ደም አቅልማት። በፍቅር መንፈስ ምንጭና ዝንተ ዓለም በሐዘን የሚንከላወሱ ሁሉ አድባርና ወዳጅ ከሆነው ጌታ በፀፀት የተሞላውን ልባችንን ዝቅ አድርገን አርዳታውን እንጠይቃለን። አሜን።»

(ከዝምታ በኃላ) «ፀልያችሁ-ታል፣ አሁንም ከተመኛችሁት ተናገሩ። የልዑል እግዚአብሄር መላእክቱኛ ይጠብቃችኋል።»

በኋላ ከተናገሩት ሁሉ አንድ የረባ ነገር አይወጣውም ተሟሎ ሰውዬው አብድ ናቸው ተባለ።



ዮቶማስ ዮበኩር ልጅ

ተስፋዬ ገብረአብ

ከስራ ባልደረቦቼ ጋር በመኖሪያ ቤቴ በመልካም ሁኔታ እየተዝናናሁ ሳለ አስቸኳይ የስልክ ጥሪ ገጠመኝ። ሳሙኤል ነበር። የልጅነት ጓደኛዬ ሚለዬነሩ ሳሙኤል።

«ሳሚ... ምን ሆንክ?»

«አፈልግሀለሁ፣ አሁኑኑ ና!» ሲል በሲቃ ተናገረ።

ደነገጥሁ፣

«ምኖህል? ችግር አለ እንዴ?»

«በሞትና በህይወት መካከል ነኝ። ፈጥነህ አሁኑኑ ድረስልኝ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

በረገማሁ።

«ምንድነው ጉዳዩ፣ የት'ህ?»

«አነ ራሂል ቤት አጠገብ ነኝ። ፍጠን!»

«ምንድነው የሆነብህ? ለምን አትነግረኝም?»

ሳሙኤል በረጅሙ ተንፍሶ ሲያበቃ፣

«ከራሂል ጋር ችግር ተፈጥሯል። አሁኑኑ ድረስልኝ!»

ምርጫ አልነበረኝም። የስራ ባልደረቦቼን ይቅርታ ጠየኳቸው። አነርሱ መዝናኛታቸውን እንዲቀጥሉ አግባቧቸያቸው ወጣሁ፤

«ከወዳጅና ሰአሪኖው መካከል ምን ተከሰቶ ይሆን?» ስል በአሳብ ተዋጥሁ። ራሂልና ሳሙኤል በእጅጉ የሚግባቡና የሚዋደዱ አርአኖሞች ናቸው። ሳሙኤል ነጋዴና የሰላሳ ዓመት ሰው ሲሆን፣ ራሂል ደግሞ ከኮሌጅ ተመርቃ በአንድ የውጭ ድርጅት ውስጥ የምትሰራ ብርቱና ቆንጅዬ የሀያ ዓመት ኮረዳ ናት። ሲዋደዱ ታይቶ አይታወቅም። በየደቂቃው መሳሳም፣ አይን ለአይን መተያየት ነው። ሁለቱም መልከመልካም፣ ወጣቶችና ጠንኞች በመሆናቸው በእጅጉ ነበር የሚያስቀኑት። እና ምን ጥሟቸው ይሆን?

ከአስር ደቂቃ በኋላ ሳሙኤል ዘንድ ደረስኩ። በቅሎ ቤት ከሚገኘው የራሂል መኖሪያ ቤት ደጅ ጨለማ ውስጥ ቁጭ ብሎ የጮርደን ጂን ጠርሙስ አንቦ ሲጠጣ አገኘሁት። ፊቱ ሳንባ መስሏል። ቁና ቁና ይተነፍሳል። ያበደ ነው የሚመስለው።

መኪናውን ከፍቼ አጠገቡ እንደተቀመጥሁ፣

«ምን ተፈጠረ?» ስል ጠየቅሁት፣

«ራሂል ከዳቺኝ!» አለ - እንደማጥልወል እያደረገው፣

«እንዴት!?»

«ከአንድ ጉረምሳ ጋር ስትዳራ አድ ከፍንጅ ያዝኳት!» ሰውነቱ በድንጋጤ ተሰነጠቀ። 'አድ ከፍንጅ' የሚለው ቃል አስበረገገኝ፣

«ርግጠኛ ነህ? ወይስ አንዲያው ከወንድ ጋር ስላየህት ብቻ!?»

«አያያለም!» ሲል ጮኸ «የአርባ አምስት ብር ቢርጉ ተከራይተው፣ ጉበተው፣ በር ቆልፈው፣ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ቆይተው፣ ከዚያም የሰው አርፉኛ የሰረቀው ልክስክስ ጉረምሳ አዚህ አድርሷት ተመልሶ ሂደ። አነም ይህን ሁሉ ጉድ ከመጀመሪያ አስክ መጨረሻ በአይኔ በብረቱ ካየሁ በኋላ፣ ሽርሙጣይቱንና አለሌውን ወይራን፣ ለመገደል ሽጥጤን አቀባበዬ ተሰናድቼያለሁ። አንተን የጠራሁህም የልጅነት ጓደኛዬ አንደመሆንህ ውሳኔዬ ላይ ስህተት መኖር አለመኖሩን አንድትነግረኝ ነው።»

ሳሙኤል ይህን ሲናገር አይኖቹ ከወዲያ ወዲህ አንደመቁናጥ ይካለቡ ነበር። ይትበጠበጣል። አጁ ሲንተቀተቀበት ማርሹ ላይ አያኖረ ሊያቆመው ይታገላል። ፈፅሞ አአምሮው ትክክል አንዳልሆነ ተረዳሁ።

«መልካም!» አልኩ ረጋብዬ «...በዘህ ጉዳይ ላይ ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያህል መወያየት አለብን። ግን ቦታው አዚህ መሆን የለበትም። ምን ይመስልሀል?»

«የስም!» ሲል ጮኸ «...ጊዜ ማቃጠል አልፈልግም። አዚሁ አንነጋገር። ጥይቶቼን ቅንዝረኛ ጡቷ ላይ ለማርከፍከፍ ቸኩያለሁ»

ይህን ካለ በኋላ አየተንቀሰቀሰ ያለቅስ ጀመር፣ አያለቀሰ በሚነፋረቅ ድምፁ አንዲህ ሲል ቀጠለ፣

«አኔኮ አምናታለሁ። ለርሷ ምን ያልሆንኩት አለ? አወዳታለሁ! ከራሴ በላይ አፈቅራታለሁ። ገንዘቤን፣ ልቤን፣ ጊዜዬን ሁሉ ሰጠሁዋት። ከዚህ በላይ ምን ልሁንላት? ከኔ ምን አጣች? ለሀቅ ፍረድ! አልጋዬ በ25ሺህ ብር የተገዛ ነው። አንሶላዬ ከለንደን ነው የተገዛው። የመኝታ ቤቴን ምንጣፍ ከፋርስ ነው ያስጫንኩት። ሳንተ ምን

t.me/OLDBOOKSPDF

እነግርሀለሁ?... ታውቀዋለህ... ታዲያ ማንም ሰህዉን ከጠረዝበት የ45 ብር ቤርጮ ውስጥ ስትጋደም በአይኔ እያየሁ ምን ልሁን?»

ጭንቅላቴን ጉልበቶቼ ላይ ደፍቶ እየተንሰቀሰቀ ያነባ ቀጠለ። በንግድ ስራ ሁሉም ነገር የተሳካለትና የሰመረለት ሚልዬኔራ የልጅነት ወዳጁ እንዲያ ደስታ ርቆት በስቃይ እየተንሰቀሰቀ ሲያለቅስ የኔም ልብ ዘራፍ ተነካ። የማያርገው ጨካኙ፣ በቅድሚያ ግን ላረጋጋው እንደሚገባ ተገነዘብሁ።

«ሰማኝ ሳሚ... በቅድሚያ ከዚህ እንሂድ?»

«አልሄድም! እንዳታጠለቺኝ አታጥላታለሁ።»

«ደግ እሺ። እዚሁ ሆነን እናውጋ» ብዬ ሰዓቴን አየሁ። ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኗል። በዚህ ሰዓት ከነራሄል መኖሪያ ቤት ብቅ ብሎ የሚያየን ሳይኖር ይችላል ብዬ ተዕናናሁ። እና ወሬ ቀጠልሁ፣

«ግን እንዴት ደረሰበት? በመከላላችሁ አለመግባት ነበር?»

«በጭራሽ! እስክ ምሳ ሰዓትስ አብረን ነበርን። ምሳ ከበላን በኋላ ግን ከሰዓት በኋላ ከጓደኞቹ ጋር ቀጠሮ እንዳላት ስትነግረኝ ተጠራጠርኩ»

«ለምን ተጠራጠርክ?»

«ቅዳሜ ነዋ ቀኑ። ቅዳሜ ከሰዓት ከኔ ተለይታ አታውቅም። እና በቅዳሜ ምድር ከኔ ይልቅ እንዴት ሴት ጓደኞቿ ይበልጡባታል? ብዬ አሰብኩ። አንድ ነገር ይኖራል ብዬም ጠረጠርኩ። ስለዚህ ሶስት ኮንትራት ታክሲዎችን ቁጥሬ በየተራ እየተሰዋወጡ እንዲከታተሏትና የምታደርገውን ሁሉ በስልክ እንዲገልፁልኝ አደረግሁ።»

«አሺ!» አልኩ በመገረም።

«በቃ! እንዳልኩህ ሆነ። ባለታክሲው ደውሎ ቤርጮ ገቡ ሲለኝ፣ ማመን ስላልቻልኩ, ወደተባለው ቦታ ሂጀ ፍቅራቸውን ሬፃፅመው፣ እጅ ለእጅ ተቆላልፈው፣ እየተንሸካሸኩ፣ ሰው እንዳያያቸው ፊታቸውን እየከለሱ ወደ ወይፈኑ ክርካሳ መኪና ሲገቡ በአይኔ በማየት እውነት መሆኑን አረጋገጥሁ።»

የምናገረው ጠፋኝ። ራሂልን ትተህ ሌላ አግባ ልለው አልቻልኩም። ሰርጋቸው አራት ወራት ብቻ እንደቀረው አውቃለሁ። በዚህ ላይ ክልክ በላይ ያፈቅራታል። ሀያወቱ ከራሂል ጋር ተቆራኝታል። በርሰዋ ሰም ጭምር የንግድ ድርጅት ከፍታል። ከቤተሰቡ ጋር አስተዋውቋታል። የትም ቦታ አብረው ታያተዋል። የሰርጋቸው ዝግጅት በስፋት መጀመሩም ሌላ ጣጣ ነበር። እና ጉዳዩን ቀለል አድርገህ ተመልከተው፣ የሚል ምክር መሰንዘር ዋጋቢስ እንደሆነ ተረዳሁ፣ ግራ ገባኝ፣

«ምን ያሸላል ታዲያ?» አልኩት።

«አንተው ንገረኛ፣ እኔ ልገድላቸው ወስኛለሁ። በል ንገረኛ? ግብረገብ መሆኑት አልፈልግም፣ ግባህ? እንዲት የቂል ታል ካንተ አንደበት ብትወጣ አዝንብህለሁ። እንዲያ ከምትሰኝ ታል ሳትተነፍስ ከዚህ ግድም ብትጠፋ. እመርጣለሁ። ራሴ የሚሆነውን አደርጋለሁ።»

ጥቂት አሰብኩበትና እንዲህ አልኩት፣

«ለመጀመሪያ ሳሚ... አንድ ታሳቅ ለሁተት ፈፅመህል። ራሂል በደፈናው ልታምናት ሲገባህ ልትሰልላት ሞክርክ። ለምን ተከታተልካት? በአለም ላይ አያሌ የሚተማመኑ ፍቅረኞች አሉ። እያንዳንዳቸው የሚተማመኑ ፍቅረኞች እውነተኛ ታሪካቸውን ቢናገሩ ስንት ጉድ የሚጉለንል ይመስልሀል? መፍትሔው በደፈናው ማመን ነው።»

አሁንም ከተዋጠበት አሳብ አልነቃም። የምናገረውን በመስማት ላይ ስለመሆኑም ርግጠኛ አልነበርኩም። ግን ቀጠልኩ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከዐሶቱ ውስጥም ወደ ፈተና ሊታግሳን የሚል አንድ ስንኝ አለ። ታዲያ ሰራሂል ለምን ፈተና አዘጋጀህሊትን ምናልባት በዚህች ደቂቃ ዛሬ በፈፀመችው ስህተት እየተፀፀተች ቢሆንስ? ይህን መሰል ድርጊት ላለመድገም እየማለች ቢሆንስ?»

ዲስኩሬን አራዘምኩ፣

«አርባ ዓመት አብረው የኖሩ ባልና ሚስት እንደሚተማመኑ ሲናገሩ ያስቀናሉ። ግን በርግጥ በመካከላቸው መሰራረቅ ኖሮ አልነበረም? ሊኖር ይችላል፣ ላይኖርም ይችላል። ማስረጃ ግን የለም። በደፈናው ግን ይተማመናሉ። አለም በተሰሩ የተምሳሌት ናት። ባል ሚስቱ ታማኝ ናት፣ ብሎ ተስፋ ያደርጋል። ሚስት በበኩሏ ባሌ ከኔ ሌላ አያውቅም፣ ብላ በተስፋ ትሞላለች። እና ህይወትና ፍቅር ይቀጥላል። እውነቱን ማወቅ ያለበት አግዚአብሄር ብቻ ነው። ምክንያቱም ለምች እውነቱን ሁሉ ካወቁ ለመወሰን ይቸኩላሉ። ለመደሰት ይቸኩላሉ። ለመከፋት ይቸኩላሉ። አግዚአብሄር ግን ይቅርታ ማድረግ ይችላል። ለመወሰን አይቸኩልም።»

በመጨረሻ ሳሙኤል ቀና አለ። አይኖቹ አንደበርሀ ቀልተዋል። እንዲህ ሲል በተዘበራረቀ ስሜት ይናገር ጀመር፣

«...ከዚህ በላይ አንዲት ቃል አንድትመዘገብ አልፈቅድልህም። በቃኝ!! እውነቱን ልንገርህ? ከንግዲህ ራሄልን አላምናትም። ገባህ? ከድታኛለች!»

እንደምንም ሰይጣናዊ አሳቡን ለማስወገድ ጥረት ሳደርግ አመሸሁ። ሆኖም ቲስሩ በቀረጠ ስሜት ነበር የሚያዳምጠኝ። አኩሰ ሌሊት አካባቢ እንደምንም ወንጀል ከመስራት ታቅቦ ወደቤቱ ይገባ ዘንድ አግባሁት። ስሜቱ ግን ልክ አልነበረም። ዞሮ ዞሮ ከዚያ የተሻለ ምርጫ ስላልነበረኝ አስከ መኖሪያ ቤቱ ሸኘቼው ወደቤቱ

ተመለስሁ። በነጋታው ግና ወገግ ሲማስቡ በፊት ነበር የሰልክ ጥሪ የቀስቀሰኝ። ደዋዩ በመምህርነት ሙያ የሚተዳደሩት የሳሙኤል ታላት ወንድም ነበሩ። በታፊነና ቡተዘጋ ጉሮሮ «ሳሙኤል ራሱን ገደለ» ሲሉ አረዱኝ።

* * *

እነሆ ዛሬ ሳልሰት ነው...

የሀብታም ሀዘን ግርግር ይበዛዋል። አልታሹ አያሉ ነው። ዘዚህ ለትሶ በእጅጉ የተነካቸው ግን ራሄል ነበረች። ጠጉሯን ትነጫለች፣ ፊትዋን ትቧጥጣለች፣ ይህ ግን አዲስ ነገር አይደለም። ኢትዮጵያውያን ሁሉ በትርብ ዘመዳቸው ቀብር ላይ እንዲህ ማድረጋቸው የተለመደ ነው። የሳሙኤል የቀብር ወዳጅ አንደመሆኑ ራሄልን የማዕናናቱ ሀላፊነት በነው ላይ የተጣለ ነበር። በሳልስቱ የወዳጀን አጮኛ የግድ መሰናበት ነበረብኝ፣

ራሄል በመሀረም አይኖቸዋን አያባበሰች፣

«ለማነው ጥለኸኝ የምትሄደ?» ስትል ሆድ በባሰው መንፈስ፣ አንጀት በሚበላ ዜማ ጠየቀችኝ።

«በዛቀኑ እገኝሻለሁ። ራሄል ተበራቺ...»

«አንዳትጠፋብኝ እደራ። ሲላ ማን አለኝ? ሳሚ እንደሁ ጨክኖ ጥሎኝ ሄዷል። ግን አባክህ ንገረኝ... ሳሚ ለምንድነው ራሱን የገደለው?»

«አላወቅሁም ራሄል» ስል ዋሸሁቀት።

«አንተ የንድ ታውታለህ። ቅዳሚ ማታ አብረኸው እንደነበርክ ሰምቻለሁ። ቢሆንስ ራሱን የገደለበትን ምክንያት መገመት አያቅትህም» ስትል ተነፋረቀች፣

«ራሄል... አሁን አረፍት አድርጊ»

«ታውታለህ ግን?»

«መገመት የምችል ይመስለኛል ራሄል»

«ያ ሀመም ይዞት ነው? ንገረኝ፣ ሳትሰጋ ንገረኝ!»

«አይደለም አመኚኝ»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከኔ ጋር የሚያያዝ ሁኔታ አለው?»

«በክፉል... »

«ልታገስ አልችልም አባክህ! ንገረኝ!»

«አሁን አልነግርሽም። ለፈታችን ቅዳሜ ቀጠሮ እንያዝና ብቻችንን ሆነን አጫውትሻለሁ»

ራሄልን በዚህ መልክ ተሰየሁዋት። ይህ በሆነ በአምስተኛው ቀን፤ ዕለተ ቅዳሜ በቀጠሯችን መሰረት ሻሎን ሆቴል ተገናኘን። በጉዳዩ ብዙ አሳስቦኩበትም። ሆኖም ርስዋ በፈፀመችው ጥፋት ሳቢያ የልጅነት ወዳጄን ሞት እንደነበቀኝ መግለፅ ተገቢ መሆኑን አምኜበታለሁ። ምንም ቢሆን የልብ ጓደኛው ነኝ። ወዳጄ ህይወቱን አጥቷል። ራሄል ጥፋት ፈፅማለች። ብዮፋትዋ መቀጣት አለባት ብዬ ባላምንም ለዘፀት መዳረግ እንዳለባት ግን ይሰማኛል። እምነቴ ይኸው ነበር።

ሻሎን ሆቴል ህብረት አዳራሽ እንደተቀመጥን የሳዋ ያቆጡን ማውጋት ያዝን። ራሄል ጥቁር ለብሳለች። ተጨነቁላለች። ያ ሁሉ የፊካ ውበቷ ጥሏት ጠፍቷል። ያቺ መንገደኛውን ሁሉ ታማልል የነበረች የውበት ቁንጮ በስራ የጉልጠች ባልቴት መስላለች። ከልብ አዘንኩላት። በጉስቁልና አፈርድሜ ከበላው ገፅታዋ ላይ የሚንከባለሱት ዓይኖቿ የጥያቄ ጨረሮችን ይተፋሉ። በጥያቄ ሞተ የተሞሉ የውሃ ጉድጓዶች መስለዋል።

በጨዋታ መሀል እንባዋ ባይንዋ ሲሞላ አስተዋልሁ። ላፅናናትና ላረጋጋት ሞክርኩ። ራሄል ተጉድታለች። ያሁሉ በራስ የመተማመን መንፈስዋ እንደሚያዝያ ጥላ ጥሏት ነጉዷል። ምስኪን ሳሙኤል! አድሰቢስ ራሄል! ያው እንደነገሩ አየተጨዋወትን ወደ ተገናኘንበት ዋና ጉዳይ ዘለቅን፤

«ተበራታሽ ታዲያ?»

«ምንም አልልህ።»

በዝምታ መፋጠጥ ሆነ። ከምን እንደምጀምር ግራ ተጋባሁ። መጀመር ግን አለብኝ። ይህ ግዴታዬ መሆኑን አምኜበታለሁ። ርስዋም ብትሆን እጮኛዋ ራሱን የገደለበትን ምክንያት ለመስማት ጆሮዎችዋን አንቅታ እየጠበቀችኝ ነበር!

«በል ንገረኝ» አለች በደከመ ድምፅ።

«ሳሚ እንደከዳሽው ተረድቶ ነበር» አልኳት።

«እንዴት?» አለች፤ ካልተጠበቀ ዜና ጋር የተላተመች መስላ አልታየችኝም። አይኖችዋ ግን ፈጠጡ። ፍርሀት በደምዋ ውስጥ ሲዘዋወር ያስተዋልሁም መሰለኝ።

«ረጋ ብለሽ አዳምጪኝ ራሄል» ስል ቀጠልሁ።

«ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ከእንድ ሌላ ሰው ጋር ፍቅር ውስጥ እንደነበርሽ ሳሚ አውቋል። በዚህ ምክንያት ፈፅሞ ክፉጥጥር ውጪ ሆኖ ነበር። አንቺንም ሆነ አብሮሽ የነበረውን ሰው የመግደል ፍላጐት ነበረው። እንደምገምተው ግን እኔ ያንን እንዳይፈፅም ላሳምነው ችያለሁ። ይሁን እንጂ ያንቺን ክህደት ሲቋቋመው ስላልቻለ ይመስለኛል ራሱን ያጠፋው። ሳሚ በእጅጉ ይወድሻል። ያምንሽም ነበር። ያ ጠንካራ አምነቱ በድንገትና በፍጥነት ባዶ ሲሆንበት አእምሮው ወደ መናጋት ደረጃ እንደደረሰ እገምታለሁ። እኔ የማውቀው የአሟሟቱ መንስኤ ይህ ነው። አንቺ የምትነግሪኝ የተሰየ ነገር ካለ ደግሞ ልስማ!?»

ራሄል ሁለት እጆችዋን ራስዋ ላይ አድርጋ አቀርቅራ ቀረች። ግንባርዋ ከተደገፍንበት ጠረጴዛ ላይ አሳተመችው። በማንባት ላይ እንዳልነበረች ርግጠኛ ነበርኩ። ሆኖም ደንዝዛለች። እጆችዋ ይንቀጠቀጡ ነበር።

«ራሄል!» ስል ተነፈስኩ።

ቀና አለች።

ገፅታዋ የተቃጠለ ላስቲክ መስሏል።

«አውነት ነው?» ስል ጠየቅሁዋት።

t.me/OLDBOOKSPDF

በደሀንነታ ራስዋን ላይ ታች መዘወሪች።

ልቤ ነጠረ። በዚያው ቅፅበት ሴት ሰይጣን መሰላ ታዮችኝ። ሴት አባብዚ መንታ ምላስ፣ መንታ ልብ፣ ሴትን ያመነ'ም የዘነጎ፣ በሳቱቹ ያን ቱጃን አንገትዋን አንቂ አዚያው ባንፈራፍራት በወደድኩ። ግን ደሞ በዚሁ ስሜት አልቀጠልሁም። ማነው ንፁህ? የማል ጥያቂ ወደ አእምሮዬ መጣ። ጥያቂውን ፈራሁት። እኔ ንፁህ ነኝ።

ራሄል ፊቷን በሁለት እጇ ሞሸፍ ስታብታ፣ እንዲህ ስትል በእለቱ ስለተፈጠረው ሁኔታ አወጋችኝ፣

«...ታላች ስሠተት ነው የተፈፀመው። ግን አንዴት ብዬ ላስረዳሀ? ሳሚ ለኔ ውድ ሰው ነበር። ግን አንድ ችግር አለበት። ይጠራጠረኛል። የመዕሀፍ ቅዱሱን ቁማስ ታውቀዋለህ? የሳሚ ተጠራጣሪነት የዚያን ያክል ነበር። የዮርማሬ ፈረስ ላይ ተፈናጠ፣ በዮርማሬ ተሞልዱ ራሱ በሚፈጥረው የታሪክ ውቅያኖስ ውስጥ የሚዋኝ ሰው ነበር። ከተገናኘንበት አለት ጀምሮ ብቻዬን በሆንኩበት ሰዓት ሁሉ ይከታተለኝ ነበር። ከቤት ወጥቼ እስክመለስ ስለምፈፅመው ድርጊት ሙሉ መረጃ ነበረው። ይህን ሁኔታ የተገነዘብኩት ዘግይቼ ነበር። በኋላ ግን የሚከታተሉኝን ባለታክሲዎችና አግረኛ ቅጥረኞች መኖራቸውን ተረዳሁ። ጀርባዬን የማጤን ልማድ ጭምር አዳበርኩ። ከዚያ በኋላ በመልክ ሰየሁዋቸው። ከአግራ ስር የማይጠፉ የሳሚ ሰላዮች፣ ቀኑን ሙሉ አጅበውኝ እንደሚውሉ አመንኩ። ይህን ሁኔታ ከዓመት በፊት ለሳሚ አነሳሁለት። አሳመሙ። በርግጠኝነት ሀሰት ነው ሲል ካደ። እኔ ግን የሚከተሉኝ ሰዎች በሳሚ የታዘዙ መሆናቸውን ከተ አልተጠራጠርኩም። ከሳሚ የቅናትና የተጠራጣሪነት ባህርይ ተነስቼ ያን ሊፈፅም እንደሚችል አምኜ ነበር። ደግሚ አነሳሁለት። መዕሀፍ ቅዱስ ይዞ ማለልኝ። መልካም፣ ሳሚ ይህን ካልፈፀመ እኔን ማን ሊከታተለኝ

ይችላል? የመንግስት የደህንነት ሰዎች? ሊሆን አይችልም። እኔን ከፖለቲካ ጋር የሚያገናኝን አንዳችም ነገር የለም። ይህን እንደምን ያደረገኝ አንድ ሀቅ ደግሞ አለ። እኔና ሳሚ አብረን በምዝገባት ደቂቃ አንዚያ ጥልግሞት መሰል ታክሲዎች አይናሩም። ብቻዬን አሊያም ከጓደኞቼና ከዘተሰበቹ ጋር በምሆንበት ሰዓት ግን ከየት አንደሚመጡ ሳይታወቅ ከተና ይለሉ። ከስድስት ወር በፊት ሳንጋፖ ለሁለት ቀን አረባት ሂጀ ነበር። ታክሲዎቹ ባይናራም በዚራይ መኪና የመጡ አሽከሮቹን አይቼያቸዋለሁ። የነበረኝ ምርጫ ያላወትኋቸው መስዩ ፕሮግራሚን መተጠል ብቻ ነበር። ሳሚ መሻሻል ባለማሳየቴ ብዙ አሳሰበኝ። ከሳሚ ጋር አብሮ የመተጠል ተስፋዬ ተሟጠጠ። ለሳሚ የነበረኝ ፍቅር ከሌሰት አለት አየቀዘቀዘ መጣ። ከዚያም አልፎ ወደ ጥላቻ ተሸጋገረ። አትፈሙ ሰተኛ ሰይጣን ይመስለኝ ጀመር። ፈራሁት። ልቡ ድፍን ነበር። ለምን ይከታተለኛል? በመጨረሻ ከታላች ወንድማ ጋር በጉዳዩ ላይ በግልፅ ተነጋገርንበት። ከሳሚ ጋር መጋባት አንደማልችል ጭምር ለአባቱ አሳወትሁ። አባቱ ተታወጠኝ። ሳሙኤል ይህን ሊፈፅም አይችልም ብሎ ሽንጡን ገትሮ ተሟገተ። ሙግታችን በአንድ ነገር ነበር የተቋጨው። እኔ ከለላ ወንድ ጋር ፍትሮ ፈፅማ አሳውቅም። ሆኖም ሳሚ አያምነኝም። ለምንድነው የማያምነኝ? ካላመነኝ ለምን አይተወኝም? የጥርጣሬ ሣር በደሙ ስለተሞላ በጉዳዩ ላይ ከሳሚ ጋር በግልፅ መነጋገር ተገቢ ነበር። በጉደዩ ላይ ለመነጋገር ግን ሳሚ ወሬ እቃባይ እንደተክሰበኝ ማመን አለበት። ካላመነ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ልንነጋገር እንችልም። ስለዚህ አባቴና ወንድማ አንድ የማረጋገጫ ሙከራ አዘጋጁ። ይህም ሙከራ ለሳሚ ሀደወት መሞኑት ምክንያት ሆነ» ብለ ግንባርዋን ጠረጴዛው ላይ ደናች። ደንዝዘና ትንፋሹን ውጠው ነበር የማይምጣት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ራሄል ጥቂት አቃስታና እንባዋን አባብሳ በተዘጋ ጉሮሮ መናገርዋን ቀጠለች፤


«ቅዳሜ አለት ታላቅ ወንድሜ ብሩክ ራሱን ለዋውጠ መኪና ተውሶ ቤርገሎ ይዞኝ እንዲገባ ተደረገ። ሳሚ ድንገት ስሜታዊ ርምጃ እንዳይዋስድ ከቤተሰብ የተውጣጣ ከፍ የጥበቃ ሀይል አዘጋጅተን ነበር። እንደጠበትነው ታክሲውቹ እየተለዋወጡ ተከተሉኝ። ቤርገሎ ከገባን በኋላ ሳሚ ራሱ መጥቶ ማረጋገጡን ጭምር አወቅን። ከዚህ በኋላ የሳሚ ጓደኞችና የኔ ቤተሰቦች ባሉበት በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ነበር አሳባችን። ሆኖም ሳይሆን ቀረ! ሳሚ ለመሞት ቸኩሎ። ግን ለምን? ለምን ሳሚ? ሊቋቋመው የማይችለውን መራራ ሀቅ ለማየት ለምን ዝዋንዋ? ለመሞት? ኩቹ አልገባኝም!»

ራሄል እየተንገፈገፈችና እየተንሰቀሰቀች እነባች። ከቶ ታል መተንፈስ አልቻልኩም። እንደ በረዶ ቀዝቅዟ፣ እንደ ሀውልት ደንዝዣ ነበር።

* * *

የሳሚ ቀብር በተፈፀመ በሰማንያኛው ቀን ስሀውልት ምረቃ ተጠራሁ። በዕለቱ ሰንበት ንጋት ላይ የሌፍ ቢተክርስቲያን ተገኘሁ። በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ልማድ መሰረት የሀውልት ምረቃ ስነስርዓቱ በመልካም ሁኔታ ተፈፀመ። የተጠራው ወዳጅ ዘመድ መበተን ሲጀምር ሀውልቱ ስር ፈገግና ደንገፀ ወደቆመችው ምስኪን ወጣት ሴት ጠጋ ብዬ ትከሻዋን ነካኋት። የህሊና ዐለት በማድረስ ላይ ስለነበረች ቀና ብላ አላየችኝም። ዓይኖቹ ግን ድንገት ከሳሚ ሀውልት ላይ በሚነበብ አጭር ዐሁፍ ላይ ተጠለፉ። በግቱር መደብ ላይ በነጭ የተቀረፀው ዐሁፍ እንዲህ ይላል «ዮቶማስ የበኩር ልጅ እዚህ አርፏልል»

ልዘለ



የሽግግት ጌዙ

መሳቱ ገብሩ

(ጊ-ደ-ሞፓሳ ከዓፈው የቀጠለ ፈጠራ ድርሰት)
(ክፍል 2)

ማቲልድ ሉዋዜል አንድ ቀን ምሽት ሚኒስትሩ ባዘጋጀው በዓል ላይ ተገኝታ ባሳለፈችው ደስታ ምክንያት ክፍድ ዘመን አሳለፈች። ለዚያ ዕለት የዳንስ ምሽት ከጓደኛዋ ከዣን ፎረስትየር ተውሳ የሄደችውን የአንገት ጌጥ ስለጠፋባት ብቻ 10 ዓመት ዕዳ ከፈለች። 36 ሺህ ፍራንክ። አስዋን ለመሰለች የቢት እመቤት፣ ባሏን ለመሰለ አንድ ተራ የመንግስት ሰራተኛ 36 ሺህ ፍራንክ መክፈል ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ተወጣችው።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳንድ ጊዜ ብቻዋን ስትሆን በዚያን የዳንስ ምሽት ውንዶች ምን ያህል አንደ ተማረኩላት፣ አንዷት ሆና አንዳመሸች ሚኒስትሩ ለንኒን ዓይናቸውን ጥሰውላት አንደ ነበር ታስታውስና፣

«ያገር*ማል የሰውን ልጅ ሕይወት ሰመሰውነ ወይም ለማጥፋት አንድ ትንሽ ነገር ይበቃል። አንድ ትንሽ ነገር ጊዜ ባይጠፋብኝ ኑሮ ሕይወቴ ምን ይመስል ነበር? ይገርማል» ትላለች የዓለም ሁኔታ አያስደነቃት። ከዚያም ጭልጥ ብላ በትካዜ ትዋጣለች።

ታዲያ አንድ ቀን ዕለድ ከሰምንቱ ከባድ ስራዎቿ ለመገናኘት በሻንዚሊዜ ጉዳና ላይ አለፍ ስትል አንድ ሴት ልጅዋን ይዛ ስትንሸራሸር ከመቅጽበት ተመለከተች። ማዳም ፎርስትየር ነበረች። ዛሬም አንደ ትላንቱ ውጣትነቷን፣ ውበቷን፣ ማራኪነቷን አንደተጐናጸፈች።

ማቲልድ ሽብርክ አለች። ሂዳ ታነጋግራት ይሆን አሥ። በእርግጥ አንጂ። አሁን ዕዳዋን ከፍላ የጨረሰች ስለሆነ ልትነግራት ትችላለች። የሚያሳፍራት ነገር የለም። ተጠግታም አንደምን አደርሽ ገና» አለቻት።

ማዳም ፎረስትየር አላወቀቻትም። በአንድ ጭርንቁስ ቤት በስሟ በመጠራቷ ተገርማ። «ነገር ግን... ማዳም እኔ አላውቅትም።... ተሳስተው ይሆናል» በተቆራረጠ ቃል መለሰችላት።

«የለም አልተሳሳትኩም... እኔ ማቲልድ ነኝ።... ማቲልዶ ሉዋዜል»

ጓደኛዋ በመደነቅ ሴትየዋን ከጫማዋ አስከ ፀጉሯ አየተመለከተቻት «አ! የኔ ሚስኪኗ ማቲልድ... አንዴት ተለውጠሻል?» አለቻት።

«አዎ ብዙ ተለውጫለሁ...» ስትል መለሰች ማቲልድ። «አርጅቼአለሁ ለመጨረሻ ጊዜ ካየሽኝ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ከባድ ቀኖች አሳልፌአለሁ። ብዙ ፈተናዎች... በአንቺ

ምክንያት»

«በእኔ ምክንያት?» ግን ጠየቃቻት።

«በሚኒስትሩ መኪሪያ ቤት ተዘጋጅቶ በነበረው የዳንስ ምሽት ላይ አውሰሽኝ ለሰነበረው የአንገት ጌጥ ታስታውሻለሽ?»

«አዎን። እሺ ታዲያስ?» ስትል ጠየቀች ገና።

«ጠፍቶብኝ ነበር» አለች ማቲልድ።

«እንዴት ጠፍቶብሽ ነበር። እንደመሰለሽልኝ አስታውሳለሁ»

«አይደለም። በ36 ሺህ ፍራንክ ተመሳሰዩን የአልማዝ ጌጥ ገዝቼ ነበር የከፈልኩሽ። ዕዳውን ለመክፈል አስር ዓመት ፈጅቦኝ። ምንም ሀብት ለሌለን ለባለቤቴና ለእኔ ቀላል ነገር አልነበረም።... ሆኖም ከፍለን ጨረስን» አለች ማቲልድ ሉዋዜል።

ማዳም ፎረስትዬር ድንግጥ ብላ ቆም አለች። «ያ ዋስኩሽ ያንገት ጌጥ ስለጠፋብሽ በ36 ሺህ ፍራንክ ከአልማዝ የተሰራ ጌጥ ገዝቼ ከፈልኩሽ ነው የምትይኝ?» በመገረም ጠየቀች።

«አዎ። ልቡነቱን ልብ አላልሽውም ነበር። በጣም ይመሳሰሉ ስለነበር መለየት አዳጋች ነበር»

ይህን ብላ ኩራት በተመላበት ሁኔታ ፈገግ አለች።

ማዳም ፎርስቴዬር በጣም አዝና የማቲልድን እጆች በሁለት እጆችዋ ጭብጥ አድርጋ ይዛ «ሚስኪኗ ማቲልድ የኔ ጌጥ እኮ አርቲፊሻል ነበር። ዋጋውም ከ500 ፍራንክ አይበልጥም ነበር» አለቻት።

* (የአንገት ጌጡ በ1868 በጊዶምፓሳ የተገዛ አጭር ልቦለድ ርዕሰት ነው። መሳቱ ንብሩ ስጊዶምፓሳ ጭብጥ በመነሳት ከዚያ የሚቀጥል የፈጠራ ድርሰት ዕርስል።

ሁለቱ ጓደኛሞች ከተገናኙ በኋላ ምን አደረጉ? እነሆ ይቀጥላል...)

t.me/OLDBOOKSPDF

ማቲልድ ፊት ለፊት የሚገኘው አርከ ደትሪዩንፍ ላይዋ ላይ የወደቀባት መሰላት። ሁሉ ነገር ዝብርቅርቅ አለባት። ሻው ብላ ልትደፋ ስትል ማዳም ፎርስትየር ደገፍ አድርጋ ያዘቻት። በሻንዜሊዜ ጉዳና ላይ ከሚተላለፉት መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ ሰሰኩንድ ዞርዞር እያሉ ተመለከቷቸው። ዣንማቲልድን እንደ ደገፈቻት ሰዋናው መንገድ ማስጓጫ ወደ ተተከሰው ዛፍ አስጠጋቻት።

ማቲልድ እንቅ እንቅ ያለ ትንፋሽ ከመተንፈስ በቀር መናገር አልቻለችም። የሰቆቃ ትንፋሽ ደጋግማ ተነፈሰች። ራስዋን ማወቅ ስትጀምር እንባዋ እንደ ጉርፍ በጉንጮቿ ላይ ይወርድ ቀጠለ።

«እባክሽን አታልቅሽ ማቲልድ፤ የኔ ምስኪኗ ማቲልድ እባክሽን አታልቅሽ» አለች ዣን ፎርስትየር የሰዋም ዓይኖች በእንባ እየተሞሉ።

የማቲልድ እንባ ሊገታ አልቻለም። ፊቷን እያጋመሰ ፈሰሰ። እልህ ጉሮሮዋ ላይ ተናንቃት። ሀቅ ሀቅ ትል ነበር። ልብ በሚሰብር የሕፃን ለቅሶ በድንገት አንድ ልጅዋን እንዲጣች እናት «እባክሽን ዣን፤ ሃሰት ነው በይኝ፤ ሰውነት አይደለም በይኝ» አለች።

«ማቲልድ እኔም ያዋስኩሽ ጊዜ ከአልማዝ የተሰራ በነበረ ደስ ባለኝ ግን አይደለም። አዝናለሁ ማቲልድ፤ የአንገት ጌጡ አርቲፊሻል ነበር።» በማለት መለሰችላት ዕውነት እንደ አለት እየከበዳት።

«አ! ሞንድዬ! አ አምላኬ» በለቅሶዋ ውስጥ ማቲልድ ደጋግማ ተናገረች።

ዣን ስለ አንገት ጌጡ ዕውነቱን ባልነገረቻት ማቲልድ በወደደች። የሕይወት ትርጉሙ አልገባት አለ። የሕይወት ምስጢር ውሉ የጠፋባት ልታቂት ሆነባት። 500 ፍራንክ የማያወጣ አንድ የአንገት ጌጥ ጥላ በየዋህነት የአልማዝ

ሐብል ከፈለች። አልማዙን ተበድራ በመግዛቷም ዕዳዋን ለመክፈል የሰራቻቸው የቤት ውስጥ አድካሚ ሥራዎች ፊቷ ላይ ድቅን አሉባት።

የቆሸሹ ልብሶችና ጨርቆች ስታጥብ ገመድ ላይ ስታሰጣ፤ የወጥ ቤት ዕቃዎችን፤ ድስቶችን በጣቷ ጥፍሮች እየቧጠጠች ስታስለቅቅ፤ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን ቆርቆሮ እየተሸከመች አምስተኛ ፎቅ ደረጃ ስትወጣ፤ ትንፋሽ አያጠራት ቆም ስትል እንደ ሕልም ታያት።

የዕለት ምግቧን ለመግዛት እንደ ተራ ሴት ለብሳ ዘንቢል አንጠልጥላ ከሱካንዳ ነጋዴዎች፤ ከፍራፍሬና ከሽንኩርት ቸርቻሪዎች፤ ከቅመማ ቅመም ነጋዴዎች ጋር የሳንቲም ቅናሽ ለማግኘት የተጨቃጨቀቻቸው ሁሉ በትክዜ ታወሳት።

ከወለድ አበዳሪዎች ጋር የተፈራረመችውን ሰነዶች ለማደስ ጊዜ ለማግኘት ስትለማመጥ፤ ባለቤቷ ተጨማሪ ገንዘብ ሰቢት ለማስገኘት በትርፍ ሰዓቱ ከነጋዴዎች ዘንድ ተቀጥሮ የሰራው በከባዱ የበረዶ ወራት፤ የቤት ማሞቂያ በሌለበት ክፍል፤ በሰነድ አንድ ሉዊ እየተከፈለ ሌሊቱን ሙሉ ጽሑፎችን ሲገለብጥ፤ ይህን ሁሉ በልቦናዋ ተመልክታ አላስችል ብሷት ሽቅብ እየሰበቃት በሲቃ አነባች።

ተፈጥሮ የለገሳት ውበት ቁንጅና በመንከባከብ ፈንታ ጥቅም ለሌለው ነገር አስር ዓመት ሙሉ የወጣችው፤ የወረደችው፤ የደከመችው፤ የዳከረችውን ሁሉ አስታውሳ «ዘፉ አጋጣሚ» አለች፤ የሰው ይሁን የአውሬ ያለየለት ድምጽ፤ ከጉሮሮዋ በፈለቀ ድምጽ።

«ማቲልድ» አለች ዣን ፎረስቲየር፤ ማቲልድን እገሟዋን ቀና እያደረገችና ተስፋ በተመላበት አመለካከት በእንባ ያበጡ ዓይኖችዋን እየተመለከተች «ጓደኛዬ ኩሩና

t.me/OLDBOOKSPDF

በይሉኝታ የተሞላሽ እመቤት፣ አሁንም እኮ ሁሉ ነገር አልተበላሸም። ሁሉ ነገር መታረም የሚችል ነው» ብላ ባጌጠ ክር የተጠለፈ የሐር ማሕረቧን ሰጠቻት።

ነገሩ ያልገባው የማኅም ፎርስትየር ልጅ ከእናቱ ቀሚስ ተከልሎ ሁኔታውን ይከታተላል። «ማን አጥፍቶ ይሆን የተገለበው?» የሚል ስሜት ፊቱ ላይ ይነበባል።

«በቃ አታልቅሽ እንጂ ማቲልድ፣ ሁሉም መታረም የሚችል ነገር ነው።» ግን ሃላቧን ጠንከር አድርጋ ተናገረች።

ማቲልድ ጓደኛዋ ምን ለማለት እንደፈለገች ቢገባትም መልስ ለመስጠት አልፈለገችም። የአንገት ጌጡ በተዋሰችበት ጊዜ የነበረ ውበቷ፣ ወጣትነቷ ዛሬ የለም። ጉንጮችዋ ማድያት አውጥቶባቸዋል። በክባድ የዕለት ተዕለት የሚያቋርጥ ሥራምኽ፣ ሽክሞች ከስማለች። የሙስየ እጆችዋ የእዘ ቆዳ መስሏል። ያ በወጣትነት ጊዜ ታልማቸው የነበረው በታላላቅ ሰምኾ መደነቅ፣ መሸኮርመም፣ በውብ ሳሎን ተቀምጣ ከምሁራን፣ ከደራሲያን፣ ከባለቅኔምኽ ጋር ልታደርግ ታስበው የነበረው ውይይት፣ የተደላደለ የቡርዣዋዋ ሕይወት ምኞት ዛሬ የሉም። እና ለማን፣ ለምን፣ ለየትኛውስ ተረ ዕድሜ? የመሳሰሉት ጥያቄዎች ዥንጉላቷ ውስጥ ተጉላሳ። ተሸሉ በመቁረጥ በጥ አለች።

«እይው ማቲልድ፣ በፊቱንም የአንገት ጌጡ እንደጠፋብሽ መኖተሽ ተነጋግረሽኝ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ፈተና ባልተቀበልሽ ነበር። ሆኖም ለምን አንድ ነገር ሆነ ማለት አንችልም። አይገባንም። አሁን አንቺና እኔ ብዙ የምናስተካክለው ነገር አለ።» አለች ማዳም ፎረስትየር።

«ምን ነገር ይኖራል? ዕድሜ አንዴ ወራጅ ውሃ ነው። በወራጅ ውሃ አንድ ጊዜ ብቻ ነው መታጠብ

የሚቻለው። ሁሉ ነገር ተበላሽቷል» በማለት ማቲልድ አንባዋን ጠረገች።

በሻንዚሊዝ ጉዳና ላይ ወደ ሚገኘው ካፌ ሻንዚሊዚ አመሩ። የማዳም ፎረስትየር ልጅ የአናቱን ቀሚስ አንደያዘ ከስር ከስራቸው ሱክ ሱክ አለ። «ካፌ ሻንዚለሊዜ» ሰፋ ያለ አፃራሽ ነው። በሰዎች ግጥም ብሏል። በደንበኞቹ ፊት በትናንሽ ዙብ ጠረጴዛዎች ላይ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ የተለያዩ ቀለማት የመጠጥ ዓይነቶች በብርጭቆዎቹ ይታያሉ። የካፌ ሻንዚሊዚ ደንበኞች አለባበስ ማንነታቸውን ይገልጣል። ማቲልድ የለበሰችው ልብስ አሳፈራት። በወንበር ላይ ሽምቅቅ ብላ ተቀመጠች። ግን አሳላፊውን ሶስት መጠጦች እንዲያመጣላት አዘዘች። ማቲልድ ረጋ ብላለች።

«ይኸውልሽ ማቲልድ።» በማለት ማዳም ፎረስትየር የተጀጠረውን ንግግሯን ቀጠለች። የማቲልድን ቅርፋፋ እጆች ከህፃን ልጅ የተሻለ በለሰለሰ እጆቿ ጭብጥ አድርጋ ይዛ።

«ዛሬ አንን ማግኘትሽ ለመልካም ነገር ነው። የሰጠሽኝ ጊዜ ቤት አለ። ተጠቅሚበት አላውቅም። ዛሬ ሞዱ ተሰውሯል። የጋሪ አልባበስ ጊዜ ሰድስት ወር አይቆይም። በየምሽቱ ይለዋወጣል። የምንተስኪዱን የፔርሺያ ደብዳቤዎች አንበሽ የለም። አንድ ሴት ከፓሪስ ወደ ገጠር ሂዳ ሰድስት ወር ብትቆይ ሰላሳ አመት ያህል ኋላ ቀር ትሆናለች ብሏል። ጊዜ አልፎበታል በማለት ያን ሀብል ከሚጣጣጥ ማስቀመጫ እንደተውኩት አምስት፣ ሰድስት ዓመታት ይሆንዋል።» ማዳም ግን ፎረስትየር ለማቲልድ ጌጡን ለመመለስ ቸኩላለች። ባለማወቅ ላደረሰችባት በደል ካሳ ቢሆናት።

«ያለም እይሆንም» አለች ማቲልድ። የአንገት ጌጡ ያንች ነው። ስጥቼሻለሁ። የአንገት ጌጡ ንብረትሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። አልቀበልም። ደሃ እንጂ ለማኝ አይደለሁም። አሁንም ለመሥራት የሚችል ጉልበት አለኝ» አለች ማቲልድ።

«እንደ እሱ አትበይ ማቲልድ! እንደ ጓደኛ እንጂ እንደ በታች ቆጥሬሽ አይደለም» ስትል ለመነቻት የቀረበላቸውን መጠጥ እየጋበዘቻት። የዣን ልጅ የእናቷን አጣጭ ይዞ ወደ አርሱ አያዞረ እንዲድ የሚል ምልክት አሳየ።

«እሺ ሞን ፕቲ» አለች የእናትነት ፈገግታዋን እየሰጣበች። ማቲልድ ልጇንና እናቱን ተራ በተራ ተመለከተቻቸው። ተከዘች። ሙሉ ጤነኛ ነች። ባሏም ጤኛ ነው። ሆኖም ግን ለልጅ አልታደሉችም። ዓይኖችዋ ወዲያውኑ ዕንባ የመሰሉ አንባሮች አዘሉ። አለመታደል! ዕዳዋን ስመክፈል ስትታገል ልጅ አልወለደችም። ባለባት ዕዳ ላይ ልጅ ተጨምሮ እንዴትስ ትወጣው ነበር። ከዓይኖችዋ ትናንሽ እንክብል እንባዎች ዱብ ባሉ ቁጥር ሊሰሯ እንክብሎች ወዲያውኑ ይከማቹ ነበር።

«ማቲልድ አባክሽ ደግሞ እንደገና አታልቅሺ። ዕንባሽን ባየሁት ቁጥር ልቤ ያዝናል። በይ አሁን ወደ ቤት እንሂድ የአንገት ጌጡን ልስጥሽ። የአሥር ዓመት የድካምሽን ፍሬ...» ብላ ማዳም ፎረስትየር ብድግ አለች። የመጠጡን ሂሳብ እንደቆመች ከፈለች። ቁጥሉ ወደ ቤት አመሩ።

«ማያም ሉዋዘል ይህን ያህል ጊዜ የት ጠፋሽ?» አለ መስየ ፎረስትየር ብድግ እያሰና መነጽሩን እያወለቀ። የሚያነበውን ጋዜጣ አጠፈና «ወደ አዲሱ አህጉር ወደ አሜሪካ ሂደሽ ነበር? ዛሬ ሁሉ ሰው ይሄዳል። ሳቪ ፍራንሷዝ ለፊጋሮ ሰንሱዋ፣ ለቪኦግ የተሰኙ ጋዜጦቻችን ሁሉ ስለ አውሮፓ ዜጎች በየወሩ በርካታ ቁጥር እንደሚፈልሱ ይጽፋሉ። ለጤናሽ ደህና ነሽ? አሜሪካ እንዴት ነው?»

«የለም ኪፓሪስ አልመጣሁም። ሳንገናኝ ቀርተን ነው። ደግሞ መንገዣውም ብዙ ነው» ስትል መለሰች ማቲልድ ዣን ያሳየቻት ማረፊያ ላይ እየተቀመጠች።

«ዛሬ በጣም ውድ አይደለም። የፈረንሳይ አስተማማኝ የሆኑ የመንገደኛ መርከቦች አሉ። ዣንና እኔ ሂደን መጥተናል። ትልቅ አገር ነው» አለ መስየ ፎረስትየር አአጠቃቢ እየተቀመጠ።

ዣን «አስቴል» እያሉች የቤት ሰራተኞዋን ጠራቻት።

አስቴል ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ቀልጠፍ ብላ ቀረበች።

«በይ የሚጠጣ» አለች ዣን ኮራ ባለ ትዕዛዝ። መስየ ፎርስትየር ስለ ጋዜጦች ቅኝ ግዛቶች ማውራቱን ቀጠለ። የአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ፈረንሳይ ብዙ ቅኝ ግዛት በሰሜን አፍሪካ በሩቅ ምስራቅ ቅኝ ግዛት ያገኘችበት። ዋና ተወዳዳሪዋ ብሪታንያ ዓለምን በማንበርከክ ከፍተኛ ቦታ እንደያዘች፣ በሌላ በኩል ግን ፖርቱጋልና ስፔን ቅኝ ግዛቶቻቸውን በአሜሪካ አያጡ መሆናቸውን ተረከላት። ማቲልድ በግማሽ ልቧ አዳመጠች።

«ፒየር» አለ ደግሞ መስየ ፎረስትየር ልጅን እየጠራና በጉልበቱ መሀከል አያስጣው «ፒየር ዝርዝሩ እንዴት ነበር?»

«አልተንሸራሸርንም ማማ ታለቅስ ነበር። የማማ ደግሞ አታልቅሽትል ነበር» አለ ፒየር የእናቱንና የማቲልድን ሁኔታዎች ለአባቱ እየገለጸ።

«የምን ለቅሶ ዣን አልትሰሽ ነበር» በመገረም ባለቤቷን ጠየቃት።

ዣን አጋጣሚ ትጠብቅ ነበር። ለባለቤቷ ማቲልድ ከሚኒስትር መስሪያ ቤት የዳንስ ምሽት ቢኒሳ የደረሰባትን ሁሉ በአጭሩ ተረከችለት። መስየ ፎረስትየር ባለቤቱን አያዳመጠ። «አ ጋርኳ » ይል ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ይሁንና ማዳም ሱዋዜል አሁንም ብዙ አላጣሽም። ወደ መጨረሻ የተገኘ ገንዘብ በወጣትነት ከምናገኘው ይሻላል። የአንገት ጌጡ በእጃችን አለ። ጥገ ፈጠን በይ እንጂ፣ የጌጣ ጌጥ ማስቀመጫ ዕቃሽን አምጭና ማቲልድን እንካሳት።»

ጥገ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። መስዬ ፎረስትየር ኢስቴል የቀዳችላቸውን ቀይ ወይን ጠጅ ማቲልደን እየጋበዘች «ለወደፊቱ መልካም ኑሮሽ» አለ በፈገግታ።

ጥገ ፎረስትየር ወደ ሳሎን ስትመለስ አንድ ትንሽ ሙዳይ ሳጥን፤ ኢስቴል የቤት ሰራተኛዋ ሌላ ሙዳይ ሳጥን ይዘዋል። ከጠረጴዛ ላይ አስቀመጡ። ኢስቴል ጓዳዋ ተመለሰች።

«ማቲልድ ነይ የአንገት ጌጥሽን ተረከቢኝ» አለች በልበሙሉነት፤ በፈገግታና በኩራት። የመጀመሪያው ሳጥን ተከፈተ። ብራስሌት፤ ሀብል፤ አምባር፤ የጣት ቀለበቶች፤ የደረት ላይ ጌጦች፤ አቨብርቀዋል። ያገዘባርቃሉ። ያመከረኛ የአንገት ጌጥ አልነበረም።

ሁለተኛው ሙዳይ ሳጥን ተከፈተ። በልዩ የአንገት፣ የእጅ፣ የጣት ጌጣጌጦች ተሞልቷል። ያ መከረኛ የአንገት ጌጥ አልነበረም። በጥታ ነገስ። መስየ ፎረስትየር ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ብንን አደሰ «ኦፒሮዲ በ1890 - 91 የዛሬ ሰስት ዓመት የዘመን መለወጫ ዋዜማ ምሽት ለቤት ሰራተኞችን ምን እንስጣት ብለሽ ባቀረብሽው ሃሳብ መሰረት ለማድመ ዋዜል ሌሌስት ፊኖ የአንገት ጌጡን ሰጥተናታል» አለ።

«ሊሆን አይችልም» አለች ጥገ በሁለት እጆችየ ከንፈሮቿን እያፈነች «ሊሆን አይችልም።»

«ማድመ ዋዜል ሌሌስት ብርቱ ልጅ ነበረች። በገዙህ ስላገለገሉችን ስራው ጥሩ የሆነ ጌጥ እንስጣት ብለን በተስማማነው መሰረት የአንገት ጌጡን ሽልመናታል።

በ1890 የዘመን መለወጫ ምሽት» አለ በድጋሚ መሲየ ፎረስትየር።

ማዳም ፎረስትየር በአስቸኳይ የግል ጠረጴዛዋን መሳቢያ ከፍታ አንድ መዝገብ አወጣች። ገጹን ገልበጥ ገልበጥ አድርጋ ማንበብ ቀጠለች። «ሌሌስት በፎንቴና ጉዳና ላይ ከወላጆችዋ ጋር ነዋሪ» መዝገቧን ዘግታ «አስመልሳታለሁ፤ ገንዘብም ቢሆን ሰጥቼ» አለች በተበሳጨ ቁጭት በተመላበት አነጋገር። እጅዋ ላይ የገባው ጌጥ በምታት እንዳመለጣት እያሰበች።

በነጋታው ከማቲልድ ጋር ጥገ ፎንቴን ጉዳና ላይ ከሚገኘው የሌሌስት መኖሪያ አድራሻ ሄደች። ወላጆችዋ ሕንፃ ጠባቂ ኮንሲየርዥ መሆናቸውን በወሬ ሰምታለች። የሕንፃው መጀመሪያ መግቢያ አንላለፈች አንድ ሴት ከአንግዳ መቀበያው መስኮት አንገታቸውን ቀረብ አድርገው «ምን ልርዳምት» አሉ። የ50 ዓመት ሴት ይሆናሉ።

«አባከምትን... እ... አባከምን ማድሙ ዋዜል ሌሌስት ፊኖን ነበር» አለች ጥገ በትህትና። «እኔ ማዳም ጥገ ፎረስትየር አባላለሁ»

«ማዳም ጥገ ፎርስትየር ኦ! ደን ሴት... ይግቡ ወደ ውስጥ» ብላ ሕንፃ ጠባቂዋ አንድ ትንሽ በር ከፍታ ወደ ቢሮዋ አስገባቻቸው «ባለቤቴ ቤት የለም። ሌሌስት ልጃችን ነች» አለች አዛውንቷ። ጥገ ደስ አላት።

«ደን ሴት! ሩህሩህ ሴት ነምት ማዳም ፎረስትየር ልጀ ሁሌም ስምምን ታነሳለች። ታመሰግንምታለች። ደን ሴት ትሁታለች» አሉች ማዳም ፊኖ።

ጥገና ማቲልድን እያስተናገደች «ማዳም ፎረስትየር ልተዋወቅምት ስፈልግ ብዙ ጊዜዬ ነው። የዘመን መለወጫ ምሽት ባከበርን ጊዜ ሁሉ ስምምን እናነሳለን።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለአንድ የቤት ሰራተኛ ከአልማዝ የተሰራ የአንገት ጌጥ መሰጠት ቀላል አይደለም» አሉት ማዳም ፊና ለእንግዶቻቸው ካማምቤር ፎርማጆና ነጭ ወይን ጠጅ እያቀረበችላቸው።

ማቲልዴ «ነገሩ ተበላሽቷል» አለች በሆድዋ።

«ደግ ሴት» ማዳም ፊና ተናገረች።

«አሁን ማድመጡ ዋጂል ሴሊያትን ማግኘት ይቻላል» ሱትል ጠየቀች ጣን በጉጉት።

«ሴሊያት?...?... አም ወደ አሳያቱ ሀገር አሜሪካ ስመሄድ ብዙ ታሪክ ነበር። ታዲያ ገንዘብ አየቸገራት ትናደድ ነበር። አንድ ፍራንሰዋ የተባለ ዘመድ አለን። የወርቅ ቤት ሰራተኛ። ጥሩ ልጅ ነው። ትሁት።... እና ሴሊያትን አንድ ቀን የመርከብ መጓጓዣ ቸገረኝ ከምትይ ለምን የአንገት ጌጥሽን አትሸጭውም» አላት።

«ኦ ምንዛዬ... ኦ አምላክ» አለች ማቲልዴ ባታውቀው በኃይል እየተነፈሰች «ይቅርታ ማዳም ፊና ይቀጥሉ» አለች ጣን።

«ልጀም የአንገት ጌጡ እኮ አርቲፊሽያል ነው አለችው። ፍራንሰዋም እኔ አርቲፊሻል ና ጥሩ ሰራ አውቃለሁ። ይኸ 50 ሺህ ፍራንክ የሚያወጣ አልማዝ ነው። ከአልማዝ የተሰራ የአንገት ጌጥ ነው አላት። ሴሊያትም ታዲያ አንተ ሽጥልኛ አለችው። በ40 ሺህ ፍራንክ ሸጠላት። ከዚያም ልጀ ሃሳቧ ተሳካላትና የመርከብ መጓጓዣ ከፍላ ወደ አሜሪካ ወደ ኑቮ ኦርሌያ ከሄደች ቆየች።... አንድ ዓመት አለፋት» አለች ማዳም ፊና አንገቷን ቀና አድርጋ በሃሳብ ወደ ሌሰት አየመጠቀች።

ልለለደ



የቢዱ ታሪክ

አሸቱ ተፈራ

ስለ ቢራ የተለያዩ አምልኮዎችና አምነቶች አሉ። አርጉዝ የሆኑ የጀርመን ሴቶች ምግብ እንዲሆናቸው ቢራ ዘወትር ይጠጣሉ። የናይጀሪያ ወንዶች የወሲብ ስንፍናን ለመከላከል ቢራ ፉት ይላሉ። የማሌዥያ ሴቶች በሽታን ለመከላከል ልጆቻቸውን በቢራ ያጥባሉ። ሩሲያ ውስጥ አንደ ስካር ማብረጃ ይገለገሉበታል።

ቢራ የተለዩ ስሞች አሉት። ቢራ፣ ቢር፣ አሌ፣ ስታወት፣ ፒልና፣ ክርስቲና፣ አናት - ይባላል። ከውሃ ቀጥሎ በዓለም ላይ የሚጠጣ መጠጥ ቢራ ነው። የ1976

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓ.ም መረጃ እንደሚያመለክተው በዓመት 12.4 ቢልዮን ሊትር ቢራ ተጠጥቷል።

ቅድመ ልደት ክርስቶስ 1800 ላይ የነበረው ንጉስ ሐሙራቢ የቢራን ዋጋ ያስወደደ ነጋዴ ከነነፍሱ ወንዝ ውስጥ እንዲጣል ደንግጐ ነበር። የግብፅ ፈርኦኖች ቢራ ከመውደዳቸውም በላይ ሲሞቱ እንኳ የቢራ በርሜል አብሯቸው ይቀበር ነበር። በአውሮፓም በመካከለኛው ዘመን በመሸታ ቤት የተደረጉ ስምምነቶች በፍርድ ቤት ተቀባይነት ነበራቸው። በተለይ በቢራ ላይ የተፈረመ ውል ክብደት ነበረው። በአክስፎርድና በኬምብሪጅ ስር የነበሩ ኮሌጆች በሙሉ አንዳንድ የቢራ ፋብሪካዎች ነበሯቸው። በታላቋ ብሪታንያም ታሪካዊው ማግና ካርታ ሰነድ ውስጥ እንኳ ላይቀር ስፍራል። የጀርመን ማዘጋጃ ቤቶችም ስብሰባ አዳራሽቻቸው ምድር ቤት ውስጥ የቢራ መቸርቸሪያ ሱቆች በብዛት አቋቁመው እደነበር ታሪክ መዝግቦታል። የወንድና የሴት ገዳማትም በቢራ መጥመቂ ተግባር ላይ ተሰማርተው ነበር። መነኮሳትም በያም ጊዜ ክብደታቸው እንዳይቀንስ በማለት ቢራ በብዛት ይጠጣሉ።

በ16ኛው ምዕተ ዓመት ደግሞ የሮማ ቤተክርስቲያን ቢራ ለመነኮሳቱ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ በብዛት እንዲመረት ቅዱስ ፈቃዷን ሰጥታለች። ይህም ቢራ በብዛት እንዲጠጣ አስተዋፅኦ አድርጓል። ለምሳሌ አንዲት የእንግሊዝ ሴት ወይዘሮ በቤተመንስቱ ውስጥ በቁርስ፣ በምሳ፣ በመክሰስና ማታ ከመተኛቷ በፊት አምስት አምስት ጠርሙስ ቢራ እንድትጠጣ ተፈቅዶላት እንደነበር ተዘግቧል። የሄንሪ 8ኛ ልጅ፣ ልዕልት ኤልሳቤጥ ደግሞ ቢራ ከመውደዷ የተነሳ ለማንም እንደማታካፍል ተዕፎ ይገኛል። አንድ የዳች ከበርቴ በዓመት 360 ሊትር ቢራ ይሰረግብ እንደነበር ታውቋል።

ቢራ ሲጠመት የሚገኘው መቀት የኬሊራንና የተስቦን

ተሀዋስያን ይገሳል። በ18ኛው ክፍለ ዘመን ሕይወት ያለ ቢራ የሚታሰብ ነገር አልነበረም። ፕሬዚዳንት ዋሺንግተንና ማዲሰን የየራሳቸው የቢራ ፋብሪካዎች ነበሯቸው። ቶማስ ጀፈርሰንም የቢራ ገብስ ከጀርመን ወደ አሜሪካ እንዲገባ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ከቢራ የሚገኘው ታክስ በሆላንድ የሚገኙ ታላላት ግድቦችን ለመስራት ጠቅሟል።

በየሀገሩ የቢራ አዘውታሪዎች ቁጥር ይለያል። አንድ ሰው በዓመት በብሪታኒያ 100፣ በአውስትራሊያ 124፣ በቤልጂግ 135፣ በቼኮዝሎቫኪያ 132፣ በምዕራብ ጀርመን 139 ሊትር ቢራ ይጠጣል። በተለይ ባቫሪያ በተባለች ጀርመን ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቢራ በመጠጣት የሚደርስባቸው የለም። አንድ ሰው በዓመት በአማካይ 440 ሊትር ቢራ ይጠጣል። ይህ አንድ ትልቅ የመዋኛ ኩሬ መጠን ነው። እኛስ ሀገር ምን ያህል ሊትር ቢራ ይጠጣ ይሆን?

በባቫሪያ ግዛት በዓመት አንድ ጊዜ የቢራ በዓል ይከበራል። በመስከረም ወር ነው የሚከበረው። በዓሉ 16 ቀናት ይወስዳል። በበዓሉ ላይ 6 ሚልዮን እንግዶች ይገኛሉ። በዚህን ወቅት 4 ሚልዮን ሊትር ቢራ ይጠጣል። በዚሁ ሳቢያ 800ሺ ሳንድዊችች፣ 400ሺ ዶሮዎችና በብዙ ሙቱ የሚቆጠሩ ድልብ ሰንጋዎች ለተመጋቢዎች ይቀርባሉ። ብዙ ኩባንያዎች ሞቅ ያለ ትርፍ ያገኛሉ።

መጣጥፍ

t.me/OLDBOOKSPDF



ድርቅ - የአድገት ፀር



ቴዎድሮስ ሙሳቱ

የታሪክ አካል ነው

የምንወጥነው የምንሰራው ሁሉ፣
የታሪክ አካል ነው ሲጠና በውሉ።
ለሰው የሚመስለው ታሪካዊ ስራ
የሚጸፍ ብቻ ነው ትውልድ የሚያኮራ።
ነገር ግን ላጤነው ጠቅላላ ኑሯችን
የታሪክ አካል ነው የግል ሕይወታችን።
ሰው በግሉ ሮጦ ጥሮ ተጣጥሮ
ወይ በድርጅት በመንግስት ተፋጥሮ
የሚሰራው ስራ በአንድ ተደምሮ
ታሪካዊ ድርሻው ያምራል ደምቆ ሰምሮ።
እያንዳንዱ ተግቶ ውጤት ቢያስመዘግብ
ሕይወቱን ቢያሻሽል ቤተሰብ ቢያጠግብ
የእያንዳንዱ ጥረት በመሆን ጅረት
ታሪክ ይወጣዋል የሚስብ ትኩረት
ግለሰብ በቡድን፣ ቡድንም በድርጅት

t.me/OLDBOOKSPDF


እየተዋቀረ፣ ቢወጣ ከማጀት
ይቻለው የለም ወይ ታሪክን ማበጀት።
ሁሉም በየድርሻው በርትቶ ከጣረ
የሚያመጣው ፋይዳ፣ የታሪክ አካል ነው እጅግ የከበረ።
ሁሉም በየሙያው ድርሻውን ቢወጣ
ይሞታል ስንፍና የትውልድ ባላንጣ።



ለፊገማታ

ሁለት ሰካራሞች መንገድ ላይ ሲሸኑ ፖሊስ ይደርስባቸውና በቁጣ፣

- «...መሽናቱን አቁሙ፣ ብልታችሁን ወደ ሱሪያችሁ ክተቱ» የሚል ትእዛዝ ይሰጣል። ፖሊሱ ትንሽ ፈቀቅ እንዳለም አንዱ ሰካራም በሳቅ ይንከተከት ጀመር ግራ የተጋባው ጓደኛው «ምን አገኘህ» ይለዋል። የሚስቀውም «ፖሊሱን አሞኝሁት፣ ወደ ሱሪዬ ክተትኩት እንጂ መሽናቱን አላቆምኩም አኮ» ሲል መለሰለት።



ደሁዳ

ከህሊል ጊብራን
(ትርጉም) ብርሃነ መስቀል ደጀኔ

አስቀድሞ ስለራሴ፣ ከኢየሩሳሌም ዳርቻ ነዋሪ እና የአስቆሮቱ ይሁዳ ባልንጀራ ነኝ።

እንዲህ ሆነላችሁ።

ዕለተ አርብ አመሻሹ ላይ ነበር። የአይሁድ ፋሲካ ዋዜማ ማለት ነው። እና ይሁዳ ከቤቱ መጣ። ገና እንደደረሰ ነበር የቤቱን በር ለጉድ የደበደበው።

በሩን ከፍቼለት ገባ። ሳስተውለው ፊቱን አመዳይ ነገቶበታል። እጆቹም ነፋስ እንደሚያርገደግዳቸው ደረቅ ቀንበጦች ይንቀጠቀጡ ነበር። ልብሶቹም ልክ ከወንዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተነፍቆ እንደወጣ ሰው በውሃ ሾተው ነበር። ሰንገሩ ያን ምሽት ሰዓት - ውሽንፍራማ የገናብ ዶፍ እየወረደ ነበር።

እና ይሁዳ አተኩሮ አየኝ። አኔም ትክ ብዬ አስተዋልኩት። የዓይኖቹ ጉድጓዶች እግዚአ! የጨለማ ጉድጓድ ይመስሉ ነበር። ዓይኖቹም ደም ሰብሰው ነበር። ወዲያው «የናዝሬቱን ኢየሱስ እሱ ሰጠላቶቹና ሰጠላቶቹ አሳልፌ ሰጠሁት!» አለኝ።

አሁንም አጆቹን እያወናጨፈ «ኢየሱስ በጠላቶቹና በህዝባችን ጠላቶች ላይ ድልን ፈፅሞ እንደሚጐናፀፍ ይናገር ነበር። እና በዚህ ምክንያት አመንኩት። ተከታዩም ሆንኩ!» አለኝ።

«አም! መጀመሪያ እንድንከተለው ወደራሱ ሊጠራን ወሰነ። ሰፊ እና ኃያል በሆነው መንግስቱ ውስጥ ስፍራ እንደሚኖረን ቃል ገብቶልን ነበረ። እና በመጪው መንግስቱ ውስጥ የከበር ስፍራ እንደሚኖረንና ፈፅሞም እንደማይረሳን አመንን።

«ኢየሱስ ስለመጪው መንግስቱ ብዙ ብዙ ብሎናል። እኔህ ሮማውያን በእኛ በእይሁዳውያን ላይ ገዥ እንደሆኑቱ እኛም በኢየሱስ መንግስት ልዑላን እንደምንሆን ገመትን። በበኩሉ እኔን ከወዲሁ የከብር ዘቡ ዋና አባገር እና የንጉስ ነባስታዊ ሰረገላዎቹ ዋና ባልደራስ አድርጐ እንደመረጠኝ አሰበ ነበር። እና በዚህ ምክንያት ጨርቄን ማቄን ሳልል በሙሉ ልቤ ተከተልኩት።

«ግና ያ ኢየሱስ የሰበክን መንግስት ሰላ የአውን መንግስት አልነበረም። አም! ከጨቋኙና ከታሳቂ የሮማ መንግስት ባርነት ነፃ የሚያወጣን አልነበረም። ለካ ሲሰብክን የከረመው ሰፊና ሰፊ ግዛቱ መንግስቱ የልብ ውስጥ ግዛት ነበር። አም! ስለርሀራሄ፣ ስለቸርነትና ስለፍቅር ሃያልነት ደጋግሞ ሲናገር ነበር። ነገሩ የገባኝ ኋላ! የኋላ የኋለማ ያ መንገደኛ ሊቶችን ሁሉ የሚያማልለው

አፍዝ አደንግዝ ስበካው ልቤን በምሬት አነደደው።

«እና ያ ታላቁን ተስፋ ጥቡበት የነበረ ንጉስ አይሁድ ድንገቴኑ ተስውጦ የመንግድ ዳር መወቴምችንና የቀማኞችን ልብ በተራ ዋሽንት የሚያነሆልል ቀላማጅ ሆነበኝ።

«እምልህ - የተቀሩቱ አይሁዳውያን ወነኖቹ ያፈቅሩት እንደነበር ሁሉ እኔም አፈቅረው ነበር። በተለይ እኔ ከተጫነብን የባዕዳን ቀንበር ነፃ እንደሚያወጣን ፍፁም ተስፋዱን ጥቡበት ነበር። ግና በሮማውያኑ ጨቋኝ ቀንበር ላይ እጀችንን እንድናነሳ እንኳን ቃል ትንፍሽ ሲል ይብሱኑ የቄሳርን ሰቀላር ስጡ! ኃያሰ ሲወተውት - ልቤ በቁጣ ከመንደድም ተስፋዱ ውስጤ ሞተ። ያኔ ለራሴ እንዲህ አልኩት - ኀስፋና ህልሜን የገደለ ሊሞት ይገባዋል!' አልኩ። አም! ተስፋዱና እምነቱ ደግሞ ከማንኛውም ሰው - በተለይ ቃሉን ከሚያጥፍ ሰው ህይወት የላቁና ኃውድ ናቸው።»

ይሽን ሁሉ ካሰኝ በኋላ ይሁዳ ጥርሶቹን እያፋጨ እንገቱን ደፋ። ትንሽ ቆይቶም ቀና አለና መልሶ «ኢየሱስን አሳልፌ ሰጥቼዋለሁ። አናም ዛሬ ሰቀሉት!! የገረመኝ ነገር መስቀሉ ላይ እንደተራ ሰው ቢቸነከርም አሚሚቱ ግን እንደ ኩሩ ንጉስ ግርማዊ ነበር። አም! ከክፉትና ከመቃብር በላይ ሀያውና ዘለዓለማዊ ሆኖ እንደሚኖር - ከአሚሚቱ ሞገስ ታላቅ ምልክት አይቻለሁ!...» አለኝ።

«ያም ሆነ ይህ - አሚሚቱ ግርማ ሞገስን የተላበሰ ነበር። ልቡም ፍፁም በሆነ ርህራሄና ጥልቅ በሆነ ይቅርታ ሞተሞላ ነበር። አሳልፌው ሰሰጡት እንኳ ርህራሄና ይቅርታው አቻ የለውም!!» አለኝ።

እስከዚህ ድረስ በፀጥታ ሳዳምጠው የቆየሁት ሰውዬ «ይሁዳ!» አልኩት «ይሁዳ! መቼም ታላቅ ስህተት ፈፅመሀል!» አልኩት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሁዳም ወዲያው መልሶ «አቪ! መቼም እንዲ የሆነው ሆኗል» አለኝ። «ይሁንና እንደገርከህ ኢየሱስ የሞተው እንደ ግርማዊ ንጉስ ነው። ግና ጅግና ከሆነ ለምን እንደ ንጉስ አይኖርም ነበር?» አለኝ።

ሰማሁትና አሁንም መልሼ «የፈለምከው ትልቅ ወንጀል ነው!» አልኩት።

ይኼኔ ተገትሮ ከነበረበት ተጠምዝዞ ከነበረ መከዳ ላይ እንዘፍ አሉ። እንደ ደንቢያም ተጉሰተ።

እኔ ግን ከፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተንጐራደድኩ ነበር። ኋላም ላንዲና ለመጨረሻ ጊዜ «ይሁዳ» አልኩት «ትልቅ ኃጢአት ሰራህ!»

ይሁዳ ሆዬ ቃል እንኳ ትንፍሽ አላለም። የሞተ ያህል ዐጥ አለ። ይሁዳ ግዑዝ መሬት ሆነብኝ።

ቆይቶ ግን የሞንቱን ከትምጡ ተነሳ። ቁመቱ ተወትሮው ተመሠ የተንቀዋለለ መሰለኝ። ድምፁም የተሸነቆረ ማድጋ የሚያስተጋባው አጉል አይነት ድምፅ መሰለኝ። እናም እንደ እኔ እንደ እኔማ - ፊት አንዳችም የበደለኛነት እና የኃጢአተኝነት መንፈስ በልቡ አልነበረም። አሁን በዚህች ምሽት ግን «ከእንግዲህስ መንግስቱን አፈልጋታለሁ!» አለኝ። «አዎ! ከፊቱም ቀርቤ ወሰን የለሽ ይቅርታውን አማለደዋለሁ!!»

«አሱ ሆዬ እንደ ንጉስ ሞተ። እኔ ምስኪኑ ግን ከእንግዲህ እንደ ወንጀለኛ ኡሞታለሁ!!» አለ ይሁዳ - በቀዘዘ ሰሜት።

ይሽን ካለ በኋላ ካባውን አጣፍቶ «ምንም እንኳ በገነ አበሳዬ ባስጨንቅህም - በዚህ ቀውጢ ምሽት አንተ መዳጀ ዘንድ መምጣቱ መልካም ሆኖልኛል። ወዳጀ ልቤ አንተስ ብትሆን ይቅርታ አታደርግልኛምን?» አለኝ።

ሰማሳሽ እንኳ ፋታ አልሰጠኝም። «መዳጅ! ለሌጆችህና ለልጅ ልጆችህ እንዲህ ትልልኛለህ - ሃናዝራቱን ኢየሱስ አሳልፎ የሰጠ የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው። እና ለፈፀመውም አሳዛኝ ከሀደት ነፍሱን ሊሰጥና ፍርዱንም ሊቀበል ወደ ታላቁ ንጉስ መንበረ መንግስት ሄዷል።' በላቸው። ድግሞም ለሱው ሰባለቤቱ እነግረዋለሁ! ምንም እንኳ ደሜ ለማፈሰስ ምድር ቃር ቢሆንም ሽባው መንፈሴ ግን ለሚፈስባት ምድር ቃር እንደሚሆን አምናለሁ!»

ፍፁም ፍውስና ነፃ እንደሚሆን አምናለሁ!»

ይሁዳ ይዜን ካለ በኋላ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮና አንገቱን ሰብሮ ደፍቶ ስትስት ብሎ አለቀሰ። የዋይታ ያህል ጫክ ብሎ «አዳሜ ሁላ ከቶ ስምህን ሊጠራው የምትከበደው አቻም የለህ አምላክ ሆይ! እነሆ ገላህ በሞት ተዳስሶ ግና እኔን እንዱን ነጠላና ድኩም ሰው - ምንዋ ነዲዱ በማይታይ የፀፀት አሳት ታቃጥለኛለህ?!» አለ። ፀፀቱ አላባራለት አለ።

«አንተ አማናዊው - የእውነት አምላክ ከቶውኑ ገሊላዊውን ይሁዳ ምስጢሩ ላልተፈታልኝ ሀገር ሀማማት ምነዋ ዳረግኸኝ! አዎ! ሮጬ የማላመልጠውንስ የምኞት ቀንበር ከቶ በልቦናዬ ለምን ጫንክብኝ? እጅቼ በደም የተነከሩ ይሄ ይሁዳ የሚሉት እኔነቴስ ከቶ ምንድነኝ? ...

«ይሽን ቡትቶና ጉስቁልቁል የፈረስ ከርቻ የመሰለ እኔነቴን ወዲያ እንዳሽቀነጠረው አቤቱ መለኮታዊውን እጅህን ስደድልኝ! ይህንኑም ዛሬውኑ ማታ እንድፈፅም አርዳኝ!

«አሁንም ከዚህች ትዕር ውጪ ራቅ ብዬ ልውጣ። አዎ! እስካሁንም በክንፈ ቢስ ነሳነት ለቆየሁበትም ጭንቁ ሊገለኝ ነው። እና ከእንግዲህ መቀመቅ ብገባ ይሻለኛል!

«አዎን! እንደ ጅረት ወደ መራራው ባህር እያቆራረጠ የሚንገፈገፍቀውን እንባዬን እነሆ ካዘንው ልቤ ምንጭ ላዝንበው! አዎ ከእንግዲህስ የገባ ልቡን በር በፀፀት ከሚደልቅ ከንቱ ሰውነት ይልቅ ምስኪንቱን በውል ለይቶ ካንተ ይቅርታህን የሚሰማን ቁርጠኛ ሰው ብሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

እመርጣለሁ!»

ይሁዳ ይሄን ተናግሮ በሩን ከፈተና ጨርሶ ላይመለስ አይነት ውጭ እንደ መአት ይወርድ ወደነበረው ዳፍ ገናም ዘው ብሎ ወጣ። በዚያውም አልም ብሎ ነጐደ።

ወደ ኢየሩሳሌም የወጣሁት ከሶስት ቀናት በኋላ ነበር። ከተማዋ እምብርት ስደርስ ሁሉም ነገር መፈፀሙን ሰማሁ። ይሁዳ ከአንዲት ቋጥኛማ አምባ ላይ የገዛ ራሱን መስቀሉን ሰማሁ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ የናዝሬቱን ኢየሱስን እና የእስቆሮቱን ይሁዳ ነገር ማውጠንጠን አልቀረልኝም። የወዳጁን የይሁዳን ልብና ነፍስ አሳምሬ የተረዳሁት ከዚያን ሁነት በኋላ ነበር። አዎ ታላቁ ነቢይና መሲህ ወደ ሰማየ ሰማያት ሲያርግ - ይሁዳም በሮማውያን ጨቧጅ መዳፍ ባርነት በወደቀች በዚህች ምድረ አይሁድ ላይ የነፍሱን ትንሽ ምኞት ሞላ።

መቼም አብዛኛው ሰው - አንድ እሱ ራሱ ብቻ ልዑል ሊሆን የሚችልበትን መንበረ መንግስት የሚያልም አይነት ይመስለኛል። ምናልባት - ምናልባት ግን ከአልፍ አእላፉ ሰው እጅግ በጣም ጥቂቱ ሰዎች ሁሉ ልዑላን ሊሆኑ የሚችሉበትን ሀዝባዊ መንግስት ይናፍቁ ይሆናል።

ልዕለ



በፑሽኪን ልደት ሳይ

ተስፋዬ ገብረአብ

ፑሽኪን ሁለት ሙዩ አመት ሞላው። ከሁለት ሙዩ አመታት በኋላ ድፍን አለም ፑሽኪንን በደመቀ ሁኔታ ሊያስታውሰው ወሰነ። ኢትዮጵያውያንም ምንም ስንኪ ድርሰቶቹንና ግጥሞቹን በቅጡ ባናውቃቸውም ፑሽኪን «የስጋ ዘመዳችን» በመሆኑ ጥሪውን አክብረን ወደ በአሉ ስፍራ ገስግሰናል።

የበአሉ አዘጋጅ የሆኑት የሳይንስና የባህል ማእከሉ ሩስያውያን እንግዶቻቸውን በየተገቢው ስፍራቸው አኑረው ሲያበቁ የበአሉን ስነስርዓት በትያም ተከተሉ ያስኬዱት ተጠሉ_

* * *

t.me/OLDBOOKSPDF

የፑሽኪን አጭር የህይወት ታሪክ መቅረብ ጀመረ...
አሌክሳንደር ሰርጌየቪች ፑሽኪን ሰኔ ቀን 1799 ሞስኮ ከተማ ተወለደ። ፑሽኪን ገና ከልጅነቱ ከነራሞቢን፣ ከቫርላሞቭ፣ ከባቱሽኪን ከራዎች ጋር ለመላተም ቻለ። ፑሽኪን ከወላጆቹ ፆም የነሳ ዕሁድ ናቅር ያደረበት ብርሀን ተመራማሪ ነበር...

* * *

የፑሽኪን ታሪክ ትረካ ቀጠለ...
የታሳቁ ገጣሚ ታሪክ ለኔ አዲስ ለሳልነበር አጠገቢ ከተቀመጡት እንግዶች ጋር ወግ ለመጀመር ብዙ ገልመጥመጥ አልኩ። በቀኝ በኩል የተቀመጡትን በአድሚ የገፉ ሰው አውቃቸዋለሁ። መልካም ሰም ያላቸው ተርገጥሚና ሀያሲ ናቸው። ከርሳቸው ጋር ማውጋት ደግ ላያደን አይቀርም፣
"ፑሽኪን ድንቅ ገጣሚ ነበር..." ስል ወሬ ጀመርኩ።
"ያጣም፣ በጣም!" ሲሉ መልስ ሰጠኝ።
"ዋራስያ በሀሳቱን ያሰቡዋቸዋል?"
"የቀድሞ ሥቹን... አዎ። ወርቅ ናቸው። ከቶ አይጠገቡም። በርግጥ ከአሁኖቹም አይተሣነቡቭ አሉ ሊለቹን እንኳ አላወቃቸውም።"

* * *

የታሳቁ ገጣሚ ታሪክ እየተነበበ ነው...
...ፑሽኪን የሩስያ ህዝብ የህይወትና የስነዕሁፍ መገገሚ ቃላት ተብሎ የሚጠራ ብርቅ የሩስያ ገጣሚ ነው።
...ፑሽኪን ባንድ በኩል የህይወት ፍቅር አለው። የሰው ልጆች ለዘመናት ያነበቱትን ልምድ ያከብራል። በሌላ በኩል ደግሞ የፈጠራ ሰራ አናቃሪም ነው። ፑሽኪን ከልጅነቱ ጀምሮ አያሳደጋቸው የመጣው አብይ ባህርያት ራስን ማድነት፣ ራስን ማክበርና መከበር የማለት ናቸው። ከገበረው ህይወት ጋርም ጥሩ ቁርኝት ነበረው። የተራ

ህዝቦችን ቋንቋ ጠጋ ብሎ ይናገራል...

* * *

ወደ ሀያሲው ዘወር አልኩ...
በሹክሹክታ እንዲህ አሉኝ፣
«የአዲሳባ አስተዳደር በፑሽኪን ሰም መንገድ ለመሰየም መወሰኑን ሰምተሃል?»
«አልሰማሁም።»
«እንዲያ ተወስኖአል ይባላል።»
«ጥሩ ነዋ! አይደለም?»
«አዎን! ለፑሽኪን ምንም ቢደረግ አይቆጭም። የአለም ህዝቦች ሁሉ ሀብት ነው። እንኳን ለፑሽኪን ለደጉልና ለቸርቺል እንኳ አደባባይና ጉዳና የሰጠን ቸሮች ነን» ብለው ረገግ አሉ።

* * *

ትረካው ቀጥሎአል...
...የታሳቁ ገጣሚ የፑሽኪን ጠላቶች በጠጉሩ ልክ ነበሩ። መኳንንቱም ሆኑ በስነዕሁፍ አነባቢ የነበሩት የቀለም ሰዎች በጠላትነት ይመለከቱት ነበር። እነዘሀም ጠላቶቹ የፑሽኪንን ሃሳት ናሩቂ አይናቸ ለማየት ፈፅመው አይሹም። ይፈሩትም ነበር። ፑሽኪን የእነዘሀን አሽቃባጮችና አሉባልተኞች የቡድን ሴራ ለመቋቋም ቢሞክርም ሰብቻው ታግሎ ድል መምታት ፈፅሞ አልቻለም። ባለበቱም የገጣሚውን ጥልቅ አውቀት ያልተረዳች፣ ከኪነ ጥበብ በጣም የራቀች፣ የስነ ዕሁፍ ስሜት የለላት፣ ወጣትና በውበትዋ የምትመካ በእነዚህ ሀብረተሰብ ዘንድ ባዶ ገቦንነትን የሰበሰበች ነበረች። በውበትዋ ንጉሰ ነገሰቱ ሳይቀር ተስቦ ነበር...

* * *

«ግን...» ሲሉ ተጠሉ ሀያሲው «የአዲሳባ አስተዳደር ለፑሽኪን ክብር ይህን ያህል ትኩረት የሰጠው ለምን ያመስልሀል?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታዋቂ ገጣሚ ስለሆነ ነዋ!»

«አይደለም» አሉ ቅጭም ብለው፤

«ታዲያ ሌላ ምን ምክንያት ሊኖር ይችላል?»

«ልታይ ልታይ ባይነት ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ የፑሽኪን ስም እየተነሳ ስለሆነ አለማቀፋዊ አስተሳሰብ እንዳለን እንዲታይልን ብቻ ነው። ሰበነ ጥቡበ በመቆርቆር ቢሆን ኖሮ የኛ የግላችን የሆኑትን ፑሽኪኖች አንረሳቸውም ነበር።»

* * *

ትረካው ቀጥሏል...

በ1834 አንድ የፈረንሳይ መኮንን በቪተመንግስት አካባቢ ብቅ አለ። ስሙ ዳንቴስ ይባላል። ...ዳንቴስ የፑሽኪንን ሚስት ያለመጠን ይከታተላትና ያጅባት ጀመር... በዚህ ምክንያት ፑሽኪን ለዳንቴስ የፍልሚያ ጥሪ አቀረበለት።... ፍልሚያም ተደረገ። ሁለቱም ተፋላሚዎች በሃያ አርምጃ ርቀት ላይ ፊት ለፊት ቆሙ። ቀጠራው ተጀመረ። ዳንቴስ ቀድሞ ተኮሰ። ፑሽኪን ተመታ። ሆዱ ላይ ነበር በከባዱ የቆሰለው። ፑሽኪንን ተሸክመው ወደ ቤቱ ወሰዱት። ፑሽኪን በቁስሉ ህመም ያለመጠን ሲሰቃይ ቆየ። ጓደኞቹ እነ ቱርጌኔቭም አስከ አስተ ሞቱ ከአጠገቡ አልተለዩም።

* * *

«እኛ አገር ስር የሰደደ ችግር አለ» ሲሉ ተጠሉ ሀያሲው «እኛ በባህላችን ማደነቅ እንወድም። ማናናትና መመቅኘት ስር የሰደዱ አጥፊ ልማድና ባህሎቻችን ናቸው። ለሩት በጋቡ ንብረመድህን ምቀኝነትን አስመልክቶ ያተረበውን አንድ ጥናታዊ ሰሀፍ አይተኸዋል?»

«ዮለም አላየሁትም»

«ያን አንብብ። በግልፅ አብራርቶታል። ታላቁ ችግራችን ምቀኝነት ነው። ወደ ውስጥ አናይም። ፈረንሳዮች የራሳቸውን ኳልሆነ የሌላ ሀገር ምርት የሆነ መኪና አይነዱም። ከውርደት ይቆጥሩታል። እኛ ግን የሀገር ውስጥ ጫማ አለማድረግ ስልጣኔ ይመስለናል። በአማርኛ የተፃፉ የስንፅሁፍ ስራዎችን ይዘን መታየትን እንደ ድንቁርና የምንቆጥርም ሞልተናል። ባዕዳን እዚህ መጥተው አሮምኛ ተምረው ስነታሉቻችንን ዝቀውና ዘርፈው ይሄዳሉ። ሂደው ይፅፉትና ዶክተር፣ ፕሮፌሰር ይባሉበታል። እኛ ግን ወደራሳችን አናይም። የራሳችንን ለመናቅ እንሽቀዳደማለን። ታውረናል። የግላችን ስለሆኑት ፑሽኪኖች ለአንድ ሰከንድ ማሰብ አንሻም። ፑሽኪንን ለማድነቅ ግን ይኸው ተንልተናል። ግን ደሞ ግጥሞቹን አናውቃቸም። አለም ያደረገው እንዳይቀርብን ነው የተሰበሰበነው። ከዚህ የከፋ ምን ድንቁርና አለ መዳጀ?»

* * *

ትረካው ቀጥሏል...

...የፑሽኪን ቤት ጤንነቱን ለመጠየቅ በሚጉርፍ የከተማው ህዝብ አንድተወረረ ይውል ነበር። እና ፑሽኪን ሞተ። የመኳንንቱ ህብረተሰብም በፑሽኪን ሞት ተደሰተ። ተራው ህዝብ ግን በያለበት ተንሰቅሰቆ ያለቅስ ነበር። መላ ሩስያ የደም እንባ አነባ። በቀብሩ ላይም ከሀምሳ ሺህ በላይ ህዝብ ተገኝቶ ነበር። የንጉሱ ስርዓት አመፅ እንዳይነሳ በመስጋት ተማሪዎች በገጣሚው ቀብር ላይ እንዳይገኙ አገደ። ከፑሽኪን ጓደኞች መካከልም ቢሆን በቀብር ስነስርዓቱ ላይ እንዲገኝ የተፈቀደለት ቱርጌኔቭ ብቻ ነበር። ጥር ፩ን፣1837 የፑሽኪን ንብስቶ መሬት ተፈፀመ። በቀብሩ ስነስርዓት ላይ የሚገኘይሰቭኪና የትሪጉርስኪ ገበሬዎች ነበሩ። ፑሽኪን ስጋው ቢሞትም ስራዎቹ ግን በእያንዳንዱ የሩስያ ህዝብ ልብ ውስጥ ሰርፀው ነበር። ፑሽኪን በህይወት ከነበረበት ጊዜ ይበልጥ የዘውድ አገዛዙን ጨቋኝ ስርዓት ያንቀጠቀጠው ከሞተ በኋላ ነው።

* * *

t.me/OLDBOOKSPDF

„የፑሽኪን የህይወት ታሪክ ትረካ አበቃ።
ፕሮግራሙ ግን እንደቀጠለ ነው።
የመድረክ መሪው ለናሙና የተወሰዱ የፑሽኪን ግጥሞች እንደሚቀርቡ ገለፀ። ይህን ጊዜ ታዳሚዎች ነቃነቃ አሉ። እናም የፑሽኪን ግጥሞች በጣፋጭ ዜማ ይፈሱ ጀመር...

...ቆራጡ መንፈሴ - አልተኛም ንቁ ነው
የነፃነት ፍቅር - በልቤ ውስጥ ያለው
ይፈላል እንደ ውሃ - ንፍርነው አሳት ነው
...የታላቁ ህዝቤ - መንፈስና ወኔ
አይበርድም አይሟሟም - አይለይም ከኔ

* * *

«ከጥቂት አመታት በፊት የግላችን የሆኑትን ፑሽኪኖችና ሌሎች ምሁራን ማድነቅ መጀመር እንደሚገባን የሚጠቁም መጣጥፍ በአንድ መፅሔት ላይ አቅርቤ ነበር» ሲሉ ተጠሉ አንጋፋው ሀያሲ «ግን ያነበበኝ ስለመኖሩም አንሸ። እየህ... በህገራችን የአመለካከትና የባህል ለውጥ ያስፈልጋል። የስነፐበብ ሰዎችን፣ ምሁራንን፣ በራሳቸው ጥረት ታላላቅ ሰመባል የበቁ ዜጐቻችንን ማድነቅና ማክበር መጀመር አለብን። ልማዳችን ግን የጦር ሰዎችንና ንጉሶችን ከማሞገስ የዘለለ አልነበረም። የኢትዮጵያ ሞዴሎች የጦር ሰዎች ብቻ መሆን የለባቸውም።»

* * *

የፑሽኪን ግጥሞች ንባብ ቀጠሎአል።
ግማሽ ክቡር - ግማሽ ኔጋዴ
ግማሽ ጠቢብ - ግማሽ መደይ
ግማሽ ታማኝ - ግማሽ ወንጀዴ
ከሆነ ሰው ጋር
ይቻላል ወይ አብሮ መኖር?

* * *

ሀያሲው...
«ድላችን ሀውልት - ድላችን ኤክስፖ፣ በላይ ዘለቀ መንገድ፣ ኃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል፣ አርበኞች አደባባይ፣ ራስ መኮንን ድልድይ፣ ድልድዩ አንኳ ይቅር፣ ኤክስፖው ግን በገብረክርስቶስ ደስታ ስም ቢሰየም ከቶ ምን ይገድ ነበር? ቸርቺል ጉዳና ቡብዙነሽ በቀለ ስም ቢጠራ እንዴት ባማረ? ቸርቺልን የት እናውቀዋለን? አሱስ የት ያውቀናል?»

* * *

ፑሽኪን ግጥሞች ቀጥለዋል...
ግርማ ሞገስ ያለው አጅግ የሚያከራ
በአድ ያልተቀረፀ በሰው ያልተሰራ
ከአስከንድር ምስሶ በቁመት የላቀ
በአሰራሩም ቢሆን ይበልጥ ያረቀቀ
ሀውልት አቁሚያለሁ ለመታሰቢያዬ
ለሚመጣው ትውልድ ለወደሁዋላዬ፤

* * *

«ወራዎቻችን በጦር ሰዎች ዙሪያ ከታጠሩ ዘመናት አልፈዋል። የጦርነት ታሪካችን በዛ። መጪ አድላችንም ጦርነት እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። ጠዋትና ማታ ከፊታችን የሚደቀኑት ሀውልቶች የተዋጊዎች፣ የምንዘራቸውና የሚዘሩብን አደባባዮች የተዋጊዎች ብቻ መሆን የለባቸውም። ይህ የመንግስታት ስህተት ብቻ ደሞ አይደለም። እኛ የጥቡብ ሰዎች ራሳችን የዚያ አመለካከት ሰለባ ነን። ምክንያቱም አስተዳደጋችን ራሱ ከጦረኛነት ስሜት የራቀ አይደለም። እስኪ የትኛው ህበሻ ህፃን ነው አርጉብ ሲያይ ሊገድል ድንጋይ የማያነሳ? እንሽላሊት ስናይ መግደል፣ ጥንዚዛ ስናይ መግደል፣ መግደል እየለመደብን ይመጣል። ከልጅነታችን ፍቅር አልተማርንም። ስለዚህም እኛ አባቶች ለህፃናት ፍቅር ማስተማር አልጀመርንም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማድነቅን አላስተማርናቸውም። እኛ ባደግንበት መንገድ አስቀምጠናቸዋል።»

* * *

...ፑሽኪን የልደት በዓል አየተከበረ ነው...
እንደ ወራጅ ወንዝ የፏፏቴ ድምፅ...
የታላቁ ገጣሚ ሰንኖች ይፈሳሉ።
ፍጡር ለመጨፍጨፍ በደም ለመዋኘት
አድል መልምሏቸው፤
እነ ፍርደ ገምድል የዱር አሳማዎች
ሰብአዊ ርህራሄ አሳ፣ የሌላቸው፤
ከጫካ የወጡ ባለባት አውሬዎች ማሰገደጃ ጅራፍ
ጨብጠው በእጃቸው፤
የአርሶ አደሩን ጉልበት... ፈዘውን፤ ልፋቱን...
እርገው ሰግላቸው፤

* * *

«ጀግኖቻችንን ዝቅ ማድረጌ አይደለም።» ሲሉ ቀጠሉ ሀያሲው «አኒያ አርበኞች ብርቆቻችን ናቸው። የነፃነታችን ዘልአለማዊ ባለቤት መሆን የቻልነው በጀግኖቻችን መስዋዕትነት ነው። ሚዛኑ ግን መጠበቅ አለበት። ባልቻ አባነፍሶ፣ መድፍ አገላባጭ ብቻ ሰብቻ፣ መድፉን ከመድፉ ሲያጐራርስው፣ ባልቻ አኮ አሳት ሳይሆን ቁጣ ነበር የሚተኩሰው፣ አያልን ለልጆቻችን አናወጋለን። ይህ ክፋት የለውም። ደግ ነው። ዳሩ ግን ስለያፈድ፣ ስለዮፍታሄ ንጉሥ፣ ስለ ዶክተር ጌታቸው ቦሱዲያ፣ ስለ መንግስቱ ሰማ፣ ስለ አቤ ጉበኛ የምንተርክላቸው መቼ ይሆን?»

* * *

ፑሽኪን ግጥም በአዳራሹ...
በሳይቤርያ አምብርት - በማዕድን ዋሻችሁ
ክብር ያሰውን ትዕግስት - አቆዩት ቁብራችሁ
ከንቱ ሆኖ አይቀርም - ጥልቁ ሀሳባችሁ...

የግፍ ታማኝ እህት - የሆነችው ተሰፋ
የምድር በላይ ዎሽን - ጨለማውን ገፋ...

* * *

ምንም ስንኳ ለሰላታት ያለንቃናቂ በመቀመጣችን ድካም እየተሰማን ቢሆንም ከቶ አልተሰላችንም። በደራሲና ተርጉዋሚ አያልነህ ሙላቱ የተተረጉሙት የፑሽኪን ግጥሞች መንፈስን በአጅጉ የሚያነቃቁ ነበሩ። ለአራት ስዓታት ያህል በጣፋጭ የስነ ግጥም ገበታ ዙሪያ ታድመን ቆየን። አናም ወደ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ መቃረባችን ተገለፀልን። የማጠቃለያው ንግግር ተሰምቶ ወደ ተዘጋጀው ግብዣ ከማምራታችን በፊት ግን ከበአሉ አዘጋጆች አንዱ ወደ መድረኩ ቀርቦ በአማርኛ አጭር ንግግር አደረገ፤

«ቀደም ሲል የፑሽኪን የህይወት ታሪክ ሲነበብ አንድ የተዘነጋ አብይ ጉጉት አለ» ሲል ጀመረ። እና ቀጠለ «...አምን፣ ሁላችንም አሳምሪን የምናውቀው አንድ የሚያከራን የታሪክ ሀቅ አለ። ይህም የፑሽኪን የዘር ሀረግ ጉዳይ ነው። የፑሽኪን እናት ናዴዥዳ አሊፓቭና የመረብ ወንዝ አካባቢ ኢትዮጵያዊ የሆነው የታላቁ ጴጥሮስ ጀኔራል የአብርሃም ጋኒባል የልጅ ልጅ ነበረች። ይህን ስናገር ኢትዮጵያዊ እንደመሆኔ አንዳች የደስታና የኩራት ስሜት መላ አካሌን እየወረረው ነው...»

ድንገተኛ የደስታ ድምፅ አዳራሹን ሞላው። በታዳሚው ስሜት ውስጥ የኩራት መንፈስ ነፍስ ሲዘራ ታየ። እንዲያውም ከጀርባችን ግድግዳውን ታክከው የተቀመጡት ወጣቶች «ፑሽኪን የኛ ነው፣ ኢትዮጵያዊ ነው» የሚል የመፈክር ጠባይ ያለው ድምፅ አሰሙ። ይህም በመዳከም ላይ ለነበረው ታዳሚ የሚያነቃቃ ፈውስ ሆኖ አገለገለ። ግን በርግጥ እንጋፋው ሀያሲ እንዳሉት የራሳችንን ብርቆች ክልብ ማድነቅ የምንጀምረው መቼ ይሆን?

መጣጥፍ

t.me/OLDBOOKSPDF



ቸሩ ሲማ

ቂም በቅቤ

ቂም ቂም
ቂም በቀል
ከልባችን ይነቀል
ጥንት ቂም
አሁን በቀል
ቂም በቀል
መበቃቀል
ከኔ ልብ
ከአንች ልብ
ከአንተ ልብ
ከአሱ ልብ
ከአሷ ልብ
ከእኛ ልብ
ይነቀል
አባት ቂም
ልጅ በቀል
በዘር በቀል
ቂም በቀል
መበቃቀል
ከአባት ልብ
ከልጅ ልብ
ይነቀል
ዘመን ከዘመን
ትውልድ ከትውልደ
አየከሰሰን
አየተናቆርን
መበቀል
ቂም በቀል
ለዘልአለም
ከእኛ ልብ ይነቀል

የመጀመሪያውን ሌላው ያርምና ይቀጥላል። «ከንፈሮቿ እንደ ዛጐል ያማሩ ናቸው።»

«ፀጉሯ የወርቅ ጥምዝ ነው»

«ሰማያዊ ዓይኖቿ እንደ ... እንደ...»

ኒንካ በጣም ትደሰታለች። አመዳም ፊቷ በደማቅ ቀለም ይሸፈናል። በኩራት አግሯን ወዲያና ወዲህ ብድግ ቁጭ ታደርጋለች። ቃላቶቻችን መስተዋት ይሆኑላትና «እዚህ ቦታ ቀረሽ» የማትባል ቆንጆ ሆና ትታያለች።

«ቆዳዋ እንደ ሀር ያበራል»

«ቅንድቦቿ ጥቋቁር ናቸው»

«ጥርሶቿ ...?»

«ጥርሶቿ? ሉል ናቸው።»

የኛዋ ኒንካ የተባለው ሁሉ እንዳላት እየተለማን፤ ከኒንካ ይበልጥ ቆንጆ ልጅ የሌለ መስሰን። የእኛ የእድናቆት ቃላት ሲያበቃ ኒንካ አንዳንድ ነገሮችን መናገር ትጀምራለች፤

«ትናንትና በሞቀ ባህር ውስጥ ዋኘሁ» ትላለች፤ በቀዝቃዛው የመዐው ነፋስ እየተኩራመተች። «ምሽት ላይ በጭለማ ባህሩ አበራ። እኔም አበራሁ። ሆሆም... አሳ ሆኜ ነበር።»

የሚገርመው ሳት እንኪን ብሏት ድንች እንዴት እንደጠበሰች፣ ትምህርቷን እንዴት እንዳጠናችና በልብስ አጠባ አናቷን እንዴት እንደረዳች ... ልታወራ አትፈልግም። አንዳንዴ ታዲያ በነገር አፏን የሚሏት አይታጡም። እርሷ ግን አትረታም።

ከጊዜ በኋላ አዳዲስ ነዋሪዎች ወደሠፈራችን መጡ። እንግዳ ልጅም በመጪወቻ ቦታችን ተገኘ። በጣም ከመርዘሙ የተነሳ አጭር መስሎ ለመታየት ያጐነብሳል። አገጩ ላይ ሞላላ የሆነ ነጥብ ነገር አለበት»። በነጥቡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚያፍር እንዳናይበት ሴላውን ጉንጩን ወደኛ ያዞራል። አፍንጫው ወደላይ ቀልበስ ያለ ሲሆን ቅንድቡ ደግሞ የሴት ዓይነት ስለሆነ በርሱም ያፍራል።

አዲሱ ልጅ ጥግ ይዞ ነበር። እኛ አርሱን ጣራንና «የውበት ጨዋታ እንጫወት» አልነው። ምን እንደሆነ ስላላወቀ ተስማማ። እኛም ተያየንና አርሱን፣ ቆንጆ አድርገን መረጥን። ስለዝይ አንገቱና ስለዛጉል መሰል ከንፈሮቹ መናገር ስንጀምር ፊቱ በጣም ቀላና ከተሰበሰብንበት ተነስቶ በረረ።

እኛም ሳቅንበትና ጮክ ብለን ነገርነው።

«እኛ እንደሆንን አንተም ባትኖር መጨዋታችንን እንቀጥላለን!»

ነገር ግን ጨዋታችንን እንደገና ስንጀምር ኒንካም በድንገት «እኔም አልጫወትም..?» አሰች።

በጣም ገረመን፤

«ምን ነክሽ ለምንድነው የማትጫወቺው?»

ኒንካ ጥላን ሐደች።

እኛን ቁር አለን። ኒንካ ስለተለየችን ቅር ቅር ይለን ጀመር። አሷም አዲሱን ልጅ ተጠጋች።

«የውበት ጨዋታ ሲጫወቱ ሁል ጊዜ እኔን ነው የሚመርጡት» አለችው።

«አንቺን? ለምን አንቺን?» አዲሱ ልጅ በጣም ተገረመ። «አንቺ ቆንጆ ነሽ'ዴ?» በመደነት ጠየቃት።

እኛ ከአርሱ ጋር ለመከራከር ስላልፈለግን ሣትገበት። ኒንካ ፊቷ ተወጣጠረ። ጠቃጠቆዋም ይበልጥ ጉልቶ ታየ።

«ግን እኔን ነው የመረጡት» አለችው።

«ደደብነት ነው» አለ አዲሱ ልጅ። «በአጠቃላይ የልጅ ጨዋታችሁ ሁሉ አያምረኝም።»

«በርግጥም ትክክል ነህ» ኒንካ ምንም ይሁን ምን

በሀሳቡ ተስማማች።

አዲሱ ልጅ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ምን እንደሆነች አናውቅም፤ በጣም ተለውጣለች። ለምሳሌ መንገድ ላይ እሱን መከተል ጀምራለች። አርሱን መከተሏን ማንም እንዳያውቅ፣ ዐጥ ብላ በመንገዱ ማደ ትጓዛለች። እኛ ግን ኒንካ አዕምሮዋን እንደሳተች ወይም የማናውቀው ጨዋታ (ለምሳሌ ከት'ት'ሽ) እንደ ጀመረች ገመትን። አርሱ ወደ ሱቅ ከጣ፤ ዓይኗን ክበሩ ላታነሳ ትጠብቃለች። ጧት- ጧት መውጫ በሩ ጋ እየጠበቀችው ትምህርት ቤት ተከትላው ትሔዳለች።

አዲሱ ልጅ ኒንካ እንደጥላው እንደምትከተለው አላወነም። በኋላ ግን ነገሩን ሲገነዘበው በጣም ተናደደ።

«እኔን አትከተይ!» ጮኸባት።

ምንም መልስ ሳትሰጠው ፊቷ ቀልቶ ሐደች።

«ፊትሽን በመስተዋት ብትመለክችው ይሻልሻል!» ሲል ጨመረላት፤ ፊቷን በመስታወት እንድትመለከት አዘዛት።

እኛ አፍንጫችን፣ አፋችን፣ አገጫችን ምን ዓይነት እንደሆነ፣ በጣር ወዴት እንደሚተኛ፣ ዮብጣር ጠባሳ ዮት እንዳለ ወዘተ.. ሁሉ፣ ስሜት አልሰጠንም። ኒንካም የምታውቀው መስተዋት ደግሞ የእኛን የውበት ጨዋታ ብቻ ነው። እኛን አምናን ነበር። ጉንጩ ላይ ነጥብ ያለበት ልጅ ግን፣ መስተዋታችንን ሰበረው። በሕያው አሰደሳችና ደግ መስተዋት ፊንታ ተዝቃዛና ከፉ መስተዋት ተተካ። ኒንካም በሕይወቷ ውስዋ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘህኛው መስተዋት ራሷን አየችበት። ይሄ መስተዋት ቅንጅዋን ገደላት። ወደ መስታውቱ በተጠጋች ቁጥር እንዳንድ ነገር ከውስጧ ይሞት ጀመር። የዝይ አንገቷ፣ የዛጉል ከንፈራ፣ እንደ ባህር ሰማያዊ የሆነው ዓይኗ... በሙሉ ጠፉባት።

t.me/OLDBOOKSPDF

እኛ ያኔ ይህን ነገር አልተረዳንም። አንገታችንን ሰበር አድርገን «ምን ነካት?» እያልን ተጠያየቅን። ጓደኛችንን ለማወቅ አልቻልንም። ፍዩም ሲላና ምናም የማይገባን ሆነችብን። እኛ ራቅናት። እርሷም ወደኛ ለመጠጋት አልፈለገችም። ዝም ብላ በአጠገባችን ታልፍ ጀመር። አዲሱን ልጅ ስታይ ግን ከርሱ አትሸሽም። ምን ታድርግ? ከከንቱ ውዳሴ ይልቅ የዕውነትን ትክክለኛ መንገድ አሳይቷታላ!

ልቦለድ



አባቴ ደግ ነበር

ቶማስ አርጋው

አፈሩን ገለባ ያድርግለትና አባቴ ደግ ሰው ነበር። ደጉም ክፉውም ይሞታሉና አባቴም አፈር ከለበሰ አያሌ ጊዜያት አለፉ። እንዲያው ለወግ የምትበቃ እንዲት ጉደኛ አመል ግን ነበረችው። ያችን አስቂኝ አመል ለአደባባይ ማብቃቴ ከነውር እንደማይቆጠርብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

እንግዲህ ሰላሳ ስድስት አመት ወደሁዋላ ተመልሼ አባቴ፣ እናቴ፣ ወንድምና እህቶቼ ወደታጨቅንባት ጐጆአችን ልውሰዳችሁ። ምሽቱን በጐጆአችን ታዛ ስር...

t.me/OLDBOOKSPDF

አባትና እናቴ ሲጨዋወቱ መስማት በእጅጉ ያስደስተኛል። የአባቱ የንግግር አመል አሠልቺ ቢሆንም እናቴ ግን ትችሰዋለች። ነገር ቢደጋግሙባትም ትታገሰዋለች። ለፍቅር ብላ ይሆን? ሲያዛባት ግን «ሌጭ አንግዲህ!» ትለዋለች። ከእናቴ አንደበት «ሌጭ» የምትሰዋ ቃል ስትወጣ ታዲያ አባቴ ነገር ማርዘምን ገታ ማድረግን አሳምሮ ያምዳል። ግን ያባቴ አመል ክፉት የለውም። እንዲያው ልማድ ብቻ እንጂ።

አንድ ቀን አባቴ ከደጅ ሲገባ፣ «ዛሬ ሰው ይዲልጉት ነበር» አሰኛ እናቴ፤

«ማነኝ ባይ ነው?»

«አቶ ዳምጤ ...»

«ዳምጤ.... ዳምጤ»

«ይሄ የርሶ ዓደኛ።»

«ዳምጤ ስዩም?»

«አዎ ዳምጤ ስዩም። የአባቱ ስም ስዩም ነው?» ትላለች እናቴ ቡናዋን ፉት እያለች።

«እኮ ይሄ ከዋርካው በታች በዘመመችው ጉጆ ውስጥ የሚኖረውን አይደል የምትይኝ?»

«አምና ታዲያ!»

«እኮ! ዳምጤ ስዩም ነዋ።»

«ልክ ነሽ»

«አንድ ከአፉ ሲጋር የማይጠፋ ዋልጌ ልጅ አሰው። የሱን አባትም አይደል የምትይኝ?»

«ይሆናል። እኔ ልጁን አላውቀውም» ትላለች እናቴ ሳይታክታት።

«ዳምጤ ይሄ ሁል ጊዜ ከትከሻው ጋቢ የማይወርደውም አይደል?»

«አምን አልኩምት እንግዲህ» እናቴ ብስጭት ትላለች።

«ታዲያ እንዴት ልጁን አታውቂውም?»

«እኔ እንጃ አላውቀውም»

«ምን ነካሽ? ይህች ወፍራም ሚስት ያለችውን ዳምጤንም አይደል የምትይኝ?»

«ሌጭ አንግዲህ?»

«በጀ ታዲያ ለምን ይሆን የፈለገኝ?» ይል ነበር አባቴ - ነፍሱን ይማረውና።

ትዝ ይለኛል። አንድ ቀን ተሰባስበን አራት ከበሷን በኋላ ቡና ተፈላ። እናቴ ጉረቤታችን የሆኑትን አማማ ተናኘን እንድጠራ ላከችኝ። መልዕክቱን አድርሼ ተመለስኩ። አማማ ተናኘ ግን ሳይመጡ ብዙ ዘገዩ። እናቴ ታዲያ ያልጠራቷቸው መስሏት «አንተ ልጅ ተናኘን አልጠራሃትም እንዴ?» ብላ ስትቆጣ አባቴ ጣልቃ ገብቶ፤

«ተናኘ ... ተናኘ?» አለ የስንት ዘመን ጉረቤታንን ዘንግቶ።

«ተናኘ ጉረቤታችን ኮ! ደሞ ጉረቤታችንን ረሳት?»

«እንዴት አረሳታለሁ? የለቡሽን እናት ማለትሽም አይደል?»

« አምና። ሴላ ማን አለ?»

«እኮ የቢሆነኝ ሚስትም አይደለች?»

«አምን» አለች እናቴ ሲኒዋን እያጣጠበች።

«አሷ ሴትዮ ለምንድነው ከጂ ላይ የሚቋጭ ነጠላ የማይጠፋው?»

«ባሏ በየሳምንቱ ስለሚገላላት ይሆናላ» ስትል ቀለደች።

«ማን ይህችው የአንች ጉረቤት?»

«አምና»

«እኮ ይህችው ተናኘሽ?»

«ሌጭ! አምን አልኩምት።»

«ሌጭ» የምትለዋ ቃል ከእናቴ እንደበት ከወጣች

t.me/OLDBOOKSPDF

አባቴ ጥያቄውን ያቆምና ወደ ሌላ ነገር ይሸጋገራል። አይ አባዬ! አፈሩን ገለባ ያርግለት። ደግ ሰው ነበር።

ምን ጊዜም እናትና አባቴ ሲያወሩ ቁጭ ብዬ እና አፋቸውን እያየሁ እስቅ ነበር። ሌላ ቀን ደግሞ እህቴ ስሙኝ ገበያ ወርዳ አምሽታ ነበር። እናቴ ጠራችኝና። «ስሙኝ ምነው ዘገየች?» ስትል ጠየቀችኝ። አባቴ በር ላይ ቁጭ ብሎ የሰኔ ጉለጉታን ያነብ ነበር። መቼም ሰኔ ጉለጉታን እንደነብሱ ነበር የሚር?ት። አንዳንዴም ለእናቴም እያነበበላት ቢሳሳብ ተያይዘው መንግሥተ ሰማያት በር ድረስ ይንሳሉ።

«መምጪዋ ነው። ለምን እንደዘገየች አላውቅም» አልኳት።

«ማነች የዘገየችው?» አለ አባቴ ድንገት አይኑን ከመፃፉ ላይ ነቅሎ።

«ስሙኝ ነቻ» አለች እናቴ እጇ ስራ ላይ ታ።

«የታ ስሙኝ?»

«ስሙኝ የኛው ጉድ ነቻ! ርስም ደ'ሞ።»

«የኛ ጉድ?»

«ያርስም ልጅ»

«ስሙኝ የኛዋን ልጅ ማለትሽ ነው?»

«ታዲያስ»

«አሷ ልጅ ለምንድነው ወጉሯን የማትታጠበው?»

«ስራ እየበዛባት» እማዬ መለሰች።

«የኔ ልጅ በስራ ብዛት ወጉሯን መታጠቢያ ጊዜ አጣች ነው የምትይኝ?»

«አምና»

«ለለኔ ልጅ ነው የምታወሪው ወይስ ለለሌላ ስሙኝ?»

«እረ ለለራስም ለሙኝ ነው»

«እኮ ይህች የአናኑ ታሳት?»

«አምነ»

«እኔኮ ለለሌላ የምታወሪ መስሎኝ። ታዲያ የት ሄደች ነው የምትሉት?»

«ገበያ ሄዳ ነበር፣ እስክ አሁን አልመጣችም»

ዛሬ አባቴን ሳስታውስ በእጅጉ ይገርመኛል። ሌላው ቀርቶ መኝታ ሰዓት ላይ እናቴ «እግርምን አይታጠቡም?» ስትለው «እግርህን ታጠብ ነው ያልሽኝ?» ይላታል «አምን» ትለዋለች። የእናቴ ትዕግስት በጣም ይደንቀኛል። በልጅነቴ ሁለቱ ወላጆቼ ሲያወሩ አባቴ ምን እንደሚል ስለማውቅ ከመናገሩ በፊት «እኮ እንዲህ ሆኖ» እላለሁ በልቤ። ልክ እኔ ያልኳትን ማለቱ አይቀርም። ታዲያ የዛን ጊዜ እስቃለሁ። አይ አባዬ! አፈሩን ገለባ ያርግለት። ደግ ሰው ነበር።

ነፍስ አያወቅሁ ሰዒድ አባቴ «ይሄ ልጅ ትምህርት ቤት መግባት አለበት፣ አረኛ ሆኖ መቅረት የለበትም። ከዘር ማንዘራችን እሱ እንኳን ይማር። መሃይምነት የዘር ውርስ ሆኖ መቅረት የለበትም» የሚል ሃሳብ አቀረበና ትምህርት ቤት እንድሄድ ተወሰነ። እኔም ደስ አለኝ። እናቴ ግን አይን አይኔን እያየች ከሷው ጋር ስጫወት ብውል ደስ ስለሚላት «ይማር» ብላ ድጋፍ ባትሰጥም ስለምትወደኝ እንዳይከፋኝ ብላ «ይሁና» ብላ ዝም አለች።

እንደ ሰኞ ትምህርት ቤት ልገባ ቅዳሜ ማምሻውን ከሳምቹ መሃል አንዷ ጠፍታብኝ ስፈልግ አምሽቼ ነበር። አባዬ ትንሽ ሞት ብሎት ነበር የገባው። ሆኖም አሱ እንደገባ እኔም ሳሚታን አግኝቼ በጓዳ በር ገብቼ ነበር። እናቴ ሰራት ወጥ ትሰራ ስለነበር የምድጃው አሳት ተንተርከኳል።

«ጥላዬ ወዴት ሄደ?» ሲል አሰማው ነበር።


t.me/OLDBOOKSPDF

«አንድ ላም ጠፍታበት ሲፈልግ ሄዷል» አለች እማዬ።
«የቷ ላም?» አለ።
ላቅ እንዳፈነኝ እያዳመጥኩ ነው።
«ይህቺ የቀይ ቡሬዋ» መለሰች እናቴ።
«ከጥቁሯ ጋር አብራ የምትውለው?»
«አዎ»
«እኮ ይህቺ ቀንደ ሰባራዋ?»
«ይሰበራት የሚሰብር፤ አሷማ ነች የጠፋችው»
«ታዲያ ምን ሆንኩ ብላ ነው የምትጠፋው?»
«ከሌላ ከብት ተደባልቃ ይሆናላ»
«ምንድነው የምታወሪው? ከመቼ ወዲህ ነው ከሌላ ከብት የምትውለው?»
«ለምን አትውልም፤ ከብት አደለች እንዴ?»
«ይህቺ ለሞኑን የወለደችውም አይደለች?»
«ኤጭ እንግዲህ»
«ጠፋች ስትይኝኮ ግራ ገብቶኝ»

ሰኞ ጠዋት ትምህርት ቤት ውዬ ማታ ስገባ «ትምህርት ጀመርክ?» አለኝ አባዬ «አዎ» አልኩት።
«እንዴት ነበር?» አለኝ
«ጥሩ ነው» አልኩት።
«ከምን ጀመራችሁ?»
«ከሀሁ»
«እኮ ከፊደል?»
«አዎ ከፊደል»
«በል በርታ» አለኝ። እኔም በረታሁ። አስተማሪው የሚለውን ሁሉ በደንብ አዳምጣለሁ። አስተማሪውን በአባቴ መሰየው ነበር ትምህርቴን የምከታተለው። ፊደሎቹ እንዳይረሱኝም ከተሰያየ ነገር ጋር እያመሳስልኩ ለማያያዝ እሞክራለሁ።

አስተማሪው «ሠ» ሲል «እኮ ኩባያ የምትመስለው?» እላለሁ በልቤ።
አስተማሪው «ቀ» ሲል «እኮ ይህቺ እንደ አስከሰታ ወራጅ ወገቧን የያዘችው?»
አስተማሪዬ «ቆ» ሲል «እኮ ይህቺ እንደ አባባ ነጋሽ ቆብ የደፋችው» እላለሁ።
አስተማሪዬ «ሐ» ሲል «እኮ የተዘቀዘቀ መንሽ የምትመስለው?»
አስተማሪው «ሳ» ሲል «እኮ ይህቺ ሰፊድ ላይ የቆመች ዶሮ የምትመስለው?»
አስተማሪው «መ» ሲል «እኮ አህቺ እጀታ የሌለው መነፅር የምትመስለው?»
አስተማሪው «ዋ» ሲል «እኮ ይህቺ ራሱን ይዞ የሚያለቀስ ሕፃን የምትመስለው?»
እያልኩ እውላለሁ። ሳላውቀው የአባቴ አመል ተጋብቶብኝ ኖሯል።
ታዲያ ማታ እቤት ገብቼ ፊደሎቹን ላስታውስ ስሞክር ድርገም ብለው ይጠፉብኛል። ፊደሎቹን ለማስታወስ ስጣጣር ኩባያ፤ እስክስታ የምትወርድ ሴት፤ ባለቆቡ አባባ ነጋሽ፤ መንሽ፤ ሰፊድ፤ ዶሮ፤ መነፅር፤ የሚያለቅስ ሕፃን፤ ጀበና፤ ጭልፋ፤... ብቻ በአይነህሊናዬ ይዞራሉ። የአባቴ መንፈስ በአስተማሪዬ ላይ አርፎ አባቴ የሚያወራ እየመሠለኝ «እኮ ... እኮ» እያልኩ ስለምውል፤ እኩና የእቃ ከምር ብቻ ጭንቅላቴ ውስጥ ተጠቅጥቆ ስላስቸገረኝ ፊደል ማስቀመጪ ቦታ እያጣሁ አቸገር ነበር። ሞት አይቀርምና አባቴ ሞተ። «እኩ» የምትለው የአባቴ ልምድም ሰብዘ ጊዜያት አብራኝ ቆየች። ሁዋላ ግን ትዝታ ብቻ ሆነች። አፈሩን ገለባ ያርግለትና አባቴ ደግ ሰው ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF





ኮንፊሽን «የባህር ጠፍ»

መኩሪያ መካሻ

ዴቪድ ፎርደን የሲአይኤ ፕሮፌሽናል ነው። ሚያዚያ፣ 1973። የሜክሲኮ ሲቲ ጉብኝቱን ሊያገባድድ እንደተቃረበ፣ የሶቭየትና የምሥራቅ አውሮፓን ስለላ የሚከታተለው አለቃው ለአጣዳፊ ጉዳይ ከዋሽንግተን መጥቶ ተገናኝተዋል። ወደ አንድ ጥግ ወሰደው።

«ያንተ ፖላንዳዊ አንዲት ነው?»

«ልምድ አልባ ነው ባክህ» አለ ፎርደን።

«መልካም መምህር መሆን አለብህ። በዋርሶ ፍፁም የተለየ ሁኔታ አጋጥሞናል። ምስጢረኞችን በሚገባ የተካነ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድ ሰው ጉዳዩን እንዲይዝልን እንፈልጋለን። አፐሬሽን ካክሰር መፍ ብለን ሲይመትዋል። አንተ በዚህ አፐሬሽን ልዩ ሚና እንድትጫወት እንሻለን።»

የስለላ ድርጅቱ ፎርደን የአፐሬሽኑ ኃላፊ አድርጉ መመደቡ ትክክል ነበር። የእሱ ችሎታና ሁኔታዎችን የመረዳት ፍጥነቱ ከአፐሬሽን የካሀር መፍ ውድቀትም ሆነ ድል ማድረግ ውስኝ ነው።

ቀዝቃዛ፣ ቁጥብና የሰማ አእምሮ ያለው ይህ የፈረ ዓመቱ ፎርደን በኒውዮርክ ቡፋሎ አካባቢ ተወለደ። በሥነ መንግሥት ትምህርትና በእንግሊዝኛ ሥንቋ ከዊስሊያን ዩኒቨርስቲ ተመረቀ። ስቪሎራዊ አገልግሎት ሠራዊቱ ውስጥ እንዲገባ ሲጠይቁ ርቷል አጠመደው። የሲአይኤ የዋርሶ ጣቢያ ሃላፊ በመሆንም በሥሚኒስታዊ ሥርዓት ለተጨቆኑ ፖላንዳውያን የልብ ወዳጅ ሆነ።

ፎርደን ወደ ዋሽንግተን እንደተመለሰ ጊዜ አላባከነም። አፐሬሽን የካሀር መፍ ቆይል አውጥቶ ማገላበጥ ቀጠለ። ፋይሉን ባጠኑበት ቁጥር የፖላንዳዊው የጎር ሠራዊት ሪዛር ኩክሊንስኪ ስብዕና ስጫቱን አመስቃቀለው። ለዚህ ደግሞ ምክንያት አለው። በመደበኛው የስለላ ጨዋታ እንደሚደረገው ኩክሊንስኪ የተመለመለ ሰው አልነበረም። ቡታፓራኒው ኩክሊንስኪ አሜሪካንን ነበር የመለመለው። ሴላም መታከል ያለበት ኑጥብ አለ። ይህ ሰው ገንዘብና ስልጣንን ፈጽም አልጠየቀም። የእሱ ብቸኛ ፍላጉት ሀገሩን መታደግ ነው። «ሕንጁት ያለ ንፁህ ስሜታዊ ነው?» ሲል ፎርደን አሰበ። «እውነቱን ይሆን እንጂ?» አያለ ራሱን በራሱ ጠየቀ።

ሪዛርድ ኩክሊንስኪ በዚህ ሞራል የተገነባው ሀፃን ሳለ ነው። ገና የዘጠኝ ዓመት ህፃን ሆኖ የሂትለር ጦር በ1939 ፖላንድን ሲወር በዋርሶ ቤተ-መክራብ አካባቢ አየኖረ ተመልክቶአቸዋል። ይህ ህፃን በዚያ የጨቅላ እእምሮው

ናዚዎች የአውራ ሞካሄ ተክትሀታል። የናዚ መታኖሮች ፲፬ ፓላንዳውያንን ግንብ አስደግፈው ጥይት ሲያርከፈክፉባቸው በነደሉ ተመልክቷል።

የናዚው ጭካኔ በመጀመሪያ በዜተሰባቹ ላይ ደረሰ። ይዘርድ አባቱን ሆየልቀት ያውሳል። ጣፋጭ ሰው ነበር። አስራሚና ደግ አባት። አባቱ በሠራ በሚዋጋው ተቃዋሚ ሰዓር ውስጥ ተሞኒ አባል ሆኖ ህያውቱን ስነሂል። በዘጲሥ ዓፈ የክክሊንስኪን ጋላት ወንድምንም የሚስዘር ፖሊሶቹ ገስታፖን ከቤቱ ደዘውት ሂዱ። ከዚህ በኋላ ቤተሰቡ የነበረ ልጻችውን ለማዬት አልተደሰም።

ከዘኛው የልደት በኃሉ በኋላ ትንሹ ኩክሊንስኪ ራሱን በጀርመኖች የፖሌ ካምፕ ውስጥ አገኘ። ከሩሲያ እስረኞች ጋር አብሮ ይሠራ ነበር። ሠዓንቱ አንዳለተ ከሞምቦ አመለጠ። በ1945 አንድ ማለዳ ወደ ሀገሩ ለመመለስ መንገድ ጀመረ። ተዩ ሠራዊት የጀጋመን ኩሎማ በመንቸው ብረስላው በሰልፍ ሲያልፍ ተመልክቷል። መንገድ ዳር ቆሞ ለድል አድራጊዎቹ ደስተውን ገልጿል። አንደ ሌሎች ፖላንዳዉያን ኩክሊንስኪ የኅዜትን ሠራዊት አንደ ጀግኖች ነበር የተመለከተው። ያ ሁሉ ደስተው ግን ወደ ሀዘን ተለወጠ። ወደ ዋርሶ ሲመለስ ከተማዋ ወድማ ተመለከተ። አት-ዙቱ የተቀበረበት ሰፈር በቁርስፉ-ሽ ክምር ተሞልቷል። በህሳቢነት ስሜት መብሰንሰን ጀመረ። ከዚህ በኋላ ከእዝህ የወደፊት መራሪዎች ሀገሩን ለመታድግ ሰራት ቃል ሰጠ።

ለኩክሊንስኪ ሀገሩን መታደግ ማለት ራሱንና ፖላንድን ከጀርመን መንጋጋ ካወጡ ከሶቭየቶች ጋር ማስተሳሰር ማለት ነው። በ1947 በሞድር ጦር ዕጩ መኮንኖች ትምህርት ቤት ገቡት ሰለዘነ። የወታደራዊ ህይወቱ ፈር ተቀደደ። በ1952 ጋብቻ ፈጽሞ የሁለት ልጆች አባት ሆነ። ከወንድ ልጆቹና እሱ ሃንነ አያለ ኮሚያቁላምጣት ባለቤቱ ጀአና የቤተሰብ ህይወት የሚያስቀና ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶቭዬቶች በፖላንድ ላይ ያሠቃቸውን ማጥቂት እንደጀመሩ የፖላንድ ሠራዊትም ያሠቃም እየተሰጠዉ ሂደቱ ኮሚኒስት ያልሆኑ መኮንኖች ከሠራዊቱ ተጠራረጉ። ሴጠርድ ሲዋሪድ የመጣው የፖላንድ ወታደራዊ የደንብ ልብስ በራሲያኛ ሞያል ተሰወጠ። ልዙን የሚሰውሩት እኒያ የፖላንድ የእርሻኛነት መዘመሪኛና የጋራ ሀሰት ማሠረጊያ ጊዜያት ማርክሲዝም ሌኒንዝምን ሠሚሰጠዉ ኮርሶቲ ከተሰባም ተተኩ። የፖላንድ የመከላከያ ሚኒስትርን ሥፍራ የሶቭየት ማርሻል ተሾመውበት እስከናተደው የጠሩ ቁልፈዊ ነዋት ተገሰሰ። ፖላንድ የሩሲያ ቅኝ ተገዥ ሠኖት። በፖላንድ ቁልፈዊ መዘመር ግን «ሕኛ እስካሰን ድረስ ፖላንድ አልጠፋችም» የሚለው ሰንኛ መደመጡን አላቋረጠም። ያለ ታል በክሰጊስክ አስምር ውስጥ ማቃጨለን ተየዓል።

ወሳኔ መኮንን አሠተሰሰዘን አምቶ በሥራው ውስጥ መደበኛ መረጠማገም በሆን እንደ ሪዛርድ ኮክሰጊስክ ጠንሬ ሠራተኛ አልነበረም። እጅግ በጣም ፈጣኖ ጠያቂዎች በመሙ ጊዜ ሁልም ጣቱን የሚተከረው «ኮክሰጊስክን ጠያቂ» እያለ ነበር። የሌሱ ጠንካራ ሠራተኛነት በማንም ዘንድ የሚያመሰግነው ነው። በ1964 ሪዛርድ በሻልቅነት ማዕረግ በፖላንድ የመከላከያ መምሪያ ውስጥ ማገልገሰን ቀጥሏል። ከዓተኖ የወታደራዊ ልምምድ ፕሳኖችን ሲሄድ ቆየ።

የሶቭዬትንና የፖላንድን የጋራ ወታደራዊ ልምምድ በደንግው ግዳንስክ አካባቢ ሲያቀናጅ የተወሰኑ መኮንኖች ቅጠልያ መልክ በነበረው መኪና ተመሳስለው ተመለከተ። በውስጡ የሶቭየት ቲክኒሺኖች የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ይቆጣጠራሉ። እንደሚታወቀው ፖላንድ ከኒሉስር ነፃ የወጣ ሀገ ናት። ዳሩ ግን አንድ የኒኩስር የጦር መሣሪያ የተተከለበት ሥፍራ ቀልቡን ሳበው። በመሣሪያው ላይ አቀርቅሮ መርዘ ተጭኖ የተያዘ አባብ ያመለከል በአጭ ዝሰሰው። ከዚህ ጊዜ በኋላ በሶቭዬቶች የኒኩስር ሚሰጠር ውስጥ አየጠሰተ በጣ ቁጥር አሰሪራ ከፅል አስምሮውን አናጠመመ። ተረሸሸ። ሞና ሥራውም በሞስራሳውያን ሳይ አመንተኛ ውሣያ ማዘጋጀት በመሆኑ ዲናው ለፖላንድ እንደሚተርኩ በግልጽ ተረዳ።

ሶቭየት ህብረት ፈጣን ሳልታ ንብ ሰፊን የምዕራቡን ዓለም ለመጠረር ሠሚያስችል መልክ አደራጅታለች። በመሳሉ ፖላንድ ሁለት ሚደለን ወታደሮች ወደ ምዕራብ እንደማለበል የሚገለጠባት ሀገር ልትሆን ነው። ኒዮ ደግሞ ሶቭዬቶች ፖላንድ ውስጥ አሰካሰ የኒውክለር ጋያሱን መጠቀሙ እንደማያቀር ኮክሰጊስክ ተገንዘበታል። ውጠቱ ግልጽ ነው፡ የኒውክለር ሳጥኖቹ ፖላንድን በሞስ የታለች ያደርጓታል። የሚጠሳት ሀገሩ ለመከላከል የቀረበች በጎ ሀሳብ። በዚህ መኮሩ ግራየተጋለው ርዝርድ ሁለት አሰቃቂ የጉዘኖቹን ድርጊት ያከታውሳል። ጎሬሌ 1968 የሩቭየት ጦር ቼኮስሎቫኪያን ወርሮ ጉራግን ያሳለ፤ በ1970 ደግሞ የፖላንድ ሠራዊት በጉዳንስክና ግዲንያ ከተሞች ሰሰማዊ ሰልፍ የወጠ ዜጎችን ጨፍጭፏል። ይህን የተመለከተው ኮክሰጊስክ ወደ ፣ሄጀው ዞር ሩተመልከት፣ እንሀ ያደሰች ያደረጉትን፣» ሲል ሥጋል። ካገዳንስክ-ግዲንያ ያግና እልቂት በኋላ ፖላንድ ከእንድ ቅኝ ግዛ ወደ ሴላ ቅኝ ተገዥ መሸጋገሯን አሰሳሰሰ። ሶቭየቶችን አንደ አደገኛ ጨቋኞች መመልከት በመጀመር የወጣትነት ዘመን አመለካከቱን ሙሉ ሰሙሉ ቀየረ።

እንደ ነገርም ሰግደረግ ወሰነ...

በሚቀጥሉት ዓመታት ኮክሰጊስክ ምን መሥራት እንደሚችል ዕቅድ አወጣ። አዚቱ ውስጥ ብቻውን ሆኖ የሶቭዬቶችን ምስጢራዊ የስትራቴጂ መረጃዎችን በማከታተሸው ላይ አሰራረ። እነዚህን መረጃዎች ለማን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚያስተላልፍ ጠንቅቆ ያውቃል። ፖላንድን ሊታደጉ የሚችሉ ፖለቲካዊና የወታደራዊ ጡንቻ ያላቸው አሜሪካውያን ብቻ ናቸው። ግን ታዲያ እንዴት አነሱን ማግኘት ይቻላል? ከዋርሶ ከተማ ሆኖ አሜሪካኖችን ማግኘት ከቶ የሚያታስብ ነበር። የፖላንድ የፀረ-መረጃ ነፍስ የአሜሪካንን ኤምባሲ በአይነ ቁራኛ ሌትና ቀን ይከታተላል። ስለዚህ ግንኙነቱ ከፖላንድ ውጭ መሆን ነበረበት። ኩክሊንስኪ በእንዎሮው አንድ ሃሳር ብልጭ አለለት። እጅግ ጠቃሚ የሆነን መረጃ ለመስጠስበስበ የተወሰኑ መኮንኖች በአውሮፓ የባህር ጸርቻ ላይ እየተንሳፈፉ መሥራት እንዳለባቸው አለቆቹን አሳመኑ። ቡዜሪስኑ ሽፋን ኩክሊንስኪና ዘጠኝ የጦር ሠራዊቱ ኮሶኒሶች ሊጊያ የተሰኘች ጀልባ ይዘው ብዙ የአውሮፓ ወደቦችን መጐበኘት ጀመሩ።

1972 የነሐሴ ወር። ከተትር በኋላ። ሊጊያ ሚልዛልምሻን በተባለ የጀርመን ወደብ ላይ መልህቋን ጣለች። ኩክሊንስኪ ከከተማው ጋር ራሱን አመሳስሎ ረዥም ጉዞ አደረገ። በመንገዱ ላይ አንድ አርሳስ፣ ማስታወሻ ደብተርና ሁለት ፖስታዎችን ገዛ። ማንም ተከታታይ የሌለበት መሆኑን እያረጋገጠ ወደ አንዲት አነስተኛ ፖስታ ቤት ዘለቀ። በጥንቃቄ በተከሸነ እንግሊዝኛ «የአንዲት የዋርሶ አባል አገር መኮንን ነኝ። በጀርመን የአሜሪካ ጦር ኃይል መኪል እንዲሰናኝኝ አፈልጋለሁ። የዚህ ሰው ማዕረግ ቢያንስ ኮሎኔል መሆን አለበት። ሩሲያኛ ወይንም የፖላንድ ቋንቋዎችን መናገር ይኖርበታል። ከአዘርላንድስ ዋና ከተማ ሆኜ ከአምስት ወይም አሥር ቀናት ጉዞዬ በኋላ ስልክ ለአምባሲያችሁ አደውላለሁ» ሲል ጽፎ አዘጋጀ።

ደብዳቤው ላይ ፈርሞ ጂ.ቪ. የሚል የሃሰት ሰም ሃፈ። የጣት አሻራውን ከደብዳቤ ላይ ለማስወገድ በመሃረቡ ጠራረገውና ፣አሜሪካ ወታደር አታሼ የሚል ቡተሳፊት ፖስታ ውስጥ ደብዳቤውን ከተተ። ከዚያም ሁለተኛውን ፖስታ ከፍቶ «ለአሜሪካ አምባሲ - ቦን » ሲል ሃፈበት። ከዚያም ወደ ፖስታው መጣሃ ሃደ ፖስታው ሳጥኑ ውስጥ በትክክል መግባቱን አረጋገጠ።

ሪዘርድ ደብዳቤውን ከከተተ ከሳምንት በኋላ ጀልባው ኔዘርላንድስ ደረሰች። ከዚያም ከቦን ሆኖ የአሜሪካ አምባሲ መታደራዊ አታሼ ቢሮን አገኘ።

«ጊ.ቪ. ነኝ» ሲል በሩሲያንኛ ራሱን አስተዋወቀ። «ለመሆኑ ደብዳቤዬ ደርሶአችኋል?»

«አዎ» (አሥ) የሚል መልስ አገኘ።

«ከዛሬ ጣቢያው ፊት ለፊት ከምሽቱ 4 ሰዓት ጠበቀኝ። የታደም መጽሐት በግራ እጅ ይገር አጠበቅሃለሁ።»

ያን ምሽት በጣቢያው ተገኝቶ ቅኝቱን ቀጠለ። አንድ ቀውሳላ፣ ግብዳና ወጉረ "ሬጫ ሰው ወርቃማ መነጽሩን አጥልቆ በዋና መግቢያው ፊት ለፊት ቆሟል። ሰውዬው በእጁ የታደም መጽሐትን ይዟል።

«ደብሬ ቬቸር (አንደምን አመሸህ?)» አለው ኩክሊንስኪ «ተከተለኝ» ብሎት ሰውዬው ንብውን ወደፊት ቀጠለ።

ኩክሊንስኪ ተከትለሎት ጣቢያው ጥግ ወደቆመች መኪና አመሩ። ሾፌሩ ወደ አንዲት አነስተኛ ሆቴል ይዞአቸው ከሄደ። ሆቴሉ ውስጥ ገብተው ወደ ሁለተኛው ፎቅ አመሩ። ሰውዬው «ስሜ ሂንሪክ ይባላል» ብሎ የወታደራዊ መታወቂያውን ለኩክሊንስኪ አሳየው። «የአሜሪካ ጦር ሠራዊት ኮሎኔል ነኝ» ኩክሊንስኪም በበኩሉ «እኔም የፖላንድ ጠቅላይ መምሪያ መኮንን ነኝ» ሲል ራሱን አስተዋወቀ። ቀጠለ። አሱና አንዳንድ የፖላንድ መኮንኖች ከአሜሪካ ጋር በመተባበር ጦርነቱን ለማስወገድና ፖላንድን ከሶቭዬት ጥላ ሥር ለማውጣት አንደሚፈልጉ አስረዳ። ስለ ሶቭዬት የጦር ዕቅድም ጠቃሚ መረጃዎችን ሊያስተላልፍ አንደሚችል ገለፀለት።

በመካከላቸው ረዥም ዝምታ ሰፈነ። የሶቭዬትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወታደራዊ ብቃት በተመለከተ ኩክሊንስኪን በጥያቄ ፍተሻ አጣደፉት። ይህን ያደረጉት ስለ ማንነቱ ማረጋገጫ ለማግኘት ነበር።

ኩክሊንስኪ መሰመሩን እንዳለፈ ያወቀዋል። አሚሪካኖችን ከማመን ያለፈ ግን ምርጫ አልነበረውም። ለጥያቄዎቻቸው ሁሉ በታማኝነት መልስ ሰጠ።

ከሁለት ሰዓት በኋላ ሄንሪክ ፖላንዳዊውን መኮንን ወደቡዳር ጣለው። ኩክሊንስኪ በሚያደርገው የግኑኝነት ጥሪ መሠረት በአምስተርዳም፤ በሮተርዳምና፤ በአስተንድ ለመገናኘት ተስማሙ። በዚያ ምሽት በከድ የታሰረ መልዕክት ከዚግ ኩተማ ወደ ዋሽንግተን ተላለፈ።

ሄንሪክ በሁኔታው ተገርሟል። ከጥርጣሬም ፈጽሞ ነፃ አልሆነም። «በሶቭዬት ወይም በፖላንድ መረጃ ማዕከሎች ኒቶን ለማታለል የተተከለ ጥልማሞት ቢሆንስ? ወታደራዊ መፈንቅል ለማካሂድ የሚችል ጀብደኛስ ከሆነ?» ሄንሪክን የሚያስጨንቁ ጥያቄዎች ነበሩ።

በሚቀጥለው ስብሰባቸው ሄንሪክ መደበኛ የሆነ የስለላ ጥያቄዎችን በማቅረብ ኩክሊንስኪን ፈተሸው። መልሱን የሚያውቀውን የዋርሶን የጦር ይዞታ አስመልክቶ ጥያቄ አንሪፈለት። ኩክሊንስኪ በሚያስደንቅ የማስታወስ ችሎታው አንኳር የመረጃ ጭብጦችንና አሃዞችን ፈትፍቶ አንረሳቸው። መልሶቹ ትክክለኛና የማያወላውሉ ናቸው። ሄንሪክ ለማረጋገጫ ሀሰተኛ የሆኑ መረጃዎችን ጠየቀው። ኩክሊንስኪ ግን የማያውቀውን አላውቅም፣ ካልሆነም ዝምታን ይመርጥ ነበረ። ሁሉም ነገር ተረጋገጠ። ይህ ሰው ዕውነተኛ መሆኑን ሄንሪክ አርግጠኛ ሆነ። «ወደ ዋርሶ ከተመለስክ በኋላ እኛን ለመገናኘት አትሞክር፤ እኛው ራሳችን እናገኝሃለን» አለው። ሲላም አንድ አጭር መመሪያ አከለለት «መኪናህን ስታቆም መስኩቱን በጥቂቱ ክፈት አድርግ።»

ሄንሪክ ልዩና አዲስ ምንጭ እንዳገኘ አርግጠኛ ሆነ። መገመት ያልቻለው ነገር ቢኖር «በተገቃላው ጦርነት ዘመን» ታላቅ የስለላ ስራ መጀመሩን ነው።

ሰላምታ ከንሥር አሞራ

ኩክሊንስኪ ሀገሩ ከተመለሰ ከአምስት ወራት በኋላ ምንም የሆነ ነገር አልነበረም። በ1973 በአንድ ጭጋጋማ ዕለት አንድ ፖስታ መኪናው ውስጥ ተጥሎ አገኘ። ሁለት የዋርሶ ኩተማ አድራሻዎች ናቸው ያሉበት። የመጀመሪያና ተለዋጭ የግንኙነት ስፍራዎች። በስፍራው ልትገኝ የምትችል ዝርዝር የመኪና መግለጫም አብሮ ተያይዟል።

ኩክሊንስኪ ዘጠኝ የፊልም ጥቅሎችን ይዞ አውቶቡስ ተሳፈረ። ወደ መጀመሪያው ቀጠሮ ስፍራ ወደ ሥልስኪ መክነ መታበር ዘነፈ። ከዚያም በተወሰነ ነጥብ ጣቢያ ላይ መኪና ያዘ። ከመኪናው ወጥቶ በእካባቢው ተንዘ – የመጀመሪያውን ስህተትም ፈፀመ። ሁለት የእግረኛ ሰዓሮች ሌትና ወንድ ሆነው መኪና ውስጥ ይጠባበቃሉ። ኩክሊንስኪ በዩኒፎርም መሆኑን ጠጋ ብለው ተመለከቱ። አይናቸውን አላመኑም። «የመሰቀያ ገመዱን» ይዞ መምጣቱ ግልጽ ነበር። ኩክሊንስኪ በፍጥነት ከኋላ ንብዱ በዚያ ህገወጥ በሚተራመሰበት ስፍራ «ይህ ለኔቶ የጦር አዛዥ ነው። ሁሉም የሶቭዬት ጉበራቶች ናቸው - ስጠታዩ ለጦር ኃይሉ» ዓሉ ፊልሙን አተበላቸው።

ሁለቱ ሰላዮች አመሰግነው ከእነሱ ጋር ሲገናኝ ሻህ ስትሮንግ የተሰኘ የሚስጢር ስም እንዲጠቀም ነግረውት በፍጥነት ከነፉ።

ኩክሊንስኪ ያስተላለፈው መረጃ ፈጽሞ ከዚህ ቀደም ያልታየ ነው። በሲአይኤ ዋና መ/ቤት ውስጥ ያሉ ኤክስፐርቶች በጉዳዩ ተገረሙ። የተላለፈውን መረጃ ፎቶ ኮፒ የሚያደርገው ሀላፊ ገጽ በገጽ አየተመለከተ በግራሞት አፏጨ። ሁሉም የተላለፉት ደነመንቶች ከፍተኛ ደረጃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምስጢሮች ናቸው። ለዚህ ያልታሰበ ከፍተኛ ምስጢር «ዋሽ ስትሮንግን» ጉዳይ በሚዘዘ የሚከታተል ሰው ተቀምጧል።

በ1973ቱ የሰኔ ሞቃታማ ሴሊት ዶቭድ ፎርድን ስሜቱን ውጠ ቁጭ ብሏል። ይህ የሆነው ከሁለት ወር በኋላ መሆኑ ነው። በጀርመን የሀንቡርግ ምስጠራዊ ቢሮ ውስጥ ሆኖ እጅግ ለከራው አስፈላጊውን ሰው ይጠባበቃል። በሩ ተበርግዶ ተከፈተ። ኮሎኔል ሄርኒክ ወደ ክፍሉ ውስጥ ዘው ብሎ ገባ። አብሮት ቀጭን፣ ወጣ የመታው ሰው በስጋርተኛ አለባበስ አዘገዘ ቆሟል። ይህ በአረፍት ላይ ያለ የሚመስል ሰው ወደፊት ተራመደ። በተጠንቀቅ ቆሞ «ኮሎኔል ሬዛርድ ኩክሊንስኪ ነኝ ጌታዬ» ሲል ሰላምታ አቀረበ። «ከንሥር አሞራ ሰላምታዬ ይድረስህ» በማለት ዶቭድ ፎርድን አወሩ ስጠው። «ለመሆኑ ምን ያህል ጊዜ አለህ?» የሚለው ጥያቄ የሁሉም ሰዎች ቀልብ ለጥቂት ጊዜ ሳበ። «ጥቂት ሰናውራ፣ ከዚያም በአሰቮኪይ ወደ ሥራችን እንገባለን።»

ፎርድን እጅ የገባውን ሰው በሚገባ አጠናው። የክለሳ ሥራ ፈጣን እንምሮን ይፈልጋል። የፎርድን ሀሣብ ይህ ሰው ምንም ዓይነት የነገር መንዛዛትና ሽንገላ አንዳይኖር እንደሚፈልግ ነገረው። «ኮሎኔል» አለው «እኔ የሠር መኮንን ሳልሆን የሲአይሕ መኪል ኖኔ። አንተ መረጃዎችን ያዘጋጀሽው ለአሜሪካ ወታደራዊ ክፍል መሆኑን እናውቃለን። ካንተ ጋር በጥንቃቄ ለመሥናኘት የሚያስችል አካልና አባላት አሉን። ወታደራዊው ክፍል ያንተን ሙሉ አገልግሎት እንደሚያገኝ አረጋግጥልሃለሁ» ብሎ የዋሽንግተንን ፍላጐት በተመለከተ ዝርዝር ጥያቄ አዘጋጀለት። ሬዛርድ ለሰጣያውቀው መልስ ከሰጠ በኋላ ላልቻለው በአእምሮው ማስታወሻውን ወሰደ።

በመረሬ ቀዳዳ መሸሸክ

ሰዓቱ ያሮጣል። «መመረዶ» አለ ፎርድን፣ «ከፍተኛ ጥንቃቄ አድረግ። ብቻህን መሆንህን ካላረጋገጥክ በስተቀር

ምንም ዓይነት ያልጠበቅኸው ፎቶ ሆኖ አንዳታደርግ። አንድ ሰው በድንገት ከደረሰብህ ተረጋጋ። በተጥያ ዓይኑን ትከር ብለህ አየው። ዓይንህን ከላዩ ላይ አትንቀል - ሊመለክት የሚችለው ዓይንህን ብቻ ነው። ተልዕኮን ለመጓብ ሴላ ታሪክ አሰናዳ። መደበኛ ሥራህን በበፉት መተጠለህን አረጋግጥ» አለው።

አስረክቦትና ለምናለባቱ የሆነ ሰው ቢጠይቀው ከዜት አንደተገ ሚምር ነገረው። ደረሰኙቹ በሙሉ በክለሳንክ ስም ተዘጋጁ። ተከታታይ ግንኙነቶችም ተቆረጡ።

«በየርሶ አተማ ውስጥ ያህሚንት ለማከረክብ ካልሆነ በስተቀር የትናንብ ግንኙነት የለም» ሲል ሄርሣቱን ገለፀለት። «እጅግ አደገኛ ነው፣ ግንኙነት በምልክት ብቻ ይሆናል።»

ሚቀጥለት ወራት ኩክሊንስኪ የስሰሳን የተለየ ዓለም ተሰማመደ። የነድ አጠራቀም፣ ምልከት መልዕክት የማስተላለፍንና የመቀበያ በደ.ያትን ልትም እደገን አጠና። በመሰከት ላይ የተጣዙ ክር ካስ «መልዕክት አለኝ» ማለት ሲሆን «መጽሐፍ ከመከና ጋሳ ከተቀመጠ «የሚከታተሰኝ ጥላ አለ» ማለት ነው። ሁለት የእጅ ፣ንጥች በግራ እጅ ከተያዙ ወሃም የቆመ መኪና ትግው ወደ ግራ ከሆረ «ሶስ ነው» የሚል መልዕክት ተለዋወጡ።

ኩክሊንስኪ ወደ ቢሮው አንደገባ ያከመጉዮቹን ሁሉ በእጅ ዓደን መመልከት ጀመረ። ራሱን ለስራ የሰጠ ይህ ጠንካራ መኮሄን መንታ ህይወት መኖሩን ተጠለ። ሲአይሕ የሰጠው አንስተኛ ኮሚራ በኪሱ ውስጥ አንዳለ ነው። በምሳ ሰዓት አጅግ በጣም ምስጠር የሠነው የሶብዬትን መረጃ በጠረጴዛው ላይ ዘርግቶ ማንሳት ጀመረ። ሳይጠበቅ አንድ የፀረመረጃ ክፍል ኮሎኔል ወደ ቢሮው ዘው ብሎ ገባ። ኮሚራው በእጅ ላይ ነበር። «ዓይንህን ከላዩ ላይ አትንቀል» የሚል የፎርድን ማስጠንቀቂያ በአእምሮው መጣ። ድርት ብሎ የኩሎኔሉን ዓይን አየተመለከተ ኮሚራውን ከሱ ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተተ፣ በፎለ እጅ የሲጋራ መለኮሻውን አውጥቶ ለክለሳት።

ሥራ በዛ» ሲል ኳሉኔሉ በቅንጉት ጠየቀው።

«እንደቀድሞው» ኳው ሲል ኩክሊንስኪ በፈጥንታ መለሰ። ከዚያም «እንካ ሲጋራ» ብሎ አቀበለው። ሁለቱም ሀሳብ ከለኩክ ሲለዋወጡ ቆይተው ኮሎኔሉ በጠረጴዛው ላይ የተዘረጉትን መረጃዎችና ኩፔራውን ሳይመለከት ጥሎት ውጭ አጥፎት ቀኖት ግን «ተመልከቱኝ ይሆን እንዴ» በሚል ሚርሚራ ኩክሊንስኪ ተብከንከነ። ምናልባትም ይኸታቱኝ ይሆናል ብሎ ቢጅምትም ቀስ በቀስ ልቦናውን ሩም አደረገ።

በመጀመሪያ ፊልጅ ሌላ ተጨማሪ አዲጋ ተከሰተ። ኮሎኔል ኩክሊንስኪ የሚያስተላልፈውን የፊልም ጥቅል ይዟል። ከዚህ በፊት የነቪል ልብሱን ቀደዶ ወደ ቁጠር ስፍራው እደተሰጠ ኩክሊንስኪ ሊነሳውን እንደረዘ ሲጠባበቅ ካፈይ ይዋል ነበር። ስትን ትመለከተ። መረጃ ተቀባይዋ መኪና ጀምሮ። ሩካት ደቂቃዎች አለፉ። ፎርድን ከአንድ ወደም ከሩካት ደቂቃ በፊ ቆም እንደፈጠብት አስጠንቅቆታል። ከዚህ ነገር የያዝውን ጥቅልል ለማቅበል እድግ ነበ። ሩካት ተስል ደቂቃ ሆነ። ምስት ደቂቃ። ጥሩ አይደለም። ሶስተን መልቀቅ ነበረበት። መኪናዋ ወደ መንገዱ ዋግ ላይ ትቅይ ነበር። ምንም ሳያስብ ሥነስነን የንግር ነበርስ ጥሀ እጅን እያውነበነበ ወደ ስፈሩ በመዛር ጠብራት አዘፈነት። የመጀመሪያ ላይ የገመተው ክትትል አየቃደጀበት መሆኑን ነው። ስለዚህ ከአካባቢው ለመስወር በነንር ኢግርጉግ ውስጥ አልፎ ቀጭት ጉዳና ላይ ሙሳ። የሚሸት መኪና ከፍተኛ መብራት እያበራት ሩሰችበት። በፍጥነት ወደ ሌላ መንገድ ላይ ተዛወረ። ከገማሽ ሰዓት ቡኋላ ፊቱን በዋርነ የጠቡር ኅዜያ አጠገብ ላይ አገኘ። ብዙ ሰዎች በነነፍ ይጠብቁት። አንዱ ባቡር አስዚያፍ መሆኖ ወደ ኖናው ማፉሚያ አለፈ። ባቡሩ ኅዜያውን

ከመልቀቁ በፊት ሁለት ፌርማታዎች ያህል ከነዳ በኋላ መኪናውን አቁሞ ከላይዋ ላይ ወረደ።

አካባቢውን ሲቃኝ የባቡር መሣፈሪያው ወናውን ቀርቷል። ተነፈሰ። ተከታታዮቹ ግን ቢያዩትስ? «ራሴን መለውጥ አለብኝ» ሲል አሰበ። ገጽታውን መቀየር የግድ ሆነ።

በመጀመሪያ ሻንጣውን ከዊስላ ወንዝ በድንጋዮች ሞላቸው። ከዚያም ታክሲ ይዞ 24 ሰዓት አገልግሎት ወደሚሰጥ ፀጉር ቤት በመሄድ ፀጉሩን ተስተካከለ። ቤቱ እንደተመለሰም የለበሰውን ልብስ አቃጠለ። በሚቀጥለው ፊለት በሥራው ላይ ተገኘ። ከሰዓት በኋላ በቢሮው መስኮት በኩል አይኑን ሲሮሃትር ለየት ያለ ሰው መኪናው አጠገብ ቆሞ ተመለከተ። «ክትትል ነው ወይስ አጋጣሚ? እንዴት ሊሰውቅ ይችላል?» ሲል ቀዘመ ዳሩ ስለላውን ከመተጠል ሌላ አማራጭ አልነበረውም።

ግዳጅ ያነገበ ሰው

ፎርድን ወደ ሲአይኤ ዋና መሥቤት እንደተመለሰ ዓለማቀፉን አፐሬሽን ሶስብሰቡትንና የምሥራት አውሮፓን መምራት ተጠለ። ኩክሊንስኪም እጅግ ዙጭም የሚያስፈንቱ መረጃወችን እየመገበው ነው። ከዚያን በፊት በ1960ዎቹ ለዩ መረጃዎች ያስተላለፈ ሰው ቢኖር አንድ የጎብዚት ከጎኔል ብቮ ነበር። ደህ ኮሎኔል በዙሀ የጎብዚትን ሚስጥል መትከል አስመልክቶ መረጃ ያስተላለፈ ሲሆን ጎብዚት መንግሥት ለመቀጣጣሪ ሙሚል ከእነ ህይወቱ በሽሳት ሉምኖ ገድሎታል። ኩክሊንስኪ ስለዚህ ሰው አሚሚት በወፌ ደረጃ ስምቷል። በፊልምም አሚሚቱ ተቀርጾ መቀመጡን አረጋግጧል። ሆኖም መረጃ ከማትበል ደህ ዘናነ ድርጊት አላገደውም።

ኩክሊንስኪ በተለያየ ጊዜ ያላቸው ምስጢሮች

t.me/OLDBOOKSPDF

ቡታጅሯን ለመጠቅለሚያ ዋጅ የመግሪያዋ አገልግሎት ነው።

ሶቭዬት ህብረት በጋዳንስክ በተፈፀመው ሁኔታ መቆጣትዋን ከክሊንስኪ ተገነዘበ። ቀዩ ሠራዊት የፖላንድ መንግሥትና የዋርሶ አባል ሀገራት የዋለሳ የሠራተኛ ማህበር ጉዳይ እጅግ አሳስቧቸዋል። ጥረታቸው ማህበሩን ማፍረስ ላይ አተኮረ። ዋለሳ ግን እንዴት ያለ ራሱን የሰጠ መሪነጅ በዋርሶ ከተማ ውስጥ እንዳለው የሳኑበ ብልጭታ መሞቱበት አያውቅም።

በ1980 ህዳር መር አንድ ያልተጠበቀ ሁኔታ ተፈጠረ። ግማሽ ሚልዮን የዋርሶ ጦር ፖላንድ ወስን ላይ ተከማቸ። ከክሊንስኪ ጉዳዩን የደረሰበት ታህሳስ መጀመሪያ ላይ ነው። የጦሩ ዕቅድ የነበረው ከሩሲያ፣ ከቼክስሎቫኪያና ከምሥራቅ ጀርመን 15 ክፍለጦሮች ይንደረደራሉ። ግባቸውም የሠራተኛ ማህበሩን አመራር ማስር ወደም ማስወገድ ነበር። የታቀደው ጥቃት ገና ከመካሄዱ በፊት ሪዛርድ አስቸኳይ ግንኙነት ለማድረግ ወሰኑ። የተወሰኑ ቀናት እንደቀሩ የወረራው ፕላን በአሜሪካ የብሔራዊ ዎጥታ አማክሪ ዝብሪኔው ብሬዝዚንስኪ እጅ ገባ።

ብሬዝዚንስኪ ፕሬዚዳንት ካርተር በአስቸኳይ እርምጃ ይወስዱ ዘንድ አግባቧቸው። ፕሬዚዳንቱ ታህሳስ 3 ቀን መግለጫ አደጡ። በግሉ ብሬዝዚንስኪ እጅግ አደገኛ ሁኔታ ሲከሰት እንደሚችል ለጎብኚዎቹ አስታወቁ። በዚሁ ሩሲያኖች ከርሃቸው ተቀጠቡ። ሆኖም የኮብኚዎቹ መሪ ብሬዝዚንስኪ ለላ መንገድ ተከተሉ። በምስጢር ለጀኔራል ሽሩዚልስኪ የመሃ ማህበሩን እንቅስቃሴ እንዲያናኑ ትዕዛዝ ሰጠ። በዚያው ወር ሽሩዚልስኪ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ዕትድ ይዘው ወደ ሞስኮ በረሩ። ከተገዘው ቡድን ውስጥ ከሶስቱ ሪዛርድ ከክሊንስኪ እንዳ ነበር። የሠራተኛው ንቅናቄ ከሰሙት ወደ ዕሰት እየፈረጠመ ሲመጣ ሆዘቡ በነዩት የመታንፈስ ስሜቱ ጥበቡ

ከክሊንስኪ አፈናው እንደሚከብት ተረድቶታል። በሚሜዙ ወደ ቤቱ ሆዘ ከመግባት ይልቅ ሰለአይኤ ጓከመኮቦችን ፎቶ ነር እየደረገ ከመኝውም ጊዜ በላይ እጅግ ብዙ ሪፖርቶችን አስተላለፉ። በሲአይኤ ጠቅላይ መምሪያ የተበራቀው የመረጃ ተንታኝ በዚህ የስለላ ጉርናፍ ተጠመዱ። ከዚሁ ጉን ከክሊንስኪ ሥራውን አጠንክሮ ገፋበት። ናፍኮቱና የሚልከው መረጃ መጠን እጅግ ጨመረ። አሜሪካኖች ከዋርሶው የስለላ ጽ ቤት ጋር ተቀናጅተው «ናፕኮቱን እንዲተንስ ንገሩት» አሉ። ሁኔታዎች እጅግ አደገኛ ሆኑ። የሶቭዬት ሰላሮች እጅግ ከፍተኛ የመረጃ መሽሳሽ እንዳለ መንግሥታቸውን አስጠንቅቀዋል። መስከረም 1981 በተወራ አንድ ምስጢራዊ ስብሰባ የፖላንድ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር «ሞስኮ በፖሊት ቢሮ ደረጃ ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮች የፖላንድ መሪ ማህበር ዘንድ በ24 ሰዓት እየደረሱ ነው» በማለት ስምታቸውን ገልፀውልናል አሉ። ለላው ቀርቶ ማህበሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተመለከተ ሙሉ መረጃ አለው። የፖሳኑ የኮድ ስም «ወደይ» መሆኑን ጭምር ልቅም አድርገው ያውቁታል። «ይህ በአደገኛ ሁኔታ የሚሾልክ መረጃ ነው» ሁኔታው ለፖላንድ ወታደሮች በትሩህ ፍፊ ላይ እንደተገ ትል የመሆን ያህል ነው። ይህ ትል ደግሞ ተደርሰበት ለጨለሰት ይገባል...

የወሂዶሮች ቀን

በዋርሶ ውስጥ ከክሊንስኪ ስለ ጉዳዩ አፈትልኮ መውጣት ስጋ ቅዝቃዜ ተሰራው። በፖላንድ ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚስጠር ስም «ወደይ» መሆን የሚያውቁ ሰዎች ሰበ አይበልጡም። ከዝሀ ውስጥ አንዱ ወዲያው ዋናርሣው ወስኖ መግባቱ አደ.ታብለም።

ከክሊንስኪ ስለም ችግር አለበት። ለመስከረሙ ስብሰባ ሌማግኖር ሽ.ሠ. ጀኔራል ፍሎሪያን ስዊኪ በስሮኪደ ጊዜ ነገሩ ፕላን ላይ ንግግር እንዲያዘጋጅ አዘዙት። ከክሊንስኪ

t.me/OLDBOOKSPDF

በተለመደ ፍጥነት «ወንጀለኛ ዓይነት ሁኔታ ኃይልን መጠቀም ያስፈልጋል» የሚል የተለመደ በረዳት ጎበር ድንቅሮ ንግግሩን ሮኦ ኮር በማድረግ ላንገስይ ለሚገኘው የሰአያኤ ጽቤት አስተላለፈ።

በኒኃታው ንግግሩን ጀነራል ስሚዝ ሲያጠቃት «ሥይልን መጠቀም የሚገለው አረፍተ ነገር የአኔ ጉዳይ አደደለም» ሲል ወረፍተ ነገሩን ከንግግሩ ውስዮ ሰረዙ። ከነለንስኪ ግን ንግግሩን አስተላልፏል። የተሰረዘው ንግግር ሾልኮ ከወጣ ከነለንስኪ ላይ ጣት መቀሰሩ አደቀሪ ነው። ያም ሆን ያለ ከነለንስኪ መረጃ ማስተላለፉን አለስተባበለም። ከመሸዘረሙ ስበስ በኒለም ቢሆን «ስለ አሸቫኒይ ጊዜ አዋጅ የመጨረሻ ቀን ስልተቀረበም። ሆኖም ገናኑ ሲጠናቀት ተቃርቧል። ከእንግሧ ዝርዝር ሪፖኒዮችን ማስተላለፍ ስለማልችል ይህን መረጃ ለፖላንድ ነባት ከሚታሰቡት ጋር ተጋሩ። ስተጨቆኑ ፖላንዳውያን ነበትን የሚያሳንፈው ሙያ ማክበር ለዘለላለም ይኑር።» የሚለውን መልእክት ጣለ።

በህናር መር ላይ በማከተል ኤሎግፕሮር ሹሙ በጅኔራል ፎርቢ ስኳል'ቪ ስዘለባ ተጠራ። በስብሰባ ጠረጴዛው ዙሪያ ሁለት ከለሎሀችና አንድ ጀኔራል ተካፍለዋል። የስኳለቪ ፊት አመድ ለብሏል። «ዛሬ አዘሀ የጠራኒችሁ ሁለት እሮግ አስፈላጊ ነገሮች በመከናወናቸው ነው። አንደኛው ጀኔራል ሽሩዘርስኪ የአስቫኒይ ጊዜ አዋጅን ካልተገበሩት የፓርቲ ዐሐፊም ሥልጣናቸው እንደሚፈልሙት ስለገለፁ ነው። ሁለተኛው ከሮማ ካለው ምንጫችን የመጨረሻው የአስቫኒይ ጊዜ አዋጅ ዕቅድ ሾልኮ መውጣቱ ተነግሮናል። በአሁኑ ጊዜ ላንገስይ ላይነው» ሲሉ ንዴት በተሞላው ንግግር ተሰብሳቢዎቹን ተገለመጣቸው።

ከናት ጠቅምታ ተዋጠ። ከነለንስኪ ፈጹዎታው ማቢቱቱን ተረዱ። ወደፊት ዘንበል ብሎ ስሜቱን ለመቆጣጠር ተጣጣረ። ለላው ጀኔራል ከተናገረ በኋላ ወዲያው «ሾልኮ የወጣው መረጃ ከእኛ አንዳልሆነ አርግጠኛ ነኝ። ለማንኛውም ለሚያደገው ምርመራ በዘኩሲ ለመተባበር ዝግጁ ኖ» አንዳለ ለጆች ሁለቱ ከሱሚስችም ተመሰሳይ ሃሰብ አቀረቡ።

ከነለንስኪ ሁለም አትኩሪው አንደሚመለከቱት ጠረጠረ። አመቀል ሚስት ነው? «ከከሳሆሆቹ ሃሰብ ጋር መሉ ለመሉ አመሳስለሁ» ሲል ከነለንስኪ በድንገት አጉተመተመ። አሸማገለሁ።

ዘዘህን ጊዜ ስካልስኪ «ልመረሃሬራችሁ አይደለም የጸዘከዚኒተ» ሲሉ ሩጭ። «ሕዘህ የጠራኒችሁ ስለ ሁኔታችን ሙሉ ስዘል እንድንተን ነው» ብለው ስዘለሳው እንደከዚያ ቀደሙ ተከሂደ። ለሚገኘውም አላወቁም። ከነለንስኪ ስበለሳውን ለየኮ አንደወሰባ ከመንከባው ለዘዘው መጫን አስተሞለ። አድግ ከሀደ የወረመረጃ ክትትል ይጠቁየሞል።

ከነለንስኪ ወደ ቤቱ አቀና። ውስጡ በሸ። አካሉ ደክመ። ሚስቱ በሩን ከፍታ ጥና እንደተመለከተችው ቡን ያለውን ፊቱን ተመልክታ ደንገጠች።

«ምን ነካህ ከነለንስኪ?»

«ነገ» አለ ዘደከመ አንደበት «ለኔመታት በበረሎቭቤት አድኖ እንረሽን ከአሜሪካኖች ጋር ተስልፈያለሁ። አሁን ግን ሃተታሽን መስሰኖል። ሠግኖውም ሰዓት ልታነር እችላለሁ» ስል ለጀ ተናት ያህል አብረው ለቆቱ የትዳር ጓደኛው የሚስጠር ቲጠርውን ፈታ። ትዳሯንና ልጅቿን በማለደግ ላደረገችው መልነም ተገባር ሁለ አመሰገናት። ጉዳዩን ከእሷ ቦግስጠር በመያዙም ይቅርታ ጠየቃት።

- በተደናገጠ ስሜት እሉተርቡበት «ሠኩል መግባት ከጀናርብንም? መጥፋት አንችልምን?»

- «አሳውቅም። ግን የጠበበ ዕድል አለ» ቦግስት ጓደኛውን ጸጥ ፎርድንን አስተወሰ። «አሜሪካኖች እናስወጣለን ቸስመኛል።»

ቦግሰዓው ቢሥራው ታጭራ ታየ። ከዚያም ከሰዓት በኋላ ከዚያች አነስተኛ መሣሪያ «ባስስልጣናቱ ስለ መረጃው

t.me/OLDBOOKSPDF

ማፈትለክ አውቀዋል። እኔን ጠርጥረውኛል። እርዳታ አሻለሁ።» ሲል አሰተላለፈ።

ሽሽት

ያን ዕለት ጠዋት ዴቪድ ፎርደን ላንግሊይ ወደ ሚገኘው ጠቅላይ መምሪያ እንዳመራ የምሽቱ ተረኛ መኮንን አንድ ደብዳቤ ይዞ ጠበቀው። «ዋርሶ አንድ ትኩስ መልዕክት ደርሶናል።» አለው። መልዕክቱን በችኮላ ተቀብሎ ወዲያው ማንበቡን ቀጠለ። ይህ ጉዳይ ላለፉት ሰምንት ዓመታት ሲያስፈራው የቆየ አባዜ ነበረ። ፎርደን የመምሪያ ታላፊዎችን ጠርቶ አስቸኳይ ስብሰባ ተቀመጡ። በአንድ ነገር ላይ ግን እርግጠኞች ነበሩ። በዚህ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሊታወጅባት በተዘጋጀች ፖላንድ ሠራዊቱ በከፍተኛ ተጠንቀቅ ላይ ይኖራል። ሁኔታው «ድብቁን ወታደር» ለማውጣት አስቸጋሪ ያደርገዋል። ኪጂቢና የፖላንድ ፀረ-መረጃ ክፍል ፍንጩን ወዳሾለከው ምንጭ እየተቃረቡ ስለሆነ ክትትሉ ጠበቂል። ፖላንድ ውስጥ ማናቸውም የሲአይኤ እንቅስቃሴ ሲትና ቀን በከፍተኛ ቁጥጥር ሥር ወድቂል። በመሆኑ አንድ እርጋታ ተፈጠረ። የዋርሶ የሲአይኤ ምክትል ታላፊ የሆነች ሴት ከክሊንስኪ ጋር ለመገናኘት ወሰነች።

ቡተፈቃቀደ ስሚት ኩክሊንስኪና ሴትየዋ መንገድ ላይ አያወሩ «ከእኔ ጋር አሁኑኑ ከሄድክ ልናወጣህ እንችላለን» አለቸው።

«አይሆንም። እኔና ቤተሰቦቼ አብረን ነው የምንኖረው። ከእነሱ ተነጥዬ ዩትም አልሄድም» ሲል እምቢተኛነቱን ገለፀላት። ኩክሊንስኪ 26ና 28 ዓመት ዕድሜ ለደረሱ ልጆቹ ሰለ ሁኔው ጠቁሞአቸዋል።

«ይህ ሁኔታ ጉዳዩን ውስብስብ ያደርገዋል» አሰች ሴቲቱ ረቡዕ ዕለት ሲያነ እንደሚችል አያሰበ ወደ ሥራው ቦታ አመራ። ክስራው መልስ በዚያው ምሽት እሱና ቤተሰቡ የሚሸለኩበትን መንገድ መርጠው አዘጋጅተው ጥር ወደ ሰፍራው አመሩ። ሁለት ደቂቃ ጠበቁ። የሲአይኤ መኪና ግን ለሰፍራው ገዘር አላለም። የፀረ-መረጃ ክትትሉን ማንቃት አመለከተባቸው ቤተሰቡ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ሀሙስ መጣ። ኩክሊንስኪ እንተለመደው ወደ ሥራው ሄደ። ማምሻውንም ቤተሰቡ ወደ ቀጠሮው ሥፍራ ተሰባሰበ። አሁንም መኪና የለም።

አርብ ደረሰ። ለመጨረሻ ጊዜ ቤተሰቡ በቀጠሮው ቦታ ተሰባሰቡ ለሁለት ደቂቃ ያህል ጠበቁ። ተስፋው ጨልሞ ነበር። ፎርደንና የሥራ ባልደረቦቹ ላንግሊይ ላይ እየተጨነቁ ነው። ሁሉም የእነሱ የዋርሶ ወኪሎች ጥብቅ ክትትል ይደረግባቸዋል። አንድ «ጭራ» እንደሸኛቸው፣ ሌለኛው «ጭራ» ይዘተላቸዋል። ስለዚህ ፎርደን ስልቱን ለወጠ። አዲስ ሰዎችን ለመላክ ወሰነ። ዓርብ ዕለት ከጀርመን ሁለት ወኪሎች ወደ ዋርሶ በረሩ። «ይህ ስልት መስራት አለበት» ሲል በረጅሙ ተነፈሰ ፎርደን።

ዓርብ ዕለት ማምሻውን ኩክሊንስኪ በልዩ መሣሪያው አዲስ መልዕክት ደረሰው «አዲስ ፕላን ነው። ቅዳሜ እኩለ ለሊት ላይ በቀጠሮ ሥፍራ 14 ተገኝ» ይላል።

የመጨረሻው ርምጃ

ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ ኩክሊንስኪ እግቱን ለመጠየት ወደ ገጠር እንደሚሄድ ለአለቃው አሳወቀ። እስከ ሶኛ ከሰዓት በኋላም ሊመለስ እንደማይችል ገለፀ። ይህ የፈጠራ ታሪክ የ48 ሰዓት የነፃነት ጊዜ እንደሚሰጠው ተስፋ አደረገ። ከዚያም ቤተሰቡ ወደ ቤቱ አመራ። እግሪ መንገዱን ከመኪናው መስኮት ቅዠዘ ብሎ የተመለደባትን ኩተማ በስስት ዓይት ቃኘ።

ከሰዓት በኋላ 10 ሰዓት ወደ ጓደኞቹ ስልክ መትዮ እሱና ገነ የልደት በዓላቸው ላይ እንደሚገኙ አረጋገጡላቸው። ሀገን የስልክ መልዕክት ተከታኖቹ እንደሚደመጡ ያውቃል። ስለዚህ ቤቱን ሰቅቱ ስዘገይ ለሚተርበልኝ ጥያቄ ማስረዳት

t.me/OLDBOOKSPDF

እቸላለሁ ብሌ ራሱን እጽናና።

10 ሰዓት ተኩል ሲሆን ንፋሱና ባለቤቱ እርሳቸውን ተሰናብረው በሳይኖቸው የልደት በዓል ላይ ለመገኘት ከነሱ። ሁኒታው ከዚህን ቀደም ከሚያደርጉት የተለየ ባይሆንም የተወሰኑ ጓደኞቹ የክሰረንሽኪን ከተሰሙ የተሰየ ጥያቄዎች አስተውለው ነበር።

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ ፓርቲው ሲጧጧይ እስኒ ሃንካ ጓደኞቻቸውን ተሰናበቱ። ወደቤታቸው ከመሄዳ ይልቅ ከስተማው ዞር አሉ። ከዚያም ከመንገድ ወሎቱ የኒርርመን አወሰቱ፣ ሲቭል ልብሱን ለብሱ። መኪናውን ደግሞ ወደ ዋርሳ ከተማ አዙር ነዱ። በስተማው ውስጥ እየተሻሉከለከ ከኋላቸው ሥጥሳ እንዳልተከተሳቸው አረጋገጡ። ከዚያም ምልክቱ መሳነመቃብር ሲያርስ መኪናውን አቆሙ። ልጆቹ እዚያ እያጠበቁት ነው። ከዚህ ወዳያ የሚያደርጉት ነገር አልነበረም። የመጨሪሻው ምርጫ ከዚያ አያልፍም። መጠበቅ ግዴታቸው ነው።

ፅዜስ ሊሊት ሳይ የምትጠቀመው መኪና ብቅ አለች። መኪናዋ ውስጥ ፎርደን ከቻርመን የሳከው አንድ አንግዳ ነው ተቀምጧል። ሁሉም መኪናዎ ውስጥ ሆነው ከጭ በኋላ የሰጓያአው መኪና ወደ አንድ ጋራዥ አመሩ። በጋራዥ የሚገኘሀ ጽር ሾፌሩ የአሚሉንን አሠሣሪ መኪና ወሰደ። በዋርሶ ያለውም ጉዳዮችን አጨራረሱ ወደ አምባሳደሩ ቅጥር ግቢ ሲገቡ ሌሊ መኪና ይጠብቃቸው ነበር። ያገሩ መኪና በፍት ውስጥ ሬዲዮ የሌጋሪሉ ሲሉት መልዕክቶችን ተሞሳጅቱ በሚገ ሰመገኘ እንደገ፣ የሚሰማቱን ሰውም ሆነ ሲደተኛ አይታይም። የሬሳው ሰዓት ሰዓት ነበር የሚሽ የተቢያደ ነው። ኦክሰረንሽኪ ግን ከከተቱ ተሰያት ተወዳዳሩ

የኦክሰረንሽኪን ቤተሰብ የጫነው መኪና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አመሩ። የጋገሃ የሳሲን መንደርች አጨሳናትዋር ንፋሱ ወጥት ሃገር ወደ ቤተክርስቲያን ሲያመራ ያህ መኪና ውስጥ የተጀመው ቡድን ምሥራቅ ያርመን። ሩራ ዝዘፈት

ደረሱ የኦክሰረንሽኪ ቤተሰቦች ትንሩሽ ወሰዱ። ሶግሰኑ አንዲችሉ ባለሥልጣናችን መጠበቅ ዝረባቸው። ሁሉም ነገር ሰሰም ተከናወነ።

ከሦት ሰዓት በኋላ የጌዮ ሁብረት አካል በሆነችው የበርሊን አምባ ውስጥ ራሳቸውን አገኙ። ከኦክሰረንሽኪ ጋር ዳግም ተገናኙ። ውጋጋኑ እየከሰመ በሃገረበት ጊዜ ከ4000 ማይል ርቀት ሰልክ አንቃጨለ። በፍጥነት ደቭይድ ፎርደን አንዱቱ አነገረ። ላንግለይ ካለው የዕለቱ ተረኛ ጋር ዝር ንግግሩ መልዕክቱ አጭር ዝር «ከሀርሲን አንድ ዜና አለን» ይላል።

የስለ ሥራ ዝርዝር ጉዳዮችን ለመግለጽ አይፈቀድም። ሯ ግን ድምፁ በደስታ የተሞላ ነበር። ከዚህ መልዕክት ጀርባ፣ የጓደኛው ቤተሰቦች በመጪሪሻ ደህንታቸው የተጠበቀ መሆኑን ፎርደን አረጋገጠ። ፎፓደን ቃሉን ጠበቀ።

ስደት

ታህሳስ 11፣ 1981 (ኢኤአ) የሚሰኙት በረጅአግ ፅሰት ነው። ደቭይድ ፎርደን በአንድሪውስ አየር ኃይል ጣቢያ ሆኖ ይጠብቃል። አንድ "ሰዙ ወታደራዊ አውርፕላን መሬት ነክቶ ወደፊት ተንደረደረ። የአውርፕላኑ የፊት በር እንደተከፈተ አራት ፖሳንጻውያን ወደ ቀዘቃው አየር ወጥተው ታዩ። ፎርደን ወደፊት አየተራመደ ኦክሰረንሽኪን አቀፈው። ወደ ሃንሳም ሮሜይቱ ዞር ብሎ ተመለከታት።

«ሰለ ሊዲችሁን እናመሰግናለን» አለች በለሰለስ አንደስት። ደቭይን ቃላት አልነበረውም። ትንሽ ተለጉጭ ከቀየ በኋላ ግን ሞኒታን የሚገባችሁ ሰውች ናችሁ አለ።

ኦክሰረንሽኪ ለአያኤ ውጤታጀለት አተማ ወጣ ወዳለ መንሪያ ቤት የስደት ኑሮውን ጀመረ። አንድ የአሜሪካ ኩሮሄሪ፣ የነበለ ማህበረሰብ የሚያገሰውን ሙሉ ክብርና ትምህ አያገኘ የተቀማጠለ ኑሮውን ቀጠለ። ከሀገሩ ከተለየ አንድ ዓመ በኋላ ፖሳንድ በየመገዶችዋ ላይ ቦርያሩ ታንኮች በረገጡ። የፖሳንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀኔራል

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽሩዘርስኪም ወደ ሞስኮ ከተጠራ በኋላ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀ።

ዋሲለና ከ5000 በላይ የሚሆኑ ዜጎች ታፍነው ወደ ኢሥር ቤት ተወረወሩ። የዴሞክራሲ አንቅስቃሴው ተጨፈለቀ። አሜሪካ ውስጥ የሚኖረው ኩክሊንስኪም በጭንቀትና በየርሣሬ ሰውነቱ ተበጫቀ።

ኩክሊንስኪ በአሜሪካ ውስጥ የወታደራዊ ጉዳይ ተንታኝና በክፍተኛ ወታደራዊ ሲሚናሮች ላይ አየተገኘ ትምህርት በመስጠት አዲስ ኑሮውን አቀናጀ። ቤተሰቡ አዳዲስ ስምና ማንረጃ፣ ያልተመዘገበ የስልክ ቁጥርና ምስጢራዊ ቤት ተሰጣቸው። በስኢይኤ አየተጠበቁ ቢሆኑም ሁላቸውም ከአደጋ ያመለጡ አልነበሩም። የሶቭዬት ዐረ መረጃ ተቋም ይቅርታ እንደማያደርግለት ኩክሊንስኪ ያውቃል። በማናቸውም ሥፍራ ሊገድሉት ይችላሉ። በ1982 ቢጋ ላይ አንድ የሶቭዬት ኤምባሲ መኪና አሱ በሚኖርበት የቨርጂኒያ መንደር ሲያልፍ ተመለከተ። ከሰዓታት በኋላ ግን ሲአይኤ ኩክሊንስኪን ወደ ሌላ ስፍራ አዛወረው። ከሦስት ዓመት በኋላም አንድ ልዩ የፖላንድ የስለላ ጠቢል የአሜሪካንን ድንበር ሲሻገር ተያዘ። ስለዚህ ኩክሊንስኪ ከአያኖቹ ሁለት ርምጃ ቀድሞ ሰመጎንት አምስት ጊዜ መኖሪያውን ለመለወጥ ተገደደ።

በዘሩ በፖላንድም ኩክሊንስኪ በክሀዲነት ተወንጀለ። በ1984 (ኤኤ.አ) ወታደራዊ ባርድ ቤት የፖላንድ ዜግነት መብቱን ገፍፎና ንብረቱን መርሶ በሌለበት የሞት ቅጣት አስተላለፈበት። ለሁለት ዓመታትም ኩክሊንስኪ ሀገር አልባ ሆኖ ቆየ። በ1986 (ኤኤ.አ) አሱና ቤተሰቡ አዲስ በፈቀዱት አዲስ ስም የአሜሪካዊ ዜግነትን አገኙ።

የዜግነት ማስረጃውን ካገኘ በኋላ ኩክሊንስኪ ቤቱ ውስጥ ድግስ አዘጋጀ። «ከሶሪኤል ኩክሊንስኪ ከእኔ አባባል ጋር የሚስማማ አይመስለኝም።» በማለት ፍርድን ንግግሩን ጀመረ፣ ከዚያ «ዳሩ ግን ሕብረን የሰራነው ሁሉ እንደ ጀግና አንቆጥረዋልን» አለ።

ይህ ውሎት የጉመዘዘ ሁኔታን ፈጠረበት ለኩክሊንስኪ ያዘጋጀቱም ተሸላሚና ሀገሩን ያጣ ሰው ሆኖአልና ነው። የዜግነት ማስረጃውን በእጅ ይዛ «አሜሪካ በመሆኔ አከራለሁ፤ ግን አባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝና በደሜና በልቤ ዝንተ አለሜን ፖላንዳዊ ሆኜ እኖራለሁ።»

የጀግንነት መቋጫ ያ

ሬዘርድ ኩክሊንስኪ በ1981 (ኤኤ.አ) ወደ አሜሪካን ከበረረ በኋላ ብዙ ነገር ተለዋውጧል። ኮሙኒዝም ተፈረካክሷል፣ ለህ ዋሴስ የፖላንድ ፕሬዚዳንት ሆነዋል፣ የዋርሶ ስምምነት ተፋሻቶ ፖላንድ ለኔቶ አባልነት ማመልከቻ አቅርባለች።

ኩክሊንስኪ እንዘሠን ሁሉ አስገራሚ ለውጦችን ከርቀት ሆኖ ይከታተላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን ማንኛውም ቤተሰብ ከደረሰበት በላይ ዘግናኝና አስፈሪ መከራ ወድቆበታል። ለቀቶቹም ቢሆኑ ኩክሊንስኪን አልረሱትም። ቴሞቸውን ቴየው ሲከታተሉት ከርመዋል። የጀመሪያው አደጋ ጥር 1994 ጀመረ። ታናሽ ልጁ ቦታስው ከፍተሪዳ የባህር ዳርቻ ይሰነው ጠፋ። የአካሉ ቁራጭ አንኳ ሊገኝ አልቻልም። ከስድስት ወር በኋላ ደግሞ ታላቅ ልጁ ዋልደማር ተገጭቶ ሞተ። አንድ በደርቢቱ እጹን የከተተ ሰው አንኳን አለመያዙ አስደናቂ ነበር።

ከዚህ ሁሉ መከራና ራስን አሳልፎ የመስጠት ውጣ ውረድ በኋላ በኩክሊንስኪ ህይወት ውስጥ የዐሐይ ጨረር ፍንትው አለበት። በ1997 (ኤኤ.አ) የፖላንድ ፍቤት የኩክሊንስኪን ጉዳይ «ለፖላንድ ከፍተኛ ጥቅም» የሥራ ሰው በሚል ጉዳዩ ዳግም ታየለት። የዜግነት መብቱና በሠራዊቱ ውስጥ ወታደራዊ ማዕረጉ ተጠበቁለት።

ባለፈው ሚያዚያ 1998 ኩክሊንስኪ የሙያ ማህበሩ፣ የክረዛውና ግዳንስኩ ኩተሞች የክበር እንግዳ ሆኖ ወደ ሚዉዮት ሀገሩ ተመለሰ። ቡቲለቪሽርንና በጋዜጦች በሰጠው መግለጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሕንደ አንድ ተራ ወታደራዊ ግዳጁን ፈጽሚያለሁ። ሙከራዬና ጥረቴ የሦስተኛ ዓለም ጦርነትን እንዳይከሰት ማድረግ ነበር። የአናንኑ ድጋፍ፣ ፈታችሁ ላይ አሁን የማየው ፈገግታና ድጋፍ ትክክለኛ ነገር አዳደረግሁ ይመስክርልኛል» አለ።

በዛደበት ሥፍራ ሁሉ የጀግና አቀባበል ተደረገለት። ህዝቡ በእጅ የተፃፈ መፈክር እየያዘ «አንኳን ደህና መጡ ኮሎኔል! እንወዶታለን» ሲሉ አሞገሱት። የ67 ዓመቱ ኮሎኔል ፈገግታ እየረጨ አንድ እጁን እነሳ አወሩ መለሰ። በአንድ የግንቦት፣ 1998 በሚያካፉ የሰንበት ዕለት የድምፅ ማጉያ ይዞ በቅድስተ ማርያም ካቴድራል ፊት ለፊት ራሱን አገኘ።

«ፍቅር ራስን መስጠትን ይሻል!» ሲል ድምፁ በቅጥር ግቢው ውስጥ አስተጋባ። ድምፁ ቀጠለ «ለአምላካቸንና ለአናት ሀገራችን ፖላንድ ፍቅር ራስን አሳልፎ መስጠት ታላቅ ክብር ነው» ብሎ ንግግሩን ቋጨ። በዚህች ደቂቃ ኩክሲንስኪ በአናት ሀገሩ ምድር መሆኑን ተረዳ። «አፐሬሽን የባህር ወፍም» ተጠናቀቀ።

አውነተኛ ታሪክ


ፍቺዬ

ሞገስ ሀብቱ

ያታመንዝርን ህግ - ስለተላለፈ
ሰው ሁሉ ያድራታል - ላስቲክ እያቀፈ
...ወይ እየረገፈ፤
የመንፈስ ውህደቱ - ያኔ ድሮ ቀርቶ
ላስቲክ ተለክቶ - ላስቲክ ተሰክቶ
እሱም ተሸምቶ - ገመናን አስጥቶ፤
አይታያችሁም - ትውልድ ተልከስክሶ
ላስቲክ ውስጥ በስብሶ - ላስቲክ ውስጥ ረክሶ
መውለድ መዋለዱም- እንደዋዛ ቀረ
ዘር እንደ ሱቅ እቃ - በላስቲክ ታሰረ
የልብ መካካዱ - ከወረሰን ቆየ
አንድ እሱ የቀረን - ስጋም ተለያየ
ተለያየ ስጋ - ተያየ ሩቅ ለሩቅ
ላስቲክ ሆነ ዳኛ - ስሜት የሚያስታርቅ
ደሞ አለ አንጂ ሌላ
የግዜር ፍርድ ኬላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባ'ይን ተመልክተው - ልብን ካሰደፉ
ይህም ማመንዘር ነው - ይለናል መፅሀፉ
እዚህ ላይ ነው ጉዱ - አስቃቂው ፍርዱ
ባ'ይናቸው ብሌን ጦስ - አልፎች ሊታረዱ
ባ'ይን እየጠቀሰ - ባይን እየሰረቀ
ባ'ይን እየገለበ - እየሸለቀቀ
በጠራራ ፀሐይ - ካላፊ አግዳሚው ጋር...
...ስንቱ ተዋደቀ፤
እዚህ ላይ ነው ጉዱ
አስቃቂው ፍርዱ፤
ውቦች በሞሉበት - በሰፊው ከተማ
አይቶ መመኘትም - ሃጥያት ከሠነማ፤
ግንፍል ስሜታችን - ሽጋ እንዳይጠማ
ደሞ እንፈብርካ - ለልብ አሳት ውሃ
ላ'ይን ብሌን ጉማ፤
ለማይረባ ስሜት - ለውስጥህ ገመና
ራስህ ባመጣኸው - በጫርከው ፈተና
ከቡር የሰው ልጅ ሆይ - ያው በ'ንስሶች ቅና፤



የበረዱ ባሎች ጠንቋይ

መኩሪያ መካሻ

አንዳንድ ሴቶች ዕድለኞች ናቸው። አያሌ ሴቶች ደግሞ እድለቢሶች። በረዶ ባሎች ያላቸው ሴቶች ዝንተ ዓለም ፍዳቸውን ይቆጥራሉ። በረዶ ባሎች ለቤታቸው ደፋ ቀና ይላሉ። አልጋ ላይ ከውሻ አፍንጫ የቀዘቀዙ ይሁኑ እንጂ ለት ጉልቻ የሚጠይቀውን ሁሉ ይፈፅማሉ። አብሮ ለመኖር ወሳኝነት ባለው ወሲባዊ ተግባር ላይ ግን በረዶዎች ናቸው። በረዶ ባሎች ስራቸውን ያከብራሉ። በወሩ መጨረሻ ሙሉ ደሞዛቸውን ይዘው ወደቤት ሊመጡ ይችላሉ። ለልጆቻቸውም እንክብካቤ ገንዘብ ሲያወጡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓይናቸውን አያሹም። ግን ታዲያ ይህ ምን ያደርጋል! ከክብርት ባለቤታቸው ጋር መንፈሳቸው ቁርኝትና አነሳሳ ውህደት የላቸውም።

«በረዶዎች» ባሎች ክፉ አመል አለባቸው። በሰበብ አስባቡ ከቤታቸው ይርቃሉ። ቢራቸውን መሽሸኒያ ምሽጋቸው ያደርጋሉ። ስብሰባ ሲወዱማ አይጣል ነው። ትርፍ ጊዜ ቢኖራቸው እንኳ የቱምብር አልበም ያገላብጣሉ ወይም ጋዜጣ ውስጥ እየተቀበሩ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ እንጂ የትዳር ኃደኛቸውን አያስደስቱም፤ አያዝናኑምም።

በፍቅር ላይ በረዶ በመቸለሱ ሚስት ታራለች፤ ትንጨረጨራለች። «ከእንግዲህስ በትዳራችን መሀል ነፋስ ገብቷል። ዘወትር ብቸኛ ነኝ። እሱ እያንዣራራ እንቅልፋን ሲለጥጥ እኔ ግን በመሀሉ እየነቃሁ እነባለሁ፤ በወሲብ ጥማት መላ አካሉቱ ይቃጠላል። ይህ ሰው በረዶ ነው» ስትል ታማርራለች፤ መጥፎ ድምዳሜም ላይ ትደርሳለች።

ለምንድነው በረዶ ባሎች ያሏቸው ሚስቶች ስለባሎቻቸው ሲያስቡ የሚበግኑት? ባለትዳር ሴቶች የየግላቸው ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተግባሮች ይኖራቸዋል። በዚህም ይጠመዳሉ። በስራቸው ደስተኛ ይሆናሉ። አልጋ ላይ ሲወጡ ግን በባሎቻቸው ባህርይ ይከፋሉ። ለምን?

«ስለ በረዶ ባሎች ብዙ እንሰማለን» ይላሉ አንድ የህክምና ዶክተር። «እውነትም ብዙ ባሎች በረዶዎች ናቸው። ይህን ስል ወሲባዊ ደክመት ያለባቸውን ብቻ ማለቴ አይደለም። ሰንግድ፤ ስስፖርት፤ ለጊዜ ማሳለፊያ ሲሉ ሚስቶቻቸውን ባይተዋር የሚያደርጉትን ጭምር እንጂ። ይህን መሰል ባሎች ወሲባዊ መጣጣም ይከሽፍባቸዋል። ቀጥሰውም በወጉ ማፍቀር የማይችሉ ይሆናሉ። ምሉዕ ስዎች ናቸው ለማለትም ያስቸግራል» ብለዋል።

የሚከተሉት ምክንያቶች ባሎች በረዶ ለሆኑባቸው ሁሉ የሚሰራ ነው። መፍትሔውንም ይጠቁማሉ።

ፍራቻ፡- ወንዶች ምንም ማለት አይደሉም፣ ተራ ፍጡራን ናቸው። የሚሉቶቻቸው ወስጣዊ ጉጉት የጋለ መሆኑን ሲረዱ በበጎ መልኩ ከመመልከት ይልቅ አንዳንዶቹ ድንጋጤ ባህር ውስጥ ይሰምጣሉ። ጨዋ ሴት ማለት ስለ ወሲብ ምንም የማታውቅ ናት ብለው ይገምታሉ። ለአያንዳንዱ የሚስታቸው ወሲባዊ ጉጉት ወደ ጥርጣሬና አጉል ስሜት ያመራቸዋል። ይህም በበኩሉ ወሲባዊ ፍላጐታቸውን ይገልባቸዋል። የዚህ አይነት ባሎች ለኃፍረት የተነሳ ከሚስታቸው የሚገለሉ» ሲባሉ ይችላሉ። የፍርሃቱ ምክንያት ግልፅ ነው። ባልየው ከጠበቀው በላይ ሴቲቱ ወሲባዊ ጉጉት አሳይታለች የሚል ነው። ስለዚህም ነው የስነ ልቡና ጠበብት «ባልየው አሀዱ ብሎ አስተሳሰቡን ማስተካከል ይገባል» ሲሉ የሚመክሩት። ከጋብቻ የሚገኘው ታላቅ ደስታ ወሲባዊ ጥማትን ማርካት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል።

ድክምና በሽታ፡- አንዳንዴ ባሎች «ድብቅ በሽታ» ይኖርባቸዋል። መታመማቸውን ላያውቁም ይችላሉ። መነሾዎቹ የአመጋገብ አለመስተካከል፣ ጠጪነትና አጫሽነት ሊሆኑ ይችላሉ። የፋብሪካ ሰራተኛ የሆነ ባል ሳይታወቀው መርዛማ ኬሚካሎችን ስቦ ይሆናል። የአይኦዲን፣ የብሮሚይን፣ የሜሪኩሪ፣ የእርሳስ ኬሚካሎች ብናኝ ሰውነቱን ሊያዳክሙት ይችላሉ። እነሀን መሰል ሁኔታዎች ሊደማመሩ የባልን ወሲባዊ ግለት ያቀዘቅዙታል።

መሰላቸት፡- አንዳንድ ሚስቶች ባሎቻቸው ስለሚሰለቹአቸው ብቻ ፍላጐታቸው ይቀዘቅዛል። የባልም ስሜት በዚያው መጠን እየደከመ ይሄዳል። ግን ሴቶች ይህ በኩል ራሳቸውን ማሻሻል ይችላሉ። መሰለቻቸትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ መነሳፈቅ፣ ጥላቻን ወደ ፍቅር፣ ቅዝቃዜን ወደ ሙቀት ለመቀየር መጣር እሰባቸው። «ፈንግጠው፣ ፈንግጪው» የሚለው አስተሳሰብና አመለካከት ግንኙነትን ያሻክራል እንጂ አያጠነክርም። የመሰላቸት ምንጮችን በሙሉ ለመድፈን መጣር ነው ትልቁ መፍትሄ።

መልካም ፍቅር፡- ሚስቶች የጋብቻቸው ትሩፋት የሆነው ወሲባዊ እርካታ እንዳይጠፋ መጣር ይጠበቅባቸዋል። ሚስቶችን ድንቅ የሚያሰኛቸው ጣፋጭና ምስጢራዊ ነገርን ደብቀው የማኖር ችሎታቸው ነው። ይህን ሁሌም ቆጥበው የሚይዙትንና የሚደብቁትን ምስጢር ለፍቅራቸው ማጣፈጫነት ቢያውሉት ፍቅር ይደረሻል፤ በረዶነት ይቀልጣል።

ሴቶች - ሚስቶች፣ እናቶች፣ እህቶች፣ አብሳሮች፣ ቤት ጠባቂዎች ሞግዚቶች ወዘተ. ናቸው። ምሉዕ - በኩልሄ ሆነው ይታያሉ። ሴቶች መዘንጋት የሌለባቸው የባሎቻቸው አውነተኛ አፍቃሪዎች መሆናቸውን ነው።

ግድየለሽ ሚስቶች፡- ጥሩ አፍቃሪ ባል ሚስቱ ስለፍቅር አንድታስብና አንድትጨነቅ ይፈልጋል። ሆኖም አንዳንድ ሚስቶች ለባሎቻቸው ሁኔታ ቁብ አይሰጥቸውም። አንደዚህ አይነቶቹ ሴቶች ለጉዳአቸው ደፋ፣ ቀና የሚሉ፣ ስኮሮአቸው ሌት ተቀን በአካል የደከሙ ይሆናሉ። የወሲባዊ ተራክቦን አስፈላጊነት ይዘነጋሉ። ይህ በባሎቻቸው ዘንድ አጉል አመለካከትን ይፈጥራል። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደ ቤት ውስጥ ቁሳቁሶች መመልከት ይጀምራሉ። የሴቶቹ ሞራል ይላሽቃል። ከአንዲህ አይነት ሚስቶች ባሎች የሞራል ድጋፍ አያገኙም። ቅዝቃዜን በወሲባዊ ግለት ከመለወጥ ይልቅ አንዲወሰልቱ ይገፋፋል። ታዲያ ባሎች በረዶ ቢሆኑ አልፈው ተርፈው በንግድ፣ በስፖርትና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳይ ቢያተኩሩ ወይም ሌላ ሴት ቢወሽመጡ ምን ያስደንቃል?

የሰነልቡና፣ የስነወሲብና የጋብቻ አማካሪዎች ከረዥም ዝርዝር ጥናቶች መረዳት አንደተቻለው መፍቀር የማይችል ሰው ፍፁም የለም። የማፍቀርን ጥበብ ባለማወቅ ግን ሁኔታው ሊበላሽ ይችላል። ሚስቶች ባለማወቅ የትዳር ጓደኞቻቸውን ወደ በረዶ ባልነት ለለውጧቸው ይችላሉ። ሴቶች በተለያየ ምክንያት የባሎቻቸውን ወሲባዊ ፍላጐት ማርካት ሲሳናቸው ለሚስት የተቀመጠን የባል ፍቅር ለሰራ፣ ለስፖርትና ለሌሎች መገናኛ ቦታዎች ይሰጣሉ። ወሲባዊ ፍላጐቷን ሚስቱ ያላረካችለት ወንድ የጐደለውን ለማሟላት ወደ ሌላ ማዘንበሉ አንደማይቀር አስቀድሞ ማጤን ያስፈልጋል።

«በረዶነት» በሽታም፣ ስነአእምሮአዊ ችግር ነው። ሽታው አካላዊ ከሆነ አንደማናቸውም በሽታ መታከም አለ። የስነልቡና ችግር ከሆነም የባለሙያ አርዳታን መሻት ነው። አንደ ወሲባዊ ፍራቻ ያሉትን በቀላሉ በማስታማርና በመንከባከብ ከበረዶነት ወደ ጤናማ ባልነት ማሸጋገር ቀላል ነው። አንከብካቤ የማድረጉ ተግባር በሌቶች ትክሻ ላይ ነው የሚያርፈው። ሚስት ባሏን ወደ ፍቅር ህይወት የመምራት ተግባር ይጠበቅባታል። ምንም አንኳ ጥሩቱ የባል ቢሆንም ሚስት የደረሰባትን በደል ቸል በማለትና ለጋራ ደስታቸው ማበብ በማሰብ የባሏን በረዶነት የማትሰጥ ድርሻዋን መወጣት ይኖርባታል።

በትዳር ዓለም ግብረስጋ ግንኙነት ማህበራዊ፣ ንይማኖታዊና ሞራላዊ ድጋፍ ያለው መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። በአንድ ጣሪያ ስር የተጠለሉ ሁለት ሰዎች ልብና ስሜታቸውን ማዋሃድ ይኖርባቸዋል። የትዳር ጓደኞሞች ችግሮቻቸውን በጊዜ ካልፈቱ መለያየት ይከተላል። ጊዜ መስጠት ውድቀትን ያፋጥናል እንጂ የሚፈይደው አንዳችም ነገር የለም። ስለዚህ ሚስቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

የደረሰባቸውን የቅስም ስብራት ለመጠገን ይጣሩ። ባልና ሚስት በግልፅ ከተወያዩ በረዶው ይቀልጣል።

«የሰሜን በረዶ እንዳይሆን ፍቅራችን
እውነተኛ ስሜት ይንደድ በልባችን»

የሚለውን ግጥም በልቦናችን ማሳደሩም ፍቅርን ያደረጃል።

t.me/OLDBOOKSPDF